- አይ ጕረቤቷ አስረዳችኝ አልኩህ እኮ
- ፖሊሶቹ ሚስት ስለመሆኗ ያጣሩት ነገር አለ?
- አዎ እንግዲህ ፖሊሶቹማ የቤቱ ባለቤት ተብሎ ቀርባ ነገሩን ነግረዋታል እንደሚፈተሽ ቤቱ በር ላይ ወደ ውስጥ ሳንገባ ገና ውጪው በር ላይ ግቢ አለው ውጪው በር ላይ እንደሚፈተሽ ተነገራት
- ወ/ሮ ሕብርተ
- አቤት
- ቤቱ የሴትየዋ ፖሊሶቹ ያናገሯት የካሚል ሽምሱ ባለቤት መሆኗን ያጣሩበት ነገር አለ ወይ ነው?
- እስቲ ቆይ ጥያቄው በዚህ መንገድ ቢቀርብላቸው የካሚል ሽምሱ ባለቤት መሆናቸውን እንዴት አወቁ?
- ያወቅኩት እኔ ከገባን በኋላ ጕረቤቲቱ የሱ ሚስት መሆኗን እና አራስ መሆኗን አስረዳችኝ በቃ
- በቃ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- እሺ ለእርዎ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ተሰጥቶት አንብበውታል ቅድም ከአራዳ ክ/ከተማ ሲሉ ምናልባትም የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ነው ያሉት ብዬ ተረድቻለሁ የፍ/ቤት ትእዛዝ የሚል ነገር አይተዋል?
- አዎ የአቶ ካሚል ቤት እንደሚፈተሽ ከአራዳ ክ/ከተማ ማህተም ያለው
- አራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር ነው ቀበሌ ነው ወይንስ ፍ/ቤት ?
- የመጀመሪያ ፍ/ቤት

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አንብበውታል እርስዎ?
- አንደኛ የሰውየውን የአቶ ካሚልን ስም አንብቤያለሁ ምን ምን
- ወ/ሮ እብርተ የምጠይቆትን ቢመልሱልን
- ቆይ ቆይ እየመለሱ እኮ ነው
- እንብበውታል ወይ ነው የኔ ጥያቄ?
- አዎ አንብቤዋለሁ የሱ መሆኑን እዩ አሉ ይኸውና አቶ ካሚል ሽፋ የሚለውን አነበብን ከዥዛ ደግሞ ምን ምን መፈተሽ እንዳለበትም እዛጋ መጀመሪያው ላይ የጦር መሣሪያ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ሌላም አለው የምልህ ወደኋላ አልሄድኩም ግን የመጀመሪያው ላይ የጦር መሣሪያ እና ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ይላል ወረቀቱ ካሳዩን በኋላ ነው ወደ ፍተሻ የገባነው ወደ ቤት ማየቱ የገባነው
- ጥሩ እሺ. ይሄ የተነበበሎት ወይም እርስዎ እንዲያነቡት የተደረገው ወደ ግቢው ከመሄዳችሁ በፊት ነው አደል ወደ ካሚል ሽምሱ ቤት ከመሄዳችሁ በፊት ነው እርስዎ አይተውት አንብበው ይሄንን የተረዱት አደል?
- ፍ/ቤቱን እኮ ማዘዣ ያነበብነው እግቢው በር ላይ ገብተን ነው ውስጥ ግቢው ተንኳኳ ተከፈተልን እበሩ ላይ አሳዩን ወደቤቱ ከመሄዳችን በፊት አሳዩን በሩ ላይ ከዛ በኋላ ቅደሚ አሏት እሷን እፊት እፊት እኛም አብረን
- እሺ. የካሚል ሽምሱ ባለቤት የተባለችዋም ሴት ተሰጥቷት እንድታነበው ተደርጓል ?
- እስቲ ድገመው
- አልተሰጣትም አደል?
- ግልጽ አደለም

http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ወረቀቱን እርስዎ አይተው እንዲያነቡ ተደርጓል የካሚል ሽምሱ ባለቤት የተባለችዋም ሴት ወረቀቱ ተሰጥቷል እንድታነብ አልተደረገም አደል?

➢ ሁላችንም ቆመን በጋራ ነው ያየነው ሰብሰብ ብለን ማለት ነው የነበርን ታዛቢዎችም እሷም አብረውንም ሊፈትሹ የመጡ ወታደሮችም አብረን ቆመን ሰብሰብ ብለን ነው እንጂ እያንዳንዳችን እየዞርን ለእያንዳንዳችን አደለም ሁላችንም ሰብሰብ ብለን ይሄ ነው ይሄ ነው ብሎ አንደኛው እየነገረን እኛም እያየን ጉዳዩን አዳመጥን

➢ እሺ ከእርስዎ ሌላ ማን ነው ታዛቢ የነበረው?

➢ አንዷ ጉረቤት ትእግስት ነች አንዱን ሰው አላውቀውም

➢ ወደቤት ስትገቡ እንግዲህ ቅድም ይፈተሽ እንደተባለ ነግረውናል ከዛ ደግሞ የተያዙ እቃዎች አሉ አሁን እሺ አንድ በአንድ ልጠይቆት ትእዛዙ ላይ መጽሃፍ ይያያዝ አይልም አደል

➢ አቤት

➢ ትእዛዙ ቅድም ጦር መሣሪያ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ይያዙ ይላል ብለዋል ዝርዝሩን አንብበዋል ስለዚህ ትእዛዙ መጽሃፎች እንዲያዙ አያዝም አደል?

➢ እንግዲህ ፖሊስ እንደመረጃ ይጠቅመኛል ካለ

➢ ወ/ሮ ሕብርተ አሁን የምጠይቆትን ብቻ ይመልሱልኝ

➢ ቁሳቁስ ስለሚል እንግዲህ ከቁሳቁሱ አንዱ መጽሃፍ ሊሆን ይችላል

➢ አሁን እኮ ትርጉም ሳይሆን አሁን የጠየቅኩት እኮ ትርጉሙን ሳይሆን ትእዛዙ መጽሃፍ ይያይ ይላል ወይ ነው ?

➢ መጽሃፍ ቁሳቁስ ግን ይላል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መጽሃፍ አይልም አደል?
- በጥቅሉ ሲዛፍ ቁሳቁስ የሚለው መጽሃፉንም ያካትታል
- እሱ እኮ የእርስዎ ትርጉም ነው እኔ አሁን ጥያቄዬ መጽሃፉ ይያዝ ይላል ወይ ነው ለምን እሱን ብቻ አይመልሱልኝም?
- መጽሃፍን ነጥሎ ባይልም እንግዲህ
- አይልም አደል በቃ ይላል ወይም አይልም ነው አይልም አደል?
- ቁሳቁስ የሚለው ውስጥ መጽሃፍ ሊካተት ይችላል ነው የኔ ሃሳብ እንግዲህ አንተ እራስህ እንደተረዳኸው ውሰደው
- ቆዩ አሁን ምንድን ነው እሳቸው እንደዛ ተናግረዋል ማለት የሚለውን ነገር በትክክል ተናግረዋል ማለት ጦር መሣሪያ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች እና ቁሳቁስ ይላል ከዛ እንትኑ ላይ መጽሃፍ የሚል አልተናገሩም ሌሎቹንም አልተናገሩም ስለዚህ ከዚህ ውጪ ያሉ እናንተም መርታችሁ ለይታችሁ የምትጠይቁት ነገር ካለ እሱን ጠይቁ
- እሺ የባንክ ደብተር ይያዝ አይልም ትእዛዙ አደል የባንክ ደብተር ቁሳቁስ አደለም ስለዚህ?
- ያም ከቁሳቁስ የሚመደብ መሰለኝ መረጃ ነው ብለው ካሰቡ እዛ ቦታ ላይ
- ኢኸውሎት ምስክር እርስዎ በቃ ያዩትን ብቻ እንትን ይበሉ አሁን ነግረውናል አይተው ከሆነ የሚነግሩን አሁን ቁሳቁስ የሚለን ትርጉም ለእኛ ተውት ችግር የለውም ያካትታል አያካትትም አሁን እርስዎ ያዩትን የተጠየቁትን ?
- አሁን እኔም እኮ እዛ ውስጥ 18 አተም ሲባሉ የባንክ ደብተሩም ተጽፏል
- እሱ ላይ ተጽፏል ልክ ነው እዚህ ምንድን ነው ትእዛዙ ላይ ተቀምጧል አልተቀመጠም ነው ጥያቄው እንጂ የተጠየቀውን አደለም እሳቸው እየጠየቁ ያሉት

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቁሳቁስ ስለሚል እዛ ውስጥ ሊካተት ይችላል ነው እኔ በተረዳሁት መንገድ
- እሺ ላፕቶፕ ቶሺባ ላፕቶፕ ተይዟል ብለዋል ይሄ ላፕቶፕ ቶሺባ ቶሺባ ላፕቶፕ የካሚል ሽምሱ ለመሆኑ በምንድን ነው የተረጋገጠው ?
- ያው ከቤት ውስጥ ነው የተገኘው
- በቤት ውስጥ ስለተገኘ እንጂ የካሚል ሽምሱ ስለመሆኑ የተሰጠ ምንም ማረጋገጫ የለም?
- ባለቤቱም እንግዲህ አብረን ነው ስናወጣ ከቤት አብራ ነበረች እና ያው የሱ ነው የሚሆነው ብዬ ነው የምገምተው ከቤት ውስጥ ነው የተገኘው
- ላፕቶፑ ሲወጣ ላፕቶፑ ላይ ምልክት አልተደረገበትም አደል?
- ቶሺባ መሆኑን እንጂ ማርኮች ግን ቶሺባው ሲመዘገብ ግን በዶክመንት እና የቶሺባው የላፕቶፕ ማርክ ተመዝግቧል እዚህ 18ቱ ነገር ላይ
- ቶሺባ ላፕቶፕ ተብሎ ነው የተመዘገበው እንጂ ?
- ቶሺባ ተብሎ ማርኩ ደግሞ ቀጥሎ ተጽፏል መለያው ማለቴ ነው
- ያንን መለያ የተፃፈው መለያ ላፕቶፑ ላይ ያለ ስለመሆኑ እርስዎ እራሶ አይተው አረጋግጠዋል ?
- እኔ ብቻ አደለሁም ሌሎችም ነበሩ እዛው ላይ ያለውምነገር ነው የተመዘገበው
- እርስዎ አረጋግጠዋል ወይ አይተው ነው ያልኮት እኮ?
- አዎ ላፕቶፑ ላይ ላፕቶፑ እንትን ካለ በኋላ
- /የማይሰማ/
- እሺ መጨረሻ በምትፈርሙበት ጊዜ ቃለ ጉባኤ ዝርዝር ተጽፎ ነው የፈረማችሁት አደል?
- አዎ

2731 2284

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዛ ላይ ሁላችሁም ፈርማችኋል?
- አዎ
- የፍ/ቤቱ ትእዛዝ የተሰጠው ይያዙ የሚለውን ዝርዝር እዛ ላይ ይገልፃል የተያዙትም እቃዎች ደግሞ 18 ዓይነት እቃዎች ተይዘዋል እነዚህ እቃዎች ከፍ/ቤቱ ትእዛዝ ዝርዝር ውስጥ የወጡ መሆን አለመሆናቸው የለያችሁት ወይም ያጣራችሁት ነገር አለ?
- በጥቅሉ ቤቱ ሲፈተሽ የተገኙት ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ይላል የጦር መሣሪያ ይላል ቁሳቁስ ይላል አደለም እነዛ በቁሳቁስ ስር ተመዝግበው እኛ በወቅቱ ያየነውን ፖሊስ በኤግዚቢትነት ሊይዛቸው የፈለገውን እኛ በታዛቢነት አይተን 18 ነገር ከአቶ ካሚል ቤት እንደተያዘ አይተን ቁጭ ብለን ሲፃፍም ቁጭ ብለን እያየን መጨረሻ ላይ ፈርመን ከግቢ አብረን ወጥተናልበጋራ
- እሺ የቴፕ ካሴት ምን ያህል የቴፕ ካሴት ነው የተያዘው?
- ብዙ ናቸው ወደ 47
- ካሴቶቹ የዘፈን ይሁኑ የትምህርት ይሁኑ ወይም ሌላ ነገር ይሁኑ አላጣራችሁም ካሴቶቹን ብቻ ነው የወሰዳችሁት አደል?
- አይ በቁጥር እንጂ ውስጣቸው ምን እንዳለ አላየንም
- እሺ ሲዲ የተያዘ ሲዲ ነበር?
- አላስታውስም
- እነዚህ ቅድም የተገኙት መጽሃፍት ያሏቸው በቃለ ጉባዔው ላይ ስማቸው ከገለፁ ውጪ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ አልፈረማችሁም አደል በመጽሃፉ ላይ በመጀመሪያ ገጽም ይሁን በአጠቃላይ አልፈረማችሁም?

2733 2085

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልፈረምንም መጽሃፉን አይተን ተመዘገበ የመጨረሻ ላይ የፈረምነው
- እናንተ ታዛቢ ሁኑ ተብለው ወደ ግቢ ሲደርሱ አስቀድሞ አካባቢው ፖሊሶች አልነበሩም እንዴ ግቢ ውስጥ?
- አካባቢው ላይ ቢኖሩም ግቢ አልነበሩም ውጪ ነበሩ እኛ ስንሄድ አብረን ገባን
- በር አካባቢ ነበሩ ?
- ያው አጠገቡ እኔም ቅርብ ነው ቤቴ እና ስንደርስ ውጪ ነበሩ አብርን የሚገቡት ለፍተሻ የሚገቡት ሁለት ወታደሮች አብረው የሚገቡት ሌሎች ግን ለጥበቃ እራቅ ብለው ቁጥራቸውን አላስታውስም ነበሩ
- ግቢ ውስጥ ስንት ፖሊስ ገባ ?
- አብረን ከእኛጋር ቤት ውስጥ የገቡት ሁለት ናቸው
- እሺ እነዚህ አብረው የገቡት ምን ይዘው ነበረ ልክ ግቢ ስትገቡ ?
- እኔ እንግዲህ በእለቱ የማስታውሰው ያየሁት ያቺን ማንበብ የያዟትን የፍ/ቤት ማዘዣ እንጂ ሌላ ነገሩን አላስታውስም ጊዜው ቆየ እኮ
- እሺ ቦርሳ ነገር እንደዚህ አላንጠለጠሉም ነበር?
- አይ ቦርሳ የለም ባዶ እጃቸውን ነው
- ቪዲዮ ካሜራስ አልተቀረፀም ?
- አላስታውስም
- ከብርበራ በኋላ ወይም ብርበራ ሲካሄድ የተቀረፀ ነገር የለም?
- አላስታውስም ካሉ ማለፍ ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን እሱን እኔ ምስክርም ሆኜ እመጣለሁ ብዬ አስቢ አደለም በእለቱ ዝም ብዬ ነው የተገኘሁት
- በቃ በቃ
- ወ/ሮ ሕብርተ ወደ ግቢው የገባነው ከሁለት ፖሊሶች ጋ ነው ብለዋል እነዛ ፖሊሶች ፖሊሶች መሆናቸውን እርስዎ በምን አወቁ ?
- ፖሊስ ለመሆናቸውማ የታዘዙበት መቼም ያን የፍ/ቤት ማዘዣ ይዘው ከሜዳ ላይ አልመጡም
- እሺ ጥያቄውን አስተካክዬ ልጠይቆት ፖሊስ መሆናቸውን የሚያሳይ መታወቂያ አሳይተዋቸዋል ?
- መታወቂያ ይዘዋል አዎ
- አሳይተዎታል ለእርስዎ?
- አሳየተውናል እንደታዘዙ ነግረዉናል
- የፍ/ቤቱ ትእዛዝ አንድ ነገር ነው እሱን አሳይተውናል ብለውኛል አሁን የጠየቁት ስማቸውን እና ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያቸውን አሳይተዎታል ወይ ነው ?
- እኔ ስማቸውን አላስታውስም 9 ወር ነው 8 ወር አለ
- መታወቂያ አይተዋል ወይ ?
- አይተዋል አላዩም ይቺን ብቻ ?
- መታወቂያ ነበራቸው ግን ስማቸውን
- አይተዋል መታወቂያውን እርስዎ አይተዋል?
- መታወቂያ እንደነበራቸው አሳይተውናል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ እሺ. እቤት ሲገቡስ እቤት ለነበሩት ?

➢ ውጪው ላይ ገና ግቢው ውስጥ ሳንገባ ባለቤቱ ተጠራች ውጪው ላይ በሩጋ ነው ያሳዩን ሁሉንም ነገር እንዲህ እንዲህ ነው የመጣነው እንደዚህ ነው አሉ እሺ. አለች ባለቤቱ እሷ ፊት ፊት እኛ ተከተልናት አብረን ገባን ፍተሻው ተጀመረ በቃ

➢ የኔ ጥያቄ ባለቤት ለተባለችዋ ሴት ፖሊሶቹ መታወቂያ አሳይተዋታል ወይ ነው ?

➢ እኮ አብራችሁ ነው ያያችሁት አሁን እንደሚሉን ?

➢ እኛ እንደዚህ ነው የመጣነው እና መታወቂያቸውን አሳዩን ደብዳቤውን አነበብን ገባን አሁን ኦርደሩን ልረሳው እችላለሁ ግን መታወቂያ ይዘዋል ወታደር እንደነበሩ ሚሊተሪም ለብሰዋል የደንብ ልብስም ለብሰዋል

➢ ባለቤት ነኝ ያለች ሴት እንደነበረች ገልፀዋል በግቢ ውስጥ ሌላ ሰው ነበረ እንዴ?

➢ ከውጪ የመጡ የሷ ዘመድ ትሁን የሷ አዲስ እንግዳ ሴት ነበረች ሰራተኛም ነበረች

➢ እሺ. ብርበራው ሲካሄድ ባለቤት ነኝ ያለችውም ሰራተኞችም ከውጭ የመጡትም ሴት የት ነበሩ?

➢ እኛ ስንፈትሽ ውጪ ነው የሆኑት

➢ ውጪ ውጡ ተባሉ?

➢ አላሉም አልተባለም ውጪ ሁኑ አልተባሉም እዛው ግቢ ውስጥ ትንንሽ ልጆች ነበሩት እና ልጆችም ስለነበሩ ሰራተኛዋ ልጆቹን እንደዚህ ማኔጅ ታረግ ነበረ ከዛ ውጪ ግን ውጡ አልተባለም ግን ቤቱ ሰርቪሱ መደዳ ስለነበረ ሰራተኛዋ ሳሪስ አካባቢ ስለነበረች ልጆቹ ትንሽ እንዳይረበሹ ትንንሽ ልጆች ነበሩ ወደ በረንዳ ይዛ እንድትቆይ ተደረገ እንጂ ውጡ

2236
2088

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ግቡ የተባለ ሰው የለም ባለቤቱ ግን እስከመጨረሻው እኛም አብረናት ነበርን አንዷ ፈታሽ ደግሞ አብራ ታዛቢ የነበረችው ጎረቤቷ ነች እኤጋ እንኳን አንተዋወቅም እና በዛ ነው

- እሺ መጨረሻ ቅድም ተፈራረምን ስትሉ ሦስቱም ታዛቢ ፈረመ?
- አዎ ሦስታችንም ፈርመናል ወንዱን አላስታውስም ስሟን ትእግስት ግን ያው ጎረቤቱ ስለሆነች ትእግስት እኔና አንድ ወንድ በታዛቢነት የተገኘ ሦስታችንም ፈርመናል 18 ነገሩን አይተን ሲመዘገብም እያየን ነበረ የተመዘገብነው
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ?
- ድጋሚ የለንም
- እናመሰግናለን ጨርሰዋል መለስ ይችላሉ
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ስምህን እስቲ የመጀመሪያ ስምህን ብቻ ንገረን?
- አቤት
- የአባትህን ስም ሳትጨምር የመጀመሪያ ስምህን ብቻ?
- ዳንኤል
- 146
- እሺ 81ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 146 ላይ የተጠቀሱ አቶ ዳንኤል ቀርበዋል ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ ዳንኤል ?
- አቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?

➢ አቶ በድሩ

➢ ሌላ እሱ ብቻ ነው በድሩ ማን ነው ?

➢ በድሩ ሁሴን

➢ በድሩ ሁሴንን ለይተው ያውቃሉ በአካል መለየት ይችላሉ ከቻልክ ተነስተህ ቼክ ማረግ ትችላለህ ተነስተህ ቆመህ በትክክል እየውና እሱ ነው በድሩ ነው ?

➢ እሺ ምስክሩ 5ኛ ተከሳሽን በስም ጠርተዋል እንደውም ለይተው አሳይተዋል ከበድሩጋር ጥላቻ ወይ ዝምድና አሎት?

➢ የለኝም አልተዋወቅም የለንም

➢ ጥላቻም ዝምድና የለም?

➢ የለም

➢ ምን ሲደረግ ነው ያዩት በድሩ ለምን ተከሰሰ አጠር ያርጉና በድሩ ምን አደረገ ተብሎ ተከሰሰ እርስዎ ምን አዩ?

➢ የተከሰሰበት እንደተረዳሁት በአሸባሪነት ወንጀል ነው እኔ ያየሁት አጋጣሚ ሳልፍ አጋጣሚ ሳልፍ መርማሪ ፖሊሶቹ እንድተባበራቸው ጠየቁኝ

➢ ምን ለማረግ ?

➢ ቤት ብርበራ

➢ እሱን ነው ያየኸው ?

➢ እሱ?

➢ ቤት ሲበረበር ነወ ያየኸው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቤት ሲበረበር መጀመሪያ ኢጋጣሚ ሳልፍ ማለት ነው
- አይ አይተሃል ወይ ?
- አቤት
- ቤት ሲበረበር አይተሃል?
- አዎ አይቻለሁ
- እሱን ለመመስከር ነው የመጣሽው?
- አዎ
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- ዳንኤል ይሄ ጊዜው መቼ ነበረ አመተምረቱ ቀኑ ወሩ ?
- ሐምሌ 17
- ሐምሌ 17 አምና ነው መቼ ነው ጊዜው ?
- 11ኛ ወር
- አመተምረቱስ?
- 2004
- የት አካባቢ ነው ቦታው ?
- ንፋስ ስልክ ላፍቶ
- ወረዳ ስንት ነው በአሁኑ ?
- ወረዳ 6
- ልዩ ቦታ አለው መጠሪያ ?
- በደንብ አይሰማኝም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልዩ ስም?
- ልዩ ስም አይ
- እሺ ስንት ሰዓት ነበር ሰዓቱ ?
- አራት ሰዓት አካባቢ ነው
- ከቀኑ ነው ከምሽቱ?
- ከቀኑ
- እሺ የዛን እለት ምን አየህ ምን ታዘብክ?
- መጀመሪያ አጋጣሚ በቦታው ሳልፍ ፖሊሶች ጠየቁኝ መርማሪ ፖሊሶች እንድተባበራቸው ማለት ነው
- ምን ብለው ?
- ጠየቁኝ ከዛ በኋላ ሄድኩኝ በሩ ተንኳኩቶ ተከፈተ
- አይ እዚጋ ፖሊሶች መጀመሪያ እንድትተባበራቸው ሲጠይቁህ ያሳዩህ ነገር የለም ?
- አቤት
- ፖሊሶች ምን አሉህ እንድትተባበራቸው ጠየቁህ ?
- አዎ
- ምንድን ነው አልካቸው ?
- ጠይቄያለሁ እኔም የፍ/ቤት መያዣ አለው ወይ መበርበሪያ ብዬ ጠይቄያለሁ
- እሺ አሳዩህ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስጠይቅ እነሱ ያሉኝ ምንድን ነው በ32 መሰረት ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር እንደሚቻል አስረዱኝ አመንኩበት ከዛ በኋላ በሩ ተከፈተ በተጠርጣሪው አማካኝነት እንዲከፈት ተደረገ ገባሁ
- ተጠርጣሪው ነበረ?
- አቤት
- ነበረ ተጠርጣሪው ?
- አዎ
- እሺ ወዴት ሄዳችሁ ከዛ?
- ተጠርጣሪው ነበረ
- ማንነው ስሙ?
- አቶ በደሩ
- እሺ ከዛ ገባችሁ?
- አዎ
- እንዴት ገባችሁ እስቲ ስለአገባባችሁ ማን ከፈተ ማን ቀደመ?
- ያው በተጠርጣሪው አማካኝነት ነው የገባነው ተጠርጣሪው እየመራን ሄድን ገባን ከዛ በኋላ ሰራተኛ አለች ሴትየዋ አልተገኘችም ባለቤቱ ማለት ነው በሰራተኛዋ አማካኝነት ቤቱ ያው በራሱ አማካኝነት እንዲከፈት ተደረገ ሦስት ክፍሎች ቤቶች ናቸው ከዛ ሲበረበር የታዘብኩት ሰነዶችም አይቻለሁ
- እስቲ ምን ምን ተገኘ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእርስዎ ድምጽ እንዲቀረጽ ነው የሚፈለገው ስለዚህ 1ኛ ፊቱንም ወደዛም ወደዚህም ሳያዞሩ ማይኩን እያዩ ቀጥሉ ከቆሙበት
- ተጠርጣሪው ባለበት ቤቱ ፍተሻው ተጀመረ ተከፍቶ ማለት ነው ከዛ በኋላ 3 ክፍሎች ናቸው በሦስት ክፍሎች ውስጥ የሲዲ ካሴት ላፕቶፕ ዴስክ ነገር መጽሄቶች መጽሃፎች ምናምን እንደዚህ እንደዚህ አይነት ነገሮች ተገኝተዋል
- እስቲ ምን ምን ተገኙ ከምታስታውሳቸው?
- ለምሳሌ አሁን አንድ ድምፃችን ይሰማ የሚል
- ምንድን ነው እሱ ?
- አንድ በራሪ ጽሁፍ በኮምፒውተር የተፃፈ እሱን አይቻለሁኝ ፍትህ ጋዜጣ ደግሞ 4 ገጽ የሆነ አይቻለሁ አዲስ ጉዳይ የሚልም ደግሞ የሙስሊሞች ጉዳይ የሚል መጽሃፍ ደግሞ ወደ 8 ይመስለኛል የሙስሊሞች ጉዳይ በሚል እርእስ የተዘጋጀ ማለት ነው
- እሺ ሌላስ?
- አል እስላም በሚል እርእስ የተዘጋጀ አንድ መጽሃፍ አይቻለሁኝ
- ስንት ይሆናሉ ጠቅላላ ዝርዝራቸው የተለያዩ የምትላቸው ?
- ወደ 12 አይነቶች ይመስሉኛል
- እነኚህ በዝርዝር ከምን ውስጥ ነው የተገኙት?
- አቤት?
- ከየት ነው የተገኙት ከምን ውስጥ ነው የተገኙት?
- ቤት ውስጥ ያው የተለያዩ ሻንጣዎች ውስጥ ምናምን ቤት ውስጥ ማለት ነው 3 ክፍሎች ናቸው በሦስቱ ክፍሎችም የተለያዩ ዶክመንቶች ተገኝተዋል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትድም ስትገልጽ ወደኒላ ልመልስ እና በተከሳሹ መሪነት ነው ብለሃል ቤቱን በሩን ማን ነው የከፈተው የቤቱን መኖሪያ ቤት ?
- አልሰማሁም
- በሩን ማን ነው የከፈተው የመኖሪያ ቤቱን በር?
- ተከራይ ነው የሚመስለኝ አቶ በድሩ
- እኮ ማን ከፈተ ሰው ነበረ ከውስጥ ወይስ እራሱ ነው የከፈተው?
- ከሰው ግቢ ነው ተከራይተው ነው የሚኖሩት
- ቤቱን ማን ከፈተው እሺ መኖሪያ ቤቱ ስትገቡ?
- አልተሰማኝም
- /የማይሰማ/
- በሩ ተንኳኳ ከውስጥ ያለ ሰው ከፈተው
- ጥያቄው መኖሪያ ቤት እና ግቢ ነው ግቢውን ነው መኖሪያ ቤቱን ነው ?
- አይ መኖሪያ ቤቱን ነው ግቢ ገብተዋል
- እኮ ሰው ግቢ ውስጥ ነው ተከራይቶ ያለው ነው የሚለው እራሱ ተጠርጣሪው ከፈተ ነው የሚሉት ከዚህ የተለየ ነገር ወይ ግቢውን ከሆነ ወይ ሌላ ከሆነ ካለዚያ ድግግሞሽ ነው የሚሆነው
- የራሱ መኖሪያ ቤት የከፈተው እሱ ተከሳሽ ነው ?
- አቤት
- ተከሳሽ ነው የከፈተው መኖሪያ ቤቱን?
- እሱን መልሷል አቃቤ ሕግ ቤቱን የከፈተው እራሱ ተጠርጣሪው ነው ብሎ መልሷል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. ስትገቡ ሰው ነበር?

- ስንገባ ሰው ነበረ አዎ

- እሺ. አሁን ቅድም ያልካቸው 12 አይነት ዝርዝር ከተገኙ በኋላ እናንተ ስለመገኘቱ ምን አደረጋችሁ?

- በደንብ አይሰማኝም

- እሺ. ስለመገኘቱ ምን አረጋችሁ መጨረሻ ላይ?

- ስለመገኘቱ ያው በተገኙት ሰነዶች ላይ ቃለ ጉባዔ ተሰራ መጀመሪያ አቶ በድሩ በተገኙት ሰነዶች ላይ ፊርማ መፈረም በሚል ሰነዶች ላይ ፈረሙ ከዛ በኋላ እያንዳንዳችን በገፆች ላይ ፈርመናል ከፈረምን በኋላ ያው ወጣን ከቤት

- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

- እሺ. መስቀለኛ ጥያቄ ካለ

- አቶ ዳንኤል ቀኑ ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም ነው ብለሃል ይሄ ቀን ምን እለት ነበረ የዋለው ሰኞ ወይ ማክሰኞ ወይ ቅዳሜ ወይ እሁድ ምን እለት ነበር? አቶ ዳንኤል ሰምተውኛል ?

- አልተሰማኝም

- እለቱ ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም. ምን እለት ነበ የሚውለው ይሄ ቀን ምን እለት ነው የዋለው ሰኞ ማክሰኞ ወይ ቅዳሜ እሁድ ምን ቀን ነበር?

- እሱን አላስታውስም ቀኑን እረዥም ስለሆነ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እርስዎ እዛ አካባቢ ለግል ጉዳዩ ነው የነበርኩት ብለዋል ፖሊሶቹ ድንገት ነው የጠሩኝ ብለዋል ጠርተዎት ቤት እንፈትሻለን ያሉት ሰወች ፖሊሶች ስለመሆናቸው ያሳዮት መታወቂያ አለ ?
- እነሱ መርማሪዎች ናቸው የሕግ ልብስ ነው የለበሱት ይኸውሎት አቶ ዳንኤል መታወቂያቸውን አሳይተዎታል ወይ ነው የጠየቅኩት አላሳዩዋችሁም አደል?
- አይቻለሁ እሱን
- አሳይተዎታል?
- አዎ
- ማን ነው ያሳዮት?
- አላስታውስም ብቻ አንድ መታወቂያ አይቻለሁ ጠይቄያለሁኝ በምን መሰረት እንደሚበረበርም ጠይቄያለሁኝ በደንብ
- እሺ ያዩት መታወቂያ ምንድን ነው የሚለው?
- አላስታውስም ጌታዬ እረዥም ጊዜ ስለነበረ
- የቀበሌ መታወቂያ ነው ወይስ የምን መታወቂያ ነው?
- አደለም የፖሊስ መታወቂያ ነው
- እሱን ነው የጠየቅኮት እኮ እሺ ስንተ ሰወች ነበሩ ከሱ ሌላ መታወቂያውን ካሳዮት ሰው ሌላ ሌሎች ስንት ሰወች ነበሩ?
- ምን ውስጥ?
- መታወቂያ ያሳዮት ፖሊስ አለ ?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሱ ሌላ ሌሎች ፖሊሶችስ ነበሩ?
- ፖሊሶች ነበሩ አዎ
- የሌሎቹን ፖሊሶች መታወቂያስ አይተዋል?
- አላየሁም የአንዱን ብቻ ካየሁ ይበቃል
- እሺ ቅድም በ32 መሰረት እንፈትሻለን አሉኝ እኔም አመንኩበት ብለዋል እስቲ ፖሊሶቹ ምን ብለው ነው የነገሮት በ32 መሰረት እንፈትሻለን ልንፈትሽ እንችላለን ሲሉ የነገሮትን ዝርዝር እስቲ አስረዱን ምን ምንድን ነው ያሉት?
- ምንድን?
- ምን ምንድን ነው ያሉት በ32 መሰረት እንፈትሻለን ሲሉ እኔም አመንኩበት ብለዋል እርስዎ ካመኑበት ፖሊሶቹ ምን ምንድን ነው የነገሮት እስቲ እሱን በዝርዝር ይንገሩን?
- ቤቱ ለመበርበሩ የፍ/ቤት ትእዛዝ አላችሁ ወይ የሚል ጥያቄ እራሴ ጠየቅኩኝ ከዛ በኋላ በ32 መሰረት ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር እንደሚችል አስረዱኝ
- እኮ ሲያስረደት ምን አሎት ምን ምን አሎት ነው?
- አመንኩ ገባሁ በቃ
- አቶ ዳንኤል ያልኩ እኮ ጥያቄ በ32 መሰረት እንፈትሻለን ብለው አስረዱኝ አሉ ሲያስረደት ፖሊሶቹ የነገሮትን ነገር ነው ንገሩን ያልኮት ምን ምን አሎት?
- ሰውየው በአሸባሪነት ወንጀል የተጠረጠረ መሆኑን አስረዱኝ ከዛ በኋላ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ጠየቅኳቸው ስጠይቃቸው የለንም በ32 መሰረት ግን መበርበር እንደሚቻል አስረዱ ከዛ በኋላ አመንኩበት ገባሁ

http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ በፖሊስ በሽብርተኝነት የተከሰሰ መሆኑን ነግረውኛል አሉ መቼ ነው የተያዘው አሉ እሱ ተያዞ ነበረ አደለም ከነሱጋ ነበረ ?

➢ ከነሱጋ ነው የመጣው

➢ መቼ ነው የተያዘው ብለው ነገሮት እርስዎ?

➢ እሱን አላስታውስም

➢ ነግረዎታል መቼ እንደተያዘ?

➢ አቤት

➢ መቼ እንደተያዘ ነግረዎታል ፖሊሶቹ?

➢ አላስታውስም አልጠየቅኩም

➢ ነግረዎታል ወይ እኮ ነው ነግሮኛል አልነገሩኝም ነው ?

➢ እኔ አልጠየቅኩም

➢ ጠበቃ ከኢሹ እየወጡ ነው እና መቼ እንደተያዘ ስለ አያያዝ ላይ አደለም አሁን ምስክሩ ስለ ብርበራ ነው እዛ ውስጥ እራሱን እንትን አድርጉ

➢ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን በ32 መሰረት

➢ እሺ እሚሰሙት

➢ ላስረዳ እሺ

➢ ማስረዳት አያስፈልግም እርስዎ ፍ/ቤት ብይን ከሰጠ በኋላ በተደጋጋሚ ያስረዳሉ ይሄ ይግባኝ ሰሚ ነው ፍ/ቤት ብይን ከሰጠ በኋላ በተደጋጋሚ የሚያረዳው እና እሱንም እያሰቡ አሁን ተከሳሹ መቼ ተያዘ ለምን ተያዘ አደለም ጭብጡ እንዴት ተበረበረ በምን ተበረበረ ስለሆነ እዛ ውስጥ እራሶን ገድበው ጥያቄውን ይቀጥሉ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ 32 ማለት ምን ማለት ነው እርስዎ የተረዱት?
- እለፉ እሱንም ይሄ የባለሙያ ክርክር እኮ ነው 32
- እሳቸው ተረድቻለሁ ስላሉ እኮ ነው
- ይሄን ይለፉና ሌላ
- በተከሳሹ ላይ የሽብርተኛነት በመጠርጠሩ ተነግሮናል ማለት አቤቱታ በሽብርተኛነት ወንጀል ተከሷል የሚል አቤቱተ የቀረበበት ስለመሆኑ በ14 መሰረት አቤቱታ የቀረበበት ስለመሆኑ ተነግሮታል?
- እሱን አላውቅም
- እጅ ከፍንጅ የተያዘ ስለመሆኑስ ነግረዎታል?
- እሱንም አላውቅም
- የተከሰሰበት ወንጀል ከ3 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ እንደሚችልስ ነግረዎታል?
- እሱንም አላውቅም
- ይሄን እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄው የሙያ አደለም የሙያ ስላልሆነ እዚህ ላይ የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆዩ እስቲ ይሄ መቃወሚያ ሳይሆን የአካሄድ ጉዳይ ነው በብይን እለፉ የተባለው አሁንም ዞረው በዛ እየመጡ ነው አሁን ይሄንንም አስተካክሉ ስለ 32 ሕጋዊነት እየጠየቁ ነው ያ ለባለሙያ የሚቀርብ ጥያቄ ነው
- ለፖሊስ አስረድቶኛል ሲል እኮ ያስረዳቸውን ይዘት ምን እንደሆነ ነው
- በቃ በ32 መሰረት እንመረምራለን አሉ አለ ከዛ ያለፈውን

http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ቆይ ያዙቱ ያዙቱ እኮ ፍ/ቤት ሲመረምር ያዙቱ የተነገራቸው ምን እንደሆነ እንዲያስረዱ ብቻ ነው?

➢ ከዛ በላይ ያለው እኮ ለፕሮፌሽን የሚተው ጥያቄ ነው ንትርክ ውስጥ ባይገቡ ይሻላል

➢ እሺ በቤት ውስጥ ስትገቡ ፍተሻ እናረጋለን ለፍተሻ ሊደረግ ገብተናል ብለዋል የተደበቀ ነገር አግኝታችኋል?

➢ ማለት ምን ?

➢ የተደበቀ ነገር መደበኛው አቀማመጥ በተለየ ሁኔታ የተደበቀ ነገር አግኝታችኋል ወይ ?

➢ እነዚህ እነዚህ አሁን የጠቀስኳቸው ከዙህ በፊት የጠቀስኳቸው ሰነዶችን አግኝተናል የተገኙትን

➢ ኢሽው ምስክር እነዙህ የተገኙ ንብረቶች የት የት ቦታ ነው የተገኙት ጉድጓድ ውስጥ ነው የተገኙት የት ውስጥ ነው ሳሎን ላይ ነው እሱን ነው እየተጠየቁ ያሉት?

➢ ቤት ውስጥ ነው

➢ ቤት ውስጥ ቦታውን የት የት ሻንጣ ውስጥ ለምሳሌ መደርደሪያ ውስጥ ምናምን መጽሃፎች የተደረደሩበት ቦታ እሱ ውስጥ የተበረበረ እዛ ውስጥ የተገኙ ማለት ነው ሰነዶቹ

➢ እሺ ተቀምጠው ነው ያገኛችኋቸው ?

➢ አዎ

➢ ተከሳሹ በዛን ጊዜ ሲያገኙት መኪና ውስጥ ነው የነበረው መጀመሪያ እርስዎ ፖሊሶቹ ጠርተዎት ቦታው ላይ ሲገኙ ተከሳሹ መኪና ውስጥ ነው የነበረው ወይስ የት ነው የነበረው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ መኪና ውስጥ ሳይሆን በር ላይ ቆመዋል ወጥተው

➢ እራሱ በር ላይ ቆመው ነው ያገኙት?

➢ አዎ

➢ እጁ ታስሮ ነበረ አደለም ?

➢ አቤት?

➢ በካቴና እጁ ታስሮ ነበረ አደል?

➢ አዎ ታስሯል

➢ ፍተሻው ተደርጐ እስኪያልቅም ድረስ እጁ እንደታሰረ ነበረ አደል?

➢ አዎ

➢ መጨረሻ ቃለ ጉባዔ ሲፈረምም እጁ እንደታሰረ ነው የፈረመው አደል?

➢ እሱን አላስታውስም

➢ ፍተሻውን ያደርጉ የነበሩት ሰወች አሁን መታወቂያ ያሳዮት ፖሊስ አለ ከዛ ፖሊስ ሌላ ደግሞ ሌሎችም ሰወች ነበሩ ብለሃል ፍተሻውን ያደርግ የነበረው መታወቂያውን ያሳዮት ፖሊስ ነው ወይስ ሌሎች ናቸው ?

➢ አልገባኝም

➢ እቤት ውስጥ ገብታችሁ እቃ እየተፈተሸ ቅድም የዘረዘሯቸው እቃዎች አሉ የተያዙ ያሏቸው እነዛን እቃዎች ስትይዙ ይፈተሽ የነበረው ማን ነው ነው እቃዎቹን ማን ነበረ እነዛን እቃዎች ከየተቀመጡበት ቦታ ይሰበስብ የነበረው ማን ነው?

➢ እኔ እኮ ጌታዬ አጋጣሚ ነው እንድተባበራቸው የጠየቁኝ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ነበረ እኮ ነው ያልኮት አሁን እርስዎ ያዩትን ነው እኮ አሁን ገብተው ሲያዩ እቃዎችን ያነሳ የነበረው ማን ነበረ ነው?
- ሁለት ፖሊሶች መኖራቸውን አስታውሳለሁ የሕግ
- ቆይ ቆይ ምስክር ፍተሻው ላይ ቤት ውስጥ አብረው የገቡ ቅድም መታወቂያ አሳዩኝ ያሏቸው ፖሊሶች ናቸው ወይስ ሌላ ፖሊሶች ናቸው ነው?
- አንድ ፖሊስ ነው መታወቂያ ያሳየኝ
- እኮ እሱ ነው የገባው ወይስ ሌላ ፖሊስ ነው ውስጥ ?
- ሌላም ፖሊስ አብሮ አለ የምርመራ ዶክመንት
- እኮ መታወቂያ ያሳዮትም አብሮ አለ ?
- አለ አዎ
- እነዚህ ቅድም የዘረዘሯቸው እቃዎች አሉ ሲዲ ከካሴት ተይዟል ብለዋል አደል?
- አዎ
- ሲዲው ላይ እርስዎ ፈርመዋል ወይ ምልክት አርገዋል?
- ሲዲው ላይ እንዴት ልፈርም እችላለሁ ሲዲው ላይ ፊርማ ያለው አይመስለኝም በቃል ጉባዔ ነው የተያዘው
- እሺ ሲዲዎቹ ሲያዙ ሲዲዎቹ ይዘታቸው ምን እንደሆነ አላያችኋቸውም አደል?
- ውስጣቸው ምን እንዳለ አላየንም ብቻ እነዛ ሲዲዎች ካሴቶች
- እሺ ላፕቶፕም ተይዟል ብለዋል ላፕቶፑ ላይ ምልክት አልተደረገበትም አደል?
- ላፕቶፑም እንዳለ ነው የተያዘው አላየሁትም
- ውስጡ ምን እንዳለም አላያችሁትም ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱን አላየሁም
- ዴስክቶፕ ኮምፒውተርም ተይዟል ብለዋል እዛም ላይ በተመሳሳይ ውስጡ ምን እንዳለ አላያችሁትም?
- እሱን አላየንም
- መጽሄፎቹ ምን እንደሆኑ ይዘታቸውን እሱንም አላያችሁም?
- አላየንም
- ድምፃችን ይሰማ የሚለው በራሪ ወረቀትም ይዘቱ ምን እንደሆነ እሱንም አላያችሁትም?
- እሱን አይተነዋል ግን ምን እንደሚል አሁን እረሳዋለሁ እንጂ እሱን አይቼዋለሁ እራሴ እንደውም በአይኔ
- እሺ ፍትህ ጋዜጣ እና አዲስ ነገር የሚለው ጋዜጣም ገበያ ላይ የሚሸጡት አይነት ጋዜጣ ነው አደለም?
- ፍትህ ጋዜጣ አዎ
- አዲስ ነገር የሚለውም ጋዜጣ ተመሳሳይ ነው?
- አዎ
- አዲስ ጉዳይ የሚለው ጋዜጣ?
- አዲስ ጉዳይ መጽሄት ነው
- እሺ እሱ መጽሄት በተመሳሳይ ገበያ ላይ ያለ መጽሄት ነው አደለም?
- እሱን አላነበብኩም እርእሱን ነው ያየሁት
- እኮ ገበያ ላይ የሚሸጠው አይነት መጽሄት ነው አደለም መጽሄቱ ?
- ይሸጥ አይሸጥ እሱን አላስታውስም ግን እርእሱን አይቼዋለሁ አዲስ ጉዳይ የሚል እርእስ

3003

2852

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዲስ ጉዳይ የሚል መጽሄት የሚሸጥ መኖሩን አያውቁም እርስዎ?
- ሊኖር ይችላል ነገር ግን በዛ ሰዓት እኔ አላየሁትም ነው እያልኩ ያለሁት
- አቶ ዳንኤል እርስዎ ታዛቢ ሆነው ሲጠሩ ተከሳሹ አስቀድሞ ቤቱ በር ላይ ነበረ ነው ያሉት?
- አቤት
- እርስዎ ከኋላ ነው የመጡት ከተከሳሹ?
- እኔ እኮ አጋጣሚ እያለፍኩ ነው ሳልፍ እንድተባበራቸው ጠየቁኝ ፖሊሶቹ
- እኮ ተከሳሹ ከሌሎች ፖሊሶች ጋር ቀድሞ ቤቱ በራፍ ደርሶ ነበር እርስዎ ከመምጣቶ በፊት?
- አዎ በር ላይ ነው የነበሩት
- በር ላይ ነበር ?
- አዎ
- ቤት ቅድም ከፍቶ ገባ ሲሉ ቁልፍ አውጥቶ ከፈተ ወይስ ምን ማለት ነው ተከሳሹ ከፈተ ሲሉ በሩን ገፍትሮ ገባ ነው በቁልፍ ከፈተ ነው ?
- ገፍትሮ ገባ አደለም እያልኩ ያለሁት በሩ ተንኳኳ በሩ ሲንኳኳ ከውስጥ ያለ ሰው ከፈተ ሰው ማን እንደከፈተው ከውስጥ ያለው አላስታውስም ከዛ በኋላ ወደ አቶ በድሩ ወደተከራዩት ቤት ቀጥታ ሄድን ስንሄድ ሰራተኛ አለች ሰራተኛዋ ከፈተች በዛ መሰረት አቶ በድሩ ቀድመው ገቡ ከዛ ብርበራው ተጀመረ የራሳቸውን መኖሪያ ቤት ማለት ነው
- ተንኳኳ ሰራተኛዋ እንዴት ከፈተች?
- አቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ሰራተኛዋ ሳይጎኳኳ ዝም ብላ ከፈተች እንዴ?

➢ አሁን እኮ እያልኩ ያለሁት የውጪው በር እና የነሱ በር ግቢው ትልቅ ግቢ ነው ጌታዬ ግቢው ትልቅ ግቢ ነው ከውስጥ መጀመሪያ ትልቁ ግቢ በሩ

➢ ኦኬ መዝግበነዋል ተወው ሌላ ጥያቄ

➢ እሺ ውስጥ ስትገቡ ከሰራተኛ ውጭ ሌላ ሰው አልነበረም አደል?

➢ ሌላ ሰው አልነበረም አዎ ሌላ ከጐን አለ ተከራዮች ይሁኑ ባለቤቶች ይሁኑ አላውቅም

➢ ሰራተኛዋ ምን ሆነች ከዛ በኋላ ወጣች እንዴ?

➢ አቤት

➢ ከቤቱ ወጣች ወይስ ከእናንተ ጋር?

➢ አልወጣችም

➢ አብራ ታስፈትሽ ነበር እየዞረች ?

➢ አዎ አብራ እንደውም ወደዚህ በኩል አንድ ክፍል ቤት ነበረ እሱን መጨረሻ ላይ ተዘግቶ ስለነበረ ከፍታ አሳይታለች እሱንም አስበርብራለች

➢ ከታዛቢዎች አብራ ፈረመች እንዴ?

➢ አቤት

➢ እሷም እንደታዛቢ ፈርማለች ?

➢ አልፈረመችም

➢ ፖሊሶች ሲገቡ ምን ይዘው ነበረ ለብርበራ የገቡት ፖሊሶች በእጃቸው ወደ አቶ በድሩ ቤት ሲገቡ ምን ይዘው ነበረ በእጃቸው ?

➢ ማስታወሻ ነገር ይዘዋል ግን ምን እንደሆነ አላወቅኩም ጌታዬ

3005

2784

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በርሳ ነገር አልያዙም ነበር በርሳ የተሸከሙት ነገር?
- በርሳ ነገር እኔ አላየሁም
- ቪዲዮ ካሜራ?
- እሱ አለ
- አልነበረም?
- ቪዲዮ ካሜራ አለ
- ተከሳሹ በር ላይ ተቀርፀዋል በቪዲዮ ካሜራ?
- አዎ
- በር ላይ ተቀርፀዋል?
- አዎ
- ውስጥ ገብተም ተቀርጿል ?
- አዎ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- አቶ ዳንኤል ቅድም ስትገልጽ እጁን ታስሮ ነበር ወይ ሲሉህ አዎ ብለሃል እና እርግጠኛ ነህ ታስታውሳለህ?
- አቤት
- ተከሳሽ አንተ ስታየው ማለት ነው እጁ ታስሮ ነበር እንዴ?
- ምን
- ታስሮ ነበር ወይ በወቅቱ እጁ ታስሮ ነበር?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎን አዎ
- እሺ ሲፈርምስ?
- ሲፈርም አላስታውስም
- ስለዚህ ይሄንንስ በማምት ነው እንዴት ነው ወይስ አልታሰረም?
- መቼም አንድ ሰው ሲፈርም እንዴት አርጎ እጁን ታስሮ ሲፈርም ይችላል እሱን አላስታውስም
- ትዝ አይልህም?
- አዎ ትዝ አይለኝም
- እሺ ጨርሰናል
- እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ
- እሺ ከዚህ በኋላ ከቀጠልን ቶሎ መጨረስ ስለማንችል እስከ 8 ሰዓት እናርፍና ልክ 8 ሰዓት ላይ እንጀምራለን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የ.መ.ቁ 124754

ቀን 04/08/2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብስራት ተዕልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ፡- ዐቃቤ ሕግ ዘረሰናይ ምስግና ቀርበዋል

ተከሣሾች፡- እነ አቡበከር አህመድ 31 ሰዎች 30ኛ ና 31ኛ ተከሣሾች የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ሲሆኑ ሌሎቹ ሁሉም ከማረሚያ በአጀቢ ሆነው ቀርበዋል

የተከሣሾች ጠበቆች የ2ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አቶ አህመድ ጀማል ቀርበዋል ለሌሎቹ 1ኛ አቶ በህሩ መካንጋ 2ኛ አቶ ሀሰን ሁሴን 3ኛ አቶ ምላልኝ መለሰ 4ኛ አቶ መሐመድ አብደላ ቀርበዋል

- መዝገቡ አድሮ የነበረው የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ተብሎ ነበር በእዚህም መሠረት የምስክሮቹ መስማት ሂደት ይቀጥል ተብሏል ተከሣሽ ዐቃቤሕግ ምስክሮቹ ይቅረቡ
- /ግልፅ ያልሆነ/ የ 2ኛ ተብሎ የተገለፀው አህመድ ጀማል
- የ 28ኛ
- የ 28ኛ ተከሣሽ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- 86ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የመጀመሪያ ስምዎትን ብቻ ነው የሚገልፁት ስምዎን ማን ይባላል ?
- አርአያ
- በማስረጃ ዝርዝሩ ስንተኛ ላይ ነው ?
- 159 ላይ
- ዕድሜዎ ስንት ነው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 36
- ስራ አሎት ?
- ስራ አዎ
- ለምን መጡ ዛሬ እዚህ ፍ/ቤት ?
- ዛሬ ያው የታዛቢ ምስክር ምስክርነት ለመስጠት
- ምንን ነው የታዘቡት ወይም በየትኛው ተከሣሽ ላይ ምን ሲደረግ ?
- በአቶ መሐመድ አባተ
- አቶ መሐመድ አባተን ያውቋቸዋል በአካል ይለያሉ ?
- አላውቃቸውም
- አያውቋቸውም ?
- አዎ
- እሺ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- እስቲ አሁን በስም የገለፁዋቸውን አቶ መሐመድ አባተን እስቲ ይለዩዋቸው በችሎት በአካል ይለዩዋቸው ?
- በአካል አላውቃቸውም
- አያውቋቸውም ?
- አዎ
- በታዛቢነት ምስክርነት ነው የመጣሁት ብለዋል የት ነው ከጊዜው ጀምረው እስቲ ይንገሩን ?
- ወቅቱ ሐምሌ 12/2004 ከቀኑ ከምሽቱ 11 ሰዓት አካባቢ ነው በእዚያ አካባቢ ከስራዬ ወደ መኖሪያ ቤቴ ስሄድ በአካባቢ የነበረው የፖሊስ ኃይሎች ያው በእዚያ አካባቢ ለፍተሻ በሚከናወን አካባቢ ላይ በታዛቢነት እንዳይላቸው ጠየቁኝ ያው እኔም ያው ፍቃደኛ ሆንኩኝ እና ያው አብሬአቸው ሄድኩኝ
- ስንት ሰዓት ላይ ነው የጀመራችሁት ?
- እዚያ አካባቢ የደረስነው 11 ሰዓት ነው ነገር ግን ተጠርጣሪው አቶ መሐመድ አባተ በወቅቱ ስላልነበሩ ባለቤታቸው ሲጠየቁ ያው ይመጣል አሁን በማለት እሳቸውን ለመጠበቅ የተወሰነ ሰዓት ጠበቅን

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስከ ስንት ሰዓት ?
- ቢያንስ እስከ 12 ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው
- የጠበቃችሁት ?
- አዎ
- ከእዚያስ ?
- ከእዚያ በኋላ ያው ወደ ብርበራ ለመግባት መጀመሪያ ያው የፍ/ቤት መበርበሪያ ትዕዛዝ የሚገልፅ ደብዳቤ ተነበበልን ዞሮ ዞሮ ግን ከ 12 ሰዓት ያው መግባት እንደማይቻልም ያው እኔም በራሴ አውቅ ስለነበረ ወደ ጥያቄው ስንገባ ዞሮ ዞሮ በወቅቱ የነበሩ ፖሊሶች መርማሪዎች ማለት ነው አይ ደውለናል ይቻላል በሚለው ነገር በስልክ እንደደወሉ ነው እነሱ ያረጋገጡልን ከእዚያም በኋላ ባለቤቱም አለች እኛም 2 ታዛቢዎች አለን ሌሎችም ያው የፖሊስ እነዚህ የብርበራ የሚያደርጉ አካሎች አሉ መጀመሪያ ባለቤቱ በማስቀደም የእሷ ፍቃደኛነቷን ገልፃ ያው እሷ ቀድማ ገባች ሌሎቹ ተከታትለን ገባን ከእዚያ በኋላ ቤት ውስጥ ያሉት ነገሮችን ለመበርበር ጀመርን
- አቶ መሐመድ አባተ እስከ 12 ተኩል ድረስ ጠበቅናቸው ብለዋል ማለት የት ሄዱ ተባለ እስከ እዚያስ ምንድን ነው እያደረጋችሁ ከ 11 ሰዓት እስከ 12 ተኩል ?
- ውጪ ነበርን ሁላችንም ማን ነው ወደ እዚያ አካባቢ የገባ አካል ነበር ውጪ ነበርን ነገር ግን እኛ ምንድን ነው የሰማነው መስኪድ ናቸው የሚል ነበር መስኪድ ናቸው ቤታቸው እራሱ ከመስኪድ ፊት ለፊት ነው ያለው ስለዚህ መስኪድ ናቸው የሚል ነበር ያው ሊመጡ አልቻሉም በእዚያ አኳኃን እዚያ እሳቸውን ለመበጠቅ የቆየነው
- ሊመጡ አልቻሉም ?
- አዎ
- ቦታው የት ነው ?
- ቦታው ወረዳ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አዲሱ ሚካኤል ወይም ቅዱስ ሚካኤል ጀርባ ነው ወደ ጨው በረንዳ በሚወስደው ውስጥ ለውስጥ መንደር ውስጥ ነው
- ክፍለ ከተማው ምንድን ነው የሚባለው ?
- አዲስ ከተማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዲስ ከተማ ?
- አዎ
- የቤት ቁጥሩን ያስታውሱታል ?
- የቤት ቁጥሩ ለማየት ሞክሬአለሁ 262 ይመስለኛል
- አሁን በገለፁት መሠረት 12 ተኩል አካባቢ ብርበራ ጀምራችዋል ምንድን ነው የታዘቡት ?
- እንግዲህ ወደ ቤቱ ስንገባ በአጋጣሚ ቤቱ ለእዳሳት ላይ የነበረ ቀለም ተቀብቶ ነበር እና ለፍተሻም ለብርበራም አስቸጋሪ ነበረ እቃው ቤቱ ለብርበራ ለመበርበር ወይም ለመፈተሽ አስቸጋሪ ነበር ምክንያቱም ቤቱ እድሳት ላይ ነበር እቃዎቹ ውስብስ ነበሩ ስለዚህ ያው አንድ በአንድ ባለቤቱ ያው እያወጣች በራስዋ እጅ እያወጣች ሲዲዎች ካሴቶች መፅሐፎች እንዲሁም አጀንዳዎች የተለያዩ ሰነድ የተለያየ ብዛት ያላቸው ሰነዶች ነው ያየሁት
- እስቲ በቁጥር የሚያስታውስን በቁጥር ?
- በእዚህ አጋጣሚ በቁጥር ደረጃ ወደ /ግልፅ ያልሆነ/ ቁጥር የያዙ ናቸው 1ኛ አስታውሳለሁ 20 ካሴት ሲዲዎች ናቸው
- የምን ካሴት ?
- ሲዲ ካሴቶች ናቸው
- ሲዲ ካሴት ?
- አዎ 2ኛ 2 አጀንዳ ይመስለኛል 2 አጀንዳ 3ኛ አካባቢ ወደ 15 ካሴቶች አካባቢ ናቸው ሌላው ሲነር ላይኖች አሉበት የተለያዩ ሰነዶች ወረቀቶች አሉበት ሌላው ያው ደብተሮችም አሉ ሌሎች 11 መፅሐፎች በአረብኛ የተፃፉ መፅሐፎች አሉበት ወደ 4 በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ የተፃፉ መፅሐፎችን አይቼአለሁ
- ሌላስ የሚያስታውሱት አለ ከእዚህ ውጪ ?
- ለጊዜው ትንሽ ያው ጊዜው ራቅ ስላለ ብዙም
- እነሱን ነው የሚያታውሱት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ስንት ሰዓት 12 ተኩል ጀምረናል ብላችዋል ስንት ሰዓት አጠናቀቃችሁ ?
- ወደ 3 ሰዓት አካባቢ ከ 2 ሰዓት 20 ጉዳይ አካባቢ ለ 3 ነው ያጠናቀቅነው

3011 2760

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያጠናቀቃችሁት ?
- አዎ
- ቤት ውስጥ ከአቶ መሐመድ አባተ ባለቤት ውጪ ሌላ ሰው አልነበረም ?
- 2 ግለሰቦች እንደነበሩ አውቃለሁ እዚያ አካባቢ ጎረቤት የነበሩ ይመስለኛል አብረው እነደገቡ ነው የማውቀው ሌላ ከእኔ ጋር የነበሩት አንድ ታዛቢ
- አይ ከእናንተ ውጪ ቤቱ ውስጥ ?
- 2 ሰዎች እንደነበሩ አውቃለሁ
- እንደነበሩ ያውቃሉ ?
- አዎ
- ቅድም ሲነግሩን የፍ/ቤት ትዕዛዝ በተመለከተ እናንተ ጠይቃችሁ ነው ወይስ እራሳቸው ነው የደወሉት ?
- ቅድሚያ ወደ ውስጥ ከመግባታችን በፊት ያው እነሱን ለእኛ ግልፅ ለማድረግ ለማድረግ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዳላቸው በእጃቸው አሳዩን ፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚለው የአራዳ 1ኛ ደረጃ ምድብ ችሎት ነው ይመስለኛል አንድ ዳኛ ፊርማ የዳኛው ስሙ ወ/ሮ ታሪኳ የማዕረግ ስም በሌለበት ታሪኳ የሚል ነበረው
- ምን ይያዝ ይላል ?
- ምንድን ነው ሲያነቡልኝ የነበሩ 1ኛ ለሽብር ተግባሮች ሊውሉ የሚችሉ 1ኛ የጦር መሣሪያዎች ሌላው የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ሌላው ደግሞ ለቅስቀሳ ሊያገለግሉ የፁሑፍ ፁሑፎች አጠቃላይ ፁሑፎች እነዚህን 3ቱን ነው እኔ የማስታውሰው እነዚህ ነገሮች
- እንዲያዙ ያዛል ?
- አዎ
- እሺ እነዚህን አሁን ቅድም የገለፁዋቸውን እና የዘረዘሯቸውን ንብረቶች መጨረሻ ምን አደረጋችዋቸው ?
- እነዚህ አንድ በአንድ እያየን ከጨረስን በኋላ እኛ 2 ታዛቢዎች እና ባለቤቷ ወ/ሮ ከድጃ የምትባል ይመስለኛል /ግልፅ ያልሆነ/ እያንዳንዱ ገፅ ላይ እያንዳንዱ ፁሑፍ ላይ እያንዳንዱ ሰነድ ላይ ፈርመን ነው እንትን ያደረግነው

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ብላችሁ ፈረማችሁ
- በቃለ ጉባኤ ነው የፈረምነው ያው አይተናል ነው የሚለው ፊርማ ነው እዚያ ላይ ያው አይተናል የሚለውን ነው ይመስለኛል እና ያው እያንዳንዱ
- የተከሣሹም ባለቤት ፈረሙ ?
- አዎ
- ምን ብለው ፈረሙ እሳቸው ?
- ያው እንደኛው ይመስለኛል ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ያው እንደኛው ያው ታይቷል ነው ይመስለኛል
- ከእዚያ ውጪ ያደረጋችሁት ነገር አለ ?
- ከእዚያ ምንም አላደረግንም
- የፈረማችሁት ምን ላይ ነው ?
- መፅሐፉ ከሆነ ጀርባው ላይ መሀከል ላይ አካባቢ ያው ጎን ለጎን ነው እኛ እሷ በምትፈርምበት አካባቢ ጎን ለጎን ነው የፈረምነው
- ነው የፈረማችሁት ?
- አዎ
- ከእዚያ ውጪ ከመፅሐፎቹ ከተያዙት ሰነዶች ውጪ ላይ የፈረማችሁት ነገር አለ ?
- በቃለ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ያው በሰነዶቹ የተያዘበት ዝርዝሮች አሉ ቃለ ጉባኤ ዝርዝር ላይ ፈርመናል
- ቃለጉባኤ ተይዟል ?
- አዎ
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት
- ዋና ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የተከሣሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥል ተብሏል
- አቶ አርአያ በቦታው ላይ አንተ ተገኘሁኝ እርሶ ተገኘሁ ያሉት 11 ሰዓት አካባቢ ላይ ነው 11 ሰዓት ተገኙ ማን ማንን ነበር ያገኙት እርሶ ታዛቢ እንዲሆኑ የጠየቁት ሰዎች እነ ማን ናቸው?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስማቸውን አልነገሩኝም ስማቸውን ለመግለፅ አልችልም ዞሮ ዞሮ ግን ያው የፖሊስ ጓዶች ናቸው በአካባቢው
- ፖሊሶች ስለመሆናቸው መታወቂያ አይተዋል አሳይተዎታል ?
- አዎ 1ኛ ነገር የደንብ ልብስ ለብሰዋል ያው ከእዚያ ውጪ
- መታወቂያ አሳይቶታል ወይ ?
- ያው እንትናቸው አለ እዚህ ጋር
- ምንድን ነው ያለው ?
- ይሄ ምንድን ነው የሚባለው ስማቸው የሚገልፅ እንትን
- ፌዴራል ፖሊስ የሚል እዚህ ላይ የተፃፈውን ምልክት ነው የሚሉት ደረት ላይ የተፃፈውን?
- እንደዚያ ነው አዎ ያየሁት አዎ
- ስማቸውን ወይም ማንነታቸውን የሚያሳይ መታወቂያ ግን አላዩም ?
- እኔ አላየሁም
- የፍ/ቤት ትዕዛዝ መኖሩ የተነገሮት ወደ ቤት ስትገቡ ነው ወይስ መጀመሪያ እንዲታዘቡ ሲጠይቋችሁ ?
- ከመግባታችን በፊት እዚያው ከሄድን በኋላ ከመግባታችን በፊት ያው ተነቦልናል
- ከመግባታችሁ በፊት ለማን ለማን ነው የተነበበው ?
- ለእኔ እና ለአቶ ሳምሶን ድምፁ 2 ታዛቢዎች ነን
- ለእርሶ እና ለአቶ ሳምሶን ነው የተነበበው ?
- አዎ
- በእዚያን ጊዜ ቤታቸው የሚፈተሸው ሰው አልነበሩም ?
- አቤት
- አቶ መሐመድ አልነበሩም ?
- አልነበሩም
- ባለቤታቸውም አልነበሩም ሲነበብ ?
- ነበሩ

3014 2767

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተጠርተው ወጥተው ነው ?
- አዎ ያው ከውስጥ ወጡ ያው ውጪ ነው የተነገረን
- እርሶ ቅድም አቶ መሐመድ አባተን አላውቃቸውም ብለዋል ?
- አዎ
- ያ የተፈተሸው ቤት የአቶ መሐመድ ቤት ስለመሆኑ ያጣሩት ነገር አለ ፖሊሶቹ ?
- አዎ ባለቤታቸው የእሳቸው ባለቤት እንደሆኑ በአካል ያው እዚያ በፊት ለፊት የተናገሩት በእዚያ መሠረት ነው እኔም ላውቅ የቻልኩት
- ያስፈተሹትን ሴት ከመጠየቅ ያለፈ ሌላ የተደረገ ማጣራት የለም ?
- አይ በቃ ባለቤታቸውን ነው በአጠቃላይ ባለቤታቸው
- እሳቸውን ብቻ በመጠየቅ ነው ?
- አዎ
- እሳቸውስ ባለቤታቸው ስለመሆናቸው ያጣራችሁት ነገር አለ የተጣራ ነገር ?
- በራሳቸው አንደበት በራሳቸው ያው ባለቤታቸው እንደሆኑ አረጋግጠውልናል
- እሳቸው ባለቤት ነኝ ስላሉ ነው ?
- አዎ
- የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ቅድም ሲገልፁ የጦር መሣሪያ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች እና የቅስቀሳ ፁሑፎች ይያዙ ይላል ብለዋል መቼ ይፈተሽ ነው ቤቱ የሚለው ?
- ቤቱ መቼ ይፍተሽ መቼ ይፈተሽ የሚለው ነገር ባለውቀውም ግን
- አይ አሁን ይኸውሎት ሰምተው ከሆነ አይተው ከሆነ ነው የሚነግሩኝ ትዕዛዙ ላይ ቤቱ መቼ ይፈተሽ ተብሎ እንደታዘዘ አይተዋል ?
- ቀኑን አላየሁም አልሰማሁም
- ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ይፈተሽ ነው የሚለው ትዕዛዙስ ትዕዛዙ የሚለውን ነው አሁን እርሶ ቅድም የገለፁት አለ አሁን እንዲመልሱልኝ የፈለኩት ትዕዛዙ የሚለውን አይተውት ከሆነ ትዕዛዙ ከስንት ሰዓት እስከ ሰዓት ነው ይፈተሽ የሚለው ?
- እሱንም ያው እኔ ከ 12 ሰዓት በፊት እንደሆነ ነው በራሴ ግንዛቤ እንጂ እዚያ ላይ ያለውን ነገር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላዩም ?
- አዎ
- ከ 12 ሰዓት በኋላ ፍተሻ የሚደረግ ስለመሆኑ እርሶ የማይቻል ስለመሆኑ እርሶ ባሉት ግንዛቤ ጠይቀው ፖሊሶቹ ደውለናል ብለዋል ብለውኛል ?
- አዎ
- ፖሊሶቹ ሲደውሉ አላዩም አይደል እርሶ ?
- ያው ውጪ ወጥተው እንደደወሉ ነው ያው እዚያ
- እርሶ አላዩም ሲደውሉ ?
- አዎ ያው እንደደወሉ ነው የነገሩኝ አዎ
- ለማን ነው ደውለናል ያሉት ?
- ያው ለሚመለከተው አካል
- ማን ነው የሚመለከተው አካል አልተነገሮትም ?
- እሱ አልተነገረኝም ያው ለሚመለከተው አካል ግን ደውለናል ነው ያለው
- ወደ ቤት ከገባችሁ በኋላ እቃ ሲፈተሽ ፍተሻውን ያደርግ የነበረው ማን ነበር ፖሊሶች ናቸው ወይስ ማን ነበር ?
- ያው እዚያ የነበሩት ኃይሎች ያው የፖሊስ አካሎች ናቸው
- ሁሉም አብራችሁ የነበራችሁት የነበሩት የደንብ ልብሳቸውን የለበሱ ነበሩ ?
- አዎ
- የደንብ ልብስ ያለበሱ ፖሊሶች አልነበሩም ?
- የደንብ ልብስ ያለበሱ አይ የደንብ ልብስ ያለበሱ አንድ ሰው /ግልፅ ያልሆነ/ ከእነሱ ጋር ያው
- ነበሩ ?
- አዎ
- እሳቸው ፍተሻው ውስጥ ተሳትፈዋል ?
- እሳቸው ቆመው ነው ከእኛ ጋር እያዩ ነበረ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፍተሻ ውስጥ አልተሳተፉም ?
- አዎ
- በተያዙት እቃዎች ላይ ፈርመናል ቃለጉባኤ ብለዋል ሲዲዎች ተይዘዋል ብለዋል 20 ሲዲዎች እነዚህ 20 ሲዲዎች ይዘታቸው ምን እንደሆነ አይታችዋቸዋል ?
- እሱን ውስጣቸውን ያየነው ነገር የለም በቁጥር ነው ያው ቁጥር ላይ እዚያ እየተቆጠሩ ያው
- ሲዲዎቹም ላይ ምልክት አላደረጋችሁባቸውም ?
- አዎ አላደረግንም ሲዲው ላይ አልፈረምንም
- አጀንዳ ተይዟል ብለዋል አጀንዳ የግል አጀንዳ ነው አይደል ?
- አጀንዳ ነው ዝም ብሎ ኖርማሊ የማስታወሻ አጀንዳ
- ውስጡ ማስታወሻ ነው የተፃፈበት በእጅ የተፃፈ ነው
- አዎ ብዙ /ግልፅ ያልሆነ/ አጀንዳ እንደሆነ ግን አስታውሳለሁ
- እሺ እሱ አጀንዳው ላይ አልፈረማችሁበትም አይደል ?
- እሱ ላይ አልፈረምንም
- ካሴቶቹን በተመሳሳይ ይዘታቸው ምን እንደሆነ አላያችዋቸውም ?
- እሱን አላየንም አዎ
- የተለያዩ ወረቀቶች እና ሰነዶችም ተይዘዋል ብለዋል ?
- እሱ አዎ
- እነዚህ ወረቀቶች እና ሰነዶቹ ይዘታቸውን አላያችዋቸውም አይደል ?
- አላየንም እዚያው ግን ፈርመንላቸዋል እሱ ላይ ፈርመናል
- ወረቀቶቹ ላይ ፈርማችዋል ?
- አዎ
- ወረቀቶቹ ላይ ሁሉም ገፅ ላይ ተፈረሟል ?
- በሁሉም ገፅ ባይሆንም ያው እሷ /ግልፅ ያልሆነ/ እኛም እየፈረምን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ይኸውሎት መፅሐፎች እና የተለያዩ ወረቀቶች ስለመፅሐፉ ቅድም በግልፅ አስረድተዋል ወረቀቶቹ ላይ ሰነዶቹ ላይ እላያቸው ላይ ሁሉም ገፅ ላይ ነው ወይ የፈረማችሁት ?
- አዎ ፈርመናል
- ማን ማን ነው የፈረመው እዚያ ላይ ?
- ባለቤታቸው ወ/ሮ ከድጃ እና 2 ታዛቢዎች
- 3ታችሁም ፈርማችዋል ፖሊሶቹ አልፈረሙም በእዚህ ሰነድ ላይ ?
- አልፈረሙም
- በመጨረሻ ደግሞ ቃለጉባኤ ተሰርቶ ቃለ ጉባኤ ፈርመናል ብለዋል ?
- አዎ
- ቃለጉባኤውን የፈረመው ማን ነው ?
- 2ታችን 2 ታዛቢዎች
- 2 ታዛቢዎች ፖሊሶቹ አልፈረሙም ?
- አልፈረሙም
- ወ/ሮ ከድጃስ ፈርመዋል ?
- ወ/ሮ ከድጃ አዎ ፈርመዋል
- አቶ አርአያ እቤትዎ ውስጥ የቤትዎ ወ/ሮ ከድጃ እና ሌሎች 2 ጎረቤት ይመስሉኛል ያሉ ሰዎች ነበሩ እነዚህ በብርበራ ወቅት እዚያው ቤት ውስጥ ነበሩ ወይስ እንዲወጡ ታዘዙ ?
- አይ ነበሩ
- አብረው ይታዘቡ ነበር እየዞሩ ?
- ቁጭ ብለው ነበር እነሱ
- አንድ ቦታ ቁጭ ብለው ነበር ?
- አዎ አንድ ቦታ ቁጭ ብለው ነበር አዎ
- እነዚህ ቅድም ተገኙ ያሏቸው ንብረቶች የት የት ጋር የተደረደሩ ላይ ለምሳሌ መፅሐፍት ያሏቸው መፅሐፍ መደርደሪያ ላይ የነበር /ግልፅ ያልሆነ/ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በወቅቱ ቅድም እንደገለፅኩት ቤቱ እድሳት ላይ ስለነበረ እቃዎች በጣም ተቀላቅለው ነበረ በፌስታል ሼልፍ ውስጥ በቃ የተለያየ ቦታ ላይ ነበሩ ምክንያቱም ቦታ ቦታ አልያዙም ነበር በነበረው የቤቱ ሁኔታ እና ከፌስታል የወጣ አለ ከሼልፍም የወጣ አለ እና እንደዚህ ዓይነት ቦታዎች ነበሩ
- እንጂ ጣሪያ ቀዳችሁ ያወጣችሁት ነገር የለም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መሬት ተቆፍሮም የወጣ ነገር የለም ?
- የለም
- የተለየ ነገር ያው ቤቱ ለቀለም እቃው ከመተረማመሱ በስተቀር የተለየ ነገር አላያችሁም ?
- ምንም አላየንም
- እቃዎቹ ከተገኙ በኋላ እነዚህ በብርበራ የተገኙ ነገሮች ወደ ሳሎን ነው ያጠራቀማችዋቸው በየቦታው ካገኛችሁ በኋላ ?
- በቃ እዚያው አጠቃላይ ሳሎን ቤት ነበር እዚያው እቃው የወጣው ቅድም እንዳልኩት እቃዎቹ ሳሎን ቤት አካባቢ ነበር የተከመሩ ሳሎን ቤት እና ያው እዚያው ነው የተከመሩት
- እኮ ተለይተው ከሌሎች እቃ ተለይተው አንድ ላይ አልተደረጉም እንዴ ?
- አዎ ተደርገዋል
- ከእዚያ በኋላ ወ/ሮ ከድጃ እዚያ ከተለዩት በብርበራ ከተለዩት እቃዎች ጋር ሆነው በካሜራ አልተነሱም አልተቀረፁም ?
- ተቀርፀዋል
- ተቀርፀዋል ?
- አዎ
- ፖሊሶች ሲገቡ ምን ይዘው ነበር በእጃቸው ምን ይዘው ነበር ?
- ቪዲዮ ካሜራ ነበራቸው
- ቪዲዮ ካሚራ በምን በቦርሳ ?
- አይደለም በእጃቸው ነው ይዘው የገቡት
- ሌላስ ምን ይዘው ነበር ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ አላስታውስም
- አቶ አርአያ በወቅቱ ፍተሻ በተደረገበት ጊዜ የአቶ መሐመድ ጎረቤቶች የሆኑ 3 ቤቶች የአቶ መሐመድ ቤት አይደለም እየተባለ ፖሊሶች ሲፈትሹ ነበር አይደል ?
- አቤት
- የአቶ መሐመድ ያልሆኑ 3 የጎረቤት ቤቶች ተፈትሸው ነበር አይደል ?
- አይ /ግልፅ ያልሆነ/
- ፍተሻ ሲደረግ የጎረቤት ቤቶች ይሄ የአቶ መሐመድ ቤት አይደለም እያሉ ነበር አይደል ?
- አይ ኖ አላሉም
- 2 ቀን የፌዴራል ፖሊሶች አቶ መሐመድ ቤት ማደራቸውንስ ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- ወደ አቶ መሐመድ ቤት የሚወስደው መንገድ በ 2 ፓትሮል መኪና ተጭነው በመጡ ፖሊሶች መዘጋቱንስ ያውቃሉ ሰው እንዳይወጣ እንዳይገባ ተደርጎ የነበረ መሆኑንስ ያውቃሉ ?
- ይሄንን አላውቅም ይሄንን
- በወቅቱ 2 ሰዎች በፖሊሶች ተይዘው መወሰዳቸውንስ ያውቃሉ ?
- ይሄንን አላውቅም
- የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰው ይያዝ አይልም አይደል ?
- አዎ
- አቶ አርአያ ይሄ ቅድም ያሉትን ቀን 12/11/04 በምን አስታወሱ ቀኑን በምን አስታወሱ ሐምሌ 12 መሆኑ ?
- ቀኑ ግልፅ ነው ምክንያቱም 1ኛ ነገር እራሴም ያው እዚያ ቦታ ላይ ለምን እንደሄድኩኝ ጭምር ያው ስለማውቅ ማስታወሻም ነበረኝ ስለዚህ በእዚህ ምክንያት ነው የማስታውሰው
- እሺ ቅድም ሲጠየቁ እነዚህ የሲዲዎቹን የፁሑፎችን ይዘት ጠቅላላ አጀንዳዎቹንም አላዩዋቸውም አይደል በትክክል ?
- ውስጣቸው
- ቆይ ቆይ ተደግሟል ይሄ ይለፍ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በእሱ ተነስቼ ወደ ሌላ ልገባ ነበር
- ተደግሟል ይለፉ
- እሺ እነዚህ ጨርሻለሁ
- ድጋሚ ካለ
- የፍ/ቤት ትዕዛዙን በተመለከተ ቅድም በዋና ጥያቄም በመስቀለኛም ጥያቄ ሲጠየቁ ስልክ ተደውሏል ብለዋል አይደል ?
- አዎ
- ስልክ የተደወለው እናንተ አጠገብ አይደለም ወይስ ወጥተው ነው እሱን እስቲ ግልፅ ያድርጉት ?
- እሱ ያው ወጥተው ነው የደወሉት ዞሮ ዞሮ እኛ ለእኛ መጥተው በቃ ተፈቅዶልናል መግባት ይቻላል የሚለው ነገር የነገሩን
- ግን ወጥተው ደውለዋል ?
- አዎ
- ስልክ መደወሉን ያውቃሉ ?
- አዎ
- ወዴት ወደ ፍ/ቤት ይደወል ወደ ፖሊስ ይደወል የሚያውቁት ነገር አለ ?
- እነሱ ያው የሚመለከተው አካል አስፈቅደናል ብለው ነው እንጂ
- እሱን ነው ያያችሁ ?
- አዎ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የዐም ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ምስክር ስምዎትን የመጀመሪያውን ስም ብቻ ነው የሚገልፁልን
- ጥላሁን
- በማስረጃ ዝርዝሩ ስንት ላይ ነው ያለው ዐቃቤ ሕግ በ 131 ዛሬ ለምን መጡ እዚህ ፍ/ቤት ?
- ለመመስከር ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለምስክርነት ?
- አዎ
- ማን ላይ ነው የሚመሰከሩት ያውቁታል የሚመሰክሩበትን ሰው ?
- ሼህ አብዱራህማን ኡስማን
- በአካል ያውቁታል ?
- አዎ
- መለየት ይችላሉ እስቲ አሳዩን ስንተኛ ናቸው ከመጨረሻ ስንተኛ በመሀከላኛ ወንበር ነው ወይስ በኋላ በመሀል ላይ ያሉት በመጨረሻ 3ኛ መጨረሻ ነው እርሶ ኖት ስምዎት ማን ነው የእርሶ ስም ማን ነው ምስክሩ 87ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሲሆኑ 27ኛውን ተከሣሽ አብዱራህማን ኡስማንን ጠቁመው አሳይተዋል ምስክሩም የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆናቸው ምክንያት ስለሚመሰክረው ነገር የፍ/ቤቱ አስተርጓሚ አቶ ሱሪ ካባ እንዳያስተረጉሙላቸው ተከሣሹ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆናቸው ምክንያት የምስክሩን ቃል አቶ ሶሪ ካባ እንዲያስተረጉሙላቸው ታዘዋል እሺ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- አቶ ጥላሁን አሁን በችሎት የለዩዋቸውን ተከሣሽ የት ነው የሚያውቋቸው ?
- ሰፈር አካባቢያችን አንድ ነው
- አካባቢያችሁ አንድ ነው ?
- አዎ
- እሺ በምን ጉዳይ ነው የሚያውቋቸው ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለዋል በምን ጉዳይ ነው የሚመሰክሩት ?
- በሽብር ተጠርጥረው ቤታቸው እንዲበረበር ፌዴራል ፖሊስ ጠይቆን ገብተናል
- መቼ ነው ቀኑ ?
- ሐምሌ 12/11ኛ ወር 2004 ዓ.ም
- 2004 ሰዓቱስ ?
- ሰዓቱ ከ 3 ሰዓት እስከ 10 ሰዓት
- ቀን ነው ማታ ነው ?
- ቀን

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀን ላይ ?
- አዎ
- ቦታው የት ነው ?
- አየር ጤና
- ምን ክፍለ ከተማ ይባላል ?
- ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01
- ቤት ቁጥሩን ታስታውሰዋለህ ?
- የቤት ቁጥር አዲስ ነው
- በእዚህ አሁን በገለፅከው ቦታ እና ጊዜ ምንድን ነው የታዘብከው ?
- የታዘብኩት ነገር ነኛ ቤቱ ሲበረበር ለብርበራ ስንገባ የፍ/ቤት ወረቀት ተነቧል የፍ/ቤት ወረቀቱ ከተነበበ በኋላ በአስተርጓሚ ነው የተነበበላቸው አማርኛ ስለማይችሉ
- በአስተርጓሚ እየተነበበላቸው ?
- አዎ
- አስተርጓሚው ከየት የመጡ ?
- ከፌዴራል ፖሊስ
- ከፌዴራል ፖሊስ እሺ የፍ/ቤት ትዕዛዙ በአማርኛ እየተተረጎመ ተነገራቸው ?
- አዎ
- ለእናንተም ተነበበላችሁ ?
- አዎ
- የፍ/ቤት ትዕዛዙ ምን ይላል ?
- የፍ/ቤት ትዕዛዙ በሼህ አብዱራህማን ኡስማን በሽብር ተጠርጥረው በቤታቸው እንዲበረበር የጦር መሣሪያዎች እና የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ እና ሌሎች ሰነዶች በሽብር ጥርጥር እንዲበረበር ተጠይቋል
- ይላል ሰነዱ ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ከእዚያ ምን ምንድን ነው የተያዘው ?
- የተያዙት 1ኛ ያልመረጥኳቸው የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉኝም የሚል ነው 2ኛው
- ምንድን ነው አሁን የነገርከን ርዕሱ ምንድን ነው ?
- ማለት ቲሸርት ነው
- ተቃውሞ ምንድን ነው ይቅረብ
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ጥያቄ መሪ ነው እና አስተካክለው እንዲጠይቁ ነው ርዕሱ ሲሉ እሳቸው ወይ ይዘቱን እንዲናገሩ መጠየቅ ነው እንጂ ያለባቸው ዐቃቤ ሕግ ወደ የሚፈልጉት ስለሚመራ ጥያቄው መሪ ነው
- መልስ ስጡበት ዐቃቤ ሕግ
- የተከበረው ችሎት አልመራንም ማለት ያልመረጥነው መጅሊስ አይወክለንም የሚል አለ ምንድን ነው ይሄ አሁን ያነበቡ ማለት በርዕስ የነገሩን ምንድን ነው በአይነት ምንድን ነው ተብሎ ነው የተጠየቀው አሁን መምራታቸው በእርግጠኝነት ይሄ መሪ ጥያቄ ሊሆን አይችልም
- ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶበታል ዐቃቤ ሕግ ርዕሱ የተገኘው ፁሑፉ ርዕሱ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ነው ያቀረበው ርዕሱ ምንድን ነው ብሎ መጠየቅ መሪ ጥያቄ አይደለም ተብሏል ጥያቄው ይቀጥል
- እሺ አሁን የነገርከን በርዕስ አሁን የነገርከን ምን ላይ የሰፈረ ነው ?
- ቲሸርት ላይ
- ቲሸርት ላይ የሰፈረ ነው ምን ያህል ነው በቁጥር ?
- ብዛት 2 ነው
- ብዛት 2 ቀጥል እሺ ሌላ ?
- 2 ላፕቶፖች አሉ
- 2 ላፕቶፖች ?
- አዎ
- በስም ስያሜአቸው ማርካቸውን ታስታውሳለህ ?
- አንዱ ኮምፓክ የሚል ነው አንደኛው ቶሺባ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቶሺባ እሺ ቲሸርት ላፕቶፕ ከእዚያስ ?
- ከእዚያ ካሴች አሉ
- የምን ካሴት ?
- የሲዲዮ ካሜራ ካሴት አለ የቴፕ ካሴት አለ የቪዲዮ ካሜራዎች አሉ ሌሎች ደግሞ በሙስሊም ተማሪዎች የሙስሊም ተማሪዎች ሚና የሚል ትንሽ መፅሐፍ አለ
- እሺ አስታውስ እያስታወስክ ንገረን ቀስ ብለህ ከእነዚህ ውጪ የምታስታውሰው ካለ በኋላ ትነግረናለህ ስንት ሰዓት ጀምረን ስንት ሰዓት ጨረስን ነው ያልከን ?
- 3 ሰዓት ጀምረን 10 ሰዓት
- 10 ሰዓት ማን ማን ነበር እቤት ውስጥ ቤት ውስጥ ስትገቡ እንዴት ነው የገባችሁት አገባባችሁን እስቲ ንገረን ?
- መጀመሪያ ስንገባ
- እሳቸው የት ነበሩ ?
- ውስጥ ናቸው ግቢ ውስጥ እሳቸው ቀደሙ ከእዚያ እኛ አቶ አብዱራህማን ኡስማን እሳቸው ሲገቡ እኛም ቀጥለን ገባን
- ስንት ሆናችሁ ነው የገባችሁት ?
- እኛ 3 ነን
- 3 /ግልፅ ያልሆነ/
- ታዛቢዎቹ 3 ነን
- 3 ታዛቢ ?
- አዎ
- እሺ ከእናንተ ውጪ ስንት ሰው ነበር ?
- ከእኛ ውጪ ፈታሾቹ አሉ
- ፈታሾች ምን ምንድን ናቸው ፈታሾቹ?
- ፈታሾቹ ከፌዴራል ፖሊስ ዋና እንትን የሚመጡት
- ከፌራዴራል ፖሊስ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ፖሊስ መሆናቸውን እናንተ በምንድን ነው ያወቃችሁት ?
- 1ኛ ልብስ ለብሰዋል መታወቂያ አሳይተውናል
- መታወቂያ አሳይተዋችዋል ?
- አዎ
- አሁን ቅድም ያስታወስካቸው ንብረቶች መጨረሻ ላይ አደረጋችሁ ?
- መጨረሻ ላይ እሳቸውም ቁጭ ብለው እኛም ቁጭ ብለን እያንዳንዱ ሰነድ ላይ ፈርመንበት ቃለጉባኤው ላይ ፈርመን ነው ጨርሰን የወጣነው
- እያንዳንዱ ሰነድ ላይ ማለት ምን ምን ሰነድ እስቲ በሰነድ ምን ምን ሰነድ የሚባል ላይ ፈርማችዋል ?
- ማለትም ወረቀት በአረብኛ የተፃፉ ወረቶች አሉ የተለያዩ ደብተሮች አሉ ደብተሮች እና ወረቀቶች አሉ
- ወረቀቶች አሉ በምን የተፃፉ ?
- በአረብኛ ነው
- ሌሎችስ ?
- ከእነዚህ ውስጥ የማስታውሰው ይሄንን ነው
- እነዚህ ሰነዶች ላይ ፈርማችሁ ?
- አዎ
- በገፅ ታስታውሳለህ የምታስታውሰው አለ በገፅ ያያዛችሁትን ሰነድ የሰነድ ብዛት በገፅ ?
- ማለት አይታወቅም
- በገፅ አታስታውስም ?
- አዎ
- እነዚህ ሰነዶች እና ቅድም የገለፅካቸውን ንብረቶች መጨረሻ ላይ ቃለጉባኤ ያዙችሁ ማን ማን ፈረመ ?
- እኛ ታዛቢዎቹ 3ቱ እና አቶ አብዱራህማን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ስትጀምር እየተተረጎመላቸው ብለኸናል ይሄስ በተመሳሳይ ተተርጉሞላቸዋል ?
- ይሄ አልተተረጎመም ያው በአረብኛ ስለሆነ አልተተረጎም
- አይ ቃለጉባኤውን ነው የምልህ ?
- ቃለጉኤው ላይ ተነቦ እዚያው እየፃፍን እየተፈረመላቸው ነው እንትን ያሉት እያንዳንዱ ላይ ማለት ነው
- እኮ የተያዘውን ንብረት አውቀውታል እሳቸው ?
- አዎ
- የተያዘባቸውን ንብረት ዝርዝር አውቀውታል ?
- አዎ
- ሌላ ከእሳቸው ውጪ ሰው ነበረ ቤተሰቦቻቸው ማለቴ ነው ?
- ቤተሰቦቻቻቸው አሉ አዎ አሉ
- ነበሩ ?
- አዎ
- ምን ያህል ነበሩ ?
- አላስታውስም ወደ 4 /5 ይሆናሉ
- ማለት እናንተ ስትበረብሩ እያዩ ማለት ነው ?
- አዎ
- እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት
- የተከሣሾች መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥል ተብሏል በጠበቆቹ በኩል መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥል
- አቶ ጥላሁን ቅድም ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቅህ 2 ላፕቶፕ ተይዟል ብለሀል በወቅቱ ላፕቶፑ የእኔ አይደለም የልጆቼ ነው ብለው ተናግረው ልጆቻቸው ተጠርተው መጥተው ነው አይደል ላፕቶፑን ከፍተው ካሳዩ በኋላ የእኛ ነው እያሉ ፖሊስ ይዞት የሄደው ?
- አዎ
- ነው አይደል ?
- አዎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነው አይደል ?
- አዎ
- የፍ/ቤት ትዕዛዝ እኔ አማርኛ አልችልም ሲላቸው ሲሉት ለፖሊሱ ካልቻሉ ብሎ ኪሱ ውስጥ ነው አይደል አጣጥፎ የከተተው ሳያነብላቸው ?
- ኦሮምኛ የሚልችል አንድ ፖሊስ ስላለ በእሱ አስተርጉሞ ተነቦላቸው
- እሺ እናንተ ቤቱ እንዲበረበር ወይም ቤቱን ለመበርበር ስትደርሱ እሳቸው ባለመኖራቸው ስልክ ተደውሎ ከሻሸመኔ ተጠርተው ነው መጥተው ብርበራው የተደረገው አይደል ?
- እቤት ውስጥ ነበሩ እዚያው ነበሩ
- ከሻሸመኔ ተጠርተው ከመጡ በኋላ አንድ ቀን ከቤታቸው ውጪ እንዲያድሩ
- እቤት ነው የነበሩት ?
- አዎ እቤት ነበሩ
- እቤት ነው ያገኛችሁ ?
- አዎ
- አንድ ቀን ከቤት ውጪ እንዲያድሩ
- አይ ቆይ ጥያቄውን አስተካክሉ
- ይኸው አስተካከልኩ የተከበረው ፍ/ቤት ከሻሸመኔ የሚለው
- ምስክሩ ያሉት ከቤት ነው የቆዩት ነው ያሉ እርሶ ያሉት ግን ከሻሸመኔ ተጠርተው ከመጡ በኋላ ነው ያሉት ?
- እኮ እሱ ምስክሩ እቤት ነበሩ አለ አስተካከልኩ እኮ የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ቀጥሉ እሺ
- በ ׀׀ ማታ እቤት እንዳይገቡ መደረጋቸውን እና ውጪ ማደራቸውን ታውቃለህ ?
- ማታ አሁን በዋና ጥያቄ ስለእዚህ ጉዳይ አልጠየቅንም አሁን ቅድም በተደጋጋሚ ጠበቃውም ከብርበራ ትዕዛዝ ውጪ ዲስቶርት የሚያደርጉ ወይም ክርክሩን ወደ ሌላ መንገድ የሚወስድ ነው ጥያቄው የሚሆነው ስለዚህ እንደዚህ መደረጋቸውን ተከበው ማደሩን የሚያውቁት ነገር አለ የሚባለው ነገር እኛ በዋና ጥያቄ አልጠየቅንም ታዛቢ ነበሩ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲታዘቡ እነዚህ እነዚህ ንብረቶች ሲወሰዱ አይቼአለሁ ነው ከእዚህ ውጪ ሌላ ምስክርነት የለም

- መልስ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ተያያዥ ነው የምንለው ተያያዥ ነው የምንልበት ምክንያት ፖሊሶቹ ለብርበራ ነው የሄዱት ብርበራው በተደረገ ጊዜ የነበረውን ነገር ምስክሩ ያውቃል ወይም አይቋል ወይም ይረዳል ብለን እናስባለን ይሄንን የሚያውቅ ከሆነ አዎ አውቃለሁ ትክክል ነው ይላል አሁን እንዳለው ማለት ነው አላውቅም ካለ ደግሞ ፍ/ቤቱ ይሄንን መዝግቦ ይሄዳል እና ተያያዥ የሆኑ ነገሮችን ስንጠይቅ ልትጠይቁ አይገባም መባል የለበትም እና ተገቢ ነው መጠየቃችን
- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቶበታል ምስክሩ በዋና ጥያቄ ላይ ያልተጠየቀው የመሰከሩት በታዛቢነት ተጠርቼ ሄጄ በብርበራ ወቅት የነበረውን ሁኔታ አውቃለሁ ብለው ይሄንን ቃላቸውን ሰጥተዋል ከእዚህ ውጪ ከእዚያ ከብርበራው ከተጀመረበት ሰዓት ውጪ ስለነበረው ሁኔታ ያውቃሉ ተብለውም አልቀረቡም ስለዚህ ዋና ጥያቄ የሚያተኩረው እዚያ ላይ ነው ከእዚህ ውጪ ባሉት ነገሮች ላይ ጥያቄው ማለፉ ከዋናው ጥያቄ ከቀረበው ነገር ውጪ ነው የሚሆነው ብሎ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቶበታል እና ወደ ዋናው ጥያቄ ላይ አተኩሩ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ጥላሁን አሁን ቀደም ብዬ ጠይቄ ልጆቻቸው መጥተው ነው ተጠርተው ኮምፒዩተሩን ከፍተው የታየው ብለሀል የእኛ ነው ይሄ ኮምፒዩተር የእኛ ነው እያሉ ነው ፖሊስ የወሰደው አይደል ?
- አዎ
- ወቅቱ የፆም ወቅት ስለሆነ ከጎረቤት እና ዘመዶቻቸው ሊጠይቋቸው መጥተው 10 የሚሆኑ ሰዎች የነበሩ መሆኑን ታውቃለህ እዚያ እሳቸው ጋር ?
- አላውቅም
- አቶ ጥላሁን ቅድም የፍ/ቤት ወረቀት ለታዛቢዎችም እንደተነበበ ገልፀዋል ከመነበቡ ውጪ እርሶ አይተውታል ?
- አይቼዋለሁ
- ከየት ፍ/ቤት ነው የሚለው ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከአራዳ ፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት
- ስንት ዳኞች እንደፈረሙበት ያውቃሉ ?
- 1
- እቃዎቹን የት የት ጋር ነው ያገኛችሁት እነዚህ ቅድም የዘረዘሯቸውን እቃዎች ቤት ውስጥ ስትበረብሩ ሲበረበር ?
- እቤት ውስጥ ነው ክፍሎች አሉት ክፍሎች ውስጥ ነው ያገኘናቸው
- ማለት የት ጋር እንደሆነ የት ክፍል ውስጥ ሳሎን አለ መኝታ ቤት እቃዎቹ የት ጋር ነበር ?
- ክፍሎቹ ብዙ ስለሆነ እቃ ቤት አለ ብዙ ነው እንትኑ ክፍሉ
- እሺ እነዚህ አሁን መፅሐፍ አንድ መፅሐፍ የገለፁት አለ ምን መደርደሪያ ላይ የመፅሐፍ መደርደሪያ ላይ የነበረ ነው ?
- አዎ
- እነዚህ ቪዲዮ ካሴቶች ቪዲዮ ካሴት ያሉን ቴፕ የቴፕ ካሴት እነዚህስ የት ጋር ነበሩ ?
- እነሱ መደርደሪያ ውስጥ ነበር ያሉት
- አጠገባቸው ማጫወቻው ነበረ ቪዲዮ ማጫወቻ ?
- የሉም ግን አንድ ላይ ነው ያለው ቦታዎቹ
- እነዚህ ብርበራው ከ 3 ሰዓት ተጀምሮ 10 ሰዓት አለቀ ብለዋል በእዚህን ጊዜ ውስጥ ረጅም ሰዓት ጊዜ ውስጥ ምን ይሰራ ነበር ማለት የተገኙ እቃዎች አሁን ዘርዝረዋቸዋል ይሄንን ያህል ጊዜ ለምን ፈጀ 7 ሰዓት ያህል ማለት ነው ?
- ክፍሎቹ ብዙ ስለሆኑ አንድ በአንድ እየተወጣ መፈተሽ ስለነበረበት ለእዚያ ነው
- ስንት የቤተሰብ አባል ነበረ ከሼህ አብዱራህማን ውጪ ?
- 5 ናቸው ያሉት ያየናቸው
- ብርበራው ሲካሄድ እነዚህ እንዲወጡ ታዘዙ ከቤት ?
- ግቢ ውስጥ ነበር ያሉት
- ግቢ ?
- ግቢ ውስጥ ናቸው ያሉት

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁሉም ግቢ ውስጥ ?
- አዎ
- ማለት መጀመሪያም ግቢ ውስጥ ነበሩ ወይስ እናንተ ስትገቡ ወጡ ?
- ከመጀመሪያውኑ ውስጥ ነበሩ ግቢ ውስጥ
- ማን ነው የፃፈው ?
- ቃለጉባኤውን እዚያው እየተፃፈ ነው የፈረምንበት
- ማን ነው ይፅፍ የነበረው ይሄንን ያህል ይሄንን ያህል እያለ ፁሑፉ የማን ነው ቃለጉባኤው ላይ የተፃፈው ?
- ማለት እዚያው ፈታሾች ናቸው ከፌዴራል ፖሊስ የመጡት
- ከፖሊሶች ነበር ?
- አዎ
- ቅድም ኮምፒዩተሮችን እነዚህ 2 ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች አሸጋችሁ እንዴ በላያቸው ላይ አሸጋችሁ ፈርማችዋል ?
- በቃለ ጉባኤው ላይ ነው የፈረምነው
- እንጂ ላፕቶፖቹ ላይ አልታሸጉም እናንተም አልፈረማችሁም አይደል ?
- አዎ
- ካሴቶችም ምን እንደሆኑ አላያችሁም ከፍታችሁ ?
- አላየንም
- በላያቸው ላይም ምልክት አላደረጋችሁም በካሴቶቹ ላይ ?
- አልተደረገም
- መፅሐፉ ላይስ ?
- መፅሐፎቹ ላይ አልተደረገም እያንዳንዱ ላይ የተገለፀ ነው የተፈረመበት
- ቃለጉባኤው ላይ ፖሊሶች ፈርመዋል እንዴ ?
- ማለት እሳቸው እና እኛ ነን የፈረምንበት
- 2 ታዛቢዎች እና ሼህ አብዱራህማን ብቻ ነው የፈረሙ ?

3235

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እነዚህ ቅድም የተጠቀሱትን ነገሮች እንዳላዩ ገልፀዋል ለፍ/ቤቱ ይዘታቸው የሁሉንም የቪዲዮ ካሴቶቹንም የሲዲዎችንም አይደል ?
- ረጅም ጊዜ ስለሆነ አላስታውሰውም
- አይታችዋል ወይስ አላዩም ይዘታቸውን ?
- ይዘታቸው አይቼዋለሁ
- ምን ምን ይላል ?
- በአረብኛ ስለተፃፈ
- አያውቁትም ምን እንደሚል አይደል ?
- አዎ
- ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ሕገ ወጥ መሆናቸውን ያውቃሉ አያውቁም እርሶ ሕገ ወጥ ናቸው የሚል ነገር አለበት ?
- የለበትም
- የዐቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ይቀጥል
- ቅድም ሲጠየቁ ላፕቶፖቹን በተመለከተ ልጆቹ ስንት ሰዓት ላይ ነው የመጡት ?
- ልጆች እኛ ፈትሸን አንድ ሁለት ቤት ሲቀረን ልጆቻቸው ነበሩ ውስጥ
- ልጆቻቸው ?
- አዎ መጥተው ነበር
- መጥተው ነበረ ?
- አዎ
- ልጆቹ ምን አሉ መጥተው ?
- ልጆቹ ምንም ላፕቶፑ የእኛ ነው ብሏል አንደኛው
- ላፕቶፑ የእኛ ነው አሉ መጀመሪያ ተከሣሹ እንደዚያ ብሏል እንዴ ላፕቶፑ የልጆቼ ነው ብሏል ?
- አላሉም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላሉም ልጆቹ መጥተው ነው የእኛ ነው ያሉት ?
- አዎ
- ልጆቹ አማርኛ ይችላሉ አይደል ?
- አማርኛ ይችላሉ
- የያዛችዋቸውን ንብረት አይተዋል አይደል ልጆቹ ?
- አይተዋል
- አይተዋል ዝርዝሩን ?
- አዎ
- ከእዚያ ውስጥ መርጠው ነው እነዚህ የእኛ ናቸው ብለው የጠየቁት ?
- የለም
- እኮ አይ ከላፕቶፖቹ ውጪ የጠየቁት ነገር የለም ?
- የለም አዎ
- ቅድም በመስቀኛ ጥያቄ ሲጠየቁ 10 ሰው በላይ እቤት ውስጥ ነበር ይሄንን ያህል ሰው ?
- ይሄንን ያህል ሰው የለም
- ምን ያህል ሰው ነበረ ቤት ውስጥ እርሶ ሲገምቱ ?
- ከ 5 ከ 4 እስከ 5 ናቸው
- የእሳቸው ቤተሰብ ማለት ነው ?
- አዎ
- ብርበራውን ስታደርጉ በቦታው የነበሩ ?
- አዎ
- ጨርሰናል ድጋሚ ጥያቄ
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ አሁን ቅድም ወይ እኔ ግልፅ ሳልሆን ቀርቼ ሊሆን ይችላል ይሄ ላፕቶፕ የእኛ ነው ያሉት ልጆች መርጠው ነው እያልከን ነው አሁን መጨረሻ ላይ እንደዚያ ነው ?
- መጀመሪያ ነው ሲወጣ የእኛ ነው ነው ያሉት
- እኮ የትኛውን ኮምፒዩተር ነው ሁሉንም ነው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 2 ነው ያለው ስሙን አላስታውሰውም አንደኛውን ኮምፓት እና ቶሺባ ነው ያለው 2 ናቸው 2ቱ ማለት ነው አንደኛው ነው የእኔ ነው ያለው አንደኛው ልጃቸው ማለት ነው
- 1ኛው ነው ?
- አዎ
- 2ቱን ነው የእኔ ነው ያለው ወይስ ?
- አንዱን ነው የእኔ ነው ያለው
- አንዱን ?
- አዎ
- አንዱስ ?
- አንዱን አልነገረኝም
- አንዱን አላለም ?
- አዎ
- እናመሰግናለን ጨርሰዋል ይመለሱ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- 88ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ስምዎትን የመጀመሪያ ስምዎትን ብቻ ነው የሚነግሩን
- ባምላኩ
- በማስረጃ ዝርዝሩ ስንተኛ ተራ ቁጥር ላይ ነው ያለው ዐቃቤ ሕግ ?
- 178 ላይ
- ለምንድን ነው የመጡት እዚህ ፍ/ቤት ?
- ያየሁትን ለፍ/ቤት
- ለመመስከር ?
- አዎ
- በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት በማን ተከሣሽ ላይ ?
- አቶ ሙሪድ ሽኩር በሚባል ሙሪድ ሽኩር
- ሙሪድ ሽኩር ?

ECLN

3032

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ያውቋቸዋል እንዴ ተከሣሹን ?
- ያው በእንትን
- በአካል ይለዩዋቸል ?
- በአከራሪነት ዙሪያ ነው ከእዚያ በፊት አንተዋወቅም
- እኮ ይልዩዋቸል አሁን መለየት ይችላሉ ?
- ካሉ ከእዚህ ልለያቸው እችላለሁ
- እስቲ ለዩዋቸው 10ኛውን ተከሣሽ ለይተው አሳይተዋል የዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ አሁን የለዩዋቸውን ተከሣሽ የት ነው የሚያውቋቸው ?
- ተከሣሹን የማውቃቸው እኔ ማለት ካራቆሬ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ካራ ቆሬ ልዩ ቦታው እዚያ አካባቢ ነዋሪ ነኝ እኔ
- ክፍለ ከተማው የት ነው ?
- ኮልፌ ቀራንዮ
- ኮልፌ ቀራንዮ ?
- አዎ
- ሙሉ አድራሻውን ይንገሩን እስቲ ሙሉ አድራሻው ምንድን ነው የሚባለው ቦታው ?
- ካራቆሬ ቦታው መለያው ካራቆሬ ይባላል
- ካራቆሬ እሺ ጊዜው መቼ ነው ?
- ጊዜው 2004 ሐምሌ 12 ቀን ማለት ነው
- ሐምሌ 12 ?
- አዎ
- ሰዓትስ ?
- ሰዓት 2 ተኩል
- ማለት 2 ተኩል ምን የሆነበት ነው ?
- 2 ተኩል በቃ እንትኑ ማለት ቤቱ መኖሪያ ቤታቸውን ለማየት በ[illegible]ቢነት /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተገኛችሁበት ነው ?
- አዎ
- ቀን ነው ማታ ነው ?
- ቀን ጠዋት ላይ ማታ አይደለም ጠዋት
- ጠዋት ላይ ነው እሺ አሁን በገለፅኩት ቦታ የቤት ቁጥሩን ያስታውሱታል ?
- የቤት ቁጥሩን አላስታውሰውም
- አያስታውሱም ?
- አዎ
- አሁን በገለፁት ቦታ እና ጊዜ ምንድን ነው የታዘቡት ?
- እዚያ በደረስንበት ሰዓት እኔ ለስራ እንደወጣሁ ነው እንደዚህ እንደዚህ በእዚህ ቤት እንትን ልንል ስለሆነ ከፍ/ቤት ማዘዣ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚባል ነገር /ግልፅ ያልሆነ/ ያው ገብቼ ብታዘብ ምንም ችግር የለውም ያየሁትን መመስከር ስለምችል ብዬ እሺ ብዬ ሄድኩኝ ፍ/ቤት የተላከውን የመበርበሪያ ትዕዛዝ አሳዩን አነበቡልን እና ከእዚያ ገባን
- የፍ/ቤት ትዕዛዝ አነበቡላችሁ ገባችሁ ?
- አዎ
- የፍ/ቤት ትዕዛዝ ለማን ለማን የት ነው የተነበበው ?
- እዚያው በር ሳንገባ ማለት ነው
- በር ሳትገቡ ?
- አዎ
- ለማን ለማን ነው የተነበበው ?
- እዚያው ላለነው አጠቃላይ
- እኮ ለማን ለማን ንገረን እዚያ በቦታው ስላልነበርን ንገረን ማን ማን ነበራችሁ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሲነበብላችሁ ?
- ካሳሁን የሚባል ልጅ ነበረ ሌሎቹን አላውቃቸውም እሱን ብቻ ነው የማውቀው
- እሺ ከታዛቢ ከፖሊሶች ውጪ ሌላስ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ የማውቀው የለኝም
- ሌላ ሰው የለም ?
- ሰው የለም ሳይሆን ስማቸውን አላውቃቸውም
- ስማቸውን አታስታውስም ?
- አዎ
- የፍ/ቤት ትዕዛዙ ከየት ይላል የምታስታውሰው ከሆነ ?
- የፍ/ቤት ትዕዛዙ የሚለው ከአራዳ
- ከአራዳ ነው የሚለው እሺ ምን ምን በብርበራ ምን ምን ይያዝ ይላል ?
- በብርበራው ይያዙ የሚል እዚያ ተዘርዝሮ እንዳየዋቸው ከሆነ የተለያዩ የጦር መሣሪያዎች ሰነዶች እና ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ነው እነዚህን ነው እኔ ያየሁት
- ይያዙ ይላል ?
- አዎ
- ይሄንን የፍ/ቤት ትዕዛዝ ከተነበበላችሁ በኋላ ገባችሁ ስትገቡ እንዴት ነበር አገባባችሁ እስቲ ንገረን ?
- የገባነው ያው እሳቸው መጀመሪያ ገቡ ከእዚያ ቀጣይ ፖሊሶች ከእዚያ እኛ ታዛቢዎች ደግሞ እየተከተልን በኋላ ሆነን ነው ያለነው
- እሺ አቶ ሙራድ ሽኩር የት ነበሩ ?
- እዚያው ቤታቸው
- ቤት ውስጥ ነው የነበሩት ?
- አዎ
- ስትገቡ እዚያው ነው ያገኙዋችዋቸው ?
- ኖ አብረን ነው የሄድነው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- እሺ ቀጥሉ

3035

2780

EOLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መቃወሚያ በምስክር አሰጣጣቸው ላይ ሳይሆን ምስክሩ ለእዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የላቸውም ምክንያቱም በኤግዚቢት አቶ ሙራድ /ግልፅ ያልሆነ/ ተያዘ የሚል እቃ የለም እዚህ ላይ
- አቤት
- በኢግዚቢት አቶ ሙራድ ቤት ተያዘ የሚል እቃ የለም እዚህ ላይ በክሱ ላይ ማለት ነው በክሱ ላይ ባልቀረበ ነገር ምስክርነት መስማት አግባብነት የለውም የተከበረው ፍ/ቤት ቢሰማም አይጠቅምም የቅድሙ ኬዝ ተመሳሳይ ነው ስለዚህ ጥያቄው /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክሩ ለእዚህ ጉዳይ አግባብነት ስለሌላቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- ምላሽ ስጡበት ምላሽ ሲሰጡ ግን ምናልባት እዚህ የተፃፈውን ነገር ገፁን ነው የምትነግሩን ካለ እንዲህ እንዲህ ዓይነት ነገር ለእሱ የሚነገር ነገር እንዳይኖር
- የተከበረው ችሎት ኤግዚቢት ዝርዝር ላይ የሲዲ ዝርዝር ላይ ተራ ቁጥር 14 ላይ ከወንጀል ተግባሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ተጨማሪ ሲዲዎች የሚል አለ 1ኛው 2ኛ ከእነዚህ ተከሣሽ ላይ የተያዘ ሞባይል አለ ሞባይሉ ላይ ደግሞ የቴክኒክ ምርመራ የፌዴራል ፎረንሲክ ምርመራ አያይዘናል የሰነድ ማስረጃ ላይ ማለት ነው ከሞባይሉ ላይ የተገኙ ቴክስቶች በማስረጃነት በሰነድ ያያዝናቸው አሉ ስለዚህ በሰነድ ማስረጃ የቴክኒክ ምርመራ ውጤት የፌዴራል ፎረንሲክ ቴክኒክ ምርመራ ውጤት እና እንዲሁም ደግሞ የሲዲ ከድምፅ ከምስል ማስረጃ በሚለው ዝርዝር ላይ ከወንጀል ተግባሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ተጨማሪ ሲዲዎች የሚል አለ በእዚያ ውስጥ የሚካተት ነው ስለዚህ የምስክሩ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የላቸውም ስለዚህ ሊመስክሩ አይገባም
- አሁን የሚነግሩን ከተከሣሹ ጋር የተያያዘውን ብቻ ነው
- እኮ እያልኩ ነው በአጠቃላይ ማስረጃ ስናቀርብ የቴክኒክ ማስረጃ አቅርበናል ለምሳሌ ከሞባይል የተገኙትን ሰነዱን አያይዘናል መልዕክት የተላላኩትን ማለት ነው ስለዚህ ከእዚህ ውስጥ ሞባይል አለ ለምሳሌ ዝርዝር ላይ በ2ኛው ላይ ደግሞ ሲዲዎችን አስመልክቶ ከጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሚል የሲዲ ዝርዝሮች በጥቅል የተቀመጠ ተራ ቁጥር 14 ላይ አለ ተራ ቁጥር 56 ላይ የገፅ ብዛት 29 የሚለው ማለት ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት መልስ እንስጥበት እዚህ እያየነው ስለሆኑ ለግንዘቤ /ግልፅ ያልሆነ/

3036

2786

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ በቀረበው የምስክሩ አግባብነት ላይ ፍ/ቤቱ አይቶ ብይን ስጥቷል በጠበቆች በኩል የቀረበው የተከሣሹ ቤት ብርበራ ስለመደረጉ የሚገልፅ የማስረጃ ዝርዝር የለውም ስለዚህ ምስክሩ ስለብርበራ ለማስረዳት አይችሉም አግባብነት የላቸውም የሚል መቃወሚያ ቀርቧል በዐቃቤ ሕግ በኩል የተሰጠው ምላሽ በኢግዚቢት ዝርዝር ተራ ቁጥር 14 ላይ ከወንጀሉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ሲዲዎች የሚሉ አሉ እንደዚሁም የተያዙ ሞባይሎች ከፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ጋር በተያያዘ ተመርምሮ የተያዙ አሉ ስለዚህ ምስክሩ አግባብነት አለው ይሰማልን የሚል ምላሽ ሰጥቶ ፍ/ቤቱም አግባብነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ከመዝገቡ ጋር ከተጠቀሱት አጠቃላይ ከመዝገቡ ጋር በተጠቀሱት አጠቃላይ ማስረጃ ዝርዝር እንደዜሁም 10ኛ ተከሣሽን በሚመለከት ከቀረበው ክስ ጋር አገናኝቶ ግንኙነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን መርምሯል ሲታይ ከ1ኛው 10ኛ ተከሣሽ ከሽብር ዓላማውን ለመደገፍ ሲንቀሳቀሱ ነበረ የሚል ዝርዝር ክስ ከተቀመጠ በኋላ በራሪ ወረቀቶችን ሲያስተላልፉ ነበር የሚል ነገር በክሱ ላይ ከእዚህም በተጨማሪ ኢግዚቢት ዝርዝር ተራ ቁጥር 14 ላይ እንደተጠቀሰው የተከሣሾች ሌሎች ተከሣሾች ዝርዝር ከተጠቀሰ በኋላ በመጨረሻ ላይ ከወንጀሉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ሲዲዎች የሚለው ሌሎቹንም ተከሣሾች ለማመልከት የተቀመጠ መሆኑን እንደዚሁም በራሪ ወረቀት ብሎ የተቀመጠውም እና አጠቃላይ ክሶች አጠቃላይ ክሱም ሲታይ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 38/1 ላይ የተያያዘ በመሆኑ በግብረአበር የፈፀሙት ድርጊት የሚል አጠቃላይ ዝርዝት ተቀምጧል ይሄ ተጠቃሎ ሲታይ የቀረበው ማስረጃ አሁን ከተጠቀሱት የፍሬ ነገሮች ጋር አግባብነት ያላቸው በመሆኑ ሊሰሙ ይገባል ተብሎ በአብላጫ ድምፅ ተወስኗል
- እሺ አቶ መላኩ ጊዜውን እና ቦታውን ነግረውናል ካቆሙበት ይጀምሩ ምን ምንድን ነው የተያዘው
- ምናልባት የተከበረው ፍ/ቤት ተሳስተን ከሆነ እኛ እንድናስተካክለው ምናልባት ከተፈቀደልን በአብላጫ ድምፅ የሚል ነገር ስለሰማን ምናልባት አብላጫ ድምፅ ከሆነ ልዩነቱ ድምፅ ነው ሊነገረን ስለሚገባ ነው ተሳስተን ከሆነ ብይን የተሰጠው በአብላጫ ድምፅ /ግልፅ ያልሆነ/
- አብላጫ ድምፅ ነው
- ልዩነቱ ሊነገረን ይገባል

3037

2786

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአብላጫ ድምፅ ተወስኗል ውሣኔው የተፃፈ ስላልሆነ ልዩነቱን የሚገልፀው ልዩነት ኃሳቡን ያመጡት ዳኛ ስለሆነ ለእዚያ ነው የአብላጫውን /ግልፅ ያልሆነ/
- አይ ልዩነቱንማ የማወቅ መብት አለን እና ሊነገረን ይገባል የተከበረው ፍ/ቤት
- ግልፅ እኮ ነው መብት የላችሁም አልተባለም እሱን የተፃፈ ቢሆን ይነበባል ያልተፃፈ ስለሆነ ይገለፃል
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ዐቃቤ ሕግ ልዩነት ድምፁ ይገለፅ ስለተባለ ይሄን መብት በመሆኑ ምክንያት የልዩነት ድምፁ ይገለፃል በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተነሳው ክርክር ምስክሩ አግባብነት የላቸውም የሚል ነው ዐቃቤ ሕግ ምስክሩ አግባብነት አላቸው በማለት ገልፆዋል በአነስተኛው ድምፅ የተነሳው ኃሳብ ምስክሩ የብርበራ ታዛቢ ተብለው የቀረቡ ሲሆኑ በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ በብርበራ የተገኙ እቃዎች ተዘርዝረው ተመልክተዋል በብርበራው የተገኙ እቃዎች ከማን ቤት እንደተገኙ እንደዚሁ ተዘርዝሮ ተመልክተዋል ዐቃቤ ሕግ በማስረጃነት ከጠቀሰው ምናልባት በተራ ቁጥር 14 ላይ በብርበራ የተገኙ ሲዲዎች ላይ 14ኛ ተራ ቁጥር የሚለው ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሲዲዎች ነው የሚለው ከ 1 እስከ 13ኛ ተራ ቁጥር ያሉት ዝርዝሮች በየተከሣሹ ተለይተው በብርበራ የተያዙ ሲዲዎች ተብለው ተለይተው ተገልፀዋል በመሆኑም እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ከተከሣሹ ቤት በብርበራ ተገኝተዋል የተባለ እቃ ያልተዘረዘረ በመሆኑ ምክንያት ምስክሩ በተከሣሹ ቤት ተገኝቷል የተባለ ብርበራን ሊያስረዱ ይችላሉ ብዬ ስላላመንኩኝ አግባብነታቸውን መሠረት ተደርጎ በተከሣሾች ተከላካይ ጠበቆች የቀረበው ተቃውሞ ተገቢ ነው እና ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባ ነበር በማለት ተለይቼአለሁ
- ቀጥል
- ይንገሩን ዝርዝሩን ምን ምንድን ነው የተያዘው ?
- በዕለቱ ቤታቸው መኖሪያ ቤታቸው ገብተን እኛ እንደታዛቢነት በምንመለከትበት ሰዓት የተበረበረ ሲዲ በተያዩ በአረብኛ የተፃፉ ማለት ነው እኛ ታዛቢዎች ምን መሴጅ እንዳላቸው ምን መልዕክት እንዳላቸው እንትን አላልንም በአረብኛ የተፃፉ ብዙም ብዙ የሆኑ በራሪ ወረቀቶች አግኝተናል ፕላስ ደግሞ ቪሲዲም ተገኝቷል ቪሲዲው በእንትን አስገብተን አላየንም ግን ቪሲዲ እንደተገኘ

3038

2787

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ያህል ነው ቪሲዲ የሚሉት ?
- አንድ ቪሲዲ ነው እኔ ያየሁት ፕላስ ደግሞ ሲዲኤምዬም አግኝተናል
- ቪሲዲው ምን ያህል ነው በቁጥር ?
- 1
- አንድ እሺ ሌላስ ?
- ሲዲኤምኤ
- ሲዲኤምኤ ?
- አዎ
- ሌላስ ?
- ሌላ ደግሞ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሙስሊም የታለ የሚል አንድ መፅሐፍ ትልቅ መፅሐፍ አብሮ እንትን ብለናል እንደተገኘ አይቼአለሁ
- ሌላስ ?
- ሌላ ደግሞ በአጠቃላይ የጉባኤው መጠናከር ሕዝበ ሙስሊሙ ተሳትፎው ምን ይመስላል የሚልም በእጅ የተፃፈ ወረቀት /ግልፅ ያልሆነ/ ትዝ ይለኛል
- ይሄንን ታስታውሳለህ እሺ እነዚህን አሁን የገለፅካቸውን ንብረቶች መጨረሻ ምን አደረጋችሁ ?
- መጨረሻ ላይ እንትን ማለት በርብረው ሲጨርሱ ስራችንን ከጨረስን በኋላ እንትን ያዝን ቃለጉባኤ ማለት ነው
- ቃለጉባኤ ያዛችሁ ?
- አዎ ቃለጉባኤ ይዘን ያው ያሉትን የተገኙትን እንትኖች በራሪ ወረቀቶች ሲዲኤምኤው ቪሲዲውንም ያገኘነውን ነገር ይሄንን ያህል በራሪ ወረቀት ወይም ታፕሌት አግኝተናል ብለን ተፈራርመን ነው የተለያየነው
- ከማን ጋር ነው የተፈራረማችሁት ?
- እሳቸው አለ ተከሣሹም
- ተከሣሹ አሉ ?

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

3039

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ተከሣሽም አሉ እሳቸው አሉ ሌሎች ሲበረብሩ የነበሩ እኛ ታዛቢዎችም ሁላችንም ያገን ያገኘነውን አዎን ብለን ተቀብለን ነው የተለያየነው
- ስንት ሰዓት ላይ አጠናቀቃችሁ ?
- 3 ሰዓት ተኩል አካባቢ እንደዚያ ነው ያጠናቀቅነው
- ስንት ሰዓት ጀምራችሁ ነው 3 ሰዓት ተኩል
- 2 ተኩል
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት
- የዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ይቅረብ
- አቶ ባምላኩ በቦታው ላይ ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል ነው የተገኘነው ብለሀል ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል ስትገኙ መጀመሪያ አንተን ያናገረህ ማን ነው በታዛቢነት እንድትገኝ ያናገረህ ሰው ማን ነው ?
- እኔን በታዛቢነት እንድገኝ እንትን ያሉኝ የእዚያው እንትን ማለት አብረውን የነበሩ ሰዎች እነሱ ናቸው በታዛቢነት እንደዚህ እንደዚህ የሚጠረጠር ሰው አለ
- ማን ናቸው እነሱ ሰዎች ምንድን ናቸው ሰዎቹ ? ያናገረህ ሰው ምንድን ነው ?
- እኔ ምንነቱን አላወኩም ምን እንደሆነ
- የስራውን ኃላፊነትንስ ታውቃለህ ?
- የስራውን ኃላፊነት እኔ አላውቅም
- ማንነቱን የሚያሳይ ነገርም አልሰጠህም አላሳየህም ?
- እኔ ማን እንደሆነ አላወኩም ሰውዬውን
- በራፉ ጋር ቆመን ተነቦልናል ብለሀል ትዕዛዙ በር ላይ ቆማችሁ የነበራችሁት ቅድም ስትገልፅ ፖሊሶቹ እና ካሳሁን የሚባል ሰው ብቻ እንደሆናችሁ ገልፀሀል በእዚያን ጊዜ ሙራድ ሽኩር አልነበረም አይደል ሲነበብ ?
- ነበረ
- የት ነበር እሱ ?
- እዚያው አብሮ ከእኛው ጋር ነበር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከየት መጥቶ ነው እዚያ ከእናንተ ጋር የተገኘው ?
- እኔ ከየት እንደመጣ እንጃ ሲሄድ እኔ ለታዛቢነት በምሄድበት ሰዓት እዚያው ከፖሊሶች ጋር አብሮ ነው ያገኘሁት
- ከየት እንደመጣ አታውቅም ?
- እኔ ከየት እንደመጣ አላወኩም
- እሺ ይ ሰው ሙራድ መሆኑንስ አንተ ያየኸው ነገር አለ ያረጋገጥከው ነገር አለ መጀመሪያ ?
- መጀመሪያ ማንም ማለት ሰውዬው ማን ቤቱ የሚበረበረው አቶ ሙራድ ሽኩር የሚባል ሰውዬ እንደሆነ ነግሮናል የቤቱ ባለቤት ማለት የሚበረበረው እሱ እንደሆነ ከእዚያ ደግሞ ስሙንም ያወኩት አጀንዳ ወይም ይሄ ቃለጉባኤ ይዘን ስንፈራረም ስሙን ከእዚያ ነው የተረዳሁት እንጂ ከእዚያ በፊት እኔ ሰውዬውን አላውቀውም
- እሺ ቅድም ቤት ውስጥ ስለተገኙ እቃዎች ዘርዝረሀል ሲዲ እቤቱ አልተገኘም አይደል ሲዲ በዝርዝራችሁ ውስጥ የለም አይደል ?
- ቪሲዲ አግኝተናል
- ሲዲ የላቸውም?
- ሲዲ እኔ እንትን አላልኩኝም ቪሲዲ መገኘቱ ትዝ ይለኛል
- እሺ በቃለጉባኤው ላይ ፖሊሶቹ አልፈረሙም አይደል ?
- እኔ እንጃ ብቻ ሰውዬው ምናምን ስንፈርም ትዝ ይለኛል እነሱ መፈረም አለመፈረማቸውን እንጃ
- ፖሊስ አልፈረመበትም ?
- እኔ አልፈረመም አልልህም በቃ ይፈርሙ አይፈርሙ እኔ አላየሁም የራሴን ግን እና ካሳሁን የሚባል አብሮት ሲታዘብ የነበረ እንደገና ተከሣሹ ስንፈርም ትዝ ይለኛል
- እሺ ትዕዛዙ የምታስታውስ ከሆነ የማን ቤት ይፈተሽ ነው የሚለው በትክክል ትዕዛዙን ሰምተሀል ?
- አዎ
- የማን ቤት ነው የሚለው ?
- የአቶ ሙራድ ሽኩር ቤት

3047

2290

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ይፈተሽ ነው የሚለው ?
- ከ 2 ተኩል እስከ 11 ተኩል ድረስ
- ሰዓቱን ይገልፃል ?
- አዎ
- መቼ ነው ይፈተሽ የሚለው ?
- በ 12 የሚል እኔ አይቼአለሁ በ 12 ሐምሌ 12 ማለት ነው 11ኛ ወር ሐምሌ 12
- ይፈተሽ የሚለው በ 12 ነው ?
- አዎ
- እናንተ ፍተሻ ያደረጋችሁት መቼ ነው ?
- በ 12
- እሺ ትዕዛዙ ላይ መፅሐፎች እንዲያዙ አያዝም አይደለም ?
- መፅሐፍ አይያዝ ይያዝ የሚል ሳይሆን የተለያዩ ሰነዶች እንዲያዙ የሚል ስላለ
- መፅሐፍ ግን ይያዝ የሚል ግልፅ ትዕዛዝ የለውም ?
- መፅሐፍ የሚል አላየሁም
- ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ሲል ከወንጀሉ ጋር የተገናኙ ነው የሚለው አይደለም ከወንጀሉ ከተጠረጠሩበት ወንጀል ጋር የተገናኙ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ነው አይደል ይያዝ የሚለው አይደል ?
- ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች እንዲያዙ የሚል መልዕክት እኔ አንብቤአለሁ
- እኮ ከሽብር ወንጀል ጋር የተያያዙ ነው የሚለው አይደል ?
- አዎ
- እናንተ እነዚህ አሁን ሲዲኤምኤ እንዲያዝ ሲደረግ ፖሊሶቹ ከወንጀሉ ጋር ከሽብር ወንጀል ጋር የተገናኘ ነው ብለው ለተከሣሽ ያስረዱበት ነገር አለ ?
- እኔ ይሄ ከሽብሩ ጋር ይያያዛል ምናምን ብለው ሲያስረዱ አልሰማዋቸውም ግን እንደተገኘ ይዘውታል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁሉም እቃዎች ከተጠረጠሩበት ወንጀል ጋር የሚገናኙ ናቸው የሚለውን ነገር አላስረዷቸውም በሚይዙበት ጊዜ አይደል ?
- እኔ እንደዚያ የሚባል እንትን አልማስሁም
- አቶ በእውነቱ እርሶ ሲመጡ አቶ ሙራድ ከፖሊሶች ጋር በር ላይ ግቢ ውስጥ ነው ከግቢ ውጪ ነበር የቆሙት ያሉት ?
- የተገናኘነው
- አዎ እርሶ ለመጀመሪያ ጊዜ ታዛቢ እንዲሆኑ ተጠይቀው ሲመጡ አቶ ሙራድን የት ጋር ነው ያገኙዋቸውም ?
- መኪና ውስጥ ቁጭ ብለው ነው ያገኘዋቸውም
- የፖሊስ መኪና ?
- እኔ ያፖሊስ መኪና ይሁን ፖሊስ መኪና የሚል የተፃፈ ነገር አላየሁም ግን መኪና ውስጥ ቁጭ ብለው አገኘዋቸው ከእዚያ ወደቤታቸው ሄድን
- እጃቸው ታስሮ ነበር በካቴና ?
- አዎ
- ከእዚያ ተያይዛችሁ ወደ አቶ ሙራድ ቤት ሄዳችሁ ?
- አዎ
- ቤቱ ግቢ አለው ?
- አዎ ግቢ አለው
- ማን ከፈተላችሁ ?
- ሴት የሆነች ሴት ናት የከፈተችው ሚስቱ ትመስለኛለች
- ማን ነው ያንኳኳው ?
- አብረው የነበሩት ፖሊሶች
- ፖሊሶች አንኳኩ ?
- አዎ
- አንድ ሴት ሚስት የምትመስል ወጣች ከእዚያ ምን አላት ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው አስረዳት እንደዚህ እንደዚህ በእዚህ ጉዳይ ስለተጠረጠራችሁ ቤታችሁን እንትን ለማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያ ግቢው ተከፈተ ገባችሁ ወደ ቤት ገባችሁ ቤት ውስጥ ሌላ ሰው ነበረ ?
- ሕፃናቶች አሉ
- ሕፃናት ብቻ ነበሩ ?
- አዎ
- ከእዚያስ ይቺ ሚስት ያሏት የት ሄደች ?
- አለች የትም አልሄደችም
- ማለት ሳሎን ቁጭ አለች ?
- አዎ
- ከእነ ልጆቿ ?
- አዎ አለች
- በብርበራ ያገኛችዋቸውን ነገሮች የት የት አካባቢ ነው ያገኛችዋቸው ክፍሎች ውስጥ የትኛው ክፍል ነው ያገኛችዋቸው ?
- ይሄ ቪሲዲ ብለን እንትን የምለው ያው ቴሌቭዥኑ አካባቢ ነው ያገኘነው ሲዲኤምኤ ብለን እንትን የምንላት ደግሞ ከሆነ ሎከር ውስጥ ነው ወረቀት ምናምን እንደዚህ እንትን ሲሉ ከእዚያ ነው ያገኙዋት ያቺን ያንን ያዙ የተለያየ በራሪ ወረቀትም እንደገና ቦክስ አለ መደርደሪያ ሼልፍ ውስጥ እዚያ ነው ሲበረበር የተገኙት
- እነዚህን እቃዎች ለይታችሁ ወደ ሳሎን ነው ያመጣችዋቸው ?
- አዎ
- ከእዚያ ከእቃዎቹ ጋር ተከሣሹ ቁጭ ብሎ በቪዲዮ ተቀረፀ አይደል ?
- ኧረ አልተቀረፀም እኔ ሲቀረፅ አላየሁም
- አልተቀረፀም ?
- እኔ ሲቀረፅ አላየሁም
- ፖሊሶቹ ወደ ቤት ሲገቡ ምን ይዘው ነበር በእጃቸው ብርበራ ያካሄዱ የነበሩ ፖሊሶች ምን ይዘው ነበር ?

3D477
2793

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንም የያዙት ነገር አላየሁም
- ቦርሳ ነገር አልያዙም ነበር ?
- እኔ አላየሁም ቦርሳ ይያዙ ምን ይይዙ እኔ እንጃ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የዐቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ ፖሊሶቹ መጀመሪያ ለታዛቢነት ጠይቀውኛል ስትል ማለት ፖሊስ እንደሆኑ በምንድን ነው ያወከው ?
- ያው በአለባበሱ ሳየው ፖሊስ ምናምን በቃ በአክቱ ፖሊስ መስሎ ስለታየኝ ነው
- በአለባበሱ ?
- አዎ
- ምን አለባበሱ ማለት ?
- በቃ አለባበሱ ፖሊስ መስሎ ስለታየኝ እኔ ፖሊስ መስሎ ነው የታየኝ በጊዜው ማለት ነው ግን ማለት ወጣ ያለ
- መስሎ ስለታየኝ ሳይሆን ይታወቃል አይደል አንተ ታዛቢ ሁንልን ማለት ሙራድ ሽኩር የሚባል ተጠርጣሪ አለ ቤቱን እንበረብራለን ሲሉ ከእዚያ በኋላ አብራችሁ ከገባችሁ በኋላ ያደረጋችሁት ነገር አለ እነዚህ ሰዎች ፖሊሶች ናቸው አይደሉም የሚሉ የሚለውን የለየህበት ነገር የለህም ወይ ነው ?
- እኔ የለየሁበት ጥርጣሬ እየተናገርኩ ነው ያለሁት በዕለቱ በማያቸው ሰዓት ፖሊስ መስለው ነው የታዩኝ
- እኮ መስለውኝ የሚለውን አስረዳን እንዴት ነው የመሰሉህ ?
- በአለባበሳቸው እና በአከታቸው ፖሊስ መስለው ለምሳሌ እያንዳንዱ የስራ ዘርፍ የሚሳተፍ ሰው አለ በአካሄዱ ወይ በአለባበሱ በዩኒፎርሙ ልትለየው ትችላለህ
- ስለዚህ በዩኒፎርማቸው ነው የለየሀቸው ?
- በዩኒፎርማቸው በአለባበሳቸው ሳያቸው ፖሊሶች መስለው ታዩኝ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ችሎት
- ምስክር መስክረው ጨርሰዋል ተሰናብተዋል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አመሰግናለሁ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክር ስምዎት የመጀመሪያ ስምዎትን ብቻ ነው የሚገልፁት ስምዎት ማን ይባላል ?
- መስፍን በላይ
- በማስረጃ ዝርዝሩ ስንተኛ ላይ ነው ያሉት ለምንድን ነው የመጡት እዚህ ፍ/ቤት ምን ለማድረግ ነው የመጡት ?
- አቶ አቡበከር /ግልፅ ያልሆነ/
- ድምፅዎ አይሰማም
- በታዛቢነት ነበር የመጣሁት
- በታዛቢነት በተገኙበት ጉዳይ ?
- አዎ
- ማን ጋር ነው በታዛቢነት የተገኙት የትኛው ተከሣሽ ጋር ?
- አቶ አቡበከር አህመድ
- አቶ አቡበከር አህመድ ያሏቸውን ያውቋቸዋል እንዴ ?
- አላውቅም
- በአካል ?
- በአካል አላውቀውም
- እሺ የዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ የመጣሁት በታዛቢነት በአቶ አቡበከር መሐመድ ነው ብለዋል በምን ጉዳይ ነው በምስክርነት የሚያውቋቸው ?
- በሽብር በመጠርጠር በሽብር ተጠርጣሪነት
- ተጠርጣሪ ሆነው ?
- አዎ
- ታዛቢ ሆኜ አሉ የት ነው የታዘቡት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀበሌ ኮልፌ ቀራንዮ ቀበሌ 06 ወረዳ 06
- ክፍለ ከተማው የት ነው ?
- ኮልፌ ቀራንዮ
- እሺ የቤት ቁጥሩን ያስታውሱታል ?
- የቤት ቁጥሩ አዲስ ነው
- ጊዜው መቼ ነው ?
- ሐምሌ 13
- ሐምሌ 13 ዓ.ምቱስ ?
- 2004
- አሁን በገለፁት ቦታ እና ጊዜ ምንድን ነው የታዘቡት ?
- የታዘብኩት በብርበራ በፖሊሶች አማካይነት የታዘብኩትን ነው
- አዎ
- የታዘብኩትኝ
- እርሶ መጀመሪያ እዚያ እንዴት ተገኙ ?
- እኔ አጋጣሚ በእዚያው ሰፈር አካባቢ ነኝ
- እዚያው አካባቢ ኖት ?
- አዎ በመንገድ እየሄድኩ እያለ ፖሊሶች ነበሩ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይዘው እንዲህ እንዲህ ልተባተረን ነው ብለውኝ በእዚያ አማካይነት ነው የተገኘሁት
- እዚያው አካባቢ ነበርኩኝ እዚያው አካባቢ ማለት እዚያው አካባቢ ነበርክ እና ማን ነው ታዛቢ እንድትሆን የጠየቀህ ?
- እዚያው ፖሊሶች ናቸው
- ፖሊሶች ?
- አዎ
- ምን ብለው ጠየኩህ ?

3047
2736

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይዘው መጥተው /ግልፅ ያልሆነ/ አብዱራህማን ቤት ብርበራ ልናካሄድ ስለሆነ
- የፍ/ቤት ትዕዛዝ ?
- አዎ ይዘው መጥተው ብርበራ ልናካሂድ ስለሆነ ይሄንን እንደታዛቢነት እንድትመለከትልን ነው ብለው
- የፍ/ቤት ትዕዛዙን አይተኸዋል ?
- አዎ አይቼዋለሁ
- አይተሀል ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከየት ነው የፍ/ቤት ትዕዛዙ የወጣው ?
- ከፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ከፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት
- ቦታው ከየትኛው እንደሆነ ታስታውሰዋለህ ምን ምን ይያዝ ይላል ?
- የጦር መሣሪያ እና አንዳንድ ሌሎች ነገሮች ካሉ ይያዝ የሚል ነው የጦር መሣሪያ እና ሌሎች ነገሮች ያሉ
- የጦር መሣሪያ ሌላስ ?
- እና አንዳንድ ሌሎች ነገሮችም ካሉ እንዲያዝ እንዲበረበር
- ነው የሚለው ?
- አዎ
- ሰዓት ስንት ሰዓት ላይ ነው እናንተ የገባችሁት ?
- 4 ሰዓት ጠዋት 4 ሰዓት ላይ
- ጠዋት 4 ሰዓት እሺ ስንት ሰዓት ጨረሳችሁ ?
- ወደ 9 ሰዓት አካባቢ
- ወደ 9 ሰዓት እስቲ በብርበራ ምንድነ ነው የታዘቡት በብርበራ ?
- የተገኙ እቃዎች ፍላሾች
- ቀስ ብለው እያስታወሱ 1ኛ
- 1ኛ 7 ፍላሽ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፍላሽ ?
- የሲዲ ካሴቶች
- ሲዲ ካሴቶች እስቲ ፍላሹ ስንት ነው በቁጥር ?
- ፍላሹ ወደ 7 ይሆናል ወደ 7 ፍላሽ
- ወደ 7 ፍላሽ እሺ ሲዲ ?
- ሲዲው በቁጥር ትዝ አይለኝም ካሜራ ተገኝቷል
- ካሜራ ?
- የድምፅ መቅረጫ
- ድምፅ መቅረጫ እሺ ?
- 17ቱ የሰላም አምባሳደር የሚል 17ቱ የሰላም አምባሳደር የሚል ፁሑፍ ያለው በራሪ ወረቀት የሰደቃ ፕሮግራም የሚል ፁሑፍ ነገር ያለበት
- የሰደቃ ?
- የሰደቃ ፕሮግራም በደሴ የሚል
- የሰደቃ ፕሮግራም በደሴ ?
- አዎ
- እሺ ሌላስ ?
- ፓስፖርቶች ተገኝተዋል ሌላ ሲም ካርድ ሲምካርዶች 8 ሲምካርድ
- ሲምካርዶች ?
- አዎ ሲምካርድ የሞባይል ሲምካርድ 8 ሲዲዎች ተገኝተዋል የቴፕ ካሴት ሪከርድ የሚያደርግ እሱም
- ሪከርድ ማድረጊያ ?
- አዎ
- ሌላስ ?
- ካሜራ
- እሺ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ደግሞ
- እነዚህን ንብረቶች ምን አደረጋችሁ ?
- እነዚህን ንብረቶች እንግዲህ ፖሊስ ያገኘው ላይ ፈርመን በታዛቢነት
- ምን ላይ ፈረማችሁ ?
- ዝርዝሩ ላይ ማለት ነው የተገኙት በየወረቀቶቹ ላይ ፈረምን
- ዝርዝሩ ላይ ?
- አዎ በእያንዳንዱ ወረቀት ላይ በተገኙት ላይ ከ 1 እስከ 29 የሚሆን ነገሮች ተገኝተዋል የተገኙት ከ 1 እስከ 29 የሚሆኑ ነገሮች ነው የተገኙት
- በዝርዝር 29 ዘርዝራችሁ ነው የያዛችሁት ንብረቶችን ?
- አዎ
- ከእዚህ ውጪ ሌላ ላይ የፈረማችሁት ነገር አለ ?
- ከእዚህ ውጪ ምንም ላይ አልፈረምንም
- ዝርዝሮቹ ላይ ብቻ ነው የፈረማችሁት ?
- አዎ
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል
- የተከሣሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥል ተብሏል
- አቶ መስፍን እርሶ በታዛቢነት ተጠየቀ ወደ ቤት የሚፈተሸው ቤት ሲሄዱ ቤቱ ግቢ አለው እንዴ ቤቱ ?
- ቤቱ ትንሽ ግቢ ነው ያለው
- ቤቱ ግቢ አለው አይደል ?
- አዎ ትንሽ ግቢ አለው እኔ ከቤቴ ስወጣ በመንገድ ላይ ነው የተገናኘው ወደ ቤት ለመግባት ሲሉ ማለት ነው ያገኙን በ2ቱም ታዛቢዎች አማካይነት እሱ የሰፈሩ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለሆነ በ3ኛ ታዛቢነት እንዲሳተፍ ብለው ነው ያገኙኝ እና የገባነው
- እኮ እርሶ ታዛቢ ሆነው ወደ የሚበረበረው ቤት ሲገቡ ፖሊሶች ግቢ ውስጥ ነበሩ አይደል?
- ግቢ ውስጥ አይደለም ከግቢ ውጪ ላይ ከመግባታቸው በፊት ነው
- ከግቢው ውጪ ነበሩ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ደጅ ላይ ቆመው ከመግባታቸው በፊት
- ግቢው ተዘግቶ ነበር ?
- በር ዝግ ነበር አዎ
- ማን ከፈተ ?
- የአቡበከር ሚስቱ ከፍታ ወጣች
- አቡበከር አልነበረም አይደል ?
- አልነበረም
- የአቡበከር ሚስት መሆኗን በምን አወቁ እርሶ ?
- እነሱ ፖሊሶቹ ሲጠይቋት ነው የአቡበከር ባለቤት ነሽ ወይ ብለው ሲጠይቋት አዎ አለች እና ከፍ/ቤት እንዲህ እንዲህ ልናደርግ ነው የመጣነው ብለው የፍ/ቤት ወረቀቱን አነበቡላት እና እንዲገቡ ፈቀደችላቸው እና ገባን
- ወረቀቱን አነበቡላት ?
- አዎ
- እንጂ ሰጥተዋት እሷ አላነበበችም አይደል ?
- አይ እሷ እነሱ ካነበቡ በኋላ እሷም ተቀብላ አንብባለች
- አንብባለች ቤት ስትገቡ ሌላ ሰው ነበር እንዴ የቤተሰብ አባል ?
- አዎ ነበሩ
- ትላልቅ ሰዎች ነበሩ ?
- 2 ልጆች እና አንድ ትልቅ ሰው ሠራተኛ ነበረ
- ብርበራው ሲካሄድ እነዚህ ሰዎች እነዚህ የቤተሰብ አባል ወዴት ከግቢ እንዲወጡ ወይም ከቤት እንዲወጡ ተደረገ ?
- አይ አልተደረገም እነሱም እዚያው ቁጭ ብለዋል
- የት ቁጭ አሉ ?
- እዚያው ሳሎን ውስጥ
- ሳሎን ቁጭ አሉ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ቅድም ሚስት የአቡበከር ሚስት ነኝ ያለችው ሴት ከእዚያ ውጪ ፖሊሶቹ እሷ ከተናገረችው ውጪ ሚስት ስለመሆኗ ያረጋገጡበት ነገር የለም አይደል ?
- ምንም ነገር የለም ሚስት ነኝ ያለችው እሷ ስለሆነች ሌላ ነገር ማረጋገጫ አላየሁም
- እቃዎቹ የት የት ጋር ተገኙ ?
- እቃዎቹ ሳሎን ውስጥ የነበሩት ካሴቶች ፍላሾቹ የተለያዩ ነገሮች በሳሎን ውስጥ ተገኝተዋል በመኝታ ቤት እንደገና ደግሞ ከመኝታ ውጪ ኪችን ውስጥ ምናምን አንዳንድ ወረቀቶች ምናምን ተገኝተዋል
- መፅሐፍ መደርደሪያ ነበር እንዴ ?
- አዎ መፅሐፍ መደርደሪያ
- ከመፅሐፍ መደርደሪያ የተገኘ ወረቀቶችም አሉ ?
- አለ አዎ ቁርንአን መደርደሪያ አለ ከእነሱ ወደታች መሳቢያዎች ውስጥ ምናምን የተገኙ ናቸው
- መሬት ተቆፍሮ ወይም ጣሪያ ተቀዶ የተገኘ ነገር የለም አይደል ?
- የለም
- ታዛቢዎቹ ከበርባሪዎች ጋር አብራችሁ ነበር የምትዞሩት ?
- አዎ በየከፍሉ አብረን እየዞርን
- እነዚህ ቅድም ተገኙ ባሉዋቸው ሲዲ ካሴት ውስጣቸውን አላያችሁም አይደል ከፍታችሁ ?
- ውስጡ ምን መረጃ እንዳለ አላየሁም
- ፍላሹንም አላያችሁም ?
- አዎ በሰዓቱ የምናይበት ነገር ስለሌለ ምንም ያየነው ነገር የለም ውስጡ ያለውን ነገር
- ቅድም በተገኙ ሰነዶች በእያንዳንዱ ላይ ፈርመናል ነው ያሉት ?
- አዎ
- እነዚህ ካሴቶቹ ላይ የሲዲ ካሴት የቴፕ ካሴት ያሏቸው ላይ ምልክት አደረጋችሁ እንዴ በእነሱ ላይ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ ላይ ምልክት አላደረግንም በቁጥር ይዘነው ይሄንን ያህል ሲዲ ይሄንን ያህል ፍላሾች ተብሎ ብቻ ነው
- ቃለጉባኤው ላይ ነው የፈረማችሁት ?
- በቃለጉባኤ አዎ የፈረምነው አንድ ላይ ነው
- ቃለጉባኤውን ማን ነበር ያዘጋጀው ?
- እራሳቸው ነው ፖሊሶች
- ፖሊሶች ናቸው ያዘጋጁት ?
- አዎ
- ፖሊሶቹ ፈረሙ እንዴ እዚያ ቃለጉባኤው ላይ ?
- አዎ ፈርመዋል ሁላችንም ፈርመናል
- ፖሊሶች ፈርመዋል ብርበራ ያደርጉ የነበሩ ፖሊሶች ፈርመዋል ?
- እሱ ትዝ አይለኝም
- ባለቤትየው እቃዎች ተበርብረው ሲወጡ የተጠየቀው ወይም የመለሰችው ነገር አለ ?
- ምንም የተጠየቀችው የለም የመለሰችው የለም
- አሁን ቅድም ወደ 8 የሞባይል ሲምካርድ እነዚህ የት ጋር ነበር የነበሩት ያገኛችኋቸው የት ጋር ሆነው ነው ?
- በኮት ውስጥም ተገኝተዋል በተለያየ ቦታ ላይ ነው ያገኘነው ኮት ውስጥም ስንበረብር በኮት ውስጥ አግኝተናል
- ከእዚያ እቃዎቹ ተሰብስበው እነዚህ የተገኙ ነገሮች ተሰብስበው ወደ ሳሎን ነው የመጡት ?
- አዎ አንድ ላይ ከሌላ ቦታ የተገኘውንም ሁሉንም ሰብስበን በጥበቃ እነሱ እየጠበቁ አንድ ላይ ሰብስበን
- እቃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ከእቃዎቹ ጋር የአቡበከር ሚስት ነኝ ያለችዋ ሴት አልተቀረፀችም እንዴ በቪዲዮ ?
- ተቀርፃለች
- ተቀርፃለች ?
- አዎ

2802

3053

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የፍ/ቤት ትዕዛዙ ላይ በቪዲዮ ይቀረፅ የሚል ነገር የለውም አይደል ይሄንን አንብቦላችዋል ፖሊሶች ?
- ግን እኔ እንደሚመስለኝ እቃውን ይቅረፅ እሷን ይቅረፅ ግን በደንብ ልብ አላልኩም እቃውን ሲቀረፅ ማለት ነው ትዕዛዙ ላይ እንዲህ ይቀረፅ የሚል እሷ ትቀረፅ የሚል ትዕዛዝ አልተነበበልኝም
- የፍ/ቤት ትዕዛዙ ላይ ከመቼ ሲያነብሎት በርባሪው ፖሊሶች ሲያነቡላችሁ መቼ ቀን ይበርበር ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት የሚል የሚለውን ነግሯችዋል ፖሊሶች ?
- ትዕዛዙ የወጣው በ 12 ነው መቼ ቀን ይበርበር የሚለውን ነገር ግን አልተጠቀሰም
- ሰዓቱም ከእዚህን ሰዓት እስከ እዚህን ሰዓት የሚለውን ፖሊሶች አልነገሯችሁም ?
- አልተነገረም
- እርሶ የአካባቢው ነዋሪ ነኝ ስላሉ ከብርበራው በኋላ ምን ሆነ ተበረበረ ቃለጉባኤ ፈረማችሁ ከእዚያ ምን ሆነ ?
- ያለውን እቃ ይዘው ሄዱ በቃ እነሱ በመኪና ያለውን እቃ እንዳለ የተበረበረውን እቃ የተገኘውን ይዘው ሄዱ
- ከእዚያ በኋላ እዚያ ፖሊሶች እዚያ አካባቢ ለመቆየታቸው የሚያውቁት ነገር አለ ?
- እነሱም ተሳፈሩ እኔም ወደ
- ሌሎች ፖሊሶች አልነበሩም ?
- ከእዚያ በኋላ ማንንም አላየሁም እኔ ስራውን እንደጨረስን እኔ ወደ ቤቴ ነው የሄድኩት
- መጀመሪያ ፖሊሶች እርሶን ሲተዋወቆት ወይም ሲነግሮት መታወቂያቸውን አላሳዩዋቸውም አይደል ?
- አሳይተውናል
- ለእርሶ አሳይቶዎታል ?
- አዎ
- እሺ ወደ ቤት በምትገቡበት ጊዜ የአቡበከር ባለቤት ነኝ ላለችው ሴት ፖሊሶቹ መታወቂያ ሰጥተዋታል ወይ አሳይተዋታል ?
- መታወቂያ አሳይተዋታል እነሱም የፖሊስ ልብስ ለብሰው ነበር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ቅድም ጦር መሣሪያ እና ሌሎች ነገሮች ይያዙ ነው የሚለው ብለዋል ሌሎች ነገሮች የሚለው ሌሎች ነገሮች በሚል ነው የተፃፈው ወይስ ከጦር መሣሪያ ጋር የተያያዙ እቃዎች ነው የሚለው ?
- ሌሎች ነገሮች እኔ ስላልኩት ነው እንጂ አሁን ሌሎች ነገሮች የተባለው በእዚያ ሰዓት ሲነበብ ስለረሳሁት ነው በቃ ግንኙነት ያለው ነገር ሁሉ ማለት ነው ከእሱ ጋር ያለው ማቴሪያሎች እንዲያዙ በሚለው
- ከጦር መሣሪያ ጋር ግንኙነት ያለው ማለት ነው ወይስ ምንድን ነው እሺ ልጠይቆት ትዕዛዙ ፍላሽ ሲዲ ካሴት ካሜራ ድምፅ መቅረጫ ፓስፖርት ሞባይል ካርድ ቴፕ ካሴት ካሜራ ይያዝ የሚል ግልፅ ዝርዝር የለውም አይደል ?
- አይ የለም
- እሺ እነዚህ የተያዙት እቃዎች ከሽብር ጋር የተገኙ ስለመሆናቸው ለተከሣሽ ባለቤት ያው የአቡበከር ባለቤት ነኝ ላለችው ሴት አልተገለፀላቸውም አይደል ?
- አልተገለፀም
- ለእናንተም አልተነገራችሁም ?
- አልተነገረንም አዎ
- እሺ አቶ መስፍን ቅድም 17 የሰላም አምባሳደር የሚል በራሪ ወረቀት አይቼአለሁ ብለው ነበረ ስም ተዘርዝሯል 17ቱ እነ ማን እንደሆኑ ?
- የሰዎቹ ስም አልተዘረዘረም
- 17 የሚል ብቻ ነው ያለው ?
- 17ቱ የሰላም አምባሰደር የሚል በራሪ ወረቀት ነው
- ዝርዝሩን አላዩትም ?
- ፎቶ አለው ፎቶ ነው የሰዎቹ ምስል
- የሰዎች ምስል ?
- አዎ
- ከእዚያ ምስል ውስጥ አሁን የሚያስታውሱት አለ ያዩት
- የት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያኔ አየሁ ያሉት ምስል ውስጥ ከእዚህ ውስጥ የሚያስታውሱት አለ ከተከሳሾቹ ያዩት ምስል ተነስተው ማየት ይቻላል ?
- ማስታወስ አልችልም
- እሺ ቅድም ፓስፖርት አይቼአለሁ ብለው ነበረ የማንን ነበር ያዩት ?
- የአቡበከር
- የአቡበከርን ነው ያዩት 8 ሲም ካርድ አየሁ ብለው ነበረ ቁጥራቸውን ያስታውሳሉ ወይም ቁጥራቸውን መዝግበዋቸዋል ያኔ ?
- አይ በሞባይል አልሞከርናቸውም በሞባይል አልሞከርነውም
- ቁጥራቸውንም አልመዘገባቸውም ?
- አልተመዘገበም
- እርሶ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ አላዩትም አይደል ተነበበሎት እንጂ ?
- አዎ ሲነበብ
- እንጂ በአይኖ አላዩም ?
- በአይኔ አላየሁም ተነበበ
- ታዛቢዎቹስ ከእርሶ ሌላ ማን እንደሆኑ ያስታውሷቸዋል ስማቸውን ወይም
- አልሰማሁም
- ታዛቢዎቹን ከእርሶ ሌላ ያሉትን ያስታውሳሉ ?
- ስማቸውን አውቃቸዋለሁ 2 ታዛቢዎች ናቸው አንዱ አያልነህ ይባላል
- ማን ይባላል ?
- አያልነህ
- አያልነህ አንዱስ ?
- አንደኛውን ስሙን አላስታውስም በመልክ ነው የማውቀው
- አቡበከር ቤት ሲገቡ ወደ አቡበከር ቤት አቡበከር ቤት ወይም የአቡበከርን ቤት እንፈትሽ ብሎ የወሰዶት ፖሊሶች ናቸው አይደል ተባበረን ታዛቢ ሁነን ብሎ የወሰዶት ታዛቢዎች ናቸው እንጂ እርሶ የአቡበከርን ቤት አያውቁትም አይደል ?

3256

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ የአቡበከርን ቤት አላውቀውም ትንሽ ከአቡበከር ቤት ወደ ዝቅ ብሎ እኔ ከቤቴ እየወጣሁ እያለ በእነዚህ ታዛቢዎች ምክንያት እሱ የሰፈሩ ልጅ ነው
- የአቡበከርን ባለቤት አየዋት ብለው ነበር መልኳን ያስታውሳሉ ?
- አይ አላየሁም እሷ የተሸፋፈነች ስለሆነ መልኳን አላውቀውም
- ተሸፋፍናለች አላዩም ?
- ተሸፋፍናለች የተሸፈነች ነች
- ስለዚህ ባለቤት መሆኗን በምን ለዩ ?
- እራሱ ባለቤቱ ነኝ ነው ያለችው
- ቤቱ ሲፈተሽ የአቡበከር ባለቤት እስከ መጨረሻው ተሸፋፍና ነበር ወይስ ?
- አይኗ ብቻ ይታያል አይኗ ብቻ ነው የሚታየው
- የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል
- የዐቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ይቀጥል
- ቤት ፖሊሶቹ አሁን መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ የአቡበከር ቤት ነው የምንበረብረው ብለው ፖሊሶች ነው የነገሮት ሲባሉ አዎ ብለዋል አቶ አቡበከር የት አሉ ተባሉ ቤት ስትሄዱ ባለቤታቸውን አልጠየቃችሁም ?
- ጠይቀዋል የለም ነው ያለችው
- የት ሄዱ ?
- የት እንደሄደ አልነገረችንም ግን የለም ነው ያለችው
- የለም ነው ያለችው ?
- አዎ
- እሺ ሰዓቱን ቅድም ማለት የብርበራ ሰዓቱ በፍ/ቤት ትዕዛዙ ላይ አላስታውሰውም ነው አልተጠቀሰም ነው የፍ/ቤት ትዕዛዝ ተነበበልን ያሉት የፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መጠቀሱን አላስታውስም ነው አልተነበበም የለውም ነው ?
- አይ አላስታውስም
- አያስታውሱትም ሰዓቱን ?
- አላስታውሰውም ሰዓቱን

2806 3057

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የፍ/ቤት ትዕዛዙ ላይ ይያዙ የተባሉ ዝርዝሮች የጦር መሣሪያ እና በተመሳሳይ ይሄንንም ሌላ ዝርዝር ይኑረው ሲነበብ ተነቧል ነገር ግን አላስታውስም ነው ወይስ የጦር መሣሪያ እና ከእዚህ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተብለው ነው የተፃፈው ?
- የጦር መሣሪያ እና ተያያዥነት ጉዳይ ያለው
- ሌላ የተዘረዘረ የሚያስታውሱት አላስታውሰውም ነው ?
- አላስታውስም የተዘረዘረውን አላስታውስም ትንሽ ስለቆየ ጊዜው ስለቆየ ማስታወስ አልቻልኩም
- ዝርዝሩን ማስታወስ አይችሉም ?
- አዎ
- ድጋሚ ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት
- ምስክር ጨርሰዋል መስክረው ተሰናብተዋል
- በዛሬው ዕለት እና ከዛሬ በፊት የተሰሙት የምስክሮች ቃል ወደ ፁሑፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር ይያያዝ ተብሏል የምስክር መስማት ሂደቱን በተከታታይ ለመቀጠል ከግንቦት 6 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 16/2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ ይዟል።

http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የ.መ.ቁ 124754

ቀን 6/9/2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብስራት ተዕልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ፡- ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወ/ማገኝ ናቴዎድሮስ ባህሩ ቀርቧል

ተከሣሽ፡-

መሐመድ አብደላ ፣ አዲስ መሐመድ እና ባህሩ መካንጋ ቀርበናል ከ 1ኛ እስከ 28ኛ

ስለ 28ኛ ተከሣሽ አህመድ ጀማል ቀርቤአለሁ

- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጣኸው ስምህን የአባትህን ስም ሳትጨምር የመጀመሪያ ስምህን ብቻ ንገረን ?
- ቢኒያም
- 90ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል አቶ ቢኒያም ቀርቧል በክስ ዝርዝር ላይ ስንተኛ ናቸው እነ ማን ላይ ነው የምትመሰክረው አቶ ቢኒያም ?
- ሰይድ አሊ እና በድሩ ሁሴን
- ሰይድ አሊ ?
- አዎ
- እሺ ሌላ ?
- በድሩ ሁሴን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ አለ ?
- የለም
- ታውቃቸዋለህ እነኚህን ሰዎች በአካል ?
- ማለት አንድ ጊዜ ነው ያየዋቸው
- አሁን መለየት ትችላለህ ?
- ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ያየዋቸው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምስክሩ 5ኛ እና 16ኛ ተከሣሽን አሳይቷል ፀብ ዝምድናም የለንም ብሏል ምን ሲፈፅሙ ነው ያዩት እስቲ አጠር አድርገው ወደ ዝርዝሩ ሳይገቡ እሱን ይግለፁልን ?
- ማለት በአጋጣሚ ያው ፌዴራል ቢሮ ጉዳይ ነበረኝ ወንጀል ምርመራ ለራሴ ጉዳይ ሄጄ አንድ መርማሪ ፖሊስ መጣ እና ለምስክርነት ፍቃደኛ ከሆንክ አለኝ እሺ አልኩት ያው ወደ ቢሮ ይዞኝ ገባ
- እሱን ነው ያየኸው የ2ቱም እዚያው ነው ያየኸው ?
- አዎ ግን በተለያየ ቀን ነው በአጋጣሚ
- የተለያየ ቀን እዚያው ?
- አዎ
- እሺ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ አሁን በችሎት ለይተው ያሳዩዋቸውን ተከሣሾች ከመቼ ጀምሮ ነው የሚያቋቸው ?
- የእዚያ ጊዜ ምስክርነት የነበርኩ ጊዜ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ያየዋቸው አሁን 2ኛ ጊዜ ሳያቸው
- እሺ ይሄንን በእዚያ ጊዜ ብለው የገለፁትን ምናልባት ጊዜውን በቀን በወር ያስታውሱታል መቼ ነበር ቀኑ ምን ወር ላይ ነው ?
- 1ኛው ነሐሴ 29/2004 ነው
- እሺ እስቲ ስለእዚህ ነሐሴ 29 ስላዩት ነገር እስቲ በዝርዝር ያብራሩልን ?
- የእዚያን ዕለት ምንድን ነው ያው ተጠርጣሪው ከግል ላፕቶፑ ላይ
- ማን የሚባለው ነው ተጠርጣሪው ?

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሰይድ አሊ አንዳንድ መረጃዎችን ሲያወጣ እንድትታዘብልን ነው አሉኝ ከእዚያ ሄድኩኝ
- የት ነው ቦታው ?
- ፌዴራል ወንጀል ምርመራ
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ?
- 4 ሰዓት
- ጠዋት ነው ምሽት ነው ?
- አዎ ጠዋት
- ቢሮ ቁጥሩን ያስታውሱታል ?
- 26 መሰለኝ
- ከማን ጋር ነበሩ እርሶ ?
- ማለት እኔ ብቻዬን ነበረ ለራሴ ጉዳይ ስሄድ ወደ እዚያ
- አይ እንዲታዘቡ የተጠየቁበት ክፍል ሲገቡ ሌላ ሰው ነበር ?
- እንደኔ ሌላ አንድ ልጅ አለ ግን አላውቀውም እሱም ለመታዘብ ይመስለኛል የመጣው
- እሺ እስቲ እንዴት ሆነ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስቲ ያለውን ነገር ያብራሩ ?
- ያለውን ነገር ያው ሄድን ያው ተጠርጣሪ እሱ እንደሆነ ነገረኝ መርማሪ ፖሊሱ ያው አሳየኝ
- እሱ ፊት ነው የነገረህ ተከሣሹ ፊት ነው የነገረህ ?
- እሱ ፊት አዎ
- ምን ብሎ ነገረህ ?
- ያው በፈቃደኝነት ይሄንን ማለት ላፕቶፑን አውጥቶ እንትን ሲል እንድታይ እና እንድትመሰክር ነው አለኝ እሱም ያው ሳይገደድ በራሱ ፍቃድ እንደሚያሳይ ገለፀ ከእዚያ ገባን
- ከማን ላፕቶፕ ነው ያ ላፕቶፕ?
- የእሱ ላፕቶፕ ነው ኤች ፒ ላፕቶፕ
- የእሱ ማለት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተጠርጣሪው ማለት ነው ከእዚያን ገባን ከፈተ ኢሜል አድራሻውን ከፈተ ከእዚያ ላይ አንዳንድ የሚፈልጉትን መረጃዎች ኮፒ እየተደረገ ተወጣ ከእዚያ አነበበ መጀመሪያ እራሱ ፈረመ ከእዚያ እኔም አንብቤ ፈርሜአለሁ
- ያ ላፕቶፕ ከየት የመጣ ላፕቶፕ ነው ?
- ከራሱ የተጠርጣሪው ነው
- በምን አወቁ የተጠርጣሪው መሆኑን እርሶ ?
- ማለት የራሱ ላፕቶፕ እንደሆነ እና በብርበራ እንደተገኘ ነው የእዚያን ሰዓት የተገለፀው
- ይሄ ሲገለፅለት ምን አለ ተከሣሹ አረጋግጦሎታል ለእርሶ የራሱ መሆኑን ?
- አዎ
- ላፕቶፑን ማን ነው የከፈተው ?
- እራሱ ነው የከፈተው
- ምን ፓስዋርድ ነበረው ወይስ እንዴት ነበር የከፈተው ?
- ፓስዋርድ ነበረው ይመስለኛል አዎ
- እሺ ከእዚያስ ከምን ውስጥ ነው የወጣው ቅድም ያሉን ኢሜል ምናምን ያሉን ነገር አለ ?
- ከኢሜሉ ነው ከኢሜሉ እና ሀርድ ዲስክም ነበር ኤክስተርናል ሀርድ ዲስክ ትዝ ይለኛል ማለት ረጅም ጊዜ ቢሆንም ኤክስተርናል ሀርድ ዲስክም ነበር
- ላፕቶፑ ኢንተርኔት ነበረው እንዴ በምን ?
- ከውስጡ ውስጥ ካሉት ነው የወጣው
- ውስጥ ካሉት ማለት ?
- ማለት ከራሱ ከላፕቶፑ ውስጥ ነው ፕሪንት እየተደረገ ሲወጣ የነበረው ሲዲዎቹም ነበሩ
- በላፕቶፑ ይሄ የሚሞሪ ክፍል ከራሱ ነው ወይስ ከሌሎች እነዚህ ዲስኮች ምናምን ናቸው ወይስ ከምኑ ላይ ነው ፕሪንት ሲደረግ የነበረው ወይስ ሲወጣ የነበረው ?
- ኤክስተርናል ሀርድ ዲስክም ነበር ኤክስተርናል ሀርድ ዲስኩ እና ከኮምፒዩተሩ ከራሱ ከላፕቶፑ
- ምን ዓይነት ሰነዶች ናቸው ሲወጡ የነበሩት ?
- ፁሑፎች ናቸው የተለያዩ ይዘት ያላቸው ፁሑፎች

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በምን ቋንቋ የተፃፉ ናቸው ?
- በአማርኛ ናቸው
- ሁሉም በአማርኛ ናቸው ?
- አዎ
- ይዘታቸውን ያስታውሱታል ፖለቲካዊ ነው ሀይማኖታዊ ነው ምን ዓይነት ይዘት ያለው ነው?
- ፖለቲካዊም ሀይማኖታዊም ይዘት አላቸው ያው በደንብ ባላስታውሳቸውም የተወሰኑት
- እሺ ገፃቸውን ያስታውሷቸዋል ምን ያህል እንደሆነ ?
- 30 አካባቢ ይመስለኛል
- እሺ ከእዚያስ እንዴት ሆነ ሰነዶቹ ከወጡ በኋላ ?
- ሰነዶቹ ከወጡ በኋላ መጀመሪያ እሱ እያነበበ ይፈርማል ከእዚያ እኔ በቀጣይ እኔ ፈርሜአለሁ እላዩ ላይ ሰነዶቹ ላይ
- ተከሣሽ እና እርሶ ብቻ ሌላ ሰው አልፈረመም ?
- ሌላ ሰው አልፈረመም ሌላ አንደእኔ አንድ ልጅ ነበር መሰለኝ እሱም ሳይፈርም አይቀርም
- እሱ መፈረሙን እርግጠኛ አይደሉም ?
- የፈረመ ይመስለኛል ፈርሟል መጀመሪያ እሱ ይፈርማል ከእዚያ እኔ ነበርኩኝ በቀጣይ ስፈርም የነበረው 3 እና 2 ምስክሮች አለን አንድ እሱ 3ታችን መሰለኝ የፈረምንበት
- እሺ ተከሣሽ ምን እያለ ነበር የሚፈርመው ?
- ያው በፍቃደኝነት ከግል ላፕቶፔ ላይ የወጣ ነው እያለ ይፈርም ነበር
- ዋና ጥያቄ አበቃን የተከበረው ፍ/ቤት ይቅርታ እንቀጥላለን አዎ እሺ አሁን ነሐሴ 29 ስለተፈፀመው ወይም ስለተመለከቱት ነገር ነው የነገሩኝ በሌላ ቀንም ሄጃለሁ ብለዋል ?
- አዎ
- እስቲ ስለእሱም ይግለፁልን መቼ ነው ያ ቀን ?
- መስከረም 8 ነው እሱ ደግሞ
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2005

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ?
- 5 ሰዓት ገደማ ይሆናል
- ቀን 5 ሰዓት ነው ወይስ ?
- ቀን 5 ሰዓት
- ከእዚያስ ? የእዚያን ቀን የሆነውን ልክ ነሐሴ 29 እንደገለፁት እስቲ ዝርዝር አድርገው የነበረውን በወቅቱ የታዘቡትን ነገር ለችሎቱ ያስረዱ ?
- ያው የእዚያን ቀን በተመሳሳይ ነው እኔ እዚያ ጉዳይ ነበረኝ የሆነ የምመላለስበት ጉዳት በአጋጣሚ እንደዚህ መጣ እና አንድ መርማሪ ለምስክርነት እንደዚህ አለኝ ያው አዲስ አልሆኑብኝም ነበር ያው ገባሁ በተመሳሳይ ነው ያደረግነው
- እንዴት አደረገ ከምን ላይ ነው የወጣውስ ?
- የወጣው ከላፕቶፕ ላይ ነው እሱም ኤችፒ ሚኒ ላፕቶፕ ናት የበድሩ ሁሴን
- ምን ዓይነት ላፕቶፕ ነው ?
- ኤችፒ ሚኒ ላፕቶፕ ትንሽዋ ላፕቶፕ ናት
- ከእዚያስ ምን ተደረገ ?
- እሷም የእሱ መሆኑን አረጋገጠ የራሱ ላፕቶፕ እንደሆነ አረጋገጠ
- እናንተስ እዚያ ለምን እንደተገኛችሁ ተነግሯችኋል ?
- ለምን እንደተገኘን ተነግሮናል አዎ
- ለተከሣሽስ ተነግሮታል
- ለተከሣሽም ተነግሮታል
- መቼ ነው የተነገረው በምን አወቁ እንደተነገረው ?
- ፊት ለፊታችን እነዚህ አዎ ምስክሮች ናቸው ተባለ እሱም ያው በገዛ ፍቃዱ ከውስጡ ያሉትን መረጃዎች ኮምፒዩተሩ መጀመሪያ የእሱ መሆኑን አረጋገጠ ከእዚያ ከውስጡ ያሉ መረጃዎች በፍቃደኝነት ለማስረጃነት ስለሚፈለጉ እንዲያወጣ ተደረገ ከእዚያ ተከፈተ ያው ከእዚያ ሂደቱ ቀጠለ ማለት ነው
- ምንድን ነው የተገኘው ከላፕቶፕ ውስጥ የወጣው ምንድን ነው ?
- የተለያዩ ፁሑፎች ናቸው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ ገፃቸውን ወይም የተፃፉበትን ይዘት ?
- ብዙ ናቸው ከ 50 በላይ ይሆናል ከ 50 በላይ ይሆናሉ በጠቅላላ አማርኛ ናቸው
- በጠቅላላ አማርኛ ነው ?
- አማርኛ ነው
- እሺ ከእዚያስ ተከሣሽ ምን አደረገ ?
- ተከሣሽ ያው እያነበበ መፈረም ጀመረ ከእዚያ በቀጣይ ደግሞ እኔም እያነበብኩኝ ፈረምኩ
- እሺ ቅድም መጀመሪያ ላይ ከኢሜል ብለው የገለፁት ነገር አለ ከኢሜል ብለው የገለፁት ነገር ነበረ ?
- አዎ
- እንዴት ነው እስቲ ያደረገው ከኢሜል ሲያወጣ ያዩት ነገር አለ ?
- ማለት ከኢሜል ዳውንሎድ የተደረገ ይሁን የተቀመጠ ከኢሜል አድሬሱ ላይ እንደሆነ እና ያው ፕሪንት እየተደረገ የወጣው ላይ ነው የፈረምነው
- እንጂ እርሶ እያዩ ኢሜል ተከፍቶ ከኢሜል ውስጥ የወጣ ነገር የለም ?
- ልብ አላልኩም
- ዋና ጥያቄ አበቃሁ
- ጠበቆች መስቀለኛ ካለ
- እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ቢኒያም ለግል ጉዳዬ ሄጄ ነበር ነው ያሉት 2ቱንም ጊዜ ለግል ጉዳዮት ነው ወይስ 2ኛውን እንኳን ተጠርተው ነው እንዲመሰክሩ የሄዱት ?
- 2ቱንም ለግል ጉዳዬ ነው የሄድኩት
- የተያዙት ላፕቶፖች መቼ እንደተያዙ አያውቁም አይደል መቼ የተያዙ ላፕቶፖች እንደሆኑ አያውቁም አይደል ላፕቶፖቹ በፖሊስ መቼ እንደተያዙ አያውቁም አይደል ?
- የተያዙበትን ቀን አላውቅም
- አያውቁም አይደል ?
- አዎ
- እርሶ ሲገቡ እነዚህ ተጠርጣሪ የተባሉት ሰዎች ነበሩ ወይስ እርሶ ከገቡ በኋላ ነው የገቡት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኩል ነው የገባነው
- ከእነሱ ጋር ነው እኩል ነው የገባችሁት ?
- አዎ
- ላፕቶፖቹን የያዘው ፖሊስ ነው አይደል የነበረው ፖሊስ ይዞ ነው አይደል አብሯቸው የገባው ?
- ፖሊስ ነው የያዘው አዎ
- ፖሊስ ነው የያዘው ላፕቶፖቹ ከሌላ ኮምፒዩተር ጋር የተገናኙበት ገመድ ነበር አይደል ?
- አዎ ማለት ተነግሯቸው ነበር በሰዓቱ
- አዎ ከሌላ ኮምፒዩተር ጋር ተያይዟል ?
- ሀርድ ዲስኩ ወጥቶ የአንደኛው ኮምፒዩተር ሀርድ ዲስኩ ወጥቶ ተጠርጣሪው ባለበት እንደውም ጠይቋል ተጠርጣሪው እንዴት ነው ምናምን ሲል ስለእንትኑ እውቀት አለው መሰለኝ ሰውዬው
- አሁን ግልፅ እንዲሆንሎት ጥያቄዬ የተጠርጣሪዎቹ ላፕቶፕ ከሌላ ኮምፒዩተር ጋር በገመድ ተገናኝቷል አይደል በ?
- በገመድ ተገናኝቷል ገመዱን አይተውታል አዎ
- ለምሳሌ በ2ኛ ጊዜ ሄጄ አየሁ ያሉት የአቶ በድሩን ነው አቶ በድሩ እነዚህ የእኔ ፋይሎች አይደሉም የእኔም ሊሆኑ አይችሉም እያለ ሲናገር ነበር አይደል እነዚህ ከየት እንደመጡ አላውቃቸውም እዚህ ላይ ልፈርም አልችልም ሲል እንደውም እናንተ እኛም እንመሰክራለን ይሄንን በሚል አስማምታችሁታል አይደል እነዚህ የእኔ አይደሉም ሲል ነበር አይደል ?
- እነዚህ የእኔ አይደሉም ብሏል ትክክል አዎ
- ብሏል የትኞቹን ነው እነዚህ የእኔ አይደሉም ያለው ?
- ማለት እኔ ብዙም ብዙ ፁሑፎች ነበሩ ዲቴል እኔም አላየዋቸውም ነበር
- እኮ ከእዚያ ላይ ፕሪንት ተደርገው የወጡትን እና ፈርም የተባለውን ነው የእኔ አይደሉም ልፈርም አልችልም እዚህ ላይ ያለው አይደል ?
- ግን በፍቃደኝነት እንደፈረመ አውቃለሁ
- አዎ እኮ ሲጀመር መጀመሪያ የእኔ አይደሉም እነዚህ እዚህ ላይ አልፈርምም ካለ በኋላ ኋላ ላይ አስማምተውት ፈርሟል አይደል ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ማለት ምንም ያለመግባባት አልነበረም በሰዓቱ
- ገባኝ የእኔ አይደሉም ግን ብሏል ?
- ከመሀል የእኔ ያልሆኑ አሉ ብሏል አዎ
- እኮ የእኔ አይደሉም የእኔ ፋይል አይደሉም እዚህ ላይ አልፈርምም የዛሬውን ዕለት ጠቅሼ ነው የምፈርመው በዛሬ ቀን ጠቅሼ ነው የምፈርመው ሲል ነበር አይደል ?
- ትክክል ሲፈረምማ ቀንም ተፅፎበታል አዎ
- እሺ ከእርሶ ጋር ሌላ ሰው እንደነበረ ነግረውናል ?
- አዎ
- አሁን በምስክርነት ማጥቷል ?
- አላውቀውም አላስታውሰውም
- አያውቁትም ?
- አዎ
- ለምሳሌ የመጀመሪያው ላይ 30 ገፆች 2ኛው ላይ 50 እና ከእዚያ በላይ ገፆች ብለዋል እና እያንዳንዱን ገፅ አንብበው አይደለም አይደል የፈረሙት በጣም ብዙ ገፆች ናቸው ?
- ማለት እረጅም ሰዓት ነው የፈጀነው ሀይላይት እያየሁት ነበር ያው
- ግን እያንዳንዱን ገፅ አንብበው ተረድተው አይደለም የፈረሙት ?
- አዎ ምናልባት ሳነበው ዲቴል አላነበብኩትም እንጂ ከላይ ከላይ አይቼዋለሁ
- እነሱም አንብበው ተረድተው አይደለም አይደል የፈረሙት ምክንያቱም በጣም ብዙ ገፆች ናቸው ረጅም ጊዜ ይወስዳል ?
- ተጠርጣሪው ግን እያነበበ ነበር ሲፈርም የነበረው እኔም አንብቤአለሁ ግን ከእኔ ያው ምንም ግንኙነት ስለሌው ብዙም እንደዚህ ትኩረት ሰጥቼ አላነበብኩትም
- ቅድም ሲያስረዱን ሁሉም በአማርኛ ናቸው ብለዋል ?
- በአማርኛ ናቸው
- ሁሉም ፁሑፎች ናቸው ፁሑፍ ነበሩ አይደል ሁሉም ?
- ፁሑፎች ናቸው

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፁሑፎች ናቸው ከእዚያ ውጪ ሌላ ነገር የለም በሌላ ቋንቋ የለም ?
- የለም
- ከፁሑፍ ውጪ ሌላም ነገር የለም አይደል ?
- የለም
- እጁ ላይ ነበረው ሰንሰለት ውስጥ ከገባ ነው ውጪ ላይ የተፈታለት እጁ ላይ የነበረው ሰንሰለት ውጪ ላይ ነው ውስጥ ነው የተፈታለት ?
- ሰንሰለት አላየሁም ጭራሽ
- አላየህም ?
- የለም
- አቶ ቢኒያም ላፕቶፑን መርማሪው ይዞት ሲገባ ታሽጎ ነበር እንዴ ላፕቶፑ ላፕቶፖቹ የመጀመሪያው የሰይድ አሊ ላፕቶፕ ታሽጎ ነበር ?
- አይ አልሰማሁም
- ታሽጎ ነበር ላፕቶፑ ?
- አዲስ አይደለም ማለት በካርቶን ምናምን ነው
- እንዴት ማለት እንዴት ሲገጣጠም አሁን መርማሪው አመጣው ሂደቱን እስቲ መርማሪው ላፕቶፑን ይዞ ገባ ?
- አዎ
- ከእዚያ ላፕቶፑን ዝም ብሎ ከፈተው ወይስ በፕላስተር በምናምን ታሽጎ ነበር እንዴ ?
- ማለት መርማሪው ከተጠርጣሪው አንድ ላይ መጣ ያው ከእዚያ ስራ ጋር ያው ግንኙነት ያላቸው ባለሙያዎች ነበሩ የአይቲ ባለሙያዎች ይመስሉኛል ከእዚያ ላፕቶፑን ለተጠርጣሪው አሳዩ የእሱ መሆኑን አረጋገጠ ከእዚያ ተከፈተ
- እንጂ አልታሸገም ነበር ከመከፈቱ በፊት ላፕቶፑ ?
- ማለት በካርቶን ምናምን ነው
- አይደለም በፕላስተር ወይም ተፈርሞበት በፕላስተር የታቀፈ ነገር ነው ከላፕቶፕ ታጥፎ ነው የሚቀመጠው አይደል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ታጥፎ ነው የሚቀመጠው አዎ
- ስለዚህ የታጠፈው ላፕቶፕ እላዩ ላይ በፕላስተር ወይም በወረቀት ታሽጓል እንደዚህ ተደርጓል ተብሎ የተፃፈበት ነገር ነበር ?
- ምናልባት ፕላስተር ሳይኖረው አይቀርም አዎ
- ፊርማ ነበረው ?
- እሱን አላስታውስም
- አቀማመጣችሁ እንዴት ነበር 2 ምስክሮች ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- ተከሣሹ አለ ስንት መርማሪ ነበር ?
- ማለት መርማሪ ነበር ከእንደገና ከኮምፒዩተር ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለሙያዎች ነበሩ መርማሪ ይሁኑ ወይም /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌሎች ሰዎች ነበሩ እዚያ ቤት ውስጥ ብዙ ኮምፒዩተሮች ነበሩ አይደል ?
- ቢሮ ነው አንድ ኮምፒዩተር አለው መሰለኝ አንድ ኮምፒዩተር አለ
- የእናንተ አቀማመጥ እንዴት ነበር ቢሮ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ትልልቅ ኮምፒዩተሮች አሉ ላፕቶፕ አለ ታዛቢዎች መርማሪ ተከሣሹ አለ አቀማመጣችሁ እንዴት ነበር ?
- ማለት እንደዚህ በጣም ብዙ የተጋነነ የተንዛዛ ምናምን አይደለም ያው አንድ ወንበር ሳቡ እና ተቀመጡ ነው የተባልነው ያው እንደውም ተጠርጣሪው እየተንቀሳቀሰ ነበር እንትን ሲል የነበረው ቆመን ሁላ ነበር ለማየት እንደዚህ ጠጋ እያለ
- እርሶ የት ጋር ነበር የተቀመጡት በተጠርጣሪው እና በታዛቢዎቹ መካከል ምን ያህል ርቀት ነበር?
- ተጠርጣሪው ሲንቀሳቀስ ነበር እንደውም ቦታውም አልነበረውም ቢሮ ውስጥ
- ሲንቀሳቀስ ማለት ተነስቶ ሲሄድ ?
- አዎ ማለት ቢሮ ውስጥ ተንቀሳቅሶ ኮምፒዩተሩንም እያየ ምናምን እንትን እያለ ነበር
- ተጠርጣሪው እስቲ አቀማመጡን አሁን ለፍ/ቤቱ ያስረዱ እስቲ ታዛቢዎች አላችሁ 2ታችሁ አንድ ወንበር ላይ ነው የተቀመጣችሁት 2ታችሁ ?

2818

3069

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት ለቢሮው አገልግሎት የሚቀመጡበት ወንበር ላይ ነው አንደኛው እንደውም ፀሐፊ ነገር የምትቀመጥበት ወንበር ላይ እኔም በበሩ በኩል ነው የተቀመጥነው ተጠርጣሪውም አለ
- ይኸውሎት ምስክር አሁን የእዚህ የፍ/ቤቱን አቀማመጥ አይተዋል ጠበቆች በእዚህ በኩል ናቸው ዐቃቤ ሕግ እዚያ አለ ስለዚህ መርማሪ አለ ላፕቶፕ የሚያወጣ ተከሣሽ አለ ታዛቢ አለ ሌላ ኮምፒዩተር ላይ የተቀመጠ አለ አቀማመጣቸው እንዴት ነበር ስንት ጠረቤዛ ነበር እንዴት ነበር የተቀመጣችሁት ?
- ማለት ላፕቶፑ ከእኔ ፊት ለፊት ዳኞች እንዳሉበት ጠረቤዛ አለ እሱ ላይ ተቀምጧል ከእሱ ጀርባ ልክ ዳኞች እንደተቀመጡበት ኮምፒዩተሩን እንትን የሚል የሚያስተካክል ባለሙያ አለ ከእዚያ ከእሱ ጠረቤዛው ጎን ደግሞ ተጠርጣሪው ቆሞ ነበር ጠጋ ብሎ እያየ ነበር ማለት ምንም የተቀመጠውም ነገር የለም ወንበር ነበር በእርግጥ ወንበር እየሳበ እየተቀመጠ ነበር እኛም እንደዚህ እየተጠጋን ነበር ስናይ የነበረው
- እናንተ አሁን የተጠርጣሪውን እና ኮምፒዩተር የሚያስተካክለው ሰውን ነግረውናል ታዛቢዎቹስ ከእነሱ ፊት ለፊት ነበር የተቀመጣችሁት ?
- ታዛቢዎቹ ደግሞ እንደዚህ በጎን ማለት ነው
- ከማን ጎን ?
- ላፕቶፑ ካለበት ጎን
- ስለዚህ ተከሣሹ አለ ከተከሣሹ ቀጥሎ ማን ነው ያለው ?
- ከተከሣሹ በጎን በኩል እኛ አለን በፊት ለፊት በኩል ደግሞ አንድ ባለሙያ አለ ኮምፒዩተር እንትን የሚል ላፕቶፖ ጠረቤዛ ላይ ተቀምጧለች
- ስለዚህ ባለሙያው ነው ላፕቶፑን የሚያንቀሳቅሰው ?
- ማለት ያሳየው ነበር የእሱ ላፕቶፕ መሆኑን ያሳየው ነበር ከእዚያ በኋላ ያው እሱ ነበር ሲከፍት የነበረው
- እሺ ፕሪንት ሆኖ የወጣ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- ፕሪንተሩ የት ጋር ነበር ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፕሪንት ተደርጎ የሚወጣበት ኮምፒዩተሩ ሀርድ ዲስኳ ወጥታ የላፕቶፓ ያው እሱ ባለበት ማለት ሀርድ ዲስኩ ወጥቶ በሌላ ኮምፒዩተር ነበር በሌላ ፕሪንተር ፕሪንት ሲደረግ ነበር
- ፕሪንተሩ የት ጋር ነበር እዚያው አጠገቡ ነው ?
- ዲስክቶፑ የቢሮው ዲስክቶፕ ያለበት ጎን
- ዲስክቶፑ ጋር ?
- አዎ
- ሌላ ኮምፒዩተር ላይ የተቀመጡት ባለሙያዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ኮምፒዩተሩን እዚያ ተቀምጠው አልከፈቱም እንዴ ?
- ላፕቶፑን
- ሌላ ሌሎች ኮምፒዩተሮች ?
- ዲስክቶፑ አልተከፈተም
- ሀርድ ዲስኩ ከምንድን ነበር የተገናኘው ?
- ይመስለኛል ማለት የኮምፒዩተሩ እንትን አለ ሞኒተሯን ምንድን ነው የሚባለው ከእሱ ጋር ተገናኘ ከእዚያ ፕሪንት መደረግ ነው የተጀመረው
- በበድኑ እና ወይም የ2ቱም ተከሳሾች ከእርሶ ጋር የነበረው ታዛቢ አንድ ዓይነት ነው ምስክር ያሉት ?
- አይደለም
- የተለያየ ሰው ነው ?
- አዎ
- አሁን ባልደረባዬ የጠየቀት የፕሪንተሩ ቦታም ተናግረዋል እና ፕሪንት ሲያደርግ የነበረው የኮምፒዩተር ባለሙያው ነው አይደል ?
- የኮምፒዩተር ባለሙያ ይመስለኛል አዎ
- እሱ ነው አይደል ፕሪንት ሲያደርግ የነበረው ?
- ማለት ያው ተጠርጣሪው ነበር ያው ፕሪንት እንደሚደረግ መጀመሪያ ተነግሮታል እያየ ያው ፕሪንት እያደረጉ ያወጡ ነበር እያየን እንፈርም ነበር
- እኮ ያው የኮምፒዩተር ባለሙያው ፕሪንት ሲያደርግ እሱ እያየ ነው አይደል ሲወጣ የነበረው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እነዚህ ፕሪንት እየተደረጉ የሚወጡት እና ሌሎችም ወረቀቶች ክስ ከተመሰረተባቸው በማስረጃነት ይቀርቡባቸዋል ተብሎ ሲነገራቸው አልሰማህም አይደል ?
- ተነግሯቸዋል
- ይሄንን ሰምተሀል አንተ እራስህ ?
- አዎ
- ምን ተብሎ ነው የተነገራቸው ?
- ማለት በፍቃደኝነት ይሄንን ማስረጃ እንደሚሰጡ እና ግን ፍ/ቤት ላይ እንደማስረጃነት እንደሚቀርብ ተነግሯቸዋል
- ማን ነው ይሄንን የነገራቸው ?
- መርማሪው
- ከአንተ ጋር የነበረውም ሰው ሰምቷል ይሄንን ?
- ሰምቷል
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ካለ
- እሺ አቶ ቢኒያም ፕሪንት ሲደረግ የነበረው ሀርድ ዲስኩ ወጥቶ ነው ብለሀል እና እንደዚሁም ከሌላ ገመድ ጋር በገመድ ላፕቶፑ ከሌላ ኮምፒዩተር ጋር ተገናኝቶ ነበር ብለሀል እና እስቲ ይሄንን ነገር አብራራው ?
- አዎ ምናልባት ሀርድዲስኩ ሲወጣ እንዴት ነው ምናምን ብሎ ተጠርጣሪው ጠይቆ ነበር እንዴት እንደዚህ ይሆናል ብሎ ከእዚያ ተግባቡ ያው ነገረው መፍቻ አመጣ ፊት ለፊት ከእዚያ አውጣው ይቺን አገናኝቼአት ነው እንትን የምንለው ሌላ ምንም መጀመሪያ አየው አሳየው ባዶ እንደሆነ ሀርድ ዲስኩ ከመግባቱ በፊት ምንም ዓይነት ሌላ ፋይል እንደሌ አሳየው ኮምፒዩተሩ ላይ ከእዚያ በኋላ
- የማን ሀርድዲስክ ነው ያ ሀርድዲስክ ?
- ከላፕቶፓ የወጣ ሀርድዲስክ ነው ከእዚያ ባዶ መሆኑን አሳየው ከእዚያ ከተግባቡ በኋላ ነው ወጥቶ ፕሪንት መደረግ የጀመረው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ የማን ነው እሱ የማን ነው ከላፕቶፕ የወጣው የማን ላፕቶፕ ነው ?
- የተጠርጣሪው
- የተጠርጣሪው 2 ነው እየመሰከርክ ያለው
- የእሱ
- እሱ ማለት በስም ?
- በድሩ
- ስለዚህ ለምንድን ነው ሀርድዲስኩን ያወጡት ከላፕቶፑ ፕሪንት ማድረግ አልተቻለም እንዴት?
- ምናልባት የሆነ የሲስተም ችግር ይመስለኛል በእዚያ ሰዓት እንደዚያ ተባብለው ተነጋግረዋል
- እንጂ ፕሪንት የተደረገው ከእዚኛው ከላፕቶፕ የወጣው ወይም መጀመሪያ ተጠርጣሪው ወይም አቶ በድሩ ሁሴን ላፕቶፕ ላይ የነበረው ዶክመንት ነው ማለት ነው አይደል ?
- አዎ መጀመሪያ ሀርድዲስኩ ከመገናኙ በፊት ከኮምፒዩተሩ ባዶ መሆኑን አሳይቶ ተግባብተዋል
- እሺ ቅድም በዋና ጥያቄ ስንጠይቆት 2ቱም ተጠርጣሪዎች ወይም 2ቱም ተከሣሾች ከእኔ የተገኘ ነው እያሉ ነበር ሲፈርሙ የነበሩት ብለዋል ?
- አዎ
- በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ሲጠየቁ ይሄ ሰነድ የእኔ አይደለም የሚል በተለይ በድሩ ሁሴን ይሄንን ነገር አንስቷል ብለዋል ላፕቶፑ የማን ላፕቶፕ ነው ያ ?
- የእሱ እንደሆነ ነው የማውቀው
- ማን ነው የከፈተው ላፕቶፑን ላፕቶፑን መጀመሪያ የከፈተው ማን ነው ?
- መጀመሪያ የእሱ ላፕቶፕ መሆኑን ሳይከፈት በፊት እንትን አለ ከእዚያ በፊት ለፊቱ ነው የተከፈተው
- ምንም ፓስዋርድ ምናምን ነበረው ብለውን ነበር መጀመሪያ ላይ ማን ነው ያስገባው ያንን ፓስዋርድ ?
- ተጠርጣሪው ነው
- እራሱ ነው ያስገባው ?
- አዎ

T

3073

2822

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ከራሱ ላፕቶፕ ውስጥ እራሱ ፓስዋርዱን ከፍቶ ካወጣው እንዴት ነው የእኔ አይደለም ሲል የተላከልኝ ነው በኢሜል ተልኮልኝ ኢምቦክስ የተደረገ ነው ወይስ ምን ዓይነት ነበር ሲል ሲያነሳ የነበረው ጥያቄ ?
- አዎ ምናልባት እንደውም የእዚያን ዕለት ኮምፒዩተሯ እራሷ ነች የፈጠረችው ምናምን ተባብለን ተሳስቀን ነበር በእዚያን ሰዓት እንደውም እኔ ይሄንን ነገር አይቼው አላውቅም ከየት እንደመጣ አላውቅም ምናልባት ፈጥራው ይሆናል ኮምፒዩተሯ የሚል ነገርም ነበር የእዚያን ዕለት
- ፓስዋርድ አልነበረውም ኮምፒዩተሩ ?
- ነበረው
- ስለዚህ እንዴት ሊገኝ ቻለ ነው ሲል የነበረው የእኔ አይደለም ሲል ወይም የእኔ አይደለም ባለው ላይ እንዴት ሊፈርም ቻለ ታዲያ ?
- ምናልባት ይሄንን ኮምፒዩተር ሌላ ሰውም ይጠቀምበት ነበር ብሎ ተናግሮ ነበር መሰለኝ በሰዓቱ ከእሱ ሌላ
- ኮምፒዩተሩን ?
- አዎ
- ፖሊስ ጋር ከመያዙ በፊት ማለት ነው ?
- አዎ
- ማን ይጠቀምበታል አለ ?
- ባለቤቴ ያለ ይመስለኛል
- እንጂ ይሄንን ሰነድ ወይም ያ ዶክመንት እዚህ በሌላ አካል ተጨምሮብኝ ነው ወይም እንደዚህ ያለው ነገር ነበር ?
- ብዥታ ነበር የእዚያን ሰዓት
- እስቲ ያብራሩት ያንን ብዥታ ?
- ማለት አዲስ አዲስ ነገሮች አይቼአለሁ እዚህ ላይ የሚል ነገር ነበር
- ማን ነው ያለው ?
- በድሩ

2823 3074

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንብባችሁታል ይሄንን ሰነድ እሱ ይሄ ከእኔ የእኔ አይደለም ወይም አላየሁትም ያለውን ዶክመንት አይታችሁታል?
- ፕሪንት ከመደረጉ በፊት ኮምፒዩተር ላይ እያለፈ ሲታይ ነው እነዚህ እነዚህ ነገሮች አላውቃቸውም ምናምን የማለት ነገር ነበር እንጂ አላነበብንም
- ስንት ገፅ ይሆናል እነዚያ ሰነዶች ?
- ጠቅላላ የፈረምነው ነው
- ኖ እነዚህ አላውቃቸውም ወይም የእኔ አይደሉም ሲላቸው የነበሩ ሰነዶች ስንት ይሆናሉ ?
- አልቆጠርናቸውም በሰዓቱ
- እሺ ሲፈርምስ ይሄንን ነገር ገልፆ ነው የፈረመው ማለት እነዚህን አላውቃቸውም ነገር ግን ከእኔ ላፕቶፕ የተገኙ ናቸው ብሎ ነው የፈረመው እንዴት ብሎ ነው የፈረመው ?
- አይ በሰዓቱ ያው ሁሉም ላይ ሌሎቹ ገፆች ላይ እንደፈረመ አድርጎ ነው የፈረመው ግን ምናልባት ኮምፕሌን እንደሚያቀርብ ግን ሲናገር ነበር ፍ/ቤት ላይ
- ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ
- እስቲ ምንድን ነው ለፍ/ቤት የሚያቀርበው ኮምፕሌን ምንድን ነው ያለው ያኔ ?
- ማለት እነዚህ አዲስ ናቸው ባላቸው ሰነዶች ላይ እንትን እንደሚል ልዩነት ነበረው አይቼአቸው አላውቃቸውም የሚላቸው
- አዲስ ናቸው የሚላቸው ሁሉንም ወይስ ?
- የተወሰኑ ናቸው
- የተወሰኑ ናቸው ?
- አዎ
- በግምት ስንት ይሆናሉ ?
- 10 የሚደርሱ አይመስለኝም
- 10 ገፅ ?
- አዎ
- ከየት መጡ ነው የሚለው ?

2824

3025

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያው ከኮምፒዩተሩ ላይ ነው
- እኮ ከየት ተጨመሩ ወይ አሁን ያኔ አዲስ ናቸው ሲል ምን ማለት ነው ?
- ለእኔም አዲስ ናቸው ነው እያለ ያለው ከየት እንደመጡ አላውቃቸውም ነው የሚለው
- ሌሎቹን አውቃቸዋለሁ ማለት ነው ?
- እንግዲህ ቢሆን ነዋ
- እንደዚያ ነው የተናገረው ?
- አዎ እንደዚያ ተባብለን ነው የተፈረመው
- እሺ የእኔ አይደሉም የተባለው ከወጡ ነው ከመውጣታቸው በፊት ፕሪንት ከመደረጋቸው በፊት ነው ?
- ፕሪንት ከመደረጋቸው በፊት
- በፎልደር ምናልባት ለይተህ ታውቃህ በየትኛው ስም እንደተቀመጠ ?
- አላስታውስም
- በፎልደር ለይተህ አታውቅም ?
- አዎ
- ታዲያ 10 ገፅ ይሆናው ያልከው እነሱ መሆናቸውን እንዳት አወክ ?
- እነዚህ እነዚህን አላውቃቸውም ሲል ዝም ብዬ እያየሁ ነበር
- አላውቃቸውም ያለው ፕሪንት ሳይደረጉ ነው ይስ ከተደረጉ በኋላ ?
- ኮምፒዩተር ላይ
- ኮምፒዩተር ላይ ?
- አዎ
- ታዲያ 10 ገፅ መሆናቸውን እንዴት አወቁ እንደዚያ ከሆነ ?
- ማለት እስክሪኑ ላይ ይመጣል ከእዚያ ያሳልፉታል ይሄንን ይሄንን እየተባለ ነው ሲያልፍ የነበረው
- ከተከፈተ በኋላ ነው በፎልደር እንዳለ ?
- ከተከፈተ በኋላ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከተከፈተ በኋላ ?
- አዎ
- ፕሪንት እንዴት እንደሚደረግ ለይተው ያውቃሉ እርሶ ፕሪንት የሚደረግ እንዴት ከየት የመጣ የትኛው ፕሪንት እንደሆነ ለይተው ያውቃሉ አጠቃቀሙን እርሶ ?
- አልገባኝም
- ማለት ፕሪንት አድርገው ያውቃሉ እርሶ የራስዎን ዶክመንት ?
- አይ አላውቅም
- ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- አሁን ሰዓቱ 5 ተኩል አካባቢ ደርሷል ቅድም ማረፊያ ቤት መቀየር አለ ወደ ሌላ ቦታ አለ የሚል ተከሣሽ ጠበቆች አመልክተው ነበር እቃ መለዋወጥ ከቤተሰብ ጋር መገናኘት ጊዜ ያስፈልገናል ብለው ነበር እና አሁን ከጀመርን ለተባለው ሰዓት መድረስ ስለማንችል አሁን ማረሚያ ቤትም ያው አድርሶ ከሰዓት ግን ልክ 8 ሻርፕ እንድንጀምር 7 ተኩል እንዲደርሱ የአሁኑ በእዚሁ ይበቃናል፡፡

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሰዓት በኋላ ችሎቱን እንቀጥላለን ቀሪው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ይቅረብ ምናልባት ጠዋት ሲሰየም ግንቦት 16 ተብሎ የተሰየመ ይመስለኛል እና ግንቦት 6 /2005 ተብሎ እሱ እንዲታረም ቀሪው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ይቅረብ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ከእዚያ በፊት የቀረ ተከሣሽ አለ የቀረ የለም ሁሉም ቀርቧል ዐቃቤ ሕግ አንድ ቀርቷል አንደ ቀርቧል ከሰዓት በፊት ነበሩ ዐቃቤ ሕግ አንዱ አቶ ብርሃኑ ወ/ማገኝ ቀርቧል በጠበቆች በኩል ከሰዓት የቀረባችሁ አስመዝግቡ
- መሐመድ አብደላ፣ አዲስ መሐመድ፣ ባህሩ መካንጋ ቀርበናል
- ቀርበዋል ለምስክርነት ነው የመጡት እርሶ ?
- አዎ
- እሺ የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ የራስዎን ስም ብቻ ይነግሩናል
- ካሳሁን
- ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ 91ኛው የዐቃቤሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 155 ላይ የተጠቀሱ አቶ ካሳሁን ቀርቧል
- እኔ ያው በ 2 ሰዎች ነው 1ኛው ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን የሚባል እና 2ኛው ሙራድ ሽኩር ጀማል የሚባል
- 2 ሰዎች ?
- አዎ
- ያውቁታል ሰዎቹን ለይተው ?
- አንዱን በእርግጠኝነት አውቃለሁ
- አንዱን ማንን ነው የሚያውቁት ?
- ሙራድ ሽኩር
- ሙራድን መለየት ይችላሉ ?
- አዎ
- ተነስተው ይለዩልን መሀል ላይ ከእዚያ ወደ እኛ ቁጠር እና ስንተኛ ላይ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- 2ኛ
- 2ኛ ላይ እርሶ ኖት ማን ስንተኛ ኖት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ሌላውንስ ማሳየት ትችላለህ
- መሀል ላይ
- ከእዚህ ወደ እዚያ ቁጠር እና ስንተኛ እርሶ ኖት እስቲ ተነሱ ሱልጣን ስንተኛ ኖት ቁጭ በሉ ካሳዩን ሰዎች ጋር ጥላቻ ወይም ዝምድና አሎት ቅሬታ ዝምድና ?
- እኔ ከእዚያ በፊትም አላውቃቸውም ከእዚያ ወዲህ ዛሬ አየዋቸው
- ስለዚህ ዝምድናም ሆነ ቅራኔ ነገር የለም ?
- የለም
- ምስክሩ 10ኛ እና 17ኛ ተከሣሾችን አሳይቷል ምንድን ነው ያዩት እስቲ አጠር አድርገው ከእነሱ ጋር በተያያዘ ስለተከሰሱበት ጉዳይ ወደ ዝርዝር ሳይገቡ ?
- ማለት ከቤት ውስጥ
- አይ እርሶ ያዩት ምንድን ነው ያዩት ምን ሲደረግ ነው ያዩት ?
- አኬ ማለት በመጀመሪያ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ከፖሊሶች ጋር
- ወደ ዝርዝሩ በኋላ እንገባለን ቤት ሲፈተሽ ነው ያዩት ?
- አዎ ቤት ሲፈተሽ ማለት ነው
- የ2ቱም ?
- አዎ
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ካሳሁን አሁን እንዳሉት እስቲ መጀመሪያ ከአቶ ሙራድ ሽኩር እንጀምር እና ቀኑ መቼ ነው ምንድን ነው ያየኸው ሰዓቱን ቀኑን በማስታወስ እስቲ ለተከበረው ፍ/ቤት ያው በዝርዝር እንድትገልፅ ነው የምንጠየቀው ?
- የአቶ ሙራድ ሽኩር ነሐሴ 12 12ኛ ወር 2004 ነው ቅዳሜ ቀን ነው ከ 4 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ባለው ውስጥ ነው
- ቀን ነው ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅዳሜ ቀን
- ቀን ላይ ?
- ቀን ማለት ነው አዎ ያው ከፖሊሶች ጋር ነው አብረን የሄድነው እሱም አብሮ ነበረ አብሮ ያው እጁ ታስሮ ምናምን አብሮ ነው የመጣው ያው የፍ/ቤት ትዕዛዙን በሽብርተኝነት የተጠረጠረ እና ማህተም አለው ቁጥርም አለው ከላይ ያንን ተነበበልን ከበር ነው የተነበበው ከእዚያ ተንኳኳ ባለቤቱ ከፈተችው በሩን ከእዚያ በኋላ ገባን ተንኳኳ በሩ የውጪው በር ማለት ነው አብረን ነው የገባነው ከእዚያ በኋላ ወደ ፍተሻ በምንገባበት ሰዓት ያው በሬት የገባው እራሱ ነው በመቀጠል ፖሊሶችም ማለት ፈታሾቹም እኛም አብረን ገባን ዳይሬክት ወደ ብርበራ ነው የገቡት ወደ ብርበራ ሲገቡ እሱም እኛም ታዛቢዎች በመሆን እኔም እራሴ ማለት ነው ያው አብረን በሚፈተሽበት ቦታ አብረን እየቆምን ነው እየዞርን በየክላሱ ሳሎን መኝታ ቤት በሚፈትሹበት ሰዓት በሚተሸበት ሰዓትም አንድ ዳይቨርት የሆነ ሞባይል እና የተለያዩ በራሪ ወረቀቶች አንድ መፅሐፍ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የት ነው ያለው የሚል 408 ገፅ ያለው አንድ የተጠረዘ መፅሐፍ ማለት ነው እና ያው በቁጥር ባላውቃቸውም ሲዲ እነሱ ናቸው የተገኙት
- ይሄ አሁን ያልክበት ቤት የት አካባቢ ነው የሚገኘው ቦታው ?
- ቦታው ኮልፌ ቀራንዮ ክፍል ከተማ ወረዳ 2 ከወረዳው በስተጀርባ
- አሁን ያልካቸውን በዝርዝር ከተገኙ በኋላ ሲዲዎች ሲዲዎቹ ስለምን እንደሚሉ ይዘታቸውን ለመለየት ችለሀል ሲዲዎች ተገኙ ብለዋል እና ስለ ሲዲው የምታውቀት ነገር አለ ይዘቱ ምን እንደሆነ እዚያ ያያችሁት ነገር አለ ?
- አልታየም ሲዲው ውስጡ ምን እንትን እንዳለው ምን ይዘት እንዳለው ምናምን አልታየም ዳይሬክት ይታያል በማለት ነው ይዘውት የመጡት
- እነኚህ አሁን የገለፁዋቸው ነገሮች ዝርዝር ከተገኙ በኋላ ምንድን ነው ምን አደረጋችሁ መጨረሻ ላይ ማለት ነው ምንድን ነው የተደረገው ?
- ዳይሬክት እነሱ ከተገኙ በኋላ ወደ ውጪ በር ላይ ነው ያወጡት ተሰብስበው ከእዚያ በኋላ እነሱ በሙሉ እየተመዘገቡ በራሪ ወረቀቶች ላይም መፅሐፉ ላይም ታዛቢዎች ፈረምንበት መጨረሻ ላይ ቃለጉባኤው ላይም ተፈረመበት ከእዚያ በኋላ ዳይሬክት ነው የወጣነው

2829 3880

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቅድም ስትገልፁ መሐፎችም እንደዚህ እንደተገኙ ገልፀሀል እና ከእዚህ ከመፅሐፍቶቹ ሌላ የተገኙት የምታስታውሰው ነገር አለ እዚያ ማለት ነው በፍተሻ ?
- አኬ ፍተሻው ላይ ማለት በራሪ ወረቀቶች
- ምን ይላሉ እነሱ በራሪ ወረቀቶቹ ?
- በራሪ ወረቀቶች ድምፃችን ይሰማ ነው የሚለው የተጠረዘው መፅሐፍ ደግሞ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የት ነው ያለው የሚል 408 ገፅ ያለው
- አዎ እነኚህ በራሪ ወረቀቶች አሁን ያልካቸው ለምን የተዘጋጁ ናቸው ምን ዓይነት ናቸው ወረቀቶቹ ምን ዓይነት ናቸው ብዛት አላቸው ?
- አይ ብዛታቸውን ለጊዜው አላስታውሳቸውም ግን የተነጣጠሉ ወረቀቶች ማለት ነው አንዳንድ ለብቻ ለብቻ የተፃፉ
- አይ ስለበራሪ ወረቀቶቹ ስለ በራሪ ወረቀቶቹ ማለቴ ነው በርከት ያሉ ናቸው ብዛት አላቸው ?
- እይ በርከት ያሉ አይደሉም የእዚህን ያህል ብዙ አይደሉም
- እና መጨረሻ ቅድም እንዳልካው ተፈራረምን ነው ያልከው ስለመገኘቱ ምን አደረጋችሁ መጨረሻ ላይ እሳቸው ጋር ማለት ነው ?
- ስለመገኘቱ
- እነኚህ ከብርበራው በኋላ ይሄንን ለማረጋገጥ ምን አደረጋችሁ መጨረሻ ላይ ?
- በቃለ ጉባኤ ምን ምን እንደወጣ በሙሉ ተፃፈ እዚያ የተፃፈበት ወረቀቶች ላይም መፅሐፉ ላይም ታዛቢዎች ፈረምንበት ከተፈረመበት በኋላ ቃለጉባኤው ላይ ፈረምን ዳይሬክት ወጣን ተጫኑ መጣን ማለት ነው እኛም ወደ ወረዳችን ገባን እነሱም ወደ እዚሁ መጡ
- እሺ ወደ የሚቀጥለው ደግሞ እንሂድ ምን አያችሁ ቅድም ያልከው 2ኛው ?
- ሱልጣን ጋር
- አዎ /ግልፅ ያልሆነ/
- ሼህ ሱልጣን ደግሞ ሐምሌ 12/11ኛ ወር ላይ ነው 2004 ላይ እሳቸው ጋር ደግሞ እንደዚሁ የደረስነው ሩብ ጉዳይ ለ 1 ላይ ነው ምሽት ማለት ነው እና ሩብ ጉዳይ ለ 1 ላይ ያው ፖሊሲ ፈትሹ ተብሎ የሆነ ስልክ ሲያነጋግር ምናምን ሰምቼዋለሁ ፈትሹ ተብለናል ነው ያለው የፍ/ቤት ትዕዛዝም አለው እና አብረው ነበር እሱም ያው እጁ ታስሯል አብሮ ነው የገባነው ከበር ላይ

2830 3081

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ተነበበ የፍ/ቤት ትዕዛዙ ዳይሬክት ተንኳኳ እንግዲህ እኔ ባለቤት ትሆን /ግልፅ ያልሆነ/ ትሁን አላውቅም በሩ ተከፈተ ገባን ዳይሬክት ወደ ፍተሻ ነው የገባነው ስንገባ መጀመሪያ እራሱ ነው የገባው ከእዚያ በኋላ አብረን ገባን ፖሊሶች እና ታዛቢዎች ወደ ፍተሻ ነው የገባነው ወደ ፍተሻ ከገባን በኋላም የተገኙ ነገሮች አብዛኛው ጥበቃ ቤት ውስጥ በራሪ ወረቀቶች ናቸው የተገኙት

- ምን የሚሉ ናቸው እነኚህ በራሪ ወረቀቶች ስለ ምን የሚገልፁ ናቸው ይዘታቸው ወረቀቶቹ ?
- እሱ ድምፃችን ይሰማ የሚል በብዛት ጥበቃ ቤት ውስጥ እኛ የጥበቃ ቤቱን ይሁን አላውቅም ግን የጥበቃ ቤት ነው እሱ ያለን ከመስገጃ ወደ ውስጥ የሆነ ክላስ አለ የጥበቃ ቤት ክላስ ነው ያለው እንደገና ከሱፉም ከኪሱም ተገኝቷል ሱፍ ተንጠልጥሏል እዚያው ከመኝታው ጋር ከኪሱም ተገኝቷል
- ምን ይላሉ እስቲ በራሪ ወረቀቶች ከእዚህ
- ድምፃችን ይሰማ የሚል በብዛት
- ሌላስ ሌላ ?
- ሌላ ደግሞ 2 ላፕቶፕ 2 ፍላሽ 63 ሲዲ 50 ካሴት 2 ክብ አንድ 4 ማዕዘን እንትን ማለት ነው መምቻ ማህተም የማህተም መምቻ ማለት ነው እንደገና ጋዜጣ እነሱም እንደዚሁ ድምፃችን ይሰማ የሚል እኔ ደህና አድርገን አላነበብኩትም በብዛትጋዜጣ እነሱ ናቸው እና ደግሞ አንድ የፎቶ ካሜራ
- እነኚህ አሁን የዘረዘርካቸው ከተገኙ በኋላ ምን ተደረገ መጨረሻ ምን አደረጋችሁ ?
- ዳይሬክት እነሱ ከተገኙ በኋላ ያው ሁሉም ተሰብስቦ አንድ ላይ ከተቀመጠ በኋላ ሁሉም ካለቀ በኋላ በር ላይ እዚያው በረንዳ ላይ ከተሰበሰበ በኋላ በቃለ ጉባኤ እየተፃፈ ፈረምንበት ከተፈረመበት በኋላ በራሪ ወረቀቱ ላይም ጋዜጣው ላይም ቃለጉባኤ የያዘበትም ላይም ታዛቢዎች ፈረምንበት ዳይሬክት ወጣን
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- በሙራድ ጉዳይ ላይ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ነበረ በር ላይ ተነቧል ብለኸናል ከመነበቡ ውጪ አንተ አይተኸዋል የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሁን አይሁን አይሰማም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለሚቀረፅ ነው አቶ ካሳሁን ከነበቡ ውጪ አንተ አይተሀል የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሁን አይሁን ?
- ማለት ዳይሬክት ፖሊሶች እንዳገኙን ያው የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዳለው እና ታዛቢ እንድንሆን ነው የጠየቁኝ በሽብር የተጠረጠረ ሰው እንዳለ እዚያ አካባቢ እና
- ጥያቄዬ ገብቶህ ከሆነ በሩ ላይ ልንገባ ስንል ተነበበልን አልክ ከመነበቡ ውጪ የአንተ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሁን አይሁን ወረቀቱን እራስህ በእጅህ ይዘት አይተኸዋል ወይ ነው ?
- አላየሁም
- አላይኸውም ?
- አዎ
- ተነበበልህ እንጂ አላየኸውም ?
- አዎ ተነቧል
- የተነበበው ነገር የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሁን አይሁን እርግጠኛ አይደለህም ስላላየኸው ማለት ነው ?
- እርግጠኛ ነኝ
- በምን እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ ?
- እኔ ይዤ አልይው እንጂ እኮ ሲነበብ አብረን ነው ከእሱ ጋር ሆኜ እያየሁት ያለሁት ማለት ነው ማህተም አለው ቁጥር አለው
- እሺ የትኛው ፍ/ቤት በየትኛው ፍ/ቤት የተሰጠ ትዕዛዝ ይላል ወደ ፍ/ቤቱ እያየህ እኔ የምልህን ጥያቄዬን ትሰማለህ ወደ ፍ/ቤቱ እያየህ ምላሽን ስጥ በየትኛው ፍ/ቤት የተሰጠ ትዕዛዝ ይላል የትኛው ፍ/ቤት ነው እንትኑን የሰጠው የብርበራ ትዕዛዙን ?
- እሱ ያው ለአሁን ረስቼዋለሁ
- አታውቀውም እሱን ?
- አዎ
- የትኛው ዳኛ እንደሰጠም አታውቅም ?
- አዎ
- መቼ ይፈተሽ እንደሚልም አታውቅም ?
- የሚፈተሽማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መቼ ይፈተሽ ይላል ?
- በነሐሴ 12/11ኛ ወር 2004 ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት
- በእዚህ ሰዓት ውስጥ
- ባለው ውስጥ
- በእዚህ ሰዓት ውስጥ ይፈተሽ ብርበራ ይደረግ ይላል ?
- አዎ

- በብርበራው ምን ምን ይያዝ ይላል ምን ምን ይበርበር እና ይያዝ ይላል ?
- እኬ የሚለው የጦር መሣሪያዎች ኤሌክትሮኒክ እቃዎች እና ከሽብርተኞች ጋር ተያያዥነት ያሉት እቃዎች ነው የሚለው
- መፅሐፍ ወይም በራሪ ወረቀት ይያዝ አይልም አይደል ?
- መፅሐፍ ምናምን አይልም
- አይደልም አይደል?
- ከሽብርተኛ ጋር ተያያዥነት ያሉት ነው የሚሉት
- እነዚህ የተያዙ መፅሐፍ ይሁን ሲዲ አንተ ከሽብርተኝነት ጋር ይያያዝ አይያያዝ የምታውቀው ነገር የለም አይደል?
- እሱ ሲዲውንም አላየነውም ዳይሬክት ነው የመጣው አላወኩትም
- አታውቀውም ?
- አዎ
- የአቶ ሙራድ እና የሼህ ሱልጣን ቤት ይበርበር የሚለው ትዕዛዝ አንድ ትዕዛዝ ነው አንድ የፍ/ቤት ትዕዛዝ በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠ ትዕዛዝ ነው ?
- እሱን አላስታውሰውም
- እኮ አሁን የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ላይ የ2ቱ ስም በአንድ ላይ ነው የተጠቀሰው ?
- በአንድ ላይ ሳይሆን በተለያየ ትዕዛዝ ነው የመጣው
- በተለያየ ወረቀት ነው የመጣው ?
- በተለያየ ወረቀት ማለት ነው

ገ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

2833 3084

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም የነገርከን የአቶ ሙራድ ነው የሼህ ሱልጣንስ ምን ይላል ፍ/ቤቱን ታውቀዋለህ የትኛው ፍ/ቤት ?
- አላውቀውም
- አታውቀውም ?
- አዎ
- ምን ይያዝ የሚለውንም አታውቀውም ?
- ምን ይያዝም ማለት ተያያዥነት ያለው አንድ ናቸው ትዕዛዛቸው
- ቅድም ዐቃቤ ሕግ ጠይቀውህ ስታስረዳ በር ላይ የሙራድ ተነበበ ብለህል ?
- አዎ
- የሼህ ሱልጣን በተመለከተ ሲነበብ አላየህም ?
- ተነቧል እንጂ አዎ ተነቧል
- ምክንያቱም ስልክ ደወሉ ነው ያልከው እንጂ ተነበበ የሚል ነገር አልተናገርከም ?
- ሩብ ጉዳይ ለ 1 ጀምሮ እንዲፈተሽ መደረጉን ነው የደወለው
- ይላል አሁን ፍ/ቤቱ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለ 1 ሩብ ጉዳይ ጀምሮ ይፈተሽ ይላል ?
- ያው የፍ/ቤት ትዕዛዙ ከ 12 ሰዓት ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽት 12 ሰዓት ነው የሚለው ግን ከእዚያን ሰዓት ጀምሮ እንዲፈተሽ ነው እሱ ደውሎ የጠየቀው
- እኮ ከፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ውጪ ነው የተፈተሸው ማለት ነው ?
- ያው ደውሎ አረጋግጦ ነው የፈተሸው
- የደወለው ማን ነው ?
- እሱን ያው ስሙን አላውቀውም
- ስሙን አታውቅም የት እንደደወለ ታውቃለህ የምታውቀው ነገር አለ ?
- እኔ አላውቅም የት
- የት እንደደወለ የምታውቀው ነገር የለም ማንን እንዳናገረ የምታውቀው ነገር የለም ማንን ደውሎ እንዳናገረ የምታውቀው ነገር የለም ?
- ያው እሱ እንደደወለ ነው እንጂ ማን ጋር ይደውል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ጋር እንደደወለ አታውቅም ?
- አዎ
- ስለዚህ የት እንደደወለ ወይም ማን ጋር እንደደወለ የማታውቅ ከሆነ ማረጋገጫ ወይም ፍቃድ ይኑረው አይረው አታውቅም ማለት ነው አይደል ?
- የፍ/ቤት ትዕዛዙ ስላለ
- የፍ/ቤቱ ትዕዛዝማ ከቀኑ ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ይፈተሽ ይላል አልከን አሁን ግን እየፈተሹ ያሉት ምሽት ላይ ለ 1 ምናምን ጉዳይ ነው አልከን እና ፍቃድ ከማን እንደሚጠይቅ ስለማታውቅ ፍቃድ በትክክል ይኑር አይኑርም አታውቅም ማለት ነው አይደል?
- እንግዲህ እሱ ስላለ /ግልፅ ያልሆነ/
- እንጃ አታውቅም
- ደውሎ ስለጠየቀ ማለት ነው
- እንጃ የማስፈተሻ ፍቃድ ይኑረው አይኑር አታውቅም ?
- ቆዩ ቆዩ እስቲ ምን አለ እሱ ስላለ የምትለው ?
- ስልኩን የሚለውን እሱ ነው ያዳመጠው እንጂ እኔ አላዳመጥኩም
- አይ ከእዚያ በኋላ ምን አለ ለእናንተ ስልክ የደወለው ?
- በቃ ፈትሹ ተብለናል ዳይሬክት እንግባ እንፈትሻለን
- እንደዚያ አለ እንጂ እንደዚያ አለ እንጂ አንተ
- በቃ ከእዚህ በኋላ ያለውን ኮንኩሊዥን ተው
- ይቅር
- ግልፅ እኮ ነው ከእዚያ በኋላ ያለው ኮንኩሊዥን
- እሺ ጨርሻለሁ
- ካሴቶች እና ሲዲዎች ተይዘዋል ብለሀል ከሼህ ሱልጣን ቤት በዝርዝር እየተከፈቱ ታይተዋል ?
- አላየንም
- አላያችዋቸውም እነዚህ ካሴቶቹ የልጆች ካሴት ናቸው የዳዋ ካሴት ነው ሲሉ ነበር አይደል ሼህ ሱልጣን ካሴቶቹ የልጆች ካሴት ናቸው የእኔ አይደሉም እያሉ ነበር አልሰማህም ይሄንን ሲሉ አንተ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን የእዚያን ቀን
- ካሴቶቹ ሲያዙ ሲዲዎቹን በዝርዝር አላያችሁም እየከፈታችሁ አላያችሁም አይደል ?
- ያው ሲዲ መሆናቸውን ነው እንጂ ቴሌቭዥን እያስገባን ምናምን አላየንም
- ውስጡ ምን ይኑረው አይኑረው አላያችሁም እሱን ?
- አላየንም
- ግን እነዚህ ካሴቶች እኮ የልጆች ናቸው የእኔ አይደሉም እያሉ ሲሉ ነበር ይሄንን አልሰማህም አንተ ?
- አልሰማሁም
- እሺ የተያዙት የተገኙት ወረቀቶች ላይ ሲፅፍ የነበረ ማን ነበር ጥያቄዬ እየተሰማህ አይደለም ወይ እናንተ የምትፈርሙበት የተገኘ ያልከኝ ወረቀት አለ አይደል ሲፅፍበት የነበረ እላዩ ላይ ማን ነበር ?
- የራሳቸው ልጅ ሲፅፍ ነበር
- ምን እያለ ሲፍፅፍ ነበር ?
- በአማርኛ መፃፍ አልችልም ብለው እሳቸው በአረብኛ እችላለሁ በአማርኛ ግን አልችልም ብለው የእሳቸው ልጅ በአማርኛ ሲፅፍ ነበር
- ምን እያለ ሲፅም ነበር ?
- ከቤት መገኘቱን
- ከቤት መገኘቱን ሲፅፍ ነበር ?
- የእሳቸው ማለት ማን ናቸው ?
- የሼህ ሱልጣን ማለት ነው
- እሺ ላፕቶፑ የእኔ አይደለም የልጄ ነው እንደውም መከፈት አልችልም እያሉ ነበር አይደል ?
- እኔ አልሰማሁም
- አልሰማህም ይሄንን ?
- አዎ
- ፍተሻው ስንት ሰዓት አለቀ ?

2836 3087

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ማለት ጠቅላላ ጨርሰን የወጣነው 5 ሰዓት ነው
- 5 ሰዓት ከምሽቱ ማለት ነው ?
- ከግቢ የወጣነው ማለት ነው
- ከግቢ የወጣችሁት ?
- እንግዲህ ፈርመን ምናምን ከቤት እንደወጣን ሰዓት አላየሁም ግን ጠቅላላ ጨርሰን የወጣነው 5 ሰዓት ነው
- ድምፃችን ይሰማ የሚለው ወረቀት ላይ ወረቀቱ እላዩ ላይ ነው የፈረማችሁት ወይስ ድምፃችን ይሰማ የሚባል ወረቀት ተገኝቷል ተብሎ ቃለጉባኤው ላይ ነው የፈረማችሁት የትኛው ላይ ነው?
- ማለት ቃለጉባኤ ላይም አለ እንትን ላይም ፈርመናል ከታች ላይ ማለት ነው በራሪ አንዳንድ ገፅ ወረቀት ስለሆነች ሁሉ ላይ ፈርመናል
- እኮ የሙራድም የሼህ ሱልጣን ላይ ነው እንደዚያ የፈረማችሁ የነበረው ?
- አዎ
- 2ቱም ላይ ነው ?
- አዎ
- 2ቱም ቤት በእዚያ አግባብ ነው የፈረማችሁት ?
- አዎ በእዚያ አግባብ ከታች ማለት ነው
- እኮ ወረቀቱም ላይ ቃለጉባኤው ላይ በእዚያ አግባብ 2ቱም ላይ
- አዎ
- ከሙራድ እንጀምር እና ቅድም በር ላይ ባለቤት ከፍታለች ብለው ነግረውናል ሌላ ሰው ነበር እንዴ እቤት ውስጥ ?
- ሕፃን ልጅ አሉ የራሱ ልጅ ማለት ነው
- ብርበራው ሲካሄድ የት ሆኑ እነዚህ አሁን ሕፃኑ እና ያቺ ባለቤት ነች ያሏት ሴት ?
- እቤት አብራ ነበረች
- አብሯ ትዞር ነበር ከእናንተ ጋር ?
- ማለት ያው ሳሎን ቆማ ነበር እንደኛ ግን ውስጥ ምናምን ምናምን አትገባም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፖሊሶቹ ስንት ፖሊስ ነበር ከእርሶ ጋር ታዛቢ 2 ነበራችሁ ?
- ታዛቢ 2
- ፖሊሶችስ ?
- ፖሊሶች
- ቤት ውስጥ የገቡት ?
- ቤት ውስጥ የገቡት 2
- 2 ፖሊሶች ?
- አዎ
- ቤት ውስጥ ሲገቡ ምን ይዘው ነበር ፖሊሶቹ ?
- ምንም አልያዙም
- ባዶ እጃቸውን ነበር ?
- አዎ
- ቢያንስ ወረቀት ይዘው ነበር የፍ/ቤቱን ?
- የፍ/ቤት ወረቀትም ይዘዋል
- በእጃቸው ወረቀቱን ብቻ ነበር የያዙት ሌላ ማስታወሻ ነገር ?
- ማለት አብረው የሆነ መስመር ያለው ወረቀት በኋላ የተፈራረምንበትን ወረቀት ይዘዋል
- ከ2ቱ ውጪ ሌላ ሰው አልገባም ፖሊስ ?
- አልገባም
- ጥሩ እቃው ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ቪዲዮ አልቀረፁም እንዴ በቪዲዮ አልተቀረፀም ?
- ተሰብስቦ ተቀርፆዋል አንድ ላይ
- ቤት ውስጥ አይደል ሳሎን ?
- ቤት ውስጥ ሳይሆን በረንዳ ላይ
- በረንዳ ላይ ተቀረፀ ?
- ቃለ ጉባኤ እየያዝን የፈረምንበት ቦታ ላይ ተሰብስቦ ተቀርፆዋል
- ጥሩ ሲቀረፅ ማን ነው አብሮ የተቀረፀው ተከሣሹ ?

2838 3089

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሙራድ
- ሙራድ ብቻውን ነው የተቀረፀው ከእቃው ጋር ?
- አዎ
- እኮ ቅድም ምንም አልያዙም ነበር ብለሀል ስለዚህ ቢያንስ ቪዲዮ በቦርሳ ነገር ይዘው ነበር ማለት ነው ሲገቡ አይደል ፖሊሶቹ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ግልፅ አይደለም ?
- አይ ግልፅ ነው እኮ በረንዳ ላይ ቀርፆታል የቀረፁትም የወጣውን ወረቀት ሲዲ እና እራሱን /ግልፅ ያልሆነ/ አድርጎ ጨምረው የቀረፁት
- ጥያቄው መጀመሪያ ምንም አልያዙም ከወረቀት ውጪ ብለሀል እና ቢያንስ ቪዲዮ ይዘው እቤት ውስጥ አልገቡም ወይ የሚለው ነው ጥያቄው ?
- እንግዲህ እኔ በኋላ ነው አውጥተው ሲቀርፁ ያየዋቸው ቀኑም ረዘም ስላለ
- ማለት እርሶ አሁን ታዛቢ ስለሆኑ ቦርሳ ወደ ኋላ ማስታወስም እኮ ይችላሉ ፖሊሶች ሲሄዱ
- ቦርሳ አልያዙም
- ስለዚህ ቪዲዮ ከየት መጣ ከቤት ውስጥ የተገኘ ነው ?
- ትንሽዋ ካሜራ ነች ትንሽዋ ካሜራ ነች እንግዲህ በኪሱ ምናምን ይመስለኛል የያዘው በኋላ ነው ሲቀርፁ ያየዋቸው እንጂ መጀመሪያ ወረቀት ነው በእጃቸው የያዙት ስንገባ ማለት ነው
- እነዚህ ላፕቶፕ እሺ ወደ አቶ ሀጂ ሱልጣን ቤት እንሂድ እና እዚያ ስትገቡስ በር ላይ ማን ነበር?
- በር ላይ ማንም የለም
- ማን ነው የከፈተላችሁ ?
- ስናንኳኳ ብቻ ነው የተከፈተው እንጂ
- ማን ከፈተ ወንድ ነው ሴት ነው የከፈተው ?
- ሴት ነች የከፈተችው
- ውስጥ ስትገቡስ ቤት ውስጥ ሰው አልነበረም ?
- ብዙ ልጆች አሉ

2839 3D9D

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነዚህ ብርበራው ሲካሄድ የት ሄዱ ?
- ለብቻ ነው አንድ ላይ ሰብስብ ብለው ወደ በር ላይ የቆሙት
- ከቤት ወጡ ማለት ነው ቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎች ሁሉም ወደ ውጪ ወጡ ?
- ኧረ እቤት ስንገባ እኛ ሰው አላገኘንም ከወደዚያ ወጥተው እዚያው እራሳቸው አንድ ቤት አንዴ ሰብስብ ይላሉ ግን እንደኛ ወደ ክላስ እንደኛ አይዞሩም አብረው
- እሺ እዚያ ስትገቡ ስንት ፖሊሶች ነው እቤት ውስጥ የገቡት ?
- ከእኛ ጋር 6 4 ፖሊሶች እና 4 ፈታሾች 2 ታዛቢዎች 6
- ምን ይዘው ነበር ፖሊሶቹ ?
- ማለት የፍ/ቤት ትዕዛዝ እና መፈራረሚያ ወረቀት በኋላ የተፈራረምንበትን ይዘዋል
- ሌላ ቦርሳ ነገር አልያዙም ነበር ?
- ሌላ አልያዙም
- እሺ እዚያስ አልተቀረፀም?
- አልተቀረፀም
- እዚያ ላፕቶፕ ተገኝቷል ብለውናል ላፕቶፑን አሸጋችሁት እንዴ በፕላስተር ወይም ተፈራርማችሁ ?
- አልታሸገም
- አልታሸገም ?
- አዎ
- ፍላሹም አልታሸገም አይደል ?
- አልታሸገም
- ሲዲ ያሉን እላዩ ላይ የታተመበት ነገር ለምሳሌ የሚሸጥ ገበያ ላይ ያሳታሚው እንደዚህ ነገር አልታተመበትም እንዴ ሲዲው ?
- ማህተም የለውም
- ማህተም ስሎት የሲዲ አሁን ገበያ ላይ ሲዲ ገዝተው ያውቃሉ ?
- እሽግ አለው ልብስ ማለት ነው

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሲዲው ላይ የሆነ ስዕል ነገር ማን እንዳዘጋጀው የሚገልፅ ነገር ፎቶ ነገር ስዕል ነገር አለው ?
- እኮ ስዕል አለው እኔ ስዕሉ ምን ዓይነት ብቻ እሽግ እንደዚህ የለበሰ ነው የተበታተነም አለ ልብስ የሌለው ማለት ነው በድምር 63 ሲዲ መውጣቱን ነው ልብስም አለው ልብስ የሌለውም አለው
- ጥሩ ጋዜጦቹ ቅድም መፅሐፍ ያሉትም የታተመ መፅሐፍ ነው አይደል ሙራድ ቤት የተገኘው መፅሐፍ ?
- ማለት የታተመ ማለት አንድ ላይ የተጠረዘ ነው
- የተጠረዘ ?
- አዎ
- ደራሲ ያለው አዘጋጅ ያለው የሚገልፅ ነገር ?
- ዳይሬክት እንደዚህ
- እኮ መፅሐፉን አሁን የውጪ ሽፋኑን ስታዩት ገበያ ላይ ሊሸጥ የሚችል አይደል እንዴ አዘጋጅ ያለው አሳታሚ ያለው ?
- አዎ
- በብርበራ ወቅት እቃዎቹን የት የት አካባቢ ነው ቤት ውስጥ ያገኛችሁት ከሙራድ ብንጀምር ?
- ሙራድ ላይ ሳሎን ላይ እና መኝታ ክፍል
- ምን መደርደሪያ ላይ የመፅሐፍ መደርደሪያ የት የት ቦታ ?
- ማለት ሳሎን እና መኝታ ክፍል ላይ ነው አብኛው የተገኙት ይሄንን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አለ ግን የት እንዳለ አሁን
- እሺ የሀጂ ሱልጣንስ የት የት ጋር ተገኘ ?
- እሱ አብዛኛው ጥበቃ የጥበቃ ማደሪያ ነው ያለው ከእዚያ በራሪ ወረቀቶች አብዛኛው እሱ እና አንድ ሴት ልጁ መተኛ ክፍል በራሪ ወረቀቶች ማለት ነው በብዛት የተገኘ ግን ጥበቃ ቤት ውስጥ እና ሱፉ ኪስ ውስጥ
- በሞራድም ሆነ በሀጂ ሱልጣን ቤት ጣሪያ ቀዳችሁ ያወጣችሁት ነገር አለ በጣሪያ ተቀዶ የወጣ እቃ አለ ?
- የለም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መሬት ተቆፍሮስ የወጣ ነገር አለ ?
- የለም
- ሀጂ ሱልጣን ቤት ሲፈተሽ ጥበቃ ቤት ነው የተገኘው ጥበቃውን አገኛችሁት በወቅቱ አናገራችሁት ?
- በወቅቱ የሉም እነሱ በኋላ ነው የመጡት
- እነ ማን ?
- በኋላ 1ኛ አንድ መጣ እንጂ በሰዓቱ የለም ነበር
- እሺ እና ጥበቃው አልነበረም በወቅቱ ?
- በኋላ ልንወጣ ስንል ጨርሰን ልንወጣ ስልን ነው መስኪድ ሄዷል ምናምን ነገር ተብሎ ልንወጣ ስንል ነው የመጣው
- ከሀጂ ሱልጣን ጋር የታሰረ ሰው ነበር አይደል አብሮ ፖሊሶቹ ይዘውት የመጡት የነበረ ሰው ነበረ ?
- ቆይ ቆይ እሱን እለፊ እና ሌላ
- የተከበረው ፍ/ቤት ማለት አብሮ የመጣ ሰው ነበረ አልነበረም ፍተሻው ላይ ስለነበረ
- እሱ ከሀጂ ሱልጣን ጋር የታሰረው ሰው ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ እሱ ይታለፍ
- ለእኛ ግን ጠቃሚ ስለሆነ ነው እያነሳሁት ያለሁት ከሀጂ ሱልጣን ውጪ ማን ነበረ እሺ ጥያቄውን አስተካክዬዋለሁ ከሀጂ ሱልጣን ውጪ ፖሊሶቹ ይዘዋቸው ከመጡት አብሮ የነበረ ?
- ይሄም ያው ነው ሌላ ጥያቄ
- ፈተሾ የእኔ ነው ያለህ ግለሰብ ነበረ አልነበረም ?
- የለም ማንም የለም
- ጥበቃው መስኪድ ሄዶ ነበር አልክ ሲመጣ ምን አለ ይሄ ወረቀት የእኔ ነው አላለም ?
- ምንም እላለም
- አልጠየቃችሁትም ጠየቁት ፖሊሶቹ ወይስ ?
- እንግዲህ እኛ ፊት አልተጠየቀም እኛ ፊት አልተጠየቀም ታዛቢ ፊት አልተጠየቀም
- ከግቢ ከወጣችሁ ነው ግቢ ውስጥ ነው ያገኛችሁት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ግቢ ውስጥ ነው ማለት እኛ እየፈረምን እያለ ነው ልጁ የመጣው ከእዚያ በኋላ እኛ እየፈረምን ነበር ይጠይቁት አይጠይቁት እኔ አላየሁም
- ስትገቡ እቤት ውስጥም ሆነ ግቢ ውስጥ ስትገቡ ከሀጂ ሱልጣን ዉጪ ሌላ የገባ ሰው አልነበረም አብሯችሁ ?
- ፖሊሶች አሉ ፈታሾች
- ከፖሊሶች ውጪ ?
- ከእዚያን ውጪ ማንም የለም
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ካለ
- ድጋሚ የለንም
- ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- አዎ
- ስምዎን የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ የራስዎን ብቻ ?
- ሽመልስ
- ዐቃቤ ሕግ ስንተኛ ላይ የተጠቀሱ ናቸው 8ኛ 92ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 8ኛ ላይ የተጠቀሱ አቶ ሽመልስ ቀርበዋል
- ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- በአቡበከር እና በሰይድ አሊ እና አህመዲን ጀባል
- አቡበከር እና ?
- ሰይድ አሊ
- እሺ ሌላ አለ ?
- አህመዲን ጀባል
- እሺ ሌላ ?
- በቃ 3

http://ethcriminalawnetwork.com/

- 3 ሰው ላይ ?
- አዎ
- ሰዎቹን መለየት ይችላሉ በአካል ለይተው ማሳየት ይችላሉ አሁን ?
- በጊዜው ሲያስተዋውቁ ብቻ ነው መስኪድ ውስጥ ያየዋቸው
- ስለዚህ በአካል መለየት ይችላሉ አይችሉም ?
- ብዙም ላላውቀው እችላለሁ
- በአካል ላይለዩ ይችላሉ ?
- አዎ
- እሺ ስንት ቀን ነው ያዩዋቸው ?
- ማን ነው ሱማሌ ተራ ተብሎ በሚጠራው ቤኒ መስኪድ ጋር
- ምን ያህል ጊዜ አዩት ለስንት ጊዜ ?
- ለአንድ ቀን ብቻ
- አንድ ቀን ብቻ ?
- አዎ
- ስለዚህ መለየት ይችላሉ አይችሉም ?
- የተወሰነ እችላለሁ ግን ብሞክር እችላለሁ
- በመሞከር ?
- አዎ
- እስቲ ተነስተው ይሞክሩ 1ኛ እሺ ሰይድ አሊ ስንተኛ ኖት 16ኛ እሺ ምስክሩ 1ኛ ተከሣሽ እና 16ኛ ተከሣሽን ጠቁሞ አሳይቷል ቀሪው ቅድም በስም የጠቀሱትን መለየት አልችልም ብለዋል ከእነኚህ ሰዎች ጋር ከአንድ ቀን መተያየት ውጪ አትተዋወቁም አይደል ?
- አዎ
- እሺ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እስቲ አሁን ቅድም ያልካቸውን ሰዎች ያው እንደምታውቅ ገልፀሀል እና የት ቦታ መቼ ምን ሲሰሩ የት ቦታ ከእነ ቦታው በማስታወስ በዝርዝር እንድትገልፅ ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የምንጠይቀው እና እስቲ መጀመሪያ አቶ አህመዲንን የት ነው አህመዲን ጀባል እና አቡበከር መቀጠል ትችላለህ ቦታ ጊዜ ሰዓት ?

- እሺ አመሰግናለሁ በመጀመሪያ እዚያ ቤኒ መስኪድ ተብሎ በሚጠራው ወይም ኑር መስኪድ ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ የሆነ ፕሮግራም ነበረ ቤኒ መስኪድ ተብሎ በሚጠራው ወይ ኑር መስኪድ በሚባለው እዚያ አካባቢ ያው እኔ ሙስሊም ስለሆንኩኝ የሆነ ፕሮግራም አለ ምናምን ሲሉኝ እዚያ ገባሁኝ ስገባ እሺ እዚያ ፕሮግራም አለ ተባለ ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ ነው እዚያ ገባሁ ስገባ መድረክ የሚመሩት አሁን የጠቀስኳቸው ሰዎች በጊዜው ነበሩ ቦታው ላይ ስማቸውን እና በጊዜው መድረክ ላይ እነሱ ወጥተው ስማቸውን እያስተዋወቁ የሆነ መልዕክቶችን ሲያስተላለፉ ነበሩ በመጀመሪያ አቡበከር የተባለው ወጥቶ ምርጫችን በመስኪዳችን እንደሆነ ነው የሚለው ምርጫችን በመስኪዳችን መሆን አለበት ምርጫችን በመስኪዳችን እንዳሆን መንግስት ፈቅዶልናል መጅሊስ የተባለው አይወክለንም መጅሊስ አይወክለንም ከእዚያ እንደገና ያው ዲናችንን አልህበሽ በሚባለው /ግልፅ ያልሆነ/ በሚባለው ስንት የደከምንበትን በእኛ ደግሞ አሳልፈን ልንስጥ አንችልም የሚሉ ጥያቄዎች እና ደግሞ ለእዚሁም ደግሞ እኛ ወደ ኋላ ማለት የለብንም እስከመጨረሻ ድረስ መታገል እንዳለብን /ግልፅ ያልሆነ/ ሲያስተላልፍ ነበረ
- ማለት እስከ መጨረሻው ትግላችንን ማለት ምን ማለት ነው ምን ነበር ስለዚህ ሲያብራራ ሰምተሀል ?
- አዎ እስከ መጨረሻ ትግላችን እንደሚቀጥል መስዋትነት ድረስ የሚለውን ሲናገሩ ነበረ በመቀጠልም ሰይድ የተባሉት እሱም መጅሊስ አይወክለንም በመጅሊስ አንመራም መጅሊስ አይመራንም ከአሁን በላይ እኛ መምራት እንዳለብን እና ትግላችን እንደሚቀጥል የሚለውን መልዕክት በ2ኛነት ያስተላለፈ አህመዲን ጀባልም የተባሉት በ3ኛ ደረጃ ላይ እሳቸውም ዕድል ተሰጥቷቸው እንትን ሲሉ ምርጫችን በመስኪዳችን ምርጫችን በመስኪዳችን መሆን እንዳለበት እና
- ማን ነው 3ኛ ደረጃ ላይ ያሉት ?
- አህመዲን ጀባል
- እሺ ቀጥሉ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምርጫችን በመስኪዳችን ከአሁን በላይ በመስኪዳችን ምርጫችን መርጠን ከአሁን በላይ የምንመራው እኛ ነን መጅሊስ አይወክለንም መጅሊስ አይመራንም የምንመራው እኛ ነን የሚሉትን ነጥቦች እየጠቀሱ መልዕክቱን ሲያስተላልፉ ነበር
- መልዕክቱን ያስተላልፉ የነበሩት በምንድን ነው ማለት ለማን ነው በምን ነበር እንዴት ነበር የሚገልፁት ?
- በጊዜው ያው /ግልፅ ያልሆነ/ የፕሮግራሙ ተካፋይ ነበረ ለአዚያ ለሕብረተሰቡ ነው ማይክ ላለ /ግልፅ ያልሆነ
- ቅድም ሲገልፁ እስከመጨረሻው መሰዋትነት ይሉ ነበር እና በመሰዋትነት ምንድን ነው የምናደርገው አሉ ?
- እንታገላለን ትግላችን እንቀጥላለን
- እኮ መስዋትነቱ በምንድን ነው የሚገለፀው ሲገልፁት ማለት ነው እነሱ ያሉትን ማለቴ ነው ?
- ያው ትግላችን ይቀጥላል እስከ መስዋት ያው ድረስ እራሳችን መስዋትነት እንከፍላለን
- ይሄ ቦታው የት ነበር ?
- ቤኒ መስኪድ አካባቢው /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀኑስ ?
- በሐምሌ 1
- ዓ.ምቱ ?
- 2004
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- መስቀለኛ ጥያቄ ካለ በጠበቆች
- አቶ ሽመልስ ቤኒ ወይም ኑር መስኪድ ያሉት የት እንደሚገኝ እስቲ ለፍ/ቤቱ ይንገሩልን የት ነው የሚገኘው ?
- እንደገና
- የት ነው የሚገኘው ?
- ቤኒ መስኪድ ሱማሌ ተራ አካባቢ ያው ኑር መስኪድ የሚባለው 01/02 ቀበሌ ሱማሌ ተራ አካባቢ

2846 3097

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄንን ንግግር አደረጉ ያሉት ቀኑ መቼ ነው ?
- ሐምሌ 1 ቀን
- ሐምሌ ?
- 1 ቀን 2004
- ከእነሱ ውጪ ንግግር ያደረገ ሰው አለ ?
- ነበረ ግን ለጊዜው የማስታውሳቸው እነሱን ስለነበር እንጂ ሌሎችም ነበሩ
- ምን አሉ ?
- ሌሎቹም ነበሩ በጊዜው እነሱን የማስታውሳቸው እነሱን
- አሁን በፍ/ቤቱ እንዲለዩ ሲጠየቁ አህመዲን ጀባልን መለየት አልቻሉም የእዚያን ጊዜ የተናገረው እሱ ይሁን አይሁን በምን ሊያውቁ ይችላሉ ?
- ጊዜ ላለመውሰድ ነው እንጂ ልለየው እችል ይሁን ይሆናል
- እኮ የእዚያን ጊዜ የተናገረው እሱ ይሁን አይሁን በምን ያውቃሉ ?
- አሁንም ቢሆን ላውቀው እችላለሁ ጊዜ እንትን ላለማለት እና ብዙ
- አሁን እየጠየኮት ያለሁት ስለአሁን ሳይሆን የእዚያን ጊዜ ከ 1ጊዜ ውጪ አይቼው አላውቅም ሌሎችንም አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያየዋቸው የእዚያን ቀን ብቻ ነው ያየዋቸው እያሉን ነው ስለዚህ እሱ አይሁን አህመዲን ይሁን ሌላ ሰው ይሁን በምን ያውቃሉ ነው ?
- በሰዓቱ እሱን ሁሉንም ቢሆን የእዚያን ሰዓት
- ከእዚያ ቀን ውጪ ያውቋቸዋል ?
- አላውቃቸውም
- እኮ በምን አወቁ አሁን ያሏቸውን ሰዎች ከነገሮት እነሱ ስማቸው ተነግሮት ነው የመጡት ወይስ በምን አወቁ ?
- ፊዚካል ስለማውቃቸው ብቻ ፊዚካል ስለማውቃቸው ብቻ ነው
- እኮ ከአንድ ቀን ውጪ ግን አላውቃቸውም ብለው መስክረዋል ከአንድ ቀን ውጪ አላየዋቸውም ብለዋል ?

3098

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ ጥያቄው አጠር ይበል እና አህመዲን ጀባል የሚባል ሰው እንዴት አወክ ነው ስሙንስ እንዴት አወክ ነው ?
- በአካል እዚያ ቦታው ስለነበር
- ቅድም ፍ/ቤቱ ሲጠይቆት ከ 1 ቀን ውጪ አላየዋቸውም አላውቃቸውም ብለዋል ይሄ ትክክል ነው አይደል ?
- ትክክል ከእዚያ በፊት አይቼአቸው አላውቅም ለ 1 ቀን ብቻ ነው ያየዋቸው
- መጀመሪያ የተናገረው ማን ነው ከ3ቱ ?
- ያው አበቡከር ናቸው የተናገሩት
- 1ኛ 2ኛ 3ኛ ብለው እስቲ ይንገሩን ?
- አቡበከር 1ኛ ተናገረ
- 1ኛ እሱ ተናገረ ?
- ሰይድ አለ ሌሎችም የተናገሩ አለ በመስረቱ ግን
- አሁን እኔ የጠየኮት ቅድም ስለሌሎቹ ስጠይቆት አላውቃቸው ብለዋል እሱን ተውኩት ስለሚያውቋቸው ሰዎች ስጠይቆት 1ኛ 2ኛ 3ኛ እሱ ተናገረ የሚለውን እስቲ በቅደም ተከተል አስቀምጡልኝ ?
- አቡበከር 1ኛ ተናገረ 2ኛ ሰይድ አሊ 3ኛ አህመዲን ጀባል
- እየመጡ ሲናገሩ ዝም ብለው እየተነሱ ሄደው የሚናገሩት ?
- አይ እነሱ ፕሮግራሙን መሪ አላቸው አቡበከር አለ አቡበከር እከሌ እንደገና ፕሮግራሙን
- አቡበከር ነው ፕሮግራሙን እየመራ እከሌ ይምጣ እከሌ ይምጣ እያለ የነበረው ?
- አዎ ተነስቶ እሱ ይሄንን ዱዋ ይሰጣችዋል እንደዚህ ያደርግላችዋል ብሎ እሳቸው ሲናገሩ ነበር
- እርሶ ፕሮግራሙ እስከሚያልቅ እስከመጨረሻው እዚያው ነበሩ ?
- ትክክል አዎ
- ከንግግር ውጪ ሌላ ምንም ነገር አልነበረም አይደል ንግግር ብቻ ነው ?
- ትክክል

2848 3099

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ዐቃቤ ሕግ እስከ መስዋትነት የሚለው ምን ማለት ነው ሲሎት የምችለውን ጥረት ማድረግ ማለት ነው አይደል መስዋትነት ማለት አንድ ነገር ለማሳካት የምችለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ማለት ነው አይደል ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ነው ካሉ ነው አይደለም ካሉ አይደለም
- ኦፒኒየኑን ይለፉት እና /ግልፅ ያልሆነ/
- ጥረት አደርጋለሁ ማለታቸው ነው አይደል ጥረት እናደርጋለን ማለታቸው ነው ?
- እለፍ የተባለው ይሄ ኦፒኒየን ነው የጠየቁት እና ሙያ ምስክር አይደለም ያዩትን ነው እና መጠየቅ የፈለጉትን ፍሬ ነገሮች
- እሺ ምርጫችን በመስኪዳችን ሲሉ ነበረ ብለዋል አይደል ?
- ትክክል
- እና ምርጫ መስኪድ ውስጥ ተደረገ እንዴ ?
- መጨረሻ ላይ ያው የትምህርት ሁኔታ ነው እንጂ ያው የትምህርቱ ሁኔታ ሲሰጡ የነበረው ምርጫ መካሄድ አለበት በመስኪዳችን ነው እንጂ በቀበሌ ወጥተን አይደለም የሚለውን ሃሳብ ሲያስተላልፉ ስለነበር ነው
- እህ በቀበሌ ሳይሆን ምርጫ በመስኪድ ይካሄድ አሉ በቀበሌ የሚላክ አልነበረም ምርጫ ቀበሌ ይካሄድ የሚል አካል ነበር ማለት ነው ?
- የእነሱ ትምህርት ነው እንደዚህ ስለተባለ ግን ምርጫችን መሆን ያለበት
- እሺ እርሶ ሙስሊም ነኝ ብለዋል ሲጀምሩ ምርጫው የት ተደረገ መስኪድ ነው የተደረገው ቀበሌ ነው ?
- ቀበሌ ነው
- ቀበሌ ነው የተደረገው ከእዚህ ውጪ በእዚህ ቀን የተፈጠረ ረብሻ ምናምን አልነበረም አይደል ንግግር ብቻ ተደርጎ ነው ሰው የተለያየው
- ያው የእዚያን ቀን ይሄንን መልዕክት ተላለፈ ከእዚያ ወዲያ ያው
- እርሶ አሁን በእዚህ ቀን ስላዩት ነገር ነው እየጠየቅኖት ያሉት ንግግር ተደረገ ሰው ወደ የቤቱ ሄደ አይደል በሰላም ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- በእዚህ ንግግር ምክንያት ምንም የተፈጠረ ረብሻ ግርግር የለም አይደል ?
- አልነበረም
- አቶ ሽመልስ እነዚህ ቅድም የጠቀሷቸው ተከሣሾች ሲናገሩ የሚቀርፃቸው ነበር አይደል ይቀረፁ ነበር ?
- የሚቀርፃቸው ያው የራሳቸው መስኪድ ውስጥ ያለ ሞባይል ምናምን ነው እንጂ ሌላ ነገር የለም እራሱ ግን ያው ዝም ብሎ ማንኛውም እዚያ ውስጥ የነበረው በራሱ ሞባይሉ ሲቀርፅ ነበር
- በሞባይል ይቀረፁ ነበር ?
- እራሱ ውስጥ ያሉት
- እኮ ውስጥ ያለው ሰው ነው የምልህ ውስጥ ያለው ሰው ሞባይሉን እያወጣ ንግግራቸውን ይቀፅር ነበር ?
- ንግግራቸውን ይሁን አይዶኖ ሞባይል ብቻ አይቼአለሁ ከእዚያን ውጪ ምን እንደቀረፀ አላውቅም
- ዕለቱ ምን አየሩ እንዴት ነበር ሐምሌ 1/2004 በኔ መስኪድ ያሉት ቦታ ዳመና ነበር ዝናብ ፀሀይ?
- ያው በጊዜው ፀሀይ ነው ጠዋት ከ 4 ሰዓት ጀምሮ ነበር ፕሮግራሙ ምንም ዓይነት ዝናብ የዘነበበት ዳመና አልነበረም ፀሀይ ነው ከ 1 ሰዓት እስከ 12 ፍፃሜ ድረስ
- የተከበረው ፍ/ቤት ዘግይቼ ነው የመጣሁት ሀሰን ሁሴን እባላለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ለጥያቄ ሳይሆን የተነሳሁት አሁን የቀረቡት ምስክር ከእዚህ ቀደም እንዳቀረብነው ዓይነት የሪለቨንሲ ወይም የአግባብነት ጉዳይን ለመቃወም ነው አሁን የተጠቀሱት 3 ምስክሮች ሐምሌ 1 ቀን ተብሎ ክስ አልተመሰረተባቸውም በኒ ወይም ኑር መስኪድም ተብሎ የቀረበባቸው ክስ የለም በኒ መስኪድ ወይም ኑር መስኪድ በእንደዚህ ዓይነት ድርጊት ወይም አሁን ምስክሩ ባብራሩት ድርጊት ፈፅሟል ተብሎ የቀረበባቸው ክስ የለም ስለዚህ ክስ ባልቀረበበት ጉዳይ ምስክር እየተሰማ የፍ/ቤቱም የእኛም ጊዜ እየባከነ ነው ይሄ ከወንጀል ሕጉ አንፃር ተገቢነት የሌለው ነገር ስለሆነ ያው ድጋሚ ብይኑ ይሰጠን ካልሆነ የቀረቡትም ምስክር የሰጡትም ቃል በእኛ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ባለሙያዎችም የተጠየቀ መስቀለኛ ጥያቄ እንዲሰረዝ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን ነው ምንም ባልተከሰሰንበት ጉዳይ መከራከር አስፈላጊ ስላይደለ

- አልቋል
- ጨረስን
- መልስ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ ይሄ አሁን የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ነው ምክንያቱም 1ኛ /ግልፅ ያልሆነ/ ምክንያት በእዚህ ጉዳይ በተነሳው ዋና ጥያቄ እንዲሁም በመስቀለኛ ጥያቄ የተከላካይ ጠበቆች ተገቢውን ክርክር አድርገናል አሁን ክርክሩም እየሄደ ነው አሁን በመጨረሻ ይሄ ሊሄድ አይገባም በክስ ላይ የለም ለተባለው በመሰረቱ ያው ወደ ኋላ ከመለስን ካልሆነ በስተቀር ከእዚህ በፊት በተደጋጋሚ ጊዜ እዚሁ ችሎት ይሄንን መሰል ጥያቄ አንዴ ቤኒ መስኪድ አንዴ መርካቶ ያለው /ግልፅ ያልሆነ/ መስኪድ አንዴ የት መስኪድ በሚል የተለያየ አካባቢ የለም በሚል በዝርዝር ተነስቶ ለእዚህ ለመቃወሚያ መልስ ስጥተን የተከበረው ፍ/ቤት ብይን ሰጥቶ በጉዳዩ ታልፎ ወደ ክርክሩ ተገብቷል እና በአዲስ አበባ ከተማ እና በሌሎች እስቲ ዝርዝር አለ ስለዚህ እኛ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙትን መስኪዶች በሙሉ መግለፅ ግዴታ የለብንም በክሱ መነሻ አላማ ግብ እዚህ በዝርዝር ውስጥ ተገልፆዋል ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት በእዚያ አግባብ እንዲያይል በትህትና እጠይቃለሁ
- ጨርሰዋል
- ጨርሰናል
- የቀረበው መቃወሚያ ምስክሩ ክስ ስላልቀረበ ፍሬ ነገር እየመሰከሩ ስለሆነ ሊመሰክሩ አይገባም ምስክሩ አግባብነት የላቸውም የሚል ነው በአጭሩ በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ዓይነት መቃወሚያ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በክስ ላይ ተጠቅሷል ብይን ተሰጥቷል ከእዚህ በፊት ተመሳሳይ ነገርም በብይን ታልፏል የሚል ነገር አንስቷል ፍ/ቤቱ አንድ ፍሬ ነገር ብቻ አንድ ጭብጥ ብቻ ነው ከእዚህ ያየው ምስክሩ ክስ ላይ ያልተጠቀሰውን መስክሯል ወይስ አልመሰከረም ወደ የሚለው መግባት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነም ምስክሩ ተገቢ አይደለም ሪለቫንት አይደለም ተብሎ መቃወሚያ የሚቀርበው በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ብቻ ነው ያየነው መስቀለኛ ጥያቄ ምን ዓይነት ጥያቄ እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው በዋና ጥያቄ ምስክሩ የመለሰው ነገር የተሳሳተ ነው በእዚህ ኤሪያ ላይ የሚል ነገር እና እሱን ለማስተባበል ከሚቀርብ ጥያቄ በስተቀር መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ደርሶ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ምስክሩ ሊመሰክሩ አይገባም የሚለው ነገር ሲነሳ የሚችልበት የሕግ አግባብ ስለሌለ ወደ ሌላ ነገር ሳናልፍ ይሄ መቃወሚያ በተገቢው ጊዜ የቀረበ ባለመሆኑ ውድቅ በማድረግ አልፈነዋል ሌላ የምትጠይቁት አለ ?

- ሽመልስ አህመዲን ስንት ሰዓት እንደተናገረ እስቲ ንገረኝ አህመዲን ስንት ሰዓት ነበር የተናገረው አህመዲን ስንት ሰዓት ነበር ንግግር ሲያደርግ የነበረው ?
- በሰዓቱ ሰዓቱ ስንት ሰዓት እሱ እንደተናገረ ሰዓቱን አልያዝኩም ከ 4 ሰዓት ጀምሮ ፕሮግራም እያለ ግን
- እኮ ከ 4 ሰዓት ስንት ሰዓት አካባቢ ይሆናል ?
- ፐርፌክት ሰዓቱን ይሄንን ነው ብዬ መናገር ትንሽ ይከብደኛል
- እሺ አንተ ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ከዙር በፊት ነው በኋላ ነው ?
- ከዙር በፊት ነው
- ከዙር በፊት ነው እሺ ሰይድ ሲናገር ጥያቄአችን ሰላማዊ ነው ሲል ነበር አይደል
- ግልፅ አይደለም
- ሰይድ ሲናገር ነበር ብለሀል አይደል ሰይድ ሲናገር ስለመጅሊስ ሲናገር ጥያቄአችን ሰላማዊ ነው ሲል ነበረ ?
- እሱን ሲጠይቅ እሱን ሲናገር አልሰማሁትም
- አልሰማኸውም እሺ
- እኛ የምንፈልገው መጅሊስ ሙስሊሙን አንድ አድርጎ የሚመራን እና ለልማት የሚያሳትፈን ነው ሲል ነበር አይደል ?
- እሱንም አላስታውስም
- አታስታውስም ይሄንን
- አቶ ሽመልስ ሕዝቡ ይቃወም ነበር ምን ይል ነበር ?
- በነገሩ ብቻ ያው ተክቢራ እንደሚያደርግ ነው እንጂ
- የተቃወመ የለም አይደል ?
- ተክቢራ ብቻ ነው የሚያሰማው
- ተክቢራ ምን ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው ንግግር ሲደረግ ብቻ ድምፅ ነው እንጂ ሌላ ነገር
- የድጋፍ ነው አይደል ?
- ተክቢራ ማለት ያው እንግዲህ ለሙስሊም ግልፅ ነው ተክቢራ ማለት
- ድጋፍ ነው ተቃውሞ አሁን በገለፁበት ተክቢራ ሲደረግ ነበር አሉ እና ምን ማለት ነው ?
- ተክቢራ ማለት ያው የሆነ ነገር ሲነገር መጨረሻው ላይ አላህ ከበር የሚባል ድምፅ አለ ያ ድምፅ ምንድን ነው ያው ያለውን ነገር
- እኮ ያለውን ነገር ምን ሆነ መቀበል ነው መቃወም ነው እሱን ነው የጠየኮት ?
- በተነገረው ነገር ላይ ሲነገር የሆነ ነገር ምርጫችን በመስኪዳችን እንደዚህ ነው ምናምን ቢለው ሲናገሩ መጨረሻ አላህ ከበር አላህ ከበር የአላህ ከበር እንግዲህ ይሄ የራሱ ያው የንግግር ቃል ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- እኮ ተስማምተናል ማለት ነው አይደል አላህ ከበር መጨረሻ ?
- እንደገና
- አላህከበር ማለት መጨረሻው ተስማምተናል ማለት ነው አይደል ?
- እንደዚያ ማለት አይደለም አልተስማማንም ማለት ነው ?
- አይደለም
- ምን ማለት ነው ታዲያ ?
- የሆነ ንግግሩ ሲገለፅ አላህከበር ማለት የሆነ ቃል ሲነገር አላህ ከበር ይላል ሕዝቡ ያው ባለው ነገር የራሱ አላህ ከበር ትርጉም ስላለው
- ስለዚህ ምንም ማለት አይደለም ?
- እንደ ንግግሩ እንደቃላቱ ንግግር እዚያ ላይ የወሰናል
- መቃወሚያ
- ምንድን ነው መቃወሚያ
- መቃወሚያ ምስክሩ ከእዚህ በላይ ማስጠንቀቅ አይቻልም በመሰረቱ የሚያውቁትን የእውነታቸውን አላህከበር ማለት ምን ማለት ነው በእዚህም ትስማማለህ በእዚያም አትስማማም እንደገና 3ኛ 4ኛ አማራጭ እያቀረቡ ነው እሳቸው የሚያውቁትን ገልፀዋል ከእዚያ በላይ ይሄንን ብለን እንለፈው ይሄንን ብለን እንደምድማለን ይሄ ለተከበረው ፍ/ቤት እንጂ

http://ethcriminalawnetwork.com/

በእዚህ አሁን የሚቀርብ ክርክር የሚቀርብ የሚሰጥ አስተያየት ስላልሆነ ውድቅ ተደርጎ ሊሏ ጥያቄ ካላቸው በእዚያ አግባብ እንዲታይ ለማለት ነው አመሰግናለሁ

- የተነሳው መቃወሚያ ግልፅ አልሆነልንም እና መልሰዋል ነው ጥያቄው ተገቢ አይደለም ነው ምንድን ነው እስቲ ግልፅ ያድርጉ
- ጥያቄ የቀረበው የትርጉም ጥያቄ ነው እሳቸው አላህከበር ይሉ ነበር አላህከበር ማለት ምን ማለት ነው ተስማምተናል ማለት ነው አልተስማማንም ማለት ነው እንደዚህ ማለት ነው እያሏቸው ነው በቃ የሚችሉትን አላህክበር ብለዋል በራሳቸው ቃል ብለውታል ይሄንን ለመንፈሳዊ ሰዎች ኖርማሊ የሚታወቅ ነው ምን ማለት እንደሆነ ከእዚያ ውጪ ያላቸውን እውነት እና አቅም ከገለፁ እንዲህ እንበለው እንደዚያ እንበለው እንዲህ እንበለው እየተባለ የጭቅጭቅ ዓይነት ጥያቄ የሚቀርብበት ምክንያት ስለሌለው ውድቅ ይደረግልን
- ምላሽ
- የተከበረው ፍ/ቤት እንደፍ/ቤቱ እኔ መቃወሚያው አልገባኝም ግን እኛ የጠየቅነው ምንድን ነው ሰውዬው አላህ ከበር ተባለ ካሉ ምን ማለት ነው በቦታው ላይ ስለነበሩ ያዩትን ነገር እንዲገልፁ ነው ስለዚህ ይሄ ደግሞ ምንም መቃወሚያ የሚያስቀረው ምክንያት አይደለም እኛም ምስክሩም የተጨናቹቸው ነገር የለም የማያውቁትን የዩትን እንዲመሰክሩ ነው ስለዘህ ይሄ ደግሞ መቃወሚያ ምንም መሠረት ስለሌለው የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄውን ወይ በራሱ እንዲያስጠይቀው ካልሆነ ምስክሩን እኛ እንድንጠይቅ እንዲታዘዝ ነው
- ግራ ቀኝ ያነሱት ክርክር መድገም አያስፈልግም ጥያቄው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነው ያየነው አላህከበር ሲሉ ነበረ ንግግሩ ሲደረግ እና ያ ማለት ድጋፍ ነው ተቃውሞ ነው የሚል ነው ጥያቄው ስለዚህ ጥያቄው ችግር ያለው ሆኖ አላገኘነውም ጥያቄው ተገቢ ነው ምስክሩ ጥያቄውን የሚያውቁ ከሆነ ይመልሳሉ የማያውቁ ከሆነ አይገደዱም ጥያቄው ይቀጥል
- የድጋፍ ነው እርሶ ተቃወሙ ወይስ ምን አደረጉ
- ቆይ እስቲ ጥያቄው ምንድን ነው ግልፅ ነው በወቅቱ እዚያ ስለነበርክ እነሱ ሲናገሩ አላህከበር የሚል ነገር ነበረ ስለዚህ እዚያ ያለውን ስሜት የምታውቀው አንተ ነህ ምን እንደሚባል እኛ አናውቀውም ስለዚህ እሱ ነገር ስምምነት ነው ወይስ ከስምምነት ወጣ ያለ ወይም ይሄንን ለመግለፅ የሚያስችግርህ ነገር ካለ ደግሞ እሱን ግለፅልን ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያ ጋር ምንድን ነው ማገናኛውም ነገር እንደአገላለፁ ነው አላህክበር የሚባለው ጥሩም መጥፎም አላህክበር የሚባልበት
- ልክ ነው አሁን ትክክል ነህ አሁን ያኔ የነበረው አገላለፅ ምንድን ነው የተረዳኸው ያኔ የነበረውን ንገረን ?
- ሕዝቡ እዚያ ጋር ላለው ወደ ሌላ ቴንሽን ወይም ሌላ ነገር አላህክበር ተብሎ ምንም የሚያነሳሳበት ግን የራሱ አላህበር ሲባል የሚባልበት ነገር ስለሆነ በኃይማኖቱ ጉዳይ እንጂ መጥፎ ነገር እንስራ ምን ብሎ ያለው ነገር አይደለም እዚያ አካባቢ ላይ ግን ያው ተክቢራ የግድ መባል ስላለበት በንግግራቸው እንደኃይማኖት መንፈሳዊ እንትን ነው እንጂ ሌላ መጥፎ ነገር ምናምን አይደለም
- ያው መልሷል ግልፅ ነው አይደለም የሚለውን ያው አንድ ላይ ይታያል ሌላ ጥያቄ
- ቅድም አቶ ሽመልስ ሀባሽን በተመለከተ ምን አሉ ነው ሀባሽ ዲናችን ለሀባሽ አንሰጥም ብለው ነበር ያሉት ምን ማለት ነው ?
- ማለት መጅሊስ አይወክለንም ሀበሽ ዲናችን እነሱ ለእሱ እንትን አንልም እኛ እራሳችን መታገል እንዳለብን እና መጅሊስ እነሱን እንደማይወክለን ያው ንግግር ሲያደርጉ ነበር
- /ግልፅ ያልሆነ/ የሚሏቸው እነ ማንን ነው ?
- አቶ አቡበከር
- ሀባሾችን ነው ?
- አዎ መጅሊስ አይወክለንም ሀበሽ አይወክለንም ማለት መጅሊሶችን ማለት ነው
- ሀባሽ ማለት መጅሊሱ ነው ?
- እንደእኔ እውቀት ያ ነው
- አሉ አሁን ሀባሾች ?
- እንደገና
- አሉ አባሾች አሁን ?
- በንግግረቸው ነው እንጂ ይኑሩ አይኑሩ በንግግራቸው ሲናገሩት የነበረው ነ...
- በአሁኑ ሰዓት አሉ ወይ መጅሊስ ውስጥ ?
- እሱን አላውቀውም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያኔ አይመራንም የሚሉት መጅሊስ በምርጫ ወርደዋል አይደል ?
- እንደገና
- ያኔ እነሱ አይመራንም ብለው ነበር መጅሊስን አይደል ወይም አይወክለንም ብለው ነበር ያ መጅሊስ አሁን ? አለ ወርዷል አይደል ?
- በጊዜው እነሱ አይወክለንም አሉ አሁን ምን ይምራ ምን ይምራ በእንትኑ እንትን ባይባል መጅሊስ አይወክለንም እያሉ እነሱ ንግግር ሲያደርጉ ነበር
- እኮ አለ ያ መጅሊስ አሁን ?
- ስለእዚያ አላውቅም
- መጅሊስ አለ ያ እነሱ አይወክለንም ያሉት መጅሊስ አለ ካሉ አለ የለም ካሉ የለም በሉ አለ ?
- አላውቀውም እዚያ ጋር ይኑር የእነሱን ንግግር ብቻ ነው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- ድጋሚ የለንም
- ጨርሰዋል እናመሰግናለን ቀጣይ ምስክር
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- አዎ
- ስምዎን ያው የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ የራስዎን ብቻ ?
- ሚካኤል
- ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ በተሰሙት ዝርዝር 93ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በክሱ ማስረጃ ዝርዝር ላይ በ 182 ላይ የተጠቀሱ አቶ ሚካኤል ቀርቧል ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- 1ኛው አቶ ያሲን
- ያሲን ?
- አዎ ያሲን ኑር በእሱ
- በእሱ ላይ ብቻ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንደኛው ማን ነው ሽምሱ የሚሉት
- ሽምሱ ማን ?
- የአባቱን ስም /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ሌላ አለ ?
- ሌላ የለም
- እሺ ያሲን ኑሩ ያሉት እና ሽምሱ ያሉትን ማሳየት ይችላሉ አሁን በአካል ለይተው ያውቃሉ ?
- ያሲን ኑር በወቅቱ
- በአካል ለይተው ማሳየት ይችላሉ አሁን እዚህ ካሉት ?
- ያኛውን ልሞክር ያሲን ኑር በወቅቱ አላገኘነውም
- ስለዚህ ሽምሱንስ ?
- እሱን በአይን ባውቀው ላስታውሰው
- ምን የለበሰ ስንተኛ ?
- 3ኛ ላይ ያለው ማን ነው ስሙ ካሚል እሱ ነው ?
- አዎ
- ስንተኛ ነህ እሺ ያሲንንስ ?
- ያሲን ኑር
- እሱን አይለዩም ምስክሩ 4ኛ ተከሣሽ ሽምሱ ብሎ አሳይቷል በክሱ ላይ ያው ሽምሱ የአባቱ ስም ነው ካሚል ሽምሱ
- ካሚል ሽምሱ
- እዚያ ሲያሳዩ ግን ያው 4ኛውን ተከሣሽን አሳይቷል እሺ ምን ሲያደርጉ አዩ እነኚህ ሰዎች ?
- የትኛው አሁን ካሚል ሽምሱ ያሉትን እና ያሲን ኑሩ ብለው ነበር አሁን ባሳዩን ምን ሲያደርጉ አዩት ምን ሰሙ ?
- ያሲን ኑር ላይ እኔ አንድ ጓደኛ አለኝ እዚያ
- ዝርዝሩን በኋላ እንገባለን ምንድን ነው ያዩት ?
- በካሚል ሽምሱ ላይ ከላፕቶፕ እና ከኢሜል ፕሪንት ተደርጎ ሲወጣ አይቼአለሁ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ከያሲንስ ?
- ከእዚያ ቤቱ ሲበረበር በወቅቱ ነበርኩ
- እሱን ነው ያዩ ?
- አዎ
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ካሚል ሽምሱ ቀድም ምስከር እንደገለፁት ካሚል ሽምሱ እንጀምር እና ከካሚል ሽምሱ ከኢሜል ሲወጣ ታዛቢ የነበሩት መቼ ነው ታዛቢ የነበሩት መቼ ነው ካሚልን በሚመለከት ማለት ነው መቼ ነው ጊዜው ቦታው የት ነበር ?
- በ 25 እዚያ ለቀብር በአጋጣሚ ስሄድ ለመለስ ቀብር አካባቢ ስሄድ ነው በእዚያ አካባቢ አጋጣሚ እንትን ያልኩት በ 25 ነሐሴ 25 ነው የአጋጣሚ ገባሁ
- ዓ.ም ?
- 2004 በእዚያው ሰዓት ላይ ነው ለታዛቢነት ፈልጌዎት ነበር አለኝ እሱ አልኩት ገባሁ ትንሽ ቁጭ እንዳልኩኝ እዚህ ማዕከላዊ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የከሚል ገባሁ ወዲያው መርማሪው ያው እንድታዘብ ነበር የጠየቀኝ እሺ አልኩት ይሄ ካሚል ሽምሱ መጣ ከመጣ በኋላ ላፕቶፕ በእጁ ይዟል ከእዚያ ከላፕቶፕ ውስጥ 2 ፔጅ የምትሆን ወረቀት እና ሌላው ፕሪንት ተደርጎ ሲወጣ ወደ 131 የአማርኛ የእንግሊዘኛ እና የአረብኛ ወረቀቶች ወጥተዋል
- እሺ ይሄንን መጀመሪያ ላፕቶፑ መጣ ከእዚያ ተቀመጠ ምን ተደረገ ማን ነው ፓስወርድ አለ ምን አለ ማን ነው የከፈተው እሺ ማን ነው ፓስወርዱን መጀመሪያ የከፈተው ማን ነው ?
- የከፈተው
- አዎ እንዴት ወጣ ወረቀቱ
- በመጀመሪያ አይስማማም የተከበረው ፍ/ቤት 2ኛ ተቃውሞአችን
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ ግን ተቃውሞ አለን ወይ ጥያቄውን ካስተካከሉ
- ምስክር ይሰማል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ይሰማል
- እሺ እዚያ ቢሮ መጣ ይኸውልህ ምስክር አሁን ከተሰማህ ያው /ግልፅ ያልሆነ/ አንተ እዚያ ገባህ ማለት ተጠራህ አጋጣሚ ብለህል ገባህ ያሲን ኑሩ መጣ ላፕቶፕ ይዞ ከእዚያ በኋላ ምን ተደረገ እስቲ ደረጃ በደረጃ ቅደም ተከተሉ እንዴት ነበር ?
- ያሲን ኑር አይደለም በለሱ
- ካሚል ሸምሱ ?
- ካሚል ሸምሱ
- አዎ መጣ ከእዚያ ቁጭ አለ አልከ አንተም አለህ ሌሎች ሰዎች ነበሩ ?
- ሌሎች ሰዎች የሉም
- እሺ አይ እንደአንተ ታዛቢ ማለት ነው ?
- አንድ ልጅ ነበረ
- ነበረ ?
- አዎ
- እሺ ከእዚያ እሱ ተቀመጠ ?
- አዎ
- አሁን ከእዚህ ጀምሮ ያለውን ቅደም ተከተል እያንዳንዱ እንዴት ወረቀቷ ወጣች ማን ላፕቶፑን ማን መጀመሪያ ምን አደረገ ይሄንን እስቲ ለተከበረው ፍ/ቤት ለእነሱም በዝርዝር እሱን እንድታስረዳ ?
- መርማሪው አለ ከእዚያ እሱ አለ አንድ ጓደኛ እንደእኔ እንትን ያለ አለ እሱ ይዞ መጣ እራሱ ነው ሁሉን ነገር እንትን ብሎ
- ማለት ሁሉ ነገር ስትል ምንድን ነው ያ ሁሉ ነገር ምን አደረገ ?
- ፕሪንትም ሲደረግ ወረቀቶቹ ውስጥ እራሱ ነው እንትን ያስደረገው ከእዚያ እራሱ አወጣ መጀመሪያ ካወጣ በኋላ ያኛውንም 2ኛ ፔጅ አወጣ እንትን አለበት ፈረመበት ከእዚያ ቀጥሎ እኛ ፈረምንበት
- ይኸውልህ አሁን ቅድም እሺ ስንት ገፅ ነው ?
- በአማርኛ 131 መሰለኝ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ሌላስ ?
- እንግሊዘኛ አለ 19 አካባቢ አረብኛ 12
- ይሄ የአማርኛው ይዘቱን ታስታውሳለህ ለማንበብ ሞክረሀል ምን ይላል ?
- የው ሙስሊም ወንድሞች በሀገርም ውስጥ በውጪም ንቅናቄ ለማድረግ ምናምን እንደዚህ ዓይነት
- ንቅናቄ ለማድረግ ምን እንሁን ይላል ?
- ያው በውጪ ዓለምም በእዚህ በሀገር ውስጥም ከአሁን የተሻለ እንቅስቃሴ እናድርግ ነው ያለው በወቅቱ ከነበረው አንፃር
- የምታስታውሰው ማለት ነው ?
- አዎ
- እሺ እነኚህ በሙሉ አሁን ያየሀቸው ከወጡ በኋላ ምን አደረጋችሁ ለመጨረሻ ለመተማመን ምን ተደረገ ?
- ያው ለፍ/ቤት እንደሚቀርቡ እዚያው መርማሪው እየነገረው ነው ከእዚያ ፈረመበት እኔ ፈረምኩ ያ ልጅ ፈረመ
- እሺ ወደ አቶ ያሲን እንሂድ እና እስቲ ምንድን ነው የምታውቀው ?
- ያሲን ኑር እዚያ ልጅ አለ ጓደኛ አንድ አይስዙ የሚነዳ ልጅ አለ አጋጣሚ እሱ ጋር ነበርኩ የዋልኩት እና አድሬ ጠዋት እንትን ልል ስል ሰዎች ፌዴራል መኪና ይዘው ቆመው ነበረ ከእዚያ አጋጣሚ ፖሊሶች አንድ ሴት እና አንድ ነበሩ ከፌዴራል ፖሊስ የለበሱ ሰዎች ነበሩ እና እንደዚሁ ሲጠይቁኝ ይሄ ነገር እንደውም ምናምን ተደጋጋሚ እያልኩ ገባሁ እሺ አልኳቸው መጥሪያ ስል መጥሪያ አሳዩኝ በያሲን ኑሩ ይላል በሽብር ምናምን ብሎ ከፌዴራል መደበኛ ምናምን አራዳ ወንጀል ችሎት የሚል አለ እሱን አየሁ እሺ አሁን መግባት እንችላለን ተባለ ሲንኳኳ አንድ ልጅ ወጣ ከእዚያ አለ ወይ ሲባል የለም ተባለ ስልክ ቁጥሩን ስጠ ስልኩ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ቦታው
- ቦታው ወደ ሸጎሌ ጉለሌ
- ጉለሌ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዎ ወረዳ ፱/ግልፅ ያልሆነ/ ጠዋት ነው ከ 2 ሰዓት አካባቢ ከእዚያ ወንድምየው ወጣ እና ደብዳቤውን አሳዩት የለም አለ ስልክ ሞከሩለት ይጠራ ነበር አይነሳም ደጋግመው ደወሉለት ተዘጋ ተያይዘን ገባን ከእዚያ ባለቤቱ እመጫት ነበረች ለባለቤቱ አሳዩዋት ወንድምየውም አለ እና ሰራተኛ ነበረች አብረን ገባን እኛ ባለንበት ቤቱ እንትን አሉት የተያዙት ሲዲዎች እነዚህ ላፕቶፖችን እነሱን አይተን ወጣሁ አብረን ተያይዘን ወጣን
- ከእዚህ ከሲዲዎች ሲዳዎች ተገኝተዋል ብለሀል እና ስለሲዲዎቹ ይዘት በወቅቱ ያያችሁት ነገር አለ ?
- አዎ የተለያዩ ሲዲዎች ናቸው የተወሰነ የስብሰባው ነው ብዙም ትዝ አይለኝም ይሄ ድምፃችን ይከበር ምናምን የሚሉትን መፅሔቶች እና ጋዜጦች ብዛት እንዳለው አስታውሳለሁ
- አሁን እነዚህ ያልካቸው በሙሉ ከተገኙ በኋላ ምን አደረጋችሁ መጨረሻ ስለመገኘታቸው ?
- ፈረምንባቸው ለባቤቱም ነገሯት አዎ አለች ወንድምየውም ነበረ አዎ አለ ተያይዘን አንድ ላይ ወጣን
- ወንድምየው ስሙን ታስታውሳለህ ወንድም ያለውን ?
- ስሙን አላስታውስም ግን አብሮ እንደተገኘ አብሮ ፈርሟል ከእኛ ጋር
- ጨርሰናል
- ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- አቶ ሚካኤል
- አቤት
- ያሲን ኑሩ በቦታው አልነበረም ብለዋል በር የከፈተላችሁ ሰው ወንድም ነኝ ስላለ ነው የያሲን ኑሩ ወንድም የሚሉት ወንድም መሆኑን በምን አወቁ ?
- አዎ ከገባንም በኋላ ከሚስትየው ጋር ያገናኘን እሱ ነው ወንድሙ ነው አዎ ብላናለች ሚስትየው እራሱ
- ሚስት ያሏት ቤት ውስጥ የነበረችዋን ?
- ቤት ውስጥ አዎ ልጅ እራሱ እመጫት ልጅ የያዙች
- እሷስ ሚስት መሆኗን በምን አወቁ ?
- ባለቤቱ ነኝ ብላናለች

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነኝ ስላለች ነው ?
- አዎ ውስጥ ገብተናል
- ከእዚያ ውጪ ባለቤት ስለመሆኗ ያረጋገጣችሁት ነገር የለም አይደል ?
- ማረጋገጫ የለንም
- የጋብቻ ወረቀት አላያችሁም ?
- አላየንም
- እነዚህ መፅሔቶች እና ጋዜጦች ያሏቸው ይሄ ገበያ ላይ የሚሸጡት ናቸው አይደል የታተሙ መፅሔቶች ?
- አዎ ገበያ ላይ ያሉ ናቸው እነዚህ ግን ድምፃችን ይከበር ምናምን የሚሉት አይቼአቸው አላውቅም የማስታውሳቸው እነሱን ሌሎች የሙስሊም መፅሔቶች ምናምኖች ናቸው ያሉት
- እነዚህ መፅሔቶች የት ነው ያገኙዋቸው ጋዜጣ እና መፅሔቶች ቤት ውስጥ የት ጋር ተገኙ ቤቱን ስትበረብሩ የት ጋር አገኛችዋቸ ?
- እሱ መኝታ ቤት ውስጥ
- ማለት መፅሐፍ መደርደሪያ ላይ ነው አልጋ ላይ ሳጥን ውስጥ ?
- ከኮሜዲኖ አለ ከእዚያ ውስጥ ነው የወጡ
- ኮመዲኖ ላይ ?
- አዎ
- ስንት ላፕቶፕ ነው ያሉት ቅድም ላፕቶፖች ነው ያሉት ?
- አንድ ላፕቶፕ ቶሺባ አለ አንድ ዴል አነስ ያለ አለ
- እነዚህ ላፕቶፖችን ምን አደረጋችሁ አሸጋችሁ አሸጋችዋቸው እንዴ ?
- አዎ ፌስታል እራሳቸው አመጡ ቤተሰብ በእነሱ በመጣ እንትን ተያ። አልታሸገም
- በፌስታል ተጠቀለሉ ?
- አዎ
- የሲዲዎቹንም ይዘት አላያችሁም?
- የሲዲዎቹን ይዘት አላየዋቸውም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሲዲዎቹ ላይ በላያቸው ላይ ወይም በሂርባቸው ፈርማችሁባችዋል ?
- አዎ ፓርከር ተባብረዋቸው ነበር በፓርከር ከሚሆን ወንድምየው ችግር የለውም የተለያዩ ሲዲዎች ናቸው ችግር የለውም ጊዜ ከምናባከን አለ ወንድምየው ሚስትየውም አዎ ልጅ እንትን እያለቀሰች ስለሆነ ችግር የለውም የተለያዩ ሲዲዎች ስብከቶች ናቸው አለች እንትን አለ ተቆጥሮ ግን ኦሪጂ ኢሰም እንትን በኋላ
- ስለዚህ እነሱ አሏችሁ ከእዚያ በላያቸው ላይ ምንም ፓርከርም በፁሑፍ በእስክሪቢቶም አልፃፋችሁም ?
- በፓርከር ጭረውባቸዋል
- ማን ነው የጫረው ?
- መርማሪው
- መርማሪው ማለት ፅፎበታል ?
- አዎ ሴቷ
- ሲዲዎቹ ላይ በላያቸው ላይ ስዕል ነገር ወይም ርዕስ የላቸውም እንዴ ?
- አላቸው አላስታውሳቸውም እንጂ እነሱን አሏቸው
- እነዚህ ሲዲዎችም የት ጋር ነው የተገኙት መደርደሪያ ላይ ቴፕ አጠገብ ቪዲዮ አጠገብ ?
- አዎ የተለያዩ ቦታ ነው ያሉት እንዳልኩት ከቅድም ከኮሜዲኖ ውስጥም የተገኙ አሉ መደርደሪያ ላይም የተገኙ አሉ
- መጨረሻ ካገኛችሁ በኋላ ቪዲዮ ቀርፃችዋል ?
- አዎ
- ስንት ፖሊስ ነው ወደ ቤት የገባው ?
- ምኑ
- ወደ ቤት ለብርበራ የገባው ስንት ፖሊስ ነው ?
- ፌዴራል ፖሊሶች አሉ የፌዴራል ልብስ የለበሱ ኖርማል ሲቪል የለበሰ አለ መቅረጫ የያዘ መርማሪ ሴት አለች እነዚህ ነው እና ከእኔ ጋር እዚያ አብሮ እንደኔ ተመሳሳይ የመጣ
- ወደቤት ሲገባ መቅረጫ የያዘው በምን ነበር የያዘው በቦርሳ ?
- በቦርሳ አይደለም ሲገባ ቦርሳውን አስቀምጦ /ግልፅ ያልሆነ/

2863

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቤት ?
- ሲገባ አውልቆት ነው የገባው
- ካሜራውን አውልቆ ?
- አዎ
- ሌሎቱ ፖሊሶቱ ምን ይዘው ነበር ?
- ምንም አልያዙም
- ካሜራውን አወለቀ ሲሉ ከምንድን ነው ያወለቀው ከቦርሳ ?
- አዎ ቦርሳ ነበር ቦርሳውን አስቀመጠ እና ገባ
- የት አስቀመጠው ?
- ውጪ እደጅ መጀመሪያ ስንገባ ግቢ ውስጥ
- ቅድም ካሚል ሸምሱ ላፕቶፑን ይዞት መጣው ነው ያሉት ?
- አዎ
- ከየት ነው ይዞት የመጣው ?
- እኔ /ማለሰ የልሆነ/
- ማለት ማን ነው ቀድሞ የገባው ታዛቢዎች ነው ወይስ ካሚል ሸምሱ ነው ?
- እኛ ነን
- እናንተ ቢሮ ውስጥ ነበራችሁ ?
- አዎ ውስጥ አስቀምጦን ነበር
- ካሚል ሸምሱ ላፕቶፕ ይዞ መጣ ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላ የነበረውን እስቲ አቀማመጣችሁን ግለፁልን ማለት ካሚል የት ጋር ተቀመጠ ታዛቢዎች የት ጋር ፖሊሶች የት የት ጋር ተቀመጣችሁ ?
- እኛ ከእሱ አጠገብ ነን እንደዚህ ጎን ለጎን ነን የቆምነው ቁጭ ያልነው መርማሪ እንትኑ በወዲያ ፊት ለፊት ለፊት ለፊት ሆኖ በወዲያ በጎን በኩል ነው
- ስንት ኮምፒዩተር ነበር እዚያ ቢሮ ውስጥ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንድ ኮምፒዩተር አይቼአለሁ
- ትልቁ የጠረቤዛው ማለት ነው ?
- አዎ እና የእሱን ላፕቶፕ
- እዚያ ኮምፒዩተር ጋር ማን ነበር የተቀመጠው ትልቁ ጋር ፖሊስ ነው የደንብ ልብስ የለበሰ ?
- አይ መጀመሪያ ማንም አልተቀመጠም ፖሊሱ ለብቻነው ነው የተቀመጠው
- ኮምፒዩተሩ ጋር ማንም አልነበረም ?
- ማንም አልነበረም
- እሺ ኮምዩተሩ ከትልቁ እና ላፕቶፑ ጋር አልተገናኙም በገመድ ?
- ከትልቁ እና
- ከትልቁ ኮምፒዩተር እና ካሚል ይዞት መጣ ያሉት ላፕቶፕ በገመድ አልተገናኙም ?
- አልተገናኙም
- ፕሪንት አደረገ ሲሉ ነበረ ቅድም ?
- እኮ የእንትኑ ነዋ ከኮምፒዩተር ላይ የራሱ እንትን ያለውን ተጠቅሞ አወጣ ከእዚያ በኋላ ላፕቶፑን ተጠቀመበት
- ጥሩ እናንተ ጉበታችሁ ነበረ ካሚል መጣ ዝም ብሎ መጥቶ ቁጭ ብሎ ኮምፒዩተሩን ከፈተ ወይስ ምን ተነጋገራችሁ ?
- እነዚህ ታዛቢዎች ናቸው ብሎ ነገረ ከእዚያ በኋላ እነዚህ ሰዎች አንተ ባለህበት የምታደርገውን ነገር እያንዳንዳችሁ ተፈራርማችሁበት ወደ ፍ/ቤት እንደሚቀርብ እየነገሩን
- በወቅቱ ካሚል ምን አለ ?
- እሺ ነው ያለው
- አቶ ሽመልስ ካሚል እናንተ ወደ ነበራችሁበት ክፍል ሲመጣ እጁ ታስሮ ነበር አይደል በካቴና ታስሮ ነበር አይደል እጁ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እጁ በካቴና ታስሮ ነበር አይደል ?
- አልታሰረም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ባልደረባዬ ሲጠይቅህ ከኮምፒዩተሩ ላይ ፕሪንት ሲደረግ ነበር ብለሀል ማን ነው ፕሪንት ሲያደርግ የነበረው ፖሊሱ ነው ?
- እራሱ ነው ወረቀቶቹን አስገባለት
- እኮ እዚያ ቢሮ ውስጥ ከነበረው ኮምፒዩተር ነው አይደል ፕሪንት ሲደረግ የነበረው ?
- አዎ ወረቀቶች ነበሩ ባዶ ደስታ ሉክ አሳየው እና ሰጠው እራሱ ከተተ
- ከኮምፒዩተሩ ቢሮ ውስጥ ካለው ኮምፒዩተር ነው ፕሪንት የተደረገው ?
- አዎ
- እሺ ካሚል ይሄ ፕሪንት የተደረገው ከእናንተ ኮምፒዩተር ላይ የወጣ ፋይል ነው እና አልፈርምም ሲል ነበር አይደል ከእናንተ ኮምፒዩተር ላይ በወጣ ፋይል ፕሪንት የተደረገ ነው አልፈርምም ሲል ነበር አይደል ሲከራከር ነበር እንዴት ፈረመ መጨረሻ ላይ ?
- እሱም አልተከራከረም መጀመሪያ ከወጣ በኋላ ፈረመበት /ግልፅ ያልሆነ/ ስናወራ ነበር እንደውም ስንነጋገር ነበር
- ይሄ የእኔ አይደለም ከእናንተ ኮምፒዩተር የወጣ ነው ከእኔ ላፕቶፕ የወጣው 2 ገፅ ብቻ ነው እና ይሄ ሁሉ ከእናንተ ኮምፒዩተር ላይ በወጣው ላይ አልፈርምም ሲል አልነበረም ?
- አይ አልነበረም
- የያሲንን በተመለከተ ሲያስረዱ ፖሊሱ መጥሪያ አሳይቶኝ ነው እያሉ የነበረው እና እዚያ ፍተሻውን ያደረጉት መጥሪያ ያሲንን የሚጠራ ነው ወይስ እርሶን የሚጠራ ነው መጥሪያው ለማን ነው ?
- በያሲን ላይ ማዘዣ አወጥቶ ነው እና ለታዛቢነት
- መጥሪያ ያሉት ምንድን ነው ?
- ይሄ የያዘው ወረቀት ማለት ነው
- እኮ ማንን ነው የሚጠራው ?
- የፍተሻ ነው
- የፍተሻ ነው ወረቀቱ ?
- አዎ
- አይተውታል እርሶ ?

2066 4017

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ አይቼዋለሁ
- አንብበውታል ?
- አዎ
- እስቲ ምን ይላል እንትኑ ያነበቡት ነገር ምን ይላል ?
- አቶ ያሲን ኑር ይላል በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው ይል እና ከታች በእዚህ ኤሌክትሮኒክስ በጦር መሣሪያ የተያዙ ሰነዶች
- ማህተም አለው ?
- ማህተም አለው ፊርማ አለው
- የማን ነው ፊርማው ?
- የዳኛው ነው አራዳ
- የማን ስሙ የለም ፊርማው ?
- ስሙን አላስታውስም
- የአራዳ ዳኛ ይላል ?
- አዎ ነው የሚለው
- ሲዲ ይያዝ ይላል እንዴ ሲዲ ይያዝ የሚል ነገር አለው እንዴ እንትኑ ላይ ?
- ኤሌክትሮኒክስ ይላል የኤሌክትሮኒክስ እላይ በፁሑፉ ነው በእስክሪቢቶ በተፃፈው ላይ የእንትን ይላል የጦር መሣሪያ በእንትን አብሮ የተያዘ ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክስ እና ከእሱ ጋር ከክሱ ጋር ተያያዥ የሆነ መዝገቦች ምናምን የሚል ነው
- በእዚያ ወቅት ያገኛችሁት የጦር መሣሪያ የለም አይደል ?
- የለም
- ሌላ እንትኑ ላይ እንደተገለፀው ከሽብር ጋር የተያያዘ ነገር ያገኛችሁት የለም አይደል ?
- ድምፃችን ይከበር ነው የሆነ ድምፁ ብዙ እንትን የሚያስቸግር ሲዲዎች ተከፍተው ነበረ ይሄ ድምፃችን ይከበር የሚለውን አስታውሳለሁ
- በወቅቱ አቶ ያሲን በአካባቢው አልነበረም የእኔ ነው ብሎም አልፈረመም አይደል አዚያ እናንተ ናችሁ እንጂ የፈረማችሁት እሱ የእኔ ነው ብሎ የፈረመበት ነገር የለም አይደል ስላልነበረ ማለት ነው ?

2867

4018

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ባለቤቴ ነበረች ባለቤቴ ናት
- እኮ ስለእሱ አሁን እየጠየኩት ያለሁት ስለእሱ ነው የእኔ ነው ብሎ የፈረመበት ነገር የለም ?
- እሱ የለም
- አቶ ሚካኤል ቅድም ከካሚል ላፕቶፕ ውስጥ 131 ገፅ የአማርኛ 12 ገፅ አረብኛ እና እንግሊዘኛ አገኘን ብለው ነበር እነዚህ ነገሮች በሙሉ ሲወጡ አይተዋል ከካሚል ላፕቶፕ ውስጥ ?
- አይ ከኮምፒዩተር ላይ ነው
- ከኮምፒዩተር ስለዚህ ከካሚል ላፕቶፕ መውጣቱን አያውቁም ?
- አዎ ከእሱ 2 ገፅ የሚሆን ወረቀት ወጥቷል
- ምን የሚል ነው 2 ገፅ የወጣው ወረቀት ?
- የተለያዩ እንትኖች ናቸው
- የሚያስታውሱት
- ብዙም አላስታውሰውም 2 ገፁን እነዚያን ነበር እኔ ጊዜ ቀብር ሰዓት ምናምን ሰዎች ስለሚሉ እዚያ ላይ ነበር /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌሎቹስ ታዲያ ?
- ሌሎቹ የእንትኑን አስታውሳለሁ ወንድማማቾች ምናምን በሀገር ውስጥም በውጪም ንቅናቄ የሚል ወረቀቶች አስታውሳለሁ
- ገባኝ እዚህ ከኮምፒዩተሩ ወጣ ያሉት ወረቀት ?
- አዎ እሱ ላይ
- እሱ የማን ነው ?
- ከእሱ ነው እሱ ነው እንትን ያለው
- ከማን ?
- ያወጣው እሱ ነው ያወጣው
- ኮምፒዩተሩ የማን ነው ነው ያሉት ቅድም ሲጠየቁ ኮምፒዩተሩ የእሱ ... ዋል ?
- ላፕቶፑ ይዞ እንደገባ አይቼአለሁ ኮምፒዩተር እዚያው የነበረ ነው
- እኮ ከኮምፒዩተሩ ነው ወረቀቶቹ የወጡት አይደል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ እሱ እራሱ እንትን ቁጭ አለ እዚያ ወንበር ላይ እራሱ እንትን አለ አወጣ
- እሺ እነዚህ የወጡትን ወረቀቶች አማርኛም እንግሊዘኛም አረብኛም እንደሆኑ አይተዋል ሁሉንም ?
- እሱን አይቼአለሁ
- ከእዚያ ከወጡት ወረቀቶች ውስጥ ለካሚል በአድራሻቸው ለካሚል የሚል አይተዋል ካሚል የሚል አለው ?
- አዎ
- ለካሚል የሚል የተፃፈበት አድራሻ አለው ?
- የተፃፉ አሉ የተሰነዘሩ እንትኖች አሉ ከሴላም እንደዚህ የመጣ አለ
- እኮ ካሚል የፃፉቸውሳ ፍርም ካሚል የሚል አለ አይተዋል በአይኖ ?
- አላስታውስም
- አላዩም ?
- እንግዲህ ከእኔ የወጣ ነው ብሎ ነው መጀመሪያ
- አዎ እሱ ከእኔ የወጣ ብሎ ይፈርም እኔ ያልኮት አሁን እርሶ ያዩትን ነገር ከእዚህ ከኮምፒዩተሮቹ ወጣ ያሉትን ነገር ነው ከወጡት ሰነዶች ውስጥ ለካሚል ተብሎ የተፃፈ ወይም ካሚል ለሌላ ሰው የፃፈው መሆኑን ያረጋገጡበት ነገር አለ እርሶ ?
- አይ የለም
- የለም አይደል ስለይዘታቸውስ ስለተፃፉት አማርኛ ያነባሉ አይደል ?
- አዎ
- ምን ቅድም ያሉት ሙስሊሞች ወንድሞች በሀገር ውስጥም በሀገር ውስጥ የተሻለ እንቅስቃሴ እናድርግ የሚል አይቼአለሁ ብለዋል ከየትኛው ላይ ነው ይሄንን ያዩት ?
- ከኮምፒዩተሩ ላይ
- ከኮምፒዩተር ከወጣ ወረቀት ላይ ነው ከኮምፒዩተሩ ላይ እራሱ ከየትኛው ወረቀት ?
- ከኮምፒዩተር ከወጣው ወረቀት ውስጥ
- ከየትኛው እኮ ከአማርኛ ከተፃፈው ላይ ነው ?

2869

4020

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከአማርኛ በተፃፈው ላይ
- እሺ ሌላስ ምን አዩ ከእዚህ ውጪ ይሄንን ሲያስታውሱ ሌሎች ያስታወሷቸው ነገሮች የሉም ?
- አላስታወስኳቸውም
- ይሄንን ብቻ ነው የሚያስታውሱት ?
- አዎ
- እሺ ወደ ያሲን እንሂድ እና ያሲን ቤት ማን አሳያችሁ የያሲንን ቤት በምን አወቁ ?
- እኔ አካባቢ እዚያ አንድ ጓደኛዬ አለ ብዬአለሁ ወደ እዚያ ሄጄ ነበር በእዚያ ስመጣ ኮረኮንቹን ነው ፌዴራል ፖሊሶች ቆመው ያገኘሁት
- ፖሊሶች ነው ያሳዮት ?
- ፖሊሶች ቆመዋል በሩ ላይ
- ማን አሳዮት ታዲያ ቤቱን ?
- ፖሊሶች አሉ መርማሪ አሉ እንደዚህ እንደዚህ ለታዛቢነት ፈልገኖት ነበር ሲለኝ ነው እሺ ያልኩት ከእዚያ በምን ነበር እንደዚህ እንደዚህ አለኝ የፍ/ቤት ማዘዣ አለህ ወይ ስለው አዎ አለኝ ስጠኝ አነበብኩት እነሱ ናቸው ያሲን ኑሩ ቤት መሆኑን እንግዲህ
- የያሲን ኑሩ ላይ የፍ/ቤት መጥሪያ አየሁ ያሉት ?
- አዎ መበርበሪያ
- መበርበሪያ ?
- አዎ
- ስንት ዳኛ ነበር ፈረመ ያሉት ?
- ምን አንድ
- ቀኑን ያስታውሱታል ?
- የት
- ትዕዛዙ የተሰጠበትን ቀን አይተዋል ተነቦሎት ነው ወይስ አይተው ነው እርሶ ?
- አዎ
- ፖሊስ ነው ያነበበሎት አይተዋል ?

2870 2021

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ አይቼአለሁ
- በአይኖ አይተዋል ?
- አዎ
- ስለዚህ
- ሐምሌ 12 ነው
- ሐምሌ 12 ቀን ነው ትዕዛዙም የወጣው የእዚያን ቀን ነው ?
- አዎ
- ኮምፒዩተር ቁጥሩን ያስታውሳሉ ?
- አይ
- ከሣሽ ማን ይላል ካዩ አይቼአለሁ ስላሉ ነው የጠየኮት አይቼአለሁ ስላሉ ነው የጠየኮት ከሣሽ ማን ይላል ካዩ ?
- ከሣሽ የፌዴራል ምናምን የሚል እሱን ነው እንጂ ያየሁት ከሣሽ በእዚህ የፌዴራል ወንጀል ምርመራ ምናምን ነው የሚለው
- ተከሣሽስ ?
- አቶ ያሲን ኑር
- ያሲን ኑሩ ?
- አዎ በመጠርጠር ምናምን ነው የሚለው
- ቅድም ያሉት በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ጋር ከሽብር ጉዳይ ጋር የተገናኘ ነገር ይያዝ ይላል አይደል እንደነገሩን ማለት ነው ?
- አዎ
- ከእዚህ ውጪ ይያዝ የሚል ነገር ነበር ?
- አዎ ከሰነዶች ጋር ተያያዥ የሆኑ መዛግብቶች የሚል ነገር አለው እነዚህ ፁሑፎች ምናምን ማለት ለመጥቀስ ያህል መሰለኝ
- መሰለኝ ሳይሆን የሚያውቁትን እርሶ ያዩትን ?
- ብዙም አላስታውስም ብቻ እንደዚያ
- አይቼአለሁ ስላሉ ነው ቅድም ትዕዛዙን አይቼአለሁ ስላሉ ትዕዛዙ ላይ በግልፅ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከከሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው እነዚህ ወረቀቶች መፅሔቶች
- ትዕዛዙ ይሄንን ይላል አይደለም እነዚህ ነገሮችን እንዲያዙ ነው ያዘዘው ፍ/ቤቱ ስለዚህ እነዚህ መፅሔቶች እና ጋዜጦች ፖሊስ አንብቧቸዋል ወይም እርሶ አንብበዋል ?
- እየተነበቡ ነበር
- መፅሔቶቹ በሙሉ ?
- አዎ ከላይ ከላይ እየተነበቡ ነው
- ጋዜጦቹም ተነበዋል ?
- ጋዜጦቹም የተወሰነ እያነበቧቸው
- ሲዲዎቹም ተነበዋል ታይተዋል ?
- ሲዲዎቹን የተወሰነ እየታየ ነበር
- እየታየ ነበር ከሽብር ድርጊት ጋር እንደሚያያዙ አረጋግጠው ነው የያዙት እርግጠኛ ኖት በእዚህ ?
- አዎ
- በምን አረጋገጡ ?
- ያው ድምፃችን የተወሰነ ስብሰባ ነገር እያየን ነበር አንደኛው ሲዲ ላይ በመሀል በእዚህ በመስኪድ ውስጥም የተቀረፁ ነገሮች ነበሩ ረብሻ እነዚህ ድንጋይ ምናምን እንትን የሚሉ እነሱ ሁላ ነበሩ
- በሲዲዎቹ ላይ እነዚህ ነገሮች ታይተዋል ?
- አዎ
- ቅድም ካሚል የራሱን ላፕቶፕ ይዞ እንደመጣ ነግረውናል ፕሪንት የተደረገው ግን ቢሮ በነበረው የጠረቤዛ ኮምፒዩተር ነው ብለዋል ይሄ ኮምፒዩተር የማን ነው ንብረትነቱ የማን እንደሆነ በወቅቱ አጣርታችዋል ?
- አላጣራሁም
- መጀመሪያ እንግዲህ ካሚል የራሱን ላፕቶፕ ከፈተ ከእዚያ ተነስቶ ሄዶ ነው እዚያ የከፈተው ኮምፒዩተሩን ትልቁን ?
- አዎ ከእኔ ኢሜል ላይ የወጣ ነው ብሎ ነው እንትን ያለው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ላፕቶፑ 2 ገፅ ላይ ነዋ ?
- ከላፕቶፑም ከእዚያም
- ያኛው ትልቁ ኮምፒዩተር ተከፍቶ ነበር ወይስ ካሚል ነው የከፈተው ?
- ቁጭ ብሎ ነበር ከገባ በኋላ ይሄንን ከተነጋገርን በኋላ ነው እሱ ነው እንግዲህ የከፈተው
- ተልቁንም የከፈተው እሱ ነው ?
- አዎ
- ትልቁን እንዲከፍት ፖሊስ አልነገረውም በምን አወቀ ላፕቶፕ ይዞ መጣ ?
- አዎ
- ከፍተህ አሳያቸው አልተባል እንዴ ?
- አዎ ያለውን ነገር እነዚህ ሰዎች እንግዲህ ብሎ ነው የነገረው በታዛቢነት ለፍ/ቤት ማረጋገጫ የሚሆኑ ናቸው ስለዚህ ያለውን ነገር አስረዳቸው እና እንትን በላቸው አለው እሱ ነገረን ለእኛ ከእዚያ በኋላ እንደሚፈርምበት እራሱ ተናገረ ከእዚያ ቀጣይ እኛ እንደምንፈርምበት ገለፀልን
- እኮ ተነረው ከእዚያ ይዞ የመጣውን ላፕቶፕ ከፈተ ?
- አዎ
- 2 ገፅ ወጣ ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላ ያለውን ሂደት በምን አውቆ ነው ተነስቶ ትልቁ ኮምፒዩተር ጋር ማን አዞት ሄደ ?
- ተነግሮታል ያለውን ነገር ሁሉንም ነገር እንደሚያወጣ እራሱ ነግሮናል እንግዲህ ይነገረው አይነገረው እኔ እዚያ ቦታ ላይ እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ ግን እራሱ ነው ለእኛ የነገረን
- ማን እራሱ ማለት ?
- ከሚል
- እኮ ከላፕቶፕ ጨርሶ ወደ ትልቁ ኮምፒዩተር ትልቁ ኮምፒዩተር ፈቀቅ ብሎ ነው እሱ ከነበረበት ቦታ ፈቀቅ ብሎ ነበር አይደል ጠረቤዛ የነበረው ?
- አዎ ብዙም የአንድ ወንበር ልዩነት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ወደ አዚያ እንዴት በምን ምክንያት ሄደ ሂደ እና አዚያ ላይ ከፍተህ አሳይ አላቸው ፖሊስ ያዘዘው ነው እራሱ ምንም ሳይታዘዝ ከውጪ እንደመጣ ይሄንን ጨርሶ ወደ አዚያኛው ሄደ እንዴት ነበር እርሶ ታዛቢ ስለነበሩ ?
- አዎ አውጣ ይሄ የትዕዛዝ ቃል የተገለፀለት የለም እራሱ ነው እራሱ ነው ሁሉን ነገር ሲነግረን የነበረው
- 2 ገዐ አውጥቶ ከአዚያ ወደ አዚያኛው ሄዶ
- ከአዚያ ወደ አዚያኛው ሄደ አዎ
- በራሱ ?
- በራሱ
- ሚካኤል የያሲን ቤት ሲፈተሽ የተሰበረ በር ነበር ?
- አዎ
- የተሰበረ በር ነበር እሺ መጀመሪያ ላይ በሩን የከፈተልን ወንድምየው ነበር ለምንድን ነበር ፖሊሶች ይዘውት የሄዱት ?
- ማንን
- ወንድሙን በሩን የከፈተላችሁን መጀመሪያ ለምን እንደሆነ ያወከው ነገር አለ አንተ ስትወጡ ?
- ስንወጣ ያው እኔ እሱን ባላውቅም እንዳለ እቃውን ተይዞ እሱም ባለበት ተያይዘን ወጣን ለምን እንደሄደ አላውቅም
- ለምን እንደወሰዱት አታውቅም ጨርሰናል
- ድጋሚ ካለ ?
- ድጋሚ የለንም
- ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- አዎ እሺ ስምዎን የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ ይነግሩናል
- አንለይ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ 94ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ በ 161 ላይ የተጠቀሰው አቶ አንለይ ቀርቧል ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ አንለይ ?
- አቶ የሱፍ ጌታቸው
- የሱፍ ማን ነው ?
- የሱፍ ጌታቸው
- ሌላስ ?
- በእሳቸው ብቻ
- የሱፍ ጌታቸውን ያውቁታል ?
- አዎ
- ማሳየት ይችላሉ አሁን ተነስተው ማሳየት ይችላሉ የት ከኋላ ከፊት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ትክክል ነው ስንተኛ ኖት ከየሱፍ ጌታቸው ላይ ቅሬታ ወይም ዝምድና ነገር አላችሁ ?
- ምንም የለም
- ምንም የለም ?
- አዎ
- ምን ሲፈፅም ነው ያዩት እስቲ አጠር አድርገው ይንገሩን ?
- ሲፈፅም ሳይሆን ያው በእንትን ላይ የሆነ/ግልፅ ያልሆነ/ ማለት ሐምሌ 12 ነው ሐምሌ 12 እዚያው አካባቢ እነሱ ሰፈር አካባቢ የሆነ ካፌ ስላለ እዚያ ቆይተን ስንመጣ ፖሊሶቹ ጠሩን እና ያው አቶ የሱፍ ቤታቸው ከእነሱ ጋር ማለት የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንደያዙ እና ፌዴራል ፖሊስ አባላት እንደሆኑ ነግረውን ከእዚያ በኋላ ከእነሱ ጋር ከሄድን በኋላ በር ጋር ስንደርስ ተንኳኳ ሲከፍቱ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይዘናል እና አቶ የሱፍ ጌታቸው በሽብር
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- አቶ አንለይ ይሄ የት ነው ቦታው ቦታው የት ነበር ?
- የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ሾላ አካባቢ ዲሲ ሰፈር የሚባል ማለት ነው
- በእዚህ ዕለት አሁን ቀድም እንደገለፁት የፍ/ቤት ትዕዛዝ ተነበበ ከተነበበ በኋላ ገባችሁ ምን አገኛችሁ ምን ተገኘ ?

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ግልፅ ያልሆነ/ _
- የፍ/ቤት ብርበራ ትዕዛዝ ተነበበ ብለዋል ?
- አዎ
- በመቀጠል ምን ተደረገ እንዴት ገባችሁ ከእዚያ የት የት ቦታ ምን አገኛችሁ እነ ማን ነበሩ እሱን እስቲ በዝርዝር የእዚያን ዕለት ያዩትን የታዘቡትን እና የተገኙትን ነገሮች እሱን በዝርዝር ያው እንዲገልፁ ነው የምንጠይቀው ?
- ገባን ገብተን ውስጥ ቤት ውስጥ ከገባን በኋላ ማለት እሳቸውም ነበሩ ባለቤታቸው 2 ሴቶች እኔ እንዴት እንደሆኑ አላውቅም ዝምድናቸውን አላውቅም ግን 2 ሴቶችም ነበሩ 3 ሴቶች ነበሩ ማለት ነው ከእዚያ በኋላ የቁም ሳጥን ዓይነት ነገር ብዙ መፅሐፍት የተደረደሩበት ነበር ከእዚያ ውስጥ 6 ሺህ ብር እና የተለያዩ መፅሐፍት የሙስሊሞች ጉዳይ የሚል 5 መፅሔቶች የተለያዩ ጥራዞች የተለያዩ ትናንሽ ዶክመንቶች ከእዚያ ውስጥ ነው የተገኙት እንደገና ከመሳቢያ ውስጥ ሚሞሪ ካርድ ሀርድዲስከ ፍላሽዲስክ እንደገና ከሌላ እቃ መደርደሪያ ቡፌ ነገር እሱ ላይ ደግሞ አንድ ዲጂታል ካሜራ እንደዚሁ ከሸልፍ ነገር ላይ እሱ ሞባይሎች እዚያ ላይ ተደርድረው ያገኘናቸው ቦርሳ ከእንትኑ ቶሽባ ላፕቶፕም እዚያው ጠረቤዛ ላይ አብሮ ቁጭ ብሎ ነበረ እሱ የተለያዩ ከመሳቢያ ውስጥ የተለያየ የቴፕ ካሴት 69 የሚሆን ሲዲ ካሴት 56 እና ብዙ የሚሞሪ እንትን ማለት የሲምካርድ ከቨሮችም ማለትም ተሰብሮ የሚወጣለት ነገር ነበር 2 መቅረፀ ድምፅ ነበር እና እነዚህ ነው የታዘብነው
- እነኚህ ይሄ ቅድም ሲዲ ያሉት ሲዲውን አይታችዋል ይዘቱ ምን እንደሚል ?
- ይዘቱ በውስጡ ያለው ምን ይሁን ምን ይሁን አናውቅም ግን ተሰብስቦ ማለት መያዙን ነው የምናውቀው
- ይሄ ነገር ከተገኘ በኋላ ምን ተደረገ በመጨረሻ ለመተማመን ያደረጋችሁት ነገር ነበር በብርበራ?
- ጉባኤው ላይ እንትን ብሎ ተሰብስበን ሁላችንም ከተደረገ በኋላ ፈርመን ተፈራርመን ወጣን
- ማለት እኚህ ቅድም የገለፁዋቸው የተዘረዘሩት በሙሉ ተፅፈዋል ?
- ተፅፈዋል እኔ የተናገርኳቸው በሙሉ ተፅፈው ከስር ፈርመንባቸዋል
- አቶ የሱፍ ፈርሚል ?
- እኔ አላየሁም እሳቸው ሲፈርሙ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ ነበር አልነበረም ?
- ነበሩ ቁጭ ብለው
- እና ታዲያ አልፈረሙም እንዴ ?
- አላየሁም
- ትዝ አይልህም ?
- ትዝ አይለኝም አላስታውስም
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አላየሁም ሲፈርም መፈረም አለመፈረሙን አላስታውስም
- እሺ ሌላ ማን ፈረመ ?
- ከእኔ ጋር የነበሩ ልጆች ሲፈርሙ አይቼአለሁ ፤ኛውን በደንብ አይቼአለሁ ስለሌሎቹ አላውቅም
- ሌላኛው ትዝ ስላላለህ ነው ?
- አዎ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- ብርበራው ሲካሄድ የነበሩት ሴቶች የት ሄዱ ቤት ውስጥ የነበሩት 3 ሴቶች ነበሩ ብለሀል አይሰማም ?
- ይሰማኛል
- ሴቶቹ ብርበራ ሲካሄድ ወደ ውጪ እንዲወጡ ታዘዙ ?
- ቁጭ ብለዋል
- እዚያው ቁጭ ብለው ነበር ?
- የትም አልሄዱም አዎ እዚያ ውስጥ ቁጭ ብለዋል
- የት ጋር ?
- እቤት ውስጥ ነዋ እንደውም ባለቤታቸው ይሄንንም ከፈቱ ይሄንንም የት እንደውም ... ስርዓት እንትን ሲሉ የነበረው
- ስንት ፖሊስ ነበር ወደ ውስጥ የገባው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብዙት አላስታውስም
- ፖሊሶች ምን ይዘው ነበር ሲገቡ ?
- ማለት የፍ/ቤት ትዕዛዙን ወይስ መሣሪያ ምናምን ነው ወይስ ምንድን ነው
- ከመሣሪያ ውጪ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይዘዋል ?
- አዎ
- ከእዚያ ውጪ ቦርሳ ነገር ?
- አይ ምንም የለም
- ምንም የያዙት ነገር የለም ?
- ምንም ያየሁት ነገር የለም
- እሺ እነዚህን እቃዎች በብርበራ ከየቦታው ካገኛችሁ በኋላ የት ጋር ነው የሰበሰባችሁ አንድ ላይ?
- እዚያው እቤት ውስጥ
- ቤት ማለት ሳሎን አለ መኝታ ቤት ?
- ሳሎን
- ሳሎን ተሰበሰቡ ?
- አዎ
- ተሰብስበው ተከሣሹ እንዲቀመጥ ተደርጎ አልተቀረፀም በቪዲዮ ?
- አላየሁም
- አቶ አንለይ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ አይተውታል እርሶ ?
- አብረን ቆመን ነው የተነበበው
- ተነበቦሎት እንጂ አላዩትም ?
- ወረቀቱን እያየሁት ነው ይዘቱን ግን አላነበብኩትም
- ይዘቱን አላነበቡም ከየት ፍ/ቤት እንደመጣም አላዩም ?
- ከምን እንደመጣ ከየትኛው ፍ/ቤት ይታዘዝ
- ከየት እንደመጣም አላዩም ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዝርዝር ሁኔታውን አላወቅም
- እሺ ምን ይያዝ እንደሚልም አላዩም ?
- ምን ይያዝ እንደሚልማ መጀመሪያ ተነግሮናል የጦር መሣሪያ
- የምጠይቆት እኔ የፍ/ቤቱን ነው የፍ/ቤቱን ነው እርሶ የሚያውቁት ወይስ /ግልፅ ያልሆነ/ ?
- እኔ እራቤ ሁሉም ሲዘብቡልን መጀመሪያ ሲናር ይችላል ተብሎ የተገመተው ጦርመሣሪያ ኤሌክትሮኒክስ እና የተለያዩ የሽብር ፈጠራ ሊያገለግሉ የሚችሉ ዶክመንቶች ካሉ የሚል ስለነበረ
- እነዚህ አሁን እርሶ ያሏቸው ሲነበብ የሰሟቸው ለሽብር የሚያገለግሉ ነገሮች የጦር መሣሪያ ተገኝተዋል እዚያ ቤት ?
- የጦር መሣሪያ አልተገኘም ኤሌክትሮኒክስ ግን ሞባይሎች እና ካሜራዎች ላፕቶፕ ተገኝቷል
- እነዚህን ነገሮች ቅድም ተገኙ ያሏቸውን ሲዲዎች ካሴቶች አይተዋቸዋል እርሶ ይዘታቸውን ?
- ውስጣቸውን አላውቅም
- አላዩም?
- በአካል ግን እንደዚሁ እንትኑን ነው ያየነው እቃውን ነው ያየሁት
- ውስጣቸውን አላዩም ?
- ውስጣቸውን አላየሁም
- ቅድም ገንዘብ ተይዟል ብለው ነበረ ?
- አዎ
- ይሄም የተያዘው ለሽብር ድርጊት ያገለግላል ተብሎ ነው ?
- እሱን አላውቅም ግን ከውስጡ ተገኝቶ ያው 6 ሺህ ብር በወረቀት ውስጥ ነው በመፅሐፍ ውስጥ
- እርሶ እኮ አቶ አንለይ ታዛቢ ኖት አይደል ?
- አዎ
- እርሶ እዚያ የተገኙት በፍ/ቤት ተዕዛዝ መሠረት ለመፈፀም ነው ሲፈፀም ለማየት ነው አሁን እንዳሉት የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ከሽብር ድርጊት ጋር የተያያዘ ነገር ካለ የተገናኘ ነገር ካለ እንዲያዝ ነው ብሩ ለእዚያ አገልግሎት የተያዘ ነው ?

ECLN

- እሱን አላውቅም
- አያውቁም
- ሲዲዎቹንም ስላላዩዋቸው ከእዚህ ጉዳይ ጋር ይገናኙ አይገናኙ የሚያውቁት ነገር የለም እርሶ ?
- እሱን ያው ምንም ይዘታቸው ውስጡ ምን ይሁን
- አላዩም ?
- ምን እንዳለ አላውቅም
- ስንት ሰዓት ጀመራችሁ ፍተሻውን ?
- ለ 12 20 ጉዳይ ሩብ ጉዳይ አካባቢ ነው
- የጀመራችሁት ?
- አዎ
- ያለቀውስ ?
- እስከ 6 ሰዓት ከሩብ 20 አካባቢ
- ከምሽቱ ?
- እዎ ፖሊሶቹ ተደዋወሉ እና ምን እንዳሉ የት እንደደወሉ አላውቅም ግን
- ቆይ እኔ የምጠይቆትን እሱን ይደርሱበታል እስከ ምሽቱ 6 ሰዓት ድረስ ቆያችሁ ?
- አዎ
- የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ግን እንደዚያ ይላል ቅድም ሰምቼአለሁ ስላሉ ?
- የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ 11 እስከ 12 ሰዓት እንደዚያ ነገር ነበር የሚለው በደንብ አላስታውስም ግን ያው
- እስከ ስንት ሰዓት ይላል ?
- መጨረሻውን አላስታውስም በደንብ ግን እስከ 12 ሰዓት አካባቢ እንደዚያ መሰለኝ እስከ 11 ተኩል እስከ 12 ሰዓት ይሆን አላስታውስም በደንብ ግን ያው ፖሊሶች እየተደዋወሉ ስለነበር ምን እና ምን እንዳሉ የት እንደደወሉ ስለማናውቅ ብቻ አብረን ቆመን እስከሚጨርሱ ታዝበናል
- ፖሊሶች ደውለው ነው የቆዩት ነው የሚሉን አቶ አንለይ እርሶን ነው ፖሊሶች ደውለው ነው የቆያችሁት እዚያ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት እኛ የቀኑን ሰዓቱን አለፈ ይለፍ አይለፍ የሚወን ነገር መጨረሻውን እኛ ማለት እንትን ስከመጨረሻው ድረስ መቆየት ስላለብን እነሱ የደወሉት ለፍ/ቤትም ይሁን ለፖሊስ ምን ትዕዛዝ እንደሆነ እኛ የምናውቀው ነገር የለም ግን እስኪጨርሱ አብረን ቆይተን ታዝበናል
- መደወላቸውንም የት እንደደወሉም አያውቁም እርሶ ?
- አዎ መደወላቸውን አውቃለሁ የት እንደደወሉ ግን ለላውቅም
- ስለዚህ አቶ አንለይ የተያዙት እቃዎች ከፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ጋር የተገናኙ አይደሉም ማለት ነው አይደል ?
- ናቸው ነው የምለው እኔ ማለት
- አስተያየትዎን አይደለም ካዩት ነገር ጋር ?
- ናቸው በቃ ኤሌክትሮኒክሶች የተጠቀሱት ናቸው
- አላዩዋቸውም ?
- ዶክመንቶቹ የተጠቀሱት ናቸው ውስጣቸውን ንባባቸውን ባላውቅም ያው ስለተጠቀሰ ናቸው ብዬ ነው እኔ የምወስደው
- እስቲ ብሩንስ ምን ይላሉ
- መለሱ እኮ ቅድም
- አይ ብሩን አልጠየኳቸውም ያው ስለሲዲው ነው ቅድም የጠየኳቸው
- ስለ ብር ተመልሷል ተጠይቆ ተመልሷል ከሹብር ጋር ይገናኝ አይገናኝ ሲባል አላውቅም ብር ተይዟል
- ላፕቶፑን አሽጋችሁት እንዴ ፈርማችሁ አሽጋችሁታል በብርበራ ካገኛችሁት በኋላ ?
- አልታሸገም
- አልታሸገም?
- አዎ
- ወደ በር ስትገቡ ከፖሊሶች ጋር አብረህ ነው የገባኸው አንተ ?
- አዎ
- 12 ሰዓት ሆኗል በሩን አልከፍትም ብሎ ነበር አይደል ?
- አላሉም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሱፍ እንደሱ አላለም ?
- አላለም እኔ አልሰማሁም
- እሺ አንተ በር ላይ ደርሰህል ከፖሊሶቹ ጋር አብረህ ?
- አብረን በር ላይ ተሰብስበናል
- እሱ ላይ ተሰብስባችሁ ከውስጥ በሩን ገፍቶ የያዘው ሰው አልነበረም ?
- አልገፋትም ስናንኳኳ ፖሊስ አንኳኳ ተከፈተ ከእዚያ በኋላ የፍ/ቤት ትዕዛዙ ተነበበ ገባን
- መሣሪያ ይዛችሁ እቤት ውስጥ አትግቡ ሲሉስ አልነበረም መሣሪያ ይዛችሁ እቤት ውስጥ አትግቡ ሲሉ ነበር አይደል ?
- አልሰማሁም
- አልሰማህም ይሄንን ?
- አዎ
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ካለ ?
- ድጋሚ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ

ትዕዛዝ

- ቀሪ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች አስቀድሞ በተያዘው መሠረት ቀሪ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ለሚያዝያ 7/2005 ቀጠሮ ተይዟል ዛሬ የተሰሙት የምስክሮች ቃል ይቅርታ ለግንቦት 7/2005 ቀጠሮ ተይዟል ዛሬ የተሰሙት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ተገልብጦ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ትዕዛዝ ትዕዛዝ ተሰጥቷል ቀሪውን ምስክር ለመቀጠል ለነገ 3 ሰዓት ተኩል ቀጠሮ ተይዟል የዛሬውን በእዚሁ አጠናቀናል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የ.መ.ቁ 124754

ቀን 7/9/2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብስራት ተዕልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ፡- ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወ/ማገኝ ዘረሰናይ ምስግና ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርበዋል

ተከሣሾች፡- እነ አቡበከር አህመድ ከማረሚያ ቤት የቀረ ተከሣሽ አለ የቀረ ተከሣሽ የለም

ጠበቆች ባህሩ መካንጋ ፣ መሐመድ አብደላ፣ ሀሰን ሁሴን አዲስ መሐመድ ቀርበዋል ልክ ነው

- መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ቀሪ የዐቃብ ሕግ ምስክር ለመስማት ነበር ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቅርባችዋል ስለዚህ ይቅረቡ ዐቃቤ ሕግ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ከዐቃቤ ሕጎች መካከል አቶ ብርሃኑ ወንድማኝ መሰየማቸው ቀሪ ሆኖ አቶ ዘረሰናይ እና አቶ ቴዎድሮስ ተሰይመዋል
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- በፍ/ቤቱ በ 95ኛ ተራ ቁጥር በዐቃቤ ሕግ ቁጥር ስንት ናቸው 91 ላይ የተጠቀሱት ምስክር የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ይነግሩናል የመጀመሪያ ስምዎ ማን ነው ?
- አደም
- ለምንድን ነው የመጡት ?
- በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ መሠረት ምስክርነት /ግልፅ ያልሆነ/
- በእነ ማን ላይ ነው የሚያስረዱት ?
- በእነ አቡበከር አህመድ እና ጓደኞቻቸው
- በማን ላይ በተለይ ?
- ሁሉም ባልደረቦቼ ናቸው

4034

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሁሉም ላይ ነው ?
- ሁሉም ባልደረቦቼ ናቸው
- እኮ በሁሉም ተከሣሾች ላይ ?
- በጓደኞቼ ላይ ማለት ነው
- እኮ ማን ማን ናቸው ?
- በኮሚቴዎቹ በአቡበከር አህመድ
- እሺ አቡበከር ?
- አህመድ
- አህዲን ጀባል ካሚል ሸምሱ ፣ ሀጂ ሱልጣን አማን ፣ /ግልፅ ያልሆነ/ ሁሴን ፣ ጀማል ያሲን በቃ እነኚህ ናቸው
- እነኚህ ናቸው ያውቋቸዋል ?
- አዎ አውቃቸዋለሁ
- ሊያሳዩን ይችላሉ ?
- ጓደኞቼ ናቸው በሙሉ ከፈሎቼ አስተማሪዎቼ ከፈሎቼ ተማሪዎቼ ከፈሎቼ የማመ የመድረክ ባልደረቦቼ ናቸው
- እና እና ማለት ወይ አሳዩና ተነሱ የሚጠቋሟችሁ ሰዎች ተነሱ
- አቡበከር አህመድ
- ቆይ /ግልፅ ያልሆነ/ የተጠቆመ 6 ሰው ብቻ ነው የተጠቆመውን
- ካሚል ሸምሱ ፣/ግልፅ ያልሆነ/
- ልክ ነው ምስክሩ በዝርዝር የጠቀሷቸውን ተከሣሾች ከእስረኞች መካከል ለይተው አሳይተዋል ከእነዚህ ተከሣሾች መካከል ፀብ ወይም ዝምድና አላችሁ ?
- ምንም የለንም
- ምን አደረጉ ተብለው ነው የተከሰሱ ያውቃሉ ?
- ኮሚቴ የሙስሊም አፈላላጊ ኮሚቴ ተብለን ተሰይመን ነበር /ግልፅ ያልሆነ/ ከእነሱ ውስጥ እነሱ ተያዙ የተወሰን ደግሞ አልተያዝንም
- እሺ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

2884

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ፕሮፌሰር እስቲ ኮሚቴ ላይ አብረን ነበርን ብለዋል እስቲ ከማን ከማን ጋር ነበረ በኮሚቴነት የሰራችሁት ?
- ከ17ቱ ጋር አብረን ሰርተናል
- ፕሮፌሰር ነው ያሉት ፊትዎን ወደ እኛ ብቻ
- 17ቱ ጋር አብረን ሰርተናል
- የምን ኮሚቴ ነበር ይሄ ኮሚቴ ?
- የሙስሊሙ ጥያቄ አፈላላጊ ጥያቄ አፈላላጊ ኮሚቴ የሚል ነው የተሰየመው
- መቼ ነው የተቋቋመው በማን ነው የተቋቋመው እንዴት ነው የተቋቋመው እስቲ ይሄንን ?
- አወሊያ በተሰበሰበው ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ጥቆማ የተመረጠ ኮሚቴ ነው
- እርሶ በምን አግባብ ተመረጡ ?
- በአጋጣሚ እኔም ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ ተጠቁሚ /ግልፅ ያልሆነ/ አቡበከር አህመድ ተጠቁመሀል እና ተመርጠሀል ሲለኝ እኔ የጤና ችግር ስላለብኝ በኮሚቴው መስራት አቅሙ ስለሌለኝ ግን በተወሰነ ሰዓት መሳተፍ እችላለሁ የሙስሊሙ ጥያቄ እስከሆነ ድረስ የሚለውን መልሼለት በቃ አንተ በአማካሪ ሲመችህ ከጤናህም ችግር በማይፈጥርብህ ደረጃ ሲኖር በስብሰባ ትገኝልኛለህ የሚለውን በእዚያው መሠረት የእኔ መገኘት ውስን ነበር በጣም በሰፊው የተገኘሁበት ጊዜ አልነበረም
- እስቲ ምናልባት ጥያቄው እጠር እያደረጉ እንዲመልሱልን አወሊያ ግን ነበሩ እንዴ እርሶ ምርጫ የተካሄደ ቀን ?
- የለሁም
- ማን እንደጠቆሞት የሚያውቁት ነገር የለም ?
- አዎ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ተጠቁመሀል ጠቁሞሀል የሚለውን ነው የደረሰኝ
- እንጂ ቦታው ላይ ሆነው በኮሚቴ ወይም በሕዝብ ስለመመረጥዎ ?
- የማውቀው ነገር የለኝም
- እሺ እስቲ ከእዚያ በኋላ ምን አደረጋችሁ አቡበከር ይሄንን ነገር ከነገሮት በኋላ ከእዚያ ምን አደረጋችሁ ?

2805

24D36

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የኮሚቴው ዓላማ በሙሉ እንጊያ ያሉትን 3 ጥያቄዎች ለመንግስት አቀርቦ በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኝ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ተረጋግቶ ጥያቄውን መልስ እስከሚያገኝ ድረስ ትዕግስት አድርጎ እንዲጠብቅ የማሳመን የማስተማር የመግለጫ ምክንያቱም የተለያዩ የመንግስት አካላቶችን እያነጋገርን ስለሆነ ትክክለኛው መልስ እስከሚገኝ ድረስ ትዕግስት አድርጎ እንዲጠብቅ የማለውን እንቅስቃሴ ነው ሲካድ የነበረው
- የት ነበር የተሰበሰቡ የነበሩት ?
- የተለያዩ ቦታዎች ናቸው የምንሰበሰበው 1ኛ ኩርቱ ሕንፃ እንሰበሰብ ነበር ከእዚያ አልቤር 2ኛ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ እነኚህ 3 ቦታዎች ላይ እኔ
- ምንድን ናቸው እነዚህ ቦታዎች ?
- የመጀመሪያው /ግልፅ ያልሆነ/ ጽ/ቤት ነው ሌላኛው የልማት ድርጅቶች ናቸው ምክንያቱም የኮሜቴ አባላቶች ስለሆኑ እነሱ ስራ በማይኖርበት ሰዓት በተለይ በእረፍት ቀን ቅዳሜ እና እሁድ እዚያ እየተሰበሰብን እኔ በምገኝበት ሌላ ካለ አላውቅም እኔ የተገኘሁት በእነዚህ በ3ቱ መድረኮች ነው
- ከኮሚቴው ከሌሎች ኮሚቴ አባላት ጋር ከእዚህ በእዚህ የኮሚቴ ስብስብ ከመተዋወቅዎ በፊት ከእዚህ በፊት እንዴዚህ በነበሩ ስብሰባዎች ላይ አብረው ይገናኙ ነበር እንዴ ?
- እኔ እና ምክንያቱም እዚህ ውስጥ ካሉት የተወሰኑት አስተማሪዎቼ ናቸው ብዩአለሁ ተማሪዎቼም አሉ ብዙዎቹ ግን አብረን በመድረክ ይሄ የሙስሊሙን ጉዳይ
- እርሶ ይገናኙ ነበረ
- አብረን እየተሰበሰብን እንገናኝ ነበር
- የየትኛው ጊዜ ጀምሮ ማለት ከአወሊያ በፊት ነው ?
- ከእዚያ በፊት በተለያዩ ጊዜ እንገናኛለን ሌላው ቀርቶ በ2002 እኔ እና /ግልፅ ያልሆነ/ አቡበከር ደሴ እና ኮምቦልቻ በተካሄደው የኢሀዴግ ምርጫ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ኢሀዲንግ እንዲመርጥ ቅስቀሳ አድርገን አካሂደናል የእዚያም ውጤት ምናልባት
- በእዚያን ጊዜ ጀምሮ
- ጠቅላይ ሚኒስቴር ገልፀውታል ደሴ እና ኮምቦልቻ ለመጀመሪያ ጊዜ መረጠን ያሉን
- ይኸሉት ፕሮፌሰር ከክሳችን ስለሆነ እንዲያስረዱ ክሳችን ስለሆነ እዚህ ችሎት ላይ የምናስመስከረው ከጭብጥ ባይወጡብን ጥሩ ነው እስቲ እነዚህ ዳዋ እና እውቀት እና

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ኤልበር.ጄ.በሎምምንት የሚባሉት ድርጅቶች የኮሚቴ አባላቶች አሉ ብለዋል ማን እና ማን ናቸው እዚያ ውስጥ የሚሰሩት ?

- ኤልቨር ሼህ ሱልጣን ናቸው
- ሼህ ሱልጣን ሙሉ ስማቸውን ያውቃሉ ?
- ሱልጣን ሀጂአማን
- ሌላስ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ሼህ ጣሂር አብዱርቃድር ናቸው ማን ነው ዳዋ እኔ ዳዋ እና ሰካፋ የሚለውን ነው ሌላውን ስያሜ ያወኩት ማዕከላዊ በቀበሌ በተየፈው ደብዳቤ ባየሁት ነው ሌላ ስያሜ መኖሩን እዚያ ድርጅት ውስጥ እዚህ እኔ የማውቀው ዳዋ እና ሰካፋ የሚለውን ነው
- እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ነበር የምትሰበሰቡት ?
- የተወሰነ ጊዜ ቅዳሜ ቀን እሁድ ቀን እንሰበሰብ ነበር
- የስብሰባችሁ ቀን ቅዳሜ እና እሁድ ነው እንዴ ?
- እንግዲህ የአወሊያ አጀንዳ እንደሚታወቀው አርብ ቀን ነው የሚካሄደው ፀሎቱ ሙስሊሙ ሕብረተብ የሚሰበሰበው አርብ ነው ስለዚህ ያ ስብሰባ በሰላማዊ መንገድ እንዲሄድ ሐሙስ ቀን ምን መደረግ እንዳለበት ተገናኝተን እንወያያለን
- ሀሙስ ሀሙስ ትገናኛላችሁ ?
- ሀሙስ ከ ॥ ሰዓት በኋላ 2ኛው ስብሰባ የሚካሄደው ቅዳሜ ቀን ነው ቅዳሜ ቀን የምንገመግምበት ቀን ነው ማለት ያ ስብሰባ በሰላማዊ መንገድ መካሄዱን እና ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ ምን ጥያቄ መጣ ምን ቀረበለት የሚለውን የምናይበት ቀን ነበረ
- ስለዚህ የምትሰባሰቡት ሀሙስ ቀን ለአርብ ዝግጅት ለማድረግ
- አዎ ለአርብ ዝግጅት
- እንደዚሁም አርብ ላይ የሆነው ነገር ለመገምገም ቅዳሜ ትገናኛላችሁ እስቲ እንዴት ነበር እኚህ ስብሰባዎች እዚያ ቢሮ ውስጥ የሚካሄዱት ምን ምን ነበር የሚካሄደው ለብስበባው ሚያስፈልጉ ሌሎች ወጪዎች በማን እንደሚሸፈኑ እስቲ በዝርዝር ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብዙ ውጪ የለውም ምክንያቱም ነኛ ሁሉም ምሳ በልቶ ነው የሚመጣው ሲቀርብ የነበረው ቆሎ ውኃ ሻይ ነው ስለዚህ የድርጅቶች ባለቤቶችም ያቀርቡ ነበር እኔም ተሳትፎ አድርጌአለሁ ሌሎችም ተሳትፎ ያደርጉ ነበር
- እርሶ በየስብሰባው ላይ ይገናኙ ነበር እንዴ ሁሉም ስብሰባዎች ላይ ይገኙ ነበር ?
- አልገኝም ጠቅሼአለሁ የጤና ችግር ስላለብኝ የልብ ኬዝ ስላለብኝ እኔ አማካሪ ነበር ኃላፊነቴ ስለዚህ በሁሉም ላይ አልገኝም የተወሰኑ ሰዓቶች ቀናቶች ነበር የምገኘው
- በሁሉም በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ስምምነቱን ያረጋግጡ ነበር እርሶ የሚቃወሙት ወይ የተለየ ነገር አለ ስብሰባዎች ላይ ?
- ከሰላም የሚያወጣ ነገር ካለ እቃወም ነበር ግን እስከእዚያ ዕለት ድረስ አልተከሰተም
- እቃወም ነበር ሲሉ የተቃወሙት ነገር አለ ?
- አዎ ምክንያቱም አማራጭ አለ ምናልባት እኔ አቋሜ የሰጡሁበት የመጨረሻው ቀን ስብሰባ አወሊያ ሰደቃ ይሁን ሲባል እሁድ ቀን ነበር ሊካሄድ የታሰበው ያ ቀን የአፍሪካ አንድነት ስብሰባ ስለሆነ እሱ ተራዝሞ ወደ እሮብ ቢሄድ የተሻለ ነው መካሄድ የለበትም የሚል አቋም ወስጄ የተወሰኑ ኮሚቴ አባላት ሁሉም አልተሰባሰቡም ነበር
- ማን ማን ነበር የተሰበሰበው የእዚያን ቀን ?
- አህመዲን ጀባል ነበር አህመድ አቡበከር አለ ሀጂ ሱልጣን አማን አሉ ሀጂ መከተ አሉ ብዙም አልነበሩም በዕለቱ ሀጂ ሁሴን አለምዳ አሉ ያ የተወሰኑት ሲስማሙ የተወሰኑት ደግሞ ምክንያት አቀረቡ ምክንያቱም ረመዳን ሊገባ 4 ቀን ስለቀረው ጊዜ የለንም እና መካሄድ አለበት የሚል አቋም ነበራቸው ያንን ተቃውሜአለሁ
- እሺ ሌላ ፕሮፌሰር እነዚህ ኮሚቴው ሰላማዊ መፍትሔ ለማፈላለግ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መሄድ ነው ብለዋል እርሶ የእዚህ ኮሚቴ አባል ከመሆንዎ በፊት ሌሎች የቡድኑ አባል ሕቡህ የሆነ አጀንዳ ማለት የሽብር /ግልፅ ያልሆነ/
- አላውቅም እሱን አላውቅም
- ቆይ ቆይ እንግዲህ ያው ተመልሷል እንግዲህ አይ እሳቸው ስለፈጠኑ ነው እንጂ የእናንተ ጥያቄ ዘግይቷል ማለት አይደለም ግን ያው ይሄ ማንንም የሚጎዳ አይደለም ቀጥሉ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እርሶ የምትገናኙበት ጊዜ ውስን ነበረ እንደዚሁም በጤና እክል ምክንያት ሁሉም ስብሰባዎቹ ላይ አልገኙም ብለዋል እርሶ ባልተገኙበት ስብሰባ ላይ የተወሰኑ ሁሉንም ውሣኔዎች ያውቃሉ እንዴ እርሶ ?
- ሁሉንም ውሣኔዎች አላውቅም ግን ሳውቅ የነበረው በሰላማዊ ጉዞ ምክንያቱም ከ 600ሺህ በላይ ሕዝብ ተሰብስቦ ድንጋይ ሳይወረወር በሰላም መበተኑን ያ ነበር መለኪያዬ እና የቀረበትን ጥያቄ ለመንግስት አካል አይ ነበር ለማን እንደሄደ ለማን እንደቀረበ ለማን እንደተላከ እና ማን እንደሚከታተል ይገልፁልኛል ያንን አውቃለሁ
- ፕሮፌሰር እስቲ የኮሚቴውን ተዋፆ ይንገሩን የኮሚቴ 17 ኮሚቴ ነበረን ብለዋል እስቲ የኮሚቴውን ከየትኛው ከየትኛው ሕብረተሰብ ክፍል እንደነበር ይንገሩን ስብስባችሁን ማለት ነው ?
- እኔ እዚህ ላይ ይቅርታ ብሔሮችን የማወቅ ሁኔታ ላውቃቸው አልችልም
- አይ ቆይ ቆይ ብሔር አይደለም ብሔር አልጠየኩም ማለት
- በዕድሜ ደረጃ በዕድሜ ደረጃ ከፈሏቸው
- በዕድሜ ደረጃ ሳይሆን
- በምንድን ነው የፈለጋችሁት ማለተ ወይ የተማረ ያልተማረ ?
- አዎ በእዚያ ነው ልገልፅሎት የፈለኩት ብሔር አልጠየኮትም ብሔር ሳይሆን ከዕድሜ ከስራ ዘርፍ ከምትሰማሩበት የስራ ዘርፍ እንዲሁም ከሙያ አንፃር ማለት ነው
- እኔ እስከማውቀው ድረስ በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነታቸው አለ የሚባለውን መለኪያ ያደረገ ይመስለኛል ጥቆማው የተካሄደው ማለት በዳዋም በሰበካም ማለት ነው በዕድሜም አኳያ አዛውንቶች ነበሩ አሎማዎችም አሉ ሙሁራኖችም አሉ ሁሉንም ያካተተ ነበር
- እስቲ ይንገሩኝ ለምሳሌ ከሙሁራን ማን ማን ነበር ?
- ከሙሁራን አህመዲን ጀባል፣ አህመድ ሙስጠፋ ፣ አቡበከር አህመድ እነኚህ ያሉበት ናቸው ሌላው ደግሞ አለ እንደዚሁ በዝረዲን እራሱ ኢንጅነር ነው የተማረ ነው በእዚህ ሙሁራኖችን ያካተተ ነው
- እሺ ሌላስ ?
- ጀማል ያሲንም ከሙሁራኖቹ ይቀጠር ነበር

2889

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሙሁራን እዚህ ነዋሪ በሊላውስ ?
- ከአዛውንቶች ሁሴን ላለምዳ ፡ ሀጂ ከማል ነበሩበት ሀጂ ሱልጣንም ከዕድሜ ባለፀጋዎች እና ከአሎማዎች ነው የምንቆጥራቸው /ግልፅ ያልሆነ/ ጣሂር አብዱርቃድርም ከአሎማዎች ናቸው የምንቆጥራቸው
- ሲላስ ከጠጣት ከአስተማሪዎች ከኦይሞሮን አስተማሪዎች ?
- ሌሎች የማውቃቸው እንግዲህ እኔ በጓደኝነትም በመድረክም አሉ ከሚባሉ የማውቃቸው ሰይድ አሊም ይኖራል መስኪድ ኢማም እነኚህን ያካተተ ነበር እነኚህ ናቸው በጉልህ የማውቃቸው
- /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ሲነግሩኝ በሙሁራን ከአዛውንቶች አሁን ከአስተማሪዎች ደግሞ የተወሰኑ ጠቅሰዋል አሁን በችሎት ተናገሩ ወይም ጠቁም ሲባሉ 6ቱን ነው የሚያውቋቸው ሁሉንም የኮሚቴ አባል አያውቋቸውም ማለት ነው ?
- አውቃቸዋለሁ ይሄንን ያካተተ ነበር ማለት ነው እንጂ እንግዲህ እኔ ያለኝ ስብሰቡ እና ወይም ተሳትፎ ውስን ስለሆነ ሁሉንም በዝርዝር የመረዳት ሁኔታ ሊያስቸግረኝ ይችላል
- ቅድም ሲነግሩን መጀመሪያ ሲጀምሩ እንዴት እዚህ ኮሚቴ ውስጥ ተካተቱ ሲባሉ ኡስታዝ አቡበክር የሕዝበ ሙስሊም ጠቁመሀል ብሎ ነግሮኛል እንጂ ሌላ እዚያ በለመመረጤ የማውቀው ነገር የለም ብሏል ከእዚያ በፊት ምርጫ ይደረግ አይደረግ የሚያውቁት ነገር አለ እንዴ ከእርሶ በፊት እርሶ በተካተቱበት ኮሚቴ በፊት ምርጫ መደረጉን አለመደረጉን ?
- የማውቀው ነገር የለኝም እኔ
- እርሶ በኋላ መካተቶትንስ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አላውቅም
- አያውቁም በኋላ እንደአዲስ በተዋቀሩ ?
- አላውቅም እኔ የተዋቀረ ኮሚቴ እንዳለ አላውቅም
- እርሶ የተካተቱበት ኮሚቴ ላይ እንደአዲስ እንደተዋቀረ ያውቃሉ አያውቁም ከእርሶ በፊት ምርጫ መደረጉን ይደረግ አይደረግ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አላውቅም እሱን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አያውቁም እዚህ ቅድም ስጠይቅት ከተለያዩ ቦታ ከተለያየ ቦታ ወይም ደግሞ ግሩፕ ነው የመጡት ብለዋል ከአወሊያ የተመረጠ አለ ከአወሊያ ?
- ከአወሊያ /ግልፅ ያልሆነ/ አላውቅም እሱን
- ጨርሰናል
- የተከበረው ፍ/ቤት ማሳሰቢያ አለን ሆን ተብሎ ነው የሚመስለው የተከበረው ፍ/ቤት ያስተካክላሉ ብለን ስንጠብቅ በላይ በላዩ ነው እያደረጉ ያሉት እና ይሄንን ያስተካክሉ
- መቼም አልሰሙትም እኔ አሁን ጥያቄውን በትክክል አልሰማሁትም መጨረሻ ላይ እሳቸው መለሱት አላውቅም አሉ ምንም ይጠየቅ ምንም ይጠየቅ አሁን አላውቅም ካሉ እንትን የለውም ስለዚህ እርሶ ምናልባት መቃወሚያ ሲቀርብ ይሄ በእዚህ በኩል ተነስቶ በተቃራኒ ከሚጠይቀው በተቃራኒ ሲነሳ ቆም ይበሉ አይደለም ቆም ይበሉ ማለት ንግግርዎን ያቋርጡ ለማለት ነው ምክንያቱም ተገቢ አይደለም የተጠየቀው ጥያቄ ተብሎ ፍ/ቤቱ ብይን እስከሚሰጥ እርሶ
- ምናልባት የተከበረው ችሎት ምስክር እዚህ ችሎት አንዳንድ ችሎት መጥቶ የማያውቅ ምስክር አለ መቃወሚያ ሲባል ላያውቀውም ይችላል በእኛ በኩል አየጠየቅን እያለ ሆን ተብሎ ተደራርቦ
- ቆይ ዐቃቤ ሕግ አልሰጠናችሁም ነኛ ይሄንን እየነገርናቸው ነው ለእሳቸው
- እኮ ምናልባት
- ይሄንን እየነገርናቸው ስለሆነ ከእዚህ በፊት አጥፍተዋል እያልናቸው አይደለም ወደ ፊት ያለውን ወደ ኋላ ያለው አልፏል ወደ ፊት ያለውን ነገር አስተውለው እንዲሄዱ ለማድረግ ጥያቄ ካላችሁ ቀጥሉ አሁን ምንም ወደ ኋላ ጊዜ ነው የሚያበዛው አቤት እነሱ ጨርሰዋል
- ፕሮፌሰር እርሶ ቅድም ስመረጥ አልነበርኩም ኡስታዝ አቡበከር ነው የነገረኝ ብለዋል እርሶ በሚሰበሰቡበት ሰዓት ከሕዝቡ እርሶን አልመረጥኖትም የሚል ተቃውሞ ገጥሞት ያውቃል?
- አላጋጠመኝም እንደውም ለምን ተሳትፎ አታደርግም የሚል ችግር ነው ያጋጠመኝ በተለያየ ቦታ
- ቅድም ኤንጅዎች ውስጥ እንሰበሰብ ነበረ ቅዳሜ ቅዳሜ ብለዋል እንድትሰበሰቡ በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ኤንጂዎች በቦርድ እንደሚተዳደሩ ያውቃሉ ?
- አውቃለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሰቢ ምንድን ነው መቃወሚያው
- ተመልሷል አቤት /ግልፅ ያልሆነ/
- መሆኑን ያውቃሉ አያውቁም የሚለውን አዎ አውቃለሁ ብለዋል ከእዚያ በኋላ የተጠየቀ ጥያቄ ነው እሱ ተመልሷል በቃ ሌላ ካለ እሺ ቀጥሉ
- ሕዩማ ላላት ተሰበሰብን በሚሉበት ጊዜ ቦርዱ የፈቀደላችሁ ነገር አለ እንድትሰበሰቡ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ ሳይመልሱት እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄ ስለኤንጅዎ ወይም ስለእዚህ ስለልማት ድርጅት ስላሉት የአስተዳደር ሁኔታ በዋና ጥያቄአችን አላነሳንም ስለሆነም ይሄ በመስቀለኛ ጥያቄ ሊነሳ አይገባም
- ምላሽ ስጡበት
- ዞሮ ዞሮ ኢንጅዎቹ የተጠየቁት ኤንጅዎቹን ለመወንጀል ስለሆነ እኛ ደግሞ ለመወንጀል የሚያበቃቸው በሚመለከተው በሚያስተዳድረው አካል ተፈቅዶ ነው ወይስ ሳይፈቀድ ነው ከእሱ እውቅና ውጪ ነው የሚለውን ቀጥታ ግንኙነት ያለው ነገር እነሱ እንዲጠይቁም አይጠበቅም እኛ ግን የተሰበሰቡት ከእውቅና ውጪ ነው ወይስ ድርጅቱ ፈቅዶ ነው የሚለውን ለማጣራት ስለሆነ ጥያቄው በአግባቡ ነው ነው በዋናው ባይነሳም ግን የውሮጅዶቹን ተጠያቂነት ጋር የተያያዘ
- ብይን ሰጥተናል ብይኑ በአብላጫ ድምፅ ነው የተወሰነው በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተሰየሙት ዳኞች ዐቃቤ ሕግ ቀደም ብሎ ይሄንን ጥያቄ የት እንደተሰበሰቡ አቅርቧል ስለዚህ ይሄ ደግሞ ከእዚህ ጋር የተያያዘ ነው የተሰበሰቡበት ቦታ የማን ቦታ ነው ቦርድ ነበረው አልነበረውም ተፈቀደ አልተፈቀደ ለምን ተሰበሰባችሁ የሚለው ከተነሳው ዋና ጥያቄ የራቀ ባለመሆኑ ጠበቆች ያነሱት ጥያቄ ተገቢ ነው ይቀጥሉ ብለናል ነኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ወይም የእሳቸው ግን ቢናገሩ ይሻላል
- በዋና ጥያቄው ላይ የተነሳው ጥያቄ የስብሰባ ቦታ ነው የሚመለከት ነው ስብሰባዎቹ የት ተካሄዱ የኮሚቴ ስብሰባ የት ተካሄደ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ አንድ የስብሰባ ቦታ ብለው የጠቀሱት በኤንጅዎች ተብለው በተጠቀሱት መስሪያ ቤት ውስጥ ኃላፊነት ላይ የሚሰሩ ሰው ቢሮ ውስጥ ለመሆኑ ገልፀዋል ይሄ ጥያቄ በቀጥታ የሚመለከተው የስብሰባ ቦታን ነው የስብሰባ ቦታን በተመለከተ ስለስብሰባ ቦታዎቹ መሠረት ተደርጎ መስቀለኛ ጥያቄ ቢቀርብ እንጂ ስብሰባው በተካሄደበት ቦታን የተመለከተውን ኤንጅዎ ሕጋዊነት ወይም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በቦርድ መተዳደር አለመተዳደሩን ተመለከት የሚቀርቡት ጥያቄዎች በዋና ጥያቄ ከተነሳው ጥያቄ መንፈስ ጋር ሩቅ በመሆኑ ምክንያት በመስቀለኛ ጥያቄ መቅረቡ ተገቢ ነው ሊባል አይገባም ነበር የሚል ነው

- እሺ ቀጥሉ ያው በአብላጫው ድምፅ መሠረት
- ፕሮፌሰር ቦርድ እንድትሰበሰቡ አልፈቀደም አይደል ?
- ፍቃድ መኖሩን አላውቅም ምክንያቱም በስራ ሰዓት አልነበረም የምንሰበሰበው ቅዳሜ ቀን ነው ብዬአለሁ ስለዚህ ክፍት ነበር ቢሮው እዚያ እንሰበሰባለን ፍቃድ ይኑር አይኑር የማውቀው ነገር የለኝም
- ቅድም ለስብሰባው የሚያስፈልግ ሻይ ቆሎ ይቀርብ ነበር በድርጅቱ ባለቤትም ከእኛም ኪስ ይወጣ ነበር ብለዋል ትክክል ነው ?
- አዎ
- የድርጅቱ ባለቤት ከግላቸው ያውጡ ወይም ከሌላ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- የማውቀው ነገር የለኝም
- የድርጅቱ ባለቤት ሲሉ ባለንብረት ማለትዎ ነው እንጂ ድርጅቱ ኤንጅዎ ነው ብለዋል ቅድም ?
- ስራ አስኪያጁን ማለቴ
- ስራ አስኪያጅ ተጠሪነታቸው ለቦርድ ነው አይደል ?
- ለቦርድ ነው
- ፕሮፌሰር ይሄ ምርጫው ከመደረጉ በፊት የኮሚቴዎች ምርጫ ከመደረጉ በፊት የሄዳችሁበት የመንግስት ተቋማት የለም ወይ ይሄንን ጉዳይ ለማመልከት የሄዳችሁበት ቦታ አለ የት የት እንደሆነ እስቲ ንገሩኝ እነሱን የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማለት ነው
- ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር ከ 6 ሰዓት ተኩል በላይ ተወያይተናል
- እሺ ሌላስ ?
- ከዶ/ር ሽፈራው ጋር የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የሕዝቡ ጥያቄ ምን እንደሆነ ምን መልስ መስጠት እንዳለበት ጥያቄው ከ 3 ያላለፈ አልነበረም እና እንዳለ ጥያቄው ቀርቧል እና በሰላማዊ መንገድ ጉዞ እየተጓዝን ነው ይሄ ነገር መፍትሔ ይስጠው የሚለውን ጠይቀናል

2893

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ብዙ ሰዓት ነው ያቃጠልነው በእዚያን ሰዓት እስታውሳለሁ ከእዚያ ቀጥሎ እኔ እንዳልኩት ተሳትፎዬ ውስን ስለሆነ ሌሎች ኮሚቴዎች ወደ ተለያዩ ቦታዎች ተንቀሳቅሰው አነጋግረዋል

- እሺ እርሶ በነበረው እርሶ በነበሩበት ጊዜ የሄዳችሁት ሌላ ተጨማሪ የሄዳችሁበት ቢሮ የት ነበር የሄዳችሁ የመንግስት ተቋማት ?
- ኮልፌ ቀራንዮ ኮማንደር ፖሊስ ቢሮ ሄደን ተወያይተናል
- እሺ ሌላስ ?
- ሌላ እኔ የተሳተፍኩበት መድረክ የለም
- ሌላ እሺ ምናልባት የአቶ ጁነዲን ጋር ሄዳችሁ ያናገራችሁበት ጊዜ ነበረ ወይም አቦይ ስብሀት ጋር ሄዳችሁ ያናገራችሁበት ጊዜ ነበር እስቲ ያስረዱን እሱን ?
- አቦይ ስብሀት ጋር በፊት ይሄ ኮሚቴ ከመዋቀሩ በፊት የተወሰነ ሰዎች ሄደን አነጋግረናል
- የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄ ያልተነሱ ጥያቄዎች እየተጠየቁ ነው ከዋና ጥያቄአችን በጥያቄአችን ሆነ ምስክሩ ሲመልሱ እገሌ ቢሮ ወይም የግለሰቦችን ስም እየጠቀሱ ወይም በአመራር ደረጃ ያሉ ሰዎችን እየጠቀሱ የመሰከሩበት ሁኔታ የለም ስለሆነም ጥያቄው በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ሊቀርብ የሚገባው ጥያቄ በዋና ጥያቄ የተነሳን ነጥብ ሊያስተባብል የሚችል ያንን መሠረት አድርጎ ነው ስለሆነም ጥያቄው ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ እንዲያደርግልን ነው
- ቢሮ ሄደናል ብለው ቀደም ብለው በፀቃቤ ሕግ እንትን ላይ መስክረዋል ክሱ ላይ ደግሞ 2001 ጀምሮ ነው የሚለው ስለዚህ ከእዚያም በፊት ቢሆን ከመዋቀራችሁ ይሄ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት ይሄንን ችግር ለመፍታት የሄዳችሁበት አግባብ ነበር ወይ ነው ያልኳቸው አረዲ ጥያቄውን እኮ መልሰዉታል ከመለሱት አዎ ሄደናል አሉ ምንድን ነበር ሄዳችሁ ምን መልስ አገኛችሁ እያልኩ ስል ነው ያስቆሙት ስለዚህ አረዲ ጥያቄውም ተመልሷል መነሳቱም ደግሞ አግባብ ነው
- ችሎቱ የተነጋገረው ምንድን ነው ያው ጥያቄው ተመልሷል ከተመለሰ ወደ ኋላ መመለስ ተገቢ ስላልሆነ ወደ የሚቀጥለው ሌላ ጥያቄ ይጠይቁ በሷል /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክሩ ግን ማሳሰቢያችን ቢያዳምጡን ጥሩ ነው ቅድም የተነጋገርነው የሆነ ነገር እዚህ ኢያዳመጡ እዚህም ንቁ ይሁኑ በእዚህ በኩል ምክንያቱም በ 2 በኩል ነው እየተጠየቁ ያሉት አሁን እረሱት ስለዚህ የሆኑ ተቃውሞ ከተነሳ እርሶ ያቁሙ እሺ ቀጥሉ.

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ ኮሚቴው መጀመሪያ ተመርጦ በድጋሚ መመረጡን የማውቀው ነገር የለም ብለዋል አወሊያ ተሰብስቦ ሕዝቡ ምርጫ አድርጎ ፒቲሽን ተፈርሞ የተመረጣችሁ መሆኑን አያውቁም እርሶ ወይም በምን አግባብ እንዳወቁ እስቲ አስረዱኝ እስኒ ?
- መመረጤን ነው የማውቀው እንግዲህ /ግልፅ የልሆነ/
- እኮ አላጣሩም መመረጦትን አውቀዋል አላጣሩም መመረጦትን አልሰሙም ወይም ከሌላም አቡበከር ከነገሮት ውጪ የሰሙበት አጋጣሚ የለም ፒቲሽንስ አላዩም ወይ የተሰበሰበ ሕዝቡ ፈርሞ እነዚህ ሰዎች ይወክሉናል ብሎ የመረጠ መሆኑን ያዩበት አጋጣሚ የለም ?
- ግልፅ ነው በተለያየ መልኩ በስልክም ደርሶኛል ተጠቁመሀል እና አቤት ብለህ ተቀበል ትዕዛዙን የሚል ብዙ ደርሶኛል እኔ የጤና ችግር ስላለብኝ አልቀጥልም ብዬአለሁ
- ቆይ ቆይ ይሸውሎት 1ኛ የተጠየቁትን ብቻ ይመልሱ አሁን የተጠየቁት ጥያቄ ፒቲሽን አይተዋል አላዩም እርሶ የተመረጡበት ?
- አላየሁም የመጀመሪያውን
- እሺ ግን ያወቁበት መጠቆሞትን እና የተመረጡ መሆኑን ያወቁበት አግባብ ነበረ አቡበከር ከነገሮት ውጪ አሁን እንዳሉኝ በስልክም ይሁን በግለሰቦች ጋር በነበረት ግንኙነት ያወቁበት አጋጣሚ አለ አይደል ?
- ቆይ ጠበቃ ግልፅ ነው መልሰውታል ማን እንደነገራቸው እንዴት እንዳወቁ መልሰዋል
- እሺ መጀመሪያ የመጀመሪያ ኩርቱ የተሰበሰባችሁ ቀን ብዛታችሁ ምን ያህል ነበራችሁ ?
- አላውቅም አሁን ማስታወስ አልችልም
- ያን ቀን የተነጋገራችሁት ነገር አልነበረም የተመረጠው በብዛት ወጣት ስለሆነ ከኡለማዎች ከትልልቅም ከሽማግሌ ይመረጥ ብሎ ይሄንን የተነጋገራችሁበት አግባብ አልነበረም ?
- ነበረ
- ይሄንኑ አቀረባችሁ ወሰዳችሁ አወሊያ ?
- አዎ አቅርበናል መረጥን ከአዛውንቶች ከአለማዎች ወጣቶች
- ሰው ቀንሳችሁ እንደገና እንዲመረጥ አደረጋችሁ ?
- እዚህ መጥቶ ይዋቀር ብለን ኃሳብ ሰጥተንበታል
- ከእዚያ ሕዝቡ መረጠ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዕድኳል ሕዝቡ
- ሕዝቡ አፀደቀ እሺ ምን ያህል ሰው ነበር አሁን አፀደቀ የተባለው የሰሙት እርሶ ምን ያህል ብዛቱ ምን ያህል ይሆናል በግምት ?
- እኔ ይሄንን ያህል ማለት አልችልም በምሰማው ግን 400 ሺህ 500 ሺህ ሰው ተሰብስቦ ነበር የሚል ነው በምን ገመቱት አላውቅም
- እሺ ሌላው ሀሙስ ሀሙስ እንሰበሰብ ነበር ብለዋል
- እስቲ ቆይ እዚህ ጋር ግልፅ አልነበሩም እንዴ የእዚያን ቀን ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አልነበሩም ?
- አዎ
- ቀጥሉ
- ሀሙስ ስንሰበሰብ ሀሙስ ስትሰበሰቡ ከየተቋማቱ ከመንግስት ተቋማት እንሄድ ነበር ብለዋል እዚያ ያገኛችሁትን ነገር ለሕዝቡ ለማስተላለፍ ለመነጋገር ነው ወይስ ምን ለማድረግ ነበር ስትሰበሰቡ የነበረው ?
- አጀንዳው በሰላማዊ መንገድ እንዲቀጥል የሚል ስለነበረ አርብ ዕለት በሚሰበሰበው ሕብረተሰብ ወይም ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ምን እርምጃ እንደተወሰደ በሣምንት ውስጥ ኮሚቴው ምን እንቅስቃሴ እንዳደረገ ማብራሪያ የሚሰጥበትን አጀንዳ ነበር የምንወያየው
- እሺ በእዚያ አሁን ማብራሪያ ሲሰጡ የተለየ የአረብኛ የሁከት እንደዚህ ዓይነት ዓላማ የነበረው መሆኑን የተገነዘቡበት አግባብ አለ እርሶ ?
- ይሄ ዓላማችን አልነበረም ከመጀመሪያ ጀምሮ
- እስቲ ቆይ እሱ አልተነሳም ረበሹ አልተባለም ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- እሺ ቀድሞ ሰላማዊ ነበር ብለዋል ሰላማዊ መሆኑን በምንድን ነው ያረጋገጡት እርሶ ሰላማዊ መሆኑን ያረጋገጡበት አግባብ አስረዱልን ?
- ሰላማዊ መሆኑን ያረጋገጥኩበት 1ኛ ጥያቄው ሕገ መንግስታዊ መሆኑን የሕዝቡ ጥያቄ መሆኑን እና ከእዚያ የማይወጣ መሆኑን ነው ያረጋገጥኩት
- ምን ምን ናቸው ጥያቄዎቹ ?

2896 2ሀ246

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 3 ጥያቄዎች ናቸው
- ምን ምን ናቸው ?
- 1ኛ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የራሱን መሪ እንዲመርጥ በመጅሊሱ 2ኛ አወሊያ በቦርድ እንዲተዳደር 3ኛ የሀባሽ አስተምሮ እንዲቆም እና ከፈለገ በራሱ ካምፕ ውስጥ እንዲያስተምር የሚል ይዞ ነው 3 ጥያቄ ነው
- እነዚህ ነበሩ ጥያቄዎቹ ?
- ሌላ ጥያቄ አልነበረም
- ቅዳሜስ የምትገናኙት ምን ለማድረግ ነው ?
- የአርቡ ዕለት ውጤት ግምገማ ለማድረግ
- ስላማዊ መሆኑን ለመነጋገር ነበር ?
- ለመወያየት እና ለማወቅ
- እሺ ፕሮፌሰር አሁን መጨረሻ ላይ ከመለሱት ጥያቄ ልጀምር እና 3 ጥያቄዎች ቀርበው ነበር ብለዋል እነዚህ ጥያቄዎች የሕዝቡ ናቸው የኮሚቴው ናቸው የማን ጥያቄዎች ናቸው ?
- መቃወሚያ አለ
- አሁን የተጠየቀው ጥያቄ የተከበረው ችሎት በግልፅ በዋና ጥያቄ አላነሳንም 3 ጥያቄ የሚል በጭራሽ በዋና ጥያቄም አላነሳንም ስለዚህ እነዚህ ጥያቄ የሕዝብ ናቸው የማን ነው የማን ናቸው ተብሎ ሲጠየቅ አይገባም በዋና ጥያቄ አልጠየቅንም ?
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ጥያቄ እነሱ ባነሱት ጥያቄ ምስክሩ መስክረዋል ኮሚቴ ሆነን 3 ጥያቄ ከሕዝብ መጥቶ ለመንግስት አቅርበናል ብለዋል ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ከማን እንደተነሳ እኛ ማረጋገጥ ስለምንፈልግ እሱን ነው የጠየቅነው የግድ ዐቃቤ ሕግ እኮ ከመጠየቅ ውጪ መመስከር የለበትም በጠየቁት መሠረት መስከሩ በዋና ጥያቄ እኛ ደግሞ በመስቀለኛ ጥያቄ ይሄንን ነገር ማረጋገጥ ስላለብን ነው እና ጥያቄው ተገቢነት ያለው ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ምስክሩ ቀደም ብለው ሲመልሱ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ሲመልሱ 3 ጥያቄዎች ነበሩን እነሱን ጥያቄዎችም በመንግስት ለማቅረብ ነው የሚል አንስተው ነበር በዚህ መሠረት እሱን መሠረት አድርገው ያነሱት ጥያቄ ስለሆነ ተገቢ ነው ይቀጥሉ ብለዋል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፕሮፌሰር ሕዝቡ [illegible] በሕዝብ መጥተው ነው አይደል ለእናንተ የተሰጣችሁ ወይም ሕዝብ ያነሳቸውን ጥያቄዎች ነው እናንተ ተቀበላችሁ ለመንግስት አካል ያስተላለፋችሁ አይደለም ?
- ሕዝቡ ጥያቄው እነኚህ ጥያቄዎች መንግስት ጋር ተነጋግራችሁ መትፍሔ አስገኙልን የሚል ስለሆነ ያ እንግዲህ 400 ሺህ 500ሺህ 600 ሺህ በተለያየ ጊዜ በእዚህ በዛዝ እየተሰጠ የመጣ ስለሆነ የሕዝብ ጥያቄ ነው ማለት እንችላለን የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ጥያቄ ነው
- ቅድም ፕሮፌሰር ሕዝቡ ውስጥ ያሉት ኮሚቴዎች የተወሰኑት አስተማሪዎቼ ናቸው የተቀሩት ተማሪዎቼ ናቸው ብለው ነበር እስቲ እንደው አስተማሪዎቻ እነ ማን ናቸው ምን ነበር የሚያስተምሮት ?
- ይሄ ምንም ከእንትኑ ጋር ግንኙነት የለውም
- እሺ ምን ነበር የሚያስተምሩት ትቼአለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አስተማሪዎቼ ናቸው ስላሉ እነዚህ ሰዎች ምን ነበር የሚያስተምሩት ?
- እኮ እሱ ይኸውሎት ይሄ ከክሱ ጋርም አይገናኝም አስተማሪዎቼ ነው ያለው ግንኙነታቸውን ነው የሚያመለክተው ስለዚህ ከግንኙነት ጋር የምትጠይቁት ካልሆነ በስተቀር ከጭብጥ ጋር ግንኙነት የለውም ምን ተማሩ አስከየት ተማሩ ማን አስተማሮት ይሄ የክሱ እንትን አይደለም ሌላ ጥያቄ ካላችሁ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ላስረዳው ከማለትዎ በፊት ከችሎት ላይ የተገለፀውን አልተረዱም መሰለኝ እርሶ እና ችሎት ላይ የተገለፀው ምስክሩ የመሰከሩት ሰዎቹን አውቃለሁ ግማሹ ተማሪቼ ግማሹ አስተማሪዎቼ እና ሌሎችም ብለው ቀጥለዋል እንዴት አወቃችሁ በማለት ነው ምን አስተማሩ ተብለው ምስክሩ እየመሰከረ አይደለም በዋና ጥያቄ የተነሳ ነገር አይደለም ምን ስላስተማሩ ነው ነገር አሁን በዋና ጥያቄ ያልተነሳውን ላስረዳ ማለቱ ሌላ ንትርክ ውስጥ መግባቱ ነው ተገቢ ስላልሆነ ወደ ሌላ ጥያቄ መሄድ ያስፈልጋል
- ፕሮፌሰር ቅድም መጨረሻ ላይ ይሄ ስብሰባ ተደረገ ያሉበት ቀን የአፍሪካ አድነት ድርጅት ስብሰባ አለ እና እሁድ ቀን መሆኑ ቀርቶ እሮብ ይሁን ብለው ነበር እርሶ እነሱ ደግሞ ረመዳን ስለመጣ 4 ቀን ብቻ ስለቀረው ስብሰባው መካሄድ [illegible] ብለው [illegible] የነገሮት ከእዚህ ሌላ የነገሮት ምክንያት አለ እንዴ ስለ ስብሰባው [illegible] እሁድ ስለ መካሄዱ አልተነገሮትም አይደል ወይም ሌላ የሚያውቁት ምክንያት የለም [illegible]

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቆይ መጀመሪያ ጥያቄው የመለሱት ጥያቄ አለ እናትው የተቃወሙበት አግባብ እነሱ ደግሞ ያሉበት አግባብ ግልፅ በሆነ መንገድ አስቀምጠዋል ስለዚህ ከእሱ ተነስታችሁ ጥያቄወን ምዘዙት እንጂ አሁን ይሄንን ቢንዲደግሙት ጊዜ መጨረስ ነው
- ስለዚህ ከእዚህ ረመዳን ቀርቧል ከማለት ውጪ ሌላ የነገሮት ምክንያት አለ ?
- ሌላ ተጨማሪ ምክንያት አለ ?
- አልተነገረኝም ሌላ
- የሚያውቁት ሌላ ምክንያት የለም ?
- የለም
- እርሶ ቅድም በተለያየ ምክንያት ስብሰባ ላይ አልገኝም አንዳንድ ውሣኔዎች ሊያልፉ ይችላሉ ብለው ነበር እና ባልተገኙበት ጊዜ ከያዛችሁት ጥያቄ ውጪ ሌሎች ጥያቄ ስብሰባዎች ስለመካሄዳቸው ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- ቅድም ከኮሚቴዎች ምርጫ ላይ በዕድሜ በትምህርት ከመሆኑ ውጪ በሌላ ነገር የተደረገ መመዘኛ ነበር ስለኮሚቴዎች ምርጫ የሚያውቁት የለም አይደል ?
- ሌላ የማውቀው ነገር የለኝም
- እሺ ፕሮፌሰር እርሶ በማይገኙበት ስብሰባዎች ከተደረገ በኋላ በሌላ ቀን እርሶ ሲገኙ እርሶ ያልነበሩበትን ስብሰባ ብሪፍ ይደረግ ነበር አይደል ስብሰባ ላይ ከመጀመሩ በፊት የባለፈው ስብሰባ እንዲህ ነበረ እንዲህ ዓይነት ውሣኔ ተወሰነ እየተባለ ላልነበሩ ሰዎች ይነገር ነበር አይደል ግልፅ ነው ጥያቄዬ ወይስ ?
- ግልፅ አይደለም ?
- ግልፅ አይደለም
- እሺ የተለያዩ ስብሰባዎች ይደረጋሉ እርሶ በተለያየ ምክንያት በጤናም በተለያየ ምክንያት ላይገኙ ይችላሉ ወይም አይገኙም እርሶም ሆኑ ሌሎች ተሰብሳቢዎች
- አጠር ባለ ጥያቄ እርሶ በሌሉበት ስብሰባ ላይ ሌላ ጊዜ ሲገኙ ሪቪዥን አለ ወይ ነው ወይም መከለስ አለ ወይ የባለፈውን ስብሰባ እርሶ በሌሉበት ?
- አይኖርም

2899

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዚያ ቀጥሉ ሌላ ጥያቄ
- እርሶ ባልነበሩበት ስብሰባ የተወሰኑ ውሣኔዎች የሚያውቁበት ዕድል አለ የለም ያውቃል አይደል ያልነበሩበት ስብሰባ ላይ የተወሰኑ ነገሮችን ?
- እስቲ ቆይ ይሄ ነገር ተመልሷል እኮ
- የተከበረው ፍ/ቤት ስለሪቪዥን ነው
- ከለሳ የለም ያኔ የምናውቀው ነገር የለም ብለዋል ከእዚያ ውጪ ነው ?
- ስለሪቪዥን ነው የጠየቅነው እንደ አሁን ደግሞ የሚያውቁበት መንገድ ወይም ያውቃሉ ወይ ነው ሌላ አጠቃላይ የሆነ ከስብሰባው ውጪ የሚያውቁበት መንገድ ካለ ነው ?
- ያውቃሉ ይሄንን ?
- ልጠይቃ የተከበረው ፍ/ቤት
- የማውቀው የለኝም
- በቃ ቀጥሉ ሌላ
- ልጠይቅ ወይስ ?
- ይሄንማ መለሱት እኮ
- /ግልፅ ያልሆነ/ የተጠየቀውን የተመለሰውን አልሰማሁም
- አላውቅም ነው
- አላውቅም አሉ
- እሺ እርሶ በተሳተፉባቸው ስብሰባዎች የስብሰባ ሂደት እንዴት ነበር ውሣኔዎች የሚወሰኑት በድምፅ ብልጫ ነው አይደል ?
- አዎ በድምፅ ብልጫ ነው
- እሺ ከስብሰባ ተሳታፊዎች መሀከል ሌላው ላይ ጫና ለማድረግ ወይም ደግሞ የራሱን ኃሳብ ሌላው ላይ ለመጫን የሚሞክር የለም አይደል ?
- የለም አላጋጠመኝም
- እነዚህ ተመራጮች የመፍትሔ አፈላላጊ ተመራጮች ቀድሞ እርሶ የሙስሊሙን ችግሮች መፍትሔ አፈላላጊ ያሏቸው ችግሩን ለመንግስት እንዲያቀርቡ እና እንዲያስረዱ ፒትሽን በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ተሰብስቧል አይደል የድጋፍ ፒትሽን ችግሩ ይፈታልን እነዚህ

2900

http://ethcriminalawnetwork.com/

ጆዋም ወኪሎቻችን ናቸው የሚል ፒቲሽን የፊርማ አሰባሰብ በየመስኪዱ በየከተማው ተደርጓል አይደል ?

- ያውቃሉ ይሄንን ?
- እኔ ምክር ሰጪ ነኝ መሰባሰቡን ሰምቼአለሁ ከእየአቅጣጫው ድጋፍ መጥቷል የሚለውን ሰምቼአለሁ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ምክር ሰጪ ስለሆነው በበዛት /ግልፅ ያልሆነ/ ስለሆነ ዝርዝሩን ማወቅ አልቻልኩም
- አወሊያ በተገኙበት ወቅት እርሶ አወሊያ ላይ በተደረገ ስብሰባ አንድ ወቅት ይኸው ከተወካዮቻችን መካከል ፕሮፌሰርም አሉ ተብሎ ሕዝቡ ድጋፉን የሰጠበትን ያስታውሳሉ ?
- አወሊያ የተገኘሁት በመጨረሻው ቀን የእሁዱ ጉዳይ ነው እንጂ ከእዚያ በፊት አልተሰበሰብኩም
- እኮ አሁን በእዚያ ስብሰባ ላይ ዛሬ ከተገኙት ኮሚቴዎቻችን ውስጥ ፕሮፌሰርም አሉ ብሎ ሕዝቡ አልተቃወመም አይደል ከድጋፍ ውጪ ?
- ሰምቼአለሁ እንጂ አልሰማሁም እሱን አልነበርኩም
- 3ኛ ጊዜ የተጠየቀ ነው ይሄ ጥያቄ ነው ጥያቄ አይደጋገሙ
- እርሶ ባልተሳተፉበት ስብሰባ የማያውቁት ነገር ወይም የማይደግፉት ነገር ተወስኖ የተቃወሙበት ዕድል አለ ይሄ ነገር መወሰን እንዲህ መሆን የለበትም ብለው
- እሱ ነገር የለሁም ብለዋል ከእዚያ በፊትም ውሣኔ የማውቅበትም የለም ብለዋል ስለዚህ ይሄንን እንዴት ከእዚህ በኋላ ምን ምላሽ ነው የምትጠብቁት
- ቅድም ዐቃቤ ሕግ ጠይቀት ከሄድንባቸው የመንግስት ቢሮዎች ውስጥ የኮልፌ ቀራንዮ ፖሊስ ጣቢያ ይገኛል ብለዋል አይደለም ፕሮፌሰር የኮልፌ ቀራንዮ ፖሊስ
- በመስቀለኛ ጥያቄ ነው የተጠየቀው ከእሱ ተነስተው መስቀለኛ ጥያቄ ነው የተጠየቀው የተጠየቀው የት የት መስሪያ ቤት ሄዳችዋል ሲባል ኮልፌ ቀራንዮ ተብሎ ከእሳቸው ነው የተጠየቀው ከእሱ ተነስታችሁ የቀራችሁ ጥያቄ ካለ መልሱ ካለዚያ ጥያቄው ተመልሷል
- እሺ ለፖሊስ ጣቢያው ምን አቀረባችሁ ፕሮፌሰር ለፖሊስ ጣቢያው ምን ጠየቃችሁ ፖሊስ ጣቢያው ጋር ሄዳችሁ ጥያቄአችሁን ሰላማዊነት
- ምንድን ነው የጠየቃችሁት እሱን ይመልሱት እስቲ ?
- እኛም ስንሄድ እነሱም የተለያዩ የመንግስት አካላት ነበር የደህንነት ፀጥታ የተለያዩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥያቄአችሁ ምን ጥያቄአችሁ ምን ነበር ?
- ጥያቄው የቀረበው አርብ እያስቸገረን ስለሆነ ስብሰባው በሰላማዊ መንገድ የሚያልቅበት መፍትሔ የሚያገኝበትን ጉዳይ ትኩረት ስጡበት የሚል ጥያቄ ነው
- የቀረበው ?
- የቀረበው
- እነሱም ስብሰባው ሰላማዊ መሆኑን አረጋገጡላችሁ አይደል ?
- አዎ ይሄ ነው በቃ ጥያቄው ከእዚህ ውጪ አልነበረም
- ለተለያዩ ሚዲያዎች ከኮሚቴዎቹ ውስጥ እርሶም የሰጧቸው መግለጫዎች አሉ ወይም
- ቆይ ቆይ ሰጥተዋል መግለጫ ?
- አልሰጠሁም
- አለቀ እለፉ
- ከእዚያ በፊት ግልፅ ያልሆነ ነገር አለ ስብሰባው ሰላማዊ መሆኑን አረጋገጡላችሁ አይደለም ወይ እነሱም የሚል ነገር አለ ግልፅ አልሆነልኝም እና እሱ አንድም ምስክሩ ያልተናገረውን ነው የተገለፀው እዚያ ጋር እና
- መሪ ጥያቄ ጠየቅን አዎ ብለው መለሱ የተከበረው ፍ/ቤት
- ያልተጠየቀው የሆነ ጀነራላይዜሽን አለ መሪ መጠየቅ ይችላል እሱ ፍሎሶፊውን እዚህ ማንሳት አይደለም
- እንድገመው እናብራራው ጥያቄውን አብራርተን እንጠይቅ ?
- አዎ ግልፅ ፖሊስ ጥያቄአቸውን ለፖሊስ አቀረቡ ሌሎች ፀጥታ ባሉበት ቦታ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- ከእዚያ በኋላ ምን ሆነ ?
- ቅድም አሁን እርሶ እንዳሉት እኔ ስጠይቆት የተለያዩ የመንግስት አካላት ደህንነትም ፖሊሶችም ባሉበት ጥያቄአችሁን አቅርባችሁ አስረድታችሁ እነሱም ጥያቄአችሁ ወይም ስብሰባችሁ ሰላማዊ ነው የሚለውን አረጋግጠውላችኋል አይደል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥያቄ ሳይሆን የመስማማት ወይይት የመግባባት ውይይት ነበር የተካሄደው ማለት ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዴት ማቆም ይቻላል ይሄንን ጉዳይ የሚለውን ኃሳብ የተወያየነው ስለዚህ ያ 3 ጥያቄ ከተመለሰ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ለሁ/ ነው እኛ ነው ያቀረብነው ያን ጊዜ 3ቱ ጥያቄ መልስ ካገኘ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ኮማንደር ልዑል ነበር ያቀረቡት የጠየቅነው የተጠየቅነው በእነሱ በኩል የቀረበው ጥያቄ አዎ ስብሰባው ይሄ አርብ አርብ ያለው ተሳትፎ ሰልፍ ወይም የሙስሊሙ ሕብረተብ ወደ አወሊያ መጓዝ የሚቋረጥበትን ሚጊስ ፍጠሩልን የሚለው ነገር ነው 3ቱ ጥያቄዎች ከተመለሰ ችግሩ ያበቃል ነው ያልነው
- እስካሁን ያለው ሂደት ሰላማዊ ነው የሚለውን ኮማንደሩ ተናግረዋል አይደል ፕሮፌሰር ?
- የስ ተናግረዋል በጊዜው በእዚህም /ግልፅ ያልሆነ/ ኮማንደሩ ሰላማዊ መንገድ ይሄ ሁሉ ሕዝብ ተሰብስቦ ድንጋይ ሳይወረወር እንደዚህ ማለቁ እና ወደ ቤቱ መመለሱ ይሄ እራሱ አንዱ አስደናቂ ከእዚያም አልፎ እኮ
- ማለት ከስብሰባ በኋላ ነው እንዴ የሄዳችሁ ከስብሰባ በኋላ ነው የሄዳችሁ ?
- አዎ በየአርቡ
- ለአርብ ስብሰባ በሚያደርጉበት ቅድመ ዝግጅት በእነሱ ጥያቄ ነው የሄድነው በአጋጣሚ
- የራሳችሁን ስብሰባ ነው ?
- አዎ
- ይሄ እንዲህ ማለቁ እንዲህ ማለቁ ስላሉን ነው አሁን መጨረሻ ላይ ?
- ኮማንደሩ ኑ እና እንወያይ ብለው በጠየቁት መሠረት ነው የሄድነው
- ፕሮፌሰር ግልፅ እንዲሆን ለፍ/ቤቱም ለእኛም ስብሰባ የተባለው መስኪድ ላይ ሕዝቡ የሚያደርገው ስብሰባን ነው አይደል ሰላማዊ እስካሁን ያለው ሒደት ሰላማዊ ነው የተባለው ሕዝቡ መስኪ ድ ላይ ተሰብስቦ የሚበተነውን ነው አይደል ?
- ሕዝቡ መስኪድ ላይ አይሰበሰብም ሕዝቡ የሚሰበሰበው አወሊያ ነው
- እኮ ገባኝ አወሊያ ተሰብስቦ እየተበተነ ያለበትን ስብሰባ ነው አይደል ሰላማዊ ነው ያለው

2903

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- በእነዚህ ስብሰባዎች የተፈጠረ ችግር የሚያውቁት ነገር አለ እንዴ ?
- እኔ እንደውም አንዱ መለኪያዬ የተፈጠረ ችግር አለመኖሩ ማረጋገጥ ነበር ለስብሰባው መቀጠል
- ስለዚህ አልተፈጠረም ምንም ዓይነት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምንም ዓይነት ችግር አልተፈጠረም ?
- አላጋጠመንም
- በተለያዩ መድረኮች
- እስቲ አትደጋግሙት ማለት እንዴ ካረጋገጡ ይበቃል 3 ጊዜ 4 ጊዜ እናንተ የምትሉት የእሳቸው ነው ፍሬ ነገሩ እናንተው ምንም መጨረሻ ላይ እናንተ ቃል ተከምሮ ተከምሮ የእነሱ ቃል መፈለግ መከራ ነው የሚሆነው
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት በተለያዩ መድረኮች እናስተምር ነበር ብለዋል ለምሳሌ የጥያቄአችሁን ሕገ መንግስታዊነት እና ሕጋዊነት ያስተማራችሁበትን ወይም የተናገራችሁበትን የሚያስታውሱት ካለ እስቲ ይንገሩን እርስዎም ሆነ ሌሎች ኮሚቴዎች ?
- የተከበረው ችሎት
- ጥያቄዬን ግልፅ ላድርገው
- ቆይ ከእዚያ በፊት ጥያቄው ምንድን ነው ከእዚህ እንዲህ የሚያስታውሱት ካለ የሚለው ነገር ዋና ጥያቄ ነው መስቀለኛ ጥያቄ አይደለም በመሰረቱ ስለዚህ እናንተ ከተጠየቀው መዛችሁ ነው መጠየቅ ያለባችሁ እንጂ አስታውሳችሁ እንዲህ ንገሩን ማለት የዋና ጥያቄ ፓርት ስለሆነ ጥያቄውን አስተካክላችሁ መርታችሁ ጠይቁ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ስብሰባ በተደረገባቸው አወሊያ ስብሰባ በተደረገባቸው ዕለቶች ሁሉ ወይም እርሶ በተገኙባቸው ስብሰባዎች ሁሉ ጥያቄው በሰላማዊ እና በሕጋዊ መንገድ በሕገ መንግስታዊ መንገድ መቅረብ እንዳለበት ስትናገሩ ነበር ወይ? ል ?
- ይሄ ነበር ተደጋግሞ የመጣው ጥያቄዎች
- ሕዝቡ የሚጠይቀው ጥያቄ ሕገ መንግስታዊ መሆኑን እያረጋገጣችሁ ነበ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይኸውሎት መለሱ እኮ ከመጀመሪያው ጀምሮ እኔ ያሰሁበት ስብሰባ ሰላማዊ ስብሰባ ነው ለእዚያ ነው እኔ ሰላማዊ እስከሆነ ድረስ ነው የምሰበሰብ ብለዋል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- ስለዚህ ከእዚህ ሌላ ያላችሁን ጥያቄ ጠይቁ
- ቅድም ጥያቄአችን 3 መሠረታዊ ጥያቄዎች ናቸው ብለው
- እሱም ተጠይቋል
- የተከበረው ፍ/ቤት ተጠይቋል ግን ሌላ ፓርት ነው እየጠየኩ ያለሁት
- እሺ የተለየ
- 3 የሚለው ብቻ ነው የሚያመሳስለው እኔ ከምጠይቀው ነገር ጋር 3 ቁጥሩ ብቻ ነው
- እሺ ቀጥሉ
- 3 ጥያቄዎች ናቸው ጥያቄዎቻችን ብለዋል ከእዚያ ውስጥ ሀባሽ ከፈለገ በራሱ ተቋም ያስተምር እንጂ በሕዝብ ላይ አይጫንም የሚል ነበር ሀባሽ የሚባል ነገር እየተጫነ የነበረ ነገር ነበረ ማለት ነው ወይም ሀባሽ የሚባል አስተምሮ ነበረ ማለት ነው?
- እሽ ይቀጥሉ
- ተከስቶ ነበር
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ እንቃወማለን በዋና ጥያቄ ስንጠይቅም ሆነ ምስክሩ ሲመልሱ ዝርዝር ስለእዚህ ሀባሽ የሚባል አስተምሮት እንደዚህ እንደዚህ በማለት 3 ጥያቄዎች አሉን እነዚህን ጥያቄዎች አቅርበናል በሚል መልኩ ነው እንትን ያሉት ከእዚህም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲመለስ እነዚህ ጥያቄ ምንድን ናቸው የሚል ገልፀዋል ነገር ግን ሀባሽ ምንድን ነው የሚል ኃይማኖታዊ ማብራሪያ እንዲሰጡ የሙያ ምስክርነት የመጡ ምስክር አይደሉም ስለሆነም ጥያቄው እንደዚህ ዓይነት ከዋና ጥያቄ ካቀረብነው በይዘትም በጣም የራቀ እና በራሳቸው በመስቀለኛ ጥያቄ ከተመለሱ ያንን መሠረት አድርጎ እየተጠየቀ ያለ ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግልን ነው
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ይሄ ጥያቄ ተመልሷል ከተመለሰ በኋላ ነው ዐቃቤ ሕግ ተቃውሞአቸውን ያቀረቡት ይሄ ይመዝገብልን 2ኛ
- ከእዚህ በኋላ ሌላ ጥያቄ አትጠይቁም በእዚህ ጉዳይ ሌላ ጥያቄ አትጠይቁም በእዚች እንትን

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ለሃጠየቀን አዎ ነው የተከበረው ፍ/ቤት እየጠየቅን ነው በኋላ ከተጠቀን ተቃውሞ ያቅርቡ እና እሱ ላይ እንከራከር እንጂ ይሄ ላይ
- እሺ ቀጥሉ ጨርሱ እሺ ?
- አዎ የተጠየቀው የተመለሰ ነው 1ኛ 2ኛ እየጠየቅን ያለነው የተመለሰ ምስክሩ እራሳቸው በነፃ ፍቃድ የተናገሩት ነገር ላይ ነው እና አዲስ ነገር ፈጥረን አይደለም እየተናገርን ያለነው የተናገሩት በመስቀለኛ ጥያቄ መብራራት ያለበት ነገር ነው እንዲብራራ እየጠየቅን ያለነው እና ጥያቄው መጠየቁ አግባቢ ነው በዋና ጥያቄነትም ተነስቷል በቀጥታ ዐቃቤ ሕግ አይጠይቋቸው እንጂ ጥያቄ ሲጠየቁ 3 መሠረታዊ ጥያቄዎች ይዘን ነው ኮሚቴውም እኔም የተነሳነው ብለው ተናግረዋል ከእዚህ በተጨማሪ ቢያስፈልግ በቂ እውቀት አላቸው ብለን ስለምናምን የሙያም ቢሆን መስጠት ይችላሉ ከተጠየቁ እና መመለስ ይችላሉ ብለን እናምናለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል የግራ ቀኙ የቀረቡትን ምክንያቶች መርምሯል ስለዚህ አልህበሽ የሚባለው ነበር እራሱን ችሎ ያስተምር በራሱ የሚል ምስክሩ ቀደም ብለው አስረድተዋል ይሄንን ፍ/ቤቱ ይዟል አሁን የተነሳው ጥያቄም ከእዚህ የተለየ ባለመሆኑ ጥያቄው አግባብ ነው ብለናል ነገር ግን ምናልባት በጠቆች በኩል ሲጠየቅ እንደሙያ ምስክር ተብሎ የተነሳው ነገር ምናልባት የሙያ ምስክር እናንተ ከፈለጋችሁ መጨረሻ ላይ የምንደርስ ከሆነ እናንተ የሚሆነው የሙያ ምስክር አድርጎ ዐቃቤ ሕግ አልጠየቀም ዐቃቤ ሕግ የጠየቀው ፋክት ነው ስለዚህ አሁንም እኛም በእዚህ በተነሳው ጥያቄ ላይ ፋክቱን ተመስርቶ ይሄ የኃይማኖት ወይም አልህበሽ የተባለው የነበረ መሆኑን ያነሱት ስለሆኑ ይሄ ፋክት ነው መኖር አለመኖሩን የሚያውቁ ከሆነ ማረጋገጥ ደግሞ የፋክት ጉዳይ በመሆኑ ምክንያት ከእዚያ በኋላ አልህባሽ ምንድን ነው የሆነ የሚለው ነገር የኃይማኖት ክርክር ሊሆን ስለሚችል መድረሻም ስለማይኖረን ዋናው ነገር ፋክቱን መስክረው እንዲሄዱ ፋክቱ ላይ ብቻ ተመርከዛችሁ ፋክቱን ጠይቁ
- ፕሮፌሰር ያው ቅድም አለ ብለውናል አሁንም የምጠይቆት እሱን ነው ሀባሽ የሚባል አስተምሮ አለ አይደል ሀባሽ የሚባል አስተምሮ አለ አይደለ እየተሰማ ነው እየሰሙኝ ነው ፕሮፌሰር ሀባሽ
- መቃወሚያ አለን የተከበረው ችሎት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እና አሁን እሱ ጊዜ የነገርናውስ ጥገር አለ እኛ ጋር አባስ ነው ትክክለኛው ?
- አዎ
- ሀባሽ እያልን ስለሆነ
- ይረዱታል
- እስኪ በእዚህ እናስተካክለው ገዷ የለም አንዷዚያ ከሆነ ትክክለኛውን በእዚህ መንገድ አርሶ በእዚህ መንገድ ይቀጥሉ መኖር አለመኖሩን ብቻ
- መቃወሚያው የተከበረው ችሎት በዋና ጥያቄ
- ብይን ተሰጥቶበታል የተከበረው ፍ/ቤት
- እስቲ ቆይ
- ጠበቃው ጨርሷል ጥያቄ ሀባሽ አለ የለም ብለው እሳቸው ባለመስማታቸው ምክንያት ነው ፍ/ቤቱም በመሀል እንትኑን ሲያጣራ የነበረው እንጂ ተጠይቋል ጥያቄው
- እንድንጠይቅ ፍ/ቤቱ ፈቅዶልናል እንጠይቅ የተከበረው ችሎት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አስቀድሞም የተጠየው ነገር ምንድን ነው ጥያቄዎች ተነስተዋል እነዚህን ጥያቄ ከነበረው ቦሜቴ ጋር አብሬ ለመግባት ለባል አቀርቤአለሁ አሉ ከእዚያ በተረፈ እና ሀባስ አለ የለም ተፅኖ ነበር አለ የሚለውን አሁን ጥያቄ የሚጠየቅ ከሆነ ግን እኛ በዋና ጥያቄ አልጠየቅንም ሀባሽ አለ የለም የሚባል ጥያቄ በፍፁም አልጠየቅንም እኛ
- እሺ የተሰጠው ብይን ምናልባት በደንብ ካልተከታተላችሁ በስተቀር የተሰጠው ብይን ይሄ ፋክት አለ የለም ነው ዐቃቤ ሕግ መጀመሪያውኑም የሆነ ጥያቄ ጠየቀ ከእዚያ ጥያቄ ላይ ተነስተው ምስክሩ የራሱን ድርጅት ከፍቶ ያስተምር ይሄ መጥቶብናል ይሄ አስተምሮት እራሱን ችሎ ያስተምር የሚል አንስተዋል እሳቸው ስለዚህ ይሄ ደግሞ ከዋና ጥያቄ ጋር ተያይ። የመጣ መልስ ስጡ ይሄንን መልስ ደግሞ እነሱ ግልፅ መሆን አለባቸው ስለዚህ ቀደም ብሎ ብይን የተሰጠበት ስለሆነ ቀጥሉ
- /ግልፅ ያልሆነ/ የተከበረው ፍ/ቤት ፕሮፌሰር ከ 3ቱ ጥያቄዎቻችሁ አንዱ የሀባሽ ጥያቄ ነው ሀባሽን በተመለከተ ምን /ግልፅ ያልሆነ/
- እስቲ ቆይ ሀባሽ የሚባል አስተምሮት አለ የለም እርሶ አሁን
- የተከበረው ፍ/ቤት እንጠይቅ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዘሎ ይሄንን ይመልሱልን ዋናው ጥያቄ ይሄ አይደል መጀመሪያ ይሄ መናገሩን አለመናገሩን
- በእኛ ቋንቋ መጠየቅ አንችልም የተከበረው ፍ/ቤት
- እስቲ አሁን ፍ/ቤቱ ጠይቋል ዋናው ዞሮ ዞሮ በአስተሳሰብ ማለት የተጠየቀው ጥያቄ እንግባባለን ይሄ አለ የለም ?
- የህገ አስተምሮ ከአዲስ አበባ አፊፎ በሀገር አቀፍ እየተገሰራፋፈ መጥቶ ነበር እና ሙስሊሙን ሕብረተሰብ የሚለያይ ከሰላም እና መረጋጋት የሚያጠፋ ስለሆነ በካምፕ ውስጥ በሕገ መንግስቱ ተጠቅሞ ብቻ ያስተምር እንጂ ለምን ሕዝቡ ላይ ጣልቃ ይገባል ብለን ይሄ ነው ዋናው ጥያቄ እና እንገብጋቢ ጥያቄ የነበረው አለ አስተምሮ አለ አሁንም አለ አይጠፋም ሙብቱ ነው በሕገ መንግስቱ የትም ቦታ ካምፕ ውስጥ አለው የራሱ የሆነ ድርጅት ከድርጅቱ አይውጣ ከመስኪዱ አይውጣ ከራሱ ካምፕ አይውጣ እንጂ ወደ ሌላው ተፅኖ ማድረግ የለበትም የሚለውን ነው እኛ ያቀረብነው
- ኮሚቴው ሲሰበሰብ እኔም አዋጥቼአለሁ ብለዋል ሌሎቹም ኮሚቴዎች ያዋጡ ነበር ከኪሳቸው የኮሚቴ አባላት ለሻይ ለቡና እንዲህ ለቆሎ ለምናምን ያዋጡ ነበር ከኪሳቸው ?
- 1ኛ ሁላችንም ምሳ በልተን ነው የምንመጣው
- [illegible] ነበር ወይ ?
- አዎ የተወሰነ ሰዓት እኔም አዋጥቼአለሁ ግን በብዛት እነ ሼህ ጣሂርም ያዋጡ ነበር እነ ሼህ ሱልጣንም ያዋጡ ነበር በቃ ተናግሬአለሁ መሰለኝ
- ከኪሳቸው ነው የሚያዋጡ የነበረው
- 1ኛ ያዳምጡ እኛ ጋር ያለው ዋና ነገር እዚህ ያለው ክርክር ለእኛ መጨረሻ ላይ ለውሣኔ አሰጣም ምቹ እንዲሆን ነው እንጂ የራስዎን መልስ ለመስጠት የሚፈልጉትን መልስ ብዙ ነገር ሲሰጡ ይችላሉ በእዚያ በኩልም ብዙ የሚፈልገውን ሊጠይቅ ይችላል በእዚህ በኩልም ሊጠየቅ ይችላል ዋናው ነገር እዚህ የተቀመጠውን ለፍትህ አሰጣም ግልፅ ማድረግ ነው ስለዚህ አሁን ይቆዩ እያልኖት ነበር አልሰሙንም ስለዚህ ወደ ፊት ያዳምጡን የሚጠየቁትን ብቻ ይመለሱልን የሚጠይቁትን ብቻ የተጠየቀው አንድ ጥየቄ ብቻ ነው እርሶ ግን መአት ነገር
- ከኪሳቸው ነበር የሚያዋጡት የኮሚቴዎች የ 17ቱ ኮሚቴዎች ስም ዝርዝር ያለበት ወረቀት አይተዋል የእርሶን ስም ጨምሮ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ አይቼአለሁ
- አይተዋል የተሰበሰበውን ፒቲሽን አላዩም አብረው ከእሱ ጋር ?
- ተጠይቋል
- ቅድም የተወሰኑ መስሪያ ቤቶች የተወሰኑ ስብሰባዎች ላይ ነው የተገኘሁ ብለዋል የመንግስት የሚገቡ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርሙ ነበር እርሶ እንደኮሚቴ አባልነተዎ ይፈርሙ ነበር ለመንግስት ተቋማት /ግልፅ ያልሆነ / ደብዳቤዎች ?
- የተወሰኑ ደብዳቤዎች ላይ ፈርሜአለሁ
- እኮ ባይገኙም የተገኙበትን ቦታ መጥቶ ያስፈርሞት እና ይፈርሙ ነበር ?
- የተወሰኑ ደብዳቤዎች ላይ
- ከአዲስ አበባ ውጪ የሄዳችሁበት አግባብ ነበር ከኮሚቴዎቹ ጋር ?
- ለሰደቃ ፕሮግራም ክፍለ ሀገር ሄደናል የተወሰነ ጊዜ
- ማለት ምንድን ነበረ እንቅስቃሴው ምን ይመስል ነበር ሰላማዊ ነበር ?
- ከአወሊያ የተለየ አልነበረም
- ቆዩ. ቆዩ. አሁንም በ ዞን ጥያቄአችሁ ይስተካከለ እንቅስቃሴው ምን ይመስል ነበር ጠቅለል የሆነ ሰፊ የሆነ መልስ ነው ያለው ስለዚህ እሱ ውስጥ የምትፈልጉትን ጥያቄ ብቻ
- ምንም የተፈጠረ ችግር አልነበረም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚህ በኋላ አንድም ድግግሞሽ አናስተናግድም ምን ተፈጠረ የሚለው ስንተኛ ተጠይቋል አሁን
- ምን ስለሆኑ ነው የተመረጡት ?
- ይሄም ተጠይቋል
- /ግልፅ ያልሆነ/ ጉብተን ወደ 6 ሰዓት አካባቢ ድረስ አናግረናቸዋል ብለዋል ምንድን ነበር ያገኛችሁት ምላሽ አጭር እና ግልፅ አድርጉ?
- መጅሊሱ
- ጥያቄዎቹን እነዚህ እነዚህ ናቸው ብላችሁ አስረድታችሁ በምን አግባብ /ግልፅ ያልሆነ ?
- መጅሊሱን በተመለከተ ምርጫ ይካሄዳል ነው እንጂ መቼ ይመረጣል ማን ይመረጣል የሚለው ነው ያልተስማማን እና መጨረሻ ያላወቅነው

2909

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሪሻለ ያሉሀ ፲/ በተመለከተ ምን ምላሽ ተሰጣችሁ መጅሊስን በተመለከተ ምርጫ ይደረጋል ተባለ ሀባሽን እና የአወሊያን በተመለከተ ምን ይደረጋል ተባለ ምላሽ አልተሰጠም ወይስ ምንድን ነበር ?
- መልስ አላገኘሁም እኔ እስከማውቀው ድረስ መልስ አላገኘንም
- ያኔ መልስ አልተሰጣችሁም ጨርሻለሁ
- ድጋሚ ጥያቄ ዐቃቤሕግ
- ከመጨረሻ ሰደቃ ፕሮግራሞች በየ ከአዲስ አበባ ውጪ ይደረጉ ነበረ ብለዋል በተደጋጋሚ ጊዜ የተፈጠረ ችግር አለ ወይ የለም ሲባሉ አላውቅም ብለዋል በእነዚህ ሰደቃ ፕሮግራም እንዲሁም እርሶ ባልነበሩበት አወሊያ ት/ቤት ይደረጉ የነበሩ ቅስቀሳን በተመለከተ የሚያውቁት ነገር አለ ለምሳሌ ሕገ ወጥ ቅስቀሳ ይደረግ አይደረግ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- የማውቀው ነገር የለኝም
- ሰደቃዎቹን የምትከታተሉበት በምንድን ነው እንዴት ነበር የምትከታተሉት ሰደቃዎቹን ?
- እያንዳንዱ ክልል ኮሚቴዎች አሉ የአካባቢ የሙስሊም ተጠሪ ሕብረተሰቦች ይሰባሰባሉ ያዘጋጃሉ ሰደቃውን እዚያ ከኮሚቴው ማብራሪያ እንዲሰጥ እና ጥያቄው የት ላይ እንደደረሰ የተወሰነ ጥያቄ ይቀርባል የተወሰነ ኮሚቴ አባል በየክልሉ ይሄዱ ነበር
- አሁን እነዚህ ሰደቃ ፕሮግራም ኮሚቴው ያው ጋይድ ያደርጋል ሰደቃውን እናንተ በኮሚቴ ተሰባሰባችሁ ከተነጋገራችሁበት ውጪ ቅስቀሳ ይደረግ አይደረግ የምታውቁት ነገር አለ ወይ ነው ?
- የማውቀው ነገር የለኝም
- የለም ሀባሽ ምንድን ነው ሀባሽ አስተምሮ ነው አንድ የኃይማኖት አስተምሮ ነው ?
- ሀባሽ በመሰረቱ ከእስልምና
- ቅድም ቆይ ፕሮፌሰር ቅድም ሲነግሩን የራሱ ካምፕ አለው መብቱ ነው ሕገ መንግስታዊ መብቱ ነው ብለዋል ስለዚህ አስተምሮ ነው አንድ አስተምሮ ነው ?
- ከሙስሊሞቹ ከእስልምና ማዕዘን የተለየ ነው ያለው መመሪያ
- አይደለም ቆይ አሁን ምንድን ነው እንትኑ የተለየም ይሁን የራሱ አስተምሮ አለው ወይ ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ አለው
- ስለዚህ እራሱን የቻለ አስተምሮ ሊስፋፋ አይገባም የራሱን ካምፕ በራሱ ካምፕ ትምህርቱን ያስተምር የሚል ጥያቄ ነው የእናንተ ?
- አዎ
- ኮሚቴውም ያንን መሠረት አድርጎ ነው የተነሳው ?
- ይሄ ነው መሠረተ ኃሳብ
- ቅድም ስለኮልፌ ቀራንዮ ሲናገሩ ፖሊስ ጋር ተያይዞ ፖሊሶች ናቸው የጠሩን አርብ አርብ ያለው ነገር እየተቸገርን ነው ብለዋል ብለዋል አይደል ?
- እሺ ምንድን ነው ተቃውሞ
- እየተቸገርን ነው የሚለው ምስከሩ ያላሉትን ዐቃቤ ሕግ እያስደገሚቸው ነው እና ወይም ጥያቄውን አስተካክለው ምስከሩ ያሉትን እንዲደግሙ
- አስተካክለው ይጠይቁ እሱን
- ተመዝግቧል አዎ እኮ አሉ አስተካክላለሁ
- አዎ ተብሎ የሚመለስ ጥያቄ ያለው ነው ስለዚህ እሱን አስተካክላችሁ ጠይቁ አሁን ጊዜ ከምንጨርስ
- እሺ እስቲ ይንገሩን ኮልፌ ቀራንዮ እናንተ ለምንድን ነው የተጠራችሁት ማለት የደህንነት የፀጥታ እንዲሁም ፖሊስ ነው የጠራን ብለዋል ሲነግሩን ደግሞ አርብ አርብ የሚደረግ የነበረው ድንጋይ የማይወረወርበት ከሆነ ሰላማዊ ከሆነ እናንተን ጠርቶ ማነጋገር ለምን /ግልፅ ያልሆነ/
- በግልፅ የነገሩን አርብ አርብ እየተቸገሩ ስለሆነ ይሄ ሰው በብዛት መሳተፍ ወደ ሕገ ወጥ መንገድ የሚሄድበት አዝማሚያ እንዳይመጣ በአስቸኳይ መፍትሔ ማግኘት አለበት መቆም አለበት ይሄ ስብሰባ የሚል ጥያቄ ነው የጠየቁን
- እንዲህ እየተቸገርን ነው ብለው ገልፀዋል ?
- አዎ ምክንያቱም ለእነሱም መሳተፉ መዘጋጀቱ ችግር እንዳመጣባቸው ነው
- እሺ በመስቀለኛ ጥያቄ ቅድም ሲጠየቁ የኮሚቴ ዝርዝር ያለበት እና ፒቲሽን ያለበት አይተዋል እንዴ እርሶ ?

2911

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፒቲሽን መኖሩን ሰምቼአለሁ እንጂ አላየሁም
- አላዩም ?
- ኮሚቴ ስም ዝርዝር ያለበት ግን የእኔም ስም ያለበት አይቼአለሁ የ 17ቱን
- በፒቲሽን ላይ ምን ያህል ሰው እንደፈረመስ ኮሚቴው ላይ ማለት እንደኮሚቴ የቀረበላችሁ ነገር አለ ይሄንን ያህል የፒቲሽን
- እስቲ ቆይ አላውቅም ነው ያሉት መኖሩን በወሬ ደረጃ ሰማሁ እንጂ የማውቀው ነገር የለም ነው ያሉ ቀጥሉ
- ድንጋይ ሳይወረወር እስከዛሬ ቆይቷል ብለውናል ፖሊሶቹ ብለውኛል ኮልፌውን ማለት ነው የኮልፌው መቼ ጊዜው እስከ መቼ ነው ይሄ ድንጋይ እስካሁን ሳይወረወር ሰላማዊ ሆኖ መቆየቱ ጥሩ ነው ብለዋል ብለዋል እስከ መቼ ድረስ ነው ይሄ ጊዜውን ያስታውሳሉ ?
- የአፍሪካ አንድነት ስብሰባ እስከተካሄደበት ዕለት ድረስ ምንም ረብሻ አልነበረም
- ከእዚያ ውጪ አሁን በገለፁት እኔ ሰላማዊ ባይሆን ኖሮ እዚያ ኮሚቴ ውስጥ የገባሁት ሰላማዊ ስለሆነ ነው ብለዋል ነገር ግን ንብረት ሰው አካል ላይ ጉዳት መድረሱን የሚያውቁት ነገር አለ ?
- ምንድነ ነው ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ በዋና ጥያቄ ላይ አልተነሳም ምስክሩም አልመለሱም እኛም መስቀለኛ ላይ አላነሳነውም በድጋሚ ጥያቄ ላይ አዲስ ነው እየተጠየቀ ያለው እና ሊጠየቅ የማይገባ ጥያቄ ነው ይሄ ነው ተቃውሞአችን
- ምላሽ ስጡበት
- ፍ/ቤቱ ደጋግሞ ይሄ ጥያቄ ተደጋግሟል የተፈጠረ ችግር የለም ወይ እየተባለ በተደጋጋሚ ጊዜ ተነስቶ ይሄ ነገር ተነስቷል ተብሎ በተደጋጋሚ ጊዜ እንዲቆሙ ተደርጓል ሰላማዊ አይደለም ወይ የተፈጠረ ችግር አለ ወይ ብሎ ሲጠየቅ ሰላማዊ ነው ማለት ነው አማርኛው አሁን ሰላማዊ ነው ሲባል እሱ ይሄ ጉዳይ መከሰቱንስ ያውቃሉ ተብሎ ነው የተጠየቁት ስለዚህ የተፈጠረ ችግር የለም ወይ ማለት እኔ ግልፅ ነው የሚመስለኝ ችግር የለም በሰላም ነው የተጠናቀቀው እያሉ ነው የጠየቁት ስለዚህ የተጠየቀ ጥያቄ ነው
- እሺ ብይን ሰጥተናል የግራ ቀኙን ተመልክተናል ስንመለከት ዐቃቤ ሕግ መጨረሻ ይብደባ የሚል ቃል ወይም የአካል ጉዳት ደርሷል አልደረሰም የሚል ቃል ነው መጨረሻ ላይ ግን

2918

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ስለሚገዛበው ጉዳይ ችግር አለ የለም የሚል ነው ሰላማዊ ነው አይደለም የሚል ነገር ምስክሩ ሰላማዊ ነው ብለዋል ከእዚህ ጋር የሰላም ተቃራኒ ችግር ነው የሚሆነው ዐቃቤ ሕግ እዚህ ላይ የሚያረጋግጡት ነገር ካለ ተገቢ ነው ብለን ብለናል ቀጥሉ

- ልድገመው ፕሮፌሰር ስምተውኛል ጥያቄውን
- ጥየቄው በሁሉም ቀን ነው የተፈጠረ ችግር መሮር አለመኖሩን እንዴት ያውቃሉ ነው ?
- አዎ ማለት እሺ ልድገምላቸው ተደጋግሞ ሲጠየቅ ችግር ተፈጥሯል ማለት በእዚህ በነበረው ሂደት ችግር የተፈጠረ ችግር አለ ወይ የለም ሲባሉ እኔ እስከማውቀው ሰላማዊ ነበር ብለው የነገሩን እስከ 6 አይደል ?
- እስከ አፍሪካ አንድነት ስብሰባ
- አዎ እስከዚያ ድረስ
- ዋዜማ ድረስ
- ከእዚያ በፊትም ከእዚያ በኋላ ግን ችግር ተፈጥሮ በሰው በንብረት ጉዳት መድረሱን ያውቃሉ ወይ ?
- የማውቀው ነገር የለኝም
- የሚያውቁት ነገር የለም ቀድም ሲጠየቁ በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ እነዚህ 3ቱ ጥያቄዎች የሕዝብ ጥያቄ ናቸው ወይ ሲባሉ ይመስለኛል ብለዋል ?
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- ጥያቄው የሕዝብ ጥያቄ ነው ተብሎ ሲጠየቁ አዎ የሕዝብ ነው ያሉት እንጂ ይመስለኛል አላሉም ዐቃቤ ሕጉ ወደያልፈለጉት አቅጣጫ እየወሰዱ ስለሆነ ወይም ምስክሩ ያልመሰከረ ስለሆነ ጥያቄው እራሱ ሊሰረዝ ይገባል የተከበረው ፍ/ቤት ዕድልም ሊሰጥ አይገባም
- ምላሽ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ችሎት እኔ የመዘገብኩት ነው የሚለው ምንድን ነው ይሄ ጥያቄ የሕዝብ እነዚህ 3 ጥያቄዎች የሕዝብ ጥያቄ ናቸው ወይ ሲባል ፒቲሽን ተሰብስቦ መጥቷል ተብሏል ስለዚህ ከእዚህ በመነሳት የሕዝብ ጥያቄ ይመስለኛል ብለዋል ምናልባት አሁን የሚያከራክር ከሆነ ድጋሚ ደግሜ ልጠይቃቸው እችላለሁ ግን እኔ የመዘገብኩት ነው ከእዚህ ተነስቼ የሕዝብ ጥያቄ ይመስለኛል የሚለው ነው እኔ የያዝኩት መልስ ማለት ነው

2913 ረ1063

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኛም ቀደም ብለን እንደያዝነው ምንድን ነው የሚለው ምስክሩ ይሄ ጥያቄ የሕዝብ ነው የኮሚቴው ነው ተብሎ ተጠይቋል ከተጠየቀ በኋላ ሲወርድ ሲዋረድ በብዙ መድረኮች ለሕዝብ ነው እየተባለ እየመጣ እኛም መጨረሻ ላይ ለሕዝብ ነው ብለን የመውሰድ ነገር ዓይነት ነገር ስላለ ጥያቄው የተረጋገጠ የሕዝብ ነው የሚል አልያዝንም ስለዚህ ይሄንን ማስተካከል የሚችሉ ከሆነ እና ምስክሩም የሚያረጋግጡት ነገር ካለ ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥሉ ብለናል
- ይመልሱ ፕሮፌሰር
- ጥያቄው የሕዝብ ጥያቄ ነው የሕዝበ ሙስሊሙ ጥያቄ ነው ስለዚህ እኛም ጥቆማ የመጣው ከእዚያው ከተሳተፈው ሕዝብ ሙስሊም ነው
- እሺ ያዳምጡ
- እና የሕዝብ ጥያቄ ነው ማለት እችላለሁ እንጂ ይመስለኛል ማለቴ አይደለም
- እሺ የሕዝብ ጥያቄ ነው ከተባለ ቅድም ሲጠየቁ ፒቲሽን ምን ያህል ሰው ነው ሕዝበ ሙስሊሙ ምን ያህል ነው በቁጥር እርስዎ ያውቃሉ አይደል እስታስቲክስ አለዎት ምን ያህል ነው ?
- የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ ነው ከ 25 ሚሊየን ከ 30 ሚሊየን በላይ ነው
- በላይ ነው ?
- አዎ
- ፒቲሽን ላይ ፊርም የሚባለው ምን ያህል ነው እርሶ እንኳን ተነገረኝ ያሉት ?
- ዝርዝሩን አላውቅም እሱ ፒቲሽን ላይ አላውቅም ስንት እንደመጣ
- እስቲ ዐቃቤ ሕግ ያው ፒቲሽን እኮ አላዩም ካላዩ
- አይ ተነግሮኛል ብለዋል እኮ በቁጥር
- ዋናው ጥያቄ ግን የእኛ እንደ እምነት
- ተነግሮታል ምን ያህል እንደሆኑ ?
- አዎ አልተነገረኝም እንደ እምነት ውስን ሰው እንኳን ቢጠይቅ የእምነቱን በተመለከተ የሁሉም ጥያቄ እዚያው ይቆጠራል በድምፃችን መሠረት
- ተደርጎ ይቆጠራል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስም
- እሺ ፕሮፌሰር ቅድም በዋና ጥያቄ ስንጠይቆት በአወሊያ ምርጫው ላይ አልነበርኩም ነገር ግን ተመርጠሀል ወይም ተጠቁመሀል ተብዬ በአቡበከር ተነግሮኛል ብለዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ኩርቱ ሕንፃ ላይ አብዛኛው የተመረጠው ወጣት ስለሆነ የተወሰኑ ሰዎች ተጨምረዋል ብለዋል እና እንዴት ነው መጀመሪያ ላይ የነበረው ምርጫ በድጋሚ ተስተካክሏል ማለት ነው እስቲ ይሄንን ግልፅ ያድርጉልን ?
- እኔ ኩርቱ ሕንፃ /ግልፅ ያልሆነ/ አቡበከር ተጠርቼ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ስለጠቆመህ እዚህ ኮሚቴ ውስጥ እንድትሳተፍ ብሎ ሲጠይቀኝ እኔ የልብ ኬዝ አለኝ መሳተፍ አልችልም ስለው አይ አንተ በምክር ሰጪነት ትቀጥላለህ ግድ የለም ብዙ ጊዜ አላቃጥልም የሚለውን ነው የተሰጠኝ ማለት
- አይ ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ስለእርሶ ሳይሆን አሁን የጠየኩት መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ሲጠየቁ አብኛው የተመረጠ ወጣት ስለሆነ የተወሰኑ አባላት እንዲጨመሩ ወይም ደግሞ መጀመሪያ የተመረጡት ወይም የተጠቆሙት ላይ ማሻሻያ ተደርጓል ስንት ሰው ተጨመረ ስንት ሰው ተቀነሰ እስቲ ወይስ መጀመሪያ ላይ የነበረው የተመረጡት ሰዎች ሪቫይስ ተዮርገዋል ማለት ነው ስለዚህ የሚያውቁት ነገር ካለ ግልፅ ያድርጉ ?
- የ17ቱን ስም ዝርዝር ሲያቀርቡልኝ የዕድሜ ባለፀጋዎች አሎማዎች እንዳሉበት አይቼአለሁ ከእዚያ በፊት እነ ማን ተመረጡ እነ ማን ነበሩ አላውቅም
- እሺ ይሄንን ከማን ነው የሰሙት አብዛኛው የተመረጠው ወጣቱ ነው ስለዚህ ያንን ማሻሻል አለብን ያለው ማን ነው ?
- እዚያው በዕለቱ ነበር በአቡበከር ቢሮ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ማን እንደተመጠረ ስለማላውቅ የመጀመሪያውን በአዲሱ መዋቅር ግን የተዋቀሩትን ስም ዝርዝር አይቼአለሁ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ለማለት ነው እንግዲህ 17ቱ
- እርግጠኛ ሆነው ይሄንን ነገር ይግለፁት ትንሽ ?
- የመጀመሪያውን ስለማላውቅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት *

2915

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በቃ ይበቃል /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ሌላው እነዚህ አሁንም በድጋሚ ጥያቄ ሲጠየቁ አረጋግጠው የገለፁት ነገርአለ ይሄ ጥያቄ ሕዝበ ሙስሊሙ ጥያቄ ነው ያሉት ነገር አለ እንዴት ነው እነዚህ 3ቱ ጥያቄዎች ተለይተው ተርበው ነጥ ወይስ በአወሊያ መጀመሪያ ላይ ከተማሪዎች በአወሊያ ኃይማኖት ት/ቤት ጋር ከነበረው አለመስማማት ጋር ተያይዞ የነበረውን ጥያቄ ነው
- መቃወሚያ አለ
- መቃወሚያ
- አሁን እያነሱ ያሉት ጥያቄዎቹን ፅፈው ሰጥተዋችሁ ነው ስለዚህ ኢሹ አልተነሳም ሲጀመር በዋና ጥያቄም አልተነሳም በመስቀለኛም አላነሳንም አሁን በማጣሪያ የሚያነሱበት አግባብ የለም
- ማለት የትኛው
- የተማሪዎቹን በተመለከተ አሁን ዐቃቤ ሕግ የጠየቁትን እንደገና እነዚህ 3 ጥያቄዎች ናቸው ብለዋል 3ቱን ጥያቄዎች ማን ሰጥቷችሁ ነው የሚል ነው እያነሱ ያሉት ፅፈው ሰጥቷችሁ ነው ሕዝቡ ወይስ በምን አግባብ ነው እነዚያ ጥያቄዎች የወጡበትን አግባብ ነው እየጠየቁ ያሉት በዋና ጥያቄ አልተነሳም መስቀለኛም አላነሳንበትም በድጋሚ የሚጠይቁበት /ግልፅ ያልሆነ/ ሊያቆሙት ይገባል
- ምላሽ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄኛው ነጥብ በዋና ጥያቄም በመስቀለኛም እንዲሁም አሁን በድጋሚ ጥያቄ ከእኔ በፊት ባልደረባዬ አቅርቦ በነበረው ጥያቄ ላይ መቃወሚያ ሲያነሱ ይሄ ጥያቄ የማን ነው የሚለውን ነገር በተደጋጋሚ ያልጠራ ነጥብ ነው ያንን መሠረት አድርገን ነው በዋና ጥያቄ ያነሳነውን በመስቀለኛ የተነሳ ነው ይሄንን መሠረት አድርገን ነው ይሄንን ጥያቄ እያነሳን ያለነው ይሄ ጥያቄ የሕዝቡ ነው የተባለው ለኮሚቴው በምን አግባብ ቀርቦ ነው የሚለው ነጥብ ለፍ/ቤቱ መጥራት አለበት ስለሆነም ተቃውሞው ያለአግባብ ነው
- እሺ ብይን ሰጥተናል ዐቃቤ ሕግ ያነሱት የአወሊያ ተማሪዎች የሚል ነገር በግራ ቀኝ አልተነሳም እሱን ታቆማላችሁ ከእዚያ ውጪ ግን 3 ጥያቄዎች ከየት ቀነሱ የማን ናቸው ከየት ተሰጡ የሚለው በግራ ቀኙም የተነሳ ስለሆነ እሱን ቀጥሉ ብለናል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ፕሮፌሰር አሁን እስቲ ችሎቱ በገለፀው መልኩ እነዚህን ጥያቄዎች እንዴት ነው ከሕዝቡ ቀርቧል የሚለውን ነገር እርሶ 1ኛ ፒቲሽን አላየሁም ብለዋል እንደዚሁም በመጀመሪያው በምርጫ በነበረበት ወይም ጥያቄ በቀረበበት ቀንም አልነበሩም ከምን ተነስተው ነው እነዚህ ጥያቄዎች ከሕዝቡ የቀረቡ የሁኑ በኮሚቴው ሪፈረም የተደረጉ ይሁኑ ይሄንን በምንድን ነው የሚያውቁት እርሶ ?
- እነዚህ 3 ጉዳዮች የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ መነጋገሪያ አጀንዳ ነበሩ በወቅቱ ከጠረፍ እስከ ጠረፍ
- እኮ ጥያቄው ምንድን ነው እንዴት አወቁ ፒቲሽን አላዩ ሰውን ሰብስበው ደግሞ ትንሽ ቀን ነው የተሰበሰቡት ዓይነት ነገር ነው እንዴት አወቁ የሁሉ መሆኑን ነው ?
- አወሊያ ተሰብስበው መረጡ የሚለው ነው መረጃ የመጣልኝ
- እሺ
- በእዚያው መሠረት ነው የኮሚቴውን ስም ዝርዝር አቀረቡልኝ አንተም ተመርጠሀል አሉ /ግልፅ ያልሆነ/ በእዚያው
- በእዚያ ነው ያወቁት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ሌላው እርሶ እዚያ ኩርቱ ሕንፃ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰባሰቡት በእዚያን ቀን ነው ?
- አዎ የመጀመሪያዬ ነው
- ከእዚያም በፊት የኮሚቴው አባላቶች እየተገናኙ ከ 2001 ጀምሮ እንደሚሰባሰቡ ያውቃሉ ?
- ተመልሷል አዎ ተመልሷል ያው እሳቸ ው እየፈጠሩ ነው አላውቅም ብለዋል
- /ግልፅ ያልሆነ/ የተከበረው ፍ/ቤት
- ማን ነው ስምህ አህመድ ማን ነው አህመድ ሙስጠፋ ስንተኛ ተከሣሽ ነህ 9ኛ እሺ ምንድን ነው ቅሬታህ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እንግዲህ በእዚህ ጉዳይ ላይ በጣም ብዙ ስንነጋገር ቆይተናል ምናልባት ይሄንን ነገር ከእኔ ውጪ ያለ ዳኛ ቢሰጠው ኖሮ ጥሩ ነበር አሁን ደግሞ እዚሁ ምናልባት እኔ ጋር መሆኑ ዞሮ ዞሮ ግን ያው ችሎት ነው በችሎቱ መሠረት መዳኘት እና መከተል ያለ ነው እንግዲህ

2917 4066

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በሉኑ ያየ ዋጋም ብለው በማሪል የገዙ ነገሮች ጥሩ ነው ጋባቱሁን በገዛ ገልፃተሁ እና እንድናስብ ማድረግ እኛ ምንድን ነው ችግር አለ ችግር ከሌለ ይሄንን ሊናገሩ አይችሉም የሚል እንድናስብ አድርጋችሁናል አሁን ብቻ ሳይሆን በፊትም ማንናቸው እሳቸው አህመዲን ጀባል እሳቸውም ይሄንኑ ነው ያነሱት ያኔ የተሰጠ መልስ አለ ይሄንን ቅድም የነገርኳችሁን በጥሩ ጎን እንወስደዋለን ጥቆማዎቹ ለእኛ ይጠቅሙናል ነገር ግን ባለፈውም ተነጋግረናል አሁንም ተነጋግረናል ብዙ ጊዜ ነው በእዚህ ጉዳይ የተነጋገርነው ለዐቃቤ ሕግ በማድላት ወይም ለጠበቃ በማድላት እንነጋገር ነበር አላሰብንም እንግዲህ ይሄ ሆኖ እያለ ከእናንተ ጋር የምናየው ነገር ግን ትንሽ ወጣ ያለ እኛንም ለመምራት አሁን ይሄ አሁን እርሶ የተናገሩት ነገር በተለይ አሁን ስምዎን የነገሩን ተከሣሽ ንቀት ነው አንትኑ እሱን አትቆጣም ይሄንን ትቆጣለህ ይሄ በጣም አንድ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ፎርማል ጠበቃ አለ 1ኛ እኛ ብዙ ጊዜ ነው የምናልፈው ብዙ ነገር እኮ /ግልፅ ያልሆነ/ ጥሩ ነው ጥሩ አይደለም ባለፈው ተጠቃሚው ነው የሚያውቀው ብለናል እኛ ጥሩ ነን ስላልን እናንተ ጥሩ ነው ትሉናላችሁ ወይም ዐቃቤ ሕግ ጥሩ ነው ይለናል ብለን አይደለም እኛ የሚሰማንን የምናውቀውን ያህል እዚህ በምናውቀው ልክ እየሰራን ነው ብለን ነው የምናስበው ስለዚህ ከእዚህ ላይ እንዲህ ዓይነት ወደ ፊት እንዲህ ዓይነት ወጣ ያለ ወይም ሳታስፈቅዱ ማጉረምረም ወጣ ብሎ ደግሞ ችሎቱን ማናናቅ እነዚህ እነዚህ ነገሮች ለችሎቱ አካሄዱ ጥሩ አይደለም ጠበቆችም ቢሆኑ እኔ መቼ ለይተን እኔ ትዝ አይለኝም በግሌ ችሎቱን ለማስከበር ስንል ነው እናንተ ጋርም ጠበቆችም ጋርም የግል እንትን ያለው ሰው የለም እዚህ ስለዚህ ይሄንን መሠረት አድርጋችሁ ብትከታተሉ ይሻላል እርሶ በተለይ እንዲህ ዓይነት ነገር ሁለተኛ እንዳይደግሙ 1ኛው ይሄ ነው 2ኛ ዳኛ አድሎ በሚያደርግበት ጊዜ ወይም አድሎ በሚሰራበት ጊዜ የራሱ መፍትሔ አለው እሱም ባለፈውም ነግረናችዋል ከጠበቆቻችሁ ጋር ተነጋገሩ ብለናል ዳኛ /ግልፅ ያልሆነ/ መነጋገር ያለባችሁ እንጂ ችሎት እየተካሄደ ምስክር ተቀምጦ ተሰይሞ ሁላችሁም አንድ ጊዜ የምትናገሩበት ይሄ ከችሎት ስነ ስርዓት ውጪ ነው የሚሆነው ግን እኛ የምናስበው ነገር ምንድን ነው እያንዳንዱን ነገር ችሎት ላይ የተሰየመ ሰው እጅግ ወጣ ያለ ነገር ካልሆነ በስተቀር አቻችሎ መምራት ተገቢ ነው ብለን ስለምናስብ ነው እስካሁን ድረስ ብዙ ጥፋቶች የሉም ማለት ጥፋቶች አሉ ግን ኮሽ ባለ ቁጥር እያንዳንዱ ነገር አንተ እንዲህ ነህ አንቺ እንዲህ ነህ እየተባባለ መሄዱ እሱ ጠቀሜታ የለውም ደህና እየሄደ የነበረው ዛሬ ምን እንዳስነሳው እኛ አናውቅም እንግዲህ ስለዚህ በግራ ቀኝ በኩል ለእኔን

2918

http://ethcriminalawnetwork.com/

/ግልፅ ያልሆነ/ ማስጠንቀቂያ እና ምክር እስቲ ጥያቄው ምን ነበር ተቃውሞ አቅርበሀል ጥያቄውን አስታውሱን

- ጥያቄው ከእዚህ ኩርቱ ሕንፃ በተባለው ቦታ ላይ መሰብሰባቸውን ገልፀዋል ነገር ግን ከእዚያን ቀን በፊት ስብሰባ ሄደው ያውቃሉ ወይ አላውቅም አሉ ሌሎች ከእዚያን ቀን በፊት ስብሰባ ስለማድረጋቸው ያውቃሉ ወይ ነው የእኛ ጥያቄ ጊዜን ጠቅሰናል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን አስተካክለዋል ዞሮ ዞሮ ግን ምስክሩ የመለሱት መሰለኝ ስለዚህ ቅድም የጠየቁት የተከበረው ፍ/ቤት ከ 2001 ጀምሮ ነው
- ስለዚህ አሁን ተስተካክሏል በእዚህ አግባብ ችግር የለውም ነው ?
- አይ አላውቅም ብለው መልሰዋል ምስክሩ ተመልሷል ተመልሷል ጥያቄው አላውቅም ስላሉ
- ስለዚህ እናንተ ትታችሁታል ?
- አዎ
- እሺ አላችሁ ጥያቄ
- አለን ቀጣይ ጥያቄአችን ፕሮፌሰር በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ሀባሽ በግድ ሊጫንብን አይገባም ወይም በራሱ ካምፕ ውስጥ ብቻ ሊሰብክ ይገባል የሚል አቋም ነበረ ብለዋል ነገር ግን ከእዚህ የተለየ ከእዚህ በተለየ አገላለፅ ለምሳሌ ሀባሽ ይወገዳል ተጠራርጎ ይወጣል የሚባል ነገር ስለመባሉ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት የድጋሚ ጥያቄን ከዋና ጥያቄ ጋር ቀላቅለው ነው እየጠየቁ ያሉት እና በተጨማሪም መሪም ነው እና 1ኛ አልተነሳም ስለሀባሽ የተመለከተ የተጠየቀው ግልፅ ነው ለፍ/ቤቱ አሁን ግን ዐቃቤ ሕግ እየጠየቁ ያሉት በዋና ጥያቄ ያልተነሳ በመስቀለኛ ያልተነሳ አዲስ ጥያቄ ነው እና ይሄ ተገቢነት የሌለው ጥያቄ ነው ሊጠየቅ አይገባም ይሰረዝልን ነው
- ምላሽ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄአችን መሪም አይደለም በዋና ጥያቄ እና በመስቀለኛ ጥያቄ የተስተባበሉ ነጥቦችን መሠረት አድርገን ነው የጠየቅነው ይኸውም 3 ጥያቄዎች እንዳቀረቡ ከገለፁ በኋላ በመስቀለኛ ጥያቄ በተለይ ከሀባሽ ከሚል አስተምሮ ጋር ዝርዝር ሀባሽ አለ የለም ወይ ካምፓችሁ ውስጥ ብቻ ካምፕ አላቸው ካምፕ ውስጥ እንደዚህ ማስተማር አለባችሁ የሚል እንደዚሁም ኮንፈርሜሽን ስጥተው ነገር ግን ማንም ሌላው እንዳያስተምር

2919 24068

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መከልከል አይችልም የእኛ እንትን ያልንበት የተቃወምንበት መንገድ ሰላማዊ ብቻ ነው የሚል ነው በመስቀለኛ ጥያቄ የተሰጠው መልስ እኛ ደግሞ ይሄንን ለማስተባበል ድጋሚ ጥያቄ እንትኑ አስፈላጊነቱ ያው የተስተባበሉ ነገሮችን ለማጠናከር ወይም ደግሞ ሌላ የተሰጡ መልሶችን ለማፍረስ ነው ስለሆነም እነሱን የሚነካ ነገር በተነሳ ቁጥር እንደዚህ ዓይነት መኖሩ ተገቢ አይደለም

- አሁን ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል አሁን መጨረሻ ላይ ዐቃቤ ሕግ ያነሳው ጥያቄ በአወሊያ ሀበሽ የሚባለውን ጠራርጎ ማስወጣት የሚል ነገር አልነበረም የሚል ነው በጠበቆች በኩል የተነሳው ይሄ በግራ ቀኙ አልተነሳም የሚል ነው እኛም ተመልክተነው ከምስክሩም ከጠበቆችም ከዐቃቤ ሕግም ሀባሽን ጠራርጎ ማስወጣት የሚል ቃል አልተነሳም ስለዚህ ይሄንን ጥያቄ እለፉት ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ሌላው እስቲ መዋጮ ላይ እዚህ የምትሰባሰቡባቸው ድርጅቶች ውስጥ ሁላችንም እናዋጣ ነበር ብለዋል መጀመሪያ ላይ በዋና ጥያቄ አንዳንድ ነገሮች ከድርጅቱ እዚያው ከተሰበሰበው ይቀርብልናል የሚል ነገር ያለው መልስ ሰጥተዋል አሁን
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ
- ጥያቄአችን አልጨረስንም
- ተቃውሞ አለን
- አልጨረስንም የተከበረው ፍ/ቤት
- እስቲ ቆይ ጨርሱ ጥያቄውን ጥያቄውን ይጨርሱት እና ቀጥሉ
- ጥያቄአችን እነዚህ በዋና ጥያቄ ሲጠየቁ መዋጮው
- ቆይ እስቲ አቤት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀጥሉ
- እሺ ፕሮፌሰር ጥያቄችን መዋጮ እዚያ በተሰበሰቡት አንዳንድ ሻይ ቆሎ ምን እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ይቀርቡልናል ብለዋል እርሶ እኔም አዋጥቼ አውቃለሁ ብለዋል እዚያው አዋጥተው እዚያው ክበብ አለ ግቢ ውስጥ ከስራ ሰዓት ውጪ እዚያው ነው የምትገዙት እንዴት ነው የሚቀርበው ?
- እሺ ቀጥሉዋ መልሱ ቆሎው ከየት ነው የሚመጣው

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥያቄው ግልፅ ቢሆን
- ጥያቄው ምንድን ነው በወቅቱ ቆሎ ይቀርብ ነበር ብለዋል አይደል ቅድም ሲጠየቁ ወጪው የስብሰባው ወጪ ማን ነው የሚችለው ምናምን ተብሎ ተጠይቀው ነበር አያስታውሱም ይሄንን ?
- ስብሰባው ቆሎ እና ውኃ ሻይ በቃ ከእዚያ ውጪ አልነበረም
- ይሄ የት ነው የሚመጣው ነው ?
- እዚያ የምንሰበሰብበት ቦታ ነዋ
- እኮ ከየት ነው የሚመጣው ከሻይ ክበብ ነው ከሆቴል ነው ከምንድን ነው የሚመጣው ?
- ከሻይ የሚሸጡ ጎረቤት አለ አይደል ሻይ ክበቦች ከእዚያ ነው እየገዙ የሚያመጧቸው
- ቀጥል
- እርሶ ሄደው ገዝተው አምጥተው ያውቃሉ ?
- ልጆች ያው ጥበቃዎችን ልኬ አስገዝቼአለሁ አንዴ /ግልፅ ያልሆነ/
- አሁን ከእዚሁ ጋር ተያይዞ ቦርድ ፈቅዷል ወይ አልፈቀደም በሚለው ላይ ስትሰበሰቡ ማለት ነው ኢንጅዎቹ ላይ እዚያ እንድትመጡ ኢንቫይት ያደረጋችሁ ወይም ደግሞ እዚያ ከእነዚህ ኤንጅዎች ጋር ተያይዞ ማን ማን ነው የነበረው ቢሮውን የፈቀደላችሁ ?
- በኢጋጣሚ ስራ አስኪያጁ የእኛ የኮሚቴ አባል ናቸው
- ማን ናቸው ?
- ለምሳሌ ሀጂ ሱልጣን የኮሜቴ አባል ናቸው
- የትኛው ድርጅት ?
- የሀልቢር
- የሀልቢር 2ኛውስ ?
- የሼህ እንትና የዳዋ የሰካፋ አባል ናቸው
- የምኑ የኮሚቴው አባል ስለሆኑ ?
- የኮሚቴ አባል ናቸው
- ስለዚህ ቢሮ የገባችሁት በእነሱ ፍቃድ ነው ?
- በእነሱ ፍቃድ ነው

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በፍ/ቤቱ የቀነሳ ጥያቄ የለም እናመሰግናለን ይመለሱ አሁን 7ሰዓት ነው ያው ትንሽ ጊዜ ሊያጥር ስለሚችል 8 ተኩል 30 ደቂቃ ጨምረን እዚህ እንገኛለን፡፡

- ከሰዓት እንቀጥላለን
- እሺ ጠዋት የነበረው ችሎት ተከሣሾች ዐቃቤ ሕግ ፤ ተቀይሯል ማን ናቸው የተሰየሙት ?
- ብርሃኑ ወንድማገኝ ከሰዓት በኋላ ተሰይሟል ከተከሣሾች የቀረ የለም ተከሣሾቹም ከሰዓት በኋላ የቀረ የለም ከጠበቆች ጠዋት ያልነበሩ ?
- ሞላልኝ መለሰ ቀርቤአለሁ
- ቀርበዋል ያው ከሰዓት በኋላ ቀሪ የዐቃቤ ሕግ ምስክር እንዲቀርቡ ነው
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- በፍ/ቤቱ 96ኛ ምስክር በዐቃቤ ሕግ ክስ
- 57ኛ
- ስምዎን ማን ነው የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ነው የሚነግሩን ?
- አንበሴ /ግልፅ ያልሆነ/
- ለምንድን ነው የመጡት እዚህ ?
- ለምስክርነት
- እነ ማን በተከሰሱበት ነው ?
- አይ እነ ማን የተከሰሱበት ሳይሆን አጠቃላይ ጀነራል በወቅቱ ሐምሌ 6/2005 የተፈጠረውን ሁኔታ ለመግለፅ ነው
- እሺ በማንም ላይ አይመሰክሩም በግለሰብ ደረጃ ተከሣሽ ግለሰብ ደረጃ
- ኢንዲቪዥዋሊ አይደለም
- እሺ ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ

2922

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን እንዳሉት ሐምሌ 6 እርሶ በአጠቃላይ የት ቦታ ምን ሲደረግ እንደነበር እና በዕለቱ ምን ሲፈፀም የነበረ መሆኑን የሚያስታውሱትን በዝርዝር ለተከበረው ፍ/ቤት ያው እንዲገልፁ እጠይቃለሁ ቀኑ ቦታው ሰዓቱ መቼ የት ምን ነበር የተሰራው እስቲ ?
- ቀኑ ሐምሌ 6 ነው
- ዓ.ም መቼ ነበር ?
- 2004 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 5 ሰዓት አካባቢ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02/03 ክልል ልዩ ቦታው አደሬ ሰፈር ባዩሼ መስኪድ አካባቢ ነው እኔ በወቅቱ ከላይ የተገለፀው ቀን እስታንድ ባይ ነበርን ምክንያቱም 1ኛ የአፍሪካ ሕብረት ጉባዔ አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ ነበር 2ኛ ደግሞ ሕብረ ሙስሊሙን ወደ አመፅ እና ሁከት ሲያገፋፉ የነበሩ በአዲስ አበባ ደረጃ 17 ኮሚቴ አለ እነኚህ 17ቱ ኮሚቴዎች ማታ ሰላማዊ ሰልፍ እንወጣለን ስላሉ ማንም ከጣቢያ እንዳይሄድ አመራሩ አባሉም ጣቢያ እስታንድ ባይ ሆናችሁ ቁጭ አሉ ተባለ 5 ሰዓት ሲሆን እኔ መርማሪ ነኝ ምርመራ ክፍል ቁጭ ብዬ ነበርኩኝ 5 ሰዓት ሲሆን ጩኸት ሰማሁ ጩኸት ሰምቼ ጣቢያ በር ፊት ለፊት ስወጣ በርካታ ሕዝብ ድምፃችን ይሰማ አላህ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ አይልም ፖሊስን ፈርተን ሳይሆን አክብረን ነው እንጂ ወደ ኋላ አትሉ ወደ ፊት ሂዱ የሚል ድምፅ እያሰሙ ወደ ጣቢያ እየመጡ ነበር ከእዚያ ጣቢያ ውስጥ የነበራችሁ ውጡ እና ይሄንን የማስወገድ ስራ ስሩ ተባለ ወጣን ስንወጣ ድንጋይ ውርወራ ነበር ጠርሙስ ምናምን ውርወራ ነበር በእዚያ በተወረወረው ድንጋይ እና ጠርሙስ እኔም ተፈነከትኩ የጣቢያው አዛዥ እንደኮማንደር ግርማይ እነ ኮንስታብል በየነ ኃይሉ እነ ቡሽራ ሀርባሳ በእዚያ በተወረወረው ድንጋይ እና ጠርሙስ የተጎዱ አባሎች ነበሩ ይሄ ነው በወቅቱ የተፈጠረው
- እርሶ ምን ነበር የደረሰቦት ጉዳት የደረሰቦት ጉዳት በአካልዎ ላይ ነው እንዴት ነበር ጉዳቱ ሕክምና አገኙ ?
- እኔ በወቅቱ መሀል ጭንቅላቴ ላይ ተፈንክቼአለሁ መሀል ጭንቅላቴ ላይ ተፈንክቼአለሁ 2ኛ ደግሞ የቀኝ እጄን ጡንቻዬ ላይ ተመትቼ በወቅቱ ሕመም ስለተሰማኝ ወደ ሕክምና ሄጃለሁ ይሄ ነው በእኔ ላይ የደረሰው ጉዳት
- በወቅቱ አሁን ቅድም ካሉት ከባዩሽ መስኪድ እነኚህ የሚ[...]ሁት ድንጋይ የሚወረውሩት ጠርሙስ የሚወረውሩት ከት ወዴት ነበረ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት እነኚህ በወቅቱ ቅድም

2923

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያኗቸው ማለት ነው ከባዩሽ መስኪድ አቅጣጫ የመጡት ድንጋይ የሚወረውሩት ጠርሙስ ይወረውሩ የነበሩት እንቅስቃሴአቸው ወዴት ለመሄድ ነበረ ረብሻውን ሲመሩ የነበሩት ?

- መነሻው ባዩሼ መስኪድ ነው ባዩሼ መስኪድ እና መርካቶ ፖሊስ ጣቢያ ብዙም ርቀት የለውም ከባዩሼ መስኪድ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ነው ሲመጡ የነበሩት እኛ የወጣነው 1ኛ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንዳይገቡ ተቋሙ ላይ ጉዳት እንዳይደርሱ ነው ወጥተን የመከላከል ስራ የሰራነው ወደ ጣቢያ ነው ሲመጡ የነበሩት ከባዩሼ መስኪድ
- /ግልፅ ያልሆነ/ እያደረጉ ነበር?
- ያው ተቋም ነው የመንግስት ተቋም ነው ምናልባት በእዚያን ሰዓት ሰላማዊ ሰልፍ የሚያስወጣው ምንም ነገር የለም ጣቢያው ላይ ጉዳት ማድረስ ነው 2ኛ ደግሞ ሕገ መንግስቱን /ግልፅ ያልሆነ/ ነው በቃ ሌላ ትርጉም የለውም
- ከእዚህ ጋር በተያያዘ ማለት ነው አሁን ቅድም ያኗቸው አባሎች የተለያየ ጉዳት እንደደረሰባቸው ገልፀዋል እና አሁን እርሶ ሕክምና አገኙ ከእዚያ በኋላ መቼ ተመለሱ ወደ ስራ ወይስ እስከመጨረሻው ነበሩ የእዚያን ጊዜ ?
- እኔም ከእኔም ጭምር ከጣቢያ አዛዡ ጭምር በወቅቱ የመጀመሪያ ሕክምና ተደረገልን እዚያው አካባቢ 18 ቀበሌ ጤና ጣቢያ አለ ወደ ቤታችን አልገባን ወይም ወደ ሆስፒቲል አልተኛንም ተመልሰን ወደ ስራ ነው የገባነው ለምን ከፍተኛ ሁከት ስለነበር የመጀመሪያ ሕክምና ተደረገልን ወደ ቀጣይ ስራ ነው የገባነው እንጂ ወደ ቤት የሄደ የለም
- እነኚህ ከእዚህ ከባዩሽ መስኪድ የመጡት ወደ ጣቢያ የመጡት ማለት ነው አሁን ቅድም እንደገፁት ከምሽቱ 5 ሰዓት ነበር እና እስከ ስንት ሰዓት ነው ይሄ ነገር ግርግሩ የቆየው ወይም ረብሻው የቆየው ?
- የተጀመረው 5 ሰዓት ነው ግን እስከ ስንት ሰዓት እንደዘለቀ ሰዓቱን አልያዝኩትም በወቅቱ እኔ ሰዓቱን የጀመረበት ሰዓት ነው ያየሁት እንጂ ያለቀበት ሰዓት ለማየት ሳይሆን በወቅቱ የተፈጠረውን ሁኔታ ለማረጋጋት ወይም ፀጥታ ሁኔታውን ለማስከበር ነው እንጂ ያለቀበት ሰዓት አልያዝኩትም
- እሺ ኮንስታብል ሲጀምሩ 17 ኮሚቴ ሐምሌ 6 ላይ 17 ኮሚቴ አመፅ ጠርተዋል የሚል ነው ያሉት አይደል ሁከት ለረብሻ ጠርቷል ነው ያሉት እሱን እስቲ ይንገሩን 17 ኮሚቴ የሚለውን እንዴት ነው ያወቁት ከየት ነው የሰሙት እሱን ይንገሩን ከእዚያ ጀምሮ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምናልባት ኢንፎርሜሽን ወይም ወሬ አይደበቅም
- እንዴት እንዳወቁ ብቻ ይንገሩን ?
- እኔ 17ቱ ኮሚቴዎችን በመልክም ሆነ በስም የማውቀው ነገር የለኝም ግን ሕዝበ ሙስሊሙ ወደ አመፅ እና ሁከት የሚያገፋፉን በአዲስ አበባ ደረጃ 17 ኮሚቴ አለ ሕዝበ ሙስሊም በሕዝበ ሙስሊሙ ያልተመረጡ የሚባል ወሬ የሰማሁት እንጂ እነኚህ በአካል
- ከየት ሰሙት ነው ?
- ማለት መርካቶ ነው የምንውለው ሻይ ቤት ስንቀመጥ ብዙ ወሬ እንሰማለን ከእዚያ አካያ ነው እንጂ እከሌ ነው የነገረኝ አር ደግሞ 17ቱ ኮሚቴ ውስጥ እከሌ ነው የሚባል እስፔስፊክ አላውቅም ግን በመልክም አላውቅም ግን 17 ኮሚቴ አሉ በአዲስ አበባ ደረጃ የሚባል ወሬ ነው የሰማሁት
- እሺ አሁን ሐምሌ 6 ላይ የነበረውን ጉዳይ ወይም የተፈፀመውን ነገር ልመስክር ነው የመጣሁት ነው ያሉን አሁን ይሄ ከገለፁዋቸው ኮሚቴዎች ጋር ማለት እንዴት እንደተገናኘ እሱን ?
- ያው መድገም ካልሆነ እኮ /ግልፅ ያልሆነ/ የሕብረ ሙስሊሙን ወደ አመፅ እና ሁከት የሚያገፋፉ 17 ኮሚቴ አለ በአዲስ አበባ ደረጃ በሕዝበ ሙስሊሙ ያልተመረጡ
- አሁን ምን መሰሎት ሐምሌ 6 ጋር ሐምሌ 6 ከተከሰተው ጋር በተያያዘ እነዚህ ሰዎች ይሄንን አመፅ እየመሩ ወይም ደግሞ ይቀሰቅሱ እንደነበር የምታውቁት መረጃ ካለ ያንን አብራረው ይንገሩን ነው ?
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- የተከበረው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ጥያቄው ሙሉ በሙሉ መሪ ነው ዐቃቤ ሕግ ያሉትን ችሎቱ ስለሰማ መድገም አያስፈልግም እና ጥያቄው መሪ በመሆኑ መሰረዝ አለበት 2ኛ እነዚህ ኮሚቴ የተባሉትን በስም አላውቃቸውም በአካል አላውቃቸውም እያለ እየመሰከረ ግድ ነው ገፍተው ለማገናኘት እየሞከሩት ያሉት ጥያቄው ተገቢነት የለውም መሰረዝ አለበት
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ችሎት መቃወሚያው አሁን መርቷል ከሆነ በግልፅ እራሳቸው ከተናገሩት ነው እየተከተለ ጥያቄው የመጣው እንጂ መርቼ የጠየኩት ጥያቄ የለም በግድ ሊያያይዙት ፈልገዋል የሚባል ግን መቃወሚያ የለም መርተዋል ከሆነ መርተዋል የሚባለውን

http://ethcriminalawnetwork.com/

በተመለከተ አሁን በገለፅኩት መልኩ አባቸው ከመለሱት ጥያቄ እያስከተልኩ ነው እየጠየኩ ያለሁት ከእዚያ ውጪ ገፍቼ ወይም ደግሞ እራሴ ለመመስከር ያደረኩት ነገር የለም አሁን በጠየቁት አግባብ ማለት ነው

- እሺ የግራ ቀኙን አዳምጠን ብይን ሰጥተናል ብይኑ ምስክሩ ቀደም ብለው 17 ኮሚቴዎች እያነሳሱ ነበር በእነሱ ምክንያት አመፅ ሊነሳ ነው እስታንድ ባይ ነበርን የሚል ምስክርነት ሰጥተዋል በእዚህ ዐቃቤ ሕግ ከእዚህ ተነስተው ጥያቄውን አቅርበዋል ምናልባት መሪ ሊያስመስለው የሚችል አንድ እነሱ እየመሩ ነበሩ የሚለው ነገር መሪ ሊያስመስለው የሚችል ነገር አለ ዞሮ ዞሮ ግን ጥያቄው ምንድን ነው ምንድን ነው ግንኙነቱ በእዚያን ቀን የነበረው ግንኙነት ምንድን ነው የሚል ነገር ያለው ጥያቄ ግን መብራራት አለበት እነዚህ ሰዎች እዚያ ከነበረው አመፅ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው መጣራት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል ስለዚህ ይሄንን መሠረት አድርጋችሁ መጨረሻ ላይ ያልነውን መሠረት አድርጋችሁ ጥያቄውን ጠይቁ
- እሺ ቀጥሉ ኮንስታብል ተረድተውኛል ጥያቄውን ወይስ ልድገምሎት
- እስቲ ይኸው ጥያቄው እነዚህ 17 ኮሚቴዎች እና ሐምሌ 6 ተካሄደ የተባለው ያ ድንጋይ ውርዋሮ የነበረበት እና እርሶ የተጎዱበት እንዴት ነው ያገናኙዋቸው ምንድን ነው ግንኙነታችሁ ?
- ማለት ይሄኛው ሐምሌ 6 የተነሳው እንደዋናነት ነው እንጂ እኛ ከእዚያ በፊትም አርብ አርብ እስታንድ ባይ ነን አመራሮች ኦረንቴሽን ይሰጡናል ኦረንቴሽን ሲሰጡን ምንድን ነው በአዲስ አበባ ደረጃ ሕብረ ሙስሊሙ እያነሳሳ ያለው 17 ኮሚቴ አለ እነሱ ናቸው ሕብረ ሙስሊሙ ወደ አመፅ እና ሁከት እንዲገቡ የሚያደርገው ስልጣንን በአቋራጭ ለመያዝ የሚሞክሩት እነሱ ናቸው ብሎ ኦረንቴሽን ነው የሚሰጡን ያንንም ቀን ማታ 17ቱ ኮሚቴዎች
- የእዚያን ቀን ሚናቸው ምንድን ነው ?
- የእዚያን ቀን ሚናቸው
- የእዚያን ቀን የነበረው ሚና ምንድን ነው ?
- የ 17ቱ ኮሚቴ
- አዎ ?
- እኔ አሁን 17ቱ ኮሚቴዎች ያንን ቀን

2926 4075

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልክ ነው አላውቃቸውም ብለሀል
- ነበሩ ውስጡ አሉ እያልኩኝ አይደለም
- ግልፅ ነው ቆይ ጥያቄውን አሁን ጥያቄው 17 ኮሚቴ እየቀሰሱ አመፅ እያስነሱ ነው እያልከን ነው እሱን ነገር ከእሱ ጋር እንዴት አገናኘሽው እነሱ መሆናቸውን እንዴት አረጋገጥክ ነው ጥያቄው ?
- አሁን በቀኑ በዕለቱ ሐምሌ 6 ላይ ነበሩ አልነበሩም የሚል ጥያቄ አይደለም ሐምሌ 6 የተነሳው እናንተ ተከላከሉ ተብላችሁ እስታንድ ባይ እንድትሆኑ የታዘዛችሁበት ጉዳይ ቀድመንም ሰምተናል አሁን ተነግሮናል አረንቴሽንም አለ ብለሀል ያን ቀን ይሄ አሁን የምትሉት ኮሚቴ ጉዳዩን ከእዚህ ከሐምሌ 6 ከተፈፀመው ጋር ግንኙነት ይኑረው አይኑረው ያገኛችሁት መረጃ ነበር ወይ የሰማኸው ነገር ካለ አጠር አድርገህ እንድትነግረን ነው ?
- አጠቃላይ እኔ ሐምሌ 6 ውስጥ እነሱ ይኑራቸው አይኑራቸው የማውቀው ነገር የለኝም ግን ሕብረ ሙስሊሙን ወደ አመፅ እና ሁከት የሚያገፋፉት እነሱ ናቸው የሚል ብቻ ነው የማውቀው
- ሰምተሀል እሺ በአካል ጉዳት ላይ በፖሊስ በወቅቱ ማለት ሰላም ለማስከበር በቦታው በነበረው የፖሊስ አባላት ላይ የደረሰውን ጉዳት ነግረኸናል ሌላስ ከእዚህ ውጪ የደረሰ ጉዳት አለ ?
- አባሎች ላይ ከደረሱ ጉዳት ውጪ ሌላ የደረሰ ጉዳት የለም
- የለም ነው አላየሁም ነው ማለት ከአካል ጉዳት ውጪ ማለቴ ነው ?
- ቅድም ገልጬዋለሁ ይሄ ከእኔ ባዩሼ መስኪድ አካባቢ ከነበሩ ሰዎች ቅድም ከጠቀስኳቸው ውጪ የተጎዳ ሰው የለም
- ሰው አይደለም ከሰው ውጪ ከሰው አካል ጉዳት ውጪ ?
- ንብረት ላይ አር ሌላ ነገር ላይ
- አዎ ?
- አይ
- እሱን አላየህም ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ጨረሰናል ዋና ጥያቄ የተከበረው ችሎት
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ኮንስታብል ቅድም ባዩሽ መስኪድ እና ፖሊስ ጣቢያው ቅርብ ለቅርብ ናቸው ብለዋል እዚያ ፖሊስ ጣቢያ ሆነው ባዩሽ መስኪድ ይታያል እንዴ እንደዚህ ወጥቶ ሌላ የሚጋርድ ነገር የለም ?
- ባዩሼ መስኪድ ለፖሊስ ጣቢያ ቅርብ ነው ምንም የሚከልለው ነገር የለም
- ሌሎች ብሎኮች ቤቶች የሉም ባዩሽ አሁን ፖሊስ ጣቢያ በር ላይ ወይም አጥሩ በር ላይ ሆኖ ወጥተው በቀጥታ ባዩሽ መስኪድን ማየት ይቻላል እንዴ ?
- በቀጥታም የላኛው ጣሪያ ይታያል ግን አመጣጣችሁ ቀጥታ
- ቆይ ስለአመጣጥ አይደለም አሁን ፖሊስ ጣቢያው በር ላይ ሆነው ወደ ባዩሽ አቅጣጫ ሲያዩ በመሀከል ሌሎች ቤቶች አሉ አይደል ከጣሪያው ውጪ ሌላው ነገር አይታይም ከፖሊስ ጣቢያው በር ላይ አጥሩ በር ላይ ቆሞ አንድ ሰው ወደ ባዩሽ አቅጣጫ ቢያይ በመካከል ሌላ ቤቶች ስላሉ በቀጥታ ማየት ይችላል እንዴ ከጣሪያው ውጪ ?
- መታየት ይችላል ግን ሰዎቹ የመጡት ከባዩሼ መስኪድ ወጥተው
- ስለ ሰዎቹ አይደለም
- ይታያል
- ቀጥታ ይታያል ሌላ የሚጋርድ ብሎክ ቤቶች ነገሮች የሉም ፊት ለፊት ይተያያሉ ?
- ቤት አለው መሀከል ቤት አለው ፎቅ አይደለም ዝም ብሎ ጣሪያ ነው ይታያል ባዩሼ መስኪድ ፖሊስ ጣቢያ በር ፊት ለፊት
- የሚታየው ጣሪያው ነው ?
- አዎ ጣሪያው
- ረብሻው ሲነሳ ቅድም ያሉት ጩኸት ሲነሳ እርሶ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ነበሩ አይደል ?
- ትክክል
- ከእዚያ ጩኸት ሰማችሁ ከፖሊስ ጣቢያ ወጣችሁ ወደ ባዩሽ አቅጣጫ ከባዩሽ አቅጣጫ የሚመጣውን ሰው ነው አይደል ያያችሁት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትክክል
- እንጂ ሲወጣ ከባዩሽ ይወጣ ወይም ከሌላ አቅጣጫ ይምጣ የሚያውቁት ነገር እኮ የለም እርሶ በወቅቱ ሲጀምር አልነበሩም አይደል ?
- ነበርኩኝ እንጂ
- ማለት ጩኸት ሰምተው እኮ ነው የወጡት ?
- አዎ ሰማሁ ጩኸት
- አሁን ጩኸት ሲሰሙ ሕዝቡ ከእዚያ ከባዩሽ አቅጣጫ ወደ እናንተ ወደ ፖሊስ ጣቢያው የሚመጣውን ሰው ነው ጋር ያያችሁት አይደል ?
- ከፖሊስ ጣቢያ ሲወጣ ከየት ይምጡ ከየት ይምጡ አይታወቅም የሚለው ግልፅ ነው ይታወቃል በላኛው በኩል 18 ጤና ጣቢያ ነው ያለው በታችኛው በኩል ባዩሼ መስኪድ ነው ያለው አመጣጣቸው ሰዎቹ ከባዩሼ መስኪድ ነው የወጡት ባዩሼ መስኪድ መጡ ወደ ጣቢያ ሲታጠፉ እኛ
- እስቲ ቆይ አሁን ጥያቄው ምንድን ነው ከተጮኸ በኋላ ነው የደረስከው አንተ ስለዚህ ከባዩሽ መስኪድ የወጡ ለመሆኑ እንዴት ነው የምታረጋግጠው ነው ?
- ከመውጣታቸው በፊት ከቡር ፍ/ቤት ሰዎቹ ከመውጣታቸው በፊት ወደ ጣቢያ ከመውጣታቸው በፊት እኔ ከቤት ወደ ስራ ስገባ ተሰብስበው ከቡና ተራ ጫፍ
- የት ላይ ነው የተሰበሰቡት ?
- ባዩሼ መስኪድ ፊት ለፊት ከቡና ተራ ጫፍ
- ውስጥ ነው ውጪ ?
- ውጪ ውስጥም ግቢው ሞልቶ ውጪ አስፋልቱ መንገዱን ዘግተው ኮብል እስቶን ነው እሱን ገዝተው ቆመው ነበሩ አመጣጣቸው ከእዚያ መሆኑ ግልፅ ነው ከእዚያ ነው የተረዳሁት ማለት ነው
- ስለዚህ እርሶ ጣቢያ ከመግባትዎ በፊት ባዩሽ መስኪድም ከባዩሽ መስኪድ ውጪም እስከ ቡና ተራ ሰው ነበረ ?
- ትክክል

2929

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ወደ ጣቢያው የመጣው ሰው ከመስኪዱ ያለው ይሁን ከውጪ እስከ ቡና ተራ የተሰለፈው ይሁን ይሄንን መለየት እኮ ያስቸግሮታል እርሶ አይደል ?
- እንደገና
- እርሶ ረብሻው ከተጀመረ በኋላ ስለሆነ የደረሱት ወደ እናንተ እየወረወረ የመጣው ሰው መነሻው ከቡና ተራ ጀምሮ እስከ አስፋልቱ ላይ ያለው ይሁን ወይም ከመስኪድ የወጣው ይሁን በትክክል መለየት ይችላሉ እንዴ ?
- በነገራችን ላይ
- ይችላሉ አይችሉም ?
- እችላለሁ ድንጋይ ውርወራ የተጀመረው 5 ሰዓት ነው እንጂ ሰው የተሰበሰበው 5 ሰዓት አይደለም ሻርፕ ግን ድንጋይ ውርወራ ወይም ጩኸት የጀመረው 5 ሰዓት ነው
- በዕለቱ ጊዜአዊ እርዳታ ተደርጎላችሁ ወደ ስራ ተመልሳችዋል ?
- ትክክል አዎ
- በዕለቱ በማግስቱም ለተጨማሪ ሕክምና ሄዳችዋል አይደል ሆስፒታል ?
- እንደገና
- በማግስቱስ ወደ ስራ ገቡ እንዴ ?
- በማግስቱ ስራ አልገባሁም ሆስፒታል ሄጄ ታከምኩኝ የተፈነከትኩበት ቦታ እንዲሰፋልኝ ተደረገ የሕክምና እርዳታ ተሰጠኝ አልገባሁም
- መቼ ወጡ በዕለቱ ተመለሱ አይደል ከሆስፒታል ማለት ወደ ሆስፒታል ሄዱ እና በእዚያው ዕለት ታክመው ተመለሱ አይደል ?
- ሩቅ አይደለም 50 ሜትር አይሞላም ከእኛ ጣቢያ 18 ጤና ጣቢያ ነው የታከምኩት ደም የማቆም ስራ ብቻ ነው የተሰራልኝ ያን ጊዜ
- ታክመው በዕለቱ አሁን በዕለቱ ረብሻው ዕለት የመጀመሪያ እርዳታ ተደረገላችሁ ወደ ስራ ተመለሳችሁ ከእዚያ በማግስቱ ወደ ሆስፒታል ሄዳችሁ ታከማችሁ አይደል ?
- ግልፅ ነው
- በዕለቱ ግን ታከማችሁ በዕለቱ ወደ ስራችሁ ተመልሳችዋል ?
- በዕለቱ በ 6 ታክምኩኝ ወደ ስራ ተመለስኩኝ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

2930 4079

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እረፍት ተሰጥቶት ወደ ቤት ሄዱ ?
- አይደለም በ 6 ሁከቱ ሲነሳ ተፈነከትኩ እንደተፈነከትኩኝ ጤና ጣቢያ ገባሁ 18 ደም የማቆም ስራ ተሰራልኝ ወደ ቀጣይ ስራ ተመልሼ ገባሁ በማግስቱ ነው ፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታል ሄጄ የታከምኩት በ 7 ማለት ነው
- እኮ ሆስፒታል እዚያው ቆዩ ወይስ ተመልሰው ወጡ በዕለቱ ፌዴራል ሆስፒታል ከሄዱ በኋላ ?
- ተመላላሽ ሕክምና ላይ ነበርኩኝ አልተኛሁም ተመላላሽ ሕክምና ነው የታከምኩት
- አሁንስ ድነዋል አይደል ቁስሉ አሁን አለ ?
- አቤት
- አሁን ሙሉ ጤነኛ ኖት አይደል ?
- እግዚአብሔር ይመስገን አሁን ጤነኛ ነኝ
- ኮንስታብል ጉዳቱን ያደረሰቦትን ሰው ለይተው ያውቃሉ አይደል እርሶ ?
- አይሰማም
- ጉዳቱን ያደረሰቦትን ሰው ለይተው ያውቃሉ አይደል ?
- ጉዳቱን የደረሰብኝ ግለሰብ በአንድ ጊዜ የሚወረወረው ጠርሙስ በአንድ ጊዜ የሚወረወረው ድንጋይ በጣም በርካታ ነው ከእዚያ መሀል እኔ እከሌ ይምታኝ እከሌ ይምታኝ የማውቀው ነገር የለኝም እኔ በተወረወረው ድንጋይ እና በተወረወረው ጠርሙስ መሀል መፈንከቴን ብቻ ነው የማውቀው
- ማን እንደመታዎት አያውቁም ?
- አላውቅም
- በእዚሁ ጉዳይ አሁን በደረሰቦት ጉዳት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ወንጀል ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38042 ቀርበው መስክረው ሰውዬው ተቀጥቷል አይደል እንዴ ?
- ትክክል ምስክርነት ቃሌን ሰጥቼአለሁ ሄጄ
- በእዚያ የተከሰሱ ሰዎች ተቀጥተዋል አይደል በእርሶ ላይ ጉዳት ያደረሱ ?

2931 2108D

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በወቅቱ እዚያ ሄጄ ምስክርነት ቃሌን ስሰጥ የፈነከተኝ አብዲ ነው መሐመድ ነው አላልኩትኝም እነኚህ ሰዎች ፊት ለፊት ነበሩ
- አይ ያልኮት በእርሶ ምክንያት እርሶ ላይ ጉዳት አደረሱ ተብለው የተከሰሱ ሰዎች ተቀጥተዋል አይደለም ወይ ነው ያልኩት ?
- አይስማም
- በእርሶ ላይ ጉዳት ያደረሱት ሰዎች
- ጥያቄው ምንድን ነው በእርሶ ላይ ጉዳት ያደረሱ ሰዎች ተለይተው ተቀጥተዋል በእርሶ ላይ ጉዳት አድርሰው በእዚህ ምክንያት ሄደው መስክረዋል ነው ?
- ሄጄ መስክሬአለሁ ፊት ለፊት ቆሞ ድንጋይ ሲወረውሩ ነው ያልኩት እንጂ እከሌ ነው የመታኝ ብዬ ቃሌን አልሰጠሁም በእዚያን ሰዓትም
- ሰዎቹ ተቀተዋል አይደል ወይም መቀጣት አለመቀጣታቸውን አያውቁም
- ሌላ ጥያቄ ቀይ ይኸውሎት አሁን ይሄ ሚዛን ነው የሚሆነው ስለዚህ ሄደው መስክረዋል የተከሰሱ መሆኑን ገልፀዋል ከእዚያ በኋላ ስለቅጣቱ እሱ ምን
- እሺ
- ቅድም ሲያስረዱ ኮንስታብል ሰው መሰብሰብ የጀመረው 5 ሰዓት አይደለም ቀድሞ ነው ብለዋል እና ስንት ሰዓት ነው ሰው መሰብሰብ የጀመረው ?
- በእርግጥ 11 ሰዓት ተኩል ወጣሁ ቤት ሄጄ እራቴን በልቼ ልብሴን ቀይሬ መጣሁ የተመለስኩበት ሰዓት ላይ 2 ሰዓት ሊሆን ይችላል 1 ሰዓት ተኩል ሊሆን ይችላል ሰዓቱን አላየሁትም ግን ሲገባ በእዚያ መተላለፋችን ስለሆነ ሰው ነበር
- እርሶ ስንት ሰዓት ገቡ ስራ ?
- የገባሁበበት እራት በልቼ የመጣሁበት ሰዓት አላየሁትም እሱን አልያዝኩትኝም
- ስለዚህ ሰውም ተሰብስቦ የነበረበትን አያስታውሱትም ወይም አያውቁትም ማለት ነው ?
- ሰው ተሰብስቧል
- ምክንያቱም ቅድም ሲያስረዱ እኔ ወደ ስራ ስገባ ሰው ተሰብስቦ ነበር አሉ አሁን ደግሞ እኔ የገባሁበትን ሰዓት አላውቀውም አሉ ስለዚህ ሰው የተሰበሰበበትም እርሶ የገቡበትም ሰዓት አያውቁትም ማለት ነው አይደል አያስታውሱትም ወይም አያውቁትም ?

2932 2408

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የገባሁበትን ሰዓት አላስታውስም ግን ሲገባ ሰው መንገድ ላይ መስኪድ ውስጥ እንደነበረ አውቀዋለሁ
- በዕለቱ ወንድሞቻችን አወሊያ ላይ ጉዳት ደርሶባቸዋል ልናጣራ ነው አሳልፉን ነበር አይደል ሲባል የነበረው ?
- እሺ ምንድን ነው መቃወሚያው
- አሁን መርተው መጠየቅ ሕጉ ቢፈቅድላቸውም ነገር ግን መምራት የሚችሉት በዋና ጥያቄ ላይ ተመርኩዘው ነው ስለዚህ አሁን ይሄ በዋና ጥያቄ ላይ አልተነሳም በዋና ጥያቄ ላይ ያልተነሳን ነገር መስቀለኛ ጥያቄ መርተው መጠየቅ ይችላሉ ስለማይባል በእዚሁ መሠረት ጥያቄአችን ውድቅ እንዲደረግ
- ምላሽ ስጡበት
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩም ሆኑ ዐቃቤ ሕጉ ጠይቀው የመሰከሩት ወይም የተናገሩት ነገር ሰው ወጥቷል ከእኛ ጋር ግጭት ተፈጥሯል የሚል ነገር ነው ግጭት ተፈጥሮ ከሆነ የእዚህ ግጭት ምክንያት ምንድን ነው የሚለውን ማጣራት ተገቢ የሆነ ጥያቄ ስለሆነ አዲስ ጥያቄ ነው ሊባል አይገባም መጠየቅ አለብን
- እሺ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል የግራ ቀኙን አዳምጧል ምስክሩ ከመጀመሪያው ግጭት እንደነበር ጠቅሰዋል ስለዚህ ግጭቱ የግጭቱ መነሻ ምን እንደሆነ መስክረዋል ስለዚህ በተቃራኒው የግጭቱ መነሻ ሌላ ነው የሚል እንድምታ ነው በጠበቃ በኩል የቀረበው ስለዚህ ይሄንን ምስክር የሚያውቁ ከሆነ ለማጣራት ተገቢ ጥያቄ ሆኖ አግኝተነዋል ቀጥሉ
- አሁን ሰምተዋል የጠየኮትን ልድገምሎት ?
- አልሰማሁም
- እሺ በወቅቱ እዚያ አካባቢ ላይ የነበሩ ሰዎች አወሊያ ያሉ ወንድሞቻችን ጉዳት ደርሶባቸዋል እና እዚያ ምን እንደደረሰ እናጣራ እንድናልፍ ፍቀዱልን ሲሉ ነበር አይደል ?
- ይሄ ግልፅ ነው አወሊያ ያለው ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መርካቶ ፖሊስ ጣቢያ አዲስ ከተማ መርካቶ ውስጥ ነው ያለው ምናልባት ወደ እዚያ ማለፍ ከተፈለገ ከባዩሼ
- ይኸው ምስክር አሁን እሱን አይደለም አሁን ዋናው ነገር ያኔ እንዲህ ይሉ ነበር ፍቀዱልን እኛ አወሊያ ያሉ ወንድሞቻችን ጉዳት ስለደረሰባቸው እዚያ ነው የምሄደው ብለው ፍቀዱልን ብላችሁ ጠይቃችሁ ነበር ያን ቀን የተደረገ ነገር ካለ እሱ ላይ ያለውን ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለአወሊያም አላነሱልንም እንለፍ ፍቀዱልንም የተባለ ነገር የለም
- ምንም የሰሙት ንግግር የለም አይደለም ?
- ምንም የሰማሁት ነገር የለም ድምፃችን ይሰማ እያሉ ብቻ ነው ወደ ጣቢያ ግር ብለው የመጡት
- ከእናንተ አባላት ውስጥ ሊያረጋጋ የሞከረ የለም አይደል ዝም ብሎ ነው ግርግሩ የተፈጠረው ?
- በጣም በዲፕሎማቲክ ነገሩን ለማረጋጋት ከጣቢያ አዛዥ እስከ ተራ አባል መሀላቸው ገብቶ ለማረጋጋት ጥረት ተደርጓል በጣም ለረጅም ጊዜም እስከ 5 ሰዓትም ሁከቱ ወይም ድንጋይ ውርወራው የቆየበት ምክንያት በዲፕሎማቲክ ጣቢያ አዛዡ ወንጀል መከላከሉ ምርመራ ክፍል ኃላፊው መሀላቸው ገብቶ ጥያቄአችሁን በአግባቡ ጠይቁ ችግር ካለ ችግራችሁን በይፋ በግልፅ ጠይቁ የሚያስጮሁችሁ ነገር የለም እንቀመጥ እንወያይ እንነጋገር ብሎ ለረጅም ጊዜ በዲፕሎማቲክ ጠይቋል ቅድም የገለፅኳቸው ሰዎች
- እሺ ሰው ስንት ሰዓት ላይ ተበተነ ተሰበሰበ ያሉት ሰው ስንት ሰዓት ላይ ተበተነ ?
- ምናልባት ድግግሞሽ እንዳይሆን እንጂ የተጀመረው 5 ሰዓት ነው የሚያልቅበት ሰዓት መያዝ አይደለም የእኔ ስራዬ በእዚያን ሰዓት በእዚያን ሰዓት እኔ ስራዬ ሲጀመር ሰዓቱን
- ቆይ ቆይ አንድ ጥያቄ ናት እኮ ስንት ሰዓት ያ ነገር ተበተነ ወይም ስንት ሰዓት በረዳ ?
- አልያዝኩትም ሰዓቱን የተበተነበት ሰዓት አልያዝኩትም
- መገመት ይችላሉ ምን ያህል ሰዓት ቆየ እሺ ሰው ከ 5 ሰዓት ለምን ያህል የሚሆን ጊዜ እዚያ እንደቆየስ መገመት ይችላሉ ?
- አልገመትኩትም
- ሰው እንዴት ተበተነ ይሄንንስ ያውቃሉ እንዴት ተበተነ እዚያ የተሰበሰበው ሰው ?
- የተሰበሰበው ሰው ፊት ለፊት የነበሩ በዋናነት ድንጋይ ሲወረውሩ የነበሩ በፖሊስ አባሎች ቁጥጥር ስር ውለዋል እነሱ ቁጥጥር ስር ሲውሉ እነሱ ጆርባ የነበሩት በራሳቸው ጊዜ ነው የተበተኑት
- እንጂ ከእዚያ ውጪ ሌላ ተጨማሪ ኃይል የመጣ ምናምን የለም ?
- ምንም ተጨማሪ ኃይል የተወሰደባቸው ነገር የለም ፖሊስ የራሱን

2934 4083

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእዚያው በእናንተ ጣቢያ አባላት እና በአካባቢው ፖሊሶች ብቻ ነው የተበተኑት ?
- በእኛ ብቻም ሳይሆን የፌዴራል ፖሊስም ጭማሪ መጥቷል
- እኮ ይሄ የተጨማሪ ኃይል ማለት ነው ?
- ትክክል
- የፌዴራል ፖሊስ በወቅቱ አስለቃሽ ጢሶችን ተኩሷል አይደል
- ምንድን ነው መቃወሚያው
- ይሄ አሁን አልተነሳም በዋና ጥያቄ የተወሰደ ኃይል አለ ወይ የተጨመረ ኃይል አለ ወይ በዋና ጥያቄ አልተጠየቀም አሁን ይሄ ከየትኛው ጥያቄ ጋር ተያይዞ እንደተነሳ አልገባንም ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄ ላይ በዋና ጥያቄ ያላነሳነው ስለሆነ ሊታለፍ ይገባል ይሄ
- ምላሽ ስጡበት
- እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት የነገሩን አጠቃላይ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ አንስተው ጠይቀው ምስክሩ መስክረዋል ግርግር ነበረ ድንጋይ ውርወራ ሁላ ነበረ እና ይሄ እንዴት ተበተነ የግርግሩ ምክንያት ምንድን ነው ምን ዓይነት ኃይል ተጠቀመ የፀጥታ አስከባሪ የሚለው በጣም ሬለቫንት ነገር ነው እና አዲስ የሚባል ጥያቄ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት ፍ/ቤቱ የተሟላ ፒክቸር እንዲኖረው 1ኛ 2ኛ ከእዚህ በፊት ከመሰከሩት ምስክሮቼ ጋር ማለያየት ነው አንዱ የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማው ስለዚህ በእዚህ ምክንያት ሊፈቀድልን ይገባል
- ስጥተናል የተነሳው ጥያቄ ሁከቱ እንዴት በረደ ምን ኃይል ተጠቀማችሁ የሚል የነበረውን ነባሪ ሁኔታ ሊያስረዳ የሚችል በመሆኑ የጠበቆች ጥያቄ ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል
- በወቅቱ እናንተ የጣቢያው አባላት ሳይሆን
- እስቲ ቆይ አሁን የቅድሙን ጥያቄ መልሱ አስለቃሽ ጋዝ ተጠቅማችኋል ወይ የተጠቀመ አካል አለ ወይ ?
- የፌዴራል ፖሊስ አስለቃሽ ጭስ ተጠቅሟል ወይ ?
- እኮ እሱን መልሱ
- ክቡር ፍ/ቤት እኔ መናገር የምፈልገው የፌዴራል
- ጥያቄው ለጥያቄው መልስ
- ያየኸውን ነገር ይኸው ምስክር ያየኸው ስየማኸው እዚያ ላይ ካለ ብቻ ነው ሌላ አትጨናነቅ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንደአዲስ አበባ ፖሊስ እኛ የወሰድነው የኃይል እርምጃ የለም የራሳችን ፖሊሳዊ ሳይንስ ተጠቅመን ተጠርጣሪዎቹ ቁጥጥር ስር አውለናል
- እኮ ያን ቀን አስለቃሽ ጭስ አለ የለም እናንተ ተጠቀማችሁ አልተጠቀማችሁ አይደለም የተጠቀመ ሰው አለ ?
- አላየሁትም
- እሺ ሌላ ጥያቄ
- ከእዚህ አሁን ቅድም ባልደረባዬ ጠይቆት እርሶ ላይ ጉዳት ያደረሱ ይሁኑ አይኑ አያውቁም ግን ተከሰው በጳውሎስ የቀረቡ አሉ
- እሱ ተጠይቋል
- ገባኝ የተከበረው ፍ/ቤት እራሱን እኮ አይደለም የምደግመው ከእሱ ጋር የተያያዘ ሌላ ጥያቄ ነው
- እስቲ ሌላ ከሆነ ቀጥል
- እሺ የጳውሎስ ፍ/ቤት ቀርበው ምስክርነትዎን በሰጡ ጊዜ ኮሚቴ ምናምን የሚል ነገር አልተናገሩም አይደል አሁን ነው እዚህ እየተናገሩ ያለው ?
- እዚያም ተናግሬአለሁ እኔ
- እርግጠኛ ኖት እዚያም ተናግረዋል ?
- እርግጠኛ ነኝ ተናግሬአለሁ ምናልባት እዚያም ስናገር
- ይበቃል ሌላ ጥያቄ
- ምስክር በዕለቱ ዝናብ ነበር እንዴ ይሄ አሁን ሐምሌ 6 ባዩሺ አካባቢ ይዘንብ ነበር እንዴት ነበር ?
- እሺ ምንድን ነው መቃወሚያው
- ማለት አሁን በእዚህ ደረጃ ምስክሩ የሚናገረው አጠራጣሪ ወይም ደግሞ እየዋሸ ነው ተብሎ የሚጠየቅ እንኳን ቢሆን የራሳቸውን አሳሳች የሆነ ጥያቄ አይደለም ማንሳት የሚገባቸው ትክክለኛው ያን ቀን እስካሁን ከተመሰከረው ጋር ወስደው እንዲህ አልነበረም ወይ እንዲህ ተብሎ አልነበረም ወይ ነው እንጂ የሆነ ኢቭንት ተወስዶ አሁን ከባለፈው ምስክሮች ወይም ደግሞ በወቅቱ ያልነበረን ኢቭንት አስበው እራሳቸው ስለው አምጥተው

2936

http://ethcriminalawnetwork.com/

አይደለም መጠየቅ የሚችሉት በእዚህ መሠረት 137 አይፈቅድላቸውም ስለዚህ የራሳቸውን ጥያቄ አይደለም መሪ ጥያቄ ከጉዳዩ ጋር በቀጥታ የሚያያዝ የተመሰከረ መሆን ይገባዋል ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ማሳሳት ነው ምስክሩን ማሳሳት ነው ማሳሳት ደግሞ 137 ላይ አልተፈቀደም የሚናገረው ነገር ሀሰተኛ ነው አጠራጣሪ ነው የሚለውን መጠየቅ ይችላሉ

- እሺ ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት መጀመሪያ ደረጃ በእዚህ ጉዳይ ሌሎች ምስክሮችም መስክረዋል ስለዚህ ከሁኔታዎች አስገዳጅነት እንጂ አንድ ላይ ነበር መመስከር የነበረባቸው እና መለያየትም አንዱ አካል ነው 2ኛ ምስክሩ በቦታው ነበሩ አልነበሩም የሚለውም የመስቀለኛ ጥያቄ አላማ አንዱ ስለሆነ ይሄ ጥያቄ ያነጣጠረው በትክክል ምስክሩ በቦታው ነበሩ አልነበሩም የሚለው ከማጣራትም ጭምር ስለሆነ በአግባቡ የቀረበ ነው እና መቃወሚያው ውድቅ ይደረግልን
- የግራ ቀኙን መቃወሚያ አዳምጠናል ምስክሩ በወቅቱ ያዩትን ነገር ሲያወሩ ነው የነበሩት ከጠበቆች እንደተነሳው አንድ ምስክር በአካባቢው መኖር አለመኖሩ ከእሱ ጋር አብረው የሚያያዙ ወይም ሊረጋገጡ የሚችሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታወቃል ስለዚህ ምስክሩ ያን ቀን ነበሩ ወይ ካለ የአየር ሁኔታው ምን ነበር ቦታው የት ነበር ብሎ መጠየቀ የምስክሩ ማንነት ማረጋገጥ ስለሆነ ጥያቄው ተገቢ ነው ከእዚያ ውጪ ግን አንድ ባለፈው እከሌ ስለተመሰከረ ባለፈው እንዲህ ስለሆነ የሚለው ነገር እሱ አይሰራም ምስክሩ በትክክል አሁን ስላለው ጉዳይ አሁን ስላለው ፋክት ነው እንጂ ይሄንን ከሌሎቹ ጋር ለመነጠል የራሱ ነው የሌሎቹ ትክክል ናቸው ትክክል አይደለም የራሱን እራሱ የሚመሰክረው ነገር ትክክል ነው ትክክል አይደለም የሚውን ብቻ ዓላማ ይዛችሁ ነው የምትጠይ እንጂ ሌሎቹ ስለጠየቁ ተብሎ እሱን አውጡት ከውስጣችሁ አውጡት እና የምስክሩ ብቻ ስላየው ነገር እሱን አረጋግጡ
- እሺ ምስክር በዕለቱ የአየሩ ሁኔታ እንዴት ነበር ይዘንብ ነበር ወይስ አልነበረም ?
- ከ 5 ሰዓት በኋላ ዝናብ አልነበረም
- ከእዚያ በፊት ነበረ ?
- ማለት ብዙም ዝናብ አይደለም ወደ 11 ሰዓት አካባቢ ነው የዘነበው ትንሽ ነው ከእዚያ በኋላ ግን አልዘነበም

2937 4086

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ 5 ሰዓት ረብሻው ጩኸቱ ከተጀመረ በኋላ መብራትስ ጠፍቶ ነበር ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መብራት ጩኸቱ በተነሳበት ጊዜ መብራት ነበረ አልነበረም ?
- ጩኸት ሲጀመር ነበር ከእዚያ በኋላ ጠፋ
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- እሺ ኮንስታብል ፓውሎስ ፍ/ቤት ቀርቤ ምስክርነት ሰጥቼአለሁ ብለዋል እነዚህ ግለሰቦች አሁን መስከርኩባቸው የሚሏቸው ግለሰቦች በምን ዓላማ ከፊት ለፊት የተገኙትን ነው ወይም ደግሞ ከፊት ሆነው ድንጋይ ሲወረውሩ የነበሩት ናቸው ብለዋል እነዚህ ሰዎች በምን አላማ ለምን ያንን እንደሚያደርጉ ያውቃሉ ?
- ጳውሎስ ፍ/ቤት ሄጄ ምስክርነት ቃሌን ስሰጥ 6 ነው 5 ግለሰቦች ነበሩ እነኚህ ግለሰቦች መብራት ከመጥፋቱ በፊት እኮ እናያለን ቅርብ ለቅርብ ነበርን ድንጋይ ውርወራ ጀመሩ ድምፃችን ይሰማ ድምፃችን ይሰማ እያሉ ፊት ለፊት ሆነው ወደ ጣቢያ ሲመጡ የነበሩት እነሱ ነበሩ ድንጋይ ውርወራ ተጀመረ እነኚህ ሰዎች በመልክ ይታወቃሉ የለበሱት ልብስ ይታወቃል ተይዘው መጡ
- ሰዎቹን መለየት አይደለም በወቅቱ እዚያ በነበረው የፖሊስ አባል ላይ ይሄንን አሁን የተናገሩትን ንግግር እና ድርጊቱን ለምን ዓላማ በማን እየተመሩ ይፈፅሙ እንደነበር አውቃችዋል ወይ
- እስቲ ቆይ ቆይ ተቃውሞ ነው እኛ አልገባንም እስከ ጥያቄው መጀመሪያ ይግባ እና እስቲ ቆይ ጥያቄው ምንድን ነው የክሱ ምክንያት ምን ነበር ለማለት ነው ?
- አይደለም እነዚህ ሰዎች ተቀጥተዋል አይደለም ወይ ተብሎ በመስቀለኛ ጥያቄ ተጠይቋል ተለይተው ተነጥለው ማለት ነው አሁን እያልን ያለነው እነዚህ ሰዎች እነ ማን ናቸው ለምን በእዚያ በእዚያ ወቅት እዚያ ድንጋይ ላይ እናንተ ላይ ጉዳት ለምን እንዳደረሱ በምንስ እዚያ እንደተገኙ በምን ዓላማስ ያንን እየፈፀሙ እንደነበር አጣርታችዋል ወይ እነ ማን እንደሆኑ ነው እየጠየኩ ያለሁት
- ሰዎች የሚለው በዝቷል እና እነዚህ ሰዎች ተቀጥተዋል አይደለም ወይ ዓላማቸው ምንድን ነው የተባለው የተቀጡት ሰዎች ዓላማ ነው የተጠየቀው ወይስ

2938 4087

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ግልፅ ለማድረግ የተከበረው ችሎት መስቀለኛ ጥያቄ ላይ እነዚህ ጳውሎስ በመዝገብ ቁጥር ተጠቅሶ እነዚህ ሰዎች ተቀጥተው የለም ወይ ውሣኔ ተሰጥቶባቸው የለም ወይ ተብሎ ተጠይቋል መስቀለኛ ጥያቄ እሳቸውም ሲመልሱ አዎ ይታወቁ የለም በስም ለይተው ተለይተው የለም ወይ በስም አለየዋቸውም በአካል ግን በወቅቱ ፊት ለፊት ስለነበሩ ለይቼአቸዋለሁ እነዚህ ናቸው ብዬ መስክሬባቸዋለሁ ብለዋል ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄም የተፈለገው እነዚህ አረዲ በተግባራቸው ተቀጥቷል እዚያ በፈፀሙት ሕገ ወጥ ተግባር ነው መስቀለኛ ጥያቄ የተጠየው ስለዚህ አሁን እየጠየቅን ያለነው በማጣሪያ ጥያቄ እየጠየቅን ያለነው እነዚህ ሰዎች ይሄንን ድርጊት ለምን እንደፈፀሙ አጣርታችዋል ወይ ያንን ንግግርስ የሚናገሩት የነበረው በምን ዓላማ ነው የሚለውን ነው የጠየቅነው
- እነዚህ የተባለው አሁን /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ እነሱን ነው
- ቀጥሉ እስቲ
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ መስቀለኛ ጥያቄ ስናነሳ አሁን ዐቃቤ ሕግ እንዳብራሩት ጉዳት ደርሷል አልደረሰም የሚለው እና ጉዳቱን ያደረሱት ሰዎች መቀጣት አለመቀጣታቸውን ብቻ ነው ከእዚህ ውጪ ጉዳቱን ያደረሱት ሰዎች ጉዳቱን ያደረሱበት ዓላማ ምንድን ነው ማን ነው ያስተባበላቸው ወይስ በማን መሪነት ነው ጉዳት ያደረሱት የሚለውን ነገር እኛ አልጠየቅንም እሳቸው በዋና ጥያቄ ላይ አንስተውት ነበር እኛ በመስቀለኛ ጥያቄ ይሄንን ጥያቄ አላነሳንም አልጠየቅንም ስለዚህ በድጋሚ ጥያቄ ላይ ዓላማው ምንድን ነው ወደ የሚለው ነገር ገብተው እሳቸው ሊጠየቁ አይገባም ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ይሄ ጥያቄ ስላልተነሳ
- ምላሽ ስጡበት
- ጉዳቱን ለማጣራት የመዝገብ ቁጥር ተጠቅሶ ተቀጥቷል ተለይቷል ተብሎ መቼስ መስቀለኛ ጥያቄ አልተጠየቀው የተጠየቀው እነዚህ ሰዎች በእዚያ ወቅት በፈፀሙት ሕገ ወጥ ተግባር እና ረብሻ ተቀጥተዋል ነው ስለዚህ ተለይቶ ተነጥሎ ማለት ነው እነዚህ ሰዎች ተነጥለው ቅጣት ካገኙ እዚህ ጉዳይ ላይ መጠየቅም አልነበረበትም መዝገብ ቁጥር ተጠቅሶ የችሎቱ በስም ተለይተው ቅጣት ተጥሎባቸው የለም ወይ ተብለው አይጠየቁም ነበር ነገር ግን የመስቀለኛ ጥያቄው ዓላማ እኛ በገባን ለማፍረስ የተሞከረው እነዚህ ሰዎች ተለይተው

ፃ፭፫ 4088

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከተከሣሾች ጋር ምንም ግንኙነት ሳይኖራቸው በፈፀሙት ወንጀል ተቀጥተዋል ለማለት ነው እኛ የተረዳነው በእዚያ በተረዳን መጠን ነው አሁን ጥያቄውን የጠየቅነው ስለዚህ ተገቢ ነው እነሱ መነጠል ነው የፈለጉት ነገር ግን አይነጠልም ግንኙነት አለው የለውም ምስክሩ የሚያውቁ ከሆነ ያንን እንዲመሰክሩ ነው የጠየቅናቸው

- እሺ ብይን ሰጥተናል ምንድን ነው ያየነው ነገር የግራ ቀኛችሁን ክርክር መጀመሪያ ሲጠየቅ የነበረው ከመስቀኛ ጥያቄ ላይ ሰዎቹ ተከሰዋል ተከሰው ምስክሩ ሄዶ መስክሯል የሚል ነው አሁን ዐቃቤ ሕግ የጠየቀው እነዚህ ሰዎች በምን ዓላማ ነው ያንን የፈፀሙት የሚል ወይም በምን ዓላማ ተከሰሱ በምን ዓላማ ተቀጡ የሚል ስለሆነ ከእዚህ ቀደም በመስቀለኛ ጥያቄ ከተነሳው ብዙ የተለየ አይደለም ምናልባት ልዩነቷ ልትሆን የምትችለው እዚያ ከፈፀሙበት ላይ ዓላማው ምንድን ነው የምትል ካልሆነ በስተቀር መጨረሻ ላይ ሄዶ ሄዶ በምን ጉዳይ ነው የተቀጡ የሚል እንድምታ ነው ያለው ወይም በምን ዓላማ ነው እነዚህ ሰዎች ሄደህ የመሰከርከው በምን ጉዳይ ነው የሚል ነው ፍ/ቤቱ በእዚህ ነው የተገነዘበው ስለዚህ ጥያቄው ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል
- ይቀጥሉ ኮንስታብል
- ጥያቄው ይደገምልኝ
- አሁን እነዚህ በፊት ለፊት የኃይል ተግባሩ ወይም ደግሞ እናንተ ላይ ጉዳት የማድረሱ ተግባር ላይ በፊት ለፊት ሆነው ሲመሩ የነበሩትን ለይተን በቁጥጥር ስር አውለናል ብላችዋል እነዚህ ተለይተው ፍ/ቤት ቀርበው እናንተ መስክራችዋል ጉዳት የደረሰባችሁ ሰዎች
- ትክክል
- እነዚህ ሰዎች በምን በምን ዓላማ ነው ይሄንን ተግባር የፈፀሙት ?
- ዓላማቸው ነኛ ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱን መናድ ነው እንጂ ሌላ ዓላማ
- በምን እስቲ እሱን ይንገሩን በምንድን ነው ሕገ መንስታዊ ስርዓቱን መናድ ነው ሲሉ እንዴት ነው የተረዱት ?
- ምናልባት ጥያቄአቸውን በግልፅ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይችላሉ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሕገ ወጥ የሆነ ሰልፍ እያካሄዱ የሀገሪቱንም ገፅታ ለማበላሸት ነኛ ቀድሞ ገልጬአለሁ የአፍሪካ ሕብረት አዲስ አበባ ላይ ጉባኤ አለው ይሄንንም ለሌላ ሀገር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሀገሪቷን ገፅታ ለማበላሸት ኢትዮጵያ እንደዚህ ዓይነት ውስጥ ነች ያለችው የሚል ሌላ ሀገር ለማስተላለፍ ተፈልጎ ነው እንጂ ሌላ ዓላማ የለም

- እሺ እናመሰግናለን ጨርሰዋል ሌላ ምስክር
- የምናሳስበው አለ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር አሁን ለጊዜው እዚህ ለዛሬ ያቀረብናቸው እኚህ ናቸው በቀጣይ ግን ምን ማድረግ እንዳለብኝ ያው ለማመልከት ነው እንደሚታወቀው ያው ዛሬ ለ 2 ሣምንት ያው ቀጠሮ ተይዞ ለ 2 ሣምንት ያህል ያው የተከበረው ፍ/ቤት ቀጠሮ እንደተያዘ ያው ይታወቃል ትላንት እና ዛሬ ምስክሮችን አይተናል አሁን ግን ቀሪ ምስክሮችን ለማምጣት በተለይ ፖሊሱ ሕግ ማስከበር ላይ የተሰማሩት ኃይሎች አሁን ምስክሮችን ለማቅረብ የተለያየ ፍሰጋ ለማድረግም ያው የሰው ኃይል እጥረት ትንሽ ችግር ስለነበረ በእዚህ ምክንያት ምስክሮችን አሟልተን ማቅረብ አልቻልንም በእኛ በኩል እርግጥ በእዚህ በገፅ 40 በክስ ማመልከቻችን ላይ እንደገለፅነው የድምፅ ማስረጃዎች አሉ እነሱም ቢሆን አጠቃላይ የሰው ማስረጃዎቻችን ስንጨርስ እናቀርባለን የሚል ነበረ አሁን ግን በእኛ በኩል ለተከበረው ፍ/ቤት የምንጠይቀው ምንድን ነው ቀሪ ምስክሮች አሉን ምስክሮች ያው የአድራሻቸውን እነሱን አፈላልጎ ለማቅረብ እንዲያስለን እና አሁን ከሰጠን ጊዜ እና አሁን ባለው በተለይ ከሕግ ማስከበር ጋር ካለው ወቅታዊ ስራ ጋር በተደራራቢነት እነኚህ ምስክሮችን ፖሊስ ያው ለማግኘት ትንሽ ጊዜ ትንሽ አጠር ስላለብን አጭር ቀጠሮ ተሰጥቶን በእዚህ ቀጠሮ አንድ ቀሪ የሰው ማስረጃዎቻችን እንዲሁም በ2ኛው የድምፅ ከምስል ማስረጃዎቻችን በእዚህ በችሎት ይቀርባሉ ያልናቸውን የቪሲዲ የሲዲዎች የተለያዩ እነኚህ ቅስቀሳ ብለን ያልናቸው እነሱን ጭምር አቅርበን የምናጠቃልልበት ይሆናል እና ከእዚህ ጋር አሁን በሚቀጥለው ሣምንትን እና ይቺን 2 ቀን ተይዞልን ከነበረው ምስክር ማቅረብ ጋር በተያያዘ አሁን በእዚህ ምክንያት ለማቅረብ ያልቻልን እና በስራ መደራረብ እና ጫና ምክንያት ስላልቻልን የተከበረው ፍ/ቤት አንድ አጠር ያለ ተለዋጭ ቀጠሮ የምጠይቀው ከእዚህ ጋር በተያያዘ ያው በተጨማሪ
- የተከበረው ችሎት ምላሽ ማለት የፖሊስ ምላሽ ተለዋጭ ቀጠሮ ለጠዋት ለነገ ጠዋት ይዘው ለቅረብ ነበረ ፎርማሊ ማለት ነው ነገር ግን ነገ የሚቀርብ ምስክር ስለሌለ ችሎቱንም እንዲሁም ተከራካሪ ወገኖችን ከማድከም ውጪ ሌላ ቀጠሮ ነው የምንጠይቀው ነገም ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠን ምክንያቱም አሁን ባለው ወቅታዊ ስራ እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎች ጋር በተያያዘ የተወሰነ ኃይል ስላለ ያንን ኃይል በትኩረት ባለፈው ሳምንት

http://ethcriminalawnetwork.com/

በአድራሻቸው ምስክሮችን እያስፈረምን ማምጣት አልቻልንም የሚል አዘጋጅተዋል እሱን ለነገ ጠዋት ነበር ሊቀርብ የነበረው ስለዚህ ነገ ጠዋት ያንን ከማመልከት ውጪ ምንም የምንቀይረው ወይም ይዘን የምንቀርበው ምስክር የሌለ በመሆኑ አሁን ፍ/ቤቱ ያንን ተገንዝቦልን ቀሪ ምስክሮችን እና እንዲሁም የድምፅ ከምስል ማስረጃ የምናሰማበት ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠን ነው ይኸውም በስነ ስርዓት ሕጉ 94 መሠረት እነዚሁ ምስክሮች በዛሬው ዕለት ሊቀርቡልን ስላልቻለ ተለዋጭ ቀጠሮ ይኸው አሁን ያ የገለፅነው ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት እነዚህን 2 ምስክሮች ማስረጃዎችን እንድናሰማ አሁን ከተያዘው ቀጠሮ ትንሽ ረዘም ተደርጎ እንዲሰጠን ነው የምናመለክተው የተከበረው ችሎት

- የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው እንግዲህ በነበረን ቀጠሮ ጠበቆችም አጀንዳችሁን አሬንጅ አድርጉ ተብሎ አንድ ወር ከ 2 ቀን አካባቢ ነው የተሰጠን እንግዲህ ወይ ዐቃቤ ሕግ በእዚህ ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አንድ ወር ከ 2 ቀን ተሰጥቶት ማቅረብ አልችልም ከሆነ በቃኝ ምስክር ጨርሻለሁ ይበል እና ሲዲዎችን እንይ ካልሆነም ደግሞ እኛ ጠበቆቹ አይመቸንም ይመቸናል እያልን በጣም ተወዛግበን በእዚህ አግባብ የተቀጠረው ችሎቱ የሚያውቀው ነው የእዚህ ማለት ነው ስለዚህ ምስክሮች ማምጣት ካልቻሉ ሲዲው የሚታይበት አግባብ ምክንያቱም አሁን ለተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣል ለሲዲው ደግሞ ሌላ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣል ስለዚህ ምስክሮቹ ማቅረብ አልቻሉም የሲዲ በችሎት /ግልፅ ያልሆነ/ ብለዋል በችሎት ይታዩ እነሱ ጊዜውን በአግባቡ እንጠቀምበት ካልሆነ እንደዚህ ቀጠሮ ቀጠሮ እየሰጠ ያው በቂ አሁን ለእኛ በቂ ምክንያት አይደለም ሆኖ የቀረበው ሌሎች ያላቸውን ይናገሩ
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ምናልባት የዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ገብቶን ከሆነ በትክክል አሁን ምስክሮቹን ማቅረብ ስለማንችል ምስክሮቹን የምናቀርብበት ሌላ ቀጠሮ ይሰጠን ነው ፍ/ቤቱ 10 ቀን ነው የያዘው ከ 6 እስከ 16 ድረስ ነው የያዘው ነገ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ ከነገ ወዲያም ቀጠሮ አለ በፍ/ቤቱ የተያዘ አጀንዳ ሰኞ ማክሰኞም ቀጠሮ አለ እነዚሁን ቀጠሮዎች ተጠቅሞ ያቅርቡ እና ምስክሮቻቸውን ያጠናክሩ ከእዚህ ውጪ ግን ይሄኛውን ቀጠሮ ጠቅላላ እስከ 16 ያለው ተሰርዞ ሌላ ቀጠሮ ይሰጠን ከሆነ ጥያቄው ግን ተገቢ አይሆንም ተከሣሾች በእስር ላይ ነው ያሉት ይሄ ምስክርነት ከተጀመረ 5 ወር ሆኖታል ምስክርነት ብቻ ከተጀመረ አሁን ደግሞ ከ 30 ምናምን ቀን በላይ ነው ለእዚህ ቀጠሮ የተሰጠው አሁን ፖሊስ ላይ ተፈጠረ የሚባለው ወቅታዊ ሁኔታ መደበኛ የፖሊስ ስራ ነው የውጪ ችግር አይደለም ፖሊስ በራሱ ፕሮግራም በራሱ ጊዜ የወሰደው እርምጃ ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የእነዚህ የተከሣሾች ጉዳይም አንዱ የፖሊ ስ ስራ ነው ፖሊ.ስ ይሄንንም አስቦ ነው የሚሰራው

አዲስ ጉዳይ ስለመጣ እስር ቤት ያሉት ሰዎች ጉዳይ ለጊዜው ይቅር ወይም ይቆይ የሚባልበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ አሁን በተያዘው መደበኛ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ በያዘው ቀጠሮ ገና ቀሪ ቀኖች አሉ በእዚያ ቀጠሮዎች ያቅርብ በእዚያ የማያቀርብ ከሆነ ግን ተከሣሾች በእዚህ ምክንያት ቀጠሮ ሊሰጥ አይባም የምስክር ማሰማቱ ተቋርጦ የሰነድ ማስረጃዎቹን የድምፅ ማስረጃዎቹን እንዲያቀርብ ይደረግልን ከእዚህ ውጪ ግን ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ቀጠሮው ሊለወጥ አይገባም ሕጉም ስነ ስርዓት ሕጉም አይፈቅድም ዐቃቤ ሕግ የጠቀሱት ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 97ም ይሄንን አይፈቅድም

- ምናልባት እንትኑን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ መርማሪ ፖሊስ እዚህ አሉ እስቲ ምንድን ነው ያደረጋችሁት ጥረት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እኮ ጥረቱን እኛ አሁን አላየነውም አሁን ዐቃቤ ሕግ በፁሑፍ ቢመጣ የሆነ የምትጠቅሱት ነገር ይኖራችዋል እሱ ምናልባት ልናይ እንችላለን ዐቃቤ ሕግ ከእናንተ ተቀብሎ ነው እያመለከቱ ያሉት እና እናንተ ምንድን ነው አሁን እነዚህን በደንብ አሰባስቦ ለማምጣት ረጅም ጊዜ ነበር አሰባስቦ ለማምጣት ያስቸገራችሁ ነገር ጥረታችሁ ምን ያህል ነበር ?
- ጥረታችን ማለት አሁን /ግልፅ ያልሆነ/ ኃይላችን እንዳለ ወደ እዚያ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ያለው ትንሽ ኃይል ነው እሱ ደግሞ ማለት ለማስፈፀም ጊዜ በጣም /ግልፅ ያልሆነ/ ሁሉም ኃይል አልሞስት እዚያ ላይ ነው ማለት ይቻላል በአሁኑ ኬዝ ላይ ማለት ነው ስለዚህ ምስክሮችን ደውሎ ወይም ደግሞ
- ምንድን ነው እሱ የአሁኑ ኃይል የአሁኑ ኬዝ ምንድን ነው ?
- ማለት በሙስና ኬዝ ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ በየጊዜው የቤት ብርበራ አለ ምናምን አለ /ግልፅ ያልሆነ/
- እንግዲህ በእዚህ ቀጠሮ ላይ ተነጋግረን ትዕዛዝ ሰጥተናል ምንድን ነው የሰጠነው ትዕዛዝ ነኛ ምናልባት ፖሊስም ዐቃቤ ሕግም ያቀረባችሁት ምክንያት ከእዚህ ከአዲሱ ጉዳይ ጋር ተገናኝቶ በእዚያ ምክንያት ነው የሚል ነገር እሱ ነገር ለፍ/ቤቱ ብዙም አሳማኝ አይደለም ነኛ ሰፊ ጊዜ ነበር በእዚህ ጊዜ ውስጥ መጥሪያውን አድርሳችሁ እሱ የተፈጠረው ምናልባት የተፈጠረበትን ባናውቀውም የእዚህም እራሱ ከባድ ነው የእዚያን ያህል ኬዝ የእዚያም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሁን ይሄም አራሱን ትሱ ወብበበብ ያለ በመሆኑ ትሱ እንዲያልቅ ይሄንን ጥረት ማድረግ ነበረባቸው ሆኖም ግን ምንድን ነው እኛ የወበድነው 1ኛ የመጀመሪያ ጥያቄአችሁ ነው 2ኛ ከጉዳዩ ውስብስብነት አንፃር ከምስክሩ ብዛት አንፃር ተመልክተን እነዚህን አሉኝ የሚላቸውን አጠቃሎ እንዲያቀርብ 1 ቀጠሮ መስጠት እንዳለበት ፍ/ቤቱ አምኗል አሁን መርሐብሔ ቀጠሮውን የሀገ ሐኞችን መስማማት ስለማሮር የቀጠሮውን ጉዳይ እርግጡን ልንጠይቅ እንችላለን ለመቼ እንደምንችል

<u>ትዕዛዝ</u>

- ዐቃቤ ሕግ ቀሪ ማስረጃዎቹን አሰባስቦ እንዲያቀርብ ቀጠሮ ከሰኔ 5 እስከ ሰኔ 19 ድረስ ቀጠሮ ተይዟል በእዚያን ቀን ማረሚያ ቤት ከጠዋቱ 3 ሰዓት ተኩል እንድታቀርቧቸው ዐቃቤ ሕግም ምስክሮቻችሁን እናንተም 3 ሰዓት ተኩል በቀጥታ ችሎቱ እንዲጀመር ይሄንን ሰዓት አክብራችሁ እንድትገኙ ነው በደህና ዋሉ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

16ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ሰኔ 5 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብስራት ተሀልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ ፡- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድም አገኘሁ ቴዎድሮስ ጌታቸው ቀርበናል

ተከሳሾች፡- እነአቡበከር አህመድ የቀረ ሰው አለ ስንተኛ ናቸው 29 ሌሎቹ ቀርበዋል ዶ/ር ከማል ማን ነው ሃጂ ገለቱ ናቸው የቀሩት 29ኛ ተከሳሽ በስተቀር ሌሎቹ ቀርበዋል የተከሳሾች ጠበቆች የ28ኛ አህመድ ጀማል ቀርቤያለሁ ከ28ኛ ውጪ ላሉት ባህሩ መካንጋ ሞላልኝ መለሰ መሃመድ አብደላ ቀርበናል

- ዛሬ ያው በተያዘው መሰረት ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር ይቅረብ
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት?
- አዎ
- እሺ ስሞን የራሶን ስም ብቻ ይገልፃሉ የአባቶን ስም ሳይጨምሩ?
- አይናለም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጠ/ሮግ
- ዋ/ኢንስፔክተር
- እሺ 07ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ ስንት ላይ የተጠቀሱ ናቸው አቃቤ ሕግ ስንት ላይ የተጠቀሱ ናቸው አቃቤ ሕግ በ07ኛው የአቃቤ ሕግ ምስክር በነሱ ላይ በማስረጃ ዝርዝር 56ኛ ላይ የተጠቀሱት ዋና ኢንስፔክተር አያናለም ቀርበዋል እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ኢንስፔክተር ?
- እኔ በአካልም በስምም አላውቃቸውም
- እሺ ስለምን ጉዳይ ነው የሚመሰክሩት?
- እኔ ላይ በደረሰ ጉዳት
- መቼ ነበር?
- በ6/11/2004
- አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ ዋና ኢንስፔክተር አሁን በገለፁት ማለት ነው በ6/11/2004 ዓ.ም. በኔ ላይ ስለደረሰው ጉዳት ለመግለጽ ነው ብለዋል እና ይሄ ጉዳት የደረሰው የት ቦታ ነው በነማን ነው ጉዳቱ የደረሰው ምን እንደነበረ አጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የሚያውቁት እና እርስዎ በደረሰቦት ጉዳት ምን ምን እንደነበረ በዝርዝር ለተከበረው ፍ/ቤት እንዲገልፁ /ግልጽ ያልሆነ/ መናገር ይችላሉ?
- የደረሰብኝ ጉዳት ያው በእለቱ የጣቢያው አዛዥ ነኝ /ግልጽ ያልሆነ/ በጊዜ አካባቢ ላይ የሆነ የተለያየ ነገሮች /ግልጽ ያልሆነ/ ኢንፎርሜሽን ነበረ እዛ በደረሰን ኢንፎርሜሽን መሰረት እዛው ላይ ጣቢያ ሆነን ስንጠባበቅ ነበር ወደ 5 ሰዓት ከምናምን አካባቢ ላይ ከመስኪድ ድምጽ ሰማን ማታ በዛ በደረሰብን ቦታው ወረዳ 10 ቀበሌ 08 ነው ልዩ ቦታው ቁባ መስኪድ ነው እዛ አካባቢ የነበሩትን አባሎቼን ይገፍ ሄድኩ ከፍተኛ ድምጽ ነበር ጩኸት ነበር ፀጥታውን ለማረጋጋት አባሎችን ይገፍ በሄድኩበት የድንጋይ እሩምታ ነበር በዛ ሰዓት ሰባት ሰዓት አካባቢ ላይ ያው እኔ ላይ ከየት መጣም ሳልለው ግራ እግሬ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ተመታሁ ወደቅኩ ያው የነበሩት አባሎቼ እራሴን ስለማላውቅ /ግልጽ ያልሆነ/ ድንጋይ ይሁን ምን አላውቅም ተመታሁ ወደቅኩ አባሎቹ ይዘው ወደ ሆስፒታል ደረሱ የነበረው ከፍተኛ ብጥብጥ ነበር ድምጽ ያለው ማለት ነው
- ብጥብጥ ቁባ መስኪድ የሚገኘው የት ክ/ከተማ ነው?
- አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ኮልፌ

2948 4094

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚህ በዚህ ለሊት ምሽት እናንተ አስቀድሞ መረጃ እንደነበራችሁ ነበረ እና ከዚጋር በተያያዘ በነማን መሀከል የተካሄደ ብጥብጥ ነው ምን ነበረ ብጥብጡ ምን ይባል ነበር ?
- አላህዋክበር ነው የሚባለው ጩኸት አለ ድምጽ አለ
- ድንጋይ ውርወራው ከማን ወዴት ነው ምንድን ነው ምክንያቱ የነበረው ማለት እናንተ ያው በወንጀል መከላከል ስለነበራችሁ ድንጋዩ ከየት ወዴት ነው በማን ላይ ነበር ምን ነበረ?
- ፀጥታ ኃይሉ ላይ እኛ ያለው ማለት ነው
- ማለት ሲሉ በማን ነው ?
- በድምጽ በሚያሰሙት
- ማለት ፀጥታ ኃይሉ ማለት በእናንተ ወንጀል ልትከላከሉ የቆማችሁት የፖሊስ አባል ማለት ነው ?
- እኛ አዎ ወንጀል ለመከላከል የሄድን አባሎች እኔ ነኝ የምመራቸው እኔ ነኝ ይገባ የሄድኩት በድምጽ ነው የሄድነው እኛው ላይ ነው ድንጋይ የሚወረወረው እኔ የምመራቸው ማለት ነው
- ማለት የአዲስ አበባ የፌደራል?
- አይ አዲስአበባ ፖሊስ የእፎይታ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ አባሎች ማለት ነው
- ከእርስዎ ሌላ በወቅቱ ማለት በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳት የደረሰባቸው አሉ ነበሩ?
- አዎ እኔ በጣም ስለተጐዳሁ ነው ከዛ በኋላ የተወሰኑ አባሎች ነበሩ ጉዳት የደረሰባቸው
- እርስዎ ጉዳት ከደረሰቦት በኋላ እንዴት ነው ወዴት ሄዱ ምን ተደረገሎት እግሮ ጉዳት የደረሰቦት ሁኔታ በምን ደረጃነው የሚገኘው ስራው መቼ ገቡ እስቲ ስለዚህ ?
- ጉዳቱ እንደደረሰብኝ ያው አጠገቤ የነበሩ አባሎች ናቸው ከቦታው እራቅ አርገው መኪና ጠሩልኝ ፖሊስ ሆስፒታል ነው የሄድኩት ከተመታሁ 1 ወር ከ15 ያህል ማስረጃ አለኝ በአጠቃላይ ግን 3 ወር ስራ አልገባሁም
- እ?
- አንድ ወር ከ15 ቀን ማስረጃ አለኝ ሃኪም የሰጠኝ ማለት ነው ከአልጋ አልወርድም እግሬን ገትሬ የምተኛው እንዳልንቀሳቀስ ከዛ ውጪ ያው የተለያየ ጊዜም አልገባሁም ሕመሙ እስቲል እስካሁን ቅዝቃዜ ሲኖር የሚሰማኝ ስሜት አለ አጥንቱ ላይ ስለሆነ የተመታሁት
- እናንተ በዚህ በመከላከል ሂደት በወስቱ እርስዎ ጉዳት ከመድረሱ በፊት እነኚህ በፀጥታው አስከባሪዎች ወይም በፖሊስ አባላት ላይ ያው እንዳሉት እየጮሁ ድንጋይ ሲወረውሩ የነበረው ከየት ወዴት ነው የመጡት ?

2947 4095

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሲጀመር መጀመሪያም እኛ ድምጽ ስንሰማ ከመስኪድ እኛ ከነበርንበት ጣቢያ ስንወጣ ሁሉም ከየመንደሩ ነው የሚወጣው ወደ መስኪዱ አካባቢ ስንደርስ መስኪድ አካባቢ ሞልቷል አካባቢው ላይ ነው እኛ ያለነው ፀጥታውን ነው የምናረጋጋው ሕዝቡ ሞልቷል ጥቅጥቅ ብሎ ከዛ እኛ ስንደርስ ወዲያውኑ ድንጋይ ውርወራ ነው ያለው የነበረው ማለት ነው ወደኛ ወደ ፀጥታ ኃይሉ
- እንዴት ተሰበሰቡ ማን ጠራቸው ይሄን ለማወቅ ችላችኋል በወቅቱ ማለት ይሄ የአካባቢው ከየመንደሩ የወጣው ሕዝብ ?
- ድምጽ ነበሩ ድምፁ እና ጣቢያው ይቀራረባል
- ምንድን ነው ድምፁ ?
- ድምፁ ያው መስኪድ ላይ የሚሰማው አዛን ያለው ድምጽ ነው የሰማነው በዛ ሰዓት እንደዚህ አይነት ድምጽ የለም በሰራሁበት አመት ማለት ነው
- ይሄ ሰዓት ስንት ሰዓት ነበር እርስዎ አዛን የማሰሙት ማለት ነው ?
- አምስት እስከ አምስት ተኩል ይሆናል
- ማለት ቀን ነው ምሽት?
- ማታ
- እርስዎ እዛ አካባቢ በቆዩበት ጊዜያት እንደዚህ አይነት ሰምተው ያውቃሉ?
- ሰምቼ አላውቅም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ምስክር እርስዎ ፖሊስ ሆስፒታል ለአንድ ወር ተኝተው እንደወጡ ነው የረፍት ጊዜ ሰጥተዎት ነው የወጡት ወይስ ሕክምናውን ጨርሰው ወጡ?
- ሆስፒታል አልተኛሁም ሆስፒታል ሳልተኛ ቁስሌ ታሽጐ ቤት ውስጥ በስርዓት እንድከታተል በመጀመሪያ 15 ቀን ከዛ የአንድ ወር ፈቃድ ከአልጋ እንዳልነሳ የተሰጠኝ ነው ከዛ በኋላ ግን የጉዳቴ መጠን እንደታየ የአለቆቼ ፈቃድ ነው መስራት ስለማትችል
- ስለዚህ 3 ወር የቆዩት በአለቆቾ ፈቃድ ነው ሥራ ሳይገቡ ?
- አንድ ወር ከ15 ቀን የሆስፒታል ፈቃዴ ነው ሌላው ግን እግሬ ላይ ስለሆነ ስለሚያስነክሰኝ ፍቃዶቼን አለቆቼ ካዩት ከደረሰብኝ ጉዳት መነሻ እያዩ ማለት ነው
- ከሆስፒታሉ በምን ተሰናበቱ ማለት ሕክምናውን ጨርሰው ተሰናበቱ ?

29ዛ 4096

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሆስፒታሉ በደረሰብኝ ሕክምና አሸገልኝ መደረግ የሚገባው ነገር ተደረገልኝ በመጣሁበት መኪና እንድሄድ ተደረግኩ
- የሜዲካል ቦርድ ቀርበው ነበር እንዴ ማለት ሕክምና ተደረገሎት በኢስፔሻሊስት ሃኪም ?
- አዎ እስፔሻል ዶክተር ጋር ቀርቢያለሁ
- እኮ ከዛ በኋላ አሁን በአካሉ ላይ ይሄን ያህል ፐርሰንት ጉዳት ደረሰ ወይም የሚል ነገር ተሰጥቶታል እንዴ የሃኪሞች ቦርድ ?
- ማስረጃው እንግዲህ ማህደሩ ላይ ነው የሚሆነው ለኔ የሕክምናው ማስረጃ ነው በተለይ መጨረሻ ላይ የወር ፍቃድ ሲሰጠኝ ከአልጋ እንዳልነሳ ማለት ስንጥቃት አለው
- ሕመሞ እስኪድን ድረስ ከአልጋ እንዳይነሱ ተባለ?
- አልጋ ላይ ሆነው በስርዓት እንዳስታምም ተገለፀልኝ ፍቃዱ ተሰጥቶኝ ማለት ነው
- አሁን ያለ ዱላ ያለ ሌላ ነገር ነው አደል የሚንቀሳቀሱት?
- አዎ
- ስብራት የለውም?
- እንግዲህ ያው የባለሙያ ስራ ነው ስንጥቃት ነበረው አሁን ዱላ አልይዝም
- እኮ አሁን ሥራዎን እየሰሩ ነው ?
- አሁን እይሰራሁ ነው የምገኘው
- ቅድም ጣቢያ ላይ ሆነው ድምጽ እንደሰሙ ከጠቀሱት መስኪድ እርስዎ ጣቢያ ሆነው መስኪዱን በአይነ ማየት ይችላሉ እንዴ ከጣቢያው በሩ ላይ ሆነው ወደ ውጭ ሲመለከቱ በመካከል ቤቶች አሉ አደል በቀጥታ መስኪዱ አይታይም ፖሊስ ጣቢያ ተኩኖ?
- አይታይም ድምጽ ይሰማል
- እሺ ሌሎች መስኪዶች የሉም በዛ አካባቢ?
- እኛጋ ያለው ዋናው ቁባ መስኪድ ነው
- ሌሎች በዛ አቅራቢያ ጣቢያ ሆናችሁ ድምጽ ልትሰሙ የምትችሉበት መስኪዶች የሉም በዛ መካባቢ በቅርብም ይሁን በእሩቅ ?
- በጣብያዬ በምመራብት ጣቢያ ላይ የምሰማው እሱን ነው እና አለ ሌላ መስኪድ የዛን ድምጽ አልሰማሁም መስኪድ አለ እዚህ ነው ያለው ቁባ መስኪድ እና ነው ድምፁንም የሰማነው
- እኮ ቁባ ይሁን?
- ቁባ መስኪድ አሁን የኔ እዛ የነበረው ድምጽ የነበረው እዛው ነው የሰማነው ከሌላ መስኪድ የነበረው እንግዲህ ያው ቦታው ላይ ስላልነበርኩ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ የለንም
- እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ እግሬ ላይ ተመትቻለሁ ነው ያሉት ድንጋይ ይሁን ምን ይሁን አላወቅኩም ነው ያሉት ከእርስዎ ውጪ የተመታ አባል ነበር ያኔ?
- አዎ እኔ እንግዲህ ከተጎዳሁም በኋላ
- አይ ከዛ በፊት ከተጎዱማ ተወሰዱ አደለ ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ?
- አዎ እዛ ያው ድንጋይ ነው የሚመታው በጣም ወድቀው ተኝቶ ይሄ ነው ብሎ ማለት ባይቻልም አባሉ ላይ የሚደርሰው ድንጋይ ነበር
- አይ በወቅቱ ያዩት አለ ወይ ነው ጥያቄው ?
- እዛው እኛው ከኔው ጋራ ሲደርስብን የነበረው እኔ ሲብስ ነው የወደቅኩት እኮ ስንከላከል እንዲህም እንዲህም እያልን እየተከላከልነው ነው ያለነው ለማረጋጋት
- ስለዚህ ሌላ አባል ይመታ አይመታ የሚያውቁት አለ ወይ ነው ጥያቄው ወደ ሆስፒታል ከመሄዶ በፊት ?
- በስም ነው መግለጽ የማልችለው በርካታ አባሎች ጥቃቅን ጉዳት የደረሰባቸው ቢኖርም ይሄ ነው ብዬ የምናገረው አሁን በስም የለኝም
- በስም ማስታወስ አይቻልም?
- አዎ
- /የማይሰማ/
- በኔ ቀጠና እኔ ነኝ
- ከዛ በኋላስ የመጡ አሉ?
- ከዛ በኋላ የመጡ አሉ
- እርስዎ ሳይወጡ ነው ከተመለሱ?
- አይ እኔ እዛው ሆኜ እኜ ስደርስ የሄዱም አሉ ያገኘኋቸው
- እሺ ድንጋይ ውርወራው ከናንተ በፊት የደረሰ ፖሊስ አለ እንዴ እዛ ?
- እኛ ነን የደረስነው
- ከናንተ ቀድሞ የደረሰ ፖሊስ የለም?
- የለም
- ድንጋይ ውርወራው እናንተ ከደረሳችሁ በኋላ ነው የጀመረው ወይስ በፊትም ነበር?

2980 4098

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው የበፊቱም እኛ ስንደርስ ያየነውን ነዋ እምንገልፀው እኔ ስደርስ እኛ ስንደርስ ያው ጥርቅሙ ብዙ ነው እኛን ሲያዩ ነው እኔ ቀጥታ ከዚህ ከግቢያ ነው የወጣሁት ስለዚህ ድንጋዩ እኛን ሲያዩ ነው ውርወራ የነበረው ሌላ አካል የለም ሀጥታ ኃይል ነን የሄድነው መጀመሪያ
- እሺ. ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ
- ምናልባት ወይ የኃይማኖታዊ እንትንም ሊኖረው ስለሚችል እሳቸውም ካነሱት እንነግር ወይ
- ምንድን ነው ተቃውሞው ስነስርዓታዊ ነው?
- አዎ መሃላው በዚህ መልክ ነው መፈፀም ያለበት ነው
- በዚህ በፈቀዱት መሰረት እንደሚሉ ፍ/ቤቱ ነው የፈቀደው ከዛ በኋላ መቃወም ይቻላል ወይ ነው ጥያቄው
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ምንድን ነው ሃሳቡን ፍ/ቤቱ ይስማን እና ካልተቀበለን
- ስለዚህ አይቻልም ፍ/ቤቱ ሰው በሚያምነው መሰረት ነው ቃለ መሃላ የሚፈጽመው እኔ በማምነው መሰረት ኡዱ ሳላደርግ ቁርአን መያዝ አልችልም ወይ ወጥቼ ኡዱ አርጌ ተመልሼ ቁርአን ልያዝ ነው ያለው ይሄ እምነቱ ከሆነ በዛ የሚያምን ከሆነ ቁርአን ሳይዝ በአላህ ስም ምሏል ይሄ ለፍ/ቤቱ በቂ ነው ብሉ ብይን ስለተሰጠ ከዚህ በኋላ የምናቀርበው ነገር የለም
- እሺ. ለምስክርነት ነው የመጡት
- አዎ
- ስሞን የራሶን ስም ብቻ ይነግሩናል የአባቶን ሳይጨምሩ ?
- ኤልያስ
- በስረጃ ዝርዝሩ በተሰማው ዝርዝር ልክ 98ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በክሱ ላይ በማስረጃ ዝርዝር 64ኛ ላይ የተጠቀሱ ኤልያስ ቀርበዋል ማን ላይ ነው የሚመስክሩት አቶ ኤልያስ ?
- እምመሰክረው አህመዲን ጀበል እና ሼህ መከተ ሙሂ ላይ ነው
- እነዚህ ሁለቱ ላይ ብቻ?
- አዎ
- ያውቁታል ሰወቹን ለይተው?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአካል ማሳየት ይችላሉ ?
- በአካል አዎ መለየት ሙሄን በደምብ ማሳየት እችላለሁ
- እሺ አህመዲንንስ ?
- አህመዲንን ማሳየት አልችልም ከዛ ከጽሁፍ ከቀረበ እና ከነበረኝ የቢሮ እሪፖርት በስተቀር
- እሺ አህመዲንን መለየት አልችልም ነው ያሉት ?
- አዎ
- እሺ ምስክሩ 6ኛ ተከሳሽን አመልክተዋል አህመዲን ጀበል ብለው በስም የጠቀሱትን ማን መለየት አልችልም በሪፖርት ነው የማውቀው ብለዋል እስቲ ምንድን ነው የሚያውቁት አጠር አርገው ይንገሩን ዝርዝሩን ያው በኋላ ?
- የሁለቱንም ይቅርታ እንዴ ድምጼም ቀስ እያለ እየጨመረ ስለሚመጡ ፍ/ቤቱ ግንዛቤ ያውሰድልኝ በቁጣ ሳይሆን ወይ ለእንትን ሳይሆን ካለኝ ባህሪ እንደሆነ እንዲረዳልኝ ለመቆጣት ወይም እንትን ለማለት አደለም እጄንም የማንቀሳቅሰው ልምድ ሆኖብኝ ነው
- ችግር የለውም እርስዎ እንደተመቸዎት ይናገሩ
- ምንድን ነው የአህመዲን ጀበል ከቢሮ እሪፖርት ያልኩት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ምክትል ሊቀመንበር ነበርኩ እኔ በዛ በነበርኩበት ወቅት አቶ አህመዲን ጀበል
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል ወደ ዝርዝር እየገቡ ስለሆነ
- ምናልባት ምስክሩ ከተከሳሾች ጋር ፀብ ወይ ዝምድና ያለው መሆኑ ስላልተጠየቀ ይሄ ቢጠየቅልን
- እሺ አሁን የሚያውቁትን ሼህ መከተን ነው ብለዋል ከሼህ መከተ ጋር ዝምድና ወይ ጥላቻ አለ'ት?
- ምንም የለኝም
- እሺ ቀጥሉ
- እሺ ሼህ ኤልያስ እምጠይቆትን እየሰሙ ይመልሳሉ እስቲ እንዳልገድቦት ይጀምሩና ከዛ እኔ መሃል ላይ እገባለሁ አሁን በስም ስለጠቀሱት እና በአካል ለይተው ስላሳዩዋቸው ሁለት ሰወች እሚያውቁትን ነገር በዝርዝረ ያስረዱን ከጊዜው ይጀምሩ ጊዜው መቼ ነው ?
- እንግዲህ በሺ ዘጠኝ መቶ 97 ምርጫ ከተካሄደ በኋላ በሙስሊሙ ዙሪያ ብዙ ከፍተኛ እንቅስቃሴዎች ይካሄድ ነበረ ይሄ እንቅስቃሴ በተለይ ትምህርት ሚ/ር በኒቃብ ጉዳይ ላይ የሰጠው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኒቃብ የምንደን ነው በተቻለ መጠን ከአሁን በኋላም ሲመሰክሩ ኃይማኖታዊ ቃል ባይጠቀሙ ጥሩ ነው ምክንያቱም ስለ ትርጉሙ አማርኛ ስለሆነ ወደ እየተረጎሙ ይንገሩን ኒቃብ ብለው ኒቃብ ምን ማለት እንደሆነ?
- ኒቃብ ማለት ይሄ ሴቶች ፊታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙበት በሸሪአችን ፒጃብ ማለት ፊትን ገልጦ እጅን እስከዚህ ድረስ ይሸፍን እና ጣቶችን በሚያሳይ ሁኔታ ፊትን ደግሞ በሚገልጽ ሁኔታ የተቀመጠ ነው የሸሪአችን ሕግ
- ጥሩ ምን ተፈጠረ ከኒቃብ ጋር ከፊት መሸፈኛ ?
- ትምህርት ሚ/ር ተቸገርኩ አለ ይሄን ኒቃብ እየለበሱ ሴቶቹ እየመጡ ፈተናም ወቅት ላይ ትምህርቱም ጉዳይ ላይ ማን እንደሚማር ማን እንደሚፈተን ለመከታተል ችግር ስለሆነ በተለየ አይነት መንገድ ከኃይማኖቱ ጋራ ግንኙነት አለው ወይ በሚል እንዲሁም አንድ ወጥ የሆነ እኛም እራሳችን እንደ እስልምና ጉዳይ ምክር ቤት ክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ ጋራ ቀርበን በዛ ወቅት ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ነበሩ ከእሳቸው ጋራ አንድ ሕግ ለምን ልጆቻችን ከኤለመንተሪ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ፒጃብ እንዳያደርጉ ሴቶች ልጆቻችን ኃይማኖታዊ ግዴጅ ነው አንዲት ሴት ልጅ የወር አበባዋን ማየት ከጀመረችበት ወቅት ጀምሮ የግድ ኃይማኖቱ ያዛል ፒጃብ እንዲያደርጉ ስለዚህ ይሄንን አድርገው መማር ስላልቻሉ በየትምህርት ቤቱ ሻሽሽን ግለጪ ይሄንን ልብስሽን ግለጪ እየተባለ ችግር ስለተፈጠረ ሕግ ይውጣልን ብለን ጠይቀን ነበር በዚህ መሰረት የሚከለከሉት ነገሮች በሸሪያ አሁን ለምሳሌ ይሄ
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ደምበኞቻችን ባልተከሰሱበት ጉዳይ ነው ምስክሩ ዝርዝር ማብራሪያ እየሰጡ ያሉት እና አቃቤ ሕጉ ወደ ጭብጡ ሄደው ትክክለኛ ጥያቄ ጠይቀው ጭብጡን እንዲያስረዱ አለበለዚያ ገጽታ ማጥፋት ካልሆነ በስተቀር ምንም የሚያስረዳው ነገር የለም
- ትንሽ ለመጨመር ነው ክሱ ከ2001 ጀምሮ ነው የሚያወራው አሁንግን ከ1997 ጀምሮ ወደ ኋላ እየተኬደ ነው እና አንደኛ የሚመሰክሩትም ከክሱጋር ግንኙነት የሌለው ነገር ስለሆነ ከክሱ ጋር የተገናኘውን ብቻ የሚያውቁ ከሆነ እንዲመሰክሩ ይታዘዝልን
- ምናልባት ይሄ የአካሄድ ጉዳይ ስለሆነ መልስ ማሰጠት አስፈላጊ አደለም ስለዚህ ክሱ ላይ ግልጽ ነው ወደዛ ፍሬ ነገር ብቻ ቀርበው ምላሽ እንዲሰጡ ይጠይ አቃቤ ሕግ ቅድምም ከ97 ሲጀምሩ ክሱ ውስጥ ወዳለው ተብሎ ነበር አሁንም ወደዛ ቀጠሉ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ምስክር የጠየቅኩት ጥያቄ አሁን በስም የጠቀሷቸውን ሰወች የት እንደሚያውቋቸው ከመቼ ጀምሮ እንደሚያውቋቸው ነበር የጠየቅኩት ብለው አሁን ወደሄዱበት እንደሄዱ ይገባኛል ግን አሁን የተከበረው ፍ/ቤት ባዘዘው መልኩ ወደተፈፀመው ነገር ከኪታብ ወይም ከፊት መሸፈኛ ጋር ተያያዞ ምን ተባለ እርስዎ ምን አሉ አበር አርገው በቃ ሰብሰብ ያረጉትልን ምን ተፈጠረ ችግር ተፈጠረ በዛ ምክንያት አወቋቸው
- ቀዩ እስቲ ምስክር እነዚህ ሰወች ምን አደረጉ ተብለው ነው የተከሰሱት?
- ምን አድርገዋል ተብለው ነው የተከሰሱት እነዚህ ሰወች ሽብር የሚፈጥር ነገር ቀስቅሰዋል
- እሺ መቼ ነው እሱ ነገር?
- እሱ የአምና 2004
- እኮ እሱን ቀን በትክክል ክሱ ይጀምሩና ከዛ በኂላ ያለውን የተደረገውን ድርጊት ነው?
- በ2004 ላይ ላለው ነገር እኔ አልነበርኩም በቦታውም በቦታው ያልነበረ ሰው ያላየውን ነገር መመስከር ይከብዳል
- ጥሩ ምስክር ከሼህ መከተ ሙሄ ጋር የት ነው የሚተዋወቁት?
- ሼህ መከተ ሙሄን የማውቃቸው ሸሪአ ፍ/ቤት ሰብሳቢ ሆነው ነው የጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት
- ጥሩ አሁን ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ምን እንዳረጉ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አዎ ይሄ አሁን በ2004 የተደረገው እንቅስቃሴ
- ኖ ከ2004 ሳይሆን በዛም በፊት ሊሆን ይችላል 2004 ብቻ አይደለም ከዛ በፊት ሊሆን ይችላል?
- እኮ ይሄ መነሻ ሳይኖረው መቼም እንቅስቃሴ አልተደረገም?
- የተከበረው ፍ/ቤት ቀጥታ ጥያቄ ይጠየቁ እና ምላሽ ይስጡ እየተመሩ ነው የተከበረው ፍ/ቤት እኔ የማውቀው ይሄን ነው የማላውቀው ይሄን ነው ብለው እየተናገሩ አቃቤ ሕግ እየመሯቸው ነው እና በዚህጊዜ ያለውን ነገር ይንገሩኝ እያሏቸው ነው አስተካክለው ይጠይቁ የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት መልስ እንስጥ
- አስተያየት ማስጠት አያስፈልግም ምንም 2004 ጀምሮ ከዛ በፊት ስላለው ነገርም ግለፁ ነው የተባለው መሪ አደለም ትክክል ነው ይቀጥሉ ነገር ግን ከክሱ ጭብጥ ከወጣ እኛ እናስቆማለን
- እሺ ምስክር ይቀጥሉ ከኪታብ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ችግር ነበረ?
- አዎ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ተባለ?
- በየ ት/ቤቱ እና ዩኒቨርስቲው ችግር ተፈጥሯል ከዛ በኋላም ደግሞ በ2000 ዓ.ም. ሚሊኒየም በሚል ምክንያት በማድረግ ከአውሮፓ እና ከአሜሪካ በድሪ ኢንተርናሽናል የሚባል አንድ ድርጅት እንዲመጣ እነ ሼህ መከተ ብዙ ቅስቀሳ አድርገው
- ለምን?
- ይሄም የመጣው ከጠቅላይ ሚንስትሩ ጋራ በመጅሊስ ዙሪያ መጅሊስ መውረድ አለበት ሕዝብን ያልወከለ መጅሊስ ነው የተቀመጠው ስለዚህ ሊነሳ ይገባዋል የሚል ነገር በማስነሳት እና አብሮ ሚሊኒየሙንም እናከብራለን ብለው ዶ/ር አብዱል ጀሊል የሚባሉ ግለሰብ እኚህ ሰው ቀደም ሲልም የኦነግ አባል የነበሩ ናቸው በሳውዲ አረቢያ ብዙ እኛንም በመጅሊስ አካባቢ በነበርንበት ወቅት
- ጥሩ በዚህ ጉዳይ ላይ ሼህ መከተ መጅሊስ ይውረድ መወገድ አለበት ብለው እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር ብለዋል ምንድን ናቸው እነ ሼህ መከተ እነ የሚሏቸው እነማን ናቸው ምንድን ናቸው?
- እነዚህ እነዶ/ር አብዱል ጀሊል በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይሄ ስሙ እዚህ ምንድን ነው ማን ነው የሚባል ሆቴል አለ አባኮራን ሰፈር ቢስ መብራት አካባቢ ከሊፋ ሕንፃ እዛ በተደጋጋሚ ከነዚህ ኃይሎች ጋር ተሰብስበው ግምባር ቀደም መሪዎች ነበሩ የመጅሊስ ይውረድ እንቅስቃሴ ከዛ ጊዜ ነው የተጀመረው በኋላም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጧቸው መልስ ነበር ያንን መልስ እነበድሪ ኢንሰርናሽናል ሰወች ሊቀበሉም ሊያረኳቸውም አልቻለም ስለዚህ እስትራቴጂክ መለወጥ ስላለባቸው እስትራቴጂካቸውን በ2004 ለውጠው ነው የወጡት እኔ እማውቀው እስከዚህ ድረስ ነው
- ጥሩ እነ ሼህ መከተ እርስዎ በወቅቱ የእስልምና ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝደንት ነበሩ በዚህ የኃላፊነት ቦታ ላይ እያሉ ከነሼህ መከተጋር ተገናኝታችሁ ነገራግራችኋል ምን እንደሚፈልጉ ያውቃሉ እነ ሼህ መከተ እርስዎ?
- የነሼህ መከተለ አላማም ሽሪአውን ፍ/ቤቱን ሲይዙ የወሃቢዝም አስተሳሰብ ወይም አስተምሮት የሚስፋፋበትን እና በተለይም መስኪዶች በነዚህ ሰወች እጅ ስር እንዲወድቁ በማጽደቅ ሲሰረ የነበረበት ነው በአብዛኛው የእሳቸው ውሳኔ እሳቸው ከተነሱ በኋላ በምክትላቸው እንዲሻር ዉሳኔው ላይ እናንተም ፍ/ቤቱም ያውቀዋል በዳኞች ጉባዔ ነው አንድ ዳኛ የሚነሳው የዳኞች ጉባዔ አይተውት የሳቸውን መነሳት አምነውበት ወዲያው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እንዲነሱ ከተደረገ በኋላ አብዛኛው የሳቸው ውሳኔ ምክትላቸው በነበሩት ሰወች እንዲሻሩ ተደርጓል

- ጥሩ አሁን ሲመልሱ እነሺህ መከተ እና ሌሎች በድሪ ኢንተርናሽናል እና ሌሎች ይሄን እንቅስቃሴ የጀመሩት በእስልምና ያሉ ቦታዎች በሙሉ በወሃቢዝም ሰወች እንዲያዙ ስለሚፈልጉ ነው ብለዋል ምንድን ነው ወሃቢዝም ምንድንነው የሚያረገው ይሄ ወሃቢዝም የሚባል?
- ወሃቢዝም እንግዲህ የአክራሪነት ባህሪ አለው
- ምን እናርግ ይላል?
- የራሱን እምነት በሰው ላይ የመጫን ስራ የሚሰራ ኢንስቲቲውሽን ነው
- ስለ ኃይማኖት ትንተና ውስጥ ከተገባ አያስፈልግም ለኛ ማለት ነው እስቲ አሁን ወዲዝም ትርጉም ውስጥ ከገቡ ገና ቁርአን ሊያጣቅሱ ነው እሱ ደግሞ የዚህ እንትን ማንዴት አደለም እና ከኃይማኖቱ ቃላትተቆጥበው የአማርኛ አቻ ትርጉም ካለው በዛ ውስጥ ተደርጐ እንዲቀጥል ጥያቄውን በዛ መሰረት ያስተካክሉ
- ጥሩ እሺ አሁን ያሏቸው ቡድኖች የሚሰብኩት ነገር ነበር ከሚያምኑት እምነት በተለየ የሚሰብኩት ነገር ምን ብለው ይሰብካሉ ?
- በአብዛኛው የሚሰብኩት አንደኛ ለክርስትያን መንግስት ግብር መክበር እንደሌለበት ይሰብኩ ነበር ይህም በተለያየ አካባቢዎች ላይ አይተናል 2ኛ ሌላውን የእምነቱን ተከታይ እንደ ባእድ አምላኪ አድርገው ሙስሊምም ቢሆን ይሄንን በመፈረጅ እና የነሱን እምነት የማይከተል ስደቃ መብላት እንደማይበቃ መውሊድ ማውጣት እንደማይበቃ እነዚህ እነዚህ ነገሮች በስፋት ሲያስተምሩ የነበረበት ነው
- የክርስትያን መንግስት /የማይሰማ/
- ማንኛውም የክርስትያን መንግስት ግብር ሊከፈለው አይገባም
- እኮ ማን ነው የትኛውን ነው የክርስትያን መንግስት የሚሉት?
- ይሄ ያለውም መንግስት ቢሆን እነሱጋ እንደክርስትያን መንግስት ነው የሚቆጥሩት
- ጥሩ እሺ በዚህ ሁኔታ እንቅስቃሴው ተጀመረ ከዛ በኋላ እርስዎ በኃላፊነት እያሉ አሁን በጠቀሱ ቡድን አማካኝነት ለሎች የተደረጉ ተከታታይ እንቅስቃሴዎች ነበሩ?
- ነበሩ በተለይ በአንድነት ስም አንዳንድ ስራዎች ለመስራት ፕሮግራም አዘጋጅተው የተወሰኑ የኃይማኖት አባቶችን አሳስተው ፊርማ እንዲፈራረሙ በማዘጋጃ ቤት ካደረጓቸው በኋላ ይሄንን በመቃወም ድብዳቤ በተከታታይ ከኔ ቢሮ በኤው ፊርማ [illegible] ሼህ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መከተማ በክብር እንግድነት በተገኙበት ቦታ ፕሬዝደንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ባሉበት ቦታ ላይ እና ትላልቅ የመንግስት ባለስልጣናት ባሉበት ቦታ ሃገሪቱ ትልቅ ችግር ላይ እየወደቀች እንዳለች እና ወደፊት የአክራሪነት አዝማሚያ የሚታይባቸው ኃይሎች በስፋት እየተንቀሳቀሰስለሆነ መንግስት ከወዲሁ አንድ ነገር ካላደረገ ይሄ ጉዳይ ወደ ከፍተኛ እስላማዊ መንግስት ወደ ማቋቋም ደረጃ ላይ ይደርሳል ስለዚህ አልባት ሊደረግ ይገባል እንዲህም ከእኛው መሃል ብለን የአዲ ስአበባ እስልምና ጉዳይ ም/ቤት አመራሮች አፈንግጠው ወጥተው ከነዚህ ኃይሎች ጋራ ተፈራርመዋል ብለን የመጀመሪያ የኃይማኖት አባት ከተናገርኩት አንዱ እኔ ነኝ

- በዛ ሁኔታ ላይ ሼህ መከተ ምን ሚና ነበራቸው ታዲያ ?
- የክብር እንግዳ በመሆን በዛ ቦታ ላይ የዚሁ የነዚሁ አካሎች አንድነት እንጂ ጥራሰኝ የሚሉ አካሎች አመራር በመሆን የክብር እንግዳ ተብለው ተጠርተው ነው የተገኙት ይሄን አስታውሳለሁ ፊልሙም አለ ማስታወቂያ ሚ/ር ውስጥ ምናልባትም መጅሊስም ሊኖርም ይችላልእኔ አሁን ስለለቀቅኩ ቢጠሩ ያንን አይተው
- ሌላስ ?
- ከዛ በኋላ ያው እንግዲህ ይሄንን እኔ ካስረዳሁ በኋላ በ2001 እኔ ተነስቻለሁ ከቦታው ከዛ ወዲህ የተፈጠረው ነገር እንግዲህ መንግስት እና ሕግ ነው የሚያውቀው
- ከዛ በኋላ አሁን 2004 ላይ ተፈጠረ ሲባል የሰሙት ነገር አለ ይሄ 2004 የተፈጠረ ነገር እርስዎ በ2001 ስልጣን ላይ እስከነበሩበት ጊዜ ድረስ ከተደረገው ነገር ጋር የሚያገናኘው ነገር እንዳለ ያውቃሉ ?
- እንግዲህ እነሱ እየተደራጁ የመጡት እረጅም አመት አላቸው አሁን በዛን ጊዜ የተጀመረ የመደራጀት ስራ ነው እየተሰራ ያለው የተለያየ ኃይማኖት /ግልጽ ያልሆነ/ እየተበተኑ አሁን ስምተነው የማናውቀው አይተነው የማናውቀው የእስልምና /ግልጽ ያልሆነ/ እየሰማን ነው ያለነው በአሁኑ ወቅት
- ለተጠየቁት ቀጥታ ምላሽ ስጡ በተባለበት ነው
- አዎ አሁን እኮ እያልኩ ያለሁት
- አሁን አጭር ነው በፊት ከነበረው ጋር ይያያዛል አይያያዝም የሚለውን ብቻ ?
- ይያያዛል ለምን አደረጃጀቱ ከዛን ጊዜ አንስቶ የመጣ እና ሌሎቹንም እያሰባሰበ እያጠራቀመ መጥቶ በ2004 /ግልጽ ያልሆነ/

2957

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ደጋግመው እነሱ መደራጀት የጀመሩት ከ2000 አመተምሬት በፊትም ነው እስከ 2001 እኔ ስልጣን ላይ እስካለሁ ተጎሳል ከዛም የ2004ቱም ይደግል ተደራጅተው ነው የመጡት ብለዋል እነሱ የሚሏቸው እነማን ናቸው?
- እንግዲህ እነሱ የምለው እኔ አሁንም ትኩረቱ ሼህ መከተ ላይ ነው ሼ. መከተ ከዛን ጊዜ ጀምሮ አባል እየሆኑ ይዘውት የመጡተ ነው
- እኮ ሼህ መከተ አንድ ሰው ናቸው አንድ ሰውን እነሱ
- አብረዋቸው ብዙ ናቸው ያሉት
- እነማን ናቸው እነሱ ?
- ብዙ ናቸው እንግዲህ ይሄንን ዝርዝራቸውን የፈረሙት ወረቀት ላይ
- ስም አላቸው ?
- ስምም አላቸው አድራሻም አላቸው
- ምንድን ነን ይላሉ?
- ዝርዝሮች አሉ የፈረሙበት ከእኛ መሃል
- የፈረሙት ምንድን ነው ?
- የፈረሙትም የሙስሊም ጉይማኖት አባቶች እነእከሌ እነከሌ ፈርመው ነበር ከዛ በኋላ ጠርተን ካነጋገርናቸው በኋላ እኛ ይሄንን ችግር አናውቅም ብለው ደሞ የወጡ ሰወች በማስረጃ መጥራት እንችላለን እኛ
- ጥሩ እሺ ከ2001 እና እስከ 2004 ተያያዥነት አለው የሚሉት ቡድን ምንድን ነው የሚፈልገው
- ተቃውሞ ያው ከፍ/ቤትም የተሰጠውን ማሳሰቢያ በማለፍ ነው አቃቤ ሕግ እንደገና ጥያቄ ውስጥ የገቡት ቡድን ብለው ነው የጠየቁት ቡድን የሚል ነገር ምስክሩ እስከ አሁን አልተናገሩም ቡድን አለም የሚል ሃሳብ አላነሱም ቡድን አለ የሚለው ነገር የአቃቤ ሕግ ሃሰብ ነው ስለዚህ አሁን ይሄ ጥያቄ መጠየቅ የለበትም ተስተካክሎ እንኳን ይጠየቅ ቢባል ቡድን የሚለው ነገር ኦሬዲ ምስክሩ የተነገራቸው ስለሆነ ምስክሩ ወደዚህ ሊመጡ ስለሚችሉ ጥየቄው በአጠቃላይ እንዲሰረዝልን ነው የምናመለክተው
- መልስ እንስጥ
- እሺ አሁንም አካሄድ ስለሆነ ምላሽ አያስፈልግም የታለፈውን ደገሙ ነው የቀረበው በፍ/ቤት ይታለፍ የተባለውን ደግመዋል ነው ያን ደግመዋል አልደገሙም የአካሄድ ስለሆነ ምላሽ መስጠት ስለማያስፈልግ ሌላ ጥያቄ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ተፈራረሙ ከሼህ መከተጋ አብረው ናቸው ብቻውን ነው ወይ ስሙት አይ አብረው ሰወች አሉ ተፈራርመው የቀጠሉ እስከ 2004 ግንኙነት አለው ብለዋል እስከአሁን እነዚህ ሰወች አሁን ያሏቸው ሰወች ምንድን ነው የሚፈልጉት ?
- እንግዲህ በዛም ወቅት የነበረው ሁኔታ ሙስሊሙን በአንድ አድርገን መብቶቻችን የተጌደሉብንን እናሟላለን
- ምን ምን ?
- ብዙ መብቶች ይጉድሉብናል እሚሉት በሕገመንግስቱ መሰረት የሚጉለን መብት ብዙ ነገር ስላለ እናሟላለን በሚል ነበር አገባባቸው በኋላም ሙስሊሙግ ከመከፋፈል አውጥተነው ወደ አንድነት ይዘነው እንመጣለን ነው ይሄ ነገር ደግሞ የሙስሊሙ ጥያቄ እየተመለሰ ስለሆነ በዚህ አይነት ሁኔታ መቀጠል የለበትም የሚል ደግሞ ከኡለማው ምክር ቤት እኛጋ ካለ ኡለማ ማለት የኃይማኖት አባቶች ምክር ቤት ማለት ነው እነሱጋ በቀረበልን ጥያቄ መሰረት የመጅሊሱ የአመራሩ ኃይሎች ተነጋግረን ለመንግስት ደብዳቤ መፃፍ እንዳለበት እና ይሄ የተፈራረሙት ጉዳይ ወደ አንድነት ሳይሆን ነገ የፖለቲካ ጥያቄም ሊያመጣ ይችላል የሚለውን ሃሳብ በስፋት አንስተነው እንደዛን ጊዜም እንደስጋት ወስደነዋል እንደ ስጋት ወስደነው ተናግረናል
- ጥሩ ቅድም ሲመሰክሩ አህመዲን ጀበልንም አውቀዋለሁ ብለዋል በአካል ባያውቁትም በሌላ መልኩ አውቀዋለሁ ብለዋል አህመዲን ጀበል ምንድን ነው ያረገው?
- አህመዲን ጀበል እንግዲህ የፃፋቸውም መፃህፍቶች አሉ የፃፈባቸውም የብእር ስሞች አሉት በነዛ መፃህፍቶቹ ላይ ሰወችን በብዛት ፎቶ ግራፋቸውን በመደርደር እነዚህ ሰወች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፀር እንደሆኑ እና እስከ መገደልም ቢደረስ ወንጀል እንደሌለ የተበተነ አንድ ጽሁፍ አለ
- እነማን ናቸው እነዚህ ሰወች ?
- እነዚህ ሰወች አህባሾች ናቸው ብሎ ነው ያወጣቸው ከሼህ አብዱላሂ ሃረሪ ጋራ እኔን ተክቶ በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ምክልት ፕሬዝደንት የነበሩትን ጨምሮ መሃመድ ኢብራሂም የሚባሉትን ሰው ፎቶ ግራፋቸውን ሁሉ አውጥተው ይሄ በብእር ስም አንድ ጽሁፍ ጽፎ ነበረ ያ ብእር ስም ደግሞ በሌላ መጽሃፉ የነ ነው ብሎ ደግሞ እራሱ አምኖ የፃፈበት ይሄንን በደንብ እናውቃለን አቅርቡ ከተባለ ልንሰጥ እንችላለን
- ይቀጥሉ ምንድን ነበረ ዋና ዋናው ይዘት የዚህ ጽሁፍ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጽሁፉ በአብዛኛው የአህባሽ እንቅስቃሴ እየተደረገ ያለው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚል ነው እነዚህን ሰወች ለዩኒቨርስቲም ተማሪዎች በተለይ ለጅማ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ከተለያዩ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ጋራ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ነው የሚነግረው እና እዛ ጽሁፍ ላይ የነዚህ ሰወች ዋና አንቀሳቃሾች ዲናሞ ናቸው ብለው ያሏቸውን ፎቶ ግራፍ እና
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ደምበኛዬ በዚህ ጉዳይ ክስ አልቀረበባቸውም አሁን ምስክረ እያብራሩ ያሉት የሰነዱን ይዘት ነው ይሄ ሰነድ ለፍ/ቤት አልቀረበም ክስ አልተመሰረተባቸውም ይኸው አሁን እሳቸው መጽሃፍ ብለው የሚናገሩት ነገር ለፍ/ቤት በማስረጃነትም አልቀረበም ክስ ላይም አልተያያዘም በሌለ ክትትል ላይ ባልተመሰረተ ፋክት ነው እና እያስረዱ ያሉት ይሄ ተገቢነት ያለው ምስክርነት አይደለም ሊሰረዝ ይገባል አቃቤ ሕግም ሊጠይቁ አይገባም
- መልስ እንስጥ የተከበረው ፍ/ቤት
- እነዚህም ስለ መፃፍ በብሔር ስም ጽፈው እነኚህ ሰወች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፀር ናቸው ብለዋል የሰው ስምም እዛ ላይ ጠቅሰን በብሔር ስም ነው የተፃፈው በብሔር ስም ላይ ደግሞ በሌላ መጽሃፍ ያ የብሔር ስም የኔ ነው ብለው ጽፈዋል የሚል ነገርን በተመለከተ ነው የእርስዎ ተቃውሞ
- እሱንም ነው አሁን የሚገልፁት መጽሃፍ ወይም ጽሁፍ
- ይሄን በተመለከተ ከሆነ ኦሬዲ ታልፏል መስክሮ ስላለፈ የሚቀጥለው ጅማ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ነው የቆመው አሁን
- እሱ ኦሬዲ የታለፈ ስለሆነ እሱ ላይ የምንለው ነገር የለም
- ይኸው ስለመጽሃፉ ነው የተከበረው ፍ/ቤት እያልኩ ያለሁት ሁለት ናቸው አንደኛው እሱ ነው እሱ ታልፏል እየተባለ ነው
- እሱ ታልፏል አሁን ጅማ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ገብቶ ነው ያቆመው ምስክሩ ከስራ ጋ በተያያዘ የሚያቀርቡት ካለ እንሰማለን የጅማ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ምናምን ብለው ነው ያቆሙት
- የተከበረው ፍ/ቤት መልስ እንስጥ
- ክሱ ላይ የለም እኮ እያሉ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት ጽሁፎቹን በተመለከተ ወዲያው አሁንም ሌሎች ጥያቄዎች ስለምጠይቅ መልስ እንስጥ መቀጠላችን አይቀርም
- አሁን ስለተባለው የብሔር ጽሁፍ በብሔር ጽሁፍ ሌላ ነገር ጽፈዋል ምናምን የተባለውን በተመለከተ መስክሮ አልፏል ሌላ የጽሁፍ የሚነሳ ነገር ካለ ክርክር ሲነሳ ነው ያን

2980

5008

14

http://ethcriminalawnetwork.com/

የምንለው ይሄ አሬዲ ታልፏል ስለዚህ ጀማ ዩኒቨርስቲ ተማሪወች ብሎ ቆሟል እና ከዛ ተጥሎ ይቀጠል

- እሺ ያው የጀማው የእኛ ጭብጥ ስላልሆነ ምስክሩ ሊያስረዱ የሄዱበት ስለሆነ እሱን አንጠይቅም
- ስለዚህ እለፉዋ
- ምስክር አሁን ሲገልፁ አህመዲን ጀበል ቀደም ብሎ በዛሬው በብእር ስሙ እና ከዛ በኋላ በመጽሃፍ መልክ ባሳተመው ጽሁፉ አውቀዋለሁ ብለዋል አሁን ከጠቀሷቸው ደብቶች ሌላ ምንድን ነው የጽሁፉ አላማ ምን ለማድረግ ነው ?
- እንግዲህ እኛ አሁን ጽሁፉም ይቅር እየተባለ ነው በፍ/ቤቱ እየተነገረኝ ያለው መሰለኝ በጽሁፉ ጭብጥ ጽሁፉ ላይ ክስ ስለሌለ
- አላልንም መጀመሪያ ምስክሩ ስለ መጽሃፍ የብእር ስም የሚለውን መስክረዋል ያኔ ተቃውሞ አላነሳችሁም ነው
- አዎ አኪ
- ስለዚህ አሁንም የሚቀጥል ከሆነ ተቃውሟቸውን ሊያነሱ ይችላሉ እርስዎ ይቀጥሉ
- ጽሁፉ ላይ በአብዛኛው
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃዉሞ አለን
- እሺ /ግልጽ ያልሆነ/ ቀጥሉ
- ቅድምም ያልነው ይሄንኑ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- የቅድሙን ተውትና አሁን የምታነሱት
- እሺ በዚህ ጽሁፍ ደምበኞችን ክስ አልቀረበበትም በማስረጃነት ለፍ/ቤቱ አልተያያዘም እና አዲስ ኢሹ ነው እኛም እየሰማን ያለነው ክስ ላይ የሌለ ነው እና ይሄ ሊታለፍ ይገባል አቃቤ ሕግ ከክሱጋ ከጭብጡጋ ተያያዥነት ያለው ጥያቄ ይጠይቁና ይመስክሩ ነው እያልን ያለነው
- ጭብጥ ለይ የለውም ሊታለፍ ይገባል ነው እሺ አቃቤ ሕግ ምላሽ ስጡ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እንግዲህ ክሱ በግልጽ እንደሚያስረዳው ተከሳሾች እነዚህን ወንጀሎች ፈፀሙ የተባለው በተለያየ መንገድ ነው እሱን ቀደም ብለን መክፈቻ ንግግር ስናደርግ ያስመዘገብነው ጭብጥ ነው ከነዚህ መንገዶች አንዱ መንገድ እነዚህ ጽሁፎች የተለያዩ ቀስቃሽ ጽሁፎችን በመፃፍ በመበተን ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ ለዚህ ለአላማቸው ሊቀሰቅሱ ሊያስተባብሩበት ተጠቅመውበታል እና በማስረጃ ተራ ቁጥር ክሱ ውስጥም አለ

http://ethcriminalawnetwork.com/

አንዱ ይሄ ነው አንደኛው ጭብጣችን ይሄን ወንጀል ፈጽመውበታል ተብሎ የቀረበው በክሱ መሰረት እነዚህ ጽሁፎች በመፃፍ በማሳተም በማከፋፈል ተጠቅመዋል ነው በርካታ ጽሁፎች እነዚህ ጽሁፎች ደግሞ በማስረጃ በዝርዝራችን ላይ ተጠቅሶ ለተከሳሾች ኮፒ ተደርጐ አህመዲንን በተመለከተ ከማስረጃ ተራ ቁጥር 31 ጀምሮ በተከታታይ ያሉትን ፍ/ቤቱ መመልከት ይችላል እና ስለዚህ ከጭብጡጋ በቀጥታ የተገናኘም ነው በማስረጃም የተጠቀሱ ስለሆኑ ለዛ ነው ምስክሩንም እየጠየቅናቸው ያለነው

- የተነሳው መቃወሚያ ስለ መፃፉጋ በተያያዘ እና በብር ስም ተፃፈ ስለተባለው ነገር ነው በጠበቆች የቀረበው መቃወሚያ ይሄ መፃፉን በተመለከተ የክሱ አካል አደለም ክሱ ላይ አልተጠቀሰም በስረጃም እኛ ላይ አልደረሰም ባልቀረበው ጉዳይ በክስም ላይ በሌለው ነገር ምስክሩ ሊመሰክሩ አይገባም የሚል ተቃውሞ ቀርቧል በአቃቤ ሕግ በኩል ይሄ የክሱ አካል ነው በማስረጃ ዝርዝራችንም ላይ ጠቅሰናል የሚል ነገር አንስተዋል ፍ/ቤቱም ምስክሩ በዚህ ጭብጥ ላይ ሊመሰክሩ ይገበል አይገባም የሚለውን ያው አግባብነት ካለው ሕግጋ በማገናዘብ አይቶታል አንደኛው አንድ ምስክር ቀርቦ ሊመሰክር አይገባም የሚባለው አግባብነት ከሌለው ነው አንደኛው ተራ ቁጥር ለጉዳዩ አግባብነት ከሌለው ያው አይቀርብም ለጉዳዩ አግባብነት ካለውም ቢሆን እንደዚህ አይነት ጉዳይ ላይ ምስክር እንዳይቀርብ የሚከለክል ግልጽ ሕግ ካለ ምስክር ይከለከላል በማስረጃው አጠቃላይ መሪ ይሄንን ነው የሚያሳዩት አሁን ወደያዝነው ጉዳይ ስንመጣ በስም የተጠቀሱት ተከሳሽ በብእር ስማቸው የፃፉት ነገር አለ እንደዚሁ ሌላ መጽሃፍ ያሳተሙት አለ ብሎ ነው ምስክሩ የጀመረው ይሄ በዚህ ጽሁፍ በክስ ላይ የቀረበው ፍሬ ነገር ተፈጥሯል አልተፈጠረም የሚለውን ነገር ለማስረዳት ሊቀርብ ይችላል ከጉዳዩጋ አግባብነት ያለው ነገር ነው ይሄ ያስረዳል አያስረዳም ሚዛን ይደፋል አይደፋም ይሄ የበኋላ የፍ/ቤት ስራ ነው የሚሆነው በሌላ መልኩ ምስክሩ ዛሬ የቀረቡት ስለ ሰነዶች አጠቃላይ ይዘት ስለነባር ምስክር ሆነው /ግልጽ ያልሆነ/ ነባር ምስክር ሆነው ተጠቅሰው አደለም ዛሬ የቀረቡት ተከሳሾች ፈጽመዋል ያሉትን ለመግለጽ ነው ያ ከሆነ ደግሞ በሕጉ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ማስረጃው አንድ ምስክር በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪም የሚያውቀውን ፍሬ ነገር ለፍ/ቤቱ ማስረዳት ይችላል የሚከለክለው ሕግ የለም ስለዚህ አሁን የተያዘው ነገር በቀጥታም ይሁን ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ያወቁት ነገር ካለ ምስክሩ ሲያስረዱ የማስረዳት ብቃቱ በኋላ ከሚመዘን ውጪ ምስክር አግባብነት የለውም ወይም በሕግ ተከልክሏል የምንልበት የሕግ አግባብ የለም ከጭብጥ ውጭ ነው የሚል ነገርም የለም እዚህ ወንጀል ላይ ተጠቀሰው የሽብርተኝነት ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

በጽሁፍ የሽብርተኝነት ወንጀል ይፈፀማል አይፈፀምም ደረጃው እንዴት ነው የሚለው የፍ/ቤት ምዘና ጉዳይ ነው የሚሆነው አሁን ፍሬ ነገር በማስረጃ ዝርዝሩ የተለያዩ ነገሮች የተጠቀሱ አሉ የክሱ ፍሬ ነገር ውስጥ አለ ምናልባት ከክሱ ላይ ከተቀመጠው ጊዜ ውጭ ምስክሩ የሚመሰክሩ ከሆነ እሱ የክሱ አካል አይሆንም ከዛ ውጭ ያለው ነገር ግን ምስክሩ አግባብነት የለም የሚባልበት የሕግ መሰረት ስለሌለው ተገቢ ነው ይቀጥሉ ብለናል

- ምስክር ይቀጥሉ ካቆሙበት
- እሺ እንግዲህ ጽሁፎች እነዚህ ጽሁፎች በማስረጃ አሉ ብያለሁ /ግልጽ ያልሆነ/ ይቀርባል በተለይ ክሱ ከ2004 በኋላ ተፈፀመ እየተባለ ጽሁፉ አለ ጽሁፉን አምጣ ከተባልኩ አመጣለሁ ጽሁፉ አለ እዛ ጽሁፍ ላይ አሀባሽ የሚባሉት ሰወች ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆናቸውን እና እነዚህ ሰወች ላይ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት የሚል ነው
- ምን አይነት እርምጃ?
- ምናልባትም እነሱ ያውቁታል ወይ የሞት ነው ወይ የምንድን ነው በደንብ
- እርስዎ ይሄንን እንዴት ተረዱ ?
- አለ መጽሀፉ መጽሀፉን እኔ እንደአጋጣሚ ተማሪዎች ናቸው ይዘውልኝ የመጡት እና እዛ ላይ ፎቶ ግራፉን ሳይ የኚህ ግለሰብ አህመድ ኢብራሂምን ፎቶ ግራፍ ሳይ እራሴም ደነገጥኩ እና ሁኔታውን ስጠይቃቸው እሳቸውም ሌላ ጽሁፍ ላይ እንትን የብእር ስማቸውን የእሳቸው መሆኑን የገለፀበት ጽሁፍም እንደያዙ አስረድተውኛል እና አላስታውሰወም የብእር ስሙን እና መጽሃፉን ግን አምጣ ከተባልኩ
- የብእርስ ስሙን አያስታውሱም?
- አዎ
- እሺ ጥሩ ሌላ ተከሳሽ አህመዲን ከዚህ ውጪ ያደረገው ነገር የሚያውቁት አለ ?
- ከዚህ ውጭ እንግዲህ እኔ የማውቀው ነገር የለም ያው ያለው በተማሪዎቹ አካባቢ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነበረ
- እነማን ናቸው ተማሪዎቹ ?
- የዩንቨርስቲ ተማሪዎች አካባቢ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ነበረ
- ምንን በተመለከተ?
- ብዙ ነገሮች ናቸው በሰደቃ ጉዳይ በተለይ በዚህ በአወልያ ዙሪያ መጨረሻ ላይ ተወካይ ሆነው መመረጣቸውን አውቃለሁ
- የምን?

2963

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ተብለው
- ምን ያህል ሰወች?
- ብዙ ሰወች ናቸው ግን ከነሱ መሃል ስማቸውን ያየሁት አህመዲን ጀበል እና ሻህ መከተን ነው ሼህ መከተ አብረንም በስራ አብረን ስለበርን በተከታታይ ለረጅም ጊዜ በመልክም አሁን ቅድም እንዳሳየሁት ግልጽ አድርጌ የማውቀው እና አላማቸው የነበረ ነገር ነው በአላማቸው ገፍተውበታል ማለት ነው እኚህ ሰው ብዬ ዝም አልኩ
- ተመርጧል የተባለው ኮሚቴ አወልያ ላይ አሁን ተመረጠ ያሉኝ ኮሚቴ ከተመረጠ በኋላ ያረገውን ነገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያወቃሉ ?
- እንግዲህ ከዛ ወዲህ ተደረገ እየተባለ የምንሰማው ነው የአመቱ የአዛን የማውጣቱ ሁኔታ ያ ነገር እኔም ባለሁበት እሰግድበት በነበረ መስኪድ አካባቢ ባአንዱ የጁምአ ሰላት ላይ አዛን ተሰብስበው ማነው አዛን አልኩ ተክቢራ እያደረጉ በአንድ ጁምአ ላይ አይቻለሁ ከዛ ባለፈ ወደ መርካቶ አንዋር መስኪድ አካባቢ ላይ የሚደረገው ሰወች እዛው አካባቢ በሚሰግዱበት ወቅት
- የት መስኪድ ነው ተክቢራ ያሉት እርስዎ የነበሩበት ?
- ተክቢራ እኔ ያልኩ ጃፋር መስኪድ ነበርኩ
- የት ያለ ነው?
- ይሄ ጃፈር መስኪድ ማለት ቦሌ ልዩ ስሙ እሩዋንዳ ይባላል ሚካኤል ይባላላ
- እሺ ሌላውስ?
- እዛ አካባቢ ነው ያየሁት እኔ የነበርኩበት እሱም ጁምአ ሰግደን ልክ መንገድ እኔ ደጅ ነው የምሰግደው ወምበር ላይ ስለምሰግድ ብዙ ጊዜ ከመስኪዱ ወጣ ብሎ ሰውም ስለሚሞላ ደጅ ላይ ነው የምሰግደው እየወጣን እያለን ኢማሙ /ግልጽ ያልሆነ/ በኋላ የተክቢራ ድምጽ ሰማን ምንድን ነው ስንል እነሱ የቀሰቀሱት ቅስቀሳ እንደሆነ ሰማን ወዲያውም ልጆቹም ሰብስበን አነጋግረናል አንዳንዶቹን ሁኔታው ቆሟል በዛው ይሄን አውቃለሁ
- እኮ አሁን የጀመሩት
- አንዋር መስኪድ ላይ በቀደም ጁምአም በአጋጣሚ አንድ ሰው እዛ ሰግዶ በእንትን አሰምቶኛል በሞባይል ያለፈው ሳምንት ጁምአ
- አይ አሁን በጠቀሱት አመተምረት በ2004 እንጂ የ2004ቱ ላይ የነበረውን ቅስቀሳ የሰማሁት የለም

2964 S012

- ኦኬ ቅድም ሲመሰክሩ አስራሰባቱ ያቅርታ የተከበረው ፍ/ቤት ለመመዝገብ ይችላል እነዚህ ተመረጡ የተባሉት ሰወች ስም ዝርዝር ላይ የአህመዲን እና የሼህ መከተ ሙሄን ስም አይቻለሁ ከዛ የሼህ መከተን ስም ላይ ይሄ ሰውዬ በአላማው ቀጥሏል ማለት ነው ብዬ አስባለሁ ብለዋል ምንድንነው አላማው ?
- አላማቸው እንግዲህ እሳቸው ቀደም ብዬም ተናግሬያለሁ ከስልጣን እንዲነሱ ያደረጋቸው መጅሊስ ነው ሸሪአ ፍ/ቤት ስልጣን ዳኞች ጉባኤ ላይም ነሱ
- አላማቸው
- እና አላማቸው የመጅሊስን የማንሳት እና መጅሊስ ላይ ተቀምጦ አስፈላጊውን የዚህ ቅድም እኮ እነትኑን ተው ስለተባልኩ ነው የሃይማኖት /ግልጽ ያልሆነ/ ትርጉም ወሃቢያ የሚባለውን አስተምሮት ይበልጥ እንዲስፋፋ እና በመጅሊስ ላይ ሆኖ የበለጠ እሱ የበላይነት ይዞ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁለት እምነት ነው የነባሪውየሱፍየ አስተምሮት እና ይሄ የወሃብያው እስኩል ኦፍ ቶውት ነው ነባራዊው እስልምና የራሱ እንትን አለው ወሃብያው እስኩል ኦፍ ቶውት ደግሞ እየተከፋፈለ የሚመጣው ያስተምሮት እንትን አለ እና ያንን ትምህርት በስፋት እንዲረጭ እንግዲህ ድጋፍ የበኩላቸውን ድርሻ ለማድረግ ነው ትልቁን ጥረት ያደርጉ የነበሩት እሳቸው ፊትም ቃዲነትም ቦታ ላይ ተቀምጠው መስኪዶቹ በእነሱ እጅ እንዲወድቁ ነበረ ሲያደርጉ የነበሩት በኋላም ደግሞ ፌደራል መጅሊስ ላይ ከመጡ ደግሞ የበለጠ ይመቻችላቸዋል ይሄን አስተምሮት እንዲስፋፋ ያደርጋሉ ይሄንን ነው አላማ ይዘውበት እየገፉበት ነው እኚህ ሰው ብዬ ያልኩትም ይሄን ነው ለምን በ2000 ላይ በተከታታይ በድሪ ኢንተርናሽናል
- የተከበረው ፍ/ቤት ዋና ጥያቄ አበቃን
- መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ምስክር ቅድም ፍ/ቤቱ መጀመሪያ ሲጀምሩ ከመሰከሩባቸው ሰወች ጋር በተለይ ከሼህ መከተጋር ፀብ የለኝም ብለዋል ትክክል አደል?
- አዎ
- በሌላ በኩል ደግሞ እርስዎ ምክትል የመጅሊሱ ምክትል በነበሩበት ጊዜ መጅሊሱ እንዲወርድ እነሼህ መከተ ይንቀሳቀሱነበረ ብለዋል አደል?
- እዚህ ስለሚያጣብቀኝ ነው ቀጭን ስለሆንኩ ወምበሩ እዚህ
- እንቅስቃሴ አደገኛ ነው ብለው ለመንግስት አሳስበዋል አደል?
- አዎ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ስለ ዋህብያም አንስተው አላማቸው እንደዚህ ነው ብለው የጠቀሷቸው አንድ 3 ነጥቦች አሉ ይሄንን ከየት ነው ያገኙት ?
- የትኛውን እስቲ ሦስት ነጥቦች ?
- አንደኛው በክርስትያን መንግስት አንመራም ይላሉ የሚል ነገር አልተናገሩም?
- ምን ምን?
- ዋህብያዎች ሌላውን ሙስሊም እንደ ሙስሊም አይቆጥሩም ግብር አይከፈል ይላሉ በክርስትያን መንግስት አንመራም ይላሉ የሚል ቅድም የተናገሩ መሰለኝ ?
- በክርስትያን መንግስት አንመራም ሳይሆን ያልኩት ምናልባት ፍ/ቤቱም ሊያርመኝ ይችላል ለክርስትያን መንግስት ግብር መክፈል አይገባም ነው ያልኩት
- ይሄንን እርስዎ ከየት ነው ያወቁት?
- ይሄንን እንግዲህ አሁን ጥያቄውን አስተካክለውታል መጀመሪያ ጠያቂ
- ለክርስትያን መንግስት
- ግብር አንከፍልም መክፈል የለበትም
- ይሄን ከየት ሰሙ?
- ይሄንን እንግዲህ በእኔ በስልጣን ላይ በነበርኩበትም ወቅት በቻግኒ አካባቢ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ይካሄድ ነበረ ይሄንን እና እንዲሁም በተለያዩ ፋንፍሌቶች እየተበተኑ ለክርስትያን መንግስት ግብር መክፈል እንደማይገባ የሚያስተምሩ ጽሁፎች እየተረጩ ነበረ ይሄ ከን እንደሚረጭ እናውቃለን ነባራዊው እስልምና ከጀመረ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ግብር እየከፈለ ነው ያለው ስለዚህ ከተቃራኒው አካል መሆኑ ግልጽ መሆኑን ያስረዳል ነው
- ስለዚህ የእርስዎ ግምት ነው ይሄ
- አቤት?
- እርስዎ ይሄንን ወረቀት ይበተናል እናውቃለን ከማለት ውጪ በተጨባጭ የያዙት ወረቀት አለ ወይ ወይም ደግሞ በቻግኒ አካባቢ ከማለት ውጪ በተጨባጭ እዚህ ቦታ በእከሌ ብለው ሊገልፁ ይችላሉ ወይስ የቀረበሎትን እሪፖርት ነው የሚነግሩን?
- እዚህ ላይ ጽሁፎችም ተብሏልም የሚለው እሪፖርት የሚቀርበው ቢሮ ነው በግለሰብ ደረጃ ለኔ አምጥቶ የሚሰጠኝ ሰው አይኖርም ቢኖርም ወደ መዝገብ ቤት ነው የምልከው
- ስለዚህ እርስዎ ቢሮ ሆነው ያወቁትን ነገር ነው አሁን ስለ ቻግኒ የሚነግሩን አደል?
- አዎ
- እንጂ ቻግኒ ቦታው ላይ አልተገኙም?

2966 SD14

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልነበርኩም አልሄድኩም
- ያ ወረቀት ወሃብያ ይሁን ወይም ሌላ ይሁን በምን አወቁ?
- እንግዲህ እንደኛ እኛ እንደ ሰፍያው አሁን ወደ እንትት ልገባ ነው በቃ አያስፈልግም ስላሉኝ እዚህ ላይ ልመልስልህ አልችልም አባዬ
- እይ እንዴት አወቁ የተባለውን ብቻ?
- እንዴት አወቅኩት የግድ እስከ አሁን ድረስ ያለው ነባራዊው እስልምና ግብርን ሲከለክልም አልተማርኩም እኔም በትምህርቱም ላይ ለክርስትያን መንግስትም አትገብሩ የሚለውንም ሲያስተምሩ አልኖሩም እንደውም የቁርአኑን ጥቅሶች እየጠቀሱ የሚያስተምሩን የነበረው ቀን ሰጥቶት ስልጣን ላይ የተቀመጠን መንግስት የሚያዘውን ትእዛዝ እና የሚያወጣውን መመሪያ ተከትሎ መሄድ እንዳለብን ነው እኔም ስማር የኖርኩት
- ስለዚህ ነባሩ ይሄን ስለሚል ከዚህ አሁን ግብር አትክፈሉ የሚል ነገር ከመጣ ይሄ ወሃብያ መሆን አለበት የሚል ግምት ነው የሚያስቀምጡት ?
- ታዲያ ከሌላ ከየት ይመጣል የኔ ወንድም
- ቅድም እነሼህ መከተ መጅሊስ ይውረት የሚል ሰወችን በወቅቱ ያስፈርሙ ነበረ ብለዋል ይሄን መቼ ነበረ ያስፈርሙ የነበረው?
- ማስፈረሚያ ሰወችን ያስፈርሙ ነበረ
- እነሼህ መከተ መጅሊሱ ይውረድ እርስዎ በስልጣን ላይ ባሉበት ጊዜ ሙስሊሙን አንድ አርገን መጅሊስ በሕገመንግስት የተቀመጠውም የተጓደለውን ነገር እናሟላለን ብለው ይንቀሳቀሱ ነበረ ሰወችንም አፈራርመው ነበር እኮ ብለውን ነበር ቅድም ?
- በ2000 ጀምሮ እኮ ይኸው ግልጽ የተቀመጠ ነው እኮ በበድሪ ኢንተርናሽናል አመራር አማካኝነት ስብሰባዎች ተደጋግመው ተደርገዋል ተጠርተዋል እነዚህ ስብሰባዎች መጅሊሱን እቢሮው ውስጥ ባለ ምናልባት የሕዝብ ግንኙነቱ ሊሰጥ ይችላል ቢጠየቅ አሁን ዋና ፀሐፊ የነበሩት የሆኑት ሰው የመጅሊሱ በዛም ወቅት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ስለነበሩ ይበልጥ እሳቸውም በደምብ ያውቁታል የነበሩበት የነበረ እንቅስቃሴ ነው ቢጠየቁም ደግሞ መልስ ይሰጡበታል
- እሺ ስለዚህ አሁን እዚህ ለፍ/ቤቱ የሚያስረዱት ወረቀቱ ተፈረመ የሚሉት ወረቀት 2000 ላይ የተፈረመ ነው ?
- አዎ ወረቀቶች በተከታታይ በ2000 ከ2000 በኋላ የተፈረሙ ወረቀቶች አሉ ለምሳሌ ልጠቅስልህ እችላለሁ ከፈለግክ የአንድነት ስራን እንሰራለን ብለው የጀመሩት በ2000

2967

SDIS

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መጨረሻ አካባቢ እና አንድላይ ትልቅ እንቅስቃሴ ነበረ ለዚህም በማዘጋጃ ቤት ስብሰባዎች አድርገው ከእኛም መሃል የተወሰኑ የኃይማኖት አባቶች ተሳስተው ፈርመዋል ብያለሁ እነዚህ ሁሉ ወረቀቶች እንግዲህ አለበት ቦታ ላይ አሉ ግለሰቦችንም ደግሞ በማስረጃነት መጥራት እችላለሁ እኔ

- እርስዎ አሁን ይሄንን ስራ እደ ሼህ መከተ ቅድም ያሉት በማዘጋጃቤት ከናንተም ሰወች ወይም ደግሞ ከሃይማኖት አባቶች የተወሰኑትን አሳስተው ብለዋል ይሄንን እነሼህ መከተ ይሁን ሌላ በምን ምን ተጨባጭ አሁን እዚጋ ለፍ/ቤት በምን ሊያረጋግጡ ይችላሉ?
- የቪዲዮ ማስረጃ አለ እኮ አባዬ የቪዲዮ ማስረጃው በስብሰባው ላይ አንድም ስብሰባ ላይ የበድሪ ኢንተርናሽናል ስብሰባ ላይ ሼህ መከተ ቀርተው አያውቁም
- አዘጋጆ የሚሉት የበድር ኢንተርናሽናል ነው ሼህ መከተ ናቸው ?
- እንግዲህ ይዘጋጅ የነበረው በሚሊኒየም ሰበብ በድሪ ኢንተርናሽናል በየቦታው እያሰበሰበ የነበረ ድርጅት ነው ይሄ ድርጅት በኋላ እንዴት ምን እንደተደረገ
- ብዙ ነገሮች ውስጥ እየገቡ ነው እና እሱ አደለም አሁን ከተከሳሾች ከጠቀሱት ተከሳሽ ጋር የሚያያዝ ነገር ብቻ ነው /ግልጽ ያልሆነ/
- እሳቸው የሌሉበት ስብሰባ የለም በየጊዜው በድሪ ኢንተርናሽናል በሚያደርገው ስብሰባ ላይ ይገኙ ነበር
- ማን?
- ሼህ መከተ
- እሺ ሌላ ጥያቄ
- ቅድም አህመዲን ጀበል ፃፈው መጽሃፍ ያሉት ነገር አለ በብእር ስምም እንደተጠቀመ እና በኋላ ያ ብእር ስም የኔ ነው ብሎ እንደገለፀ ገልፀዋል አህመዲን ጀበል የሚለውን ስም ከማውቀው ከማወቆ በስተቀር የትኛው አህመዲን ጀበል እንደሆነ አያውቁም አደል እርስዎ የሚያውቁት አህመዲን ጀበል በሚል የተፃፈ መጽሃፍ ነው ?
- አዎ እንግዲህ ይሄንን ጽሁፍ የኔ ነው ብለው እሳቸው ያወጡበት መጽሃፍ አለ ብለውኛል ያንን ማስረጃ አምጣ ከተባልኩ አህመዲን ጀበል የሚለውን ነው የማውቀው
- ይኸውሉት ምስክር አሁን እርስዎ መጽሃፉን እኛ ስንፈልገው ትእዛዝ እንሰጣለን ከፈለግነው አሁን እርስዎ ስለሚያውቁት ነው አህመዲን ጀበል የሚለውን እንዴት አወቁት እሱ መሆኑን ነው ?
- ስሙን ነዋ

2988 SDT6

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ መጽሃፉ ላይ ያነበቡት መጽሃፍ ላይ ደራሲው አህመዲን ጀበል ስለሚል ነው አህመዲን ጀበል አሁን የተከሰሰው ይሁን ወይም ሌላ ሞክሼ ይሁን የሚያውቁት ነገር የለም ?
- የለም ስለሱ
- የመጽሃፉ እርእስ ምን ነበረ የሚለው?
- የመጽሃፉን እርእስ አሁን አላስታውሰውም ብያለሁ አምጣው ከተባልኩ ግን አመጣዋለሁ እኔ ብዙ መጽሃፍቶች ስለማይ ላስታውሰው አልችልም
- መቼ እንደተፃፈም አያውቁም?
- ወቅቱንም አላስታውሰውም ግን መጽሃፉ አለ ግድ የለህም
- የገፁን ብዛት ያውቃሉ ?
- አላውቀውም እንግዲህ ይሄንን ሁሉ ዝርዝር እንዴት አድርጌ እነግርሃለው
- ቅድም በጃፈር መስኪድ ተሰባስበው አላህዋክበር አሉ ይሄንን ያሉ ሰወች በቁጥር ብዙ ናቸው ትንሽ ?
- እንግዲህ መ ንገድ ካስፈለገ በጣም ጥቂቶች ናቸው ከሰገደው ሕዝብ አኳያ ሲታይ ብዙ ሕዝብ አለ የተወሰነ ግሩፕ ነው
- እሺ እነዚህ ሰወች የተሰበሰቡትን ሰወች በአካል አያውቋቸውም?
- አናውቃቸውም
- አላህዋክበር ማለት ምን ማለት ነው?
- አላህ ትልቅ ነው ማለት ነው
- አቶ እሬድዋን ቅድም ሲያስረዱ ሼህ መከተም እኔም በተሰበሰብንበት የመንግስት ባለስልጣናት ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሌሎቹም ባሉበት እያሉ ነበረ እና ይሄ ስብሰባ የት ነበረ የተደረገው?
- ይሄ ስብሰባ ሳይሆን እኛ እራሳችን ያዘጋጀነው በተለይ የሚሊኒየም አዘጋጅ ኮሚቴው በኮልፍ ክለብ ላይ ያዘጋጀው አንድ ስብሰባ ነበረ የሽልማት አሰጣጥ በተለይ ሚሊኒየም
- አጭር ያድርጉልን
- እኮ እየዘረዘርኩልህ ነው የኔ ወንድም
- እኮ አሁን
- ገልፍ ክለብ ነው እንግዲያውስ

1969 5016

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. የተከበረው ፍ/ቤት በዚህ አይነት እንቸገራለን ቢያስረዳልን ምስክሩን አጭር አጭር መልስ እንዲሰጠን ማለት ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ መቃወሚያ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ማለት አሁን ክርክሩን ላለመቆራረጥ ነው እንደጠበቆቹ መሃል መሃል ላይ እየገባን መቃወሚያ ማለት አትቶን አደለም ግን እንዳይቆራረጥ እና ፍሰቱን እንዲጠብቅ ነው የመጣው ምስክሩን ሃራስ ማረግ በተለያየ መንገድ አግባብ አደለም ምለው እየመሰከሩ ያሉ ምስክር ናቸው እስከማሉ ድረስ ጠበቆቹ ክብር ሊሰጡ ይገባል ለምስክሮች እና ሃራስ እያረጓቸው ነው ምስክሩን መበሳጨትም ምንም ማለትም ያለባቸው አይመስለኝም ፍትህን ለማገዝ ነው የመጡት ያው
- እ?
- ምስክሩ ሃራስ እየተደረጉ ነው ያሉት
- እሺ. ሌላ አለ ሌላ መቃወሚያ
- ሌላ የለም መስቀለኛም ስለሆነ መርተው መጠየቅ ይችላሉ የተከበሩ ጠበቃ እና /ግልጽ ያልሆነ/
- አሁን ሃራስ ያደረጉበትንም አግባብ አላየንም እኛ ምንድን ነው ምስክሩ ቅድም አስረድተዋል ባህሪዬ ነው ብለዋል እናንተም ይሄን ወጣ ብለው ሲናገሩ ባህሪያቸውን መረዳት ያስፈልጋል የሰውን ባህሪ እኛ የምንወስደው ከባህሪያቸው ተነስተን የሚሰጡትን ፍሬ ፍሬ ቃልነው ስለዚህ ምስክሩ ቦታ ነው የተጠየቁት ሲሄዱ ፍ/ቤቱ አስቆማቸው እና ቦታውን ብቻ መለሱ ስለዚህ እናንተም ቢሆን የተቸገራችሁበት ነገር ያለ አይመስለኝም
- ያው በቀጣይም እንደዚህ አጨር እንዲሆንልን
- በቃ እየተነጋገርን እኮ ነው እየተነጋገርን እና ችሎቱን እየመራን ነው ያለነው ስለዚህ ምስክሩ ምንድን ነው ባህሪያቸው በመሆኑ ምክንያት ጥያቄያችሁን ነጥላችሁ ማቅረብ ነው አንድ መልስ እንዲመልሱ እርስዎም ለተጠየቀው ጥያቄ ብቻ ለምሳሌ የት ቦታ ተሰበሰባችሁ ከተባለ መርካቶ ከተባለ መርካቶ እንዲህ አይነት መልስ ብቻ ስጡ እናንተም ለይታችሁ ጠይቁ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት እዚህ ስብሰባ ላይ ተገኝተው የነበሩ የመንግስት ባለስልጣናት እነማን ነበሩ?
- መቃወሚያ አለን
- ጥያቄው ምንድን ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስብሰባ ቅድም የተከበረው ፍ/ቤት ሲያስረዱ የሽልማት አሰጣጥ የመንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት ስጋት ያልኩትን ነገር ተናግሬያለሁ እያሉ አስረድተዋል እና ማን ተገኘ ምንድን ነው የእርስዎ ስጋት የነበረው ወደሚል ጥያቄ ልንሄድ ነው እና ምን እንደሚቃወሙ እኔም አልገባኝም
- ቀጥሉ እስቲ
- በስብሰባው ላይ ስለተገኘ የመንግስት ባለስልጣን አግባብነትም የለውም ሲጀምር ሲቀጥል ደግሞ እኛ በዋና ጥያቄ አንድን ስብሰባ ነጥለን የጠየቅነው ነገር የለም ምስክሩም በዛ መልኩ አልነበረም ለማስረዳት የሞከሩት እና አግባብነትም የለውም በዋና ጥያቄም ያልተነሳ ነው የባለስልጣኖቹ ስም ዝርዝር ማለት ነው
- ምላሽ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እንግዲህ በጣም በዝርዝረ አስረድተዋል ምስክሩ ስጋት ነው ያሉት ነገር እና ይሄ ስጋት ምንድን ነው ስጋት ያደረገው ነገር ለየትኛው የመንግስት ኃላፊስ ደረሰ ይሄ ስጋት ከዛ በኋላ ይኸው አሁን ፈነዳም እያሉ ያ ስብስብ ፈነዳም እያሉ እያስረዱ ነው ወደዛ ነው ልንሄድ ያለነው እና ከተናገሩት ነገር ተጠይቀው ከመለሱት ነገር እንጂ እኛ በራሳችን ያመጣነው ነገር አይደለም ሊጠየቅ ይገባል
- /የማይሰማ/ ሰጥተናል ስብሰባ ተካሂዶ ነበር ብሎ ነበረ ምስክሩ ከዛጋ በተያያዘ በመስቀለኛ ያቀረበው በስብሰባ ላይ የተገኙት እነማን ናቸው የመንግስ ትኃላፊዎች እነማን ናቸው የሚል ቀርቧል በአቃቤ ሕግ በኩል ይሄ በዋና ጥያቄም አልተነሳም የክሱ አካል አደለም ሊጠየቅ አይገባም የሚል ነገር ቀርቧል ፍ/ቤቱም ጥያቄው ተገቢ ነው አደለም የሚለውን አይቶታል ተገቢ ነው አደለም ለሚለው ምላሽ ለመስጠት ይሄ ነገር በዋና ጥያቄ ተነስቷል አልተነሳም ነው በዋና ጥያቄ ከተነሳ በመስቀለኛ ላይ መነሳት ስለሚችል ማለት ነው በዋና ጥያቄው ላይ ምስክሩ ስብሰባ ተደርጐ ነበር በእኛ ጥያቄ እኛም ስጋታችንን እዛ ላይ ገልፀናል ብሎ የመንግስት ኃላፊዎችንም ባለስልጣናትንም ስም ጠቅሷል ከእሱ የተለየ ስላልሆነ አግባብነት የለውም የሚባልበት የሕግ መሰረት ስለሌለው ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥል ተብሏል
- አሁን /ግልጽ ያልሆነ/ እንዳሉ በዝርዝር ነገረን ነው እኔ የማስታውሰው እንግዲህ የክብር እንግዳችን ፕሬዝዳንት ግርማ ናቸው በዛ ወቅት ላይ
- እሺ ሌሎች

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌሎች ባለስልጣኖች እንግዲህ የአዲስ አበባ ባለአደራ ተብለው ያኔ በዚህ በተፈጠረው ሁከት ምክንያት ከንቲባ አልነበረንም በመሃል ለባለ አደራ ከንቲባዎች እና ሸሪፍ ኪሪ ነበሩ
- የመንግስ ኃላፊ ናቸው ?
- አዎ ያው የባለአደራ ኮሚቴ ማለት ነው የአዲስ አበባ ከንቲባዎች ማለት ነው
- እሺ አጀንዳው ምን ነበረ የስብሰባው አጀንዳ ?
- መቼ ነው ጊዜው ?
- 2000 ላይ ነው
- የስብሰባው አጀንዳ ምን ነበረ ?
- ቅድም በዝርዝር አስቀምጨው ነበረ ጀምሬው ነው የተቋረጠው የሽልማት አሰጣጥ በሚሊኒየም ላይ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰወች አሸልማት አሰጣጥ ስርዓት ላይ ነው ብያለሁ
- እሺ ቅድም ስጋቴን ገለጽኩ ያሉት በዚህ ስብሰባ ላይ ነው ?
- አዎ
- በዚህ ስብሰባ ላይ ከተሸለሙት ውስጥ አህመዲን ጀበል ነበር አደል?
- አላየሁትም እኔ እሱን
- እርስዎ ሰርተፍኬት ሲያቀብሉት አልነበረም?
- አላስታውስም
- እሺ ሼህ መከተ ሙሄ የሸሪአ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት እንደነበሩ ሲያስረዱ ነበረ አደለ?
- አዎ
- የሸሪያ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ተደርገው በመጅሊስ ጠቋሚነት ነው አደል?
- ከኔ በፊት የነበሩ መጅሊስ ጠቋሚነት ነው
- እሺ መጅሊሱ ከኡለማ ምክር ቤት ጋር ተመካክሮ እያሉ ሲናገሩ ነበረ የኡለማ ምክር ቤትን የሚሾመው መጅሊስ ነው አደል ?
- እሱ ላይ እኔ መልስ ልሰጥ አልችልም
- አሁንም ከክሱጋር የተያያዘውን
- እርስዎ እነዚህን አሁን ለምስክርነት የመጡባቸውን መረጃዎች ያገኙት የመጅሊስ ኀላፊ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት ነው አደል?
- የትኛውን እስቲ በዝርዝር ብታቀርቡልኝ
- አሁን አብዛኞቹ የተናገሯቸው የመጅሊስ ባለስልጣን ሆነው እርስዎ በነበሩበት ወቅት ያገኙት መረጃ ነው አደል?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አብዛኛውን አዎ
- በሕዝብ ተቃውሞ ነበር አደል የተነሱት ከመጅሊስ?
- ይሄንን ልመልስልህ አልችልም
- ቅድም ሲያስረዱ የክርስትያን መንግስት ግብር አትክፈሉ ይባል ነበረ ብለዋል ከነዚህ ሁለት ተከሳሾች አሁን ሊመሰክሩባቸው ከመጡ ሁለት ተከሳሾች በዚህ ቦታ በዚህ ጊዜ ይሄን ሲናገር ነበር ብለው ሊያስረዱን አይችሉም አደል አልሰሙም ይሄንን
- ተጠይቋል ቅድም እሳቸው ጠይቀው ምላሽ ተሰጥቷል
- ከመጠየቁ በተጨማሪ መስቀለኛ ጥያቄ ፐርፐዙ በዋና ጥያቄ ምስክሩ የመሰከሩትን ነገር እውት ውስጥ ማስገባት ነው ሌላ ነገር የለውም ምስክሩ በዚህ ነገር ሁለቱ በስም የጠቀሱት ተከሳሾች ይሄን አታርጉ ብለው ሲቀሰቅሱ አይቻለሁ ሰምቻለሁ አላሉም ስለዚህ ምንም አይገናኝም ይሄ ጥያቄ ከዋናው በተነሳው ማለት ነው
- እሺ ቅድም ስማቸው ተዘርዝሮ አየሁ ከሌሎች ሰወች ጋር ያሉት የሁለቱ አሁን የሚመሰክሩባቸው ሰወች ስም አይተዋል ?
- በኮሚቴነት መመረጣቸውን ነው ?
- እርስዎ ያዩት አለ አዎ መመረጣቸውን ?
- በኮሚቴነት መመረጣቸውን አይቻለሁ አዎ
- ይሄንን ብቻ ነው ያዩት እንጂ ሌላ ነገር አላዩም?
- ሌላ የቪዲዮ ፊልም
- ቆይ ቆይ ሌላ ነገር ማለት?
- ከፊርማጋር በተያያዘ ወይም የስም ዝርዝጋ በተያያዘ እርስዎ የመሰከሩት እና ያዩት ይሄንን ብቻ ነው አደል ይሄንን እንያዝ ?
- እኔ እንግዲህ ስም ዝርዝራቸውን ያው አይቻለሁ ብያለሁ ስም ዝርዝራቸውን ብቻነው ያየሁት
- እኮ አሁን ያዩት በኮሚቴነት ስለመመረጣቸው ነው አደል?
- አዎ
- እሺ መቼ ተመረጡ ይላል እንትኑ ያዩት ነገር ?
- በኮሚቴነት የተመረጡት በ2004 ነው ክፍሉን አላስታውሰውም በየጋዜጣውም ወጥቷል እኮ
- በ2004 በኮሚቴነት ተመረጡ ይላል ምን ለመስራት ነው በኮሚቴነት የተመረጡት?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ይሄንን ዝርዝር እኔ ላውቀው አልችልም ይሄንን ዝርዝር የሚያውቀው እዛው ጋዜጣው ላይ የተፃፈ የሙስሊም ተወካዮች ናቸው ተብሎ ነው የተነገረው በአወልያ ት/ቤት ተሰብስበው መመረጣቸው እንደውም ሲዲውም አብሮ አንድላይ በየእንትኑ ተበትኖ አይቻለሁ
- ሕዝብ ነው አደል የመረጣቸው ?
- የአንድ መስኪድ ሕዝብ ?
- አዎ የአንድ መስኪድ ሕዝብ ነው አደለ የመረጣቸው ?
- የአንድ መስኪድ ነው የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ወይም መላው አዲስ አበባ አደለም የአንድ መስኪድ ነው አወልያ መስኪድ ብቻ
- ቅድም ሲያስረዱ እኛ አንድነት አንፈልግም የአዲስ አበባ መጅሊስ የመጅሊስ አካል ነው አደለ የፌደራል መጅሊሱ አካል ነው አደለም?
- ይቅርታ እዚህ ላይ አንድ ነገር እየተሳሳቱ ነው ያሉት ጠያቂው ክቡር ፍ/ቤት እኛ አንድነት አንፈልግም ብዬ አልተናገርኩም እኔ
- እሱን እኮ ጀመርኩት እና ትቼዋለሁ ጥያቄዬን አሁን ስምተውኝ ከሆነ የአዲስ አበባ መጅሊስ የፌደራል መጅሊስ አካል ነው አደለም የአዲስ አበባ መጅሊስ ማንን ነው የሚወክለው?
- አዲስ አበባን ነዋ
- የአዲስ አበባ ሙስሊም ማለቶ ነው?
- ይቆዩ እስቲ አሁን ቴክኒካል ፓርት ውስጥ እየገቡ ነው ይሄ ከተፈለገ ዝርዝሩ ተጽፎ ስላለ ችግር የለውም ወደ አሁን ወደ እንትን ብቻ ተመለሱና እምትጠይቁትን
- እሺ የአዲስ አበባ መጅሊ አፈንግጦ ከነሱጋ ሆኖ እያሉ ነበረ ቅድም ሲያስረዱ የነበረው አፈንግጦ ምን አደረገ?
- አሁንም እዚህ ላይ ጥያቄው ቢስተካከል ከእኛ መመሪያ ውጪ ወጥቶ ለምን በእኛ መተዳደሪያ ደምብ ውስጥ የተቀመጠ ሕግ አለ የፌደራሉ
- ማን ነው ከእናንተ መመሪያ ያወጣው ?
- የአዲስ አበባ መጅሊስ
- እሺ ጥሩ በዚህ ምክንያት የፌደራል መጅሊስ እና የአዲስ አበባ መጅሊስ አለመግባባት ነበራቸው አደለ?
- በዚህ ምክንያት የተወሰኑ አመራሮቹ ናቸው እንጂ መጅሊስ ሲባል እዚህ ላይ እንዲለይልኝ እፈልጋለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ እርስዎ የፌደራል መጅሊስ ስራ አስፈፃሚ እና የአዲስ አበባ መጅሊስ ስራ አስፈፃሚ በተገኙበት የሁለቱን መጅሊሶች አለመግባባት ለመፍታት በሽማግሌዎች
- የሁለቱ እንትናዎች አለመግባባት የእኛ ኢሹአደለም ይቀጥሉ
- እኮ በዛ ላይ የማሳየው ነገር አለኝ
- የምታሳየውን ብቻ ነው
- ከደምበኛዬጋ የተያያዘ የማሳየው ነገር አለኝ
- መርተው ይጠይቁ የተከበረው ፍ/ቤት መስቀለኛ አደለም እንዴ
- ቆይ አንዴ እንደማመጥ እና አሁን የሁለቱ መጅሊስ አለመግባባት የክሱ አካል ስላልሆነ የክሱ አካል የሆነውን የምትጠይቀውን ብቻ መርተህ ጠይቅ ይሄንን ይለፈው
- አህመዲን ጀበል መጅሊሶች በነበራቸው አለመግባባት ከሽማግሌዎች ጋር አብሮ መጥቶ ሲያደራድር ነበር አደለ?
- እኔ ይሄንን አላውቅም ብዬሃለው እኮ የኔ ጌታ ይሄ የኔ
- እኮ አላወቅም ካሉ እዛው
- እሺ መጅሊስ /ግልጽ ያልሆነ/
- እሺ በዶ/ር አብዱል ጀሊል ስብሰባ ይመሩ ነበር ብለዋል በተለያየ ጊዜ ማን ናቸው ዶ/ር አብዱል ጀሊል ?
- ዶ/ር አብዱል ጀሊል ማለት በሳውዲ አረቢያ የሚገኙ የዋህብያው አካል ተወካይ ናቸው እንደውም
- ኢትዮጵያዊ ናቸው ?
- እንደውም በቅርቡ
- አዎ
- እሺ በድሪ ኢንተርናሽናል በመንግስት ታውቆ ነበር አደለም ወደ አገር ውስጥ ገብቶ ይሰራ የነበረው ?
- ጥያቄው ይደገምልኛ በደንብ እንትን አላልኩም
- በድሪ ኢንተርናሽናል የሚባል ድርጅት ቅድም ሲገልፁት የነበረው ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ይሰራ የነበረው በመንግስት እውቅና ነው አደለም ?
- ይሄን እኔ አላውቅም እኔ የመንግስት አካል አደለሁም
- መንግስት ጋብዞት የመጣ መሆኑንም አያውቁም?
- አሁንም ጥያቄው ከኔጋራ የሚገናኝ አደለም

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያውቃሉ አያውቁም ነው የሚያውቁት ከሆነ?
- የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆይ እስቲ
- በንግስት ተጋብዞ የመጣ ድርጅት መሆኑን ወደ ኢትዮጵያ ያውቃሉ አደለም ወይ ነው?
- ይሄ የሱ ስራ አደለም ይለፋት ተብሎ ደገሙት እኮ እርስዎ ይሄን ማወቅ ካስፈለገ ወይቆ ማትረብ ይቻላል ካስፈለገ ማለት ነው ይሄ የስዊሹ አደለም
- እሳቸው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚያውቁትን ነገር ስለሆነ የሚመሰክሩት ያውቃሉ አያውቁም ነው አላውቅም
- ወደ ሌላ እሳቸው መልሰው ሊሆን ይችላል ግን ይለፉ የተባለውን መልሰው እየጠየቁ ስለሆነ እሱን እየተጠነቀቁ እለፉ ማለት ብዬን ነው
- እሺ ቅድም ሲመሰክሩ ወሃብያዎች እያሉ ሲገልፁ ነበር ወሃቢዝም ያሉትን ቅድም እስኩል ኦፍ ቶውት ያሉትን ነገር የሚከተሉትን ሰወች ነው ወሃብያ ያሏቸው ?
- አልገባኝም ጥያቄው ኃይማኖታዊ ጥያቄ
- ወሃብያ ያሏቸው እና ማንን ነው ቅድም ወሃብያዎች ናቸው ሲሉ
- ቅድም ፍ/ቤቱ እንደዚህ አይነቶቹን ትንተናዎች በምናውቀው በአማርኛ እንትን አስረዳን እያሉ ነው
- አሁን የሚያደርጉት ምንድን ነው እኛ ወደ ዝርዝሩ ኃይማኖታዊ የሆነ ትንታኔ እንዳይገቡ ነው ምክንያቱም እሱን እኛም አናውቀውም ጥልቀትም ያለው ስለሆነ ከባድ ስለሆነ አሁን ግን ምንድን ነው ይሄ ቀላል ነገር ነው ወሃብያ የተባሉት እነማንን ነው ያላችሁት ነው ጥያቄው ይሄ ብቻ ነው
- ወሃብይ የማባሉት አካላቶች እራሳቸውን ለይተው ያስቀመጡ እና በተለይም በመውሊድ በሰደቃ
- አይ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ ነው
- አሉ
- እኮ እነማን ናቸው የሚያውቋቸው ከሆነ በአካል በስም እነማን ናቸው?
- በብዛት ይኸው ትምህርት የሚሰጡት እስከነ መስኪዳቸውም ዝርዝር መስጠት እንችላለን ይሄ ትምህርት የሚሰጥበት መስኪድ
- እኮ አሁን የሚያውቁት ከሆነ እና የሚያስታውሱ ከሆነ ብቻ
- ምን ልበል አሁን ሼህ መከተ ለምሳሌ የዛ ተማሪ ናቸው

2976

SD23

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንድ እሺ ሌላ?
- አህመዲን ጀበል አሽኬንደድ ሙስሊም ነኝ ይላሉ እንጂ የዛ አንድ ብራንች ተገንጣይ ናቸው ሌሎቹን አላውቅም እኔ በሌሎቹ ላይ መመስከርም አልችልም አላውቅምም
- እንዚህ አሁን ያሏቸው ሰወች እራሳቸውን ወሃብያ ብለው ጠርተው አያውቁም አደል ?
- እንግዲህ ይሄ ስም ማንም በሚጠራበት በሚሰጠው ስም ነኝ ብሎ ሳይሆን በሚያስተምሩ አስተምሮት ነው የሚፈረጀው አባዩ
- ስለዚህ በሚያስተምሩት አስተምሮት ነው ወሃብያ ናቸው ያሉት እርስዎ?
- አዎ
- እሺ
- ሼህ መከተ ወይንም አህመዲን ጀበል ሰበከት ሲያደርጉ ሰምተው ያውቃሉ እርስዎ ሲያስተምሩ ?
- ሁለቱም ሲያስተምሩ ሰምቻቸው አላውቅም
- ቅድም ፕሬዝደንት ግርማ ባሉበት በኢትዮጵያ ውስጥ የእስልምና መንግስትን ለማቋቋም እንቅስቃሴ እየተደረገ ያለ ስለመሆኑ ያሎትን ስጋት ገልጫለሁ ብለዋል በዚህ ስጋቶ ላይ እርስዎ ስጋት ያሉት ነገር ላይ እርስዎ ይመሩት በነበረው መጅሊስ ውስጥ የተለያየ አቋም ነበር አደል ቅድም ገልፀውታል ?
- ይሄ የመጅሊስ ጉዳይ ነው እንግዲህ ልመልስ እምገደድ ከሆነ ፍ/ቤቱ ካዘዘኝ እመልሳለሁ
- በዚህ መካከል ከእናንተ መካከል በዚህ ምክንያት በአቋም የተከፈለ አለ የለም ?
- የለም
- በቃ ሌላ ጥያቄ
- ቅድም ሲመሰክሩ ይሄን ሃሳብ በመደገፋቸው ከመጅሊሱ እንዲሰናበቱ የተደረጉ አባላት አሉ ብለው ነበር አደል በዚህ ምክንያት ይሄን ሃሳብ ትደግፋላችሁ ተብሎ ከመጅሊስ የተሰናበቱ አባላት የሉ
- ቆይ ማን ተሰናበተ የሚል አያስፈልግም ተነስ እሱጋ ቢሞን የሚያሹት እርስዎስ ቢሞን የሚያሹት አዎ ምን ሆነው ነው እንዴ ያለው ማን /ግልጽ ያልሆነ/ በጉልበት የሚሰራ ስራ እኮ አደለም ስለዚህ ሁለተኛ እንደዚህ አይነት ቃል አይፈለግም ከናንተ በጉልበት የሚሰራ ስራ ቢሆን ሁሉም ተሰብስቦ አይቀመጥም እዚህ ስለዚህ ቁጭ በል ተገበ አደለም
- ምናልባት ይሄ ጥያቄ ምክንያቱንም አላስረዳሁም ውድቅ ሲደረግ ጥያቄዬን ሳስረዳና ፍ/ቤቱ ካልተቀበለው ልታለፍ

2977

5024

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከስራ የተሰናበተ አለ ወይ ነው አደል ጥያቄው?
- መስክረዋል እኮ እሳቸው ስለመሰከሩ ይሄንን ቅድም
- እ?
- ቅድም መስክረዋል ይሄን ጉዳይ ከመጅሊሱ አባላት ውስጥ የተሰናበቱ የመጅሊሱ አባላት አሉ በስም መጥቀስ እችላለሁ ብለው ሳይጠቅሱ ነው ያለፉት እኔ እነዛን ዝርዝሮች እንዲጠቅሱ ለማድረግ እና የተሰናበቱበትን ምክንያት እንዲያስረዱ ነው ይሄ በመጅሊስም የሚታወቅ የነበረ ሃሳብ መሆኑን ለማስረዳት ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- አላሉም የተከበረው ፍ/ቤት
- የተነሳውን ጉዳይ በተመለከተ ከምክር ቤቱ እነማን መጡ እነማን ገቡ የሚለውን ነገር ከጭብጡጋ ተያያዥነት የለውም ከጭብጡጋ አሁን ተያያዥነት አለው የሚሉትን ፓርት ብቻ መርጠው ማንሳት ቅድምም አልተከለከሉም አሁንም መቀጠል ይችላሉ ነገር ግን እነማን ወጡ እነማን ገቡ የስራ ክርክር ነው የሚሆነው ስለዚህ ኢሹ አደለም እሱ ስለዚህ ወደ ጭብጡ መጥተው ማንሳት የፈለጉትን
- እሺ ይሄን የሚቃወሙ ሰወች ከመጅሊስ እንዲሰናበት ተደርገዋል ሲሉ ማለት የእርስዎን
- ክቡር ፍ/ቤት አላልኩም ያላልኩትን ነገር እንደ እንትን እንዳይቀርብብኝ
- አሁን እሳቸው ጥያቄውን ይጠይቁ ካልተባለ አልተባለም አሁን የሚመልሱትን መልስ በኋላ መመለስ ይችላሉ መጀመሪያ አዳምጡ እሺ ቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ሼህመከተ ያራምዱት ነበር ያሉትን ሃሳብ ሲደግፉ የነበሩ ወይም ከነሱጋ ሲሰሩ የነበሩት ሰወች ከመጅሊሱ እንዲሰናበቱ ተደርገዋል ብለዋል ሲደግፉ ነበር ወይም አብረው ሲሰሩ ስለነበረ ማለት ምን ማለት ነው እስቲ ይሄን ያስረዱ ?
- አንደኛ ከመጅሊሱ የተነሱ ሰወች ብዬ አላልኩም ምናልባት እሪቫይዝ አደርጉ የሚቀዳም ከሆነ
- እሱን አላልኩም ብለዋል እሺ የቀጣዩን
- የሼህ መከተን አላማ ያራምዱ የነበሩ ሰወች
- አይ እዚሁጋ የተባረሩ የሉም አሉ ሁለተኛው ጥያቄ ምን ነበር እሺ ቀጥሉ ሁለተኛው
- እየመለሱ ጀምረውት ነበር ይቀጥሉ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ መመለስ ጀምረው ነበረ የተሰናበቱት ሰወች የሉም ሲል ግን እዛው መጅሊስ ውስጥ የሼህ መከተን ሃሳብ የማይደግፉ ሰወች ወይም ከእሳቸውጎ ይሰሩ የነበሩ ሰወች የነበሩ መሆኑን ስለገለፁ መመለስ ጀምረውት የነበረውን ቢጨርሱ ለጥያቄው ምላሽ ይሆን ነበር

2978

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመጅሊስ አባላቶች ሳይሆኑ በመስኪድ ኢማሞች ደረጃ ነበር ይሄ ነገር የተኬደው ለአዲስ አበባ ኡለማ ምክር ቤት የመስኪድ ኢማም ናቸው እና ይሄ ተነሱ አደለም አልተነሱምም የተነሳም ሰው የለም ጠርተን አነጋግረናቸው ሁኔታው ምን እንደሆነም አውቀዉት ከዛ በኋላ እኛ እንደዚህ መሆኑን አናውቅም ብለው እራሳቸውን አግለዋል ኡለማው ምክር ቤት ነው ያቀረበባቸው ፌደራል ኡለማ ምክር ቤት አነጋግሯቸው
- እሺ የነሼህ መከተ ጥያቄዎች አንደኛው ጥያቄ ኃይማኖቱ በእስልምና ኃይማኖት ወይንም በአጠቃላይ ስለኃይማኖት በሕገመንግስቱ መሰረት የተከበሩት መብቶች ውስጥ የተጓደሉ መብቶች ስላሉ እነዚህ የተጓደሉት መብቶች ይከበሩልን የሚል ነበር አደል ?
- እንግዲህ ዝርዝሩ ብዙ ነው ወደ አንድነት እንመጣለን በአንድነት እንታገል ነው
- እኮ ይሄ በሕገመንግስቱ የተከበሩ ጥያቄዎቻችን የተጓደሉ መብቶቻችን ይከበሩልን የሚል ጥያቄ ነበራቸው አደል ?
- ይቅርታ አድርጉልኝ አንድ ነገር አለ
- ጥያቄዬን ይመልሱልኝ
- በደንብ ስላልገባኝ ጥያቄው
- ቆዩ ቆይ ልክ ነው ጥያቄው ብዛት ንግግር ስላለው ጥያቄው የት እንደሆነ አይታወቅም ስለዚህ ጥያቄውን ብቻ አሁን ያሉት ከሆነ ችግር የለውም ውስጣቸው ላይ ስላለ ጥያቄውን ብቻ መዛችሁ ጠይቁ
- እሺ የነሼህ መከተ ጥያቄ በሕገመንግስቱ የተከበሩ ግን የተጓደሉ መብቶቻችን ይከበሩልን የሚል ጥያቄ ነበረው አደል?
- ሕገመንግስቱ ላይ የተቀመጠው የሙስሊሞቹ መብት አልተከበረም ነው
- የሙስሊሙ ሕብረተሰብ አንድነት ይጠበቅ የሚል ጥያቄ ነበራቸው አደል?
- የሙስሊም አንድነት ማለት ይኸው አሁንም ወደዛ ትንታኔ ውስጥ ልትከተኝ ነው ሴክቱ ሁለት ነው ቅድም እንዳልኩት ነባራዊ እስልምና እና አዲስ አዲሱንም እንጨፍልቅ ነው
- ሁለቱ የየትኛው አንድነት ነው ይጠበቅ የተባለው የሁለቱም ነው የአንዱ ነው?
- ሁለቱንም አንድላይ እናድርገው ነው እና በአዲሱ ሂዱ ነው ጫና እየተፈጠረ ነው የእኛን እምነት ተከተሉ ነው
- እሺ እርስዎ ቅድም ስጋት ነበረኝ ነው ያሉት የነዚህ ጥያቄዎች የአክራሪነት ሁኔታን ያሳያል ከሚል ተነስተው ነው ?
- በደምብ አልሰማሁም

2979 SD26

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም የእስላማዊ መንግስት ለማቋቋም ስጋት አለኝ ብለው ነበረ እና ይሄ ስጋቱን ፕሬዝዳንት ግርማ በተገኙበት መግለፆን ገልጠዋል ይሄ ስጋቱ የተነሳው ከነዚህ ጥያቄዎች ነው ወይ ነው?
- እዚህ ላይ አንድ ነገር አለ ስጋት ስንል ይሄ ጥያቄዎች እና የመሰባሰቡ የመደራጀቱ ጉዳይ በሕገመንግስት ተደንግጎ የተቀመጠ ነገር አለ በኃይማኖት ስም ኃይማኖታዊ ስራ ለመስራት ካልሆነ በስተቀር ፖለቲካዊ ይዘት ያዘ መደራጀት እና ፓርቲ ማቋቋም እንደማይቻል ሕገመንግስቱም ደንግጎ ያስቀመጠው ነገር ስለነበረ ይሄ አሰባሰብ ይሄ አደረጃጀት ወደ ሊወስድ ስለሚችል ከወዲሁ ጥንቃቄ ይደረግ ብሎ ለመንግስት ስጋትን መግለጽ ወንጀል አይመስለኝም
- እሺ ቅድም ይሄ ግሩፕ የነሼህ መከተ ጥያቄ በዚህ መልክ መቅረቡ የአክራሪነት ስጋትን ይፈጥራል ብለው ነበር የነዚህ ጥያቄዎች የአክራሪነት ስጋትንም ይፈጥራሉ ብለው ቅድም ገልፀው ነበር አክራሪነት እንዴት ነው የሚረዱት እርስዎ ?
- ጥያቄውን /ግልጽ ያልሆነ/
- እሺ ቅድም ሲመሰክሩ እነዚህ ጥያቄዎች የነሼህ መከተ ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ አክራሪነት ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት የነበሮት መሆኑን ገልፀዋል አክራሪነትን እርስዎ እንዴት ነው የሚረዱት አክራሪነትስ ምን ማለት ነው ?
- ኃይማኖታዊ ትንታኔ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ አንደኛ አግባብነት የለውም 2ኛ እና ስለአክራሪነት በዋና ጥያቄ ስንጠይቅ የዋልነው እሱን አይደለም 2ኛ ከጉዳዩ ጋ አግባብነቱ የሬሌቫንት ነወ ጥቅሙስ ምንድን ነው አሁን ዝም ብሎ ጊዜ ከመፍጀት ቅድምም ፍ/ቤቱ የሰጠው ብይን አለ እና በተቻለ መጠን እንዲወገዱ ተብሎ ዋና ጥያቄ ላይ እኛ በጣም ስንገደብ ነበር እያንዳንዱን ነገር እና ከዛ ብይን ጋር የሚጋጭ ነው ስለዚህ በዛ መልኩ እንዲታለፍ ነው የምንጠይቀው
- እሺ ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት አንደኛ ክሱም ላይ ያለው ሃሳብ ይሄው ነው ሁለተኛው ነገር አቃቤ ሕግ እራሳቸው ሲያስመሰክሩ ምስክሩን ቅድም ያወም በጭብጡ ውስጥ ሆኖ እንዲያስመሰክሩ በተሰጣቸው ትእዛዝ መሰረት ሲያስመሰክሩ ነው ምስክሩ ይሄን የመሰክሩት አክራሪነት የሰወች ጥያቄ የአክራሪነት ስጋት ፈጥሮ ነበር ይሄን ስጋቱን ገልጫለሁ ብለዋል ስለዚህ አክራሪነት ስጋት አለኝ ካሉ አክራሪነትን እሳቸው እንዴት ተረድተውት ይሄን ስጋታቸውን እንዴት እንደገለፁ እንዲያስረዱ ነው አክራሪነት ምን ማለት ነው እርስዎ እንዴት ነው

2980

SD27

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚረዱት ነው ጥያቄው ከእሳቸው አረዳድ እና ስጋታቸውን ከገለፁበት መንገድ አንፃር አክራሪነትን እንዲገልፁልን ነው

- ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥቷል ምንድን ነው የሰጠው ብይን የግራ ቀኝ ክርክር ያው ሁላችንም እንደሰማነው ነው ስለዚህ ፍ/ቤቱ የተስማማው ምስክሩ ቀደም ብለው በአቃቤ ሕግ ምስክር ላይም አክራሪነት እየተስፋፋ እንደሆነ ሲያነሱ ነበረ ስለዚህ ምንድን ነው እዚጋ ኃይማኖተዊ ክርክር ነው የሚባለው ነገር አክራሪነት በቀጥታ ኃይማኖትም ብቻ ስለማይሆን አክራሪነትን የተረዱበት አግባብ እንዴት ነው አሁን ወደ ትንታኔው ሳይሆን አክራሪነት እንዲህ ነው ይሄ እንዲህ ነው ሳይሆን አክራሪነት ብለው እሳቸው የተረዱበት አግባብ ምንድን ነው እሚለውን ለማስረዳት ስለሆነ ጥያቄውም ቀደም ብሎ የተነሳ ነው ስለዚህ አግባብ ነው ቀጥሉ ብለናል
- ልመልስ
- አዎ እሚያውቁትን ይመልሱ
- አክራሪነት ማለት በእኔ እምነት የራስን እምነት በጉልበት መጨመር
- ታዲያ ቅድም ሲመሰክሩ በሕገመንግስቱ የተከበሩት የኃይማኖት መብቶች ይከበሩልን የሚል ጥያቄ ነው ጥያቄያቸው ብለው ነበር ይሄ ጥያቄ በኃይል እምነትን መጫን ይሆናል እንዴ ጥያቄ ነው ወይ በአክራሪነት አሁን ባሉት መልክ የተረዱት ነው የነሼህ መከተ ጥያቄ ቅድም በሕገመንግስቱ የተከበሩት የኃይማኖት ትምህርቶቻችን ይከበሩልን የሚል ነው የሚል ጥያቄ አላቸው ብለዋል ይሄ ጥያቄ እምነትን በሰው ላይ ኃይል መጫን ማለት ነው ወይነው ?
- እንግዲህ
- እርስዎ አክራሪነት ያሉት ይሄንን ማመልከቻ ይዘው ወደ መንግስት ስለቀረቡ ነው ?
- አይደለም ይሄ ጥያቄ
- እሺ ከዚህ በኋላ ጠይቁ እናንተ
- ከምን ተነስተው ነው ታዲያ የነሱ ጥያቄ አክራሪነትን ያሳያል ያሉት አሁን በገለፁት ስለ አክራሪነት በሰጡት ትርጉም መሰረት የነሼህ መከተ ጥያቄ አክራሪነትን የሚያሳየው እንዴት ነው ?
- እንግዲህ ኃይማኖታዊ ትንታኔ ውስጥ ልንገባ ነው
- ቆይ ቆይ እዛ ውስጥ ሳይገቡ ምንድን ነው አክራሪነት የሚለውን ተረድተናል ችግር የለውም አሁን እነሱ አክራሪ ናቸው የራሳቸውን ኃይል በላይ ሊጭኑ ነው ያሉበት ምክንያት እሷን ብቻ ያስረዱኝ እሷን ያወቁበትን ምክንያት ?

2981 3028

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአስተምሮታቸው ሰውን ገንጥለው ስለሚያስተምሩ ኃይማኖታዊ ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት ይሄን ይሄን ያልተከተለ ከእኛ አደለም ይሄ ነው አክራሪነት
- እሺ በሕገመንግስቱ የተከበሩለትን የሙስሊሙን መብት አንድሎብናል ያሉት በወቅቱ የነበረው መጅሊስ ነው አደለም የነሼህ መከተ ጥያቄ በሕገመንግስቱ የተከበሩልን መብቶች እንዳይከበሩ አንድሎብናል ብለው ቅሬታ ያቀረቡት በወቅቱ በነበረው መጅሊስ ላይ ነው አደለም ?
- ይሄ በኔ ጊዜ የቀረበ አይደለም
- ቅድም መብታችንን አንድሎብናል ብለዋል ብለው ነበረ ማን አንደለብን ነው ያሉት እነሱ?
- መብት እንግዲህ እንዴት አድርጌ ልንገርህ?
- በህገመንግስቱ የተከበረው የኃይማኖት መብት ተንድሎብናል የሚል ጥያቄ አላቸው እና ማን አንደለብን ነው የሚለው ጥያቄያቸው ነው ?
- መንግስት
- እሺ መንግስት አንድሎብናል ያሉት በምን ሁኔታ ነው ወይም በምን ምክንያት ነው ?
- እንግዲህ
- ማን ነው ያንደለው ስላቸው መንግስት ብለው መልሰዋል መንግስት በሕገመንግስት የተረጋገጠውን የሃይማኖት መብት አንደለብን ያሉት እንዴት ነው ነው ?
- ይሄን እኔ አላውቀውም እኔ አልመልሰውም
- የሙስሊሙ አንድነት እንዳይከበር አድርጉብናል ያሉት በወቅቱ የነበረውን መጅሊስ ነው ይሄ ጥያቄ ነበራቸው አደለም በወቅቱ የነበረው መጅሊስ የሙስሊሙን አንድነት እንዳይጠበቅ አድርጓል የሚል ጥያቄ ነበራቸው አደል?
- የትኛው መጅሊስ ብትለዩልኝ
- እርስዎ ይመሩት የነበረው መጅሊስ?
- አይደለም ይሄ ነገር የተነሳው አሁን ከኔ በኋላ የተካው መጅሊስ
- በአዲሱ መጅሊስ ላይ ነው ይሄ ጥያቄ የተነሳው?
- አዎ
- እርስዎ ይመሩት የነበረው መጅሊስ እነሱ ተቃውሞ ካቀረቡ በኋላ በተደረገ ምርጫ ከስልጣን ወርደዋል አደል?
- ይሄን ልመልስ አልችልም ቅድምም በዚህ ጉዳይ ላይ መልስ አልሰጥም ብያለሁ እንደገና ድጋሚ በእጅ አዙር መጥቷል ቅድም ይሄ ጥያቄ ተነስቶ ክቡር ፍ/ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት ብይን ተሰጥቶበታል ስለሳቸው የግል ሁኔታ ሲጠየቁ በሕዝብ ተቃውሞ ነው የወረዱት የመጅሊስ ስልጣን ምናምን ሲባይ ብይን ተሰጥቶ መጠየቅ አይቻልም ተብሏል አሁን ያ ጥያቄ የሚፈቀድ ከሆነ የተከበረው ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን እየተጠበቀ አይደለም ማለት ነው እሳቸውም ይሄን ነው ለማለት እየፈለጉ ያሉት
- እሺ
- በወቅቱ ከነሼህ መከተ ጥያቄ የሙስሊሙ ሙብትን በተለከተ ጥያቄ ካቀረቡ በኋላ ምርጫ ተደርጐ በወቅቱ የነበረው መጅሊስ ከስልጣን ወርዷል አደለም ወይ ብዬ ነው የጠየቅኩት ይሄን ጥያቄ ያነሳሁት እሳቸው ቅድም የጠየቅኳቸው ጥያቄዎች መጅሊሱ ሳይሆን መንግስት ላይ ነው ጥያቄያቸው የሚል ስለነበረ ይሄንን እንዲያሳይ ነው በወቅቱ የነበረው መጅሊስ ላይ በነበረው ተቃውሞ ምርጫ ተደርጐ በወቅቱ የነበሩት የመጅሊስ አባላት ከስልጣን ወርደው የለም ወይ ነው ጥያቄው እሳቸው ይመሩት የነበረው የመጅሊስ አባል ?
- የወረደ መጅሊስ ከኔ በኋላ የመጣው ነው እኛ አርክክብ
- ምስክር ቅድም በተደጋጋሚ እነ ሼህ መከተ የሚል ነገር ስለተናገሩ እርስዎ የሚያወሩት በ2000 አካባቢ ስለነበረው ስለሆነ እነሼህ መከተ ሲሉ ከሼህ መከተ ውጪ ማንን ለማለት ፈልገው ነዉ?
- እንግዲህ እነሼህ መከተ ማለት ሼህ መከተጋራ አብረዋቸው የነበሩ ሰወች ነበሩ እነዛን በዝርዝረ አላስታውስም
- አሁን እዚህ ውስጥ የሉም አደል?
- እኔ አላስታውስም ሊኖሩም ላይኖሩም ይችላሉ አላስታውስም
- ሼህ መከተ ዳኛ እያሉ እርስዎ ወይም መጅሊስ እርስዎ ይመሩት የነበረው መጅሊስ የማይፈልገውን ውሳኔ ይወስኑ ነበር አደል?
- አልገባኝም
- ማለት መስኪዶችን ለወሃቢያዎች እንዲሰጥ አድርገዋል የሚል ነገር አልተናገሩም ቅድም ?
- ብያለሁ
- ይሄን ውሳኔያቸውን በወቅቱ የነበረው መጅሊስ ይፈልገው ነበር?
- አይፈልገውም ነበር
- እሳቸው እንዲነሱ ከተደረገ በኋላ የእሳቸው ውሳኔ እንዲሻር ተደርጓል አደል?
- በአብዛኛው
- መጅሊስ መልሶ መስኪዶቹን ተረከበ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቤት
- እርስዎ ይመሩት የነበረው መጅሊስ መስኪዶችን መልሶ ተረከበ?
- መስኪዶችን መልሶ የመረከብ ስራ ሳይሆን ለምሳሌ በወቅፎች ዙሪያ በአንዋር መስኪድ ወቅፍ ዙሪያ እነሼህ መከተ የወሰኑት ውሳኔ አሳግባብ የነበረ ስለነበረ ያ እንዲስተካከል ተደርጐ ወደ መጀመሪያው ለሙህተሲብ ብለው አረብኛ ቃል ነው እንግዲህ ተቆርቋሪዎች ለሚባሉት ሰወች እንዲሰጥ ብዙ ነገሮች አግደው ነበረ ኪራይም እንዳይከፈል አድርገው ነበረ ያ ውሳኔ ተሽሯል
- አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ድግግሞሽ እንዳይሆን በዛ በጣም አሁን
- ለክርስትያን መንግስት ግብር መክፈል አያስፈልግም በማለቱ በሕግ የተጠየቀ እርስዎ የማያውቁት ሰው አለ
- አልሰማሁም
- ቅድመ ሲያስረዱ ለክርስትያን መንግስት ግብር መክፈል አያስፈልግም የሚል ነገር ተናግረዋል ይሄንን በማለቱ በሕግ የተጠየቀ ሰው ወይም ለሕግ የቀረበ ሰው የሚያውቁት አለ እርስዎ የለም አደል ?
- እከሌ ተብሎ ተመስክሮበት የመጣ ሰው የለም
- ቅድም ሲያስረዱ በአንድነት ስም የተለያዩ የሃይማኖት አባቶች እንዲሰበሰቡ አድርገው የሃይማኖት መንግስት ለማቋቋም እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ስጋቱን ለመንግስት በስብሰባ ላይ አቅርቤያለሁ ብለዋል ይህንን እንግዲህ የመንግስት አካላት ባሉበት ነው የተናገሩት ይህን ሰምቶ ምን አደረገ መንግስት?
- እኔ ጥያቄው አሁንም አልገባኝም ጌታዬ
- ስጋት አለኝ አሁን በአንድነት ስም የሚሰባሰቡ ሙስሊሞች አሉ
- እናሳጥረው እና እርስዎ ስጋት ነበረኝ ብለዋል ቅድም አደል?
- አዎ
- ስጋቶን አቅርበው ነበረ ለመንግስት ?
- ለመንግስትማ በግልጽ በአደባባይ ነው የተናገርኩት
- መንግስት ምን ምላሽ ሰጠ ነው አሁን ?
- መንግስት ስጋቱን እንደስጋት ተቀብሎታል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. ለተለያዩ የመንግስት ቢሮዎች እኔ እራሴ ደብዳቤ ጽፌያለሁ ብሸዋል ምን ይደረግ ብለው ነው የፃፉት ?
- ስብሰባዎቹ በዚህ በኀይማኖት ስም በአንድነት ስም የሚደረጉ ስብሰባዎች መቋረጥ እንዳለባቸው ለአዲስአበባ ፖሊስ ኮሚሽነት በወቅቱ ለነበሩት ጽፌያለሁ ደብዳቤ የተወሰኑም ስብሰባዎች እንዳያካሄዱ ተከልክሏል
- እነዚህ ለአንድነት የሚደረጉ ስብሰባዎች እንዳያካሄዱ ተደረገ?
- ያለውን ብኋል ሌላ መቼ ነበርማን አመተምረቱ ያን ደብዳቤ የፃፉት?
- በ2001 ጀምሮ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ነበሩ
- አይ እርስዎ የፃፉት?
- በባው አካባቢ ነው
- እሺ ሌላ
- ሙስሊሙ መሃል አንድነት ሊኖር ይገባል በሚል ስብሰባ ተደርጓል ብለዋል ስብሰባውን የመሩት የአዲስ አበባ መጅሊስ ፀሐፊ እና ሙፍቲ ሼህ ኡመር አደሉ ይሄን ስብሰባ የአንድነት ስብሰባ የመሩት እሳቸው ናቸው አደለም?
- እኔ በቦታው አልነበርኩም
- እሺ በቃ የሙፍቲ ሼህ ኡመር የአዲስአበባ መጅሊስ እና ሙፍቲ ናቸው አደለ ቅድም ተሳሳቱ ካላቸው ውስጥ ይገኛል የተከበረው ፍ/ቤት ወደ ፍ/ቤቱ እያዩ ምላሽ እንዲሰጡ የነገርልኝ ?
- አረ አላዩም አቃቤ ሕግን አላዩም ወደ መሬት ነው ያዩት
- እኮ ትኩረታቸው ጥያቄ ላይ እንዲሆን ብዬ ነው
- ለመስማት እንዲመቸኝ ብዬ ነው
- ሙፍቲ ሼህ ኡመር እድሪስ የአዲስ አበባ መጅሊስ ፀሐፊ ቅድም ተሳሳቱ ካሏቸው ውስጥ ይገኛል አንዳንድ የመጅሊሱ ሰወች ተሳስተው ነበረ ተመለሱ ብለዋል ከዛ ውስጥ እሳቸው ነበሩበት ?
- ልመልስ ለመመለስ ከሆነ አዎ
- እሺ ከተሳሳቱት ውስጥ እሳቸው ነበሩ እና እንዴት ከስተታቸው እንዲመለሱ አደረጋችሁ ?
- መጀመሪያም ስተት የተፈጠረው እንደመርህ አሁንም ወደ እንትን ሊያስገቡኝ ነው እንደ መርህ ያገራችን የመጅሊሱ አራት
- በኋላ ተመለሱ አልተመለሱም እሱን ብቻ ተመልሰዋል ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተመልሰዋል
- ትድም ያስረዱት ስብሰባ ይዘት በሙስሊሙ መሃል ኃይማኖታዊ የሆኑ ልዩነቶች ሊኖሩ አይገቡም ለኡለሞች ወይም ለሙፍቲዎች ቀርቦ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ወይም ማብራሪያ ሊሰጥባቸው ይገባል በዚህ ምክንያት መለያየት ሊኖር አይገባም የሚል ነበር አደል ስብሰባው ?
- ይሄንን አላስታውሰውም እኔ
- እርስዎ ነበሩ ስብሰባው ላይ?
- እኔ ስብሰባውም ላይ አልነበርኩም
- ስብሰባው ላይ የተደረጉ ስለመደረጉ እንዴት አወቁ?
- በተሰጠኝ ከኡለማ ምክር ቤት በተሰጠኝ ጥቆማ መሰረት ደብዳቤ ጽፌያለሁ ኡለማ ምክር ቤትም ጥቆማውንም የሰጠው በደብዳቤ ነው
- አሃ ስጋቶ መሰረት ያደረገው ለመንግስት አቀረብኩት ያሉት ስጋት መሰረት ያደረገው ከሰው የተነገሮት ነው ወይም ይሄ ጥቆማ ነው ማለት ነው?
- አይደለም ከነበረው እንቅስቃሴ ነው
- የትኛው እንቅስቃሴ?
- እንግዲህ ብዙ እንቅስቃሴ ተደርጓል ከኔ በፊትም ከኔም በኋላ
- እሺ በድር ኢንተርናሽናል የሚባል ድርጅት ጠቅላይ ሚንስትሩን አናግረዋል ብለዋል ስለምን ጉዳይ ነው ያናገረው ?
- አልነበርኩም በወቅቱ
- ስለማናገሩስ በምን አወቁ?
- አሉ ባፋቸው
- ማን ነው ያለው ?
- እነሱ
- አሃ ምን ምን አናገረን አሏቸው ?
- በድር ኢንተርናሽናል እኛ ቢሮ መጥተው ሲያነጋግሩን እሳቸውን እንዳነገሩ ነው የነገሩን እንጂ ከጠቅላይ ሚንስትሩ አፍ ደግሞም አልሰማንም
- እሺ ይሄ አሁን የጠራሁት ድርጅት መጅሊሱን የሚመሩት ግለሰቦች በኃይማኖት እውቀታቸው በስነምግባራቸው ሙስሊሙን የሚመጥኑ አይደሉም መንግስት የመጅሊስ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ኃላዎችን አይሹምብን እኛ በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንድንመርጥ ይፈቀድልን የሚል ጥያቄ አቅርቦ ነበር አደል?

- አይደለም
- ምንድን ነው ታዲያ /ግልጽ ያልሆነ/ ጥያቄ?
- ጥያቄያቸው ሰፊ ነው ይሄንን ጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮ መጠየቅ እና ከዛ መረዳት ይቻላል
- አይ ሰፊ ነው አሁን ለምሳሌ ሰፊ ነው ሲሉ ያውቃሉ ማለት ነው የተወሰነውን ስፋቱን ያውቃሉ ማለት ነው የሚያውቁት ከሆነ የተወሰነውን እስቲ?
- እነሱ ለእኛ የነገሩን ሌላ ነው
- ምን ነገሯችሁ?
- የነገሩን የፖለቲካ ጥያቄ ነው እንደጠየቁ የነገሩን
- ከዛ ውስጥ መጅሊስ ሙስሊሙን ለመወከል ብቃት የለውም የሚለ የለውም አደል?
- ማጠናከሪያ ነው ያሉን ለእኛ
- ማጠናከሪያ ማለት?
- አዎ
- ማጠናከሪያ ማለት ምንድን ነው?
- መጅሊሱን በተሻሉ በተማሩ ሰወች በምሁራን ማጠናከር አለብን በሚል ሽፋን ነው የመጡት
- አሁን ያሉት የሃይማኖት እውቀት የአካዳሚ እውቀት የላቸውም ማለታቸው ነው?
- እኛ እንግዲህ አናውቅም የነሱ አባባል በምን እንደተረጐሙት ብቃታትም በምን እንደሚለካ በጢም ነው በምን እንደሆነ አላወቅነውም
- ብቃት የለውም የሚልነገር ሰምተዋል ወይ?
- አቤት
- ብቃት የለውም ያለው አመራር የሚልነገር አንስተዋል ወይ?
- አላነሱም እኛጋ እንደዚህ አይነት ነገር የለም
- ሌላ ጥያቄ
- የመጅሊሱ አስተዳደር የሆነ ሰወች ከየት መጥተው ነው የመጅሊሱ አስተዳደር የሆኑት
- የትኞቹ?
- እርስዎን ጨምሮ ሌሎችም ከየት መጣችሁ በሕዝብ ተመርጣችሁነው
- ተቃውሞ አለ
- ይሄን እለፈው እና ሌላ ካስፈለገ ባክግራውንዳቸው እስ እዚህ

2987

SD34

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ስለአንድነት በተደረገ ስብሰባ ላይ በወቅቱ የመንግስት ኃላፊ የነበሩት ሴኩ ቱሬ ነበሩ አደል?
- እ?
- ሴኩ ቱሬ የሚባሉ የመንግስት ?
- ይሄን አልሰማሁም እኔ ኢትዮጵያዊ ናቸው እኚህ ሰው
- ጨርሰናል የተከበረው ፈ/ቤት
- ድጋሚ ካለ
- ድጋሚ የለንም
- እሺ አሁን ያው ሰባት ሰዓት አካባቢ ሆኗል ስለዚህ ስምንት ሰዓት ተኩል ላይ እንገናኝ እና ሁለት ምስክር አለ ይባላል እሱን እንጨርስ
- የከሰዓት ችሎቱን እንቀጥላለን ቀሪ ምስክር ይቅረብ ችሎቱን ያው ከሰዓት በኋላ በተያዘው ቀጠሮ መሰረት እንጀምራለንቀነ አልተቀየረም ሰኔ 5 ቀን 2005 ዳኞች የጠዋቱ አልተቀየሩም የመዝገብ ቁጥሩ 124754 ነው ከሳሽ የጠዋቱ አቃቤ ሕጐች አልተቀየሩም ተከሳሾች የተቀየረ አለ እንደጠዋቱ እንደነበረው ነው እሺ ምናልባት ጠበቆች ላይ ለውጥ ተደርጓል አዲስ የመጣ ብቻ ከሰዓት
- ሃሰን ሁሴን ከሰዓት መጥቷል ከተከሳሾቹ ጠበቆች ሌሎች ጠዋት የነበሩት አሉ ጠዋት ከነበሩት አንድ ጠበቃ ውጪ ሌሎቹ አሉ የአቃቤ ሕግ ምስክር ከሰዓት በፊት ያው 98ኛው ያቀብ ነው አሁን የመጣው 99ኛው የአቃቤ ሕግ ምስክር ነው የሚሆኑት ማለት ነው እሺ ምክር ያው የራሶን ስም ብቻ ነው የሚገልፁት የአባቶን ስም አይጨምሩም
- አብዶ ነኝ
- ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ እሺ 99ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር አቶ አብዱ ቀርበዋል በማስረጃ ዝርዝሩ 101 ላይ የተጠቀሱ ናቸው እሺ አቶ አብዱ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- አህመድ ሙስጠፋ ላይ እና ያሲን ኑሩ
- ሌላ ሰው አለ?
- የለም
- ይተዋወቃሉ ?
- አልተዋወቅም
- እሺ አሁን ማሳየት ይችላሉ ?
- አይ አላውቃቸውም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማሳየት አይችሉም ?
- አዎ
- እሺ ምን አደረጉ ተብለው ነው የተከሰሱት?
- እኛ ለስራ ስንገባ ሰው ሞልቶ አገኘን መስኪድ ላይ ጠዋት ስንገባ ሰው መስኪድ ላይ ጫፍ ላይ ሞልቶ አገኘናቸው ገብተው ማለት ነው
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ እስቲ
- አቶ አብዱ አሁን የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለዋል እና እስቲ ቅድም ያሏቸው ሰወች ምን ሲያደርጉ እንደነበረና ጊዜው ቦታው የት አካባቢ ምን ሲፈፀም የነበረ መሆኑን እስቲ የሚያውቁትን አሁን ለተከበረው ፍ/ቤት ያው በዝርዝር እንዲገልፁ ነው የምጠይቀው አሁን መናገር ይችላሉ ቀጥሉ
- አይ እኛ ስንገባ መስኪድ ላይ ሰው አገኘናቸው
- የት መስኪድ ነው ?
- አንዋር መስኪድ ነው
- መቼ ነበር?
- ሐምሌ 7
- መቼ ነው ጊዜው አመተምረቱ መቼ ነበር?
- አገኘናቸው ከዛ በኋላ ሰው እየሞላ መጣ
- አመተምረቱ መቼ ነው ?
- 2004
- እሺቀጥሉ
- አሁን እየሞላ መጣ ሰው እየሞላ እየሞላ ሲመጣ ፈትሸው ማስገባት ጀመሩ
- የት መስኪድ ነው ያሉት?
- አንዋር መስኪድ ፈትሸው ሲገቡ መንግስት በሃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ እጁን ያንሳልን
- መንግስት ምን ላይ ጣልቃ ይግባ አሉ?
- በኃይማኖቱ
- እሺ?
- እጁን ያንሳልን ወንድማሞች እና ሴቶቻችን ደም ፈሶ አይቀርም መንግስት ይጠይቅልን እያሉ መብራት ጠፋ መብራት ጠፍቶ አንዱ መጥቶ ጠየቀኝ ጀለብያ የለበሰ ሰው መጥቶ ጠየቀኝ

2989

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እ?
- መጥቶ ጠየቀኝ ጄኔሬተር ቁልፍ ሊጠይቀን መጣ
- ማን ነው እሱ?
- አላውቀውም እኛ ቁልፍ አንይዝም ቁልፍ ያለው ናስር ዘይኔ ጋር ነው ቁልፍ ያለው ብለን አልነውና ወደላይ ወጣ ያ ጄኔሬተር ተሰበረ ገባ
- እ?
- ቁልፉ ተሰበረ
- እኔጋ የለም ነው ያሉት እርስዎ?
- እ?
- ቁልፉ እኔጋ የለም አሉ እርስዎ?
- የለም ሲለው ወጡ ጄኔሬተሩን ቁልፉን ገንጥሎ ገብቶ ጄኔሬተሩን አስነሱ
- ቁልፉ ማለት የምን ቁልፍ ነው?
- የጄኔሬተር ቁልፍ /ግልጽ ያልሆነ/ ንግግሩን ጀመሩ
- ንግግሩ የተጀመረው በጄኔሬተር ማለት ነው ?
- አዎ መብራት ስለሌለ ጄኔሬተሩ ተነሳ በቃ እንደገና ነው የተጀመረው በቃ እያሉ እኛ ምርጫችን በመስኪዳችን
- እሺ ቀጥሉ
- ምርጫች መስኪዳችን ጣልቃ አይግባ መንግስት
- እየደከሞት ነው ?
- አልደከመኝም
- አበቃሁ
- አሁን ቅድም እንደገለፁት ማለት ነው እስቲ አህመድ ሙስጠፋ ምንድን ነው ያደረገው እርስዎ እንዳዩት ምን አደረገ እስቲ ስለሱ ይንገሩን?
- አህመድ ሙስጠፋ መንግስት ጣልቃ አይግባ እጁን ያንሳልን የወንድሞቻችን ደም ፈሶ አይቀርም
- እሺ ሌላስ የሚያስታውሱት ካለ ይሄንን የሚለው የት ነው ?
- አቤት
- የት ነው ይሄንን ሲናገር የሰሙት ይሄንን መልእክት ያስተላለፈው ለማን ነው የት ነው?
- አንዋር መስኪድ

2990 5037

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ላይ ሆኖ ነው ሲያስተላልፍ የነበረው ?
- መድረክ ላይ
- ለማን ነው የሚያስተላልፈው ?
- ለሕዝቡ
- ሕዝቡ እንዴት ነበር ያኔ?
- ሕዝቡ ሙሉ ነው
- እንዴት ነበር አገባባችሁ ሲገባ ከዛ በኋላ ያለው ይህን ሲቀሰቅስ ወይም ደግሞ ሲገልጽ የነበረው ምንድንነው ቀኑ መቼ ነበር ?
- ቀኑ ቅዳሜ ነው
- እንዴት ነበር እሺ እርስዎ እዛ ነበሩ እንዴት ገባችሁ ወደ መስኪድ ስትገቡ ወደ አንዋር ስትገቡ እንዴት ነበር አገባባችሁ?
- አገባባችን ሰው ነበረ እውስጡ ማለት ነው በውስጡ የነበረ ሰው በኋላ እየጨመረ እየጨመረ መጣ
- አይ ከበር ጀምሮ ያለው ከበር ጀምሮ እንዴት ነው ሲገባ የነበረው አገባቡ ?
- እየፈተሹ ነው ያስገቡት
- ማን ነው የሚፈትሸው ማን ነው ያቆማቸው ናቸው?
- ከነሱ የመጣ ሕዝብ ነው
- ከራሳቸው?
- አዎ ከራሳቸው
- ይሄን እንዴት ማወቅ ቻሉ ይሄንን?
- የራሳቸውን ደህንነት ለመጠበቅ ነው
- እራሳቸው ይሄን ያደረጉት?
- አዎ
- እሺ ከዛ ስንት ሰዓት ተጀመረ ይሄ ንግግር ?
- ጠዋት ጀመረ ያው
- እስቲ ከራሳቸው ማለት ከማን ማለት ነው ?
- ከራሳቸው ሕዝብ ማለት ነው
- ከሕዝቡ ?
- አዎ ከሕዝቡ ከዛው ካለው ሕዝብ ማለት ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስኪዱ ውስጥ ካለው ሕዝብ?
- አዎ መስኪዱ ውስጥ ካለ ሕዝብ
- እሺ ቀጥሉ
- ማለት ሰወች ሲገቡ መስኪድ ሲገቡ እንዲፈተሹ ብሎ ያለው ወይም ትእዛዝ ያስተላለፈው ማን ነው እርስዎ ያውቃሉ ይሄንን ?
- እየፈተሹ ነው የሚያስገቡት
- እሚፈትሹት ምን ሲያገኙ እሚያስወጡት ነገር አለ ይሄን እንደዚህ አድርገሃል ይሄን አይገባም ይገባል የሚሉት ነገር አለ እንዴ ሲፈትሹ ?
- የለም
- ግን ይፈትሻሉ ?
- እየፈተሹ እስክሪኑን እየፈተሹ ያስገባሉ
- ከዛ በፊት አንዋር እንዲህ አሁን ለፀሎት ለማድረስ ሲገባ ፍተሻ ይካሄዳል እንዴ ?
- አልነበረም
- የዛእለት ነው የተደረገው?
- የዛን ቀን ነው የተጀመረው
- እሺ እንትናስ ማን ነው ቅድም ያሉት ሁለተኛው ያሲንስ መን ነበረ ሲል የነበረው?
- እ?
- ያሲንንም አውቀዋለሁ ብለዋል እና ያሲንስ ምንድን ነው ያረገው?
- ያሲንም እንደዚህ ነው ያለው
- ምን አለ?
- ያው ወንድማማቾችን ደም መንግስት ይጠይቅልን ምርጫችን በመስኪዳችን እያሉ ነው
- ይሄን ሲናገሩ እርስዎስ በማይክ ነው በመትረፀ ነው ወይስ በምን ነበር ሲናገር የነበረው?
- በማይክራፎን
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ጠበቆች መስቀለኛ ካላችሁ
- አቶ አብዱ
- አቤት
- እርስዎ የትጋ ነበሩ?
- የጥበቃ በር ላይ

5039

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥበቃ በር ምን ክፍል አለው ለጥበቃ ?
- የተለያየ ጥበቃ ማለት የምናድርባት ቦታ አለች እዛ በር ላይ ነው
- እኮ የምታድሩበት ትንሽ ክፍል ነው ከመስኪዱ ግምብ አጥር ግምብ ጋር ተያይዞ የተሰራ ነው ?
- ትንሽ ወጣ ይላል ቆርቆሮ በቆርቆ ነው
- እሺ እርስዎ ቆርቆሮ ውስጥ ነበሩ?
- ውጭ በር አፍ ላይ
- እነሱ ተከሳሾቹ ይናገሩ የነበረው መስኪድ ውስጥ ነው ብለውናል
- መስኪድ ውስጥ ነው
- የትኛው ሁለት መስኪድ አለ አደል አንዋር መስኪድ ውስጥ ?
- አይ አንድ ነው
- ማለት ትልቁ መስኪድ ከፊት ለፊት እና ከጐን ደግሞ ይሄ ፎቁ?
- ትዋቁ መስኪድ እሱ ነው
- እርስዎ ዘበኛ ቤት በር ላይ ቆመዋል ትልቁ መስኪድ በግምት ምን ያህል ይርቃል እርስዎ ከቆሙበት ውስጥ እነሱ መድረክ ላይ ይናገሩ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- አሁን ከዚህ በግምት አንድ የኳስ ሜዳ ምን ያህል ይርቃል መቶ ሜትር ሁለት መቶ ሜትር እርስዎ ከነበሩበት ያሲን ኑሩ ከሚናገርበት ያለው እርቀት ?
- ያሲን ኑሩ
- ያሲን ኑሩ መስኪድ ውስጥ መድረክ ላይ ይናገር ነበረ አህመድ ሙስጠፋም ብለዋል ?
- ሲባል ነው የሰማሁት በአካል አላየሁም ሰው እርስ በእርሳቸው እንዲህ እየተናገረ ነው ሲባል ነው የሰማሁት
- እሺ እርስዎ የነበሩበት ቦታ እነዚህ ይናገር ሲባል የሰሙት ሰወች ሲናገሩ በምን ያህል እርቀት ሆነው ነበረ ይሰሙ የነበረው?
- እርቀት አለው
- እርቀት አለው አደል?
- አዎ ወደ ውስጥ ነው
- አሁን ይሄን አዳራሽ ሲመጡአይተዋል
- እንትናቸው አይታይም ድምፃቸው እንጂ መልካቸውም ሥናቸውም አይታይም

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በርም አለው አደል?
- የሕዝቡ ብዛት ሸፍኖታል
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ተናግሩ ያሉት ?
- ስንት ሰዓት ላይ ?
- አዎ አሁን ያሲን ኑሩ ስንት ሰዓት ላይ?
- ከአራት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዝሁር ሰዓት ድረስ እንደገና ሰላት ሰግደን እንደገና ይቀጥላል
- እሃ ሁለቱ አሁን ያሲን ኑሩ እና አህመድ ሙስጠፋ ከአራት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ነው የተናገሩት?
- አይ ሁሉም ተራ በተራ ነው የሚናገሩት
- እነዚህ አሁን የጀመሩበትን ሰዓት አያውቁም?
- አላውቀውም
- ማን ነው ቀድሞ የተናገረው?
- አህመድ ሙስጠፋ ነው
- እርስዎ ስንት ሰዓት ላይ ነበረ አንዋር የደረሱት ?
- ሁለት ሰዓት ነው
- /የማይሰማ/ ነው የሚል ሌላ ነገር አልሰማሁም እንዴ
- አቤት
- አሁን ከተናገሩት ውጭ ጥያቄያችን ሰላማዊ ነው የሚልነገር ሲናገሩ አልሰሙም?
- አልሰማሁም
- ከነሱ በፊትስ ሌላ አስተዋዋቂ አልነበረም የሚናገር?
- ማን እንደሚናገር እኛ ይሄን ነው የሰማነው እንጂ ሌላ የሰማነው ነገር የለም
- እሺ ቅድም የወንድሞቻችን ደም ፈሶ አይቀርም መንግስት ይጠይቅልን ሲሉ ነበረ ብለዋል ?
- ብያለሁ
- ማንን ነው መንግስት የሚጠይቀው ይሄንን ያውቃሉ?
- አይ አላውቅም
- እርስዎ እስከ ስንት ሰዓት ቆዩ እዛ ?
- እስከ ማታ አድረን ነው የምንወጣው
- መጨረሻው እንዴት ተበተነ እሺ?
- አስር ሰግደው በአስራአንድ ይወጣሉ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ • የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት • ...

2994

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በራሱ በሰላማዊ መንገድ ተጠናቀቀ አደል?
- በሰላማዊ መንገድ /ግልጽ ያልሆነ/
- የተነሳ አረብሻ የለም?
- አዎ በዛን ጊዜ የተነሳ ነገር የለም
- እርስዎ የጥበቃ ቦታ ነበረ የቆሙት ጄኔሬተሩ የት ነበረ ያለው ?
- ማን?
- ጄኔሬተሩ እርስዎ ካሉበት እሩቅ ያለ ነው አደል?
- አዎ ወደላይ ነው
- የት ወደላይ?
- ወደ ሴቶች መውጫ
- እርስዎ ካሉበት ይርቃል?
- ይርቃል
- ስለዚህ እርስዎ ጄኔሬተሩ መሰበሩን እንጂ ሲሰበር እኮ አላዩም ሕዝብ ሙሉ ነው ?
- ሰው ሙሉ ነው አይታይም የእግር መርገጫ የለም
- ስለዚህ ተሰበረ የሚለውን ነው የሰሙት?
- አዎ
- ተሰበረ የሚሉት ቁልፉን ነው አደለ?
- ቁልፉ ነው
- ጄኔሬተር የሚቀመጥበት የቤቱ ቁልፍ ?
- የበቱ ቁልፍ
- ተሰበረ ሲባል ሰምተዋል?
- አዎ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ካለ
- ድጋሚ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ
- አሁን የሁለት ስም ጠርተዋል እርስዎ እና
- አቤት
- የሁለት ሰው ስም ጠርተው ነበረ አህመድ እና ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ያሲን ኑሩ እና አህመድ ሙስጠፋ
- አህመድ ሙስጠፋ ብለው ጠርተው ነበር?
- አዎ
- እነኚህ ሰወች ስሙን ከየት አገኙ እርስዎ?
- ሲናገሩ እርስ በእርሳቸው እየተነጋገሩ ነው የሰማሁት
- እ?
- አህመድ ሙስጠፋ ሲሉ ኑሩ ያሲን ሲሉ በቻ ነው
- ከዛ ውስጥ በድምጽ ማጉያው ውስጥ በዛው ሲናገሩ ነው የሰሙት ?
- አዎ
- ሰወቹ ንግግር ካረጉ በኋላ ነው በፊት ?
- እ?
- እከሌ ይናገራል ብቻ /ግልጽ ያልሆነ/
- አስቀድሞ ነው በኋላ ነው በፊት ነው የሚባለው ?
- መጀመሪያ ሲጀምር ማለት ነው
- እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- አሁን ምስክሩን እንቀጥላለን በተሰሙ ዝርዝር ልክ 100ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል ምስክር የአባቶን ስም ሳያጨምሩ የራሶን ስም ብቻ ይገልፁልናል ?
- አያልነህ
- እሺ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ እሺ ምስክሩ 100ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር አቶ አያልነህ ቀርቧል በማስረጃ ዝርዝሩ በ134ኛ ላይ የተጠቀሱ ናቸው እሺ አቶ አያልነህ
- አቤት
- ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ለምስክርነት ከመጡ ?
- አቶ አቦከር አህመድ ሌላ የለም
- በአካል ያውቁታል ?
- አላውቀውም
- አሁን መለየት ይችላሉ ?
- አይ አላውቀውም መጨረሻ
- አያውቁትም?
- አዎ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ምን ፈፀመ ተብሎ ነው እስቲ አጠር አርገው መናገር ከቻሉ?
- አዎ እኔ በዛው የሆነ ወደላይ እየተንገዙ ነበረ
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዝርዝር ውስጥ እየገቡ ስለሆነ እንትን እናርግና አቃቤ ሕግ ያው ጥያቄ በዛው በኩል ያቀርቡሎታል አዳምጠው የሚያውቁትን ይመልሳሉ
- ወደላይ ስንዝ አሉ ቅድም መቼ ነበረ ጊዜው ?
- ሐምሌ 13
- አመተምረቱ መቼ ነው ?
- 2004
- የት ክ/ከተማ ነው?
- ኮልፌ ቀራንዮ
- እስቲ አሁን ባሉት ቀን ሰዓቱ ስንት ሰዓት ነበር?
- አራት ሰዓት ተኩል አካባቢ ይሆናል
- ልዩ መጠሪያ አለው አካባቢያችሁ ?
- እ?
- አካባቢያችሁ ልዩ መጠሪያ አለው ወይ ኮልፌ ቀራንዮ የት ቦታ ነው?
- ወረዳ 6 ሸዋ ዳቦ አካባቢ ነው ቤቴልይባላል
- በዚህ እለት ምንድን ነው የገጠሞት እስቲ ምን አዩ ምን ታዘቡ?
- አይ እኔ የታዘብኩትኝ ያው ፖሊሶቹ የፍ/ቤት ትእዛዝ አለ እዚህ እና ተባበረን ምናምን አለን አለ በዛ ወጥቼ ስሄድ እኔም እሺ ምን የፍ/ቤት ወረቀት ካለ እሺ እተባበራለሁ ምናምን ብዬ የፍ/ቤት ወረቀቱን አንብበውልኝ የታዛቢነቱን ያው ያየሁትን እይቻለሁ
- እስቲ ምን ታዘቡ እንዴት ገባችሁ ማንን አገኛችሁ እስቲ ከመግባት ጀምሮ የነበው ሂደት ምን እንደሚመስል እሱን እስቲ ይግለፁ?
- አይ ገባን በሩ ተከፈተ ባለቤቱ አለች
- የማን ባለቤት?
- የአቶ አቡበከር ባለቤት እዛ ያም የእኛም ታዛቢዎችም አብረን ነበርን 3 ነበርን ሰነዶቹን እና ሲም ካርዶች ካሴቶች ሲዲ ካሴት ምናምን ሰነዶች ነው ያየነው በወቅቱ
- ሌላስ ሲዲ ካሴቱ ምንድን ነው ሰነድ ብለዋል ?
- ሲዲ በብዛት ነው እኛ ገለፃውን አላየነውም ግን እየቆጠርን ሲቆጠር አይተናል ሲዲ ካሴት 43 የቴፕ ካሴት 102 ድምፃችን ይሰማ የሚል አንድ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው እሱ ?
- በራሪ ወረቀት የሙስሊሞች አቋም መግለጫ የተሰጠ የሚል አጀንዳ አነድ የሰላም አምባሳደር የሚል በራሪ ወረቀቶች ሃስት
- የሚያስታውሷቸው ካለ ቲሸርት ደግሞ የሰደቃ ነው የሚል ቲሸርት አንድ
- ቲሸርቱ ላይ ምን የተፃፈ ነው ?
- አገር ውስጥ የፌደራል ኢንዱስትሪ ዳይሬክቶሬት የሚል ወረቀት ሰነድ ከአገርውስጥ ከፌደራል በእንትን የታተሙ ወረቀቶች አረስቻቸዋለሁ 26 ምናምን የሚሆኑ እነዚህ እነዚህን አይቻለሁ
- /ግልጽ ያልሆነ/ ያው ቀኑ አረፍተም ስለሆነ ብዙ ነገሮች ጠፍተውብኛል
- እሺ አሁን ቅድም ሲገልፁ ማለት ነው ልክ ስትገቡ የአቶ አቡበከር ባለቤት ነኝ ያሉ በር እንደከፈቱላቸው ስተገቡ ወይም ፖሊሶቹ አብራችሁ ስትገቡ ምን አላችኋቸው ለእሳቸው ለባለቤት ምን ተብሎ ሲገባ ሰሙ እርስዎ ልክ ለእርስዎ እርስዎን እንዳሳዩት ፖሊሶቹ እሳቸውስ በር ሲከፍቱ የተነገራቸው ነገር ነበር ?
- አዎ በአሸባሪነት የተጠረጠ ነው ባለቤትሽ ምናምን ተብላ ነው እንድታስበረብር የነገሯት
- አይ ከዛስ ምን ይሄ ተባለ በኋላ በር ተከፈተ ምን አሉ ለእሳቸው ምን ተነገራቸው ለባለቤታቸው ?
- ተነበበላት ወረቀቱ
- ወረቀቱ ተነበበ?
- ወረቀቱን ለእኛ አብረን ነው ያነበቡልን
- እኮ ማለት ለእርስዎ እንደተነበበው ለእሳቸውም ተነበበ ?
- እሺ ግቡ እና እዩ ነው ያለችው
- ለእንደዚህ ነው ብለው አነበቡላቸው የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ማለቴ ነው ?
- እ?
- የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ተነበበላቸው?
- አይ እኔ የዛን ጊዜውን በቃ አጋጣሚ
- ተቃውሞ አለን
- ተመልሷል የሚነሳ ነገር ካለ ከዚህ የሚነሳውን ትእዛዝ ጠብቁ እሺ አሁን ሌላ ጥያቄ
- ጨርሳችኋል

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም እንደገለፁት በዝርዝር እነኚህ የተገኙት እርስዎ የገለጿቸው ከተገኘ በኋላ መጨረሻ ላይ ምን ተደረገ ምን አረጋችሁ እርስዎ ይዛ እነኚህ ነገር ከአቶ አቡበክር ቤት ስለመገኘቱ ምንድን ነው ያደረጉት ስለመታዘበ ማለት ነው ?
- በቃ እዛ ላይ ቁጭ አልንና ሁላችንም ያው ተሰባስበን ባለቤቱንም እኛም ተፈራርመን ፈርመንበታል ወረቀቱ ላይም ተፈራርመን ተለያየን በቃ ወደ አራት ሰዓት ተኩል አካባቢ ገብተን ዘጠኝ ሰዓት ላይ ተለያየን
- የፈረማችሁበት ወረቀት ማለት የራሳችሁ በተዘጋጀ ወረቀት ላይ ነው የፈረማችሁት ወይስ ?
- አይ እዛው ሰነዱ ላይ ነው የፈረምነው ሰነዱ ላይ እንዳይጠፉብን እኛም ደግሞ እንሳሳታለን የሚል እንደውም ምናምን ብለን ሁላችንም እያንዳንዳችን ፈረምንበት ባለቤቱንም እያየን እየፈረመችበት ነበር
- መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ጠበቆች
- አቶ አያልነህ አቡበክር አህመድን አላውቀውም ብለሃል ?
- አላውቀውም
- በእለቱ እዛ ፍተሻ ሲካሄድም አልነበረም አደል?
- አልነበረም
- የእሱ ባለቤት የሆነች ሴት እንደነበረች ተነግሯል ?
- አዎ
- ባለቤት ለመሆኗ በምን አወቁ?
- አይ ነግራ ነው ለሁላችን የተናገረችው ነገረችን እና ሌሎቹም አሉ ነግራናለች ሰራተኞች እና እኔ ባለቤቱ ነኝ ምናምን ብላ
- ባለቤቱ ነኝ ስላለቻችሁ ነው ?
- አለችን አዎ
- ከዛ ውጭ ባለቤት ለመሆኗ የጋብቻ ወረቀት ጠይቃችኋል ?
- አላየነም
- ሴትየዋ ፊቷን ተሸፍና ነበር ወይስ ተገልጣ ነበር?
- አይ ብዙም ተሸፍናለች ግን ብዙም አልተሸፈነችም ትንሽ የተወሰነ እያየች ነበረ
- ማለት አይኗ ነው የሚታየው?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄን ፊቷ ላይ አላወለቀችውም ፊቱን ገልጣ እያየች ነበረ አይ በደምብ እያልናት ነበረ እያየች ነበረ
- አደለም እንድታይ ማየት አላየችም ሳይሆን ያልኩት እናንተ በር የከፈተችላችሁ ሴት ፊቷን በጨርቅ አልሸፈነችም ?
- አይ
- ተገልጦ ነበረ ፊቷ ?
- አልገለጠችውም ግን እኛ ትታየናለች አይቻታለሁ
- እርስዎ እንዲታዘቡ የተጠየቁት ከቤቱ በምን ያህል እርቀት ነው መጀመሪያ ፖሊሶች ታዛቢ እንዲሆኑ የጠየቆት ከቤቶ እራቅ ብለው ነው ?
- አይ እኔ ወደላይ ወደ ቤተል እየወጣሁ ነበረ በመንገዱ ላይ በነሱ ደጅ አፍ ላይ በር ላይ እየወጣሁ ነበረ ከዛ መንገድ ላይ ፖሊሶች ቆመዋል ከዛ የዚህ ሰፈር ነዋሪ ነህ ምናምን አሉ ጠየቁኝ በዚሁ አጋጣሚ እንደዚ እንደዚ ነው ያለው ተባበረን ምናምን ሲሉኝ አይ እኔ አይሆንም ምናምን ስላቸው የፍ/ቤት ትእዛዝ ይዘናል ችግር የለውም ምናምን ሲለኝ የፍ/ቤት ትእዛዝ ካለው እሺ ብዬ ያው 3 ነበርሩ ሰወቹ እነዛው ሌላ ደግሞ እኔ ነኝ መጀመሪያ የመጣሁት ከዛ በኋላ መስፍን የሚባል መጣ ከዛ በኋላ ኡጅራ የሚባል መጡ ከዛ በሩ ተከፈተልን ገባን ባለቤቱም ነበረች ያው ገባን ወጣን ይሄን ነው የማውቀው
- እርስዎ ወደቤቱ ሲጠገቡ ፖሊሶች ቀድመው ቤቶ ዙሪያ አልነበሩም እንዴ እርስዎ ለመታዘብ ሲሄዱ ?
- አይ ምን ሰዓት እንደመጡ አላውቅም ግን ያገኘኋቸው በር ላይ ነው ውጪ ላይ ሆነው በር ላይ ነው መንገዱ ላይ ነው ያገኘኋቸው
- እኮ እርስዎ ሲጠጉ ፖሊሶች ነበሩ በሩ ላይ?
- አዎ በር ላይ ነበሩ ወደላይ እወጣሁ ነው ወደ ቤተል እየወጣሁ ነበረ
- የፍ/ቤቱን ወረቀት ተነቦልናል ነው ያሉት እርስዎ አላነበቡትም?
- አዎ አነበበልኝ
- ምን ምን ይያዝ የሚለውን ነግሯችኋል?
- አዎ የጦር መሣሪያ የሚል የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እና ሰነዶች የሚል ተገኘ እንዲበረበር የሚል ነው የተፃፈው ልደታ ምድብ ፍ/ቤት የሚለውን ወረቀቱን አይቻለሁኝ በወቅቱ ላይ /ግልጽ ያልሆነ/ ሌላ አላየሁም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቤት ስትገቡ ግቢ ተከፈተላችሁ ቅድም ባለቤት ነች ካሏት ውጪ ሌላ ሰው አልነበረም እንዴ እዛ ቤት ውስጥ ?
- ሌላ የባለቤቷ እናት አሉ ቤት ስንገባ እሳቸውም ነበሩ ግን እሳቸው ምንም አላረጉም እዛ ልጇን ይዘው ቁጭ አሉ እዛው ላይ ሁለት ሰራተኞች ናቸው ሁለት ልጆች ይሁኑ እህቶቹ ምናምን አላውቅም ሁለቱም አሉ ውስጥ ቤት ውስጥ እነሱንም ወደዚህ ወደ እደጅ ይሁኑ ምናምን ብሏቸው ወደ ግቢ ያቆማቸው እና እኛ ወደ ግቢው ውስጥ እቤት ውስጥ ገባን
- እነዚህ እቃዎች የትጋ ነው የተገኙት ቅድም ያሏቸው የዘረዘሯቸው የትጋ ተገኙ ቤት ውስጥ?
- ቤት ውስጥ ሁሉን ነገር ነው የፈተሽነው ያው በተለያዩ ላይ ነው የቱ ላይ የሚለውን እረሳለሁ ግን ብዙም ስለነበሩ ወጥተው ተቆጥረው ምን ብለን
- እሺ ቆይ ለምሳሌ ሰነድ ያሏቸው መጽሃፍ መደርደሪያ ላይ ነው ?
- የሆነ እቃ ማስቀመጫዎች አሉ ካሴቶች እዛ ውስጥ ነው
- ካሴቱን የካሴት ማስቀመጫ ቦታ ሰነዶቹን ደግሞ መጽሃፍ መደርደሪያ ላይ ?
- አዎ የተወሰነ ሁሉንም ፊልገን የት እንዳለ ይሄኛው ይፈለጋል ሲሉን ወደዚጋ አርጉ እያልን ሌሎቹን ደግሞ እዛው ላይ ይሄ አይፈለግም ሲባል ሲቀመጥ ያለውን ነገር ያው እኛ ዝም ብለን ነው ቆመን የነበረው እያየን ነበረ እዚህ ላይ እያስቀመጡት ነው የነበረው በኋላ ላይ መጨረሻ ግን ሁላችንም ተሰባስበን ሳሎኑ ላይ ቁጭ ብለን ባለቤቱም እያለች እሷም የፈረመችበትን እኛም ፈርመንበት ነው መለያየት የማውቀው
- እነዚህ የቆጠሯቸው ሲዲዎች ሲዲ ካሴት 43 የቴፕ ካሴት 102 ብለዋል ቅድም ሰነዶቹ ላይ ፈርመናል በሰነዶቹ በራሳቸው ላይ ሲዲዎችስ ቆጠራችሁ እና ሲዲ 43 ቴፕ ካሴት 102 መሆኑን ቆጠራችሁ እንጂ በላያቸው ላይ አልፈረማችሁም አደል?
- አይ እነሱ ላይ አልፈረምንም ግን ቁጥራቸዉን አስቀምጠናል ቁጥራቸውን ያው እንዳለ እኛ አረጋግጠናል የተገኙት እነዚህ እነዚህ ናቸው በሚል ሌላም ቢጨመርበት ቢቀነስበትም እኛ ይሄን ያየነውን የፈረምንበት ነው ምናምን ብለን ተለያይተናል ሁላችንም
- እሺ ሲዲዎቹ ተከፍተው አላያችኋቸውም ውስጣቸው ምን እንደሆነ?
- አይ አላየንም
- ቴፕ ካሴቱንም አላያችሁም አላዳመጣችሁም?
- አላዳመጥንም

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሲዲዎቹ ስታዩዋቸው ከላይ የታተሙ ናቸው ስእል ምናምን አለባቸው አሁን ገበያ የሚሸጥ ሲዲ አለ ምን አይነት ነበር ይዘታቸው እነዚህ ካሴት የሚሏቸው ?
- አይ እኔ ያው እንትናቸው አይታይም እኛ ከፍተን አላየንም ያው እማስታውሰውን ከለራቸውን አሁን ባየው እለየው ነበረ ግን ከለራቸው ስላላየሁት አሁን እረሳዋለሁ ይሄ ነው ማለትም አይቻልም ማለትም እኔ ያን ጊዜው እና የአሁኑ ወይም የፊት ከለራቸው እነዚህ እነዚህ ናቸው ብዬ ልለያቸው እችል ነበር
- የሚሸጥ ሲዲ አይተዋል አደል ገበያ ላይ ?
- አይ የዚህ አይነት ሲዲ ሳይሆን ዝም ብሎ አልባሳት አላቸው ልበስ ልብስ አላቸው በልብስ ልብስ ነው የቋጠርናቸው እንጂ ከፍተን አላየንም
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ያጠናቀቃችሁት?
- ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ይሆናል በአካባቢው ነው የማውቀው ማለትም እኔም ስራ ስለነበረኝ አግጣሚ እዛ ስለዋልኩኝ በቃ ቸኩዬ ስለነበረ ሰዓቴን አላየሁም ግን ጨርሰን እንደሄድን ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ
- ስንተ ፖሊሶች ነበር ወደቤት ውስጥ የገቡት?
- ቁጥራቸውን አላውቀውም
- ማለት ታዛቢ ኖት እኮ እርስዎ ?
- እኛ ታዛቢ /ግልጽ ያልሆነ/ መሆናችን ነው እንጂ እነዚህ ፈታሾች ግን ምን ያህሉ እንደሆኑ በቃ ቁጥራቸውን አላስቀመጡም
- ሲገቡስ ፖሊሶች ምን ይዘው ነበር ቤት ውስጥ ሲገቡ?
- እስክሪፕቶ እና መመዝገቢያ ወረቀት
- እሺ እነዚህ ከየቦታው ያገኛችኋቸውን እቃዎች ከመፈራረማቸው በፊት የት ነው የሰበሰባችኋቸው ሳሎን?
- ምንድን ነው ድምጽ አልባ የሚሉት የሚባል አንድ
- ሳሎን ነው የሰበሰባችሁት ወረቀቱን አይሰማዎትም?
- እ?
- ይሄ ቅድም ከየቦታው የሰበሰባችኋቸውን እቃዎች የትነው አንድላይ ያጠራቀማችሁት የተፈራረማችሁት የት ነው ሳሎን ነው?
- ሳሎን ላይ ነው
- እቃው ከተሰበሰበ በኋላ ሚስት ነኝ ያለችው ሴትዮ ከእሳው ጋር ቪዲዮ አልተነሳችም?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አረ ቪዲዮ የሚባል ነገር የለም
- ፖሊሶች አላነሱም?
- እኔ እንጃ እኔ ትዝ አይለኝም ግን አሁን ልረሳው እችላለሁ ይመስለኛል ግን ሁላችንም ተሰባስበን ሳሎን ላይ አፈራረሙን ነው የማውቀው ካሜራ ምናምን እኔ እንጃ እኔ አሁን /ግልጽ ያልሆነ/
- ጨርሰናል የከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚአለ አቃቤ ሕግ
- ድጋሚ የለንም
- እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- እሺ 101ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል ለምስክርነት ነው የመጡት አይደል?
- አዎ
- እሺ የራሱን ስም ብቻ ይገልፃሉ የአባቱን ሳይጨምሩ ?
- ታጀበ
- እሺ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ በዝርዝሩ
- እሺ 101ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ታጀበ ቀርበዋል በክሱ ማስረጃ ዝርዝረ 156ኛ ላይ የተጠቀሱ ናቸው እሺ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ ታጀበ?
- ሺህ ስልጣን ሃጃማን
- እሺ ሌላ ሰው አለ ?
- የለም
- እሱ ላይ ብቻ ነው ?
- አዎ
- ሼህ ሱልጣን ሃጃማንን ያውቁታል እርስዎ?
- በዛን ቀን ያው ነበሩ እሳቸው
- አይ አሁን መለየት ይችላሉ ?
- እሞክራለሁ
- አሳቸውም ነበሩ ማለት ምን ሲደረግ ነው?

3003

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዛው ላይ ነበሩ በቦታው ለማለት ፈልጊ ነው
- እስቲ ተነስና ካለ አሳየን አሳይቷል በስምም እንደዚሁ ጠርቷል
- እስቲ ምን ሲደረግ ነው ያዩት ሼህ ሱልጣንን ሼህ ሱልጣን ምን ሲያደርጉ ነው ያዩት አጠር አርገው ይንገሩን?
- ያው ቢታቸው ሲበረበር
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ አቶ ታጀበ ቅድም ሲገልፁ ያው ቢታቸው ሲበረበር ብለዋል እና ይሄ ጊዜው መቼ ነው ቦታው የት ነበር እስቲ ከዚህ ጀምረው የት ነው ቦታው የሼህ ሱልጣን አሁን ያሏቸው አካባቢው የት ነው እርዎ በብርበራ ወቅት ነበርኩ ነው ያሉትአደል ?
- አዎ
- የት ነው ቦታው?
- ቦታው ኮልፌ ቀራንዮ
- እሺ የት አካባቢ ነው ልዩ መጠሪያ አለው?
- ካራ ቆሬ
- እስቲ እርስዎ እንዴት እዛ ተገኙምን አዩ ከመሄዶ በፊት ወደብርበራው ከመግባታችሁ በፊት ማን ምን አሳዮት ?
- ያው እዛው አካባቢ ነበረኩኝ ስራ ላይ ነበርኩ ፖሊሶቹ ለእንትትን ሲቀርቡ ይተባበሩኝ አሉኝ ተባበረኝ አሉኝ ያው ማለት የፍ/ቤት ትእዛዝም ነበረ የፍ/ቤት ትእዛዝ አይቼ ሄድኩኝ
- ተነበበሎት ወይስ አነበቡ እንዴት ነው?
- እ?
- አይቼ የፍ/ቤቱን ስም ማን አሳዮት?
- ፖሊስ ነዋ
- ምን ይላል?
- ያው የማለው የጦር መሣሪያ የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እና ከተጠረጠሩበት ተግባር ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰነዶች ካሉ ይያዙ የሚል ነገር ነው
- እሹ ይሄንን እርስዎ ካዩ በኋላ ወዴት ገባችሁ ማን ቤት ገባችሁ ?
- ያው እሳቸው አቶ ሼህ ሱልጣን ሃጂ አማን ጋር ሄድን ለእሳቸው ተነበበላቸው ወረቀቱ በር ላይ ነው ሳንገባ የተነበበላቸው ከዛ እንድንገባ ያው እሳቸው ፈቃደኛ ሆኑ ያው ገባን
- እሺ እቤት ከገባችሁ በኋላ ምን ምን አገኛችሁ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያገኘነው ያው 63 ሲ.ዲ. ካሴት 50 ቴፕ ካሴት 2 ፍላሽ 2 ላፕቶፕ አንድ ፎቶ ካሜራ እና 3 ማህተም ፎቶ ካሜራ
- እሺ. ሌላስ ምን ተገኘ ?
- ሌላው የተለያዩ በራሪ ወረቀቶች ነው ያገኘነው
- በራሪ ወረቀቶቹ ምንድን ነው ይዘታቸው ስለምን የሚያመለክቱ ናቸው ?
- በራሪ ወረቀቶች የሚሉት ድምፃችን ይሰማ ይላል ያው በብዛት ነው እነዚህ ያሉት
- ምን ያህል ይሆናል በራሪ ወረቀቱ ብዛት አለው?
- በብዛት አልተገለጠም
- እሺ. ሌላስ ምንድን ነው ይሄ ቅድም የተገኘው ሲ.ዲ. ምናምን ያሉት ስለሱ ይዘቱ ምን ያህል ነው አውቃችኋል ማወቅ ችላችኋል ወይም አይታችኋል ?
- አላየንም
- እሺ. ሌላስ የሚያስታውሱት ምንድን ነው ?
- ሌላ ያው ከበራሪ ወረቀቶች ላይ የአህበሽ ዘመቻ በሰላም ላይ ጥያቄያችን እስኪፈታ ተቃውሟችን በመስኪዳችን ይቀጥላል ነው የሚለው
- እነኚህ ቅድም የጠቀሷቸው ከተገኙ በኋላ ምን አረጋችሁ ስለመጠይቃችሁ ?
- እነዚህ ከተገኙ በኋላ ያው እሳቸውም ፈረሙ ያው እኛም ታዛቢዎች ፈረምን ያው እሳቸውም የፈረሙት በዛን ሰዓት አማርኛ አልችልም መፃፍ ነው ያሉት ልጃቸው በአማርኛ እንዲጽፍ ተደረገ እሳቸው ያው በአረብኛ እንዲፈርሙ ነው የተደረገው
- ስለዚህ እሳቸውም ያው ፈርመዋል
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- አቶ ታጀበ
- አቤት
- ብርበራ ሲካሄድ እርስዎ የት ጋ ነበሩ?
- አብረን ነበርን እዛው
- ማለት አብረን ሲሉ እቃዎቹ የት ነው የተገኙት የት የትጋ ተገኙ?
- እቃዎቹ ያው እቃዎቹ የተገኙበት መኝታ ቤትም አለ መስገጃ ቤትም ነው የተገኘው
- እነዚህ ሲዲ የቴፕ ካሴት ያሏቸው ቴፕ መደርደሪያ ሲዲ ማስቀመጫ ቦታ ላይ ነው የተገኙት?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መደርደሪያ ላይ ነው የተገኙት
- ዝም ብለው ከላይ ተቀምጠው ማለትነው ?
- አዎ
- ሌሎቹስ እነዚህ ፍላሽ ፎቶ ካሜራ ያሉትም እነሱም እንደዚሁ?
- አዎ
- አማርኛ አልሰማም አልጽፍም ነው አላነብም ነው ያለው?
- እሳቸው አልጽፍም ነው ያሉት
- ይሰማሉ ?
- አዎ
- እሺ የሚሰሙ ከሆነ ይቀጥሉ
- በነዚህ በሲዲ ቴፕ ካሴት ፍላሽ ባኋቸው ላይ ምልክት አረጋችሁ እንዴ ታዛቢዎቹ?
- ምልክት አላረግንም
- ከፍታችሁም አላያችኋቸውም ይዘታቸው ምን እንደሆነም አታውቁም?
- አዎ
- ሲዲው ምን አይነት ነው ከላዩ ላይ አዘጋጁ ፎቶ የተለጠፈበት ነገር የለውም ?
- የለውም
- ልሙጥነው ዝም ብሎ ?
- አዎ
- ሁሉም 63ቱም ?
- አዎ
- ቴፕ ካሴቱስ በላዩ ላይ ያለው ጽሁፍ ምንድን ነው አረብኛ ነው አማርኛ ነው ?
- የለውም እሱ
- ጽሁፍ የለውም?
- አዎ
- ስለዚህ ባዶ ይሁን በውስጡ ይኑረው የምታውቀው ነገር የለም?
- የለም
- ስትገቡ ስንት ፖሊስ ነበር ከታዛቢዎች ሌላ ወደ ቤት ውስጥ የገባው?
- ብዛታቸውን አላስታውስም
- እሺ ምን ይዘው ነበር ፖሊሶች ወደቤት ሲገቡ?

3006

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፖሊሶቹ መግሪያ ውስጥ ሲገቡ መግሪያ አልያዙም ዝም ብለው ነው የገቡት
- መግሪያ አልያዙም?
- አዎ ውጭ ላይ ያው ሌሎቹ ምናምን አሉ
- ቪዲዮ ካሜራ አልያዙም ነገር የሚቀርፁበት?
- አያስማም
- እቃው ከተገኘ በኋላ ፖሊሶቹ አልቀረፁትም እንደ ሼህ ሱልጣንን አስተምጠው ከእቃው ጋር አልቀረጿቸውም
- ፍተሻ በሚደረግበት ሰዓት መብራት ጠፍቶ ነበር አደል ?
- አዎ የተወሰነ ሰዓት ጠፍቶ ነበረ
- በማሽ ነበር አደል?
- እ?
- ማሾ አብርተው ነበር አደል በዛ እየተጠቀማችሁ ፍተሻ ሲደረግ የነበረው ?
- ያው እሳቸው ላይት አመጡ ያው በዛ ነው ስንጠቀም የነበረው
- እኮ ያው ማሾ ማለት ነው?
- እ?
- ያው ማሾ ብርሃን የሚያወጣ ነገር አመጡ አደል የሚያሳይ ነገር እሳቸው ነው ያመጡት?
- አዎ እሳቸው ናቸው
- እሺ ስንተ ሰዓት ነው የገባችሁት?
- እሩብ ጉዳይ ለአንድ
- ስንት ሰዓት አለቀ ፍተሻው?
- ሦስት ሰዓት ከምናምን ነው ያለቀው
- ትእዛዙ የፍ/ቤት ትእዛዝ ሲሉ ነበረ ቅድም ስንት ሰዓት ላይ ይፈተሽ ይላል ትእዛዙ?
- ከሁለት ሰዓት ተኩል እስከ አስራሁለት ሰዓት
- ማታ ነው ቀን ?
- ቀን
- ከቀኑ ሁለት ሰዓት ተኩለ?
- እስከ አስራሀለት ሰዓት
- ለምን በዛ ሰዓት እንደሚፈተሽ አታውቁም ዝም ብላችሁ ተባበሩን ስለተባላችሁ ነው የገባችሁት?

3007

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው ፖሊሱ በዛን ሰዓት ደወለ ደውሎ ያው ይፈተሽ ግቡ ተብለናል ምናምን አለን ያው ገባን የት እንደደወለ ግን አላውቅም
- የት እንደደወለ ወይ ማንን እንዳናገረ አያውቁም?
- አዎ
- እሺ ደውሎ ሲናገርም አልሰሙም እርስዎ ግቡ ተብለናል ከማለቱ ውጪ ደውሎ ሲናገርም አልሰሙም ?
- አልሰማሁም
- ይሄ እነዚህ ላፕቶፖች እና ሲዲዎች የልጆቹ ናቸው እኔ ኮምፒውተርም መክፈት አልችልም ሲሉ ነበር አደል?
- አይ እኔ አልሰማሁም አላሉም
- እሺ እነዚህ ተገኙ ያሏቸው ወረቀቶች የተገኙት ዘበኛ ቤት ውስጥነው አደል?
- ይደገምልኝ
- የዘበኛ ቤት ውስጥ ነው አደል ተገኙ ያሏቸው ወረቀቶች የተገኙት?
- አዎ ወረቀቶች እዛም ተገኙ ከመስገጃ ቦታም ተገኝተዋል የተለያየ ቦታ ነው የተገኙት
- እኮ ዘበኛ ቤት ውስጥ ነው የተገኙት?
- አዎ
- እሺ ዘበኛውንም በዛው ቀን ይዘውት ሄደዋል አደል ፖሊሶች እንፈልግሃለን ልናናግርህ ብለው ይዘውት ሄደዋል አደል?
- አዎ
- ታጀበ
- አቤት
- ቅድም በአቃቤ ሕግ ጥያቄ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አሳየኝ ብሎ ነበረ ልክ ነኝ?
- አዎ
- ምን ይላል የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ከየት ፍ/ቤት የወጣ ነው ከከፍተኛ ፍ/ቤት ነው ከኮልፌ ነው ?
- ከፌደራል ፍ/ቤት ነው
- ከፌደራል የት ኮልፌ ነው ከፍተኛ ፍ/ቤት
- ከፍተኛ
- እሺ ምን ነበረ የሚለው ለማስታወስ ያህል የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ካዩት?

3008

SDS4

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ሲመሰክሩ ያሉት በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሰረት እንዲያዝ የታዘዘው የጦር መሣሪያ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እና የመሳሰሉት ናቸው ብለው ነበረ ቅድም ሲመሰክሩ ደግሞ እነዚህ የተያዙት የሲዲ ካሴቶች አላየኋቸውም ብለዋል አደል ይዘታቸውን?
- ይዘታቸው በውስጡ ምን እንዳለ አላየሁም አዎ
- የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ደግሞ የሚለው ከተጠረጠሩበት ወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው ከሆነ ይያዝ ነው የሚለው አደለም?
- አዎ
- እናንተ እነዚህ የተያዙት እቃዎች ከዛጋር ግንኙነት ይኑራቸው አይኑራቸው ሳታውቁ ነው የያዛችሁት አደል?
- ያው የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ማለት እኮ
- አደለም ከይዘታቸው ጋር ነው የጠየቅኩትበቃ አሁን ይሄ ግልጽ እኮ ነው ያዩት ነገር የለም ስለዚህ ስለ እንትኑ ጉዳይ ያዩት ነገር ከሌለ አያውቁም ማለት ነው እንደሱ ከተረዳህልኝ
- አቶ ታጀበ ቤት ስትገቡ ሼህ ሱልጣን በር ላይ አስገቧችሁ ሌላ ማን ነበረ የቤተሰብ አባል ቤት ውስጥ?
- ቤት ውስጥ አንድ ሰራተኛም ነበረች ሌሎች ልጆች ብዙአሉ እና ባለቤታቸውም መሰለችኝ ነበረች እና ልጃቸው
- ኦኬ ብርበራ እያካዳችሁ ከውጭ የገባ ሰው አለ በመሃል ?
- የገባ ሰው የለም ከውጪ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ካለ
- ድጋሚ የለንም
- እሺ ጨርሰሃል እናመሰግናለን
- የተከበረው ፍ/ቤት አንድ ምስክር ስላለ በችሎት ቀርቦ ተመዝግቦ እንዲሰናበት ከዛ ባለፈ ሁለት ምስክሮች
- ስሙ ማን ነው እስቲ ይሄኛው ?
- እሱ ሁሴን ቂጤሳ 67ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለው ነው
- የአቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ሰይድ እና /የማይሰማ/ ተመዝግበው እንዲሰናበቱ ነው ከሌሎቹ ተመሳሳይ ስለሆነ በችሎት እንዲሰናበቱ ነው

3009

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አክብረው ፍትህ ለማገዝ ስለመጡ በፍ/ቤቱ ስም እናመሰግናለን አቃቤ ሕግ ከሌሎች ከመሰከሩት ምስክሮች ጋር ተመሳሳይ ናቸው ምስክርነታቸውን አልፈልግም ስላሉ አሰናብተኖታል መሄድ ይችላሉ
- 115ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያሉ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ፖሊስ ከዚህ ቀደም በነበሩ ቀጠሮዎች በተደጋጋሚ ጊዜ በአድራሻ
- መቶ ስንት?
- 105ኛ እና 115ኛ
- እሺ?
- ፖሊስ በተደጋጋሚ ጊዜ በአድራሻቸው ሄዶ ሊያገኛቸው ስላልቻለ ይሄንኑ ማረጋገጫ በ5/10/2005 በተፃፈ ደብዳቤ ማረጋገጫ አቅርበዋል በመሆኑም እነዚህ ምስክሮች ከአሁን በኋላ ልናገኛቸው የማንችል መሆኑ በማረጋገጫ ጭምር የተረጋገጠ ስለሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 145 በሚያዘው መሰረት ለፖሊስ አይ ኦሪጅናሉ አለ ስለዚህ ለፖሊስ የሰጡት በወንጀለኛ መቅጫ 5 መሰረት ለፖሊስ የሰጡት የምስክርነት ቃል ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር ተያይዞ እንዲታይልን ነው የምናመለክተው ሌቹን በተመለከተ ያው የተከበረው ፍ/ቤትም በሚያውቀው መልኩ እንደሚታወቀው ከጥር ወር ጀምሮ ለተከታታይ ወራት በነበሩ ቀጠሮዎች በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ ከተጠቀሱ 197 ምስክሮች ዛሬ ከተሰሙት ጨምሮ 101 በችሎት ቀርበው የተሰሙ ናቸው የቀሩት ከ90 በላይ የሆኑት ምስክሮች እስከዛሬ ቀርበው ከተሰሙ ምስክሮች የተለየ የሚያስረዱት ጭብጥ የለም በመሆኑም ከዚህ በኋላ እነዚህን ምስክሮች መስማት የተከሳሾችን ቀጠሮ ማራዘምም ሆነ የፍ/ቤትንም ሆነ የአቃቤ ሕግን የስራ ጊዜ ከመሻማት ባለፈ ከዚህ የተለየ የሚያረጋግጠው ፍትህ ባለመኖሩ እነዚህ ምስክሮች በበተሰሙ ምስክሮች በቂ ሆኖ በዚሁ እንዲሰናበቱልን እናመለክተለን ከዚህ ቀጥሎ ያው በማስረጃ ዝርዝር በተጠቀሰው ቅደም ተከተል መሰረት ከጥር ወር ጀምሮ ለ6 ወራትን የወሰደው የምስክሮች መሰማት ሂደት በአቃቤ ሕግ በኩል በዚሁ ተጠናቋል በቀጣይ በክስ ማመልከቻ የጠቀስነውን የቪዲዮ ማስረጃ ለማሰማት እንድንቀጥል ነው የምናመለክተው ይህን በተመለከተ ያው ፍ/ቤቱ የሚያስፈልጋቸውን ማቴሪያሎች አሟልቶ በሚይዘው ቀጠሮ በአጭር ቀን ውስጥ የቪዲዮ ማስረጃውን ማቅረብ ይችላል አቃቤ ሕግ
- 145 የስነስርዓት ሕጉን መሰረት በማድረግ የቀረበውን ጥያቄ አስመልክቶ ማለት 105ኛ እና 115ኛ ምስክርን አስመልክቶ ነው በቀጥታ

300 5056

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ በጠበቆች በኩል በፖሊስ የተሰማው የምስክር ቃል ይያያዝልኝ ተብሎ በቀረበው ላይ አስተያየት
- መቃወሚያ አለን
- እሺ መቃወሚያ
- አቃቤ ሕግ አሁን እየጠየቁ ያሉት ፖሊስጋ የተሰጠ ቃል ይያያዝልን የሚሉነው ፖሊስጋ የተሰጠ ቃል እራሱን ችሎ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም የስነስርዓት ሕጉ 145 ንዑስ 2 በግልጽ እንደሚያስቀምጠው ፖሊስጋ የተሰጠ ቃል ማስረጃ ሆኖ ፍ/ቤት የሚቀርበው ለኢምፒችመንት ፐርፐዝ ነው ቀርበው የመሰከረ ምስክርን ለማስተባበል አላማ ብቻ ነው ስለዚህ አሁን እየተጠየቀ ያለው እራሱን የቻለ ማስረጃ ሆኖ እንዲቀርብ የቀረበ ጥያቄ በመሆኑ ይህ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው በቀዳሚ ምርመራየተሰጠ ቃልን እንጂ ፖሊስጋ የተሰጠ ቃልም ስላልሆነ ምናልባት 105ኛ እና 115ኛ ተብሎ የተገለፁት ምስክሮች የኔን ደምበኛ የሚመለከቱ ከሆነ ይህ የአቃቤ ሕግ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግልን እንጠይቃለን
- መልስ እንስጥ የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት የ28ኛ ተከሳሽ ያቀረቡት መቃወሚያ ከዛ የተለየ የለውም የእኛን መቃወሚያ /ግልጽ ያልሆነ/
- ሌሎችም ተከሳሾች ጠበቆች መቃወሚያ ነው ይህ መዝገብ ?
- አዎ የኛም እንደሆነ ይመዝገብልን
- ኦኬ እሺ የተለየ አለ ከዚህ ውጪ ?
- የለንም
- እሺ ምላሽ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- አሁን ስለ ይዘት ውስጥ ሳትገቡ መያያዝ አለመያያዙን
- አዎ መያያዝ አለመያያዙን በተመለከተ ቅድም የጠቀስነው የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 145 በፖሊስ ምርመራ ጊዜ የተሰጠ ቃል ለፍ/ቤት ሊቀርብ እንደሚችል የተቀመጠ ስነስርዓት ነው ይሄ ስነስርዓት የተቀመጠበት ዋነኛው አላማ አሁን የሚያጋጥመው አይነት ነገሮች ሲያጋጥሙ እነዚህን ጉዳዮች ለመዳኘት ሆነ ተብሎ በሕግ አውጪው የተደነገገ ድንጋጌ ነው ድንጋጌው በግልጽ እንደሚያዘው የተከበሩ የ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃ እንዳሉት ሳይሆን ንዑስ ቁጥር ሁለትም ቢሆን አቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሹ በፖሊስ

3011

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ምርመራ ጊዜ የተሰጠን ቃል ለፍ/ቤት እንዲቀርብ ያመለክታል ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ካየ በኋላ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ ሲያምን ለተከሳሾች እንዲደርስ አርጎ ተከሳሾች ወይም የቀረበበት ወይም አቃቤ ሕግ እንዲያስተባብሉ ያረጋል ይላል እንጂ ኢንፒችመንት የሚል ትርጉም በፍፁም የለውም በትርጉም ሰበብ ደግሞ አዲስ ሕግ መፍጠር እንደማይቻል ነው ድንጋጌ ስለሆነ በዚህ መልኩ የቀረበው ክርክር ውድቅ ሊሆን ይገባል ከዛ ባለፈ ግን እኛ ከ90 በላይ ምስክሮችን እዚህ ችሎት አቅርበን አላሰማንም እየጠየቅንም ያለነው የነዚህን የዘጠና ምስክሮች ቃል እንዲያያዝ አይደለም የነዚህ የሁለት ምስክሮች ቃል በተለየ ሁኔታ እንዲያዝ የተፈለገው ፍ/ቤቱም ሆነ ተከሳሾች ቢያዩት ለፍትህ ይጠቅማል ተብሎ ስለታመነበት የሁለት ምስክሮች ቃል ከ90 ምስክሮች ቃል የሁለት ምስክሮች ቃል ተመርጦ የቀረበው እና የተጋነነም ነገር አይደለም የጠየቅነው ስነስርዓት ሕጉ ይሄን እንዲዳኝ ነው የተፈጠረው 145 ሌላው ጠበቃው ያነሱት በቀዳሚ ምርመራ ጊዜ የተሰጠ ቃል ነው የሚያያዘው በሚለው ይሄን የሚዳኝ እራሱን የቻለ ሕግ አለ እሱ 144 ምስክር በሞተ ወይም በጠፋ ጊዜ የሚል ፕሪኮንዲሽን አስቀምጦ በፕሪሊሚሪ ኢንኳሪ የተደረጉ የተሰጡ ምስክርነቶች ወይም ሌሎች ነገሮች ሊቀርቡ ይችላሉ ዋናውን ጉዳይ በሚያየው ፍ/ቤት እኛ የጠየቅነው አሁን በፖሊስ ምርመራ ወቅት የተሰጠውን ምስክርነት ፍ/ቤቱ እንዲመለከተው እና ለተከሳሽ ደርሶ እንዲያስተባብሉትነው ይሄም 145 መሰረት አድርገን ነው የጠየቅነው ሕግን መሰረት ያረገ ጥያቄ ስለሆነ አግባብነት ያለው አደለም የተከሳሾች መቃወሚያ

የቀረበውን በ145 በፖሊስ የተሰማ ምስክር ይያያዝ አይያያዝም በተመለከተ ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኝ የቀረበውን ክርክር ተመልክቶ ብይን ሰጥቷል በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት 145 እንደሚለው ለፖሊስ የተሰጠው ቃል ፍ/ቤቱ ሊመለከተው ይችላል ከዛም አልፎ ለፍትህ የሚጠቅም መስሎ ከታየው ለተከራካሪ ወገን ደርሶ አስተያየት እንዲሰጡ ይደረጋልነው የሚለው ሕጉ ከዚህ የተለየ አይልም ሕጉ ይሄ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን መተርጎም ካልሆነ ሕጉ አሁን የሚለው ይሄንኑ ነው ወደ ሌላ ነገር ስንመለስ አሁን ይያያዝ ተብሎ የቀረበው ምስክሩን ማግኘት አልቻልንም ማግኘት አለመቻላችንም የፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ የታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት ቁጥር ያለው ደብዳቤ በሰኔ 5 ቀን 2005 በፃፈው ደብዳቤ ምስክሮችን በስም ጠቅሶ ገልጿል አቃቤ ሕግ አሁን ያቀረበው እሱን ነው ምስክሮቹ መገኘት ካልተቻሉ 145 መቼ ነው ስራ ላይ የሚውለው የሚለውን ስንመለከት ምስክሮቹ ማግኘት ማግኘት የማይቻል ከሆነ ፍ/ቤቱ እሱን ተቀብሎ ከሌላ ወገን ማድረስ የሚል በዛ ወገን ተነስቷል በዚህ ወገን ደግሞ ይሄ ምስክሮቹን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለማስተባበል ወይ ለምፒችመንት ብቻ እንጂ ብቻውን እራሱን ችሎ ለማስረጃነት አይቀርብም የሚለውን ስንመለከት 1ኛ ይ.ሄ. ኢምፒችመንት የሚለው በግልጽ ሕጉ ላይ የተቀመጠ ነገር የለም ፍ/ቤቱ ይመለከተዋል ሌላ ወገን አስተያየት ይሰጠዋል ነው ስለዚህ ኢምፒችመንት የሚለውን ነገር በግልጽ /ግልጽ ያልሆነ/ በአንድ በኩል በሌላ ደግሞ እንደዚህ አይነት እንዳይቀርብ በግልጽ እስካልተከለከለ ድረስ አጠቃላይ ያለው የማስረጃ ደምብም እንደዚህ አይነት ማስረጃ አይቀርብም ብሎ እስካልከለከለ ድረስ አይቀርብም ተብሎ የሚከለከልበት የሕግ መሰረት የለውም 145 የተቀመጠው ይሄንኑ ለማሳየት ነው እንጂ መከልከል ቢፈልግ በግልጽ እንደዚህ አይነት ማስረጃ አይቀርብም ብሎ ማስቀመጥ ስለሚችል ለኢምፒችመንት እንጂ አይቀርብም የሚለው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም ስለዚህ አሁን በስም የተጠቀሱት ሁለት ምስክሮች የአቶ ኡመር እና ሰይድ የተባሉት በማስረጃ ዝርዝሩ 105ኛው እና 115ኛ ላይ የተጠቀሱት የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ለፖሊስ የሰጡት ቃል ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ፍ/ቤቱ ስለዚህ ይቅረብ ከዛ በኋላ ያለውን ፍ/ቤቱ ተመልክቶ አስተያየት መስጠት አለባቸው የለባቸውም የሚለውን አይቶ የሚወሰን ይሆናል እሺ አልጨረስንም በዚሁ ለመጨረስ ያክል አሁን የቀረበው ትንሽ ብዛት ያለው ስለሆነ አሁኑኑ አይተን አስተያየት ስጡበት ለማለት አይደርስም ስለዚህ ሌላ ኤግዚቢቶችን መስማት በሚያዘው ቀጠሮ እኛ ተመልክተን በዛኑ ቀን ለአስተያየት ትእዛዝ ብንሰጥ ነው የሚሻለው ስለዚህ ዛሬ ገና እዚህ ቁጭ ብለን ብናነብ እረጅም ስለሆነ ማለት ነው ለፍትህ አስፈላጊውን አስተያየት ስጡ የሚባሉ ከሆነ ያኔ ትእዛዝ የምንሰጥ ይሆናል ስለዚህ ማስረጃ ያው በዚህ ተጠናቋል ስለተባለ የሰው መስማቱ በዚህ ተጠናቋል የቀሩ የሚሰሙ ኦዲዮ ቪዥዋል እና ቪዥዋል የሆኑ ማስረጃዎችን ለመመልከት በፍ/ቤቱም በኩል አስፈላጊ ኤል ሲዲ እና ሌሎቹ ተሟልቶ መታየት ስላለባቸው ለሰኔ 13 ቀን 2005 ጀምሮ አስቀድሞ በተያዘው ቀጠሮ እስኪያልቅ ድረስ እንሰማለን ማለት ነው ስለዚህ ሰኔ 13 ቀን 3፡30 እዚሁ እንገናኛለን ማስረጃዎች የሚሰሙ ቪዲዮዎች ተደራጅተው በቀጠሮ ቀን እንዲቀርቡ ለፍ/ቤት ቀን ከዛ ቀን አስቀድመው በቂ ኮፒ ከመዝገብ ጋር እንዲያያዝ እ ተመልክተን እዚህ ችሎት ላይ እንድናይ ተጨማሪ ትእዛዝ ተሰጥቷል አቃቤ ሕግ ከቀጠሮ ቀን በፊት ያዘጋጅ ይሄንን የፍ/ቤቱ አስተዳደርም ያው የሚሰሙበት እና የሚታዩበትን ማቴሪያል አስቀድሞ እንዲያዘጋጅ በዚሁ ታዟል የዚህን መዝገብ በዚሁ ጨርሰናል፡፡

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ሰኔ 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ፡- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድም አገኝ ዘረሰናይ ምስግና ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርበዋል

ተከሳሾች፡- እነአቡበከር አህመድ ከማረሚያ ቤት ሁሉም ቀርበዋል የተከሳሽ ጠበቆች ባህሩ መካንጋ ሃሰን ሁሴን አህመድ ጀማል ቀርበዋል ሌሎቹ አልቀረቡም

- መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው አቃቤ ሕግ የቪዲዮ ማስረጃ ቀደም ብሎ አያይዞ በፍ/ቤቱ ዛሬ ለመመልከት ነበር ሆኖም ግን እስከ አሁን ባለው ጊዜ አቃቤ ሕግ የቪዲዮ ማስረጃውን አቅርቦ እዚህ የተያያዘ ነገር የለም ስለዚህ አቃቤ ሕግ የምታነሱት ነገር ካለ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን በክሳችን ላይ የጠቀስናቸው ሲዲዎች ብዛታቸው ከ30 በላይ የሚሆን ነው ዛሬ በክፊል አስራስድስቱን ሲዲዎች ኮፒ አድርገን የፍ/ቤቱንም ድርሻ ኮፒ አድርገን የደረሰልንን ወደ 16 ሲዲ አቅርበናል ያው ጊዜው በፈቀደልን መጠን እናሰማለን ቀሪዎቹንም ኮፒ አድርገን እስከ ነገ ይጨርሱልናል ብለን እንገምታለን ስለሆነም አጠቃለን በችሎቱ የታዩትን የድምጽ ከምስል ማስረጃዎች ለችሎቱ እናቀርባለን ባለማድረሳችን ይቅርታ እንጠይቃለን ማሰማቱ ምናልባት እንደየ
- ማሰማቱን አደለም አሁን አልተያያዙም እዚህ ማስረጃው መያያዝ አለበት ፍ/ቤትጋ ማለት ነው ስለዚህ መረጋገጥም አለበት አሁን ያልተረጋገጠ ማስረጃ ነው እያላችሁን ያላችሁት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እናንተ ምናልባት 16ቱን መርጣችሁ ልታሳዩ የፈለጋችሁትን ነው የነገራችሁን ስለዚህ አሁን ቀሪዎቹን መቼ ነው የምታጠቃልለው ?

- አሁን የተከበረው ችሎት የድምጽ ከምስል ማስረጃውን በችሎት እናቀርባለን ነው በዚህ በችሎት እናቀርባለን በሚልነው በማስረጃ ዝርዝራችንም ያቀረብነው ነገር ግን ፍ/ቤቱ ማስረጃው ይድረሰኝ በማለቱ ምክንያት በአጭር ጊዜም ስለነበረ ሊደርስልን
- ባለመቻሉ ነው የተወሰኑትን የደረሱልንን ይዘን መጥተናል አሁንም እያደረጉ ነው ነገ ከቻልን ነገ ጠዋት አጠቃለን ይዘን ለመምጣት እንሞክራለን ነገር ግን በሬጅስትራር በኩል ለማረጋገጥም በተመሳሳይ የጊዜ እጥረት ስለነበረብን ነው አሁንም ፍ/ቤቱ እሚፈቅድልን ከሆነ ይሄን እያሳየን ያንን አረጋግጠን ጠዋት ወይም ደግሞ ሰኞ ከነማረጋገጫው አንድ ላይ ይዘን እንድንቀርብ እንዲፈቅድልን ነው ማለት ዛሬ ያቀረብናቸው እና እስከ አሁን ያልተረጋገጡት ወይም ያልተመሳከሩትን አስመልክቶ ኦሪጅናሉ የእኛ ቀሪው ማለት ነው ችሎቱጋ ሆነው በሬጅስትራር ተረጋግጦ እሚመለስልን ቢሆን በእኛ በኩል ነገሩን ያስኬድልናል ብለን እናምናለን
- ይሄን መሰረት አድርገን አቃቤ ሕግ ላይ ያቀረቡትን መሰረት አድርገን ትእዛዝ ሰጥተናል

ትእዛዝ

- አቃቤ ሕግ ቀደም ብሎ ማስረጃውን ማያያዝ ነበረባቸው እንግዲህ ባለው የጊዜ እጥረት ከብዛቱ አንፃር አጠቃለው አላቀረቡም እሱ ሳይቀርብ ደግሞ ማየት በጀመሩ ትክክለኛ ተረጋግጦ ማስረጃ እና እሱ ተረጋግጦ ነው በፍ/ቤት በኩል መታየት የሚጀምረው ስለዚህ አቃቤ ሕግ እሱን በሬጅስትራር በኩል በዛሬው እለት እና ነገ አጠቃለው ይሆነናል የሚሉትን ማስረጃ ያቅርቡ ሰኞ ሦስት ሰዓት ተኩል በተለመደው እዚሁ እንጀምራለን ማለት ነው ሰኞ ማለት ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም. ነው ካሴቱ ወይም ቪዲዮ በተለይ ቪዲዮ የሚቀርበው በእያንዳንዱ በትራክ ከነመግለጫው ነው የሚቀርበው እሱን ጨምራችሁ ማን ምን ሊያስረዳ እንደሚችል ተዘርዝሮ እንደሆነ እሱን በማጠናከር ከዛ ውጪ ምን ሊያስረዳላችሁ እንደሚችል በትራክ በትራክ ከፋፍላችሁ ጊዜ ለማሳጠር በዛ መንገድ አያይዙት ይረጋገጥ።

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ፡- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድም አገኝ ቴዎድሮስ ጌታቸው ቀርበዋል

ተከሳሾች፡- እነአቡበከር አህመድ የቀረበ ተከሳሽ አለ ሁሉም ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል

ጠበቆች ባህሩ መካንጋ ፣ መሃመድ አብደላ፣አህመድ ጀማል ፣አዲስ መሃመድ ቀርበዋል ሌሎቹ አልቀረቡም

- መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው አቃቤ ሕግ የ ቪዲዮ ማስረጃ ለማሰማት ነበር በዚህም መሰረት የቪዲዮ ማስረጃው ቀርቧል ስለዚህ መስማት እንቀጥላለን ማለት ነው ስለዚህ አካሄዱ ምንድን ነው የሚሆነው አቃቤ ሕግ ሲዲያችሁ ላይ ያለውን ሊሰማ የምትፈልጉትን ትራክ በእያንዳንዱ ላይ መግለጫ እየሰጣችሁ እሱን እየሰማን ነው የምንሄደው አንድ ጊዜ ከሆነ ሊያዝ አይችልም ስለዚህ በትራክ በትራኩ ላይ ሊያስረዳላችሁ የሚችለውን መግለጫ ትናገራላችሁ ሲዲውን እናያለን እንቀጥላለን በዚህ መንገድ ነው የምንሄደው ወይ በትራክ ወይ ሙሉ ሲዲ ከሆነ ሙሉ ሲዲ በዛ መንገድ ይቀርባል ማለት ነው ከትራኳ ወይም ከሙሉ ሲዲው ግን አይቀነስም ከትራክ አቃቤ ሕግ ሊፈቀድለት የሚችለው ከትራክ ወይም ከሙሉ ሲዲ እንዳለ እንጂ ሙሉ ሲዲ ግማሽ ከተሰማ በኋላ አይ እዚህ ድረስ ይበቃኛል ምናምን የሚልነገር አይኖርም ይሄን አስባችሁ ነው የምትሄዱት ስለዚህ አሁን እንቀጥላለን

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን በቅድሚያ የሚሰማው ሲዲ እርእሱ የጥፋት ነጋሪት በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ ሲጕሰም በሚል እርእስ የተዘጋጀ ነው አሁን እዚህ ከቀረቡ ተከሳሾች የተወሰኑት በኮሚቴ አባልነት ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ጭምር የተካተቱበት ነው በብርበራ ከተከሳሾቹ የተያዘ ሲሆን ይዘቱ አጠቃላይ ይዘቱ እስልምናን በኢትዮጵያ የነበሩ የቀደሙ መንግስታት እንዴት አርገው ይጨቁኑ እንደነበረ አጠቃላይ ታሪካዊ ዳራውን የሚያሳይ ሲሆን ቀጥሎም የአሁኑ መንግስትም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ እንዴት እስልምናን በተቀነባበረ መልኩ እያጠቃ እንዳለ በሲዲው አገላለጽ የእስልምና መሪዎች በምን መልኩ እንደሚሾሙ በፖለቲ ምክንያት ወደ ስልጣን እንደሚመጡ እና ሙስሊሙ ላይ በጣም የተጋነነ የመብት ጭቆና እየደረሰበት መሆኑን በመግለጽ ተከሳሾች ለቅስቀሳ ሲጠቀሙበት ከነበረው ሲዲ አንደኛው ነው
- አቤት
- መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያ አይኖርም አሁን እናንተ ሊኖራችሁ የሚችለው ምንድን ነው መግለጫው የሰጡት መግለጫ ግልጽ ካልሆነ እሱ ነው ግልጽ ይሁን ነው እንጂ አሁን ማስረጃ ነው ብለን የምንመለከተው እሱ መጨረሻ ላይ የናንተ ይኖራችኋል ጊዜ እዛ ላይ እንትን የምትሉት ነው እንጂ አሁን መግለጫው ነው ግልጽ ካልሆናችሁ መግለጫው ላይ ነው
- አዎ መግለጫው ላይ እኮ ነው
- እኮ መግለጫው ላይ ግልጽ አደለም ከተባለ ግልጽ ያድርጉ
- ከተከሳሾች የተገኘ በሚል በጥቅሉ ነው የተቀመጠው ከሁሉም ተከሳሽ ማለት ነው አሁን የሚቀርበው ሲዲ ወይስ ከተከሳሾች ውስጥ ከእከሌ ተብሎ ሳይገለጽ በጥቅሉ ከተከሳሾች የሚለው አሳሳች ነው ወይም ከሁሉም ተከሳሾች የተገኘ የሚታየው አንድ ሲዲ ከሆነ በማስረጃ ዝርዝር ውስጥ የትኛው ላይ እንደወደቀ በብርበራ የተገኙ ትብሎ ስለተገለፀ ግልጽ በሆነ መንገድ ቢቀርብ ለማለት ነው
- እሺ ይሄ ብቻ ነው
- እሺ አቃቤ ሕግ ግልጽ አድርጉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ያው ክሱ ሲቀርብ በክስ የማስረጃ ዝርዝር ላይ ለተከሳሾችም ከደረሰው ላይ ከእያንዳንዱ ተከሳሽ ምን ያህል ሲዲ እንደተያዘ አስቀድመን ገልፀናል አሁን ይሄኛው ሲዲ ከብዙ ተከሳሾች ነው የተያዘው ለይተን እያንዳንዱን ተከሳሽ እነዚህ እነዚህ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲዲዎች ተብሎ በተከሳሽ ደረጃ አልተለየም ግን ቀድመን ስጥተናችዋል ምን ያህል ሲዲ ከእያንዳንዱ ተከሳሽ እንደተያዘ ያልተያዘባቸውም አሉ የመረጥናቸው በክሱ ገጽ ከገጽ 40 ጀምሮ ድምጽ ከምስል ማስረጃውን ለምሳሌ ከ1ኛ አንድ ብቻ እንደተያዘ ከ2ኛ ተከሳሽ 7 እየተባለ ከሁሉም ተጠቅሷል እና በርካታ ተከሳሾች ላይ ነው የተያዘው በተከሳሽ ደረጃ በዚህ መልኩ ነው ቀድመን ያቀረብነው ስለሆነ

- /ግልጽ ያልሆነ/ ማን ማን ላይነው?
- ያው ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ክሱም እንደሚያስረዳው ያቀረብነው ክስ ኮንስፓይሬሲ ነው የወንጀል አድማ ስምምነት አርገዋል ነው ሁሉም ተከሳሾች ላይነው ማስረጃው እያንዳንዷ ማስረጃ አሁን ለምሳሌ አሁን ይሄ የሚታየው ሲዲ ከ3ኛ ተከሳሽ ከያሲን ኑሩ የተያዘ ነው ግን ብዙ ተከሳሾች ላይ ይሄ ተመሳሳይ ሲዲ ተገኝቷል ነው ሁሉም ይጠቀሙበት የነበረ ስለሆነ ስለዚህ እያንዳንዷን ማስረጃ ልክ ሰነድ ማስረጃ ለሁሉም ይድረሳቸው እንደተባለ ሁሉ ይሄኛውም ሲዲሁሉንም የሚመለከት ነው ኮንስፓይሬሲ ስለሆነ እንደቲም እንደኮሚቴ ኮሌክቲቭሊ ነው አክት ሲያረጉ የነበረው ስለዚህ ሁሉንም የሚመለከት ነው ኮንስፓይሬሲ ነው ይሄን እስፔስፊክ ግን ይሄን ሲዲ በተመለከተ 3ኛ ተከሳሽጋ ነው የተያዘው ለምሳሌ አህመዲን ጋር ተገኝቷል ይሄ ሲዲ ሌሎችም የተያዘባቸው አሉ ይሄ ሲዲ በኋላ መግለጽ ካስፈለገ የምንገልጽ ይሆናል በእረፍት ሰዓት ቼክ አርገን ግን ማስረጃውን በተመለከተ ግን ሁሉም ነው የሚመለከተው ሁሉም ነው መልስ የሚሰጡበት ሁሉንም እንደኮንስፓይሬሲ ነው
- እሺ ቀጥሉ
- የተከበረው ፍ/ቤት
- ግልጽ ስለሆነ ግልጽ አደረጉ በማን ላይ እንደሚያስረዳ በሁሉም ላይ የተያዘው ከ3ኛ ተከሳሽ ይሄኛው
- አዎ 3ኛ ተከሳሽ የተያዙ ሲዲዎች እንዳሉ ተመልሰውልኛል ምንም የቀረ የለም
- እኮ ይኸውላችሁ አሁን እሱን አላችሁ እናንተ ላይ ካለ አሁን አቃቤ ሕግ እኮ እውነት ይሁን ውሸት ይሁን እኛ ማየት ብቻ ነው አሁን የቀረ ይኑር አይኑር እሱን እንደገና ማረጋገጡ ሌላ ቦታ ልንሄድ ነው ስለዚህ አሁን እኛ ማየት ብቻ ነው በኋላ ነው የሚመዘነው ቀጥሉ
- የእስላማዊ መንግስትም ከመቋቋሙ በፊትም የነበሩ እስላማዊ ሱልጣኔቶች የሆኑ መንግስታቶች ነበሩ እነዚህ መንግስታቶች ጋር የነበረው ምኝነት አንድም በራሱ /ግለጽ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያልሆነ/ በተቃውሞ ሲንኮታኮት ስልጣን ሰለሞናዊ ነኝ በሚሉት አፈታሪካውያን እጅ ወደቀ በ1270 ክርስትና የሚገለፀው ለሙስሊሙ በሚኖር ጥላቻ እንደሆነ የሚያስበው የሰለሞናውያን መንግስት በርካታ ግፍን ፈፀመ ሙስሊሙን ማዳከም መስኪዶችን ማቃጠል በክፈፉ ዘመቻ ሺዎችን ማረድ ለሰለሞናውያን ገድል ነበር በ1314 የነገሰው አምደ ጽዮን ከሱም በኋላ ተከትለው የነገሱት እነዘራያቆብ በሙሉ ሙሲሙን ሕዝብ ፈጁት መስኪድ መስራትንም ከለከሉ ወቅቱ ለሙስሊሞች ጨለመ ከሰለሞናዊ ስርወ መንግስት መቋቋም በፊትም የነበሩ እስላማዊ ሱልጣኔቶች የሆኑ መንግስታቶች ነበሩ እነዚህ መንግስታቶች ጋር የነበረው ሞኝነት አንድም /ግልጽ ያልሆነ/ ሙስሊሞች ላይ የሃይማኖት ነፃነት እንዳይኖራቸው ሚስጥር መስራት እንዳይችሉ ሰለፊዎችን ማሰቃየት መስኪዶችን ማፈረስ ሙስሊሙ ኢምፖርታንት የሚባሉ ኢኮኖሚካሊ ያሉት የኢኮኖሚ ኤርያዎችን መንጠቅ /ግልጽያልሆነ/ ሉ እንደ እስትራቴጂ ከግዛቱ ውጪ ያሉ ሌሎች የእስላማዊ ሱልጣኔቶች ጋራ የነበረው እሪአክሽን በኃይል በመደፍጠጥ የራሱ አካል የማድረግ ነው ይህንን ሲያደርግ በአንድ ጊዜ አደለም ሙሉ ለሙሉ መደፍጠጥ የሚሰራው መጀመሪያ እናስከብርና ኢምፖርታንት የሚባለውን ኢኮኖሚያቸውን መቆጣጠር መስኪዶችን ማፍረስ እና በቤተ ክርስትያን መተካት እንዲሁ እያለ ይቀጥልና ሙሉ ለሙሉ እስላም የሚባለው /ግልጽ ያልሆነ/ እና ሱልጣኔቶቹን ተራውን ሕዝብ ከእስልምና የማውጣት የረቀቀ ፖሊሲዎችን /ግልጽ ያልሆነ/ ቀናት ወራትን ወራት አመታትን አመታት ዘመናትን ወለዱ ከፍተኛ ስልጣኔ የነበራቸው የእስላማዊ ሱልጣኔቶች ለዘመናት የተሸከሙትን

- የተከበረው ፍ/ቤት አንዴ ማመልከቻ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- የግፍ ቀምበር አራገፉ ታላቁ ሙጃሂድ ኢማም አህመድ ተነሳ ይህ ጀግና በ15 ሃያዎቹ ተነስቶ ኢትዮጵያን በኃይማኖት ሳይሆን በአመራር አንድ አደረጋት ሱማሌን፣ጅቡቲን ፣ኤርትራን እና ኢትዮጵያን በፍትህ ገዛ በወቅቱ ለዘራያቆብ እና ለተከታዮቹ በአመት አንድ ሴት ለመገበር የተገደሉትን የሃድያ ሙስሊሞች ሲጉበኝ መሪያቸው የዘመናትን እምባ ከአይናቸው እየዘረገፉ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል ጥንት ከእኛ በፊት በነበሩት አባቶቻችን ላይ የክርስትያኑ ንጉስ ይህን ጫነባቸው ከነሱ በላይ ኃይል ነበረው የጦር ልብስ እንዳንለብስ አልያም ሰይፍ እንዳንይዝ ፈረስ ከነኮርቻው እንዳንጋልብ ከለከለን ሌጣውን ፈረስ ብቻ እንድንጋልብ ፈቀደልን ሴት ልጆቻችንን እንድንገብር አስገደደን ይገድለናል አልያም መስኪዳችንን ያቃጥላል ብለን ፈርተን ሴቶቻችንን እንገብር ነበር ገንዘብ እና ሴቷን እሚወስድ ሴት ሲላክብን የተመረጠችውን ሴት አልጋ ላይ እናስቀምጣታለን እናጥባታለን

3019 5065

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እንገነዛታለን እስልምናዋን ስለሚያስቀይሩባት እንደሞተች ቀርበን ሰላት ኢልጀናዛ እንሰግድባታለን ከዚያ በኋላ እናስረክባታለን አያቶቻችን እንዲህ ያደርጉ ነበር አሁን ግን ሃያሉ አላህ እናንተን ሙስሊሞችን ወደእኛ አመጣ በእኛ ይጫወት እና ይገዛን የነበረውን ክርስትያን ንጉስ አንተ አሸነፍከው አባረርከው ጦሩን ደመሰስከው ለአላህ ብለን ከአንተ ጋር ሆነን እንዋጋለን አንተ እንኳን ብትመለስ ንጉሱ ላይ ካደረግክበት የተነሳ እንደጥንቱ አያደርገንም ኃይሉን አሟጠጥከው 1543 ከኢማሙ መሰዋት በኋላ የሙስሊሞች ግስጋሴ በጥቂቱ ተገታ ከማጥቃት ወደመከላከል የተሻገረው እና በአስረኛው ክፍለ ዘመን ምስረታውን ያገኘው የሃረር ኢስላማዊ መንግስት ግን ማበቡን ቀጥሎ ነበር የራሱ የመገበያያ ሳንቲሞች እጅግ አስገራሚ የኪነ ሕንፃ ውጤቶች እና የተደራጁ የሰነድ አያያዞች ያንን ድንቅ የስልጣኔ ቀንዲል ልዩ ያደርጉታል ዘመን አብቅቶ ዘመን ሲተካ የሰለሞናውያን ስልጣን ወደ ጉንደር ተዛወረ ጉንደር ውስጥ በርካታ ሙስሊሞች የነበሩ ቢሆንም እጅግ ጭቁኖች ነበሩ በቀኝ እጅ የማይጨበጡ አብሯው ማእድ የማይቀረቡ የማይጉራበቷቸው ተደረጉ እስላምጌ በተባለ የተከለለ ቦታ ውስጥም እንዲኖሩ ከመደረጋቸው በላይ ከንግድ በስተቀር ምንም አይነት ሚና እንዳይኖራቸው ተደረገ የጉንደር ስርወ መንግስት በአንድ ጐኑ ሙስሊሞች ትንሽ እፎይታ ያገኙበት ዘመንም ነበር እርስ በእርስ በስልጣን ሽኩቻ ይታመስ የነበረው መንግስት በዘመነ መሳፍንት ተወጥሮ ተይዞ ነበር ካቶሊኮች እና ኦርቶዶክሶች እርስ በእርሳቸው ሲጫረሱ ቆዩ በ1855 ዘመነ መሳፍንት ተገባዶ የሙስሊሞች ፍዳ እንደ አዲስ ይቆጠር ጀመር ከመነሻው ሙስሊሞችን ማዳከምን አገራዊ ፖሊሲ አድርጐ ጦር የሰበቀው የአፄ ቴዎድሮስ ግፈኛ መንግስት ስልጣን ያዘ አፄው የወሰዳቸው የፖሊሲ እርምጃዎች ቤተክርስትያንን የሚያስከፉ በመሆናቸው በተቀናቃኛቸው በተቀናቃኛቸው አፄ ዮሃንስ እና በእንግሊዞች ትብብር ስልጣናቸው አከተመ በጭካኔ ቴዎድሮስን ያስከነዳው የዮሃንስ ዘመነ መንግስት ተጀመረ የሙስሊሞች ደም ደመከልብ ተደርጐ ይታረዱ ጀመር ወይ ተጠመቁ ወይ አገር ልቀቁ በሚል ተዘለዘሉ /ግልጽ ያልሆነ/ እስላማዊ ኤርያዎችን በግድ ክርስትያን የማድረግ ሂደቶች አሉ ከቴዎድሮስ ጊዜ አንስቶ ቴዎድሮስ ጊዜ አንስቶ ቴዎድሮስም ዮሃንስም ሚኒሊክም የሰሯቸው ግፎች አሉ በሺ የሚቆጠሩ ሕዝቦችን ለምሳሌ አፄ ዮሃንስ 1878 ከጦር ሜዳ /ግልጽ ያልሆነ/ ባደጉት ዘመቻ በርካታ ጥፋቶችን አድርሰዋል በአንድ ቀን 1886 ወሎ ላይ በኬ የሚባል ቦታ ላይ ሃያ ሺ ሙስሊሞች በግድ እስልምናን አንተውም በማለታቸው ታርደዋል አምስት መቶ ሺ የሆኑ ሙስሊሞች በግድ ክርስትያን ተደርገዋል ሃምሳ ሺ /ግልጽ ያልሆነ/ ሙስሊሞችን በግድ ክርስትያን ተደርገዋል አፄ ሚኒሊክም እንደዚሁ ኪታብ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚባል እንዳይኖር እስላማዊ መጽሃፎችን የማጥፋት ዘመቻዎችን ክርስትናን እና ሰው /ግልጽ ያልሆነ/ ከሊልን /ግልጽ ያልሆነ/ ከኃይማኖቱ የማጥፋት እና ኡለሞችን የማጥፋት ሂደቶችን ተከትለዋል የአፄ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት ሲጠናቀቅ በምትካቸው እጅግ ብልጣብልጥ የነበሩት አፄ ሚኒሊክ ነገሱ ሉአላዊነቷ ተጠብቆ የቆየችውን ሃረርን በ1887 ደፈሯት ከተማዋ መሃል ላይ የነበረውን እረኡፍ ፓሻ መስኪድ ወደ ቤተክርስትያንነት በማስለወጥም ለትውልድ ተላላፊ ቂም ተከሉ ሙስሊሞችን አሸማቀቁ ሕዝቡን በሱስ አስጠመዱ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የሰለሞናውያን ግፍ በዚህ የሚያበቃ አልነበረም ከሚኒሊክ ሞት በኂላ ስልጣን ይዞ የነበረው ልጅ እያሱ እስልምናን በመቀበሉ የተነሳ አገር ተሸበረች ሙስሊም እንዴት ኢትዮጵያን ነይገዛል በሚል ቤተክርስትያን እና መኳንንት ባስነሱት ግርግር በ3 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ልጅ እያሱ ወርደው እራስ ተፈሪ ተተኩ ሃይለስላሴ በሚለው ስማቸው የሚታወቁት እራስ ተፈሪ ሙስሊሙን እንደቀድሞ በግልጽ ማጥቃቱን አልመረጡም ይልቁንም እጅግ ስልታዊ እና ዘላቂ ውጤት ባለው መንገድ ሙስሊሙን ማዳከም ጀመሩ ሙስሊሙን ከብሄራዊ ጥቅሙ ማራቅ ከትምህርት ማግለል በሃገራዊ ስሜቱ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ መቸለስ እና ነጋዴውን ማክሰር ተያያዙት አፄ ኃ/ስላሴም ብዙ ፀረ እስላማዊ እርስምጃዎችን ወስደዋል ሙስሊሙም ትምህርት ላይ እንዳይሳተፍ እንደዚሁም ሚሽነሪዎች ሚሽን አካባቢ እንዲንቀሳቀሱ እና ወደ ክርስትና እንዲቀርቡ እስፖንሰር ከማድረግ ጀምሮ ሕግ ማውጣት አግዟቸዋል ለዚህም ሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚንስቴር የሚባል መስሪያቤት ሙስሊሙ ላይ እርምጃ የሚወስድ እና ከላይ ከላይ ሲታይ ኃይማኖታዊ ነገሮችን ሳይሆን እድገት ላይ እድገት ላይ የኑሮ እድገት ማለት ስልት አድርገው የሚመለከተውን እሱ ስሩ ያለው ነገር ለእስልምና ኢምፖርታንት የሆኑ ሰወችን ማጥቃት አንዳንድ ቦታዎች ላይ /ግለጽ ያልሆነ/ እንደዚሁም ደግሞ /ግልጽ ያልሆነ/ የሙስሊሙ ሴንተር ተብሎ የሚታወቁት እንደ አክሱም ያሉትን ሙስሊሙ ሕዝብ /ግልጽ ያልሆነ/ ነፃነት እንዳይኖር ሲጋፉ የሙስሊሙ ሴንተር ተደርገው የነበሩትን እንደ ሃረር እንደ ጅማ ያሉትን ማጥቃት ብቻ ሳይሆን /ግልጽ ያልሆነ/ ቤተርክስትያን ቀይሮ የማሸማቀቅ አይነት እርምጃዎች ነበሩ በሱስ እንዲጠመዱ የማድረግ ሂደቶች /ግለጽ ያልሆነ/ ተፈጽሟል በአፄው ዘመነ መንግስት መሃከል ኢትዮጵያ ለ5 ዓመታት በቆየችበት የቅኝ ግዛት አመታት ውስጥ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የተሻለ ነፃነት መጉናፀፍ ችለው ነበር ምንም እንኳን ወራሪው የጣሊያን መንግስት ለራሱ ፖለቲካዊ ጥቅም በማለት ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች የተሻለ ነፃነት ቢለግስም ወቅቱ ለዘመናት በአፄዎች ግፍ ሲፈፀምባቸው ለነበሩት

3024

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የተሻለ ሆኖ አልፈዋል በነዚህ 5 የቅኝ ግዛት አመታት በርካታ መስኪዶች እና የዲን ማእከላት በመላው ኢትዮጵያ ተገንብተዋል ሚኒሊክ ሊያጠፏት ያልቻሏትን የመጨረሻዋን ኢስላማዊ ሱልጣኔት ጅማን ሕልዉና መሪዋን እስር ቤት በመክተት የደመደመው የኃይለስላሴ መንግስት የሙስሊሙን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለመግደል ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ሙስሊሙ ከትምህርት እና ከኃይማኖቱ አንዱን እንዲመርጥ በዘዴ በማስገደድም የአገሪቷን ግማሽ ሕዝብ በድሏል ከዛ ውጪም ሙስሊሙ ሆነ ተብሎ ለፖሊስነት ለደህንነት መንግስት ባለስልጣን እንዳይሆን የማድረግ ሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚ/ር ያሳለፋቸው ውሳኔዎች እና የቦርድ ቃለ ጉባዔው ምናምን ይታያል እና ትምህርት ሚኒስቴርም ጋር ስንመጣ ከትምህርት ወይም ከኃይማኖታችሁ አንዱን ምረጡ ነበር በዚህ ሰበብ ብዙ ሙስሊሞች ከምንከፍል ብለው ሸሽተዋል በአፍሪካ ደግሞ ምንም ስማቸውን ለውጠው ትምህርት ውስጥም ገብተው ተምረው ያለፉ ሰወችም አሉ እንደ ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን ስናይ በተለይ አፄ ኃይለስላሴ መንግስት መጨረሻ የሰለሞናዊ መንግስት እንደመሆኑ ብዙ ጥፋቶችን በልክ እንደዚህ ፊት ለፊት እንደ ዮሃንስ እና እንደ ቴዎድሮስ ሚኒሊክ ግጭት በነበረበት እና አግሬሲቭ ሆኖ የኃይል እርምጃው ሳይሆን ብእር የተሞላ የማጥፋት እርምጃ በጥቅማ ጥቅም ኃይማኖትን ማስለወጥ ትምህርት ላይ እንዳይሳተፉ አንድነት እንዲያጡ ከሙስሊሙ ትምህርት ነፃነት የሚጠይቁ ሰወች ቦታ እንዳያገኙ እና ዝም ብለው የሚኖሩ ሰወችን ፕሮሞት የማድረግ ሂደቶች በስፋት ተስተውለዋል እና እነዚህ ሁሉ የመንግስታቶቹ ፖሊሲዎች ናቸው በትምህርት በኩል ይደረግ የነበረው ተጽእኖ ግልጽ የወጣ ነበር በትምህርት ሚኒስቴርነት ደረጃ ተቀምጠው ስርዓተ ትምህርቱን ይቀርፁ የነበሩ ግለሰቦችም በግልጽ ለክርስትና እንዲያድሩ ተደርጓል በትምህርት ላይ በምናይበት ጊዜ በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ሙስሊሙ /ግልጽ ያልሆነ / እንደውም በሃያ እና ከሃያ አመት በፊት ወደኋላ መለስ ብለን ምንም ሚና ያልነበረበት ሁኔታ አለ ይሄ ማለት የአገሪቷ ጉዳይ ላይ የሚወስኑት አቅጣጫ የሚያሳዩን የሚናገሩት የሚደመጡት ፖለቲካውንም የሚዘውሩ በሁሉም አቅጣጫ አገሪቷ ላይ ወሳኝ የሚባሉ ሚና ያላቸውሰወች ሙስሊም ያልሆኑ ሰወች ነው ሙስሊሞች ይሄንን እድል አላገኙም እንደዚሁም የሙስሊሙ በሃል ታሪክ ማንነቱ ሴቶቹ የአገሪቷ አካል ተደርገው አልተወሰዱም ሙስሊሞች ለትምህርት ያልታደሉ ይመስል እንግልት ደርሶባቸዋል ሌላው ኃይማኖት ማንነቱን በኩራት ሲያንፀባርቅ ሙስሊሙ ተማሪ ግን ተሸማቆ አንገቱን ደፍቶ ሃየማኖቱን ጨቁኖ እንዲማር ተደረገ ይህንን ት/ቤት ይይዙት የነበሩት በግልጽ ለማውራት አፄዎች እና የነሱ አስተሳሰብ

5068

3022

EGLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያላቸው ሰወች ናቸው ትምህርት ቤት ብሎ ማለት ለነሱ የተቀደሰ ቦታ እና የነሱ ልጆች ወይንም የነሱን አስተሳሰብ የሚከተሉ ለነሱ ተገዢ የሆኑ ሰወች የሚገቡበት ሌላው የማይገባበት ነገር ነው የነበረው በአፄው ኢፍትሃዊ መንግስት እንግልት የደረሰበት ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ሚያዝያ 1 ቀን 1966 ምሬቱን አሰማ አምስት መቶ ሺ ያህል ሙስሊሞች እና የወገኖቻቸው ተበዳይነት የተሰማቸው ክርስትያን ወንድሞች አዲስ አበባን በሰላማዊ ሰልፍ ናጧት በርካታ የመብት ጥያቄዎችን አነሱ ለአንዳቸውም እንኳን ምላሽ ለመስጠት ፍላጐት ያልነበረው ግፈኛው መንግስት ግን በተስፋ ለማታለል እንደሞከረ ውድቀት ቀደመው የሶሻሊስት አብዮት አገሪቱን ከቤተክርስትያን ጋብቻዋ አፋቶ አለማዊ ስርዓት ተመሰረተ ዛሬ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. ጀምሮ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ከስልጣናቸው ወርደዋል ለሙስሊሞች ታላቅ ፍስሃ ነበር ሙስሊሞች ንጉሰ ነገስቱን ከጠየቋቸው የመብት ጥያቄዎች ቢያንስ ሦስቱ ምላሽ አገኙ ሙስሊሙ በምክክር የሚመራበት የያኔው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት በሃጂ መሃመድ ሳኒ ሃቢብ ሊቀመንበርነት ተመሰረተ የሙስሊም በአላት ብሔራዊ እውቅና ተሰጣቸው በኢትዮጵያ የሚገኙ ሙስሊሞች ይባል የነበረውም ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በሚለው ተቀየረ ምንም እንኳን ደርግ በለጋ እድሜው ሳለ ጭቁን ኃይማኖቶችን ለማነቃቃት ቢጥርም ሲቆይ ግን በሶሻሊዝም እርእዮተ አለም ሰበብ ኃይማኖትን እንደ አደንዛዥ እጽ መቁጠር ጀመረ ኃይማኖተኝነትን አኮሰሰ በውጤቱም መድረሳዎች ተመናመኑ ዛውያዎች ነጠፉ ኡለማዎች በቀይ ሽብር ሰበብ ተረሸኑ አገሪቱ ላይ በተከለው ኢፍሃዊ ስርዓትም የተነሳ ለዘለአለም የማይሽር ጠባሳ ተክሎ ሄደ ኢሕአዴግ ከመሪር ትግል በኋላ በ1983 ስልጣኑን ተቆጣጠረ ክልሎች በፌደራሊዝም እራሳቸውን የማስተዳደር እድል አገኙ ዲሞክራሲ እና የመድብለ ፓርቲ ስርዓትም ታወጀ ለ17 ዓመታት ያህል አሰቃቂውን የደርግ ስርዓት ሲታገል የቆየው ኢህአዴግ በ1983 ወደ ስልጣን ሲወጣ በአገሪቱ የዲሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት ቃል ገባ በሽግግር መንግስት ምስረታ ወቅትም የተለያዩ የፖለቲካ እርእዮተ አለሞችን የሚያራምዱ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ወደ ሽግግር መንግስቱ ጉባኤ በመጋበዝ ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት መመስረት ያለውን ቁርጠኝነት ማሳየት ችሎ ነበር በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችም ላይ ሚዛናዊ የሆነ ስርዓት ለመፍጠር አሳይቶት የነበረው አቋምም የሚዘነጋ አልነበረም በተለይም የኃይማኖቶች እኩልነትን በማያሻማ መልኩ በማጽደቅ በቀድሞዎቹ አሰቃቂ የፊውዳል እና የሶሻሊስት ስርዓቶች ፈጽሞ የተለየ የነፃነት ምህዳር መፍጠር ችሏል ለዚህም በሺ ዘጠኝ 1987 የፀደቀው የኢትዮጵያ ሕገመንግስት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አብይ ማሳያ ነው የሕገመንግስቱ መጽደቅ በዘራቸው እና በኃይማኖታቸው ሳቢያ አፈና ይፈፀምባቸው ለነበሩት ኢትዮጵያውያን በተለይም ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ትልቅ እፎይታ ነበር ከዚህም በላይ የመደራጀት መብት እና ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት በሕገመንግስቱ ጉልህ ቦታ ተሰጣቸው በደርግ ዘመነ መንግስት ተመስርቶ የነበረው ኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ይመራ ከነበረሙ ሕዝብ ቁጥር አንፃር ሚናው የሳሳ ስለነበረ ድርጅቱ በተሻለ መልኩ ጉልብቶ ይንቀሳቀሳል የሚል እምነት በብዙ ሙስሊሞች ልብ ውስጥ ተጫረ ሆኖም ይህ ሊሳካ አልቻለም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ብቸኛ መሪ ድርጅታቸውን የመምራት መብት ተነፈጉ በተለያዩ ወቅቶች ሕዝበ ሙስሊሙ ሳያምንባቸው ወደ መጅሊስ ወምበር የሚወጡ ግለሰቦች ቁጥርም ጨምሮ ተስተዋለ ከዚህም በላይ በመጅሊስ ወምበር ላይ የሚቀመጡ ግለሰቦች ለኢትዮጵያዉያን ሙስሊሞች ሁለንተናዊ የመብት ጥያቄ ጆሮ በመንፈግ ሙስሊሙ በልዩነቱ ተቻችሎ እንዳይኖር የራሳቸውን አሉታዊ ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል በሕዝበ ሙስሊሙ መሃከል ያሉትን ልዩነቶች በማራገብም ሙስሊሙ በአንድነቱ እርስ በእርሱ ተቻችሎ እንዳይኖር ከፍተኛውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል እነዚህን እና መሰል ቅራኔዎች ሙስሊሙ ህብረተሰብ በጥቅሉ መሪ የለኝም ብሎ እንዲያስብ አድርገውታል ብዙ የመብት ጥያቄዎች አሉን ያላለቁ ጠቅላይ ሚ/ር እንዳሉት ሙስሊሞቹ አንዴ ጠይቀው በቃ በዛ መልስ አልተሰጠንም ብለው መተው የለባችሁም እንዳሉ መጠየቅ አለብን ይሄን እንድንጠይቅ ግን ጠይቁ እየተባለ በአንድ በኩል ግን አፋችን እየተያዘ ነው ያለው በምን በኩል በማን በኩል ትጠይቃለህ ይሄ ሁሳ ሰው ወጥቶ እንዴት አድርጐ ነው ሊጠይቅ የሚችለው እሱን እሪፕሬዘንት የሚያደርግ በትክክል እሪፕሬዘንት ወይም ሊወክለው የሚችለው አካል መኖር መቻል አለበት መጅሊስ ነው እንዳትለኝ መጅሊስ እኔን አይወክለኝም ለምሳሌ እኔ ማንም ሰውጋ እምናገረው ማንም ቢጠይቀኝ በኮምፊደንትሊ እምናገረው ነገር ነው አብዛኛው ሙስሊምንም ደግሞ እንደማይወክልም አምናለሁ እንዳይወክል ያደረገው ማን ነው ምናልባት ፀሃይ የሞቀ ጉዳይ ነው ፓራላይዝ ሆነ ተብሎ ፓራላይዝድ እንድሆን ሆነ ተብሎ ፋክሽናል እንዳይሆን የተደረገ ኢንስቲትውሽን እንደሆነ የታወቀ ነው ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ተጠቃሚ ከሚያደርጓቸው ጉዳዮች አንዱ ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆነ መሪ ድርጅት ባለቤት መሆን ነው ዳሩ ግን ከዚህ የዲሞክራሲ ትሩፋት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መጠቀም አልቻሉም ታማኝ መሪ ድርጅት ማጣታቸው ለኃይማኖታቸው እና ለአገራቸው ሊሰሩት የሚገባቸውን አዎንታዊ ሚና እንዳይጫወቱ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ኃይማኖታቸውን በስፋት እንዳይተገብሩና እና በነፃነት አየር እንዳይንቀሳቀሱ ጋሬጣ ሆኖባቸዋል ለዚህ አብይ የመሪ ጦስ ጥያቄ መፍትሄ ለማምጣት በተያዩ ወቅቶች ጥረቶች ተደርገዋል ከነዚም መሃከል በሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ከኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ጋር ውይይት አድርጎ የነበረው የበድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ድርጅት ልኡክ አንዱ ነው ልኡኩ በወቅቱ ለኢትዮጵያ መንግስት ከጠየቃቸው 8 ጥያቄዎች አንዱ ለመዘናት መፍትሄ ያልተገኘለት የሙስሊሙ የመሪ ጥያቄ ግምባርቀደሙ ነበር ሆኖም ችግሩ ዛሬም ድረስ ተባብሶ የቀጠለ ሲሆን በየጊዜው ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ሳያውቃቸው እና ሳይመርጣቸው ወደ ስልጣን በሚወጡ አፋኝ የመጅሊስ አመራሮች ኃይማኖታዊ መብቱን እየተገፈፈ ከመሆኑም በላይ ሃብትና ንብረቱም ለምዝበራ እና ለብክነት እየተዳረገ ይገኛል ዛሬ እለቱ ጁምአ ነው በአክሱም ከተማ ነዋሪ የሆኑት የዚህ መንደር ሙስሊሞች ለጁምአ ሰላት ወደ መንደራቸው የሚመጣውም የጁምአ ሰላት እድምተኛ ለማስተናገድ እነዚህን ያረጁ ሰሌኖች በዚህች ጠባብ መንገድ ላይ ያነጥፉሉ ታጁ እና የመነደሩ ነዋሪዎች ላለፉት ሃያ እና ከዛ በላይ አመታት ይህንን ተግባር ሲፈጽሙ ቆይተዋል ይህንኑ የሚፈጽሙትም የአምልኮ ስርአት የሚፈጽሙበት መስኪድ ስለሌላቸው ለመገንባትም በመከልከላቸው ነው አክሱም ሁለት ሕገመንግስት አላት የቤተ ክህነት ሕግ እና የመንግስቱ ሕግ እስ አሁን የሚተዳደረው አክሱም በቤተ ክህነት በኩል ነው ዲሞክራሲ የሚባል የለም እስፔሻሊ በኃይማኖት ደረጃ ይሄ ከኢትዮጵያ ክልሎች ለየት ያደርገዋል የኢትዮጵያ እስታትስቲክስ ባለስልጣን በ2005 እ.ኤ.አ ባወጣው መጽሃፍ የአክሱም ከተማ አጠቃላይ ነዋሪ ብዛት አርባ ሰባት ሦስት መቶ ሃያ እንደሆነ ገልፀዋል በዚህም ውስጥ ክርስትና እምነት ተከታዮችን ቁጥር ወደ ሰባ አምስት ከመቶ ማለትም ሰላሳ አምስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ሲያደርሰው የሙስሊሞችን ቁጥር ስምንት ሺ ያደርሰዋል የአክሱም ከተማ ሙስሊሞች ግን ቁጥራቸው ወደ ሃያ ሺ እንደሚጠጋ ይገልፃሉ በከተማዋ ሶላት እና ሌሎች ኃይማኖታዊ ተግባራት የሚፈፀሙት በግለሰቦች መኖሪያ ቤት ውስጥ ነው ወደ 14 የሚጠጉ የመኖሪያ ቤት መስኪዶች በከተማዋ የሚገኙ ሲሆን ትልቁ የሚባለው እና የጁምአ ሰላት የሚፈፀምበት ይሄኛው መኖሪያ ቤት ነው ብዙዎችም የመኖሪያ ቤት መስኪዶች ግለሰቦች መኖሪያ ቤታቸውን እና ሱቃቸውን ከፍለው ስለሰጡ የተገኙ ናቸው ከዚህም በተጨማሪ ይሄን መሰል መድረሳዎች ለግለሰቦች ኪራይ እየተከፈለባቸው ግልጋሎት እየሰጡ ይገኛሉ ከሃምሳ አመታት በላይ በዚህ መድረሳ ውስጥ ቁርአን ሲያስቀሩ የቆዩት ወ/ሮ ሽምሲያ ሼህ ሷልሂም የመኖሪያ ቤታቸውን ከፍለው ከአራት መቶ በላይ ለሚሆኑ ሕፃናት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ቁርአን ያስተምራሉ ወይዘሮዋ በከተማው ያለውን የመድረሳ እጥረት ለመቅረፍ የበኩላቸውን ቢጥሩም ዛሬም መሬት ላይ ተቀምጠው ቁርአን የሚቀሩ ሕፃናት መኖራቸው አልቀረም ከምንም በላይ ግን ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት መቆም ከፍተኛውን የአካል እና የሕይወት መስዋእትነት የከፈሉት ታጋይ ሙስሊሞች ደም ሳይደርቅ መስኪድ እንዳይኖራቸው መከልከላቸው ሃዘናቸውን መሪር እንዳደረጉ የሚገልፁት የአክሱም ሙስሊሞች በሌላ ጥልቅ የሃዘን ስሜት ውስጥ ተውጠው ነው አዛን የማይሰማበት አገር አክሱም ብቻ ነው ስለዚህ እስልምና እና አክሱም ለማነፃፀር በማይሞክሩበት ቃላት ያጥረኛል በጣም አፀያፊ የሆነ አኗኗር የሚኖር የአክሱም ሕዝብ ብቻ ነው የታገለው ሕዝብ አብሮ የተቀበረ ሕዝብ አክሱም ሁለቱ በአንድ ጉድጓድ የተቀበሩ ጓዶች እያሉ በእስላም እየማሉ እንደገባን እንፈታዋለን ብለው እያሉ እዚህ ከገቡ በኋላ ባላችሁበት እረፉ አርፋችሁ ኑሩ ለመስገድ የማቻልበት ቦታ አዛን የማይሰማበት ቦታ እስልምና የተከለከለበት አገር እረጃት የሌለው ቢደበድ ለነሱ አቤት ይላል ሁሉም ነገር በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ያለው አክሱም ብቻ ነው ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በዚህ ወቅት ጐልተው እየገጠሟቸው ካሉ ችግሮች መሃከል በየጊዜው የሚፈፀምባቸው ኃይማኖታዊ ትንኮሳ አንዱ ነው ትንኮሳው በይዘቱ እና በባህሪው ብዙ አይነት ነው በአላት በመጡ ቁጥር ዋና ዋና አውራ ጐዳናዎች እና የሕዝብ መገልገያ በተወሹን ጥላቻ እና ሽብር በሚነዙ ጥቅሶች መሙላት መልእክታቸው ተገቢ ያልሆነ ጽሁፎች የሰፈሩባቸውን ቲሸርቶች መልበት በጣም የተለመዱ እና ሙስሊሞችን ማሸማቀቂያ ተደርገው የተወሰዱ የትንኮሳ ስልቶት ናቸው ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የሕትመት ሚዲያዎች አማካኝነት የእስልምናን ኃይማኖት ማቃለል እና የእምነቱን ተከታዮች ሞራል መንካት እየተሰራባቸው ካሉ የሽብር ስልቶች የሚመደቡ ናቸው አስቀድሜ እንደነገርኳችሁ ግራኝ ለቱርክ ቅጥረኛ ሆኖ ይችን ምድር እና ቤተክርስትያን አገሪቱን እንዳመሳት ዛሬም ዛሬም ደግሞ በየዋሃኑ ስም የሚቀልዱ በሳውዲ ዶላር እና በአረባውያን ቅኝ ግዛት እንድሆን የሚፈልጉት ብዙ ሰወች /ያልተሰማ/ ይህች ውድ አገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ባህሎች ቋንቋዎች እና ኃይማኖቶች ደሴት መሆኗን የታሪክ ሁነት ይገልጽልናል ኢትዮጵያ ባህሏም ቁንቋዋም ኃይማኖቷም አንድ እና አንድ ብቻ ነው የሚለው ጽንፈኝነት እና ትናንትን የመናፈቅ አባዜ ሕገመንግስትን መሰረት ያደረገ መፍትሄ ያሻዋል የኃይማኖት ታሪኳ የእለት ኑሮ የሆነባት ሃገራችን መንፈሳዊ ሕይወትን ከአለማዊ ሕይወት ጋር በማጣረስ የዜጐች የእምነት ነፃነት በግለሰቦች ፍላጐት ላይ እንዲንጠለጠል አድርጋለች ያ የዜጐችን እኩልነት እና ነፃነት ያረጋገጠው ሕገመንግስት ለሙስሊም ዜጐቹ የወንፊት ጥላ ሆኖባቸዋል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ዋስትናም ተነፍገዋል ይቺ አገር የኃይማኖት ጭቆና ሲካሄድባት የነበረች አገር ነች የብሔር ጭቆና ሲካሄድባት የነበረች አገር ነች የክላስ ጭቆና ሲካሄድባት የነበረች አገር ነች /ግልጽ ይለሆነ/ የመጣው በ1987 ሕገመንግስቱ ሲፀድቅ ይህ ነገር ለአገራችን አይበጅንም ስለዚህ መቀየር አለበት ተብሎ ነው የተቀመጠው ይሄን አስመልክቶ ሕገመንግስቱ ከታሪክ የወረስነው የተዛባ ግንኙነት ስላለ ያንን ግንኙነት በማረም የወደፊት እጣ ፈንታችንን ለመወሰን አቅደን አስልተን ተነስተናል ነው የሚሉት የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ይህን ሕገመንግስት ሲያፀድቁ ስለዚህ ሴኩላሪዝም አንቀጽ 11 የኃይማኖል እና የመንግስት መለያየትን በግልጽ ሲያስቀምጥ ከምን አንፃር ነው ያስቀመጠው የኃይማኖትንም መብት ከማክበር አንፃር ነው የተቀመጠው በኃይማኖት ላይ የሚደርሱ አፈናዎችን ከማስቀረት አንፃር ነው የተቀመጠው ስለዚህ እነኚህ ሁሉ መታየት አለባቸው ሴኩላሪዝምም መተርጐም ያለበት መታየት ያለበት እያንዳንዱ ሃገር ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር መተርጐም አለበት ብዬ ነው የማስበው ኃይማኖት ከመንግስት ጫንቃ ተነጥሎ በታየበት የታሪክ አጋጣሚ በነፃነት እና በአደባባይ ኃይማኖትን መተርጐም እና መተግበር የስጋት እና የሽብር ምንጭ ተደርጐ መታየት የለበትም በዚህ ታሪካዊ ለውጥ አማኞች ወደ መስኪድ ሲመላለሱ ኃይማኖታዊ አለባበስ ሲለብሱ የእምነት ቦታ ሲገነቡ እንደስጋት መቆጠሩ ተጽእኖ መፈጠሩ ሲውል ሲያድር ብሔራዊ ስሜትን ያደፈርሳል መንግስት ነገሮችን ቆም ብሎ ማየት አለበት ይሄን ከግማሽ ፐርሰንት በላይ የሆነ የኢትዮጵያውያን ሙስሊምስ ማህበረሰብ በተለያዩ ጊዜያቶች እየደረሱበት ያሉበት አደጋ እና መከራ እስከዚህ እስከመቼ ድረስ ነው በዚህ ሊቀጥሉ የሚችሉት ሙስሊሙስ መብቱ እየተረገጠ እስከ መቼ ድረስ ነው ሊኖር የሚችለው መብቱ ሕገመንግስት የተሰጠው መብት ሲሸራረፍ የሙስሊሙ መብት ሲጣስ ለአደጋ ሲጋለጥ እና ችግር ላይ ሲወድቅ እየተመለከተ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ሁል ጊዜ እየተድበሰበሰ ካለፈ /ግልጽ ያልሆነ/ ይፈነዳል አንድ ቀን ይወጣል ለሁሉም የማይበጅ ነገር ሊፈጠር ይችላል አገሪቱ ላይ ሁሉንም እሚጐዳ ነገር ሊከሰት ይችላል ያ እንዳይሆን መንግስትም ማሰብ አለበት በሙስሊም ተማሪዎች ላይ የሚደርሰው አለባበሳችሁን አታሳዩን በጋራ ሶላት አትስገዱም የሚለው ዘወትራዊ ትንኮሳ በጋራ አብሮ የመኖር ባህልን የሚያደፈርስ የነገር አታሞ ድለቃ ነው ይህ የሙስሊም ተማሪዎች የትምህርት ተነሳሽነትን ለማቀጨጭ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ችግር መፍጠር ሕግን መሰረት ያላደረገ ግለሰባዊ ጥላቻ መበራከት መፍትሄ ያሻዋል ሌላ መንግስት እነዚህ ተማሪዎች እንደ ዜጐቹ አድርጐ መቁጠር መቻል አለበት ይህ ዲስክሪሚኔሽን አድሎአዊነት

3027 SD73

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መቆም መቻል አለበት ማንኛውም መብት ሙስሊም ይሁን ክርስትያን መብቱ በሚነካበት ጊዜ በአንድ አይን ሊታይ ይገባል በየትኛውም ቦታ ላይ በሕግ ፊትም በኩል መታየት አለበት ተብሎ እንደሚታመን በየትኛውም አስተዳደር ዘንድ በየትኛውም መሪ ዘንድ እኩል መታየት አለበት ሕገመንግስታዊ መሰረት የሌለው የጀመአ ሰላት ክልከላ ሂጃብ አበያ ጂልባብ አትለብሱም የሚለው ሰብአዊ መብትን የመጋፋት እርምጃ ሁሌም የሙስሊም ተማሪዎች እራስ ምታት ሆኖ መቆየቱ ምላሽ ያሻዋል አማኙ የኃይማኖቱን እሴት በግልም ሆነ በቡድን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበትና 1ኛ የሚከለክለው ሰው ችግር ነው 2ኛ ሰርኩሌሽን የሚሰጠው ሰው ችግር ነው ሰርኩሌሽኑ ምናልባትም የሚበተነው ሕግ ማለት ነው ሙስሊም ሴቶች ትምህርት ቤት ውስጥ በኃይ እስኩል እና በኢለመንተሪ ደረጃ ብትሄድ ሂጃብ መልበስ አለባቸው ተፈቅዶልናል መልበስ አለብን እንለብሳለን እምንለብሰው ምናልባት እኔ ነጭ ሂጃብ ተፈቅዶ ጥቁር ለብሼ ከሄድኩኝ እኔ ነኝ ጥፋተኛ ት/ቤት ውስጥ በስምምነት እኔን አማክረውኝ ከሆነ ማለት ነው ሙስሊም ተማሪዎች እኔን አማክረው ከሆነ ሁሌም ነጭ ለብሼ ት/ቤት እገኛለሁ ማለት ነው ከዩኒፎርሜጋ ማች እንዳደርገው ማለት ነው ጥቁር ከተስማማን ጥቁር ለብሼ እሄዳለሁ ማለት ነው ግን አሁን ይህ በሌለበት እንደዚህ አይነት ሂጃብ ነው የሚለበሰው በሌለበት ሂጃብ መልበስ ክልክል ነው በተባለበት ቦታ ላይ ግን የከለከለውም ጥፋተኛ ነው እንዲከለክል ያዘዘውም ጥፋተኛ ነው ማለት ነው በሕገ መንግስቱ ያለው የኃይማኖት ነፃነት በግለሰቦች ፍላጐት ማጣሱ የሕግ የበላይነቱን ፈተኛ ውስጥ ጥሎታል በአክሱም ያሉ ሙስሊም የሃገሬው ዜጐች ዛሬም ድረስ ኃይማኖታቸውን ለመተግበር ተሸማቀዋል በክልሉ የእስልምና አሻራ እንዳይኖር የጋራ አገራችንን ኢትዮጵያን በክርስትና የመመሰሉ ፂዮናዊነት በዚህ ስርዓትም ቀጥሏል የአክሱም ሙስሊሞች በክልላችን መስኪድ የመገንባት መብታችን ይከበርልን የሚለው ጩኸታቸው 20 ዓመታት ሙሉ መፍትሄ አላገኘም መፍትሄው መንግስት እና መንግስት ብቻ ነው ሕዝብ ለሕዝብ ምንም ቅራኔ የለውም መንግስት እጁን ቢያስገባ የ10 ደቂቃ በአንድ አመት ውይይት ቢያደርግ ኖሮ ተፈቷል ዋናው ሁለታችን እንዳንገናኝ ትልቁ ገደል የሆነብን መንግስት ነው አላገናኘንም ብንገናኝ መፍትሄ በቀጥታ ይገኛል በእርግጠኛነት ነው የምነግራችሁ ሕዝብ ለሕዝብ በጣም እጅና ጓንት ነው መንግስት ብቻ ነው መንግስት እንደ ሕዝብ አገልጋይነቱ በሃገሪቱ ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ እና ፈጣን እልባት ሊያበጅ ይገባል መስኪድ ዜጐች የመረጡትን ኃይማኖት የሚተገብሩበት የአምልኮ ስፍራ ነው የአላህ ቤት የአማኞች የኢባዳ ስፍራ በመሆኑ ክብር ሊሰጠው ይገባል እናም በጠራራ ፀሐይ በድቅድቅ ጨለማ በገጠር እና

http://ethcriminalawnetwork.com/

በከተማ መስኪድን የማጋየት ተግባር መንግስት እና ሕግ ባለበት አገር እየተፈፀመ ነው ይህን መሰል ወንጀል በሃገር ውስጥም ከባህር ወዲያ ባሉ የሃገሬው ዜጐች መሃከል ያለውን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የሚያሻክር ነው ተደራራቢ ወንጀልም ነው የፍትህ ያለ የሚያስኘም ሆኖ ታይቷል አንዱ ሲሸሽ አንዱ ሲያባርር መኖር አይቻልም ሰላም የሚፈልገው አንዱ ወገን ብቻ መሆን የለበትም ነው እኔ የምለው ሰላም ፈላጊ ሁሉም ወገን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ካለ በዚህ አለም ላይ ካለ ሁሉም ሰላም ፈላጊ መሆን አለበት መስኪድ ሲቃጠል የመላው ሙስሊሞች ኃይማኖታዊ መመሪያ የሆነው ቅዱስ ቁርአን ክብር ሲረክስ የተናጠል እርምጃ አደጋውን እና አቅጣጫውን የከፋ ያደርገዋል በመሆኑም ለሚቀሰቀሱ ችግሮች እና ትንኮሳዎች የጋራ ድምጽን የሚያሰማ መፍትሄ አፈላላጊ ያስፈልጋል እንደኔ አስተያየትማ ቢኖር በተለይ የኃይማኖት ተቃዋሚ ቦታ ወይንም መጽሃፍም ሆነ ዋቢ ሊኖረው ይገባል አባት ሊኖረው ይገባል ቀድሞ ማን ነው የሚደርስለት ተብሎ የእኛ ንብረት ነው ብሎ ሊልለት ይገባል ከዛም ቀጥሎ ደግሞ ከመንግስት አካልም ይሄ ንብረት የሕዝብ ንብረት ነው ሕዝብ መንግስት ማለት ነው መጥቶ ተያይዞ አንድላይ እንዲህ ያለው ነገር መፍትሄ ቢሰጡት ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ አለዚያ በተለይ የኃይማኖት ቦታዎች ላይ እንዲህ አይነት ችግር እየደረሰ ከመንግስት ተከታታይ ካላገኘ ወደፊት ምን ይመጣል የሚለው ለወደፊት ምን ይከሰታል የሚለው ለሁሉም መታሰብ ያለበት ይመስለኛል ኃይማኖትን መሰረት ያደረገ ግጭቶች እያቀጠቀጡ እና ብልጭ ድርግም እያሉ በተደጋጋሚ ጊዜ ሲከሰቱ የጥቃቱ እና የፍትህ እጦት ሰለባዎች ሙስሊሞች ሆነው ታይተዋል እናም ይህን ችግራቸውን በተቆሪነት የሚያሰሙበት ተቋም ያስፈልጋል የሕዝበ ሙስሊሙ ኃይማኖታዊ ተቋም ሁሉም በጋራ የሚገለገሉበት መሆን ይገባዋል መንግስት የራሱን ስራ ከመስራቱ ቀጥሎ ይሄንን ኢንስቲቲውሽን ከዚህ ኢንስቲትዩሽን እጁን ማንሳት አለበት ይህ ኢንስቲቲዩሽን መንግስት የራሱን ምርጫ ከታች ጀመሮ እስከ እላይ ድረስ እንደሚያካሂድ ሁሉ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በነፃነት ይሄንን ኢንስቲቲውሽን እንዲያቋቁም እና የራሱ ብሎ እንዲል ማድረግ ማቻል አለበት ሃይማኖቶች የሰላም ምንጭ ናቸው ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው ኃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች የሃገር እና የሕዝብን ሰላም ያደፈርሳሉ ይህ እንዳይሆን የኃይማኖት ተቋማት ከፖለቲካ ፍጆታ ባሻገር ተቀራርበው የሃይማኖት ግጭቶችን የማስወገድ ስራ መስራት አለባቸው በፌደራል ጉዳዮች ሚ/ር ስር ያለው የኃይማኖቶች የሰላም እና የልማት ጉባኤ ጥምረትም መስኪድ ሲቃጠል የቁርአን ክብር ሲደፈር ፒጃብ ሲከለከል በጀመአ አትስገዱ ሲባል ከሃይማኖቶቹ ተልእኮ እና

http://ethcriminalawnetwork.com/

እሴት አንገር መፍትሄ ሊያበጅ ይገባል የኃይማኖት ተቋማት መሪዎች እና የኃይማኖት ሊቃውንቶች በየቤተ እምነታቸው አማኞችን የጋራ እሚያደርገውን የሰላምን መርህ ማስተማርን የመፍትሄው አካል ነው ሙስሊም ማህበረሰብ አንድ በተደራጀ መልኩ አንድ መሪ ማጣቱ ነው በተደራጀ መልኩ መብቱን ሊያስከብርለት የሕገ መንግስታዊ መብቱን ለ ያስጠብቅለት የሚችል አካል ጠንካራ የሆነ አካል ሊመሰረትለት ግድ ነው በቃ መሪ ያስፈልገዋል መሪ ሲኖርህ ነው ነገሮችን ልታሰማ የምትችለው አንድ ያ ነው ሁለት መሪውም ደግሞ ያለው መሪ አቅም እንዲኖረው ደግሞ ሙስሊም ማህበረሰብ ጫና መፍጠር አለበት አሁንም መሪ መቀመጥ አይደለም የመረጣቸው መሪዎች መጥተው እነዛ መሪዎች ከመንግስት አካላት እና ከሚመለከተው አስፈፃሚ አካል ጫና ከተፈጠረባቸው አድመህ ተቀመጥ ከተባሉ እንደሌላው እምነት እውቅና ተሰጥቷቸው የአገሪቱን ከፍተኛ ማህበረሰብ ክፍል የሚወክሉ ሙስሊም ማህበረሰብ መሪ መሆናቸው ታውቆላቸው ክብር ተሰጥቷቸው በየትኛውም ቦታ ላይ ሊሰሙ የሚችሉበት እድል ካለ አንድ መፍትሄ ነው ማንም ሰው ከሕግረ የበላይ ባለመሆኑ የፍትህ አካላትም ፍትህን ለዜጎች በእኩል መስጠት ይጠበቅባቸዋል በልዩነት ውስጥ ተግባብቶ አብሮ የመኖር መርህ የሁሉም መርህ ሊሆን ይገባል በዋናነት ግን መሰራት ያለበት መንግስት ነው የኃይማኖት ተቋማትን ሌላውን ማህበረሰብ በአጠቃላይ መስራት ያለበት ትልቅ ነገር የመቻቻል መርህ ስርዓ እንዲገባ ማድረግ ጉዳይ ላይነው ይህች አገራችን የሁሉም አገር በመሆኗ የኃይማኖት ነፃነት ገደብ እና ክልከላ ሕገመንግስታዊ መሰረት የሌለው መሆኑን የመግለጽ ንቃት ሊፈጠር ይገባል ሙስሊሞችም እንዲህ አይነት ችግር በሚደርስባቸው ጊዜ ዝም ማለት የለባቸውም መብት ብሎ ማለት ማንም እንካ ብሎ የሚሰጥህ ነገር አይደለም ይሄ በታሪክ ውስጥም የምናውቀው እስካሁንም ድረስም የምናውቀው ወደፊትም ቢሆን እንካ ይህ የአንተ መብት ነው ተብሎ የሚሰጥህ ነገር የለም እራስህ ነው ሄደህ መውሰድ ያለብህ በምታስባቸው ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸው ሰላት ሲከለከሉ ፒጃብ ሲነጠቁ ከትምህርት ያለአግባብ ሲጉላሉ ዝም ማለት የለባቸውም ሙስሊሙ ማህበረሰብም ዝም ማለት የለበትም ፒስፉሊ መብቱን ለማስከበር መንቀሳቀስ መቻል አለበት እስከመጨረሻው ድረስ ማለት ነው ሙስሊሙ አሁንም መሪ የለኝም ብሎ እስከመቼም ድረስ የበይ ተመልካች እየሆነ የሚደርስበትን መከራ ሁሉ ከንፈሩን እየመጠጠ እና እንባውን እያፈሰሰ ብቻ ማለፍ መቻል የለበትም ጥያቄዎቹም መድረስ መድረስ ያለባቸው ቦታዎች ድረስ የሚችልበት ከሁሉም አቅጣጫ ሁሉም ሊያነሳው የሚገባው ነገር ይኖራል መብቱ ሲደፈር አሁንም ተደፈረ ብሎ አድበስብሶ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲታለፍ ዝም ማለት የለበትም መብታችን ነው የተነካው ሕገመንግስታዊ መብታችን ነው የተጣሰው ይከበርልን ብሎ /ግልጽ ያልሆነ/ ማሰማት የሚችልባቸው መድረስ የሚገባን ቦታ ላይ ሁሉ ሊደርስ ይገባዋል የሁሉንም ትብብር ይፈልጋል አሁን መሪውም ብቻውን የሚሰራው ስራ የለም መሪውም የተሻለ መሪ ከተገኘ ማለት ነው ከዛም አልፎ ደግሞ ሕዝቡ ጠንካራ ሆኖ አጋዥ አካል ሆኖ መምጣት አለበት ሁል ጊዜ /ግልጽ ያልሆነ/ የሚነሳው ነገር ለውጤት ይበቃል ሕዝብ ስለሚነሳ ለሕዝብ ድምጽ መንግስትም መልስ ይሰጣል በጋራ የሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ ሕዝቡ ጥያቄ ማንሳት አለበት ለሚደርሱበት ችግሮች እና ነገሮች መፍትሄ እንዲሰጥለት መድረስ ያለበት ቦታ ላይ ሊደርስ የሚችለውን መልእክት ማሰማት መቻል አለበት ያን ካላደረገ እና ሁል ጊዜ በተነካ ቁጥር እየተሸማቀቀ የሚያልፍ ከሆነ እራሱን እንደ 2ኛ ዜጋ ቆጥሮ የሚሄድበት ተጨባጭ ውስጥ ካለ መቼም መብቱን ሊያስከብር አይችልም መቼም ደግሞ ተከብሮ ሊኖር አይችልም እዚች አገር

- ጠዋት የነበረው ችሎት ቀጥሏል ከሰዓት በስተቀር ቀኑ አልተቀየረም ዳኞች አልተቀየሩም አቃቤ ሕጎች አልተቀየሩም ተከሾቹም ሁሉም ቀርበዋል የተከሳሽ ጠበቆች ጠዋት ከነበሩት አዲስ መሃመድ ሲቀሩ ሌላ ተጨማሪ
- ሃሰን ሁሴን
- ቀርበዋል ስለዚህ ጠዋት ከቆመበት እንቀጥላለን ስለዚህ መግለጫችሁን ቀጥሉዋ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄኛው ሲ.ዲ. የኢህአዴግ እና የአህባሽ ሴራ በኢትዮጵያ የሚል እርእስ ያለው ነው በአጠቃላይ አንድ ሰዓት ከሰባት ደቂቃ ከሰላሳ አምስት ሰከንድ የሚፈጅ ነው በይዘት ደረጃ ያው በሙስሊም እምነት ተከታዮች ላይ ፈተናው እንደቀጠለ ከዚህ ባለፈ መንግስት ከተለያዩ የውጭ አገር መንግስታት ጋር በመተባበር አህባሽ የሚባል አዲስ ኃይማኖት እንዳመጣ በተጨማሪም የዚህ አስተሳሰብ ወይም የዚህ አስተምሮ አራማጅ የሆኑ ግለሰቦችን በግለሰብ በስም ደረጃ በመጥቀስ እነዚህን ግለሰቦች በማጥቀር ከዛ ባለፈም ሌሎች የአረብ መንግስታት እና የኃይማኖቱ ተከታዮች በውጭ አገር የሚገኙ የውጭ ዜግነት ያላቸው የኃይማኖቱን ተከታዮች እንዲሁም አስተማሪዎች ከፊሎቹን በማወደስ ከፊሎቹን በማንቋሸሽ በተለይ የእስራኤል እና የምእራባውያን አገራት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ተባብሮ ይሄን አስተምሮ በገንዘብ እየደገፋ ጭምር ወደ አገር ውስጥ እንዳስገቡት እያሳየ ያው ቅድም በተመለከተው መልኩ የሃሰት ቅስቀሳዎችን እያረገ ሕዝቡን ወይም ሕዝበ ሙስሊሙን ለማነሳሳት ተጠቅሞበታል በሚል የተያዘውን ኤግዚብ ጭብጥ የሚያስረዳ ነው

3031 SD77

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሄ አሁን መጥቷል የተባለውም አዲስ አስተምሮ ወይም አስተሳሰብ የተለያዩ ነገሮችን አርጉ ይላል በሚል በዛ መልኩ ለቅስቀሳ ሲውል የነበረ ሲዲ ነው

- እስቲ ማለት በማን ላይ እንደሚያስረዳ ከየት እንደተያዘ ?
- ይሄኛው ቪሲዲ ያው ቅድም በገለጽነው መልኩ ከበርካታ ተከሳሾች ተይዞ የሚያስረዳውም ቅድም በተጠቀሰው መልኩ ክሱ በቀረበበት መንፈስ በወንጀል አድማ ስምምነት የፈፀመ ስለሆነ የስምምነቱ ተካፋዮችን በሙሉ የሚመለከት ነው ሁሉንም ተከሳሾች
- የተከበረው ፍ/ቤት ሲዲ ቪሲዲ ተያዘ የተባለው ተዘርዝሮ ቀርቧል በማስረጃ በአቃቤ ሕግ የማስረጃ ዝርዝር ላይ ስለዚህ ከበርካታ የሚለው አሻሚ ነው ሲዲ የተያዘበትም ያልተያዘበትም ተብሎ ስለተዘረዘረ ከነማን በርካታ ማለት ምን ማለት ነው ከነማን ነው የተያዘው የሚለው ቢገለጽልን
- የተከበረው ፍ/ቤት እነኚህን ድምጽ ከምስል ማስረጃን ብንመለከት በችሎት ይቀርባል ብለን ስንል በስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ 13 የተጠቀሱ ሰወች እነኚህ በእያንዳንዳቸው ዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል ከዚህ ውስጥ ከ10ኛ ተከሳሽ ከ19ኛ ተከሳሽ እያሉ የተያዙ ሲዲዎችን ብዛት ሦስት ሦስት እያልን ስንገልጽ እያንዳንዳቸው በዚህ ማስረጃ መግለጫችን ቀደም ሲል ሲዲዎቹ ከነማን እንደተገኙ ምን አይነት እርእስ እንዳላቸው ቀደም ሲል ያቀረብናቸው በዚህ በርበራ ወቅት ታዛቢ የነበሩ ሰወች ምስክሮቻችን በሚገባ በዝርዝር አስረድተዋል በዚህ የማስረጃ መግለጫ እንደተመለከተው በተራ ቁጥር 12 ላይ ለምሳሌ ከ25ኛ ተከሳሽ ላይ በብርበራ የተያዙ ሲዲዎች ብዛት 1 ከ29ኛ ተከሳሽ ብርበራ የተያዙ የኢህአዴግ እና አህባሽ ሴራ የሚሉ ሲዲዎች ብዛት 3 ከወንጀል ትግበራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተጨማሪ ሲዲዎች እያልን አስቀምጠናል ከዚህ ውጪ ከዚ.ጋር በተያያዘ ማለት ነው
- ይሄኛው ከሱ ውስጥ የትኛው ውስጥ ነው ?
- ይሄኛው ከዚህ ውስጥ ከነኚህ ከ1-13 ከተጠቀሱት በአንደኛው ተከሳሽ ጋር ነው ይሄ ማለት በእያንዳንዱ ሲዲ ላይ በቬሬብ አለ ቬርባል ቀርቧል ተያይዟል አሁን የእከሌ ነው ለማለት ይሄንን የኢህአዴግ አሁን የሚቀርበውን በሚመለከት የማን ነው ለማለት ወይ ሲዲው ላይ ተጽፏል አለበለዚያም ደግሞ በማስረጃ ተረጋግጧል በቬርባልም ተረጋግጧል በብርበራ ላይም ስለዚህ ልክ እንደ አዲስ እና ከማን ነው የቀረበው ማለት የሚለው አካሄድ አግባብ መስሎ አልታየንም ምክንያቱም ይሄንን ማስረጃ እያንዳንዱን በሚመለከት ማን ምንድን ነው የሚለውን ቀደም ሲል አስረድተናል በማስረጃ መግለጫችንም በደፈናው ማለት የሲዲው ብዛት ተቃርቧል በዝርዝር ተገልጿል ስለዚህ አሁን ከማን ተገኘ እንዴት ተገኘ የሚለው

3032 SD78

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አግባብነት ያለው አልመሰለንም ቬርባሉን በተመለከተ በማስረጃ ዝርዝር ላይ ተጠቅሷል የብርበራ ቤቫሩ እና እያንዳንዱ ተከሳሽ ምን አይነት እርእስ ያለው ሲዲ እንደተያዘበት ተጠቅሷል እዛ ላይ የስእል ማስረጃው ላይ እዛ ላይ ሊገኝ ይችላል ያም ደግሞ እንትን የሚልከሆነ በነገው እለት ያንን ማምጣት እንችላለን ቤርቫሉን ለምሳሌ አሁን አሁን የሚታየው ሲዲ ከ29ኛ ተከሳሽ ከዶ/ር ከማል የተያዘ ነው ግን ከዶክተር ከማል ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹ ከ2ኛ ከሌሎች በርካታ ተከሳሾችም ተይዞ ይገኛል ይሄ ቤርቫሉ ላይ አለ ምናልባት የፍ/ቤቱ ዋናው መዝገብ ካለ ከዛጋ ክሮስ እሪፈር ሊደረግ ይችላል እንገና ደግሞ ቅድም ብይን ተሰጥቶበታል ይሄ መጀመሪያ ተነስቶ መቃወሚያው እኛ ኮንስፓይሬሲ መሆኑ ሁሉንም ተከሳሾች የሚመለከት እና ሁሉም ተከሳሾች ቻሌንጅ ሊያረጉት የሚችል ማስረጃ መሆኑን ገልፀናል ይሄን ተቀብሎ ፍ/ቤቱ ይቀጥል ስላለ ነው የመጀመሪያው ሲዲ የታየው አሁን ድጋሚ ክርክር ማንሳት የፍ/ቤቱን ብይን አለማክበር ነው

- ያው በሁሉም ላይ ስላላችሁ እሱን እንዳለ ይቀጥላል የዛሬው ምናልባት አሁን በቀረበው መልኩ ነገ ግን ተዘጋጅታችሁ በዚህ መንገድ ላይ ማን የት እንደተያዘ ቤርቫሉን አምጥታችሁ አብራችሁ ማስረዳት ነው ምክንያቱም ሁለት ነገር ነው ከእከሌ ተያዘ የሚል የታዛቢ ምስክር ቀርቧል አሁን ደግሞ ይሄኛው በማን ላይ እንደሚያስረዳ ግልጽ ነው ግን የተያዘበትንም ግልጽ አድርጋችሁ ብትመጡ ለእኛ ለመጨረሻ ለውሳኔ አሰጣጥ ምቹ ነው የሚሆነው የዛሬውን በዚሁ ቀጥሉ
- እስልምና ኃይማኖት በተለያዩ ወቅቶች እና ጊዜያት የተያዩ ፈተናዎችን ሲያስተናግድ ቆይቷል የፈተናው ባህሪ እንደጊዜው እና ወቅቱ ቢለያይም ፈተናው ጥሎት የሚሄደው አሰቃቂ ጠባሳ ግን ሕያው ነው የኢትዮጵያ ሙስሊሞችም እንዲሁ በተለያዩ ወቅቶች መራር ፈተናዎችን ሲያስተናግዱ ቆይተዋል ፈተናው ዛሬም አላበቃም ፈተናው ይደርስብን የነበረው በውጭ አገር እስፖንሰር አድራጊነት እና በሌሎች ወገኖች አስፈፃሚነት ነበር ዛሬ ግን የፀረ ሙስሊም ሴራው አስፈፃሚ ሆኖ ብቅ ያለው አህባሽ የተባለው ሙስሊም ተብዬ ቡድን ነው አህባሽ ለመሆኑ ማን ነው መስራቹስ የአህባሽ አንጃ መስራች አብደላሂን መሃመድ አልሃረሪ ይባላሉ የተወለዱት ሃረር ውስጥ በ1910 ሲሆን ሰፊ የኃይማኖትን እውቀትን እዛው ባደጉበት ሃረር ከተማ በልጅነታቸው ቀስመዋል ሰውየው እጅግ አወዛጋቢ እና ግራ አጋቢ ነገሮችን በመፈፀም በሰፊው መታወቅ የጀመሩት ከዚያው ከትውልድ መንደራቸው ነበር ሼህ ሙስጠፋ አብዱራህማን የተባሉት አማቻቸው በሃረር ከተማ የከፈቱትን የሪም ትምህርት ቤት ፀረ ሙስሊም ሆነው የኃይለስላሴ መንግስት ጋር በማበር እንዲዘጋ አድርገዋል

3033 5079

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የትምህርት ቤቱን አስተማሪዎችም ኃይለስላሴ መንግስት የሚጠቅስ ጽሁፍ በውጭ ጋዜጦች ላይ ጽፈዋል ብለው ለመንግስት በማመልከት አስተማሪዎቹ ለበርካታ አመታት በእስር እንዲቆዩ እና በዚያው እንዲሞቱ አድርገዋል ሼህ አብደላ አልሃረሪ ሼህ የሱፍ ከከፈቱት የሪም ትምህርት ቤት ጋር በአስተሳሰብ የማይጋሩ ቢሆንም ለኢስላም እሰራለሁ ብሎ የተመሰረተን ማህበር ለጠላት አሳልፈው መስጠታቸው እና እንዲዘጋ ማረድረጋቸው በጣም ብዙዎችን አሳዝኖ ነበር አንድን ሙስሊም ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለጠላት አሳልፎ መስጠት ምን ያህል ወንጀል እንደሆነ ለሼህ አብደላ ይጠፉቸዋል ብሎ መገመት ከቶም አይቻልም ሆኖም ግን መድረሳው መዘጋቱ እና ማህበሩ በመፍረሱ ሼህ አብደላ እጅደግ ተደስተው የሙፍቲነት ማእረግቢሰጣቸው የሃረር ሕዝብ ግን በተከሰተው ነገር እጅግ አዝኖ /ግልጽ ያልሆነ/ አለ ትምህርት ቤቱን በማዘጋት እና አስተማሪዎቹን በማሳሰር ደስ የተሰኙት ሼህ አብደላ ደግሞ የፊት ናሽ ተባሉ ሼህ አብደላ አልሃረሪ ወደ ውጭ አገራት ከመሄዳቸው በፊት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የዲል ትእህርት ተምረዋል አስተምረዋል ባደጉባት መንደር በጣም ይታወቅ የነበረውን የቃድሪያ የሱፍ እያጠሪቃ ይከተሉ የነበረ ሲሆን በኋላም ወደ ቲጃሪያ ጠሪቃ ተሻግረዋል በቲጃኒያ ጣሪቃ ውስጥ ጥቂት ጊዜያትን ካሳለፉ በኋላ የቲጃኒያ ጣሪቃ ተከታዮችን በሙሉ በማክፈር ወደ ቃዲያ ተመልሰዋል ሼህ አብደለ የቲጃንያ ጣረቃ ተከታዮች ያከፈሩበትን ማስረጃ እንመለስበታለን ለዲቢ እና አፈንጋጭ ባህሪያቸው በስፋት ይታወቁ ነበር ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት ሙፍቲ መሃመድ ሲራጅ አልጀበቲ ጋር ለዲም ትምህርት ሄደው ነበር ሆኖም ሼህ አብደላ አንድም ቀን ከሙፍቲ መሃመድ ሲራጅ እና ተማሪዎቻቸው ጋር የጀመአ ሰላት ሰግደው አያውቁም ነበር ይህን ያስተዋሉት ሙፍቲ መሃመድ ሲራጅ ለምን በጀማ ሰላት አትሰግድም ብለው ሼህ አብደላን ይጠይቋቸዋል ሼህ አብደላም የአረብኛ ፊደላትን አስተካክሎ በማያነብ ኢማም ተከትዬ አልሰግድም በማለት መለሱ ሆኖም ያሰግዱ የነበሩት ኢማም ቁርአን ይሃፊዙና በተጁዊድም ጭምር የሚቀሩ ነበሩ ሙፍቲ መሃመድ ሲራጅ አልጀበርዲ በሼህ አብደላ ባህሪ እጅግ በመገረም ብቻቸው ቡና መጠጫ ክፍል ውስጥ እንዲሲግድ አዘዙት ይህነ ያደረጉት በማህበረሰቡ ውስጥ ሂክና እንዳይፈጠር በመስጋት ነበር ሼህ አብደላ ከዛን ወቅት ጀምሮ ለሙፍቲ መሃመድ ሲራጅ አልጀበርቲ አሰላም ዋሌኩም ብለው ሰላምታ ሰጥተዋቸው አያውቁም ሁኔታው ያላማራቸው ሙፍቲ መሃመድ ሲራጅም ፈተና ከመፈጠሩ በፊት ሼህ አብደላ ከመድረሳቸው እንዲወጡ በማሰብ ሁለት ተማሪዎቻቸው እራቅ ያለ ቦታ አድርሰዋቸው እንዲመለሱ አዘዟቸው ሼህ መሃመድ ይህን ያደረጉት ሼህ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አብደላ ፈተና ይፈጥራል ብለው በመስጋታቸው ሲሆን ይህንንም ስጋታቸውን ይህ ሰው ወደፊት ከባድ ፈተና ይፈጥራል በማለት ገልፀውት ነበር ሼህ አብደላ በኦሮሚያ በአማራ እና የደቡብ ክልል አጐራባች አገሮች በመሄድ የዲም ትምህርት ተከታትለዋል ጅማ ዞን አንባሼህ አብደላ ኪታብ ከቀሩባቸው እና ካቀሩባቸው ቦታቸው ትጠቀሳለች በዚህች ዞን ልዩ ስሟ አናሌ በምትባል ቦታ ግሉበል መረም የተባለው ኪታብ ያስቀሩ በነበረበት ወቅት ድንገት ቅርአቱን በማቋረጥ ለ30 ደቂቃዎች እና ለ1 ሰዓት ያህል ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ እና ፊታቸው በማጨማደድ ይቆዩ ነበር በዚህ የተገረሙት እና ግራ የተጋቡት ብዙዎቹ የቂርአ ተከታታዮች ሼህ አብደላህን ጥለው ለመሄድ የተገደዱበት ወቅት ነበር ከዚህ በተጨማሪም ምንነቱ ያልታወቀ ነገር በመጠቅለል እና እንደ መሃተም አንገት ላይ እንዲንጠለጠል በማድረግ የቡዳ መድሃኒት እያሉ ለአካባቢው ሕዝብ ይሸጡ ነበር በአሁኑ ወቅት ያሉትም አህባሾች ይህን ማህተም መሰል ነገር አንገታቸው ላይ ያንጠለጥላሉ ሼህ አብደላህ አጠራጣሪ እና አሻሚ ነገሮች ላይ ጊዜያቸውን መፍጀት ያዘወትሩ ነበር አላህማአለለአሺስ ጠዋ የሚለውን የቁርአን አንቀጽ ለትርጉም አሻሚ እንዳይሆን ቁርአን ስትቀሩ ኢስተውላ ብላችሁ በአረብኛ ቅሩት እያሉ ተማሪዎቻቸው ያዙ እንደነበረ ሼህ መሃመድ አብዱል ወሃብ ያሲን የተሰኙ ለቀድሞ ተማሪያቸው ተናግረው ነበር ይህ ቁርአንን በአዲስ ለመለወጥ ያደረጉትን ጥረት ግን ተማሪዎቻቸው በፀጋ አልተቀበሉትም ሼህ አብደላ እጅግ ተጠራጣሪ ከመሆናቸው የተነሳ የሰላት ወቅት ደርሶ እንኳን ቆይ ሰዓቱ አልደረሰም ይሆናል በሚል አጉል ጥርጣሬ ሰላታቸውን አዘግይተው ይሰግዱ የነበረ ሲሆን የሄዱባቸው አካባቢዎች ሁሉ አሰጋጆቹ የቁርአን አንቀፆችንበትክክል አያነቧቸውም በሚል ሰበብ ማንንም ኢማም ተከትለው በጀማአ አይሰግዱም አያሰግዱምም ነበር ሼህ አብደላህ ከሃረሩ ግርግር ጥቂት ጊዜያት በኋላ በቀጥታ ያቀኑት ወደ መካ ነበር በመካ ቆይታቸው ከታላላቅ ሃሊሞች ጋር ትውውቅ ያደረጉ ሲሆን ትክክለኛ የሆነውን አመለካከታቸውን ግን ሊያንፀባርቁ እንዳልቻሉ ተነግሯል ሆኖም በመካ ከነበሩ ኡለማዎች ጋር መስማማት ባለመቻላቸው ብዙም ሳይቆዩ ወደ እስራኤል አቅንተዋል ወቅቱ እ.ኤ.አ በ1948 ሲሆን እስራኤል ከፍልስጥኤም ጭቁን ሕዝቦች መሬት ቀምታ እንደ ሃገር የተመሰረተችበት ወቅት ነው ሼህ አብደላ በዛች ወሳኝ ወቅት እስራኤል ለምን እንደሄዱ እና ምን እንደፈፀሙ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም የተለያዩመላ ምቶች ግን መሰጠታቸው አልቀረም ከዚህም አንዱ እስራኤል በቆዩባቸው ሁለተ አመታት ከአይሁዳውያን በተለይም ከእስራኤል የስለላ ድርጅት ሞሳድ ጋር ቋሚ የግንኙነት መስመር እንደዘረጉና ወደፊት ለሚመሰርቱት የአህባሽ አንጃ መሰረት መጣላቸው

http://ethcriminalawnetwork.com/

ነው ከእስራኤል በኋላ በቀጥታ የሄዱት ወደ ሶሪያ መዲና ደማስቆ ነበር ደማስቆም ብትሆን የሼህ አብደላን አፈንጋጭ አመለካከቶች ለማስተናገድ ዝግጁ አልነበረችም ሆኖም ከተለያዩ አሊሞች እና ምሁራን ጋር በተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ ውይይት እና ክርክር ጭምር ያደርጉ ነበር ከሼህ አብደላ ጋር ውይይት ካደረጉ አሊሞች መካከል የሃጂ ሱሊክ ሼህ ነስሩዲን አልባኣኒ ይገኙበታል አልባኣኒ ከሼህ አብደላ ጋር ውይይት ካደረጉ በኋላ ሼህ አብደላ ምንም አይነት የአይዲስ እውቀት እንደሌላቸው እና ሰሂህ እና ደኢህ ሃዲሶችን እንኳን ለመለየት እንደማይቻላቸው ገልፀዋል ከዚህም በላይ ደማስቆ ያሉ ምሁራን የሼህ አብደላን ያፈነገጡ አቋሞች በአደባባይ ማብጠልጠል ጀመሩ ይህ ሁኔታ በጥቅሉ ያልጣማቸው ሼህ አብደላ ደማስቆ ከተዋወቋቸው ሊባኖሳውያን ጋር በመነጋገር እኩይ አስተሳሰባቸውን በስፋት ሊረጩባት ወደምትችለው መረከኛዋ ሊባኖስ አቀኑ አብደላ ሃረሪ ሊባኖስ እንደደረሱ ተለምዷዊ የሆኑትን ትምህርቶቻቸውን ከመስጠት በዘለለ ወጣ ያሉ ሃሳቦቻቸውን በማተማር ስራ አልተጠመዱም ነበር በሂደት ግን የተጽእኖ አቅማቸው እና የተማሪዎቻው ቁጥር እያሻቀበ መጣ ለዚህ አይነተኛውን አስተዋጽኦ ያመለከተው ሚዘር ሃላቢ የተባለው ቀዳሚ ተማሪያቸው ነበር ኒዘርከተለያዩ የሊባኖስ አካባቢዎች ግለሰቦችን በማግባባት ወደ ሼህ አብደላ መድረሳ ይዞ ይመጣ ነበር የተማሪዎቻቸው ቁጥር ማደጉ የማእከላቸውን እውቅና ጨምረው የሼሁን አመለካከት የሚተቹ ሊባኖሳውያን ኡለሞች አለመኖራቸው በብዙ መልኩ ለእውቅናቸው አስተዋጽኦ አድርጓል የሼህ አብደላ ሊባኖስ እንቅስቃሴ የተማሪዎቻቸው እና ማንነታቸው በዉል በማይታወቁ ኃይሎች ድጋፍ ማደግ እና መስፋፋቱን ቀጥሎ ጐረቤት አገራት ብሎም በአውሮፓ አውስትራሊያ እና አሜሪካ መታወቅ ጀመረ ሰወቹም የሼህ አብደላን ቡድን ከመስራቹ ዜግነት በመነሳት አህባሽ እያሉ ይጠሩት ጀመር በሂደትም አህባሽ ይፋዊ የአንጃው ስም ሆነ ቡድኑ አህባሽ የተባለው ሃበሾችን ያቀፈ በመሆኑ አልነበረም ምክንያቱም አሁንም ድረስ የቡድኑ ዘጠና ከመቶ በላይ አባላት ሊባኖሳውያን ናቸው የአንጃው አባላትን መበራከት ነበረ እራሱን ቋሚ ተቃዋሚ እንዲመሰርት በር የከፈተለት ሆኖም ቡድኑ አዲስ ተቋም መመስረት አልተጠበቀበትም በ1930 ተቋቁሞ የነበረ አንድ ማህበር ወቅታዊ እና ኢኮኖሚያዊ እስትራቴጂያዊ በመጠቀም ከአባላቱ እጅ ፈልቅቆ የአህባሾች ሕጋዊ ማህበር አደረገው አጀሚያቱን መሻሪያል እስላሚያ የሚል ስያሜ የነበረው ይኸው ማህበር በገጠመው ቀውስ ምክንያት ችግር ላይ ወድቆ ሳለ ሼህ አብደላ ሃረሪ ማህበሩን በመቀላቀል ሃይማኖታዊ ቅስቀሳ በማህበሩ ስም ማድረግ ጀመሩ የተለያዩ ባለሃብቶችም ማህበሩን እንዲቀላቀሉ ጥሪ አቀረቡ በገንዘብ አቅም ተዳክሞ የነበረው

3036 5082

http://ethcriminalawnetwork.com/

ማህበርም ዳግም ማንሰራራት ጀመረ በቅርብ አመት ውስጥ በ1975 የተጀመረው የሊባኖስ የእርስ በእርስ ጣርነትም ማህበሩ አባላቱ እንዲበዙለት ምክንያት ከመሆኑም በላይ የገንዘብ አቅሙም የፈረጠበት ወቅት ነበር ቡድኑም በእርስ በእርስ ጦርነቱ የቀጥታ ሳይሆን የተዘዋዋሪ ተሳትፎ አድርጓል የተለያዩ ወታደራዊ ና ሲቪል ፓርቲዎችንም በተዘዋዋሪ መልኩ አቋቁሟል የሊባኖስ የእርስ በእርስ ጦርነት ሲጠናቀቅም የአህባሾች ማህበር በ1983 በመሪው ሚዛን ሃላቢ አማካኝነት ይፋዊ ስራውን ጀመረ አዲስ ባቋቋመው የእርዳታ ድርጅት ስም መላው ሊባኖስ ማዳረስ ጀመረ የእርዳታ ድርጅቱ ቀድሞ ከተቋቋመበት አላማ ወጥቶም የሼህ አብደላ አፈንጋጭ አስተሳሰቦች ማራመጃ ሆነ በዚህ አላማውም አለማዊ እና የዲን ትምህርት ቤቶች ሴቶች እና መዝናኛ ማእከላት የምርምር ተቋማት እና የእስፖርት ማዘውተሪያዎችን ከፍተኛ በሚባል ወጪ ገነባ የመሃበሩም ስም በከፍተኛ ሁኔታ ገዘፎ መታየት ጀመረ /ግልጽ ያልሆነ/ እራሱን ለማሳደግ በተለያዩ መስኮች ተሳትፎ ማድረግ ጀምሮ ነበር ከዚህም አንዱ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ነው ማህበሩ እና መስራቹ ሼህ አብደላ ፖለቲካዊ ተሳትፎን ሃራም ቢያደርጉም ሁለቱ የማህበራቸውን አባላት በሊባኖስ ፓርላማ እንዳያሳትፉ አላደረጋቸውም አህባሾችን ወክለው ከተወዳደሩት ሁለቱ ተመራጮች አንዱ በቂ ድምጽ አግኝቶ የሊባኖስፓርላማ ውስጥ መግባት ችሏል ለላው የእንስቅስቃሴያቸው ዘርፍ ትምህርት ሲሆን በአለማዊ ኃይማኖታዊ እና ሙያዊ ትምህርቶች ዘርፍ ከፍተኛ ገንዘብ በመበጀት እንቅስቃሴ ያደርጋሉ ማህበራዊ እንቅስቃሴያቸው ብዙ አባላትን በተለይም የሴቶች እና ሕፃናትን ቁጥር ለማሳደግ እረድቷቸዋል በብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች የሚያደርጓቸው እንቅስቅሴዎችም ቀላይ የሚባሉ አይደሉም ድርጅታቸው የራሱ የሆነ ምንአሉል ሁዳ የተባለ መጽሄት አለው በሊባኖስ የሚደመጥ እራዲዎ እና በቋሚነት የሚተላለፍ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችም አሏቸው አለምአቀፍ እውቅና ያላቸው የአንጃው ድረ ገፆትም ከፍተኛውን የፕሮፓጋንዳ ስራ ያከናውናሉ ከዚህም በተጨማሪ አመታዊ በጀቱ 3.2 ቢሊየን ዶላር የሚደርስ እና ዳርን መሻርዮን የተባለ ግዙፍ ማተሚያ ቤት አላቸው የድርጅቱ አባላት ቁጥር ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ቢሆንም የገንዘብ አቅማቸው ይሄን ያህል ግዙፍ መሆኑ ብዙዎች ነገሩን በጥርጣሬ እንዲያዩት ይጋብዛሉ አህባሾች ቁጥራቸው እጅግ አናሳ ቢሆንም በጠንካራው ኢኮኖሚያቸው እስትራቴጂያዊ ጥንካሬያቸው እና ከድርጅታቸው ፈጣን እድገት ጀርባ ማን ነው ያለው የሚለው ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው አህባሾች በጥቅሉ ከምእራቡ አለም አገራት እና ከእስራኤል እንዲሁም ሙስሪያ ኮሚቴ እንደ ከፍተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ድጋፎች እንደሚደረግላቸው በብዙ ምሳሌዎች ማየት ይቻላል ከእነዚሁ አገራት

3037 5083

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚደረጉላቸው ድጋፎች ዘርፈ ብዙ ሲሆኑ አንዱ እርእዮተ አለማዊ ድጋፍ ነው ወደ ኋላ በዚህ በዚህ ዶክመንተሪ ፊልም ውስጥ እንደምንመለከተው የምእራቡ አለም አለም አቀፍ ተቋማት ለቡድኑ አዎንታዊ አመለካከት ይቸራሉ ሊደገፍ የሚገባው ቡድን መሆኑንም አበክረው ይገልፃሉ ፕሮፌሰር አህጋይ ኤርሊች የተባለ ጽዮናዊ አይሁድ አል አህባሽ ኤንድ ዋህብያ ኢንተርፕሪቴሽን ኦፍ ኤዝላም የሚል እርእስ በሰጠው የምርምር ጽሁፉ አህባሾች ሙስሊሙን በሙሉ ጠላት አድርገው የፈረጁ መሆኑ እና ሙስሊም ላልሆነ ወገኖች በጉ አመለካከት ያላቸው መሆኑ ያስመሰግናቸዋል ብሎ ጽፏል የአህባሽ ቡድን ከላይ በተጠቀሱ እና ከሌሎች የምእራቡ አለም አገራት ከሌሎች ሙስሊሞች በተለየ የሚያገኙት ነፃነት እና በአገራቱ የሚደረግላቸው ድጋፍ ልዩ ጥርጣሬን የሚያጭር ሲሆን ወዳጅነታቸውም የጠነከረ ነው በአንድ ወቅት ሼህ አብደላ ሃረሪ አስተሳሰባቸውን ለማስተማር ወደ ሌሎች አገራት ተጉዘው ነበር የወቅቱ የሊባኖስ ሙፍቲ ሼህ ሃሰን ሃሊድም ሼሁ በሊባኖስ ውስጥ ከፍተኛ ቀውስ እየፈጠሩ ለመሆኑ ዳግም ወደ ሊባኖስ ሊገቡ አይገባም በማለት ለሊባኖስ መንግስት ስምታቸውን ያቀርባሉ የሊባኖስ መንግስትም ጥያቄውን ተቀብሎ ሼህ አብደላህን ወደ ሊባኖስ እንዳይገቡ በመከልከል የመኖሪያ ፍቃዳቸውን ይነጥቃል ሆኖም የእንግሊዝ መንግስት በጉዳዩ ቀጥተኛ እጁን በማስገባት እና ዲፕሎማሲያዊ ጫና በማሳደር ሼህ አብደላ ወደ ሊባሃስ እንዲገቡ አድርጓል እንግሊዝ ለሼህ አብደላ ይሄን ያህል ትጨነቃለች ለምን ይሆን አስመልክቶ ቡድኑ እና መስራቹ የሚያራምዷቸው አቋሞችም እጅግ ግራ አጋቢ ናቸው የእስራኤል ጦር በ1982 ሊባኖስን በወታደራዊ ኃይል ወሮ ነበር በዚህ ወቅት የአህባሽ አንጃ እስራኤሎች ጠንካሮች እና ኃይለኞች መሆናቸውን በመጥቀስ እነሱን መውጋትም ሆነ መጋደል ሃራም ነው ብሎ /ግልጽ ያልሆነ/ ብዙዎች በቡድኑ አቋም ግርምታ ውስጥ በገቡበት በዚህ ወቅት ግርምታቸውን የሚያባብስ ሌላ ታሪክ ተፈጠረ ይኸውም እስራኤል በሊባሃስ ቡርጂ አልሃይደር የሚገኙ መስኪዶችን ት/ቤቶችን እና ሌሎችን ተቋማት አንድም ሳታስቀር በሚሳኤል ስታወድም እዛው የሚገኘው የአህባሾችን ጽ/ቤት ምንም አለመንካቷን ነበር ከዛን ወቅት በኋላም የእስራኤል የስለላ ድርጅት ወይም ሞሳድ የአህባሾችን ተቋም አስመልክቶ ደህንነታቸው ሊጠበቅ እና ምንም አይነት እድል እንዳይገጥማቸው ከሊባኖስ የደህንነት ኃይሎች መልእክት መላኩን አንድ ከፍተኛ የሊባኖስ ወታደራዊ ኃይል አጋለጠ ለመሆኑ እስራኤል ለአህባሾች ጥበቃ እንዲደረግ መሻቷ መነሻ ምክንያቱ ምንድን ይሆን ሌላም አስነዋሪ የአህባሾችን እና የአይሁዳውያንን ግንኙነት የሚያሳይ መረጃ እንመልከት ኤዲኤል ወይም አንቲ ዲፋሜሽን ሊግ የሚባል አለም አቀፍ

5D821 3078

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የአሁዳውያን ተቋም አለ ይህ ተቋም የፈለገውን በፀረ ሴማዊነት በጽንፈኝነት እና በአሸባሪነት ያስፈርጃል አሜሪካ እና ምእራባዉያን እሱ በሚጠላቸው ድርጅቶች እና ገለሰቦች ላይ የአሸባሪነት ካርድ እንዲመዙ ሙሉ መረጃከትእዛዝ ጋር ያቀርባሉ ከነዚህ ግለሰቦች መካከል አንዳንዶቹ ስም የማውጣቱን ተጠናቋል እንዲጠብቀው ሰወችን ለቃቅሞ ቂሙን የሚወጣበትን አጋጣሚ ብቻ ነው በዚህ መልኩ ኤዲኤል ስም ከሰጣቸው ሰወች መካከል አንዱ ግብፃዊው ምሁር ዶ/ር የሱፍ አልቃራዳዊ ናቸው ኤዲኤል አልቃራዳዊ ናቸው ኤዲኤል አልቃራዳዊን ቴዎሎጂያኖፍ ሄረር ወይም የሽብር ሰባኪ በማለት ፈርጇቸዋል ይህም ኤዲኤል ድህረ ገጽ www.ADL.ARG ሰፍሯል ይህም ለአይሁዳውያን በአይሁዳውያን የቆመ ተቋም የሚደግፉ እና አብረው የሚሰሩ ድርጅቶች ስም ዝርዝር በድረ ገፁ የተቀመጠ ሲሆን እንደምትመለከተትም በ4ኛው መስመር ላይ አህባሽ አሶሴሽን አፍ ኢዝላሚክ ቸሪቴብል ፕሮጀክት በማለው የእንግሊዘኛ ስሙ ሰፍሮ ይገኛል አይሁዳውያን በሚሰሩት ፀያፍ ተግባርም ተባባሪነቱን በይፋ እያሳዩ ነው በዚህ ዝርዝር ውስጥ ከአህባሽ በስተቀር ሌላ የሱኒም ሆነ ሼህ ቡድን የለም በዝርዝሩ ላይ ከአራት ያላነሱ የአይሁድ ድርጅቶች ይገኛሉ ለምሳሌ 1ኛ ፣2ኛ እና 6ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት የአይሁድ ድርጅቶች ናቸው ለግብረ ሰዶማውያን እና ለሴት ለሴት ጋብቻ መብት እንታገላለን የሚሉ ሁለት ድርጅቶችም በዝርዝሩ ላይ አሉ ይህም የሚያሳየን አህባሽ ከአየሁዳውያን ጋር ብቻ ሳይሆን የግብረሰዶማውያንን መብት እናስከብራለን ከሚሉ ድርጅቶችም ጋር ጭምር እየሰራ መሆኑን ነው እጅግ በሚገርም ሁኔታ ሜትሮ ፖሊታንት ክርስትያንስ ካውንስል ፊላደልፊያ ከሚባል ድርጅት በስተቀር አንድም ሌላ የክርስትያን ተቋም በዝርዝር ውስጥ የለም ጽዮናዊው ፒኤል ሌሎችን ለማደናገር የፈለገ ይመስል አህባሽ የተሰለፈበትን ጥምረት ኖ ሄድ ፕሮጀክት ብሎታል ጥላቻ በእኛ መሃል የለም ለማለት ነው በእውነትም በእነሱ መሃል ጥላቻ የለም አህባሽ ከአይሁዳውያን ጋር ፍቅር እንጂ ጥላቻ የለበትም ኤዲኤል የፍልስጤም ጭቁን ሕዝቦች ነፃነታቸውን እንዳያገኙ ሲታገል የቆየ ትቋም ነው ፍልስጤም አስተዳደር እራሱን እንደ አገር ለማስቆጠር ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማመልከቻውን አስገብቶ ነበር ሆኖም ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ኤዲኤል እና መሰል የአይሁዳውያን ተቋማት ከአሜሪካን ጋር በመጣመር ጥያቄው ተቀባይነት እንዳያገኝ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ከሰሞኑ የፍልስጤም አስተዳደር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አንድ ክንፍ ለሆነው ዩኔስኮ የአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ጥያቄውም ተቀባይነት አግኝቷል ሆኖም ኤዲኤል በድህረ ገፁ ላይ ባሰፈረው ጋዜጣዊ መግለጫ እንደምትመለከቱት ዩኔስኮ ፍልስጤምን በአባልነት መቀበሉ

3039

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እንዳስቀጣው እና ዩናይትድ ኔሽን ያልበሰለ እርምጃ ወስዷል በማለት ወቀሳውን ሰንዝሯል ይህም ማለት ኤድኤል እና አህባሽን የመሰሉት አጋር ድርጅቶቹ ለፍልስጤማውያን ጭቁን ሕዝባች ነፃነት በጐ አመለካከት እንደሌለው በግልጽ ያሳየናል /ግልጽ ያልሆነ/ ለቡድኑ የኢኮኖሚ አቅም በውል የሚታወቅ አደለም ምንም እንኳን አህባሾች የገቢያቸው ምንጭ ከሴት አባላቶቻቸው የሚበረከትላቸው ወርቅ ስጦታ እንደሆነ ቢገልፁም የሴት አባላቶቻቸው ጥቅም እና የሃብት መጠናቸው ተነፃጽሮ የሚባለውን አያሳይም አንጻው መላው አለም የከፈታቸው የትምህርት የመዝናኛ የአስተዳደር ማእከላት ትልቀት እና ስፋት የማተሚያ ቤታቸው 3.2 ቢሊየን ዶላር አመታዊ በጀት እና ሌሎች ሴክተሮች ላይ ያለው ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ምንጩም የጥቂት ሴቶች የወርቅ ስጦታ ነው ማለት ፍፁም የሚዋጥ አይደለም ሆኖም መሪው ሼህ አብደላህ የገንዘብ ድጋፍ ከየተኛውም የውጭ ኃይል አናገኝም ብለው አስተባብለዋል በዚህ ዶክመንሪ ውስጥ ሌላው ሳይጠቀስ የማይታለፈው አህባሾች የአለም ኡለማዎች በሙሉ በአንድ ድምጽ ከእስልምና አስተምህሮ ስለማፈንገጡ ፈቱዋ ከሰጡበት የሺአ አንጃ ጋር ያላቸው ጤነኛ የማይመስል ግንኙነት ነው ብዙዎቹ የአህባሽ ኪታቦች የሺአዎችን ኪታቦች የሺሃዎችን ኪታቦች በምንጭነት የሚጠቀሙ ሲሆን እንደ ሺሃዎች ሁሉ ከከሊፋ ወአሊ ኢብአቢቦ አሊብ ጋር የተዋጉ ሰአቦችንም መሳደብ እና መራገም ችግር እንደሌለው ይገልፃሉ የአህባሽ አንጃ በዋነኛነት አለዊ ወይንም ሰይሪያ ከተባለው ጽንፈኛ ሺ አንጻ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው ፕሬዝዳንት ሃፊዝ አልአሳድ እና እና ቤተቦቹ የዚህ እምነት ተከታይ ሲሆኑ አንጻው በእምነቱ አሊ ኢብን አቢብ ጣሊፍ በሰው መልክ የተገለፀው አምላክ ነው ይላሉ ይህ የሺሃ አንጃ በአህባሾች መስፋፋት እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦውን በሶሪያ መንግስት መሳቢብ በኩል ሲያደርግ ቆይቷል አህባሾችም በምላሹ ከሃሊፋ ወአሊ ኢብን አሊ ጠዋሪብ ጋር ውጊያ ያደረጉትም ታላቁ ሳህባ ሞአዉያን ፋሲክ ወይም አወናባጅ ብሎ በመስደብ ሙሰይሪያዎችን ለማስደሰት ሞክረዋል አህባሾች ከዚህም በላይ የሶሪያን ብሔራዊ ባእል በሰፊው ያከብራሉ የአህባሽ ቡድን ከፍተኛ አመራሮችም ከሶሪያ ባለስልጣናት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት አላቸው ሃፊዝ አልአሳድ በሞተ ወቅትም ጅምኢ የቱል መሻሪያ ይሄንን የሃዘን መግለጫ አውጥቶ ነበር አንዳንዶቹ እንደውም አህባሾች ለኢብን ተይሚያ ያላቸውን ከልክ ያለፈ ጥላቻ ሙሰይሪያዎች ካላቸው ከልብ የመነጨ ፍቅር መነሻ እንደሆነ ያስረዳሉ ምክንያቱም የሙሴሪያን አስተሳሰብ ምኡራዊ በሆነ መልኩ የነቀፈና ቀኖናውን የተቸ በመሆኑ ነው የአህባሽ አንጃ አስተሳሰብ ነፃነትን ክፉኛ ይቃረናል ለዚህም እንደማሳያ የሚወሰደው ቡድኑ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከአስተሳሰብ ውጪ የሆኑትን ሁሉ በጠላትነት ማየት ነው ሃጋይ ኤርሊችም አህባሽ ሌሎችን ሙስሊም ቡድኖችን ሁሉ በጠላትነት ማየቱን እንደበጉ ነገር ያየዋል አህባሾች ጠላት አድርገው የወሰዷቸውን አንጃዎች ከሶሪያ እና ሊባኖስ የደህንነት መስሪያቤቶች ጋር በመጣመር አደጋ ውስጥ ይከታሉ ለዚህ አላማቸው መሳካት በዋነኛነት የሚጠቀሙት ዘዴ ቡድኖቹም መጀመሪያ በአፍካሪነት እና ጽንፈኝነት መፈረጁ ነው የፍረጃቸው መሰረትም ሃሰተኛ ማስረጃ ነው ዳረል ፈትዋ የተባለው አንድ እስላማዊ ማህበር የዚህ ሴራ ሰለባ ሆነ የተለያዩ ማህበራቱ ውህደት የሆነውን ዳርል ፈትዋ ማህበር አህባሾች በመጥላታቸው ብቻ የተቋሙ ስም እንዲጠፋ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ የድርጅቱ ስም እንዲጉድፍ አድርገው ማህበሩ ለመዘጋት በቅቷል የዚህ የዳረል ፈትዋ እና ሌሎች ማህበራት አመራሮችም የግድያ ዛቻዎች በተለያዩ ወቅቶች ከዚህ ቡድን እንደተሰነዘረባቸው አስረድተዋል ሌላው የመዘጋት እጣ የገጠመው የቱሂጋውን ኢሳን የተሰኘው ማህበር ሲሆን ማህበሩ በአህባሾች ግፊት እና ስም አጥፊነት ንብረቱ በሙሉ ተወርሶ ለመዘጋት በቅቷል አህባሾችም በወቅቱ ደስታቸውን በአደባባይ ገልፀዋል ከዚህ በላይ የሊባኖስ ሙፍቲ የነበሩትን ሼህ ሃሰን ሃቢብን ከሙፍቲነት ማእረጋቸው እንዲነሱ ያደረጉ ሲሆን ከወራት በኋላም ሙፍቲው ላይ ግድያ ፈጽመዋል አህባሾች ከዚህም በተጨማሪም በቀድሞ የሊባኖስ ጠቅላይ ሚ/ር እራፊቅ አልሃሪሪ ላይ ግድያ ስለመፈፀማቸው የግድያውን ወንጀል የመረመረው አለም አቀፍ ዳኛ ፍሊስፕሊስ በሪፖርቱ አስታውቆ ነበር በወቅቱም የአህባሽ ከፍተኛ አመራሮች በቁጥርር ስር ውለው ነበር አህባሾች ይህን ሁሉ የሚያደርጉት አስተሳሰባቸው እና ቡድናቸው ብቻ ሕልውና እንዲኖረው በመሻታቸው ነው በሙስሊሞች መካከል ያለውም አንድነት እና ሰላም ጠፍቶ ነውጥ እና ሽብር እነዲነግስ በመመኘታቸው ነው የዚህ ሁሉ ሴራ ተባባሪዎቻቸው ደግሞ ምእራቡ አለም የደህንነት መስሪያቤቶች እና ሞሳድን የመሳሰሉ የስለላ ተቋማት ናቸው የዚህ አስተሳሰብ ውጤት የሆኑት አብደላ አል ሃረሪ ተከታዮች በወጉ እስላማዊ ስነምግባርን አለመላበሳቸው ሌላው አሳፋሪ ጉዳይነው በሊባኖስ እና በሌሎች የአለም አገራት የሚገኙ የአህባሽ ተከታዮች እስላማዊ የሞራል ሕግጋት በማፈንገጥ ከመስመር ያለፈ ፆታዊ ድብልቅ ውስጥ እየተዘፈቁ በባዶ ተረታ ተረት አማኝ ሆነዋል አህባሽ ቡድን አስተሳሰብ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉት እና መፃፍትንም ያበረከቱት ዶ/ር አብዱራህማን አብዲ መሸቂ የሰጡት ተከታዩ ገለፃ የአህባሽን ማህበረሰብ ማንነት በደምብ ያመላክተናል /ግልጽ ያልሆነ/ በመሪዎቻቸው ዙሪያ የገነቡት አስተሳሰብም ቢሆን እጅግ ወጣ ያለና የተለየ ነው የአህባሽ መስራች ሼህ አብደላ አልሃረሪ ኢትዮጵያ ወጥተው አረብ አገራት

3041

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከገቡ በኋላ ከስማቸው ኋላ አሽምቢ አለአበሪ የሚል ቃል በመጨመር እራሳቸውን በነብዩ ሰለላ ወአለሂ ወሰለም ዘር ተከታይ ለማድረግ ሞክረዋል በተጨማሪም ብቸኛው የሃዲስ ሊቅ ነኝ ከራማም አለኝ በማለት እራሳቸውን ከፍ አድርገው ለማስቀመጥ ሞክረዋል ሊባኖስ በደረሱ በጀመሪያዎቹ ወቅቶችም ራሳቸውን የሶማሌ የአገር ሙፍቲ አድርገው ለማስተዋወቅ ጥረት አደርገዋል ሆኖም በስዊድን የሚገኙ የሶማሌ ዜጐች መሃበር ሼህ አብደላ አልሃረረ የሚባል ሙፍቲ የሱማሌ ታሪክ እንዳልነበረ የሚገልጽ ተቃውሞ ደብዳቤ እ.ኤ.አ በ1994 ጽፈዋል ሼህ አብደላህም የሱማሌን ምድር የረገጡት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን አምነዋል በሕይወቱ የሱማሌን ምድር አንዴ ብቻ የረገጠ ግለሰብ እንዴት ብሎ የሱማሌ ሙፍቲ ሊሆን እንደሚችል ማናችንም ግልጽ አደለንም ሼህ አብደላ ተከታዮች ለመሪያቸው ያላቸው ከልክ ያለፈ ግምት ያስተዛዝባል ጣልአል በድሩ ጠለአል ሽምሱ የተለመዱ የሼህ አብደላ የሙገሳ መጠሪያዎች ናቸው በታላቁ ነብዩ መሃመድ ሰለላ ወአሊ ወሰለም የተሰጡ ነበሩ ዛሬ ግን ለሼህ አብደላ ሌሎችም ከመስመር የወጡ የክብር መጠሪያ ስሞች ለሼሁ ተሰጥቷቸዋል በተለያዩ ወቅቶች ሼህ አብደላ ጨረቃ ላይ ታዩ በረሩ የሚሉ የበሬ ወለደ ፈጠራዎች የጊዜው የተከታዮቻቸው ይወራሉ እስቲ ቪዲዮውን ይመልከቱ ሕንፃ ስር ካረፈው የሼህ አ ብደላ አልሃረሪ አስከሬን አፈር እየተቆጠነረ በተከታዮቻቸው ሲከፋፈል ይታያል አብደላ አልሃረሪ የፈጠሩትን ማህበረሰብ ለመግለጽ ከዚህ የተሻለ ምን ማስረጃ ይኖራል /የማይሰማ/ የተባለው አጥፊ ቡድን ሙስሊሙን እርስ በእርስ ለማበጣበጥ በዋነኛነት የሚጠቀመው ዘዴ አወዛጋቢ አጀንዳዎችን መምረጥ ነው በተለይ ደግሞ ሙስሊም ኡለማዎች እስካሁን ያልተስማሙባቸውን እምነት ነክ አጀንዳዎች እያጣመሙ በማንሳት ሕዝባዊ ውዝግብ ለመፍጠር ይሞክራሊ ከነዚህ መሰል አጀንዳዎች መካከል ዋነኛ መጠቀሚያቸው የአላህ ስሞች እና ባህሪያትን የተመለከተ ነው አዎን አይሁዶች ምን ጊዜም ሙስሊሞች የሚጣሉባቸውን አጀንዳዎች ከመፍጠር ቦዝነት አያውቁም የሰማያት እና የምድር ፈጣሪ ሁሉም ተንከባካቢ እና አንዋሪ የሆነው ታላቁ ጌታቸው አላህ ከጉድለት ሁሉ የጠራ እና የማይመረመር ጌታ ነው ፍጡራን ስለሱ እራሱ ከነገራቸው ውጪ ተመራምረው ሊደርሱበት የሚችሉት ጌታ አደለም ታላቁ ነብይም ሰለላ ወአሊ ወሰለም ስለ አላህ አትመራመሩ ይልቁንም ስለ አለህ ፍጡራን ተመራመሩ ሲሉ ወሰን ያስቀመጡልንም ውሱን ሰብአዊ አእምሮ ተጠቅመን አላህን በመመርመር መንገድ እንዳንሄድ ነበር ይህ አህባሽ የሚባል ቡድን ግን ለኢስላም እና ለተውሂድ ያሰበ በመምሰል በአላህ ባህሪያት ዙሪያ መመራመርን የሁል ጊዜ ልምዱ አድርጓል መሰረታዊ የእስልምና እውቀት ያላሟላውን እና ከኢልም

3042 SD88

http://ethcriminalawnetwork.com/

መድረክ የራቀውን ሙስሊም ወደዚህ ጥልቅ እውቀት የሚጠይቅ የኢልም ዘርፍ ጐትቶ በመዝፈቅ የሙስሊም መሆን አለመሆን መለያ ያደርጉታል የፈተናው ሼህ አብደላ አልሃረሪ ድካሞች የተሞሉት የአላህን ባህሪያት በመመራመር ላይሲሆን ከነሱ ውጪ ያለውን አስተሳሰብ በሙሉ የካፊር እያሉ በመግለጽ ታላላቅ የአለም ኡለማዎችን ለማክፈር መሣሪያው ያደርጉታል ይህንን የሚያደርጉት ለተውሂድ ተጨንቀው ከመሰሎት በእርግጥ ተሳስተዋል ለተውሂድ አንዳችም ጭንቀት እንደሌላቸው ለማወቅ የአለም ኡለሞች ሽርክ ናቸው ሲሉ የፈረጇቸውም በርካታ ተግባራት በተድበሰበሱ መረጃዎች እያሳበቡ ሃላል ማድረጋቸውን ማወቅ ይበቃል በተጨማሪም የቡድኑ ተከታዮች በተደጋጋሚ የሚታይበት እና በቀብር አካባቢ የሚፈጽሟቸው ሕገወጥ ተግባራት ለተውሂድ ግድ እንደሌላቸው በእርግጥም ያሳያሉ በተቃራኒው ኡለማዎች ያልተስማሙባቸውን /ግልጽ ያልሆነ/ ጌታ አደለም ታላቁ ነብይም ማወቅ ይበቃል በተጨማሪም የቡድኑ ተከታዮች በተደጋጋሚ የሚታዩበት እና የጅብሪል እንጂ የአላህ ቃል አይደለም በማለት ስለ አላህ ባህሪያት የሚያወሩ በማስመሰል ብዙዎችን ያሳስታሉ ትንሽ ቂራት ላለው ሰው አጀንዳው ከላይ እንደሚታየው ቢመስለውም ዋነኛ አላማቸው ግን ተራው ሕብረተሰብ በቁርአን ያለው ጥብቅ እምነት እንዲሸረሸር ትክክለኛነቱም ላይ ጥርጣሬ እንዲገባው ማድረግ ነው አላህ ይጠብቀን ሜክሲኮ ቡና እና ሻይ አካባቢ በሚገኘው እና በተለምዶ ጀርመን ግቢ ተብሎ በሚጠራው ተባረክ መስኪድ የተፈጠረውን ያስታውሱ አንድ ዳኢ ስለ ቁርአን እያስተማረ ነበር ቁርአን የአላህ ቃል መሆኑን እና ይሄንን የሚያስተባብሉ ሰወች ትክክል አለመሆናቸውን ልክ መናገር ሲጀመር ይህ ቶታል ጦርሃይሎች በሚገኘው የአህባሾች መሃከል የምረቃ ስነስርዓት ላይ /የማይሰማ/ ሙስሊሙን መሪ አልባ ለማድረግ እና ሕዝቡን ከመሪዎቹ ለመነጠል ይህንን ቡድን እስከ ጥግ እንደተጠቀሙበት ላስተዋለው ሁሉ ግልጽ ነው የፈተናው ሼህ አብደላ ሃረሪም ሆኑ ተማሪዎቻቸው ዋነኛ ስራ የአለም ኡለማዎችን በጅምላ ማክፈር ነው ፊት ለፊታችሁ የምታዩት መጽሃፍ ተአውነ አለምነ ኢአልን ሙንከር የሚባል የፈተናው ሼህ መጽሃፍ ሲሆን በዳለር መሸራሪያ በ2009 ለ4ኛ ጊዜ የታተመ ነው በርካታ የአለም ኡለማዎችም መጽሃፍ ሳይለዩ ያከፈሩበት አደገኛ መጽሃፍ መሆኑ አልቀረም ከነገሌ አስተሳሰብ ማስጠንቀቂያ እየተባሉ ማውጣው ላይ የተዘረዘሩ ስሞችን ከላይ እስከታች እስቲ ዘርዘር እያደረግን ያከፈሯቸውን ኡለማዎች ለማየት እንሞክር ማክፈር የሚጀምሩት ከቀደምት ብርቅዬ ኡለማዎች ነው አለም ሼህ ኡል ኢስላም ሲል ያሞገሳቸውን ታላቅ /ግልጽ ያልሆነ/ ገጽ 30 ይመልከቱ /ግልጽ ያልሆነ/ ሼህን እስላም ብሎ የጠራ ሁሉ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ካፊር ነው የሚል ጥቅስ ተቀምጧል የአላህ በዚህ ጥቅስ ብቻ ምን ያህል ሚሊዮን ሙስሊም እንደከፈረው ያስቡት ሼህን እስላም የሚለውን መጠሪያ ከቀደምትም ከአሁኖችም /ግልጽ ያልሆነ/ የተጠቀሙት ብዙ ሺህ ናቸው ሁሉም በጅምላ ሲከፍሩ /ግልጽ ያልሆነ/ አሁንም ገጽ 37 ይመልከቱ እነሱ ወሃብያ እያሉ የሚጠሩት ስለ ፊያደአዋ ተከታዮች በሙሉ ካፊር መሆናቸውን እንደቀልድ ይገልፃል ካፊሮች ናቸው የሚለውን አዩት እውን እላም እንዲህ የሚቀለድበት ሃይማኖት ነበርን /ግልጽ ያልሆነ/ ቡድኑ የሚያከፍረው ሰለፊያን ብቻ መስሎ ከሆነ በእርግጥም ተሳስተዋል አይሁዶች የሚፈልጉት በሙስሊሙ መሪ አልባነት እንጂ ተውሂድን አደለም እና ታላላቅ የአለማችንን ሱፊያ ኡለሞች ሲያከፍሩ ተመልከቱ ሼህ ሙተወል ሼህ አረዊ እጅግ ታዋቂ ግብፃዊ የሱፍ ኢያሊም ናቸው ይልቁንም ብዙዎች እንደሱፊያ አሊም መሪ ያህል ይቆጥሯቸዋል የፈተናው ሼህ በዛው ጦሰኛ መጽሃፋቸው ገጽ 63 ሼህ ሸህ አራዊ ጽፈዉታል ያሉትን ንግግር በመጥቀስ ከኩፍርም ኩፍር ነው ሲሉ ተመለከቱ የአላህ አካል የሰጠ ሙጀሲም ካፊርነው የሚለውን የቀደምት ኡለሞች መርህ በተሳሳተ መልኩ በመጠቀም እና ሁሉም ኡለሞች ላይ በመለጠፍም ቆጥረን የማንዘልቃቸውን የአለም ታላላቅ ኡለሞችን አከፍራሉ እነአሊላሂ ወኢና ኢለሂራጂያሁ ሰኢድ እረመዳን አልሙጢ ሌላው እጅግ ታዋቂ የሱፊያ መስመር አሊ ናቸው ታላቅ ሱፊ መሆናቸው ግን ከፈተናው ሼህ የኩፈር በትር አላዳናቸውም አንድ ምእራፍ ለእርሳቸው በመተው ስለ ኩፍራቸው ይዘረዝሩልናል ከውጪ ለሚያየው በእርግጥም የፈተናው ሼህ አሊም የሚባል እንዳይኖር የሚመኙን ይመስላሉ ገጽ 65 ላይ ይመልከቱ ሼህ ናሆም ብለውታል ያሉትን ቃል ከተለመደው ፍልስፍና ጋር በማያያዝ ካፊር ሲሉ ይፈርጃሉ ከቶ ማን ሊሊቀድሁም ደማስቆ ታዋቂ ሱፊያሊም ሼህ እረጀብ ዲብም ከቁፍር አልተረፉም አንድ ምእራፍ ተዘጋጅቶላቸው ኩፍራቸው ከተዘረዘረ በኋላ እንደነዚህ አይነቶቹ መክፈራቸውን አለመናገር እንዴት ሃላል ይሆናል በሚል መጠይቅ የኮፈር ችሎቱ ይዘጋል ሱህሃላህ የየመን ቻናሎችንም ሆነ ሂቅራ የተባለውንየሳተላይት ጣቢያ የተከታተለ ታላቁ ሙፍቲያ አሊም ሼህ ሃቢብ አሊ ጀፍሪል አይስታቸውም የፈተናው ሼህ ግን በገጽ 38 ጀስምን ያላከፈረ እራሱ ካፊር ነው ሲሉ በሶፊያው አለም የኩፍራቸውን መርዶ ይነግሩታል የኩፍሩ በትር በዚህ የሚያበቃ ከመሰሎ አሁንም ተሳስተዋል ሱፊያውን የአስተሳሰብ መስመር ወክለው በርካታ መጽሃፎችን ለአለም ያበረከቱትን ስኡደውን ሱፊ ዶ/ር መሃመድ አእረዊ የሙፍቲ አንድ መቶኛ እንኳን አይሞላም ሙስሊሙ ሲያንንጥጧቸው በገጽ 97 ይመልከቱ በተጨማሪም ፈትናው ሼህ በ1996 ዳረል መሽራሪ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ባሳተሙት አስቶሱሚያ በተባለው መጽሃፋቸው 3ኛ እትም የጃኒያን ጣሪቃ በግልጽ ሲያወግዙ እና ከእስላም ሲያስወጡ ተስተውለዋል እስክሪኑ ላይ እንደምትመለከቱት በገጽ 223 አሉላ ፊሪቃዎች በሙሉ ቁርአን እና ከሃዲስ ጋር የሚስማሙ ናቸው ከቱጃኒያ ጣሪቃ በስተቀር ያሳተሟቸው መጽሃፍት በግልጽ ከቁርአን እና ከሃዲስ ጋር ይጋጫሉ በማለት እንከተለዋለን ከሚሉት ሱፊያ ማህበረሰብም ጋር እንኳን ፍፁም ስምምነት እንደሌላቸው እና ማንንም ከማውገዝ እንደማይመለሱ ለማየት እንችላለን ሱሚ ፎረም የተባለው የውይይት ድረገጽ ላይ በተጠቀሰው መሰረት የሚከተሉት የሱፊያ ጠሪቃ ኡለሞች በበፊፍናው ሼህ አብደላ ሃረሪ ካፊር እንደሆኑ የታወጀባቸው ናቸው ሼህ ሰኢድ ፈውባ ሼህ ሃምዛ የሱፍ የሼህ ናዚ ማልቁብሮሲ መቅሸበንዲ ሃቅፋኒ ጣሪቃ ሼህ ጅብሪል ሃዳድ ሼህ ሊሻን ከባኒ ሼህ አህመድ አልአረዊ ሻዝሊያ ጦሪቃ ኡለሞች ማለትም ሼህ መሃመድ አልሃሽኒ ሼህ አብዱል ቃድር ኢሳ ሼህ አህመድ ጃሚር ሼህ አብዱራህማን አሽሆሪ ሼህ ኑህ ኬለር ሼህ ፋራህ ዘረባኒ ሼህ አቡበከር ሲራጅ ውዲን ሼህ አብዱልቃድር አሶፊ ሼህ አህመድ ቲጃኒ እራሳቸው በቀር የቲጃኒያ ኡለሞች በሙሉ ባርሊቪ እና የድሮ ባኒዲ ጣሪቃዎች በሙሉ በቁፍር ተወግዘዋል እነዚህን ሁሉ የሱፊያ ኡለሞች አክፍረውልን ፈተናው ሼህ ሱፊያ እንደሆኑ ይናገራሉ ሲሃላላ እውን የሚያምናቸው ይኖር ይሆን የተባለው በቡድኑ ድረገጽ ላይ የሚገኘው ፈትናው ሼህ ታህቢር አሸደኢህ አልዋጅብ የተባለ መጽሃፍ በርካታ የአለም ኡለሞችን እንደተለመደው በማውገዝ እና በማክፈር እንዲሁም በመኮነን በስራ የተወጠረ ሆኖ እናገኘዋለን እስክሪኑ ላይ እንደምትመለከቱት በሃሰት ላይ የሚሰነዘር ምላሽ በሚል ምእራፉ የበርካታ ኡለሞችን እና ኪታቦችን ስም በመዘርዘር ሰወችን ያስጠነቅቃሉ አለፍ አለፍ እያልን እንያቸው የታዋቂ የተበሲል መጽሃፍ አንዱ የሆነውን ታፍሲር ዘማህሸሪን እንደምታዩት ግልጽ ኩፍር ያለበት ሲዲ ሲል ይፈርጀዋል እዚጋር ደግሞ ከሼህ ኢብራሂም ኢዝዋሚ ኢምእረዋኒ ዲህ እና መሃመድ ኢምሉም ሙሰና ንግግሮች እንድንጠነቀቅ ይረዳናል አለፍ ብሎ ደግሞ ለዘዋሂርያ መዛሃፍ መስራች ከሆኑት አልሃፊዝ ኢምናሃዝ መዛሂሪ መጽሃፍት እጅግ እንድንጠነቀቅ አደራ ይሉናል ካምላኩ ናኢሊም ኢብንእሩሽድም በስም በመጥራት በድጋሚ ተጠንቀቁ ይለናል ግልጽ ኩፍር አለበት ሲል ደግሞ ከሼህ አራኒ እጅግ ታዋቂ ኪታብ አልሙናጃ ቱልኩብራ እንድንጠነቀቅ ይነግረናል ይኸው የፊትናው ሼህ ረደኛ ኪታብ ኢንሳኑል ካሚ የተባለው የሼህ አብዱል ከሪም አልጀኢሊ ኪታብ እና ሼህ አብዱል ቃድር አልሂምሲ አሻዝሊ ያዘጋጁት ኦሚደን ነብይ የተባለው ስለ መውሊድ የሚያወራው ኪታብ ከተወገዙት ውስጥ ናቸው ታላላቅ ያሃበሻ ሱፊ ኡለሞችም ከዚሁ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ኪታብ ሳይወገዱ አሳለፉም በ15ኛ ክፍለ ዘመን ታላቁ የሃረር ሼህ ኒብራስ የተዘጋጀው አልፍ ኪሳሳት አለን ነቢ የተባለው ኪታብ እንደተለመደው ኩፍር የያዘ ሲል ተወግዟል በሼህ መሃመድ አቢይ ወፋ አል ሃለቢ የተዘጋጀው መውሊድ አልነቢ የተሰኘ ኪታብ እና ኢብ ሃጀራል ሃተሚ ይርመቱልኩብራ አለል አለሚ የተሰኙት ሁለት ኪታቦችም እንደዚሁ ተወግዘዋል የሃረሩ ሼህ ሃሺም ኢልና ኦብዱላዚዝ አልሃረሪ ፊትሁሩህማን ሁሰላት አላኢሽሬል ነውኢል ኢንሳኒ የተባለ ኪታቢም እንዲሁ ከውሰት በትር አልተረፈም የሼህ ኢምለቀይም አልጀውዚ እና የሺህ ሰይድ ስራቢቅ ክታቦችም እንዲሁ የተጠቀሱ እና የተወገዙ ሲሆን ሌሎችም በርካታ ታዋቂ ኡለሞች እና መፃህፍቶቻቸው ተዘልፈዋል ሱንሃነላህ ከሼሁ የውግዘት በትር የሚተርፈው ከቶ ማን ይሆን /ግልጽ ያልሆነ/ በአህባሽ አጥፊ ፍልስፍና ችሎት ኩፍር ተበይኖባቸዋል አምስት ሚሊየን አባላት ያሉትም ሱና ኦል ሃያት የተባለ የበጐ ምግባር ድርጅት የሚመራው እና ወደ አዋው የወጣቱን ቀልብ መቆጣጠር የቻለው ጋእይ አምርሃሊድ ኩፍር ከተበየነባቸው አንዱ ነበር ጀሲ የሚል ስም እንደተለመደው ተለጥፎበታል ኩፍር እውነትም እንዴት ቀላል ሆኗል የአለም ኡለሞች ማህበር ፕሬዝዳንት የሆኑት ዶ/ር የሱፍ አልቃራባዊ ከዚህ አህባሽ ከተባለ ጀመአ ውግዘት አልተረፉም የፈተናው ሼህ ሰውን በሆነ ባልሆነው ከማክፈር የሚቆጠበው የሱፍያ አካል /ግልጽ ያልሆነ/ አምስት ሚሊየን አባላት ያሉትን ሱና ኦል ሃያት /ግልጽ ያልሆነ/ አምስት መቶ ያህል ድርጅታዊ ፈትዋዎች ዶ/ር ዛኪር መክፈራቸውን ገልፀዋል ዶ/ር ዛኪር በቁርአን እና በሃዲስ ላይ ይዋሻሉ እና ሌሎችንም በርካታ ዉግዘቶችን በመሰንዘር የዶ/ር ዛኪርን ካፊርነት ይገልፃል አላህ ይጠብቀን ለሚሊዮኖች የሂዲሃያት ሰበብ የሆነን ታላቅ ዳኢ ማክፈር በእርግጥስ ከአይሁዶች በቀር ከየት ይመነጫል /ግልጽ ያልሆነ/ ውግዘት ከደረሰባቸው እና ኩፍራቸው ከታወጀላቸው እጅግ ጥቂቶቹ ናቸው ዛኪርን የማያውቅ ሙስሊም አለ ለማለት በእርግጥም ይቸግራል አዎ እኒህ ከእስላም ጀግና ዳኢዎች ውስጥ በግምባር ቀደምነት የተሰለፉ ዳኢ የምእራቡን አለም እጅጉን መሳብ የቻሉ ሙስሊሞችን አንገት በኩራት ቀና ያደረጉ እና ለእስላም ጥብቅና የቆሙ መሆናቸው አለም አቀፍ እውቅና ያስቸራቸው ሲሆን ላቋቋሙት ፒስ ቲቪ ለተባለ የዳእዋ ሳተላይት ጣቢያ ከአንድ መቶ ሚሊየን በላይ ተመልካቾች እንዳሉት ይነገርለታል ሲፊያ ኦን ላይን ዶት ኮም የተባለው እና የፊትናውን ሼህ ድርጅት ኤአይ ሲፒን ከዋነኛ ተባባሪዎቼ አንዱ ሲል በ4ኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጠው የሼሁ ተማሪዎች ያቋቋሙት ድረ ገጽ ግን የዶ/ር ዛኪርን ካፊርነት ይነግረናል ይኸው ድረገጽ ከታታላቅ የእስላም ኡለሞች ዋነኛው ሲል ያስቀመጣቸውን ሼህ አብደላ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሃረሪን አሲን ለሉለሞች ተምሳሌት ኢማም ሞሃዲስ አአቢድ እያለ የሌላቸውን ማእረግ እያሸከመ ቢያቆላምጥም ዶ/ር ዛኪርን በኩፍር ለማውገዝ ግን በጭራሽ አይሰንፍም ድረገፁ እጅግ ብዙ ነጥቦችን እየጠቀሰ የተወዳጁን ዳኢ መክፈር በግድ ሊግተው ይሞክራል እንደምታዩትም ዶ/ር /ግልጽ ያልሆነ/ አምስት መቶ ያህል ድርጅታዊ ፈትዋዎች ዶ/ር ዛኪር መክፈራቸውን ገልፀዋል ዶ/ር ዛኪር በቁርአን እና በሃዲስ ላይ ይዋሻሉ እና ሌሎችንም በርካታ ውግዘቶችን በመሰንዘር የዶ/ር ዛኪርን ካፊርነት ይገልፃል አሳህ ይጠብቀን ለሚዮኖች የሂዳያት ሰበብ የሆነን ታላቅ ዳኢ ማክፈር በእርግጥስ ከአይሁዶች በቀር ከየት ይመነጫል ከፍተኛ የአስተሳሰብ እና የፖለቲካ ድጋፍ የሚደረግለት የአህባሽ ቡድን የሕዝበ ሙስሊሙን አንድነት ለመበታተን ከሚጠቀምበት መንገድ አንዱ ወሃቢያ ብለው የሚጠሩት አካል ላይ ሰወችን መቀስቀስ ነው በቁጥር ብዙ የሆነው የሱፊ ማህበረሰብ ወሃብያ የሚሉትን ቡድን እንዲጠላና እንዲያከፍር ያነሳሳሉ በተለይ ደግሞ በሰለፊያ እና ሱፊያ የአስተሳሰብ መስመሮች መካከል ፍትጊያ በነበረበት አገር ሲገቡ ዋህብያን ለማጥፋት ነው የመጣነው የሚል ሽፋን በመጠቀም አንዱን ሙስሊም ሌላው ወንድሙ ላይ ያነሳሳሉ እውነታው ግን ሌላ ነው እነሱ የእስልምና ጠላት እንጂ የዋህብያ ጠላት አይደሉም ሶፍያ ነን ይላሉ እንጂ ሰውን በሆነ ባልሆነው ከማክፈር የሚቆጠበው ሶፍያ አካል በጭራሽ አይደሉም የሶፍያ መስመር ሃሳብ አመንጪ እና መሪ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ኢማም አቡሃሚድ አለሳዛሊ አንድን ሰው በስህተት ካፊር ከማለት አንድ ሺ ሰወችን በስህተት ሙስሊም ማለት ይሻላል ማለታውን ልብ ይለዋል ከዚህም ሌላ የሶፍያ አስተሳሰብ መስመር ሰወች የራሳቸውን ነውር ወደማየት የበለጠ የሚጠመዱበት እንጂ አሁን አህባሽ እንደምናየው በሆነ ባልሆነው ሰወችም በጅምላ የሚያከፍሩበት አይደለም በተጨማሪም አህባሾች ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የአለማችን ታላላቅ የሱፍያ ኡለሞች ያከፍራሉ ያንጓጥጣሉ ክብር የነካሉ የታወቁ የሱፍያ እምነቶችን በማውገዝም ይታወቃሉ ጥቂት ጥቅሶችን ማየት እንችላለን ሶሪሁልበያን ገጽ 83 እስክሪኑ ላይ እንደምታዩት ሶፍያዎችን ሲያንጓጥጥ ይመልከቱ ከሱፍያ ጃሂሮች ከፊሎቹ ከያዙት አስቀያሚ ድፍረት አንዱ የሚለውን ተመልከቱ ገጽ 84 ይመልከቱ /ግልጽ ያልሆነ/ ያለው እነዛ ሸሪያን ከማይጠብቁ ሱፊዎች ይጠንቀቅ የሚለውን ይመልከቱ እውን እስላም ያስቀመጠው የመተራረሚያ መንገድ ይህ ነውን ከዚህም በላይ የፈተናው ሼህ አብደላ ሃረሪ ትላልቅ የሱፍያ እምነቶችን አጥፊ የሚል ስም በመስጠት መልስ ለመፃፍ መጽሃፍ እስከማሳተም ደርሰዋል በዚህ መልኩ ሱፊዮችን እያንጓጠጡ ግን መልሰው ሱፊዮች ነን ወሃብያን እንጠላለን በማለት ሙስሊሙን ለማታለል ሞክረዋል እነዚህ አጥፊ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሃረሪን አሲን ለኡለሞች ተምሳሌት ኢማም ሞሃዲስ አአቢድ እያለ የሌላቸውን ማእረግ እያሸከመ ቢያቆላምጥም ዶ/ር ዛኪርን በኩፍር ለማውገዝ ግን በጭራሽ አይሰንፍም ድረገፁ እጅግ ብዙ ነጥቦችን እየጠቀሰ የተወዳጁን ዳኢ. መክፈር በግድ ሲግተው ይሞክራል እንደምታዩትም ዶ/ር /ግልጽ ያልሆነ/ አምስት መቶ ያህል ድርጅታዊ ፈትዋዎች ዶ/ር ዛኪር መክፈራቸውን ገልፀዋል ዶ/ር ዛኪር በቁርአን እና በሃዲስ ላይ ይዋሻሉ እና ሌሎችንም በርካታ ውግዘቶችን በመሰንዘር የዶ/ር ዛኪርን ካፊርነት ይገልፃል አሳህ ይጠብቀን ለሚዮኖች የሂዳያት ሰበብ የሆንን ታላቅ ዳኢ. ማክፈር በእርግጥስ ከአይሁዶች በቀር ከየት ይመነጫል ከፍተኛ የአስተሳሰብ እና የፖለቲካ ድጋፍ የሚደረግለት የአህባሽ ቡድን የሕዝበ ሙስሊሙን አንድነት ለመበታተን ከሚጠቀምበት መንገድ አንዱ ወሃቢያ ብለው የሚጠሩት አካል ላይ ሰወችን መቀስቀስ ነው በቁጥር ብዙ የሆነው የሱፊ ማህበረሰብ ወሃብያ የሚሉትን ቡድን እንዲጠላና እንዲያከፍር ያነሳሳሉ በተለይ ደግሞ በሰለፊያ እና ሱፊያ የአስተሳሰብ መስመሮች መካከል ፍትጊያ በነበረበት አገር ሲገቡ ዋህብያን ለማጥፋት ነው የመጣነው የሚል ሽፋን በመጠቀም አንዱን ሙስሊም ሌላው ወንድሙ ላይ ያነሳሳሉ እውነታው ግን ሌላ ነው እነሱ የእስልምና ጠላት እንጂ የዋህብያ ጠላት አይደሉም ሶፍያ ነን ይላሉ እንጂ ሰውን በሆነ ባልሆነው ከማክፈር የሚቆጠበው ሶፍያ አካል በጭራሽ አይደሉም የሶፍያ መስመር ሃሳብ አመንጪ እና መሪ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ኢማም አቡሃሚድ አለሳዛሊ. አንድን ሰው በስህተት ካፊር ከማለት አንድ ሺ ሰወችን በስህተት ሙስሊም ማለት ይሻላል ማለታውን ልብ ይለዋል ከዚህም ሌላ የሶፍያ አስተሳሰብ መስመር ሰወች የራሳቸውን ነውር ወደማየት የበለጠ የሚጠመዱበት እንጂ አሁን አህባሽ እንደምናየው በሆነ ባልሆነው ሰወችም በጅምላ የሚያከፍሩበት አይደለም በተጨማሪም አህባሾች ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የአለማችን ታላላቅ የሱፍያ ኡለሞች ያከፍራሉ ያንጓጥጣሉ ክብር የነካሉ የታወቁ የሱፍያ እምነቶችን በማውገዝም ይታወቃሉ ጥቂት ጥቅሶችን ማየት እንችላለን ሶሪሁልበያን ገጽ 83 እስክሪኑ ላይ እንደምታዩት ሶፍያዎችን ሲያንጓጥጥ ይመልከቱ ከሱፍያ ጃሂሮች ከፊሎቹ ከያዙት አስቀያሚ ድፍረት አንዱ የሚለውን ተመለከቱ ገጽ 84 ይመልከቱ /ግልጽ ያልሆነ/ ያለው እነዛ ሸሪያን ከማይጠብቁ ሱፊዎች ይጠንቀቅ የሚለውን ይመልከቱ እውን እስላም ያስቀመጠው የመተራረሚያ መንገድ ይህ ነውን ከዚህም በላይ የፈተናው ሼህ አብደላ ሃረሪ ትላልቅ የሱፍያ እምነቶችን አጥፊ የሚል ስም በመስጠት መልስ ለመፃፍ መጽሃፍ እስከማሳተም ደርሰዋል በዚህ መልኩ ሱፊዮችን እያንጓጠጡ ግን መልሰው ሱፊዮች ነን ወሃብያን እንጠላለን በማለት ሙስሊሙን ለማታለል ሞክረዋል እነዚህ አጥፊ

3048

SD94

http://ethcriminalawnetwork.com/

ቢናገሩም የሚሰነዝሯቸው ሃሳቦች ግን በሻህብይ የመረጃ ማበጠሪያ ዘዴ የተጣሩ አደሉም በአንድ ብይን ውስጥ ብቻ የሻህሪያ ወደ ሃምበሊያ ከማሊኪያ ወደ ሃለፊያ በመዝለል ወጣ ያለውን እየመረጡ ያስቀምጣሉ ቆየት ብለለን በምሳሌ እንደምናየው መዛህፍየለሽነትን ያበረታታሉ ሰውየው በዚህ ጀና በሌሎች ኪታቦቻቸውም ጭምር አሻሚ ገለፃዎችን መጠቀምን በማዘውተር /ግልጽ ያልሆነ/ እራሱ የሺአው አለም ስለ መጽሃፉ ኪቢዲያ የተባለው ድረገጽ ላይ ባስቀመጠው መረጃ መሰረት ግን መጽሃፉ የሰነድ ፍተሻ በጭራሽ አልተደረገበትም መልእክቱ ትክክለኛ ስለሆነ ሰነዱ ሊፈተሽ አይገባም ከሚል የተቀመጠውን የሺአ ኡለሞች ገለፃ እራሶ ከፍተው /ግልጽ ያልሆነ/ ሼሁ የሺአ ዘገባዎችን የሱኒ አስመስለው ሲጠቀሙ አላህን አይፈሩም ይህ በጊዮናውያን አይሁዶች ከፍተኛ ድጋፍ የሚደረግለት ቡድን ሊያስፋፋ የሚችለውን ጥፋት እንረዳ ዘንድ በሼህ ተብዬው አብደላ ሃረሪ ሁለት ኪታቦች የተጠቀሱ ነጥቦችን ማየት ብቻውን በቂ ነው ቁርአንን /ግልጽ ያልሆነ/ ድሮ ነበር ከዚህም አንዱ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ነው ከሱፍያው አለም ውጪ ያሉ /ግልጽ ያልሆነ/ ወጣ ያለውን እየመረጡ ያስቀምጣሉ በደረሰ ሰነድ ተዘግቧል በማለትም ሃሰትን ይጽፋሉ ሱፍሃናላህ መጽሃፉ በሱኒው አለም በጭራሽ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ሳለ በሱኒው መጽሃፍ እንዲመስል ሙክተሲል የሆነ ዘገባ የሚል ካርድ አልተለጠፈበትም እራሱ የሺአው አለም ስለመጽሃፉ ኪፒዲያ የተባለው ድረገጽ ላይ ባስቀመጠው መሰረት ግን መጽሃፉ የሰነድ ፍተሻ በጭራሽ አልተደረገበትም መልእክቱ ትክክለኛ ስለሆነ ሰነዱ ሊፈተሽ አይገባም በሚል የተቀመጠውን የሺአ ኡለሞች ገለፃ እራሶ ከፍተው ያስተኙ ሼሁ የሺአ ዘገባዎችን የሱኛ አስመስለው ሲጠቀሙ አላህን አይፈሩምም ይህ /የማይሰማ/ ቡድን ሊያስፋፋ የሚሻውን ጥፋት እንረዳ ዘንድ የሼህ ተብዬው አብደላ ሃረሪ ሁለት ኪታቦች የተጠቀሱ ነጥቦችን ማየት ብቻውን በቂ ነው ቁርአንን በሚሃልፍ ግልጽ መልስ /ግልጽ ያልሆነ/ በሚል ያዘጋጁት ሶሪ ሁልበያን እና ሁኡ የቁቅጠዋሊን የተባሉትን ሁለት ኪታቦች ነክሰን ምሳሌዎችን እንመልከት ሰይድ ኡልበያን አራተኛ እትም ባረል መሻሪ በ2002 ያሳተመው ሲሆን /ግልጽ ያልሆነ/ ጥራዝ አንዱ የ2003 እትም ጥራዝ 2 ደግሞ በ2007 እትም ናቸው /ግልጽ ያሆነ/ የምእራፍ እርእስ ይመልከቱ አላህ አማኞች እንዲያምኑ ካፊሮችም እንዲከፍሩ ያግዛቸዋል ይላል ይህንኑ ሃሳብ ለማብራራትም ላይና እታች ይወርዳል ሕዝብን የሚያደናግሩ የፍልስፍና ሃሳቦችን በማንሳትም ይጠቃቀሳሉ ሱፃናላህ ከዚህ ነጥብ ምን ተፈልጉልን ይሆን ለሙስሊሞችስ ምን እንዲጠቀሙ ይሆን ይህ የሚሻራቸው ኩፍርን እንዲቀበሉ ያላህ እገዛ ነው እንዲሉ አላህ ይጠብቀን እናና የአፈራ ስሌትን ይለግመዱበታል

3049 MR

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ነብዩም የኢባዳ መቅሲ ሲሉ ጠርተውታል ከቶ ያለ ዱአ ምን ይሳካል እርስኦ የአላህን እዝነት እና ማርታ ይመኛሉ ለራሶ የወደዱትን ለሌሎች በመውደድም አላህ ሙስሊሞችን በሙሉ እንዲምር ጀነት እንዲያስገባ ይጠይቁታል የፈተናው ሼህ አብደላ ሃረሪ ግን ይህ ዱአ ከቁርአን እና ሃዲስ ጋር ይጋጫል አረ እንደውም ያከፍራል ይሉታል ያንኑ መጽሃፍ ጥራዝ 1 ገጽ 194 ይመልከቱ አላህ የምእመናን እና ምእመናትን ወንጀል በሙሉ እንዲምር መጠየቅ ሃራም ነው የሚል የምእራፍ እርእስ ያፈጥቦታል ዝቅ ሲሉ ደግሞ ከነጭራሹ ኩፍር በማለት ይኮንነዋል ከቶ ሙስሊሞች ለምህረት ዱአ ቢያደርጉ አይሁዶች ምን ይጐዱ ይሆን የአህባሽ አስተምእሮ ቀደምት የሃገራችንን ኡለሞች እነአይንን እና እነዳንኘን እንደማይቃረን ይነግረናል ነገር ግን አንይም ሆነ ዳኒ በመንዙማዎቻቸው አዘውትረው የሚያደርጉትን /ግልጽ ያልሆነ/ ሙስሊማት የሚለውን ዱአ ኩፍር ሲል ይፈርጀዋል አንይ እና ዳንይ ሌሎችም መንዙማ የሚሉ ሼሆች ካፊር ናቸውን ታላላቅ የሱፍያ ሼሆችን እያከፈሩ ሱፊ ነን ሲሉ አያፍሩምን እስልምና መሰረት ነው የኢስላም ህንፃ በእርግጥም በአምስቱ አእማዶች ላይ ተገምብቷል የአህባሽ አስተሳሰብ ግን ይህንን ሕንፃ ለመናድ የሚሞክረው በአስመሳይነት ነው ሕልም ነክ የሚመስሉ አጀንዳዎችን በማንሳት ሙስሊሙን ወደ ረፍላ እና ዝንጋጤ ይቀራል ጥቂት ጥቦችን እንይ ጳሕራ የኢማን ግማሽ ነው ሰላት ደግሞ የዲኑን ምሰሶ እና የእምነት ለና ኩፍር መለያ ነዳባ ባለበተ ሰላት እንደማይሳካም ማንም ሙስሊም የሚያውቀው እውነታ ነው ከአህባሾች በቀር የፈተናው ሼህ አብደላ ሃረሪ ቡእየቱታሊድ በተባለው መጽሃፋቸው ጥራዝ አንድ ገጽ 232 ይህንን በዘመናት ያወቅነውን እውነታ በማሊ ኪያ መጽሃፍ ሽም ይንዱታል እንደተለመደው ባአነሳሁ የሚለውን ቃል በመጠቀም ነጃሳን ማስወገድ ሱና እንጂ ፈርድ እንዳልሆነ በጠንካራው የማሊኪያ መዛህፍ ብይን መሰረት በነጃሳ የሰገደ ሰላቱ ትክክል ነው ሲሉ ይነግሩናል እጃጅም ጥቅሶችን በመጠቀም ተራውን አንባቢ ካደነባበሩ በኋላም ይህንን ገር ብይን በማሞገስ ይፈጽመታል ሱሃን ሃላህ ይህ ኡማውን ሰላት ለማበላሸት የተደረገ ሴራ አይደለምን ወጣ ያሉ አስተሳሰቦችን በመሰብሰብ መዝሃፍ የለሸነትን በማበረታታት እና ጥቅሶችን በማምታታት መሰል አደገኛ ብይኖችን ለሕዝቡ ማቀበል እንዴትስ ይጠቅማል በአገራችን ጡአራ በመጠበቅ እረገድ ጠንቃቃ የሆነውን እና ለዘመናት የኖርንበትን የሸ[illegible] እየናድን ሰላትን የለጠሃራ እየሰገዱ ሻፍሪዮች ነን ሲሉ አላህን አይፈሩምን እስላም ላይ [illegible] ዘመቻው በርትቷል ዘካላይ ቡድኑ ያለውን አቋም ይመልከቱ [illegible] ወ[illegible] ዘካን ከስ[illegible]ት ነጥሎት አያውቅም ሁል ጊዜም ቁርአን ውስጥ ተያይዘው ተጠቅሰዋል ሃሊፋው አቡበከርም ዘካ

http://ethcriminalawnetwork.com/

የከለከሉ ሰወችን /ግልጽ ያልሆነ/ ደርሰዋል የኢቢባሃን መበረቶች በየተራ መሸራረፍ ለደገኛ በመሆኑ ከባባድ እርምጃዎችን ወስደዋል አሁን ደግሞ ይህ እስላምን የመሸራረፍ ዘመቻ መለኩን ቀይሮ አህባሾች አይሁዳዊ ተንኮል የእልም ለምድ ለብሶ መጣ የፈተኛው ሼህ አብደላ ሃረሪ ሰይፍ ኡልበያን በተባለው መጽሃፋቸው ጥራዝ 2 ገጽ 147 የተለመዱትን የማምታቻ ዘዴዎች በመጠቀም በወረቀት ገንዘብ ዘካ ማውጣት የምርጫ ጉዳይ መሆኑን ይነግሩናል ከአራቱ መዛሃፎች ሦስቱም በወርቀት ገንዘብ ወይም ከወርቅ እና ብር ውጪ ባሉ መገበያያዎች ዘካ ማውጣት ግዴታ አይደለም ይላሉ በማለትም ዘካ ማውጣቱ ግን ለጥንቃሴ የተሻለ እንደሆኘ ይነግሩናል ሱብሃን አላህ በአሁኑ ሰዓት ወርቅና ብርን ተክቶ የሚሰራው የወረቀት ገንዘብ እንደሆነ እየታወቀ የኡለሞችን ፈትዋ በማምታታት ዘካን ማስቀረት እስልምናን መናድ አይደለምን ከባድ የሆነውን የዘካ ግዴታነት ለጥንቃቄ ይሻላል በሚል /ግልጽ ያልሆነ/ ታላቅ የአይሁድ ሴራ አይደለምን አላህ ይጠብቀን መሰረት ነው ሙስሊሞች በሙሉ ከላይ እስከ ታች ከሊቅ እስከ ደቂቅ በጉጉት የሚጠብቁት ግዴታ እንዲሁም ለአካለ መጠን የደረሰ ሙስሊም ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያ ከምግብ ከመጠጥ እና ከወሲባዊ እርካታ ተቆጥቦ አላህን በመገዛት ይጠመዳል ሱብሃን አላህ የፈተናው ሼህ አብደላ ሃረሪ ግን የሴትም የወንድም ብልት ካለው ሰው ወይም ከወንድ አገረድ ጋር ወሰብ ማድረግ ፆምን አያስፈታም ይሉናል ለማመን ከቸገሮ ወህየቱኮአሊብ ጥራዝ 1 ገጽ 395 ይመልከቱ እስክሪኑ ላይ እንደሚመለከቱት ፆታው ሴት ይሁን ወንድ ስለማይለይ ፆም አያስፈታም ይላል ወሲባዊ ሊባል የሚችል እርካታን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እያገኙ ፆመኛ ነኝ ማለትም ከቶ የሚታሰብ ነውን

- እሺ ዛሬ ሁለት ሲዲዎች አይተናል ይሄን በነገው እለት እንቀጥላለን ስለዚህ በዚህ መሰረት የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጥተናል

ትእዛዝ

- የችሎት ውሎ ከመቅረፀ ድምጽ ወደ ጽሁፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር ይያያዝ ብለናል ቀሪ የሲዲ ቪዲዮዎችን ለማየት ቀጠሮ ለሰኔ 18 ቀን 2005 ዓ.ም. ተቀጥሯል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ፡- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድም አገኝ እና ዘረሰናይ ምስግና ቀርበዋል

ተከሳሾች፡- እነአቡበከር መሃመድ 31 ሰወች ከ1ኛ እስከ 29ኛ ተከሳሾች የቀረቡ ሲሆን 30ኛ እና 31ኛ ተከሳሾች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ናቸው ጠበቆቻቸው ሃሰን ሁሴን ባህሩ መካንጋ መሃመድ አብደላ እና ምላልኝ መለሰም ቀርበዋል

- መዝገቡ አድሮ የነበረው የሲዲ ማስረጃዎችን ለመስማት ወይም ለመከታተል ተብሎ ነበር በዚሁም መሰረት በትላንትናው እለት ሁለት ሲዲ ማስረጃዎች ተሰምተዋል በዛሬው እለትም 3ኛ የሲዲ ማስረጃ መሰማቱ ይቀጥል ተብሏል እሚያስመዘግበው ሃሳብ ካለ ያስመዝግቡ
- እሺ የተከበረው ችሎት ትላንትና ክፍል 1 እና ዛሬም የሚሰማው በክስ መግቢያችን ላይ እንደገለጽነው በዚህ በአወልያ ት/ቤት መስኪዱም ጋር አንድላይ እያጣመሩ ግቢው ውስጥ ተከሳሾች ይኸዉ በክስ ዝርዝራችን ላይ እንደተገለፀው ተከሳሾች ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ አላማውን ለማራመድ እንዲሁም በመንግስት ላይ እንዲሁም በተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ድምፃችን ይሰማ በሚል ሎጐ ወይም ደግሞ መፈክር መነሻ በማድረግ በአወልያ ት/ቤት የተያዩ መገናኛ ዘዴዎች የሕዝበ ሙስሊሙ ጥሪ እየተደረገለት አርብ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ከተለያየ ቦታ እዚህ አወልያ ተገኝቶ እንዲሰግድ ጥሪ እየተደረገለት እሚሰበሰብበት ፕሮግራም የነበረ እና በዚህ ፕሮግራም ላይ ይኸው የተወሰኑ ተከሳሾች ያሉት ግሩፕ በዚህ ይሄንን መድረግ እንደ ፕላት ፎርም እየተጠቀመበት ወይም ደግሞ እንደ ፍሎሪ እየተጠቀመበት የተለያዩ ቅስቀሳዎችን ሲያደርግበት የነበረ ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በአጠቃላይ እዚህ ድምፃችን ይሰማ ላይ የነበረውን ድባብ ወይም ደግሞ ሁኔታ የሚያሳየው በምስክሮቻችን በአቃቤ ሕግ ምስክሮቻችን አስረድተናል ምን ማለት በወቅቱ ምን ምን ይባሉ እንደነበረ በወቅቱ እዛ ቦታው ላይ ይገኝ የነበረ ሕዝበ ሙስሊም ያሳይ የነበረው ስሜታዊነትን በተመለከተ በጥቅል በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ያስረዳነው እንዳለ ሆኖ ነገር ግን ይሄ አሁን እምናቀርበው የኦዲዮ ቪዲዮ ወይም ደግሞ የድምጽ ከምስል ማስረጃ ፍ/ቤቱ በትክክል በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ በተከሳሾች ተግባር ይኸው ሕዝበ ሙስሊሙ የተቀሰቀሰ በመንግስት እና አስቀድሜ በገለጽኩት በሕዝብ እና በመንግስት እና በተወኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ማለት ተጽእኖ ለመፍጠር ይደረግ የነበረውን ጥረት እሚያሳይልን ማስረጃ ነው ጥቅል ይዘቱ ይሄንን ይመስላል

- ማስረጃው ከማን እንደተገኘም አስመዝግቡ
- ማስረጃውን በተመለከተ የተከበረው ችሎት አንዳንዶቹ ላይ ተከሳሾቹ የፈረሙባቸው አሉ አንዳንዶቹ ላይ ግን ምንም አይነት ፊርማ የላቸው ስለዚህ መለየት የሚቻለው በሸርቫላቸው ነው ስለዚህ ሸርቫላቸውን በኋላ ላይ ፍ/ቤቱ ለማየት የሚፈልግ ከሆነ በዚህ ሲዲዎችን በተመለከተ በአብዛኞቹ ይሄ ድምፃችን ይሰማ የሚለው በአብዛኛው ተከሳሾች ላይ በብርበራ የተገኘ ነገር ነው ነገር ግን በርቫል አለ የተያዘ በርቫል አለ ከዛ አልፎ ግን የተከበረው ችሎትም እንደሚረዳው የቀረበውም ክስ እያንዳንዱ ማስረጃ ለሁሉም ተከሳሽ የቀረበ ነው ነገር ግን አሁን መለየት አልቻልንም የተፈረመባቸው አሉ አሁን ለምሳሌ በእነደዚህ አይነት መልኩ ከኔ የተገኘ ነው እየተባለ አንዳንዶቹ ግን ተለቅሞ ዝም ብሎ ተደርድሮ የተያዙ አሉ መጨረሻ ላይ ግን ሲያዙ እላያቸው ላይ እርእስ አለ ድምፃችን ይሰማ ተብሎ በዝርዝር ተይዟል ነገር ግን እላያቸው ላይ ከማን እንደተያዘ ግን የተፈረመ ነገር የለም ስለዚህ ፍ/ቤቱ ምናልባት መጨረሻ ላይ የሚፈልግ ከሆነ በርቫሎችን አታች እናደርጋለን ለጠበቆችም እናደርሳለን ከማን ከማን እንደተያዘ ማለት ነው
- እሺ ይቀጥል
- የተከበረው ፍ/ቤት እምንለው ስላለ ነው ሲዲ እነዚህ የኦዲዮ ቪዲዮ ማስረጃዎች ከማን ቤት እንደተገኘ በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተቀመጠ ነገር አለ ብዛቱ ሁሉ ተገልጿል አሁን በማን ላይ እንደተገኘ ባልታወቀበት ሁኔታ እንደዚህ በኮንስፓይሬሲ ወንጀል ውስጥ እያንዳንዱ በስራው ተሳትፎ ነው ሊጠየቅ የሚችለው ስለዚህ ከከሌ ቤት በብርበራ የተገኘ ነው የሚል ሁኔታ ባልተረጋገጠበት ወደፊት እናረጋግጣለን በሚል አስቀድሞ ማንን ይመለከታል የሚለው ባልታወቀበት ሁኔታ ሊታይ አይገባም መጀመሪያ ከተከሳሾቹ የተወሰኑት ላይ ነው

3057

http://ethcriminalawnetwork.com/

አሁን የማስረጃ ዝርዝር ላይ የተገለፀው ሌሎች ላይ ሲዲ ተገኝቷል የሚልም ነገር የለም ይሄ በሆነበት ሁኔታ አሁን ከማን እንደተገኘ ስለዚህ ከ28ቱ በአንዱ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ነው እኛ የምንረዳው መጀመሪያ ግልልጽ ሆኖ መቅረብ አለበት 2ኛ ትላንትና ሲዲው ፓርት 2 ይቀጥላል በሚል አልተቋጨም ትላንትና የተጀመረውም ስለዚህ ግማሽ እውነት ነው አሁን የቀረበው ኮንቴክስቹዋሉ ፍ/ቤቱም ሊረዳ የሚችለው ሙሉ ታሪኩ በአንድ ዶክመንተሪ ፊልም በማስረጃ ዝርዝሩም አቃቤ ሕግ ያቀረበው ገጽ 41 ላይ ትላንት ከሰዓት በኋላ የታየው በአንድ እርእስ ኢህአዴግ እና የአህባሽ ሴራ የሚለው ሲዲ ብዛት 3 ነው የሚለው በዛው እርእስ ላይ ነው ስለዚህ በአንድ ወቅት የተዘጋጀ በማስረጃ ዝርዝር ብዛቱ 3 መሆኑ የተገለፀው ሲዲ ግማሹ ተቆርጦ ግማሹ እውነት ይሆናል እና አሳሳችም ስለሆነ ከታየ ሙሉ ዶክመንተሪ ፊልሙ ሙሉ በሙሉ ሲታይ ነው ፍ/ቤቱም ግንዛቤ የሚወስደው እና አንድም ማቅረብ የማይፈልግ ከሆነ ሙሉ ሲዲው ነው መሰረዝ ያለበት ካልሆነ ሙሉ ታሪኩን ከዛ በኋላ ነው ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥም የሚረዳው እና ዝም ብሎ በደፈናው መታለፉ አግባብ አደለም ነው

- ሌላው የተከበረው ፍ/ቤት ከዚህ ከስነስርዓት ሕጉ ጋር በተያያዘም ደግሞ እምናነሳው ጥያቄ በስነስርዓት ሕጉ ቁጥር 33 መሰረት አንድ የብርበራ ትእዛዝ በብርበራ ትእዛዝ መሰረት ብርበራ በሚፈፀምበት ጊዜ መርማሪው ፖሊስ እቃዎቹን ሲይዝ ዝርዝሩን መፃፍ እና ከማንኛውም ተከሳሽ የተገኘ መሆኑን ለይቶ መያዝ ያለበት መሆኑን አስገዳጅ አድርጐ ነው የሚያስቀምጠው አሁን አቃቤ ሕግ ግን እንደገለፁት ይሄ ሲዲ አሁን እዚህ ሊታይ የተዘጋጀው ሲዲ ከማን ቤት የተያዘ እንደሆነ የሚያሳይ ዝርዝርም የላቸውም ይሄም ሲዲም ከማን ቤት እንደተገኘም ማረጋገጫ የላቸውም ይሄ ከሆነ በስነስርዓት ሕጉ መሰረት የተያዘ ወይም የቀረበ ሲዲ አይደለም ማለት ነው ይሄ ከሆነ ደግሞ ይሄ አስገዳጅ ስለሆነ ስነስርዓት ሕጉ ሲዲው በአጠቃላይ በማስረጃነት ለፍ/ቤቱ ሊቀርብም ሊታይም አይገባም ምክንያቱም የመሰረታዊ ከሕገመንግስቱ ተነስቶ የሚመጣ መሰረታዊ የሆነ የተከሰሱ ሰወች የመብት ጥያቄ ስለሚሆን ሲዲው በአጠቃላይ ከማስረጃነት እንዲሰረዝ ወይም እንዲወጣ እንዲደረግልን ነው የምንጠይቀው
- ማለት የማስረጃውን መቆራረጥ በተመለከተ ሙሉ ሲዲ እያሳየን ነው ከዚህ መዝገብ በተለየ ከዚህ መዝገብ አስቀድሞ በተለያዩ ችሎቶች የተከበረው ችሎትም እንደሚያየው እኛ እንደማስረጃ ይጠቀሙናል ያልነውን ብቻ በደቂቃ እየለየን ነበረ የምናሳየው ነገር ግን ይሄ ነገር በመከላከያ ማስረጃ ሙሉ ይዘቱ ይሰማ እየተባለ ሙሉ ይዘቱ መሰማቱ የማይቀር

3054

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በመሆኑና ጊዜም እየፈጀ በመሆኑ እዛ ውስጥ ላለመግባት በማለት አሁን እኛ መቆራረጥ ውስጥም አልገባንም ማስረጃ እንዲቆራረጥም አንፈልግም ሙሉ ይዘቱ ተሰምቶ ሙሉ ይዘቱ እንዲመዘን ነው የእኛም አቀራረባችን ነገር ግን ከዛ በፊት ቢሆን ኖሮ ማስረጃ መቆራረጥ ብንፈልግ ኖሮ በሲዲ ኮፒ ስናደርግ በደቂቃ እየለየን እምንፈልገውን ብቻ እናቀርብ ነበር ያንን

- ቆይ እስቲ ትላንት አልነበሩም እርስዎ
- እመጣለሁ እሱን
- ሁለት ነገሮች ተሰጥተዋል እሺ ግልጽ ከሆናችሁ ቀጥሉ
- አዎ ሁለተኛውን በተመለከተ አሁን የኢህአዴግ እና የአህባሽ ሴራን በተመለከተ ትክክል ነው ፓርት ዋን እና ቱ አለው እኛ ቱ ማስረጃችን ነው ከዋን የበለጠ ማለት ነው እንዲቀርም አንፈልግም ነገር ግን አሁን እዚህ ትላንትና በነበረው መቀባበል ይመስለኛል ቱ ተቆርጧል ኢቭን እዚህ ኮፒ ሲደረግ ማለት ነው ፎልደሩ ላይ ሲገባ ዋን ብቻ ነው ኮፒ የተደረገው ማስረጃችን ነው ነገር ግን ያንን አሁን ማምጣት የምንችል ከሆነ ከሰዓት እናቀርባለን እንጂ ያንን እኛ ቆርጠን አስቀርተነው አደለም እናቀርበዋለን አንዱ እሱ ነው ስለዚህ በዚሁ ችሎቱንም ተከሳሾቹንም የተከሳሽ ጠበቆችን ይቅርታ እንጠይቃለን በመቆረጡ ምክንያት ከሰዓት ግን እናቀርባለን ዋን በዚህ ምክንያት ነው ያልቀረበው ሌላው ግን ይሄ የወንጀል ተባትፎን በተመለከተ እዚህ ውስጥ ተከሳሽ ሲዲ ስለተገኘበት እዚህ ውስጥ እቤት ውስጥ ሲዲ ስለተገኘበት የተከሰሰ ሰው የለም አሁን ይሄ ማስረጃ በሰው ማስረጃ በአብዛኛው የተረጋገጠ ነው በሰነድ ማስረጃ በሰው ማስረጃ የተረጋገጠ ነው ነገር ግን ይሄ ድምጽ ከምስል ማስረጃው በትክክል ፍ/ቤቱ የነበረውን ሁኔታ በትክክል ካለው ከኦሪጅናል ምንጩ ለመረዳት ያመቸዋል በሚል የድምጽ ከምስሉ ቀርቧል ከየትኛው ተከሳሽ የትኛው ማስረጃ ተይዟል የሚለው በርቫል ላይ ተጽፏል ያልተፃፈ ነገር የለም አሁን ጠበቃውም እንደገለፁት በ33 ላይ የሚለው ከዛ ቤት ውስጥ ስለመገኘቱ ያ ማስረጃ ከዛ ቤት ውስጥ ስለመገኘቱ ገለልተኛ ሰወች ባሉበት ተፈርሞ ይያዛል እንጂ ይሄም ማስረጃ በዝርዝር ለፍ/ቤት ይቀርባል አደለም ኮንቴስት የሚያረገው ሰው ወይም ደግሞ ይሄም ማስረጃ ከቤቴ አልተገኘም የሚል ሰው ካለ ያንን ፊርማ እና ያንን ዝርዝር ያንን ቨርባል ነው ኮንቴስት እንዲያደርገው በዛ መልኩ ለተከሳሹ የመከላከል መብቱ እንዳይጣበብበት ስነስርዓቱ እንደመፍትሄ አርጐ ያበጀለት ከዛ ባለፈ ግን በ33 መሰረት ቨርባል ተይዞ ገለልተኛ ሰወች እንዲፈርሙበት ማረጉ ፖሊስ መመዝገቡ ተከሳሹ ጋር አሁን ከፍ/ቤት ማስረጃ አቀራረብ ጋር በፍፁም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚያገናኘው ነገር የለም ከ146 ጋርም የሚያገናኘው ነገር የለም ይሄ ማስረጃ ከኔ አልተገኘም በፍፁም ብሎ እሚክደው እና ኮንቴስት የሚያረገው ሰው ወይም ደግሞ ይሄ ማስረጃ ከቤቴ አልተገኘም የሚል ሰው ካለ ያንን ፊርማ እና ያንን ዝርዝር ያንን ቨርባል ነው ኮንቴስት እንዲያደርገው በዛ መልኩ ለተከሳሹ የመከላከል መብቱ እንዳይጣበብበት ስነስርዓቱ እንደመፍትሄ አርጎ ያበጀለት ከዛ ባለፈ ግን በ33 መሰረት ቨርባል ተይዞ ገለልተኛ ሰወች እንዲፈርሙበት ማረጉ ፖሊስ መመዝገቡ ተከሳሹጋር አሁን ከፍ/ቤት ማስረጃ አቀራረብ ጋር በፍፁም የሚያገናኘው ነገር የለም ከ146 ጋርም የሚያገናኘው ነገር የለም ይሄ ማስረጃ ከኔ አልተገኘም በፍፁም ብሎ እሚክደው እና ኮንቴስት የሚያደርግው ከሆነ ብቻ ነው የቨርባሉ ጉዳይ ፍ/ቤት መጥቶ እንደማስረጃ ሆኖ ይሄ ፊርማ የሱ ነው አደለም የሚለው ነገር እንደ ጭብጥ ሆኖ ተይዞ ነው ክርክር የሚደረግበት ከዛ ባለፈ አሁን አስቀድሜ እንደገለጽኩት አንድ ሲዲ ሁለት ሲዲ በመያዙ ተከሳሽ ቤት በመያዙ የተከሰሰ ሰው የለም ይሄ ማስረጃ በዚህ ቀርቦ ችሎቱ ሲመለከተው እንዲመዝነው ከአጠቃላይ ማስረጃው ጋር መዝኖ የክርክሩ አካል እንዲያደርገው ነው እንጂ በዚህ በብርበራ አንድ ተከሳስ ቤት ተገኘ አልተገኘ በሚል የቀረበ ክስ የለም ይሄም ተሳትፎም አያሳይም ነገር ግን ፍ/ቤቱ ቅድምም ተናግሬያለሁኝ በበርባል የተያዘ ስለሆነ ድምፃችን ይሰማ የሚባል ሌላው የኢሃዲግ እና የአህባሽ ሴራ የሚለው ማስረጃ ወይም ደግሞ ሲዲ ከማን ከማን ተገኘ የሚለውን በተመለከተ ግን በርባሉ ከተፈለገ ኮፒ ተደርጎ ማምጣት ይቻላል ነገር ግን እሱ እንዲመጣ ከተፈለገ ግን ይሄ ማስረጃ ከእኛጋር አልተገኘም ጭራሽ አናውቀውም የሚል ሰው መምጣት አለበት በአጠቃላይ ግን ይሄ ማስረጃ እንዲያስረዳ የተፈለገው ግን በሰነድ እና በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ያስረዳውን ምስል ማስረጃ ፍ/ቤቱ ከኦሪጅናል በአግባቡ ከነሙሉ ይዘቱ እንዲመዝነው ስለተፈለገ ብቻ ነው እሚለውን ፍ/ቤቱ እንዲወስድልን ነው

ብይን ሰጥተናል ብይኑ ምንድን ነው የቀረበው ሲዲ ሁለት ነገሮች ነው የሚያስረዳው አንደኛ ከማን ተያዘ ነው ሁለተኛው በማን ላይ ነው የሚያስረዳው የሚያስረዳው ምንድን ነው የሚል ነው መግለጫው በዛ መንገድ እንዲቀርብ ነው ፍ/ቤቱ ትላንትም የሰጠው ብይን ይሄንን መሰረት አድርገን አቃቤ ሕግ ሁለቱንም እንዲያቀርብ እንፈልጋለን እኛ ሁለቱንም ማቅረብ ከቻለ ጥሩ ነው ለራሱ ማስረጃ ነው የሚያጠናቅርለት ካላቀረበ ግን ቤርቫሉን አላቀረበም በሚል ምክንያት ዋናውን ማስረጃ የምንጥልበት የሕግ መሰረት የለውም ምናልባትም ይሄ መጨረ ሰላይ ከተሰማ በኋላ ሲዲውም ሁሉም ተጠቃሎ ማን ከማን እንደተያዘ ቤርቫሉም ተጠቃሎ ማን ከማን እንደተያዘ ምን እንደተያዘ ፍ/ቤቱ ሲመረምር

3956

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እያንዳንዱን ያየዋል ከተያዘበት ተያዘበት ካልተያዘበት ምን ይሆናል የሚለው ነገር የማስረጃ ክሬዲቢሊቲ ነው የሚሆነው ስለዚህ ማስረጃው ብቂ ነው በቂ አይደለም ምን ይሆናል የሚለው በኋላ የሚመዘን ስለሆነ አሁን ይሄ ዝርዝሩ ብቻ ባለመገለፁ ምክንያት ውድቅ የምናደርግበት ምክንያት ባለመኖሩ እና በኋላ ጠቅላላ የሚመዘን በመሆኑ አሁን በዚሁ ንእንቀጥላለን ብለናል እናቀርባለን ስላሉ ነው የተቆራረጠው የሚለው ነገር እናቀርባለን ስላሉ ነው አንደኛው ትላንት የተባለው የነበረው በተሰጠው መግለጫ ላይ የተቆራረጠ ሲዲ መኖር የለበትም በተሰጠው መግለጫ አንደኛ በትራክም መርጠው መግለጫዎችን ብቻ ነው የሚያስረዳልኝ የሚል በትራክ ከቀረበ ትራኩ አይቆራረጥም የሆነ መሃል ላይ ደርሶ አይቆራረጥም በተሰጠው መግለጫ ላይ አንድ ሲዲም ሊሆን ይችላል ሁለት ሲዲም ሊሆን ይችላል ስለሱ የሚያስረዳው ጉዳይ አይቆራረጥም ሊቆራረጥ የሚችለው በጣም የተለያየ የማይገናኙ ሃሳቦች ኖረው ይሄን ማስረጃ አንፈልገውም በሚል አቃቤ ሕግ መሃል ላይ የሚያገኘው ካለ የማይገናኝ ሃሳብ ከተሰጠው ሊያስረዳ ከተፈለገው ጭብጥ ጋር የማይገናኝ ከሆነ እሱን ነው ትላንት የተነጋገርነው እና ትላንት መግለጫ ተሰጥቷል ክፍል ሁለት የሚል ነገር አለው ስለዚህ እሱ ሙሉው መሰማት አለበት ከዚህአንፃር ነው

- አሁን ፍ/ቤቱ ብይን በሰጠው መሰረት ቁጥር 2 ነው እያሉ ነው ቁጥር አንድ ስላለ ይጀምር
- እንሰማዋለን ጠቅለን ግን እኛ የምናስረዳው ይሄን ነው ይሄ ማስረጃ የኛ ማስረጃ ነው ካለ ይሄንን ነው የምንሰማው እናንተ ቀርቷል የምትሉ ከሆነ ደግሞ የናንተ ድርሻ አለ ከደረሳችሁ ያኔ ልታቀርቡ ትችላላችሁ
- እኛ የሰው ኃይማኖት አልነካንም የሰው ድምበር አልነካንም አልተሻገርንም እኛ ያልነው ኃይማኖታችንን በራሳችን እናኮሂድ ከይሁዳ መጥቶ ናታኒያሁ የሚረዳው ድርጅት እስልምናን ሊያስረክበን ይፈልጋል አንቀበልም ይህ ትግል እስከ መ ጨረሻው ድረስ ነው ነውእስልምና /ግልጽ ያልሆነ/ የንግግር መብዛት አደለም የንግግር ዘዴም አደለም ከአሁን ወዲያ ኢሽ አላህ ምንም አይነት መልስ ሳይመጣ ካምፓሳችን አንመለስም አስፈላጊውን ነገር እናስቀድማለን ሃይላ ሃይለላ ላይላ ሂለላ /ግልጽ ያልሆነ/ ወለሁከቤ ሃላህባሽ አላህዋክበር
- አንድ ቀልድ እየነገረኝ ነበር ለናንት ላደርስ እና ወደ ግጥሙ እገባለሁ አንድ ጊዜ ከባድ የሂሣብ ችግር መጅሊስ ውስጥ ተከሰተ ያ ሂሣብ ተጣራ ኋላ ላይ በቃ አፉ እንባባል ተብሎ ተዘጋ እስካሁን ድረስ ከዛ በኋላ ለሚመጡት ስተቶች ከአፉታው በፊት ነው በኋላ እያሉ ነው የሚደራደሩት ታሪክ አለን ኩሩ ኩሩ ታሪክ አለን እጅግ የገነነ ሕዝብን ያስጠለለ እስላምን ያዳነ ያኔ በጨቅላ እድሜ በቡቃያው ዘመን እኛ ሃበሾቹ ድንቅ ታሪክ አለን አለን

http://ethcriminalawnetwork.com/

ድንቅ ታሪክ እስላም የማይረሳው ኢላየሁሚኒያድ እስከመጨረሻው ሁሉም የሚያወሳው አይሁንብን ኩራት አይሁንብን ጉራ ድንቅ ታሪክ አለን ሁሌ የሚዘከር ሁሌ የሚወራ ያኔ በዚያ ዘመን ቁረሾች ሲያምፁ በነብያችን ላይ ሃሰት እየነዙ ሰይፍ ሲማዘዙ ያኔ እኮ ነበርን እኛ ሃበሾቹ ጋሻ እና መከታ የስደት ቤቶቹ ባገር ሲዋረዱ በአገር ሲሰደዱ አብሽሩ መርሃባ /ግልጽ ያልሆነ/ የአበሻ ልጆች መች ሰው የስከፉና መች ሰው አሳደዱ ተንከባከቡ እንጂ ፍቅር ሰላም ሰጥተው ቆዩ አላህዋክበር ያኔ ሕፃን ሳሉ ሰሃቢቡ ሙስጠፋ ጡቶቿን ደግፋ ጡቷ ደግዳ ለእናትነት ክብር ለእናትነት ፈንታ ትልቅ ስፍራ ያላት በልባችን ቦታ ይነገር ታሪኳ በከንቱ አይረሳ የሃበሻዋ እንስት ኡሚይ ልትወሳ አላህዋክበር ተረታ ሃበሻ ትልቅ ማስታወሻ ደግሞ እንዴት እንፈርጅ የዛን ወጣት ፈንታ የዛን ኩሩ ጀግና የቢላልን ቦታ በአረቢያ አክቢር በዛ በበረሃ ጥላ በሌለበት /ግልጽ ያልሆነ/ በዛ የጭካኔ በዛ /ግልጽ ያልሆነ/ በበረሃ ድንጋይ የኒሊት ተንጋሎ ውሃ ውሃ እያለን የረሱም ወዳጅ ያ የጥቁር ጀግና አይረሳም ምን ጊዜም ይዘከራል ገና ታዲያ ይቺ ታሪካዊት ይቺ የአበሻ ምድር የእስላም ባለውለታ ያላህ ትልቅ ክብር የታለ /ግልጽ ያልሆነ/ የታለ መድረሳ ኮሌጅ መማሪያዋ ይምጡ ሃገር አቋርጠው ይጉብኙ ይማሩባት የሃበሻ ምድር እስላም ያደረባት ሰላም ይስፈንባት አላህዋክበር ዛሬ ግን ዛሬ በዚህ ምትክ ዛሬ በዚህ ፈንታ የሃሰት ምስክር የቀበሮ ባህታ እንዲህ አንደረጋልኝ በቃሉ ሊያጠምቀኝ /ግልጽ ያልሆነ/ እስላሜን ሊነጥቀኝ አላህዋክበር ዛሬ በዚህ ምትክ ዛሬ በዚህ ፈንታ የሃሰት ምስክር የቀበሮ ባህታ እጁን ዘረጋልኝ በቃሉ ሊያጠምቀኝ የአይሁድ ፍልስፍና ኢስላሜን ሊነጥቀኝ አላህዋክበር ጠላቴ ደግ ሆኖ ለኔ መልካም ሽቶ በሃሰት ሊያጠምቀኝ ማስልጠኛ ከቶ እጁን ዘረጋልኝ ሊቀብረኝ ቆፍሮ በአይሁድ ፍልስፍና በገንዘብ ታውሮ አላህዋክበር ግና አስተማረኝ እንጂ የኒላ/ግልጽ ያልሆነ/ ሁመን አላለኝም ናጁዛ ቀስ ብሎ ሲያዘኝ በዋዛ ፈዛዛ አላህዋክበር ይሄ ውለታ ነው የሸይጣን ስጦታ የጠላቴ እሩጫ ሁሉም ነቅቶበታል የለውም ማምለጫ አላህዋክበር ይገርማል ጠላቴ ደግ ነው ለኔ ይጨነቃል በመጥገቤ ያዝናል በመራቤ ይስቃል /ግልጽ ያልሆነ/ ይሄ ሁሉ ሆኖ በጣም ያዝንልኛል እየገዘገዘ /ግልጽ ያልሆነ/ ያርደኛል ዛሬ ግን በዛብኝ ውለታው ተሰማኝ እምነቴን ሕይወቴን እስላሜን ሊቀማኝ አሁን ግን በቅቶኛል በስሜ የሚነግድ የአይሁድ ተባባሪ /ግልጽ ያልሆነ/ ሙስሊም መስሎ አዳሪ የሰላም እንቅፋት የልማት ቀበኛ ወደ አምላኪ ከርታ አታላይ ሙሰኛ አላህዋክበር እንዲህ ያለ ወዳጅ ለአገሬም አይበጃት በሰላት ሃዲና አስማምቶ የሚሸጣት ባያውቀው ነው እንጂ ሃገር አይሸጥም /ግልጽ ያልሆነ/ በርካሽ ነገር እንዲህ አይለወጥም ሃገሬ እናቴ ናት እስላም ነው ሕይወቴ መቀለጫ

3ፀ8 6004

http://ethcriminalawnetwork.com/

አይደለም ክብሬ ነው ሕይወቴ አላህዋክበር ይኸው ነው አቋሜ አምጣ ለጥፍልኝ ስም አውጡልኝ ዛሬ አሸባሪ በለኝ ለጥፍ አውራ ወሬ አላህዋክበር አዎ አሸባሪ ነኝ ለጥፍ በደምብ አውራ ነገ ግን ታፍራለህ ነገሩ ሲጣራ አንገት ትደፋለህ በዱኔየምባሄራ አላህዋክበር አዎ አሸባሪ ነኝ ፀር ነኝ ለዱሰኛ ሃገር እና ዲኔን እምጠብቅ አርበኛ አላህዋክበር አዎ አሸባሪ ነኝ ለሌባ እማልመች እንቅልፍ የማልተኛ አላህዋክበር ለጥፍልኝ ሌላም ፈልግ ስም አውጣና የሌባ አይነደረቅ ሃያ መች ያውቅና አላህዋክበር አክራሪ ነው በለኝ አዎ አክራሪ ነኝ የሰው መብት የማልነካ የራሴን የማልሰጥ ውሸት የማይጥመኝ እውነትን የምመርጥ አላህዋክበር ጉባኤ ተሰብሰብ ሂድ ሌላ ስም አውጣ አንገትህን ሳትደፋ ከመጅሊስ ሳትወጣ

- በመንጫጫት የምናመጣው የለም በተስፋ ነው የአላህን ትእዛዝ በመከተል ነው ኢስላማዊ አንድነትን በማጠናከር ነው /ግልጽ ያልሆነ/ ተገቢ ነው የሆኑ ሰወችን መርዳት ነው ይሄ እንደዚህ አይደለም ታክሲ ይዘን በፀሐይ እየተንከራተትን ነው ያለነው ስለዚህ አንዳንድ /ግልጽ ያልሆነ/ ለዲን ቦታ የሌላቸው /ግልጽ ያልሆነ/ ሌላ አደጋ ውስጥ እንዳይጥሉን መጠንቀቅ አለብን ግን ማንም /ግልጽ ያልሆነ/ አልፈራም አላህዋክበር
- እሮብ ቀን ከቀኑ 8 ሰዓት አቶ ጁነዲን ሳዶ ቢሮ ተገኝተናል አጠቃላይ ኮሚቴው ተሰብስቦ በቦታው በሰዓቱ ሻርፕ 8 ሰዓት ላይ እዛ ደርሷል በዚህ መካከል እዛ ደርሰን አጠቃለይ ኮሚቴው ቢሮ ውስጥ በገባበት ሰዓት ከማንወክላቸው የተወከሉ 3 የመጅሊስ ተወካዮች እቢሮ ውስጥ ሲገቡ የሕዝብን ውክልና የያዘው ኮሚቴ የማይወክላቸው መጅሊስ ጋር እንዲደራደር መብት ያልተሰጠው ኮሚቴ ቢሮውን ለቆ መውጣት ግዴታ ስለነበረበት የመጀመሪያ ተግባራችን ቢሮውን ለቀን ወጥተናል አላህዋክበር በቦታው ላይ እንድንገኝ የጠሩን ሚ/ር አቶ ጁነዲን ሳዶ የስብሰባው ቦታ መቀየሩን ስብሰባው ወደ ፌደራል ጉዳዮች የእምነት ጉዳይ የሚመለከተው ፌደራል ጉዳዮች በመሆኑ ይሄ አካል ወደ ፌደራል ጉዳዮች እንዲሄድ እና የሚመለከታቸው አካል እየጠበቁት ስለሆነ እነሱ ጋር ተሰብስቦ ጉዳዩን እንዲፈታ የሚል አጭር እና በጣም ድንገተኛ የሆነ መልእክት አስተላለፉ ፌደራል ጉዳዮች ተሰብስበን ሄድን እዛ ስንገባ አሁንም ያልወከልናቸው የመጅሊስ ተወካዮች እኛጋር እኩል ደረሱ ወደ ስብሰባ አዳራሽ እነሱ ገቡ በዚህ ሰዓት ላይ ከስብሰባው ጋር እነሱ ያሉበት ቦታ ላይ ለመደራደርም ለመወያየትም ሕዝቡ ውክልና ስላልሰጠን እነሱ ያሉበት ስብሰባ አዳራሽ መግባቡ እንደ ወንጀል ስለቆጠርን አንገባም ብለን የኮሚቴው 3 ተወካዮች ሆነን የሚመለከተውን አካል ለማነጋገር ጥሪ ነው ያደረግነው ከ3 ተወካዮች አንዱ ነበርኩኝ አላህዋክበር ስብሰባ አዳራሽ እንድንገባ ስንጠየቅ አንገባም የሚ/ር ደኤታው የሆኑት አቶ

3059 6005

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሙሉጌታ መጥተው እንዲያናግሩን ጠየቅን በጥያቄያችን መሰረት እቢሮዋቸው ድረስ መጡልኝ እኛ እዚህ ቦታ ወክሉ የላከን መርጦ የላከን ሕዝብ ነው እና ሕዝብ ደግሞ የማይወክለው መጅሊስጋር እንድንደራደር መጅሊስ ስላልሰጠን ወይም ደግሞ መብት ስላልሰጠን እነሱጋር ተቀምጠን እንደራደርም በሁለተኛ ደረጃ እኛ ቀጠሮ የተደረገልን የሕዝቡ ጥያቄ እና የልብ ትርታ ምላሽ ለመስጠት መንግስት በቀጠረን ቀጠሮ መሰረት ስለመጣን አወያይተው ጉዳያችን መፍትሄ ባስያዝነው አጀንዳ መሰረት የሚሰጡን ከሆነ እነሱ እንዲሰጡን ጠየቅን ከዛ ውጭ መጅሊስ ባለበት ቦታ እንማንቀመጥ ገለጽን ይሄ ሂደት ባለበት ሁኔታ ላይ የመንግስቱ ተወካይ ጉዳዩከላይ እስከታች ውሳኔ እና መፍትሄ እንዲያገኝ ትእዛዝ መጥቶበታል ነገር ግን ይሄን ትእዛዝ ለመፈፀም ወይም ደግሞ ለመተግበር ጊዜ ይፈልጋል መሰረት ያለው ነገር ሰርተን የበለጠ ጉዳዩን አስፍተን መፍትሄ እስክንሰጣችሁ ድረስ አስር ቀን ወይም 12 ቀን ይፈልጋል እና ስብሰባችን ለየካቲት 5 እንድናደርግ ውሳኔ ተላልፏል አሉ እንግዲህ እኛም በተሰጠን መሰረት አንድ ማስታወቂያ ማሳሰብ ነበርብን ማሳሰቢያውን ስጥተናል ምን ነበረ ያስተላለፍነው ይሄ ሕዝብ 4ኛ ሳምንቱ እየመጣ ነው መብቱን ለማስከበር የሰላማዊ ትግል ጉዞ ጀምረዋል በዚህ መካከል ይሄንን ሰላማዊ ትግል ለማደናቀፍ በየጊዜው የሚሰሩ ስራዎች አሉ አሁንም ዛሬ አብረን ተቀምጠን ንደራደርም ያልነው የመጅሊስ አካል እኛ ጠየናንቱ ቢሮ ከመምጣታችን በፊት በየመስኪዶቹ እና በተለያዩ ተቋማቶች ላይ ልቅ የሆነ ስርዓት የጎደለው እስለማዊ ስንምግባር ያልተሟላ የሙስሊምን ሕዝብ የሚንቅ እና አሁንም ያንኑ ጥፋቱን የሚገልጽ የሕዝብን ተወካይ አሸባሪ ጽንፈኛ ስልጣን ፈላጊ እያለ በመወንጀል የሚያደርገውን ጉዞ ሁሉ የሚገልጽ አስከፊ ደብዳቤ በየመሳጅሮች ላይ እየለጠፈ ሁከት እየፈጠረ በዚሁም ሰላማዊ ትግል የሚያደርጉ ልጆችን ከየመስኪዱ እየተያዙ እየታሰሩ ስለሆነ ለሚፈጠረው ችግር ኃላፊነቱን መንግስት ይውሰድልን የሚል ጥያቄ አቅርበናል ይሄን ነገር ተረዱልን ፈጥናችሁ ምላሽ ስጡት ይሄ ሕዝብ ጥያቄው ሰላማዊ ሕገመንግስታዊ የመብት ጥያቄ እያቀረበ ያለበት ስለሆነ ለዚህ ፈጣን እና አጭር ምላሽ ሳይዘገይ ይሰጠው ያላችሁትን ቀጠሮ አሁንም ሕዝቡ በሰላማዊ ትግሉ መብቱን ለማስከበር ጊዜውን ይጠብቃል አህባሽ የተባሉ የመስሪያቤታችን ፖስተኛ ይላል ፖስተኛ ናቸው እኚህ ሰው በ1994 ከሁለት ሦስት ግለሰቦች ገንዘብ ትኬት እቆርጥላቸዋለሁ ይኸው ይኸው /ግልጽ ያልሆነ/ ብለው ተቀብለን ነበረ አይቻልም እንዲህ መቀበል በመሰረቱ ነገር ግን ተቀብለው ትኬት ቆርጨላችኋለው አንዴ ጠፍቶብኛል አንዴ እንደዚህ እያሉ ከቆዩ በኋላ እነዚህ ሰወች ሲንከራተቱ ስራሱ ለሚሰሩበት መስሪያቤት

3060

6006

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት በማመልከቻ ያሳውቃሉ በዚህም መሰረት እርቅ እንዲፈፀም-በምክር ቤቱ በተደረገ ስምምነት ወሳኝነብ ከነበረው ገንዘብ ብር አስራአራት ሺ. ስምንት መቶ ሁለት ውስጥ መጀመሪያ ሦስት ሺ. አምስት መቶ ብር ሊከፍሉ ቀሪውን ከዛ በኋላ ሊከፍሉ ከተስማሙ በኋላ ጫይ ይሄንንም ይክዳሉ በዚህም መሰረት በዚህ የማወናበድ ድርጊታቸው ይላል ቃል በቃል ደብዳቤው በዚህ በማወናበድ ድርጊታቸው ይላል ተከሳሹ በሚገኙበት ሃጂና ኡምራ ጽ/ቤት በመሄድ ማን ፖሊስ በቁጥጥር ስር አውሎ ገንዘባቸውን የተቀሙት ግለሰቦች ውሳኔ እንዲያገኙ የፖሊስ ጣቢያውን ትብብር እንጠይቃለን ይላል ይህ ደብዳቤ ቁጥር ቀን/0646/45/94 በቀን ታህሳስ 30 ቀን 1994 ከጠቅላይ ምክር ቤቱ የወጣ ደብዳቤ ነው የተፃፈበት አድርሻ ለወረዳ 18 ፖሊስ ጣቢያ አስቸኳይ አርጀንት በሚለው ማለት ነው እኚሁ አቶ ዳሽ ወይም ሚስተር ዳሽ ሌላ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል ከሰባት አመታት በኋላ እኚሁ ግለሰብ የደረሳቸው ደብዳቤ ሙሉ ቃል እንዲህ ይነበባል ለሃጂ ዳሽ ቁጥር ቀ/መ/032/32/01 29/6/01 ቀኑ መሆኑ ነው ጉዳዩ ሹመት መስጠትን ይመለከታል ተመሳሳይ ስም ናቸው እራሳቸው ናቸው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በቃለ ጉባዔ ቁጥር 307 መሰረት እርስዎ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሆነው እንዲሰሩ የተመረጡ ስለሆነ ይህንን ኃላፊነቶን አውቀው በብቃት እና በታማኝነት እንዲያገለግሉ ከየካቲት 2001 ጀምሮ ሥራዎትን እንዲጀምሩ እናሳስባለን ግልባጭ ለጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ለፌደራል ጉዳዮች ሚ/ር እና የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ለጠቅላይ ምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ም/ፕሬዝዳንት እያለ ለ17 ቢሮዎች በግልባጭ ጭንቅላታቸው እንዲናውዝ ተደርገዋል እኚህ ሰው ማን ናቸው እናንተ እያሰባችሁ ቆዩ

- ቅድም ሙኒር በግጥሙ ላይ እንዳለው ኢስላም ሃበሻ ባትኖር ምን ነበር እጣ ፈንታው የሚለው በጣም ከባድ ጥያቄ ነው ሊመለስ የማይችል ከባድ ጥያቄ ነው ትልቅ ውለታ ያላት አገር ነች ሃበሻ መናርለኢልሚ ወይሁዳ የዲን የዩኒቨርስቲ የትልልቅ እስኮላሮች ማመንጫ መሆን ያለባት አገር ነች ነብዩ ሰለላ ወአለሂ ወሰለም ያልወደደ ሰው ይከፍራል አይከፍርም ይከፍራል ነብዩ ሰለላ ወአለሂ ወሰለም መውደድ የኢማን ክፍል ነው አይደለም ነው ስለዚህ ሁላችንም ነብያችን አለይ ይሰላት ወሰላም እንወዳለን ነብያችን አለይ ይሰላት ወሰላም የበድር ዘመቻ ጊዜ ተወሃድ የሚባል ተሃባቸውን /ግልጽ ያልሆነ/ በሚያሲዙበት ጊዜ ወጋ አደረጉት ሆዱን /ግልጽ ያልሆነ/ አስተካክል ብለው አውጃአተኒ ያረሶለላህ አሳመምከኝ አንተ የአላህ መልክተኛ አላቸው አለኢ ሶላት ወሰላም ኢስተክስያሰላድ እንካ አንተም አሳምመኝ አለው አለሂሰላትወሰላም ቢአቢ.ወኡሙሚ ሁባአረሱሉላህ መልእክተኛ ናቸዋል እራህመተኢ

6007

3061

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ስአለሚ ምንም ነገር ይዘው ወደ አላህ መቅረብ አይፈልጉም እና ምን አላቸው ሰወሃድ ያረሱለላህ ሆዴ ተገልጦ እኮ ነው የመቷኸኝ ልብስህን ግለጥ እንጂ አላቸው እሺ መርሃባ ብለው እረስድ ሰለላ ወአሌ ወሰለም ልብሳቸውን ገለጡለት ይሄኔ ሰወሃድ እቅፍ አደረጋቸው እና ያለቅስ ጀመር ምነው ያሰወሃድ ይሄንን ለማድረግ ምን አነሳሳት ያረሱለላህ ለቀደሃል ለማተራ እምታየው ነገር እየተከሰተ ነው ጦርነቱ ሊጀመር ነው ወደ አኬራ ልሄድ እችላለሁ ልሞት እችላለሁ ስለዚህ አረቱአኒየመሰል ጂልዲጂልከያረሱለላህ የመጨረሻ ሕይወቴ ሊሆን ይችላል እና አካሌ አካልህን ነክቶ ወደ አኬራ መሄድ ፈለግኩ አንተ የአላህ መልእክተኛ አላቸው መውሊድ አይከፋፍለንም መውሊድን ምክንያት አድርገው የሚከፋፍሉ ሰወች አይከፋፍሉንም አንድ ነን አንድ ነን የነብዩ አለሂሰላት ወሰላም ፍቅር አንደ ያደርገናል ሁላችንም እረሱንን እንወዳለን

- የአወልያ ኮሌጅ ተማሪዎች አቋም እኛ የአወልያ ኮሌጅ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም /ግልጽ ያልሆነ/የመጅሊስ ስልጣን /ግልጽ ያልሆነ/ በተመለከተ ያለንን አቋም እንደሚከተለው እንገልፃለን አላህዋክበር አንድ የመጅሊስ ጥሪ የሕዝብ ጥያቄው ተድበስብሶ እንዲታለፍ ለማድረግ የታለመ ነው ስለዚህ የእኛም ጥያቄ መጅሊስ የሕዝብ የሆነውን /ግልጽ ያልሆነ/ ሙሉ በሙሉ ለሕዝብ ሙስሊሙ አስረክቦ ለሕዝብ ሙስሊሙ ያስረክብ በመሆኑ ጥያቄያችን ባልተመለሰበት ሁኔታ ጥሪጡን አንቀበልም አላህዋክበር ሁለት የሕዝብ ሙስሊሙ ጥያቄ ጥያቄያችን ነው የአወልያ ጉዳይ የሕዝብ ሙስሊም ጉዳይ በመሆኑ የሕዝብ ውክልና ከሌለው የመጅሊስ አመራር ጋር ምንም አይነት ድርድር አናደርግም አላህዋክበር ሦስት መጅሊስ ጥያቄያችንን ወደጐን በመተው መጅሊስ /ግልጽ ያልሆነ/ ለድርድር መጥራቱ ፈላጭ ቆራጭነቱን መቀጠሉን የሕዝብን ጥያቄ መናቁን እና በአቋራጭ እውቅና ለማግኘት /ግልጽ ያልሆነ/ የሚያሳይ ተግባር በመሆኑ እንዲያስተዉል እንጠይቃለን አላህዋክበር አራት ይህንን ትእዛዝ /ግልጽ ያልሆነ/ የሕዝብን ጥያቄ ባልተመለሰበት ወቅት ማንሳት በሰበብ አስባቡ ኮሌጁን የአህባሽ ማስልጠኛ ለማድረግ እና ተማሪውን እንዲተኛ አስመስሎ ለማሳየት የተሸረበ ድንቅ ሴራ ስለሆነ እንዲቆምልን እንጠይቃለን አላህዋክበር አምስት መንግስት ሙሉ በሙሉ ለሕዝቡ ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ተስፋ በተደረገበት ወቅት የማስተማሩ ሂደት እንዲቀጥል ነው የትምህርት ሂደቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲቀጥል መጅሊስ በአስቸኳይ ከአወልያ እጁን እንዲያነሳ እንጠይቃለን አላህዋክበር
- ይሄ ሕገወጥ ሕጋዊነቱ ያልተረጋገጠ የሕዝብ ውክልና የሌለው እስልምና ጉዳይ ተቋም ላይ ተቀምጦ እየመራ ያለው አካለ ሂደቱን ለማኮላሸት ሰላማዊ ትግሉን ለመቀልበስ አሁንም

3062 6008

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያልተሳካላቸውን ነገር እንደገና ለማምጣት እድል እንደተሰጣቸው ተሰምቷቸው የተነጋገሩት አካል ጋር ባናውቅም ይችን ወቅት ኢድራስ ለማድረግ ያለ የሌለ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ላይ የኮሚቴውን ሂደት እንቅፋት ለመፍጠር በተለያዩ ጊዜያቶች የለጠፏቸው በየመድረኩ እየሄዱ የሚለፍፏቸው አላምድሪላህ የአላህሱካኒወታአላ ፈቃድ ሆኖ የሚያደርጓት እያንዳንዷ እንቅስቃሴ የገቡባት ቢሮ ሳይቀር ኢንፎርሜሽኗ እነሱ ሳይወጡ ለእኛ ይደርሰናል አላህዋክበር ጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ደብዳቤ አስገቡ የተመረጡት 17 ሰዎች አደጋ ለማህበረሰቡ እንቅፋት የተለያየ በአክራሪነት የሚፈረጁ የግል ጥቅማቸውን እሚፈልጉ ስልጣን ናፋቂዎች ናቸው እና መንግስት እንዲጠነቀቅ ብለው ነው የተናገሩት አላህዋክበር ሱብሃን አላህ እዚህ ቦታ ላይ ይሄ ሕዝብ የመረጠው አካል ስልጣን ናፍቆ ስልጣን ፈልጉም አልመጣም ብዙ ኃላፊነት ተሸክሟል በዚህ መድረክ ላይ ዛሬ እንደ ኮሚቴ ሆኜ የምናረጋግጠው አንድ ነገር አለ ምንድን ነው የምናረጋግጠው ነገር ይሄ ኮሚቴ ለምርጫ የቀረበ ኮሚቴ አደለም ያለበትን ችግር ድምፁን እንዲያሰማለት ሕዝብ የወከለው አካል ነውና ው ክልናውን ተቀብሎ ውክልናው ቦታውን እስኪያገኝ ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ በገንዘቡም በጊዜውም በሕይወቱም መስዋእት አድርጐ ይሄን ድምጽ ለመንግስት አካል ያስማል ውጤቱንም ያሳውቃል አላህዋክበር የተነገሩት ነገሮች መጅሊስ እያደረገ ባላቸው ስብሰባዎች ላይ የመጅሊስ አመራሮች አሁንም ይሄው ጥቅም ናፋቂ ሆነው ማስባቸው ነገሮችን ለመከፋፈል እና ለመለያየት ያስባሉ መሠረታዊ ጉዳያችንን መጅሊስን ለማፍረስ አላማ ያለው ኮሚቴ እና ሕዝብ እንደሆነ ደግሞ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ትላንት የናቁትን አሁንም ሲንቁት የፈለጉትን እና እግራቸው ስር ማስገባት የፈለጉትን ሕዝብ ሃቂቅ አላህን የማይፈሩ ሰው አላህን ሲፈራ ያኒ ያውቃል እና ይጠነቀቃል እውቀት ሲኖረውም ደግሞ ነገሮችን ያገናዝባል የዲን እውቀት የሌለው የአላህ ፍራቻ ውስጡ ያላደረበት አመራር ሰው ኃላፊነት ሲሸከም አደጋው ብዙ ነው ይሄን ሕዝብ አሁንም መናቁን ቀጥሎ አወልያ መድረክ ላይ የሚሰበሰቡት ሰዎች በቫት በተለያየ ጉዳይ የተለያየ ችግር ደርሶባቸው አጋጣሚውን ተጠቅመው መንግስት ላይ ችግር ለመፍጠር የመጡ ሰዎች እንጂ ጥያቄያቸው የሙስሊሙ ጥያቄ አደለም እያሉ እየተናገሩ ነው ሱብሃን አላህ አላህዋክበር ሃቂቃ ይሄንን የሚለፍፉት የሚናገሩት ቃል ምናልባት ሰው መውደቂያው ሲደርስ የሚናገረው ብዙ ነው ሰው በተለያየ አይነት መልኩ ብዙ ነገር ያገኝበት የነበረውን አህራን እንዲያስቡ እሄ የሌላቸው ሰዎች ናቸው በአህራ ዋጋ እናገኛለን እንዳይሉ ለአህራ የሚሰራ ሰው አያሉም እና ይቺን ስልጣን ለማቆየት የሚያደርጉት ጥረት ነው አሁንም ግን መንግስት እንዲያውቅ የምንፈልገው

3063 6009

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያውቃልም ብለን የምንገነዘበው ይሄ አካል ጥያቄው የሙስሊሞች ጥያቄ ነው አጠቃላይ ከተማው ያሉት መስኪዶች አጠቃላይ አገሪቱ ላይ የሚገኙት ሙስሊሙ የለፋባቸው ደም ከፍሎ ያቆማቸው ተቋማቶች ሁሉ ተቋሞቹ ናቸው እና ድምፁን ሊያሰማባቸው ይችላል አላህዋክበር ለሰላሙ ስንል ሰላም ፈላጊ በመሆኑ ጥያቄው የመብት ጥያቄ በመሆኑ አሁንም አምስቱ ጁምአዎችን አንድ ድንጋይ ሳይወረወር አንድ ችግር ሳይፈጠር የማንንም መብት ሳይጋፋ የማንንም አይነት አካል ድምበር ሳያልፍ ጥያቄው ሰላማዊ ጥያቄ መሆኑን ለማረጋገጥ የቀጠለው ጉዞ መሆኑን የምናሳይበት ነው አላህዋክበር ከዚህ አንፃር አሁንም ይሄንን ሊረዳት ይገባል ማንም ሆነ ምንም የተነሱት ነገሮች መጅሊስ ለማፍረስ ነው ብለው ነው በፓምፕሌቱ ላይ የፃፉት ይሄ አካል መጅሊሱ ተቋማችን ነው ግን እምንፈልገው ጥያቄ አለ መጅሊሱ እንደተቋምነቱ በኤንጂኦ እንዲቀጥል ግን አንፈልግም አላህዋክበር አዎ እነሱ እኛ የመንግስት አካል እንደመንግስት አካልነቱ ኤንጂኦን ፍቃድ የሚሰጠው ፍትህ ሚ/ር ይቆጣጠረዋል ጥፋት ሲያጠፋም እርምጃ ይወስድበታል ይታገዳል ይሄ ኤንጂኦ ግን ይሄን ያክል በሕዝብ ሲጫወት አለመታገዱ እርምጃ አለመወሰዱ ነው ያሳሰበን ስለዚህ አንድ ተቋሙ እንደተቋም ኤንጂኦነቱ ቀርቶ በመንግስት የተረጋገጠለት ሕጋዊ እውቅና ያለው የሙስሊመ ማህበረሰብ ወኪል ሆኖ እንዲቀጥል ይሄ አካል ይፈልጋል ይሄ ነው ጥያቄያችን ተቋሙ ተቋማችን ነው ነገር ግን ያልመረጥናቸው ኡማውን የማይወክሉ ማህበረሰቡን መምራት የማይችሉ የዲን እውቀት የሌላቸው አደለም ዲናዊ ዱናዊ ግንዛቤ የሌላቸው አስተከክለው ቁርአን የማይቀሩ ሰወች ግን በዚሁም አይጫወቱበትም አላህዋክበር ይሄ ጥያቄ ነው ጥያቄያችን አላህዋክበር አዎ አባቶቻችን አቁመውታል መጅሊስን ደማቸውን ሰውተው ለፍተው ደክመው እንዲቆም አድርገውታል ይሄ ተቋም ኢሽ አላህ በተቻለ እንዲቀጥል ለማድረግ ይሄ ትውልድ ኃላፊነቱን ይረከባል አላህዋክበር ስለዚህ የ15 ቀን እና የ1 ወር ትግል ላይጥለው ይችል ይሆናል ነገር ግን ይወድቃል እኛ ሶብር አድርገን በትእግስት እስከታገልን ድረስ አላህዋክበር አቋማችን ይሄ ነው ኮሚቴውም ይሄንን እና ይሄንን መስመር ተከትሎ በጀመረው ሰላማዊ ጉዞ የጀመረው ሰላማዊ እንቅስቃሴ ቀጥሎ የሚደረገውንም ውይይት ውጤቱን እንመለከታለን የሕዝብ ጥያቄ መንግስት ምላሽ ይሰጣል ብለንም እናምናለን የሙስሊሙን ማንነት ከማይወክሉ መሪ ነኝ ብለው ከተቀመጡት አካላቶች እሚወጣውነገር ሁሉ ትላንት ተቋም ያላሳሰባቸው የገነቡት አንድ ተቋም የሌላቸው የተገነባን ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ ሕዝባዊ ውክልና የሌላቸው መሪዎች መቼም ቢሆን ይወርዳሉ ይወቁት አላህዋክበር ቅድም ተነግሯል አንድ ቀን ቢቀራችሁ በእኛዘመን

3064

http://ethcriminalawnetwork.com/

አትማሩም ያሉ መሪዎች ዛሬ ተማሪዎቻችን ወደ ትምህርት ቤት ተመለሱ እያሉ መጥተውላቸዋል ሃቂቃ ይሄ አቅል የሌለው ማሰብ የማይችል አካል ያለ መሰላቸው ቁርአን የቀራ ሰው ባለፈውም ተናግረናል ዛሬም እደግመዋለው ሰይድነአመር ኑኽጣብ ያሉትን ነገር ብልጦች አይደለንም ብልጣ ብልጦች ግን አያታልሉንም

- ልጆች እናቶች እህቶች ሚስቶች ይሄ ጉዳይ ከወንዶች የበለጠ ያሳስበናል የአህባሽ ጉዳይ የመጀመሪያ ተጠቂዎቹ እኛ ሴቶች ነን ምክንያቱም ማህበረሰቡን የምትመሰርተው ወይም የምታመርተው ሴት ናት አንዲት ሴት /ግልጽ ያልሆነ/ ለአራት ወንድ ትዳራላች ስለዚህ ይሄ ጉዳይ ከማንም በላይ ሴቶችን የሚያሳስብ ነው /የማይሰማ/ በተናገሩት /ግልጽ ያልሆነ/ እንግዲህ እኛም የሙስሊሙ ጉዳይ የማይገባው ሰው እጅ ነው ያለው ስለዚህ ወደሚገባቸው ሰወች እንዲመለስ እንላለን እኛም እናቶች እህቶች እና ሚስቶች እንዲሁም ልጆች መጅሊስ አይወክለንም የመጅሊስ /ግልጽ ያልሆነ/ አላህዋክበር እሺ አሁን እንደሚታወቀው መጅሊስ ወይም አህባሽ ያው መጅሊስከተባለ አህባሽ ነው አህባሽ ከተባለ መጅሊስ ነው አላህዋክበር እና /ግልጽ ያልሆነ/ የሚለው ነገር እዚጋ ይሰራል በነሱ አህባሽ መጅሊስ ላይ ማለት ነው አንድ ናቸው ምንም የሚለያቸው ነገር የለም መጅሊስ ትክክለኛ መንግስት መልስ እስኪሰጠን ድረስ መታገል አለብን ምክንያቱም እነዚህ ሰወች አሁን ምን እያደረጉ ነው ያሉት ሕዝበ ሙስሊሙን ከመንግስት ጋር እያጋጩት ነው ያሉት በቀጥታ እንደውም መንግስትም በጣም እይዞረበት /ግልጽ ያልሆነ/ ለምንድን ነው እርምጃ የማይወሰድባቸው እነዚህ የአህባሽን አስተምሮት አንቀበልም ያሉ እነዚህ ሽብርተኞች ናቸው ለምን እርምጃ አይወሰድባቸውም ለምንድን ነው እርምጃ መንግስት የማይወስደው መንግስት የሚፈልገው ምንድን ነው ሃረሪ ሱማሌ ወይም ደግሞ ሱሪያ አፍጋኒስታን እስከምትሆን ነው ወይ የምንጠይቀው እያሉ መንግስትን እየጐተጐቱ ነው ለምን ሕዝቡ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ማለት ነው ከመንግስት ብቻ አደለም የሚያጋድሉት ግልጽ ነው ሕዝበ ሙስሊም እርስ በራሱ ደም እንዲፋሰስ እንዲጋጭ ነው የሚያደርገው ምክንያቱም /ግልጽ ያልሆነ/ እንኳን አደለም እኛን ሱሃቦችን እንኳን ሱሃቦች /የማይሰማ/ ያሳደጋቸው ልጅን ሱሃቦችን ያጋደለ ነገር ነው አንድ አይሁድ/ግልጽ ያልሆነ/ ጠንስሶ ዛሬ ይህ የአይሁድ ጥንስስ አሜን ብለን ከተቀበልነው አልተባበርነው ካልተቃወምነው ፈንቅለን ካላስወጣነው በጣም የከፋ ነገር ነው የሚገጥመን ለዚህ ደግሞ ኢሽ አላህ መንግስት ምንድን ነው ይሄን ነገር አጣርቶ እንደውም እንዚህ ሰወች ሽብርተኞች ናቸው እንደውም ለአገራችን ሰላም ጥሩ አይደለም

3065

604

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ዝሎ ከእና የበለጠ መንግስት በቀድሚያ እነዚህን ተንኮል እና ሰይጣን ያለበት ያላቸውን ተቋሞች ፈንቅሎ እንደሚያወጣልን ኢሽ አላህ አላህዋክበር አላህዋክበር

- ሰውየው አህያ ሊሸጥ ይዞ ይመጣል ከተማ ላይ ማለት ነው ከገጠር እና አህያዋ ደግሞ እድሜዋ የሚታወቀው በጥርሷ ነው ሌሎችም እንስሳዎች ሁል ጊዜ እንዲህ ጥርሷን እየከፈተ ሲያሳይ ሲያሳይ ገገርዎች ሲመጡ ልምድ ሆነባት እና እኝ ብላ መጠበቅ ጀመረች እና መጅሊስም እራሳችን ያበላሸነው አይመስላችሁም በጣም ብዙ ስተቶችን ሲሰራ ዝም ዝም ብለን አሁን ግን በዲን መጣ ይሆናል እንዲህ አይነት ነገር
- አይሆንም
- በጥፊ ሲመቱ ወዲያውኑ አረ ይሄ ነገር ጉበዝ ይቅርብን እና ወደቤታችን እንግባ የሚልም ሰው ሊኖር ይችላል አላህ ወሚል እና ሲመያ አጉዱላሃ አለሃርፌን ይላል ከሰዎች መሃከል አላህእንሱብሃን ወታእላን ጫፍ ላይ ሆኖ የሚገዛ ሰው አለ ከኢላአስዋበሁ ከኢሩን ኢትማአነቢይ ጥሩ ነገር ካገኘው እሰየው አላምድሊላ ሙስሊም በሆኔ እያለ ጉዞውን ለመቀጠል ይሞክራል ወይን አሳህበቱ ፊትነቱን ትንሽ መከራ ትንሽ ጥፊ እርግጫ መቁሰል መውደቅ እስራት ሌሎችም ነገሮች ሲገጥሙት ደግሞ ኢንከለባእላ ወጂ ይላል አላህ ድሮ ወደነበረበት ቦታ ወደበፊቱ ይመለሳል አለ እንዲህ አይነቱን ሰው አላህ ምንድን ነው ያለው ሃሲር አብዱኒያ ወላአሄራ ዱኒያውንም አሂራውንም የጣ ሰው ነው ምናልባት ግር ሊያሰኘን አይገባም ሊነጋጋ ሲል ይጨልማል ይባላል ኢነማእሉልዩስሪ ዩስራ ከመከራ ጋራ ነስሩ አለ እያለ ነው አላህ ገሩ ሁሉ ነገር የሚመጣው ትላንት ግን ምን አይነት ኢትዮጵያ ውስጥ ነበርን ትላንትና እንደነ አፄ ቴዎድሮስ የነበሩ ሰወች ምን እያሉ ነበር ኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትያን ላልሆናችሁ ሰወች አዋጅ ብለው ነው ያነሱት ምንድን ነው ያነሱት ወይ ክርስትያን መሆን ነው ወይ አገሬን ለቃችሁ ትወጣላችሁ ነው ያሉት እነዛ ሙጅሊሞች ሁሉ ዛሬ ከአፈር በታች ነው ያሉት እነዮሃንስ ትላንትና ምንድን ነው ያደረጉት ትላንትና የተደረገው ኢትዮጵያ ላይ ወይ ነስሯኒያን ትቀበላለህ አልያም ደግሞ ትገደላለህ ነው ዮሃንስ ደግሞ እየከፋ ሲመጣ ማለት ነው ከዛ በኋላ የፈራ ኩፍር ተቀበለ ከፈረ ከአምስት መቶ ሺ ሰው በላይ የሚሆነው እምቢ ያለ ከገደል አፋፍ ላይ ተወረወረ ትላንትና ማለት ነው የቀረው የጀገነው ደግሞ ወደበረሃ ገባ አማራጭ ሲጠፋ ማለት ነው የምንድን ነው የመብት ጥያቄ ማለት ነው በየዘመኑ ያ ሁሉ ሚኒሊክ ሲመጣ የሰራውን ታሪክ ታውቃላችሁ ሃይለስላሴ ሲመጣ ምን እንደሰራ መጨረሻ ያ ሁሉ ግፉ ጠልፎ ጥሎት መጨረሻ አላህ በገዛ ወታደሮቹ እንዲዋረድ ነው ያደረገው ከዛ አላህዋክበር አላህዋክበር ማለት ይቻላል ከዚህ ከዮሃንስ ጀምሮ

3066

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሙስሊሙ ከሚኒሊክ ጀምሮ እየተዳከመ መጨረሻ ማደንዘዣ መርፌ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ፡ ውስጥነው ያስገባው ዛሬ ደግሞ የሁለት መቶ አመት መርፌ ለመውጋት እሩጫ እየተካሄደ ነው በየአቅጣጫው ሁለት መቶ አመት የሚያስተኛን ማለት ነው አንድ ትንሽ እርምጃ ሲራመድ አይ ሙስሊሞች መንቃታቸው ሙሊሞች ኃይማኖታቸውን ማወቃቸው ለእኛ አይበጀንም የሚሉ መሰሪዎች ይሁዳ በየቦታው ሸሃፊን እርጅን ወኢንስ ሞልተዋል እንደዚህ አይነቶቹ ሁል ጊዜም ለፈተና ነው ምክንያቱም አላህ እነዚህ መኖራቸው ሙስሊሞች ተፈትነው ማለፊያቸው ነው ወርቅና ሌላውን ነገር በልያ እሳት ነው እሳት ክፉ ነገር ቢመስልም ነገር ግን ወርቅና ወርቅ ያልሆነውን ምን ያደርጋል ይለያል ፈተናም ደግሞ እነዚህ አካሎች መኖራቸው አንተ እኔ እሷ አንቺ ሁላችንም ማለት ነው ማንነታችንን እንድናው ቅአላህ ሱታንወታእላ ለፈተና ያዘጋጀው ነው ምርቱን ቆሻሻውን ሊያበጥርበት ነው አላህ ሱታነህ ወታእላ በስድስት ሳምንት ትግል ወይም ደግሞ በስድስት ጁምአዎች በሰባት ጁምአዎች ብቻ ይገኛል ብለን አናስብም ምናልባት ዛሬ የምናደርገው ሙከራ ሊሰምርም ላይሰምርም ይችላል ከመብት አኳያ ማለት ነው ሁስነት ዝናችን ይሰምራል የሚል ኢሽ አላህ ተፋውላችን እንደዚህ ነው የሰሙናል ያዳምጡናል ለሕዝብ ኢትዮጵያ ትላንትና ፍትህን ለአለም ያስተማረች አገር ናት የሌላ አገር ዜጐች ስለ ኃይማኖት ብለው ኢትዮጵያ ላይ መጥተው ፍትህ አግኝተው በፍትህ ጥላ ስር ኖረው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ሱሃቦች እቢያላሃን በዛች ምድር ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደው ያደጉ የኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ አፈር የሚፈጠረውን ነገር በልተው ከዛ የተፀነሱ ሰወች በኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ ዛሬ መብት የማያገኙባት አገር ኢትዮጵያ በጭራሽ አትሆንም ኢሽ አላህ ፈተና ይመጣል ሙስሊምን ከእምነቱ የሚያፈናቅለው ወደ ኩፍር ወደተለያየ ነገር የሚወስደው እንደ ማእበል ማለት ነው ማእበል ላይ እንዳለች መርከብ ወዲህ ወዲያ የሚያላጋው ፈተና ከየአቅጣጫው ይመጣል አሉ ነብዩ ሰለላ ሃጂ ሰለም ዩስቢሁረጁሉ ሙእሚ ነን ወዩሲካፊረን አሉ ዛሬ ጠዋት አማኝ የነበረው ማታ ይከፍራል አሉ የዛን ሰዓት ማታ አማኝ የነበረው ወዩምሲሙሚኡነን ወዩስቢኡካፊረን ማታ ላይ አማኝ የነበረው ጠዋት ይከፍራል የዲኡህአዱሁም ዲለሁቢአወሂዲሚኒዱያ ይላሉ በዱኒያ ጥቅማ ጥቅም በሽቀጥ ዲኑን የሚሸጥ ሰው ይመጣል ያን ዘመን ይላሉ ሱብሃን አላህ ይሄ የምናየው /ግልጽ ያልሆነ/ ዛሬም ቢሆን ሰወች ገንዘብ ከተሰጣቸው ትላንት ሲጮሁለት የነበረ ማለት ነው እንዲህ እየተደረግክ ነው የይሁዳ የአህባሽ መጣ ብለው ሲጮሁ የነበሩ ሰወች ዛሬ ደግሞ ተገልብጠው ምን እየሰሩ እንደሆነ ከናንተ የተሰወረ አይደለም በአሁኑ ሰዓት ማለት ነው

3067 6013

http://ethcriminalawnetwork.com/

በአሁኑ ሰዓት ሙስሊሞችን በጭጭሮ ብዙ ብዙ ፕሮፖጋንዳዎች በየአቅጣጫው እየተሰሩ ነው ያሉት ሙስሊሞች ወደ አወልያ እንዳይሄዱ የማይደረግ ነገር የለም መብታቸውን እንዳይጠይቁ ማለት ነው መውደቂያ ሰዓታቸው ሲደርስ ሁሉም እላይ ታች ውር ውር ይላሉ ግን ይሳካል አይሳካም ኢሽ አላህ አንድ ጊዜ ይባላል እንደ አረቦች ምሳሌ ግድግዳው ሚስማሩን ሲሸነቁረው ለምን ትሸነቁረኛለህ አለው ዲንአላህተሸቁኒ ሲል ካአለሰልመይድሪቡኒ አለው ይባላል ለምንድን ነው አንተ እንደዚህ የምትወጋኝ ብሎ ሲጠይቀው ሚስማሩን ግድግዳው ከጀርባዬ በመዶሻ የሚመታኝን ጠይቀው ብሎታል ይባላል ትግሉ እረጅም ነው ጉዞው እንዲህ መንጠባጠብ የለም ተሳቁት ካለ አሰብንበት ቦታ አንደርስም ነስር የሚባለው ነገር የሚመጣው ጽናት ሲኖረን ነው አላህካለሞታእላ ጽናት ይስጠን እስከዛሬ ድረስ እዚህ ቦታም እየመጣን ሳንመጣም ባለንበት ቦታ ሆነን በዚህ ከተማ ብቻ ሳይሆን በአገሪቷ በአጠቃላይ እያነሳን ያለነው ጥያቄ ሕጋዊ ጥያቄ ነው ይህንን ሕጋዊነቱን ማወቃችን ለምንድን ነው የሚጠቅመን ሕጋዊ መንገድን ተከትሎ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ሁሌም አሸናፊ ነው የሚሆነው አላህዋክበር ስሜቱን የሚከተል ሰው ወይንም የሌላን ስሜትን የሚከተልሰው በሆነ ቦታ ላይ ይቆማል ይሰላቻል ይደክማል ይመታል ሌላም ሌላም ነገር ሊደርስበት ይችላል እዚህ ቦታ ስንመጣ እኛ ሕጋዊ ነን ሕገመንግስታዊ ጥያቄ ነው ያለን በሕገመንግስቱ ላይ የተረጋገጠልን የኃይማኖት ነፃነት የመደራጀት ነፃነት እራስን በራስ የመምራት ነፃነታችን ይከበርልን ብለን ነው እንቅስቃሴ ሕዝቡ የጀመረው ማንም መርቶት ማንም ተንቀሳቀስ ብሎት አደለም ከመንግስት አካላትም ይህ እጅግ በጣም ከ20 ጊዜ በላይ የተሰመረበት ጥያቄው ሕጋዊ ጥያቄ አግባብ ያለው ጥያቄ ሰላማዊ ጥያቄ ስለሆነ መንግስት ከዚህ ጥያቄ ጐን ይቆማል ብሎ አረጋግጦልናል አላህዋክበር ተቃውሞን ማቅረብ መቃወም ይቻላል ተብለናል ይህንን ስንባል ሂደታችንን ሕጋዊ መሆን መቻል አለበት በየመስኪዱ በየአዳራሹ በየመድረኩ እኛን ወደ አላስፈላጊ የሆነ ፍልሚያ ወይንም ጥፋት ወይንም ባይብረንስ ወደሚሆን ነገር ሊወስዱ ጥረቶች ይደረጋሉ ለዚህ ደግሞ እጅ መስጠት የለብንም ሁሌም እኛ በምን አይነት መልኩ ነው መብታችንን የምንጠይቀው ሰላማዊ በሆነ መልኩ መሆን አለበት ማለት ነው በአፀፋው እናንተ ኢፍትሃዊ ሆናችሁ ድምበር እንድታልፉ አያድርጋችሁ ይላል አላህ ሱታን ወሳእላ እስላም ሚዛናዊነትን ነው የሚያስተምረን ፍትሃዊነትን ነው የሚያስተምረን ሃታ ለጠላቶቻችን ሃታ በደል ለፈፀሙብን ሰወች እንኳን ድምበር ማለፍ እንደሌለብን ያስተምረናል እነዚህ ሰወች እዚጋ እንዲህ አደረጉን እንዲህ በደሉን ብለን ያልሆነ ስርዓት በሌለው ነገር ውስጥ መግባት የለብንም ለማለት ነው እኛ

3068

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሄንን ለማድረግ የመንግስት በሮችን አንኳኩተን ባለፈው ቃል በገባን መሰረት ጥያቄውን ለተወካዮች ምክር ቤት አስገብተናል ለፌደራል ጉዳዮች አስገብተናል ለጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ አስገብተናል ለጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ አስገብተናል እንደዚሁም ለኢህአዴግ ጽ/ቤትም ጥያቄውን አስገብተናል አላህዋክበር አንዳንድ እየተነገሩ ያሉ ነገሮች ስላሉ ማወቅም ስላለባችሁ እዚህ በመሃከል እኔ ጉን የቆሙት ኮሚቴው ውስጥ ያሉ አካላቶች ናቸው እዚህ ኡስታል ያሲን ኑሩ ኡስጣን ጀማል አሉ በጀርባዬ አንድ እየተነገረ ያለ ነገር አለ ኢሽ አላህ እምታዩዋቸው እንግዲህ ሼህ ሱልጣን ሃጂ አማን ሼህ መከተ ሙሄ ሼህ ጣሂር እና ኡስጣል ሼህ መሃመድ ከድር ካሚል ሽምሱ አህመድ ሙስጠፋ ኡስጣል ያሲን ኑሩ ኡስጣል ጀማል ያሲን እዚሁ ፊት ለፊት ይገኛሉ እንግዲህ እነዚህ የኮሚቴዎች አህመድ ጀበልም አለ ሌሎችም ኮሚቴዎች እዚህም ቆመው የማታይዋቸው ኮሚቴዎች በአሁኑ ሰዓት ላይ አንዳንድ ወሬዎች ስለተናፈሱ እንድታውቁት ብለን ነው ከኮሚቴዎቹ አራት ሰዎች ለቀዋል የተወሰኑ ሰወች ወጥተዋል እየተባለ ይወራል እና ኮሚቴው ያሲን ከመጅሊስ የወጡትን እንዳይሆን ይላል በመሃከላችሁ የምንገኘው እኛ ኮሚቴዎቹ እንግዲህ መንግስት ጋር በነበረን ቀጠሮ ቀርበን ጥያቄያችንን አቅርበን በቀጠሯችን ተገኝተን የተሰጠንን ምላሽ ዛሬ እናቀርባለን ብዙ ሰወች ይሄ ጁምአ ሊያልፍ ነው እያሉ እየጠየቁ ነው ጁምአ ይነገራል ተብሎ ምንድን ነው እኛ እስካሁን ድረስ የነበረውን ኸበር ጁምአ ማድረስን የተገደድነው አንድ ኢንፎርሜሽን አለ አግባብ በመውጣት እንደዚሁ በተለያየ ስራ በተለያየ ሂደት ላይ ችግር ለመፍጠር ሂደቱን ለማደናቀፍ የሚፈልጉ ሰወች እንዳይጠቀሙበት 2ኛ እዚህ መድረክ ላይ ቆመን ያገኘነውን ምላሽ በዚሁ መድረክ ላይ ላለ ማህበረሰብ ሁሉም በአንድላይ አንድ አይነት አካል ነው እና ሜሴጅ የማያገኘው ፌስ ቡክ የማይገባው ሰው የተዛባ ኢንፎርሜሽን መስማት ስለሌለበት አንድ ቦታ ላይ በአንድ እለት እዚችው ቦታ ድምጽ እናሰማለን ብለን ስላሰብን ነው ኢንፎርሜሽኑን በአጠቃላይ ኮሚቴው ብቻ ሚስጥር አድርጐ ይዞ መድረክ የሚመሩ ሰወች እንኳን ሳያውቁት ቆይተዋል አላህዋክበር እንግዲህ አንድ ነገር ልናምን ይገባል የምንሰጣችሁ የደረስንበት ወይም ባደረግነው ውይይት የተገኘው ውጤት እና የሚነገረው ነገር ሁለት ጉን ሊኖረው ይችላል እኛ በምንፈልገው ፍላጐት ሄዷል አልሄደም የሚለው ነገር እንዳለ ሆኖ የሚመጣው ምላሽ ሁሉ ወይም ደግሞ የምናገኘውን ነገር ሁሉ አሁንም እስከመጨረሻው ሰዓት ድረስ ሰላማዊ ትግላችንን ውጤት እስክናገኝ እንደምንቀጥል በማመን ያለውን ነገር በፀጋ ለመቀበል ቃል እንገባለን ኢሽ አላህ አላህዋክበር አላህዋክበር ኢሽ አላህ ያው የመጀመሪያ ስራችን ቀድም ወንድም ካሚል

3089 6015

http://ethcriminalawnetwork.com/

እንደገለፀው ጉዳችንን ጥያቄያችንን አንድ ቦታ ላይ ብቻ አይደለም ወይም አንድ አካል ጋ ብቻ አይደለም ብዙ ጊዜ ጥያቄዎች አላግባብ እየሄዱ ኢንፎርሜሽኖች እየተዛቡ ያለው እውነታ እየተዛፈ ሃሰት መረጃ እየቀረበ አርባ ሺ የመጣውን ሰው አራት ሺ እያሉ የሚያቀርቡ የተወሰኑ የግል ጥቅም ያላቸው የመንግስትም አካላት ስላሉ ጉዳዩ ከዳር እስከ ዳር እንዲደርስ የሚመለከተው አካል ሁሉ እንዲያውቅ በየቢሮ እንዲገባ አድርገናል አላህዋክበር ከዚህ በመቀጠል እንግዲህ ያደረግነው ስብሰባችን ላይ በተቀጠርነው የካቲት 5 ስምንት ሰዓት ተኩል አጠቃላይ በድንገተኛ ችግር ምክንያት ከቀሩ ሁለት ኮሚቴዎች በስተቀር አስራአምስታችንም ተገኝተናል አላህዋክበር በዚህ መሰረት ውይይቱ ተጀመረ እንግዲህ ውይይታችን ያቀረብነው ደብዳቤ አለ ወይም ደግሞ ያቀረብነው ጥያቄ የእኛን ጥያቄ ያቀረብናቸው ጥያቄ ትንታኔ የሚገልጽ ሰባት ገጽ ደብዳቤ ከመግባቱ ጋር ሂደቱን ገለጽን አሁን የምናደርገው ነገር ምንድን ነው አሉን እነሱ ይሄ እዚህ ሙሉ ያለውን ነገር አቅርበን ምላሽ መስጠት እምንችልበት ቃል የገባነው ነገር እንዳለ እናውቃለን ከዚህ አንፃር አንድ ነገር እንነግራችኋለን አሉ ያም ምንድን ነው ጉዳያችሁ መፍትሄ ያገኛል ብለዋል አላህዋክበር አላህዋክበር አላህዋክበር ምላሽ እንሰጣለን ምላሽ የማንሰጠው ነገር ካለም በግልጽ እናሳውቃለን ይሄ /ግልጽ ያልሆነ/ ስለዚህ ጥያቄያችሁን አሁንም ባለው አግባብ መቀጠል ትችላላችሁ የነሱ ምላሽ ነው አላህዋክበር በመቀጠል ጥያቄዎቻችሁ ሁሉ ግልጽ ነው የጠየቃችሁት ጥያቄ ሁሉ ተረድተናል ገብቶናል እሚል ቃል ተነግሮናል አላህዋክበር እኛም የምንፈልገው ጥያቄያችን ሳይዛባ ፍላጎታችን በተለያየ አቅጣጫ ሳይለወጥ ጥያቄው ሰላማዊ የቀረበው የመብት ጥያቄ መሆኑ እንዲታወቅ ነበረ እና ያን በትክክል ተረድተናል ብለዋል አላህዋክበር አሁን እንግዲህ የምንነግራችሁ አንድ ነገር ምንደን ነው ይሄ ቀጠሮ እዚያ በደረስንበት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ለየካቲት 26 ተቀጥሯል አላህዋክበር አንድ ነገር እወቁ ለየካቲት 26 የመጨረሻ ምላሽ እንሰጣለን ያን ጊዜ ምላሽ ካልሰጠን አልሰጠንም ብለዋል እና እምትፈልጉትን ማድረግ እንደምትችሉ ቃል ገብተዋል አላህዎክበር አላህዋክበር አላህዋክበር አላህዋክበር አላህዋክበር አላህዋክበር አላህወክበር አላህዋክበር አላህዋክበር አላህዋክበር ተክቢራው እዚህ ቤት ላይ ነው የሚያልቀው ጥያቄያችን ሰላማዊ ጥያቄ ነው አሁንም እግቢው ዉስጥ ቆይተን በጋራ ጉዳያችንን ጨርሰን በጋራ እንወጣለን ይሄ ድምፃችን ለሃዳችን ቃል ኪዳናችን ነው አላህዋክበር በዚህ እስከ የካቲት 26 ድረስ እንደጀመርነው ሁሉ በሰላም በትግስት እየተገናኘን ጉዳያችንን አንድ ቃል የገባልን የፌደራል ጉዳይ መስሪያቤት ሁለተኛ ያስገባንባቸው ወሬ የሚባሉ ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር መለስ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ዜናዊ ጀምሮ ያሉት አካሎት ደብዳቤያችን በግልጽ ጥያቄያችን ስለቀረበ አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሰጡን ተስፋ እናደርጋለን በትእግስት እንጠብቃለን ኢሽ አላህ ይዘን ከዚጋር በተያያዘ የተነሱ ነገሮች ይሄ አካል ሕዝባዊ ውክልና ያለው የአዲስ አበባ ነው የሚል አስተሳሰብ የተፈጠረበት ሁኔታ ነበር ይሄ ግን እንዳልሆነ እንዳይሳሳቱ እነሱ ተሳስታችሁ የኢትዮጵያ ውስሊሞች ነን ብላችሁ እንዳታስቡ እኛ ውክልና የሰጠን አካል በአዲስ አበባ ብቻ ከመቶ ሃያ ሺ ሰው በላይ ፊርማውን አስቀምጧል አላህዋክበር በእጃችን ላይ ይሄ ውክልና ፊርማ አለን ከዛም ውጭ በተለያየ ክልሎች ያሉ አካላቶች በፊርማ ውክልና ሰጥተው በዛሬው እለትም ከተለያዩ ወረዳዎች እና ክልሎች ይሄን ጉዳይ ለመመልከት አ ጠገባችን የሚገኙ ብዙ ወንድሞች አሉን አላህዋክበር ስለዚህ ጥያቄያችን የሕዝብ ጥያቄ ጥያቄው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ ቅድም እንደተገለፀው አገርም ውስጥ ከአገርም ውጭ ያሉ አካላቶች ይሄን ጉዳይ ለማስያዝ በቅርቡም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገቡ የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ የሚወክሉ ተወካዮች ይመጣሉ ኢሽ አላህ አላህዋክበር ስለዚህ ጥያቄው የጋራ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሙስሊም ጥያቄ ነው እና ምላሽ እንደምናገኝ ተስፋ እያደርግን በሰላም በትእግስት አሁንም እንጠብቃለን እኛ ትግላችን የሰላም ትግል ጥያቄያችን የመብት ጥያቄ ያለአንድ እረብሻ ያለ አንድ ችግር ያለ አንድ ብጥብጥ እንደማይሄድ አሁንም እናሳየለን በየትም ቦታ ላይ ለሚነሱት ነገሮች ሁሉ ሰላማዊ ምላሽ እንሰጣለን ኢሽ አላህ አላህዋክበር በዚህ ቃል እንገባለን የትኛውም ቦታ ላይ ቢሆን ጥያቄያችን በሰላም ምላሽ እንዲያገኝ ማንም እንዳያደናቅፈው የጋራ ጥረታችንም ቢሆን እስከመጨረሻው ድረስ ሁሉን ነገር ከፍሎ ይሄ ኮሚቴ እንደሚቆም ቃል እንገባላችኋለን ኢሽ አላህ እንግዲህ አጠቃላይ ያሉ ነገሮች ካሉ ኮሚቴው ጋር እየተመካከራችሁ ጥያቄያችን የጋራ ድምጽ ጥያቄ አድርገን እስከ መጨረሻው ድረስ ደርሰን አላህን የሚፈሩ ኡማውን በአግባብ ሊመሩ የሚችሉ የተቋም መሪዎቻችን እንደሚተኩልን ተስፋ እናደርጋለን

- ለ7ኛ ጊዜ ላለፉት 14 ክፍለ ዘመናት ወቅታዊ ሳምንታዊ ጉዳያችንን በእምነት ተቋሞቻችን ተገኝተን በምንመካከርበት የጁምአ መድረካችን ላይ እንኳን ደህና መጣችሁ እንላለን
- ግራ ቀኝ ግራ ቀኝ እንተቃቀፋለን እንሳሳማለን ቢስሚላ ደሞ አላህዋከበር አላህዋከበር ማንም ቃላት በመፈብረክ ሊነጣጥለን አይችልም አላህዋክበር ውጪ አካባቢ ያልተሰማችሁ ሰወች ካላችሁ ሁላችንም ተቃቅፈናል አንድነታችንን ገልፀናል ያልሰማ ካለ አሁን ይስማ ይተቃቀፍ ይሳሳም እጅ ለእጅ ይያያዝ እንድገመው አንድ ጊዜ ሁላችንም መጅሊስ አይወክለኝም /ግልጽ ያልሆነ/ በዚህ ግቢ ዙሪያ ያላችሁ የፀጥታ አስከባሪዎች ፖሊሶች እና የደህነንት አባሎች

3ዐ1 6017

http://ethcriminalawnetwork.com/

በሙሉ እንድታውቁ የምንፈልገው ለዚህ ግዜ ውስጥ እየተበተነ ያለ አንድ ሌላ ባጅ አለ ያ ባጅ ከመጅሊስ ወይም ከሌላ ለመበጥበት ያሰቡ አካላት የመጣ እንጂ ከዚህ ያልወጣ መሆኑን እንድታውቁ እና አላማችንም ጥያቄያችንም ሕጋዊ ሆኖ

- አሁን የሚለውን ተከሳሽ 7ኛ ተከሳሽ ይመስለኛል ካልተሳሳትኩኝ አቶ ሳቢር ይርጉ ላይ አሁን የሚለውን በተመለከተ ከአቶ ጃመል ያሲን ተከሳሽ ላይ የተገኘ ሰነድ አለ ይሄ አሁን መጅሊስ አይወክለንም የሚለው ባጅ ላይ ኢህአዴግ አይወክለንም የሚል ወረቀት በዚህ በነበረው እንትን ላይ ተበትኗል ስለዚህ ይሄንን ስናብራራ ወይም ስንገልጽ ከመድረክ እንዲህ ተብሎ መገለጽ አለበት ኢህአዴግ አይወክለንም የሚለው ነገር እንዲህ ተደርጐ መብራራት አለበት ተብሎ በዚህ ከጀማል ያሲን ስንተኛ ተከሳሽ /ግልጽ ያልሆነ/ የብርበራ ሰነድ ላይ በእጅ ጽሁፍ የተፃፈ ስብሰባ ኮሚቴው ስብሰባ አደረገበት የሚል ሰነድ አለ እሱ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ነው እንደ አንድ እስትራቴጂ ተደርጐ የተወሰደ ነው ከዚጋ እንዲናበብልን ያቀረብነው ማስረጃ ነው ይሄኛው ማስረጃ ይሄ በመጅሊስ አይወክለንም የሚለው በተመሳሳይ ወረቀት ተበትኗል ኢህአዴግ አይወክለንም የሚል ነገር ግን ይሄንን አስትራቴጂ እንደ እ ስትራቴጂ አርገን መውሰድ አለብን ተብለው ከ1-7 ይመስለኛል ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱ መድረክ ላይ እንዲህ ብሎ መናገር ተብሎ የተወሰደ 7ኛ ተከሳሰ ነው አሁንም እየገለፁት ያሉት በ27ኛ ተከሳሽ ላይ ከ19ኛ ተከሳሽ ላይ በብርበራ ከተያዘው ሰነድ ላይ ጋር አንድላይ እንዲገናዘብልን ነው የምንጠይቀው የተከበረው ችሎት
- ምናልባት እንትኑን ለመጠበቅ ብለን ነው እስኪጨርሱ የጠበቅነው 1ኛ አስፈቅደው አደለም እየተናገሩ ያሉት 2ኛ ነገር ግን ማስረጃ አቀራረብ ስርዓቱ ደግሞ በደምብ መከበር አለበት አሁን ቪዲዮ ቀርቦ ቪዲዮ እየታየ ነው ያለው አቃቤ ሕግ ያሁኑ ክርክራቸውን ክርክር ማጠቃለያ ላይ ሲቀርብ እዛጋ ሊያቀርቡ ይችላሉ ከዛ ውጪ ግን ያላቀረቡትን ሰነድ እና እኛም አሁን እዚጋር የማናውቀውን ሰነድ እንደገና እዚህ የቪዲዮን ሰነድ እሳቸው ማብራሪያ እየሰጡበት ሊሰማ የሚችልበት ምንም የሕግ ስርዓት የለም አሁን ያቀረቡት ማብራሪያ አሁን ያቀረቡት ሃሳብም እ ነዲቀርብ ወይም ይሄን ማብራሪያ አቃቤ ሕግ እንዲሰጥ የሚያደርግ ምንም የማስረጃ አቀራርብ ስርዓት በሌለበት ሁኔታ የሳቸውን ሃሳብ ጨምረው እንደገና ማስረጃዎቻቸውን ተንትነው የሚያቀርቡ ከሆነ የማስረጃ አሰማም ስርዓት ያዛባዋል እኛም የመከላከል መብታችንን ያጠባል ስለዚህ ተገቢ የክርክር ስርዓት አይደለም አሁን ያቀረቡት ሃሳብ ሙሉ በሙሉ መሰረዝ አለበት ከዚህ በኋላም እንዲህ አይነት ነገር መኖር የለበትም እንዲህ አይነት ክርክሮችን ሁላችንም የምናቀርበው የክርክር ማጠቃለያ

2072 6018

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ላይ ነው የክርክር ማጠቃለያ ማስረጃዎቻችን እንተነትናለን እናስረዳለን ያን ጊዜ ጠብቀው ያስረዱ ከዛ ውጪ ግን እንዲህ አይነት ስርዓት ሊፈቀድ አይገባም ሊቆም ይገባል የተከበረው ፍ/ቤት

- ትንሽ የምንጨምረው ነገር ምንድን ነው የተከበረው ፍ/ቤት አሁን የጠቀሷቸው ከአቶ ጀማል ያሲን የእጅ ጽሁፍ የሚሉትም ሆነ አሁን እያቀረቡ ያሉት ሁለቱም ማስረጃዬ ናቸው ብለው አቃቤ ሕግ ያቀረበው ስለዚህ ይሄን ይታመንልኝ ያኛው አይታመንልኝ ተቃራኒ ማስረጃ በመጀመሪያ ደረጃ አለማቅረብ ነው ይጠቅመኛል ብለው ካቀረቡ በኋላ ይሄኛው ከዛጋር ይገናዘብልኝ ማለት አንዱን ማስረጃቸው በሌላው ማስረጃ ይስተባበልልኝ ማለት መሆኑንም እንዲገነዘብልን
- እሺ ምንድን ነው ይሄ ነገር ያው ብይን ነው በመጀመሪያ ደረጃ እንደተባለው አቃቤ ሕግ ሰያስፈቅዱ ነው የገቡት ማስፈቀድ ነበረባቸው ያ ምን አንዳንዴ የተፈጠረ ነገር ካለ ዝም እንላለን ምክንያቱም ሊስተካከል የሚችል ጊዜ የማይሰጥ ፍ/ቤቱ ፍቃድ እስከሚሰጥ ድረስ ጊዜ የማይሰጥ ነገር ካለ ለዛ ነው ዝም እምንለው እንጂ ጊዜ የሚሰጥ ነገር ካለ ወደኋላም ሄደን የምናየው ነገር ስለሆነ ማስፈቀዱ በመጀመሪያ ደረጃ ተገቢ ነው እንግዲህ የቪዲዮ ማስረጃን በተመለከተ እንዲህ ነው መሰማት የሚል ክሊር የሆነ ፕሮሲጀር የለም ይሄን ሁላችንም እናውቀዋለን ስለዚህ ምንድን ነው የሚሆነው ይሄን ክፍተት ፍ /ቤቱ ነው የሚሞላው ፍ/ቤቱ ነው የሚያስተካክለው ስለዚህ ፍ/ቤቱ የሚመራው መጀመሪያ ላይ መግለጫችሁን በትክክል ያ ማስረጃ ሊያስረዳላችሁ የሚችለውን ነገር በትክክል አስቀምጡ ከዛ በኋላ ማስረጃውን እንሰማለን ምናልባትም ፍ/ቤቱ መሃል ላይ ማብራሪያ የሚጠይቅ ከሆነ ስለጉዳዩ ፍ/ቤቱ ሲፈቅድ አ ቃቤ ሕጐቹ ሊያብራሩ ይችላሉ ወይም ማን ነው ቪዲዮውን የሚያሳይ ሰው መሃል ላይ ገብቶ ማብራሪያ እንዲሰጥ ይደረጋል ምክንያቱም ለግልጽነት ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች ተብሎ የሚወሰድ ነው የሚሆነው ስለዚህ አሁን የሚሆነው ምንድን ነው አሁን ፍ/ቤቱ የተነጋገረበት ዋናው ጉዳይ 1ኛ አቃቤ ሕግ መጀመሪያ ላይ አሟጣችሁ ይሄን ሁሉ አንዱን ካሴት አ ንዷን መግለጫ እንደ ጭብጥ ነው የሚወሰደው አብዛኛውን ጊዜ አንዷን መግለጫ በመጀመሪያው አሁን የተናገራችሁትን, መጀመሪያ ላይ አጠቃላችሁ ማስቀመጥ ነው ሁለት ነገሮች ናቸው እንትን የሚሉት 1ኛ መጀመሪያ ላይ ማቋረጥ አንድ ይሆናል ሁለተኛው ደግሞ መሃል ላይ የሚሆን ከሆነ /ግልጽ ያልሆነ/ የተለያየ የተለያየ ጭብጥ ነው የሚያደርገው ስለዚህ በኋላም ለፍትህ አሰጣጥ አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል አቃቤ ሕግ ከዚህ በኋላ ያሉትን ካሴቶች መጀመሪያ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለጠቃላችሁ አቅርቡ በዚህ ለጋጣሚ ፍ/ቤቱ ማብራሪያ የሚፈልግ ከሆነ ይጠይቃል ሌሎቹ ማስረጃዎች እዚህጋ የሚገናኙ ነገር ከሆነም መጀመሪያ እንዲገናኙ አድርጋችሁ ማቅረብ ነው ካለዚያም ደግሞ የተያያዙ ስለሆኑ ፍ/ቤቱ ይሄንንም ያንንም ሁሉንም አይቶ የሚወስን ስለሆነ ሠን ያህል የሚያስቸግር አደለም አሁን በዚህ ነው የምንቀጥለው

/ግልጽ ያልሆነ/ የነበረን አቋም እና የፕሮግራሙን ይዘት አጭር ነገር ለማለት እፈልጋለሁ አየቃላይ የፕሮግራሙ ቀረፃ ውስጥ ከመግባታችን በፊት ወይም የፕሮግራሙ ቀረፃ ከመደረጉ በፊት የፕሮግራሙ መሪጋ ወይም ደግሞ የፕሮግራም አዘጋጅ ጋር ከሁለት ቀን ያላነሰ በጉዳዩ ውይይት አድርገናል በምንወያይበት አርስትም ላይ ተነጋግረናል የተወያየንበት እና የተነጋገርንበት አርስት በወቅታዊ ጉዳይ እና የመብት ጉዳይ ላይ ነው እኛ /ግልጽ ያልሆነ/ የምናወወራበት ተጨባጭ እንደሌለ ተነጋግረናል ያ የኡለሞች ስራ ነው መድረግ ተፈጥሮላቸው ሲያወሩ እንደሚችሉም ገልፀናል በዚህ ተስማምተን የመድረኩ ይዘት ተቀይሮ በቀረፃው እለት ግን የሰማችሁት አይነት ተጨባጭ ወይም ደግሞ አህዋል ተፈጥሯል ይሄ ነገር ሲፈጠር አንድ ነገር መታመን አለበት ለተነሱት ጥያቄዎች በተለያየ አስተሳሰብ ላይ ያለ አካሄድን ተመልክቶ ለተነሱት ነገሮች በቂ ምላሽ ከመድረኩ ተሰጥቷል የአህባሽን አስተምሮት በተመለከተ የተናገሯቸው እና ለሃገር እንደማይጠቅም አስቸጋሪ መሆኑንም ኪታቦቻቸውን በማጣቀስ 3 ኪታቦች በተለይ እነሱ ባለፈው የቀረቡት መሻይት አካላቶች የገለጿቸው ቡጌ ሰጣልቢን ሰሪሁን በያን እና እንዲሁ ተአውል አለምነህ አሲ ሙንከር የሚለውን ሦስቱን ኪታቦች በግልጽ መድረክ ላይ ይዘን ቀርበን /ግልጽ ያልሆነ/ የሚለው ይሄ ነው እነሱ ግን ቀጥፈዋል የሚለውን ቃል አሳይተናል ያም አልቀረበም በ3ኛ ደረጃ መጅሊስ እና የማህበረሱ ጥያቄ ከመንግስት ጋር ያለንን ያቀረብናቸውን ይዘት በተመለከተም በስፋት ገልፀናል አጠቃላይ የገለጽነው ነገር እንዳለ ሆኖ የቀረበው የተቀረጽነው አንድ ሰዓት ከሃያ ነው የቀረበው የ40 ደቂቃ ፕሮግራም ነው 40 ደቂቃው ተቆርጧል እንግዲህ ለዝግጅታቸው ይመቸናል ያስፈልገናል ባሉት መልኩ እራሳቸው ቆርጠውት አቅርበውታል መሰረታዊ የተባሉ በአህባሽ ላይ መጅሊስን ተያይዞ የተናገርናቸው ነገሮች በመቆረጣቸው በጣም አዝነናል ቅር ብሎናል ከዛም አልፎ ከነበርነው ታዳሚዎች አራት የውይይት ተካፋይ ነበርን የነበርነው የወንድማችን ካሚል ሸምሱ ሀለት ጊዜ ያቀረባቸው ሙሉ ፕሮግራም ከፕሮግራም ውጪ ሆኗል ፕሮግራም ውስጥ እንዳልነበረ ማለት ነው እና በተነሱት ጥያቄዎች ሁሉ ኮሚቴው በቂ ምላሽ ለተነሱት አጀንዳችን

http://ethcriminalawnetwork.com/

ባይሆንም የመወያያ እርእሳችን ሆኖ ባይቀርብም ለተነሱት ነገሮች ግን አስፈላጊ እና በቂ ምላሽ በወቅቱ ሰጥተናል

- ከማን አንሼ ሲሉ ሰምቶ ማውራት ጥቃቅን አነስተኛ ስሞች መርጦ ማውጣት የመጅሊስ ልማድ ነው /ግልጽ ያልሆነ/ መግጥት እንዲህ አይነቱ ነው እንዲህ አይነቱ አሸባሪ ማለት
- አላሁ ዋክበር
- /ግልጽ ያልሆነ/ አላህምድሊላህ /ግልጽ ያልሆነ/
- አላህዋክበር /ግልጽ ያልሆነ/ ሸለቆ የሞላው የቀን ቅዠታቸው ለኢስላም ሕልውና የፀዳው ማንነት /ግልጽ ያልሆነ/ በስቃይ የወጣው የሙት መንፈሳቸው በእንግልት ያለፈው ስጋና አጥንታቸው በግፍ የፈሰሰው የብዙሃን ደማቸው እስላም ለእኛ እንዲደርስ የከፈሉት ዋጋ /ግልጽ ያልሆነ/ እኛ እናልቅስ እንጂ ታሪክ የሳቀብን ወንጀላችን ገዝፎ ቀን የጨለመብን ሃይድራችን መንምኖ በኖ የጠፋብን ለድሉማ እሱ አለ ሱልሃን /ግልጽ ያልሆነ/ ያሻውን የሚችል በጥበቡ እረቂቅ /ግልጽ ያልሆነ/ ጉድና ጅራት /ግልጽ ያልሆነ/ እንዲሉ ጆሮ አይሰማው የለም ስሙና /ግልጽ ያልሆነ/ ጅብ ካልታወቀበት ቁርበት አስነጠፈ ልክ እንደ አሁኑ አህባሽ ሱፒ ነኝ እያለ ብዙ ለፈለፈ እኔ አውቀዋለሁ አድጌበታለሁ በአህባሽ ቅጥፈት ሴራ መች እሸወዳለሁ አቅሜ ደህና ሆኖ እያለሁ ጤነኛ አሁን ሊያጋድለኝ አይሁድ /ግልጽ ያልሆነ/ እስቲ በአንድ ድምጽ አይሆንም በሉኛ አይሆንም አይሆንም አይሆንም ነፍሴ /ግልጽ ያልሆነ/ ሰበረች ልጓሟን በሰው /ግልጽ ያልሆነ/ ተሸክማ ኑሮዋ ከሚዳከም /ግልጽ ያልሆነ/ ሲሉ እየሰማሁ ነው ያደግኩት ሼሆቼ ሌሎችን ሲገድሉ ጭራሽ የት ሰምቼ ኡለማ ሲያከብሩ ጭራሽ የት አይቼ እኔስ አውቀዋለሁ/ግልጽ ያልሆነ/ በአህባሽ ፊት /ግልጽ ያልሆነ/ መች እሸወዳለሁ /ግለጽ ያልሆነ/ አይሁድ ቅጥረኛ ሁሉን አቀፈረ ለማንም አልተኛ በእንቁ ስራቸው አለም ያወቃቸው ታላላቅ /ግልጽ ያልሆነ/ በአህባሽ ድንቅ ሴራ ኩፍር /ግልጽ ያልሆነ/ ይኸው ስንቱን አየን ግምብ ይዞ መች ቀረ አህባሽ በምግባሩ ሁሉን አከፈረ /ግልጽ ይልሆነ/ ይሄን ሁሉ ተንኮል የሰሩትን ሰርተው ሱቢዎች ነን አሉ አፋቸውን ሞልተው እንደነዚህ ላሉት /ግልጽ ያልሆነ/ ፈራርሰው በከንቱ ፋኖሱ ቢሰበር ቀንዲሉ ቢደፋ /ግልጽ ያልሆነ/ አህባሽ ቢንሰራፋ /ግልጽ ያልሆነ/ ቁርአን ተቀይሮ በቃል ሊቀራበት በመጨረሻ መንገድ ሃላል ሊበሉበት አይሆንም አይሆንም በብዙ ሊጫወት የአይሁድ ቅጥረኛ እጄን /ግልጽ ያልሆነ/ አይሆንም በሉኛ አይሆንም አይሆንም /ግልጽ ያልሆነ/ አይሆንም አይሆንም እኛ እንደው ገብቶናል የአባይ /ግለጽ ያልሆነ/ ይመለስ ሊባኖስ በመጣበት ጎዳና /ግልጽ ያልሆነ/ አንፈልግም ይሂድ ተመልሶ ይውጣ ከውስጥ የውርደት ማቅ ለብሶ ያለሃ /ግልጽ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ያልሆነ/ ከአናታችን ይውረድ አንቁ /ግልጽ ያልሆነ/ አንድ ነው ጉልበቱ አይከፋፈልም ለልማት ለሰላም ወደኋላ የለም ሦስት አራት ቦታ በግፍ የፈሰሰው የመስዋእት ደማቸው ይስሪ በካሜራ /ግልጽ ያልሆነ/ ፋኖሱ ይሰበር ቀንዲሉ ይደፋ /ግልጽ ያልሆነ/ የአህባሽ ቢንሰራፋ /ግልጽ ያልሆነ/ በአህባሽ የግፍ ሴራ /ግልጽ ያልሆነ/ ቁርአን ተቀይሮ በቃል ሊቀራበት /ግልጽ ያልሆነ/ አይሆንም አይሆንም /ግልጽ ያልሆነ/ አይሆንም በሉኛ አይሆንም አይሆንም /ግልጽ ያልሆነ/ አይሆንም አይሆንም /ግልጽያልሆነ/ እስቲ በአንድ ድምጽ አይሆንም በሉኛ አይሆንም እኛ እንደው ገብቶናል የአባይ /ግልጽ ያልሆነ/ ይመለስ ሲባኖስ በመጣበት እግሩ አንፈልግም ይሂድ ተመልሶ ይውጣ ከውብጣችን የውርደት ማቅ ለብሶ /ግልጽ ያልሆነ/ ከራሳችን ይውረድ /ግልጽ ያልሆነ/ አንድ ነው ሕይወቱ አይከፋፈልም ለልማት ለሰላም ወደኋላ አንልም ሦስት አራት ቦታ /ግልጽ ያልሆነ/ የጭቆና ድንጋይ አልተጫነንም ታዲያ አሃዱን አሃድ በሉዋ

- አሃዱን አሃድ
- ያለችው 20 ደቂቃ ነች መስማት የሚቻል አይመስልመ ከሰዓት በኋላ ግን /ግልጽ ያልሆነ/ ነበር ምላሽ አልመጣም አሁን እኛ ወጥተን ደውለን ቼክ እናደርግና የማይገኝ ከሆነ ተመልሰን እዚህ መገኘታችን ጥቅም ስለሌለው ነው ስለዚህ ትንሽ ጠብቁን እነግራችኋለን አሁን ጠዋት ከማይመጡት /ግልጽ ያልሆነ/ በጊዜ ለመምጣት እንሞክር እረኛም ጊዜ የሚወስድ ይመስለኛል በዚህ አይነት በቀን አንድ ሲዲ እና ሁለት ሲዲ እየተሰማ ያስቸግራል ስለዚህ እንደምንም አጣበን በሰዓት ተጠቅመን አንድ ሲዲ አሁን ከነበረው መጨመር ይኖርብናል ብዬ አስባለሁ ስለዚህ ይሄን ማሳሰቢያ መስዳችሁ ጠዋት ነገ ሦስት ተኩልም ከተገናኘንም ጥሩ ነው ቢያንስ ሦስት ሰዓት እንገናኝና ሦስት ተኩል ከጀመርንም ጥሩ ነው አንድ ሰላሳ ደቂቃ እናተርፋለን ሦስት ሰዓት ተገኙ ሦስት ሰዓት ተኩል እዚህ እንጀምራለን ማለት ነው

ትእዛዝ

- የዛሬው ችሎት በዚህ ተጠናቋል አንድ ዳኛ ባለመኖራቸው ከሰዓት በኋላ መቀጠል አልቻንም ዳኛ ተፈልጉም ማግኘት አልተቻለም ስለዚህ በቀጠሮ ይህንን ቀሪውን የአቃቤ ሕግ ሲዲ ለመስማት 19/10/2005 ዓ.ም. ተቀጠረ ጨርሰናል።

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የ.መ.ቁ 124754

ቀን 19/10/2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብስራት ተዕልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝ ቴዎድሮስ ጌታቸው እና ዘረሰናይ ምስግና ቀርበዋል

ተከሣሾች፡- እነ አቡበከር አህመድ የቀረ ሰው አለ ሁሉም ቀርበዋል

የተከሣሾች ጠበቆች ባህሩ መካንን፣ አዲስ መሐመድ እና መሐመድ አብደላ ቀርበዋል

- የተከበረው ፍ/ቤት የዐቃቤ ሕግ የድምፅ እና የምስል ማስረጃ ከመጨመሩ በፊት ደንበኞቻችንን የማረሚያ ቤት አስተዳደር /ግልፅ ያልሆነ/ በጣም የተቸገሩበት እና ያልተፈታላቸው ችግሮች አሉባቸው ያንን አስረዱልን የተከበረው ፍ/ቤት
- ቀጥሉ ዐቃቤ ሕግ
- የተከበረው ችሎት ትላትና እንዳመለከትነው የህባሽ እና የኢህዴግ ሴራ የሚለው ቁጥር 1 ታይቷል አሁን የምናሳየው ቁጥር 2 ነው ቁጥር 1 ሲታይ የእኔ ባልደረሳ አስቀድሞ ከትላትና በፊት በነበረው ቀጠሮ ስለሚያስረዳልን ስለ ቁጥር 1 ገለፃ ሰጥቷል አሁን የማቀርበው የቁጥር 2ን በተመለከተ በትክክል የሚያስረዳልንን ነው የማስቀምጠው ይሄንን በተመለከተ ይሄ ሲዲ በአጠቃላይ ይሄ የኢህዴግ እና የህባሽ ሴራ የሚለው በአጠቃላይ እንዲያስረዳልን የተፈለገው በክሱ ላይ የተገለፀውን ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ አላማቸውን ለማራመድ በተለይም ደግሞ በመንግስት እና በተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ተፅኖ ለማሳደር

6023

3077

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የተዘጋጀ ዶክመንተሪ ፊልም ነው ይሄ ዶክመንተሪ ፊልም በዋነኛነት የሚያጠነጥነው ከእኛ እምነት ውጪ ከሚሉት ውጪ ያለውን ኃይማኖት እና በመንግስት ላይ ሲሆን ከመንግስት ጋር በተያያዘ መንግስት ለምን ያሰቃየናል ለምን መጅሊሱን በካድሬ ይሞላብናል ለምን የአክሱም ሙስሊሞች መስኪድ ይከለከላሉ የሀበሹ በሽሁ ሀሪሪ የኢትዮጵያ ሀረር የኢትዮጵያ አካል እንዳልሆነች እየገለፀ እኚህ ሼህ ለምንድን ነው እዚህ ሀገር መንግስት የሚቀበላቸው ሀይማኖታቸውንስ እንዲያስፋፉ የሚተባበራቸው ኢህዴግ ሙስሊሙን የሕብረተሰቡ ክፉኛ ንቆታል ሕዝቡን በክንዱ ለመስበር ሊቆርጠው ተነስቷል 87 እንዳደረገው ለቃቅም ማረሚያ ቤት ለመክተት ተቋም ለመዘጋት በዝግጅት ላይ ይገኛል ደንታ ቢስ ሙስሊም ለመፍጠር እንዲሁ ሌትተቀን እየተጋ ነው ልክ እንደበፊተኞቹ አሁንም በመንግስት ወጪ እና ኃይል ሀበሽ ኃይማኖቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እና እንዲስፋፋ እየተደረገብን ነው የሚል ከፍተኛ ቅስቀሳ የሚደረግበት የዶክመንተሪ ፊልም ነው በመጨረሻ በተመሳሳይ ይሄም ዶክመንተሪ ፊልም የሚያጠናቅቀው ይሄ ተግባራችን ሰላማዊ መሆን አለበት ይል እና የመፍትሔ ኃሳቦች በማለት መጨረሻ ላይ ሲያጠቃልል ወይም ሲዘጋ በተመሳሳይ ትግሉ ሰላማዊ መሆን እንዳለበት ብሎ ይዘጋል ነገር ግን ይሄ አሁን ማጠቃለያው ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 ከሚደረገው ቅስቀሳ ጋር በፍፁም በማይገናኝ መልኩ ይሄ ትግል ሰላማዊ መሆን እንዳለበት በካሬ የተነጠቅነውን ተቋማችን ሊመልስልን እንደሚገባ መክረናቸው መመለስ ያቃታቸውን ሰዎች ማግለል እንዳለብን ከእዚህ ውጪ መሰረታዊ መብቶቻችንን ከፊት በማድረግ ማድረግ እንዳለብን የሚል እነዚህን ቅስቀሳዎች የሚያሳይ ዶክመንተሪ ፊልም ነው ስለዚህ በዋነኛነት በክሳችን ላይ የተገለፀውን ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ አላማቸውን ለማራመድ በመንግስት እና በተወሰኑ የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ተፅኖ ለማሳደር የተደረገ ወይም ደግሞ የተዘጋጀ ዶክመንተሪ ፊልም ነው ይሄንን ነው የሚያስረዳልን በአጭሩ

- /ግልፅ ያልሆነ/
- ትላትናም ለማስረዳት እንደቻልነው በተለያዩ ተከሣሾች ላይ ተገኝቷል ያንን ከቨርቫል ላይ መልቀም ነው የምንችለው ሲያዝም በርካታ ካበርካታ ተከሣሾች ላይ ተይዟል ነገር ግን ለምሳሌ አሁን የምናሳየው በፊርማ ላይ የተፈረመበት ኦርጂናሉ ላይ ከዶክተር ከማል ሀጂ ገለቱ ላይ ነው የተገኘው አሁን በኦርጂናል ላይ ለፍ/ቤቱ ያቀረብነው የመሳከርንበት

6024

3278

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከዶክተር ሀጂ ገለቱ ላይ ነው የተገኘው ትላትና እንዳልነው ግን በዝርዝር የሚስፈልግ ከሆነ ከቨርቫል ላይ መልቀም ስለሚጠበቅብን እና እየታየ በእዚህ መልኩ ማቅረብ ስላለብን ፍ/ቤቱ ያንን የሚፈልግ ከሆነ ከቨርቫል ላይ ለቅሞ በማጠቃለያው ላይ የምናቀርብ ነው የሚሆነው ሲዲዎቹን በተመለከተ

- በቀረቡት የተረዳሁት ወደ ፊት የምናየው ሲዲ /ግልፅ ያልሆነ/ እንዳለ ዝርዝር ጭብጡ አልገባንም የተከበረው ፍ/ቤት ጭብጡን በግልፅ እንዲነግረን ከእዚህ ሲዲ ዐቃቤ ሕግ ያቀረቡት ዝርዝር ነው እንደሰማነው እንዲህ ለማድረግ እንዲህ ለማድረግ በሚል ዝርዝር ተቀምጧል እና እነዚህ ጭብጥ ነው ብለን ልንይዘው አንችልም እና ከከሳቸው ጋር ምን እንደሚያገናኘው ጭብጡ ይሄ ነው ይሄንን ነው የሚያስረዳልን በሚል እንዲያስቀምጡ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ እንኳን የምጠይቀው ከማን ጋር ተገኘ የሚለው አሁን ገልፀውታል ግን በኋላ የሚለው ነገር ሲዲው ከእኔ ቤት ነው አይደለም የሚለው ተከሣሹ መቃወም የሚችለው በማስረጃ ዝርዝራቸውም ላይ ከተወሰኑ ተከሣሾች ላይ ነው ሲዲ ተገኘ እየተባለ በዝርዝር ዐቃቤ ሕግ የማስረጃ ዝርዝራቸውን ካልረሱት በስተቀር ከግማሽ በላይ አይሆንም አሁን ተገኘበቸው የተባሉት ስለዚህ መጀመሪያውኑ ቨርቫል የሚሉትን ነገር አይተው ከእከሌ ነው ካላሉ በስተቀር የሚቀርበው ሲዲ ከእነዚህ ውስጥ በማን እንደተገኘ እንኳን ባላወቁበት መጨረሻ ላይ እኮ ማስረጃው ተሰምቶ ካለቀ በኋላ የእኔ አይደለም ነው ለማለትም ይቸገራሉ እኮ ስለዚህ አሁን በፖሊስ እጅ ካለ ዐቃቤ ሕግ ጋር አቅርበው ማየት የሚችሉት ቀላል ነገር ስለሆነ ያንን እያዩ ፈርም መሆን አለባቸው እኮ ይሄ ሲዲ ከየት ተገኘ እዚህ ጋር የማስረጃ ዝርዝር ቀረበው ውጪ ከእከሌ ተገኘ ብለው ሊያቀርቡም ስለማይችሉ ይኸው አሁንም እንደገና ጥብቅ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው ዐቃቤ ሕግ ሲዲውን ሲያቀርብ ከእከሌ ቤት የተገኘ ነው እያሉ እያቀረቡ ማስረዳት ምንም የሚስቸግርም ነገርም እኮ የለም ይሄንኑ አሁን እያስቸገረን እኛ ለመከራከርም ለምን ቨርቫሉ ሲቀርብ ሲዲው እራሱ ተመልሷል ብለው እኮ ፈርመው ተከሣሾች የፈረሙበት አለ ፖሊስ እጅ ተመልሷል የተባለው ሲዲ ይቅረብ ወይም ያልተመለሰው ይቅረብ የምናውቀው ነገር የለም ምንም አስቸጋሪ ነገር ስላልሆነ ይሄ እንደገና ይታዘዝልን ነው

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ለእዚህ የምንሰጠው መልስ ምንድን ነው ከትላንትና ጀምሮ ይሄንን ነገር እየደጋገሙት ነው እዚህ በማስረጃ መግለጫችን እንደገለፅነው ከአንድ ተከሣሽ ለምሳሌ ከ 29ኛ ተከሣሽ ብለን ለክስ ዝርዝር መግለጫ ላይ 3 ሲዲ ይላል እንደዚህ ዓይነት 3 ሲዲ በርካታ ሲዲዎች እዚህ ባለፈው የተከበረው ችሎት እዚህ ቀርበው የእኛ ታዛቢ ሆነው ቀርበው የመሰከሩት ምስክሮች እንደገለፁት ከአንዱ ቤት እኮ 50/60/70 ከእዚያም በላይ እኮ የተገኘበት ሁኔታ ነበረ አስረድተዋል ነገር ግን እኛ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ማስረጃ ይሆነኛል ብሎ የሚለውን አቅርቧል ያንን ከእነኚየ ውስጥ ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ እዚህ ዛሬ በተከታታይ ይቀርባሉ ያልናቸውን ለተከበረው ፍ/ቤት ያቀረብናቸውን ሲዲዎችን በሚመለከት ትላትናም ለመግለፅ ሞክረናል እኛ እያልን ያለነው ዛሬ ይሄ የሚቀርበው የኢሀዲግ እና የሀበሽ ሴራ የሚለው ይሄ የተገኘው ከዶክተር የ 29ኛ ተከሣሽ ከማል /ግልፅ ያልሆነ/ ሁኔታ እንደዚህ ዓይነት ሲዲዎች በርካታ ከሁሉም ተከሣሾች ተገኝተዋል ይሄንን ለማመልከት ካስፈለገ ግን በተናጥል ይሄ የተገኘው ዛሬ የሚቀርበው ልክ በተመሳሳይ ሁኔታ ሲፈተሽ በየቤታቸው ሁሉ አለ የሀበሽ ሴራ ሀበሽ እና እንደዚህ የተለያዩ የገለፅናቸው ነገር ግን ከእዚያ ውስጥ ይሄ ምንም እኛ የተቸገርንበት የለም የሚያስቸግርም አይደለም ቬርቫል ኣለ ካቬርቫሉ በተጨማሪ ደግሞ ታዛቢ ምስክሮቻችንን ገልፀዋል ከእዚህም በተጨማሪ ዛሬ እንደገለፅነው ከ 29ኛ ተከሣሽ ቤት የተገኘ ነው ብለናል በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች ጋርም አለ ነገር ግን የምንፈልገውን የምንመርጠውን ይጠቅመናል ያልነውን ማስረጃችን ይሆናል ያልነውን አቅርበናል ከእዚያ ውጪ ቅድም እንደተባለው 2ኛው ቅድም በተነሳው የመጀመሪያው ደግሞ ጭብጥን በሚመለከት እዚህ ያስረዳልናል ያልነው ከትላንትና ወዲያ በቀረበው ዝርዝር መግለጫ ክፍል 1 እና ክፍል 2 ላይ መሠረት አድርገን ምን ሲያደርጉ እንደነበር ክሳችን መሠረት በማድረግ በሌላው ላይ ምን ዓይነት ተፅኖ ሊፈጥር እንደነበር እና /ግልፅ ያልሆነ/ በመግለጫ ማለት ነው ስለዚህ ይሄንን ሲዲ በሚመለከት ወይም የሚታየው ይሄንን ምስክርነት ድምፅ የሚቀርበውን እሱን አስመልክቶ በተለየ ሁኔታ ጭብጡ እንደዚህ ነበር ጭብጣችን ክሳችን ግን ክሳችን መሠረት ያደረገ ነው ከእዚያ ውጪ በተጨማሪ የሀበሽ እና የኢሀዲግ ሴራ ምንድን ነው መልዕክቱ መልዕክቱ የሚታይ ነው የተከበረው ፍ/ቤት የሚያየው ነው እነሱም የሚያዩት ነው ያውቁታል እኛ ደግሞ ለክሳችን

3080 6026

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ማስረጃችን መሠረት ያደረገልንን አቅርበናል ከእዚያ ውጪ አጭር ዝርዝር መግለጫ ከማቅረቤ የዘለለ የሚቀርብ አልመሰለኝም እና በተጨማሪ

- ከእዚያ ውጪ የተከበረው ችሎት አሁን ይሄ አሁን ማስረጃ የማሰማት ጊዜው የእኛ ሂደት ነው ስለዚህ አሁን ማስረጃችንን ምን እንደሚያስረዳልን በተለይም ደግሞ አሁን የድምፅ ከምስል ማስረጃ ስናሰማ በተከበሩ ጠበቆች በተደጋጋሚ ጊዜ ኢንተርአፕት እየተደረገ ይሄ ምን ያስረዳል ይሄ ምን አያስረዳም እየተባለ እንዲሁም ደግሞ መጀመሪያውኑ መግለጫ ይቅረብበት እየተባለ /ግልፅ ያልሆነ/ በመሀል እየገባን ይሄ ነገር ይሄንን ያስረዳልናል ይሄ ነገር ይሄንን ጭብጥ ከእዚህ ጭብጥ ጋር ተያይዞ ይታይልን እያለን ማስረዳት እና ያ ጊዜ ዕድል ሊሰጠን የሚገባው ነው እኛም በተመሳሳይ የመደመጥ ሙብት አለን ተከራካሪ ወገኖች ነን ተከሣሾቹ ያንን ማለት በተለይ ደግሞ በጠበቆች አማካይነት ከትላንትናም ጀምሮ ነው የተረዳሁት አቢዩዝ ባያደረጉን ጥሩ ነው በመሀል በመሀል እየተገባ ምንድን ነው ጭብጡ ምንድን ነው ሊያስረዳ የተፈለገው የሚለውን ነገር እኛ ከሌሎች መዝገቦች በተለየ ሁኔታ ምንም አቡዩዝ ለማድረግ ያደረግነው ጥረት የለም ሙሉ ሲዲው ከእነ ሙሉ ይዘቱ መጥቶ እዚህ ይደመጥ ሙሉ ይዘቱ ይመዘንልን ሙሉን እያሰማን ነው ነገር ግን ይሄ ሲዲ ይሄ ማስረጃ ምንድን ነው የሚያስረዳልን የሚለውን በተመለከተ ፍ/ቤቱ መጀመሪያውኑ አስቀድማችሁ መግለጫውን ስጡ ስላለን በእዚያ መሠረት ለማስረዳት ጥረት እያደረግን ነው አቀራረቡ ሊሆን የሚገባው የነበረው እኛም መጀመሪያ አቅደን የነበርነው በመሀል በመሀል ይሄ ነገር ከእዚህ ጋር ይያያዝልን ይሄ ነገር ከእዚህ ጭብጥ ጋር ይታይልን እየተባለ ነበር ነገር ግን አሁን ለአካሄድ እያልን ይሄ ማስረጃ ይሄንን ያስረዳልናል እያልን በተለመደው አነጋገር ጭብጥ ይባላል እንጂ ጭብጥ የሚባል ነገር ክስ ነው አሁን ያለው ፍሬ ነገር የማስረጃ ፍሬ ነገር ነው የማስረጃ ፍሬ ነገር በአጭሩ ምን እንደሚያስረዳልን አረዲ ተናግረናል ስለዚህ በመሀል በመሀል የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን የማስረጃ አሰማም ሂደታችን ማለት የሚያውክ ስለሆነ እነሱም ተረድተው የመሰማት ሂደቱ በእዚህ መልኩ እንዲቀጥል እንዲያደርግልን ነው የምንጠይቀው
- ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኝ የተነሱትን በመመልከት ብይን ስጥቷል 1ኛው ሲዲዎቹ ከማን እንደተያዙ እንዴት እንደተገኙ የሚገልፅ ነገር የለም የተባለው መቃወሚያ 3 ጊዜ ቀርቧል ከእዚህ በፊት ዛሬ 3ኛ ጊዜ ተነስቷል ብይንም ተሰጥቷል እሱ በተደጋጋሚ የሚነሳ ነው በተደጋጋሚ

http://ethcriminalawnetwork.com/

መነሳት ይችላል አይችልም ነው አንዱ ፍ/ቤቱ የያዘው የተያዙት ነገሮች ምን ይገልፃሉ አንድ ማስረጃ ተብሎ የቀረበው ነገር ካልተገለፀ አንድ በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተገለፀው ነገር ከእገሌ ቤት ተያዘ አልተያዘ የሚለው ነገር ካልተገለፀ ከማስረጃነት ይወገዳል ወይስ አይወገድም ከእዚህ በፊት በተመሳሳይ ብይን ተሰጥቷል ለማንኛውም 1ኛው አንዴ በብይን የታለፈውን በተመሳሳይ ፍ/ቤት 2ቴ ማንሳቱ ተገቢ አይደለም አንድ ሰው ማስረጃ ነው ብሎ ከጠቀሰ ያ ነገር በማስረጃ እንዳይቀርብ በግልፅ የሚከለክል ሕግ ካለ ወይም ማስረጃው አግባብነት የሌለው ካልሆነ በስተቀር ማስረጃ በግልፅ ከእገሌ ቤት ተያዘ የሚለው ነገር ካልተገለፀ አይሰማም የምንልበት የሕግ መሠረት የለም በተደጋጋሚ የቀረበ ስለሆነ ነው ይሄንን ያነሳነው ያው አረዲ የታለፈ ነገር ቢሆንም ማለት ነው እንደዚህ ዓይነት ሕግ የለም የሚከለክል ማለት ነው ከእዚያ ቀጥሎ ከእገሌ ቤት ካልተባለ ምን ይሆናል ውጤቱ የሚለው የክሬደቢሊቲ ጉዳይ ነው በማስረጃ ሲመዘን ማለት ነው እሱ በእዚህ ደረጃ የሚነሳ ስላልሆነ በተደጋጋሚ መነሳት የለበትም ሌላው ማስረጃውን በተመለከተ ከተከሣሾች እንደተያዘ አለ እዚህ ላይ ፍ/ቤቱም ጠይቋል ከማን ቤት ተያዘ የሚለው ለምን ከክሬደቢሊቲ ጋር መያያዝ ያለበት ነገር ስለሆነ ከአሁኑኑ መጣራት ስላለበት እየጠየቅን ነው ከማን ቤት ተያዘ የተባለውን ከእገሌ ቤት ተያዘ ያለውን ዐቃቤ ሕግ ይላል ያላለውም ተጠይቋል ዐቃቤ ሕግ የሰጠው ምላሽ አለ አንድ ላይ ነው ተብሎ የተጠቀሰ ከእገሌ ቤት ተያዘ የሚለው እዚህ ላይ ስለሌለ አይሰማም የሚለው የሕግ አግባብ ስለሌለ ተደጋጋሚ ይሄ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በኋላ መግለጫ ላይ የሚቀርብ ነገር ነው ይሄ በእናንተም በኩል ምን ያስረዳል የሚለው ላይ የሚሰጠው የግራ ቀኝ አስተያየት መዝጊያ ላይ የሚታይ ነገር ከሚሆን ውጪ በተደጋጋሚ ይሄ መነሳት የለበትም በእዚህ መልኩ ቢታይ ይሄኛው ወደ 2ኛው ስናልፍ መግለጫው ግልፅ ነው አይደለም የሚለውን በተመለከተ አሁን ጭብጥ ክሱ አይያዝም የክስ ጭብጡ ነው ግልፅ ነው ነገር ግን አሁን ሊቀርብ የነበረው ነገር ምንን ያስረዳል የሚለው መግለጫ እኛ እየጠየቅን ነው እየተመዘገበ ነው አሁን የተያዘው መግለጫ ግልፅ ነው ለእኛ ግልፅ ያልሆነ ነገር የለም ዓላማው ይሄ ነው ይሄንን ያስረዳል ነው ከእዚህ ጋር ይያያዛል አይያያዝም ተሰምቶ መጨረሻ ላይ የሚመዘን ነው ከእዚህ ውጪ ግን ጭብጥ የሚለው ነገር ስለሆነ ግልፅነት የጎደለው የቱ ጋር እንደሆነ ለፍ/ቤቱ ግልፅ አይደለም የቀረበው ነገር ግልፅ ነው ስለዚህ በእዚህ መሠረት መስማቱ ይቀጥል ብለን ብይን ሰጥተናል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አስተምሮ ከዘመተባቸው የእስልምና መርሆች አንዱ ሂጃብ፤ እስልምና ሴት ልጅ በውነቷ ከባዕድ ወንዶች እይታ መሰተር እንዳለባት በፅኑ በማስተማር ፆታዊ ስነ ምግባርን ለመጠበቅ ቢተጋም በፈተናው ሼህ አብደላ ሀረሪ ግን ይህንን መርህ መቀመቀቅ ይከቱታል ፀይሁበያን በተባለው መፅሐፍ ጥራዝ 2 ገፅ 110 ላይ እንደምታዩት ሰላትም ውስጥ ሆነ ከሰላት ውጪ ሰውነት ላይ የተጣበቀ ልብስ ለሴት ልጅ ሀራም አለመሆኑን በግልፅ እንናገራለን በማለት እስላማዊውን ሂጃብ በምዕራባዊያን የተጣበቀ ልብስ ሊለውጡ ሲሞክሩ ይስተዋላል በጥራዝ 2 ገፅ 107 እንደምታዩ ከሴት ልጅ /ግልፅ ያልሆነ/ ተሰጥቷል ለማለት መስፈርቱ ቆዳን መሸፈኑ ነው የጠባብ ሱሪ ቅርፅዋን ቢያሳይም እንኳን በማለት የእስላም ቅርፅዋን ለባልዋ ብቻ ታሳይ ዘንድ የፈቀደላትም /ግልፅ ያልሆነ/ በተዘዋዋሪ ምዕራባውያንን አለባበስ በእስላም የተፈቀደ ያስመስላል ይታያችሁ እንግዲህ የምዕራባውያን ዘፋኞች ሰውነታቸው ላይ የሚለጥፏቸው የተጣበቁ የራት ልብሶች እና ጅንስ ሱሪዎች ሀላል ከተባሉ ምን ያህል ስነ ምግባር አደጋ ውስጥ እንደሚገባ ይህም የተጣመመ አስተሳሰብ በመያዝ ሊባኖሳዊያን ሀባሾች /ግልፅ ያልሆነ/ በተሰኘ መፅሔታቸው ሂጃብን ከፋሽን ጋር ለማጣጣም ችለናል እያሉ የሚፎክሩት እውን እስልምና መስሏቸው ነውን ለመደርመስ ያለመው የሀባሽ ቡድን የተጣመሙ ፆታዊ አስተምሮዎችን ማሰራጨቱን ቀጥሏል ሙፍራህ አዛ ከእነዚህ ፆታዊ ልቅነቶች አንዱ ሲሆን ትርጉሙም በሀጂ ነቢ ሴት ልጅ ታፋ መሀል ብልትን በመከተት ወሲባዊ ንቅቃቄ ማድረግ እንደማለት ነው ይህም በእስላም የተወገዘ ተግባር የፈተናው ሼህ አብደላ ሀረሪ መፅሐፍ ቀላል ወንጀል ሲል ያቃልለዋል /ግልፅ ያልሆነ/ ጥራዝ 2 ገፅ 195 ላይ እንደምታዩት /ግልፅ ያልሆነ/ የሚል ቃል በመጠቀም ሙስሊሞችን ለእዚህ ፀያፍ ተግባር በተዘዋዋሪ ይጋበዛል ይህም መሰል አስተሳሰብ በአይሁዶች ድጋፍ ከሚደረግለት አጥፊ ቡድን ሲሰነዘር መልዕክቱ ግልፅ ነው አፍ አውጥቶም ይናገራል /ግልፅ ያልሆነ/ በሉዱ የሚታጠብ ቀላል ወንጀል ስለሆነ አይዟችሁ ነው ድብቅ መልዕክቱ ሱባሀን አላህ እውነትም ሙስሊሙ ጉድጓድ ተቆፍሎለታል ኃይማኖቶች ሁሉም ግብረሰዶማዊነትን በአንድ ድምፅ ያወግዙታል በተለይ እስልምና አስተምሮት በእዚህ በኩል ጥብቅ ነው ድርጊቱ አላህ እጅግ የጠላው እና የተወገዘ መሆኑን ቁርአን ያስተምረናል /ግልፅ ያልሆነ/ ሕዝቦች የጠፉበት እርኩስ ድርጊት መሆኑንም ያሳውቀናል ያስጠነቅቀናል በእዚህ ረገድ የሚኖር ገራገርነት እና /ግልፅ ያልሆነ/ የሚያስከፍለው መስዋትነት ቀላል አይደለም ይሄንን [illegible] ድርጊት በማራገር

http://ethcriminalawnetwork.com/

አይን ያዩት ምዕራባዊያን የገዙበትን ጠበ ያስተውሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ዶ/ር ዛኪር ባበርካታ ሲዲዎቻቸው እንደጠቀሱት ከኒዮርክ ሕዝብ አንድ ሶስተኛ ያህሉ ግብረሰዶማዊ መሆኑም የድርጊቱን ተስፋፊነት እና አስከፊነት ያሳየናል አዎ ይሄንን እስላም አስተምሮናል እና ሁላችንም እናውቃለን ሙስሊሙን መቀመቅ ሊከቱ ያለሙት የፈተናው ሼህ አብደላ ሀረሪ መፅሐፍ ግን ነገሩን አታካብዱት የሚለን ይመስለናል /ግልፅ ያልሆነ/ ጥራዝ 2 ገፅ 293 ይመልከቱ እስከሪን ላይ እንደምታዩት ባል ሚስቱን በመቀመጫዋ በኩል ቢገናኝ ሀራም እንጂ ሰዶማዊነት አይሆንም በማለት ድርጊቱን ቀለል ለማድረግ እንደተራ ወሲብ ተፈጥሮአዊ ለማስመሰል ተሞክሯል ሱብሀን አላህ ግብረሰዶማዊነት ከተፈጥሮ ጋር የሚቃረን ፀያፍ ተግባር ሆኖ ሳለ ወደ ተራ ወሲብነት ተግባር ዝቅ ለማድረግ ማለም ጤነኝነት ነውን ባል ሚስቱ ጋር ግብረሰዶማዊነት መፈፀምን እንደሌሎች ሀራም ነገሮች /ግልፅ ያልሆነ/ እንዲያየው ማድረግ ከኢስላም ነው አላህ ከመረጠላት ፍኖት አውጥተው እንደፈለጓት አድርገው ሊቀርፁዋት ሁሌም እንደጓጓጉ ናቸው ይኸው አሁንም ሌላ ወጥመድ አዘጋጁላት የፈተናው ሼህ አብደላ ሀረሪ /ግልፅ ያልሆነ/ በሚለው መፅሐፋቸው ጥራዝ 2 ገፅ 162 ሴት ልጅ /ግልፅ ያልሆነ/ ከሽፈነች ሽቶ ተቀብታ ብትወጣም ይጠላል እንጂ ሀራም አይሆንባትም ሆነ ብላ ወንዶችን ለመፈተን እስካልሆነ ድረስ ይሉናል ሱብሀን አላህ ታላቁ ነብይ በሀዲሳቸው ሽቶ ተቀብታ ወንዶችን ለመፈተን የምትወጣ ሴት ዝሙተኛ ናት ሲሉም የነገሩን ክብደት አስተምረውን ሳለ አብደላ ሀረሪ ግን ሆነ ብላ ካልሆነ ግድ የለም ይሉናል አዎ እነሱ ሙስሊሟ እንዲህ ዓይነት ሴት እንድትሆንላቸው ነው የሚፈልጉት የተጣበቁ ልብሶችን የምትለብስ የሚሰነፍጥ ሽቶ በዙሪዋ እያዘራች እና የወንዶችን ቀልብ እየሳበች ሆነ ብዬ ሳይሆን ጥሩ ጥሩ ለመሽተት ነው በሚል እራስዋን የምታታልል ሴት አላህ በቁራአኑ እንዲህ ይለናል /ግልፅ ያልሆነ/ አላህም በእናንተ ላይ ፀፀትን ሊቀበል ይችላል እነዚያም ፍላጎታቸውን የሚከተሉት እውነት ትልቅም መዘንበል እንድትዘነበሉ ይፈልጋሉ ሱረቱን ኒሳ አንቀፅ 27 እስላም እጅግ ካወገዛቸው ተግባራት ዋነኛው መሆኑን የሚስት ሙስሊም የለም ከባድ የውግዘት በትር አሳርፎበታል የውግዘቱን ምክንያት በሚገባ የምንረዳውም አለማችን በወለድ ምክንያት የገባችበትን ችግር ስናስተውል ነው የአለምን ዘጠና በመቶ ሀብት አስር በመቶ እጅ እንዲጠቀለል ያደረገው ወለድ እንጂ ሌላ አይደለም ቁማርም እስላም በቁርአን አንቀፅ ያወገዘው የሼጣን ስራ ሲሆን አላህን ከማስታወስ ... እስር በእ... የሚያባላ

http://ethcriminalawnetwork.com/

እርኩስ ተግባር መሆኑ ይታወቃል እንደሕዝቡ እነዚህ 2 እርኩስ ተግባራት ርቆ የቆየው የሙስሊም ማህበረሰብ ግን ዛሬ በፈተና ሼሆቹ ከባድ መከራ ተጋርጦበታል አይዞህ ወለድ እና ቁማር ከካፊር ከሆነ ሀላል እያሉ ፈተና ላይ የሚጥሉት ሼህ ተብዬዎች ይወተውቱታል እንዳይደናገጥም ይህን መሳይ አቀራረብ ይዘው /ግልፅ ያልሆነ/ የቀደምት ኡሎሞችን ንግግር ከታቦቻቸውን እንደፈለጉ ቆርጠው እየቀጠሉ ከተፈለገበት ኃሳብ ውጪ እየጠቀሱ ሰው በማደናገር የተካኑት /ግልፅ ያልሆነ/ ሼህ አብደላ ሀረሪ /ግልፅ ያልሆነ/ ጥራዝ 2 ገፅ 152 ላይ በጠላት ካፊር ሀገር ከሆነ ወለድም ቁማርም ችግር የላቸውም /ግልፅ ያልሆነ/ ቢሆን ሀላል አድርገውታል በማለት ለወንጀል ያነሳሳሉ ሰው እንዳይደነግጥም በመሀል ቆርጠው የተቀጠሉ ንግግሮችን ከእዚህም ከእዚያም በመውሰድ ጉዳዩ የእውቀት ነክ ልዩነት መሆኑን ለማሳየት ይሞክራሉ የሚያስደነግጠው ግን ይህ ብቻ አይደለም በሌሎች ትምህርቶቻቸው እና ማህደሮቻቸው ሰውዬው በአሁኑ ወቅት ለአለማችን አብዛኛው ሀገራት የጠላት መሆናቸውን በተደጋጋሚ አስተምረዋል አንዳንዶች የሰውዬውን አምታች አቀራረብ በማየት ተታለው /ግልፅ ያልሆነ/ ልዩነት እያስተናገዱ ሊመስላቸው ይችል ይሆናል እውነታውን የምንረዳው ግን አስተሳሰቦቻቸውን ሕብረተሰባዊ ውጤት እና ከአይሁዶች ጋር ያላቸውንም ግንኙነት /ግልፅ ያልሆነ/ ከላይ የተጠቀሱትን 2 ነገሮች ስናገጣጥማቸው የሚሰጡን ስዕል በፈተናው ሼህ አስተምሮ መሠረት ወለድ እና ቁማር በአሁኑ ሰዓት በሁሉም ቦታ የተፈቀዱ መሆኑን አይደለም ይህ ከነጃሳ ገንዘብ እንደሕዝብ ርቀው ለቆዩት ሙስሊሞች ታላቅ ውርደት አይደለም ሱቡሀን አላህ እዚህ ላይ ልብ ይበሉ ለኃይማኖት መፅሐፋቸው /ግልፅ ያልሆነ/ ውጪ ላለው ተራ ሕዝብ በወለድ እንዲያበድሩ እንደሚፈቅድላቸው የሚናገሩት አይሁዳዊያን መላ ሀብታቸውን ያከማቹት በወለድ እና በቁማር አለማቀፍ ስርዓቶች ላይ ነው በመሆኑም ከሁሉም ቦታ ወለድ እና ቁማር ማስፋፋቱ በዋናነኛነት የሚጠቅመው ለማንም ሳይሆን ለአይሁዶች መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው ስለምን ይሁን ሀባሽ እና መሪዎቹ ወለድን ለማበረታታት ሀገራት በሙሉ የጠላት ናቸው የሚሉን ይሄንን መሰሉ አስተሳሰብ በደንብ ሲያጤኑት ምንጩ ከወደ እስራኤል አይመስልምን /ግልፅ ያልሆነ/ ሼህ አብደላ ሀረሪ የሚያሳትሟቸው መፅሐፍ ውስጥ አደናጋሪ ነገሮችን ሲያስተምሩ ቆይተዋል ከእነዚህ አንዱ ደግሞ ቡድኑ ቀድሞ ባሳተማቸው እና አሁን በሚያስተማቸው ኪታቦች መካከል የተስተዋለው የተለየ የዓመታት አቆጣጠር ነው እንደሚታወቀው ሙስሊሙ አለም

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚጠቀመው አቆጣጠር /ግልፅ ያልሆነ/ አቆጣጠር ሲሆን ከእየሱስ ውልደት ጋር ዘተያያዘ አውሮፓውያንን የዘመን ቀመር መጠቀም ሲያስፈልግ ሚላድ ወይም አመተ ልደት የሚለውን ቃል የምትወክለው /ግልፅ ያልሆነ/ ፊደል ጥቅም ላይ ትውላለች ይህም ሙስሊሞች እየሱስ የተወለደበትን ወቅት ለመጠቆም እንጂ በእሱ መወለድ አለም ምህረት ማግኘቱን እንደማናምን ታሳያለች በአረብ ሀገራት የሚታተሙ መፅሐፍትም ይቺኑ ሚን ፊደል ወይም አመተ ልደት ሲጠቀሙ ቆይተዋል የሀባሽ መፅሐፍት ግን ባልታወቀ ምክንያት ዓ.ም የሚለውን ቃል የምትወክለውን ራህማ ወይም ራ ፊደል መጠቀም ከጀመሩ ሰነባብተዋል 1995 የታተመው /ግልፅ ያልሆነ/ ሚ በሚል ያስቀመጠ ቢሆንም በቅርብ ዓመታት የታተሙት ግን ራን መርጠዋል ለምን ይሆን በምሳሌነት እንደ በ2004 የታተመው /ግልፅ ያልሆነ/ 2ኛ እትም ገፅ 3 ራ የሚለውን ይጠቀማል በ2008 የታተመው /ግልፅ ያልሆነ/ 8ኛ እትም ገፅ 3 ራ የሚለውን ተጠቅሟል በ 2002 የታተመው /ግልፅ ያልሆነ/ 11ኛ እትም ገፅ 2 ራ የሚለውን እንዲሁ ተጠቅም እናገኘዋለን በተጠቀሱት በርካታ አጥፊ ተግባራቱ የተወገዘው የሀባሽ ቡድን አለማቀፍ ውግዘት /ግልፅ ያልሆነ/ በርካታ ዘዴዎችን በመጠቀም ሙከራ ማድረጉ አልቀረም ይህም /ግልፅ ያልሆነ/ በየጊዜው መለዋወጥ ነው ከአይሁዶች ከፍተኛ ድጋፍ የሚደረግለት /ግልፅ ያልሆነ/ የተሰፕ የግል ማተሚያ ቤቱን በመጠቀም ቡድኑ በየዓመቱ እትሞቹን ይለዋውጣል የተወገዘባቸውን ነጥቦች ያሻሽላል ይጨምርል ይቀንሳልም ቡድኑን አስከፊ አስተሳሰብ ለመገንባት በፈተናው ሼህ አብደላ ሀረሪ በርካታ መፅሐፍትም የፃፉ ሲሆን ከዓመት ዓመት እንደአዲስ የሚታተሙት የአንድ መፅሐፍ በርካታ ቅጂዎች ግን መጀመሪያዎቹ በገፅም በብዛትም ይለያያሉ በየመሀሉ ውግዘት ያመጡ ቃላቶች እና ሀረጎች ተቆርጠው ይስተካከላሉ በየእትሙ የምዕራፍ ቅደም ተከተሉን በማለዋወጥ ለአንባቢው ገፁ እንዲጠፋበት ያደርጋሉ ዓመት እስከ ዓመት ይዋሻሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ነጥቦች በምሳሌነት እንመልከት /ግልፅ ያልሆነ/ በጣለው በእኛ እትም እንደሆነ ባልተገለፀበት መፅሐፋቸው ገፅ 34 ኢለላህ ከምትለዋ አንቀፅ ቀጥሎ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚል አንቀፅ የተዘረዘረ ቢሆንም በ 1995 በታተመው ይኸው መፅሐፍ ገፅ 26 ላይ ኢለላህ ከሚለው ቃል ቀጥሎ /ግልፅ ያልሆነ/ ነብይ የሚል ሌላ አንቀፅ ተዘርዝሯል ይህ ግልፅ ልዩነት ሲሆን በሌሎች በተለያዩ /ግልፅ ያልሆነ/ መለያየቱን ቀጥሏል ሙቹ እንደታተመ ባልተገለፀበት /ግልፅ ያልሆነ/ መፅሐፋቸው ከገፅ 41 እስከ 63 ድረስ ተዋሊዱ ሙሒማ

3086 6032

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚል ምዕራፍ ያለ ሲሆን በ 1995 ባሳተሙት ይኸው መፅሐፍ ግን ይህ ምዕራፍ ጨርሶ የለም መቼ እንደታተመ ባልተገለፀበት /ግልፅ ያልሆነ/ መፅሐፋቸው ከገፅ 86 እስከ 113 የሚገኙት ገፆች በ 1995ቱ የእዚሁ መፅሐፍ እትም ውስጥ በጭራሽ አናገቸውም /ግልፅ ያልሆነ/ የሚለው ምዕራፍ መቼ እንደታተመ ባልተገለፀው ሰሪሁንበያን መፅሐፍ ገፅ 213 ላይ የምናገኘው ሲሆን በ 1995 የሰሪሁንበያን እትም ላይ ግን በጭራሽ አናገኘውም ለምሳሌ እንመልከት ይህ እስክሪኑ ላይ የምትመለከቱት /ግልፅ ያልሆነ/ የተሰኘ /ግልፅ ያልሆነ/ በ 1996 /ግልፅ ያልሆነ/ 3ኛ ጊዜ የታተመ ሲሆን በገፅ 223 /ግልፅ ያልሆነ/ በሙሉ በቁርአን እና ከሀዲስ ጋር የሚስማሙ ናቸው /ግልፅ ያልሆነ/ በስተቀር ያሳተሟቸው መፅሐፍ በግልፅ ከቁርአን እና ከሀዲስ ይጋጫሉ በማለት /ግልፅ ያልሆነ/ በጥቅሉ አውግዘዋል በገፅ 225 በጃንያ ና በቃድሪያ ተከታዮች መካከል ተደረገ ያሉትን የከራማ ውድድር በመጥቀስ ጃንዮች መሸሻቸውን በመግለፅ ሊያሸፉ ሲሞክሩ ይስተዋላል ይህ በሶፊዮ ማህበረሰብ ዘንድ ተቃውሞ እንዳስነሳባቸው ካዩ በኋላ ግን 2008 በታተመው ይኸው መፅሐፍ 8ኛ እትም እንደምታዩት ወለሀዲዝ ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያለውን ጃንያን ያወገዙበትን አረፍተ ነገር ቆርጠው አውጥተውታል በእዚህም ጃንያን ማውገዛቸውን ጭልጥ አድርገው አስተባብለዋል ይህም ሀባሽ የተባለው ቡድን ኪታቦቹን ከዓመት እስከ ዓመት በመለዋወጥ የተወቀሰበትን ነጥቦችን በማስተካከል ሕዝቡን እያጭበረበረ እንደሆነ በሚገባ ያሳያል አላህ ይጠብቀን /ግልፅ ያልሆነ/ የአለም አሉሞች ተመሳሳይ ድምፅ አላቸው ቡድኑ ምንጊዜዎቹም የእስላም ጠላቶች ኡሁዶች በኩል የሚደረግለትን ከፍተኛ ድጋፍ በማጤን እና መሠረት በማድረግ በርካታ አሉሞች ሰዎች ከቡድኑ አደገኛ አስተሳሰብ እንዲጠነቀቁ አደራ ብለዋል ምንም እንኳ ሀባሾች በተደጋጋሚ ሱፍያ ነን /ግልፅ ያልሆነ/ ነን ሲሉ የገለፁ ቢሆንም ታላላቅ የሱፊ አሉሞች ግን አናውቃችሁም ከእኛ አይደላችሁም ሲሉ መልሰውላቸዋል ሌሎች የዳዋ እና የአስተሳሰብ መስመሮች ላይ ያሉ አሉሞችም ቡድኑን እና አይሁዳዊ ተልኮውን አውግዘዋል ከእነዚህም /ግልፅ ያልሆነ/ እጅግ ጥቂቱን አብረን እንመለከታለን 1ኛ ዶ/ር /ግልፅ ያልሆነ/ ከሶሪያ ታላላቅ ሱፊያ /ግልፅ ያልሆነ/ አንዱ ሲሆኑ /ግልፅ ያልሆነ/ ለረጅም ጊዜ አገልግለዋል በተለይ /ግልፅ ያልሆነ/ ያላቸው ጉልህ አስተዋፆ እና ጥቅል እውቀት ግዙፍ ክብርን ያስገኘላቸው ሰው ናቸው በደማስቆ ዩኒቨርስቲ የእስላማዊ /ግልፅ ያልሆነ/ ማህበር ፕሬዘዳንት ሲሆኑ /ግልፅ ያልሆነ/ ለተባለው 8 ጥራዝ /ግልፅ ያልሆነ/ መፅሐፋቸው በአለም

3ዐ¹⁄₆ 6033

http://ethcriminalawnetwork.com/

ዘንድ ይታወቃሉ እኚህ ታላቅ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሁን እና እንቅስቃሴውን አስመልክቶ ተጠይቀው-የሚከተለውን ብለዋል /ግልፅ ያልሆነ/ የተወሰኑ ወጣቶች የሚሰበሰቡበት /ግልፅ ያልሆነ/ የሚባል ቡድን አለ እና ስለእነዚህ ጠሞ አጥማሚዎች እኔም ሳልሰማ አልቀረሁም ከእነሱ መራቅ እና ሰዎችን ማስጠንቀቅ የግድ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ሰዎች ናቸው በስሜት ለሕዝቡ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሰጣሉ ሀራሙን ኣላል ሀላሉን ሀራም አድርገዋል የግብፁ አላሳር ዩኒቨርስቲ በአለም ሙስሊሞች ዘንድ እጅግ ተቀባይነትን /ግልፅ ያልሆነ/ እስላማዊ እውቀት ተቋም ነው በሻፍያመዛብ የበለጠ መጠናከሩ የሚነገርለት ይህ ተቋም ከሀባሾች እንጠነቀቅ ዘንድ ፈትዋ የሰጠ ሲሆን ፈትዋውን በበርካታ አለማቀፍ እስላማዊ ድህረገፆች እና ሎጎች ላይ ማግኘት ይቻላል አዛህርን እና /ግልፅ ያልሆነ/ አልመስሪያን ወክለው ፈትዋ የሰጡት /ግልፅ ያልሆነ/ ፕሮፌር ዶ/ር አሊ ጁማአ ሲሆኑ በ 1993 ጀምሮ የግብፅ ተቀዳሚ ሙፍቲ ሆነው ያገለገሉት ታላቅ አሊም ናቸው የሚከተለውን ብለዋል ይህ የሀባሽ ቡድን የሚከተለው አብደላ አልሀረሬ አልሀበሽን ሲሆን ግልፅ እና ድብቅም አጀንዳ አላቸው ከላይ ከላይ ሲታይ ቡድኑ /ግልፅ ያልሆነ/ በአቂዳ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ሀሰን /ግልፅ ያልሆነ/ የሚከተል ቢመስልም በውስጥ ግን አላማቸው የሙስሊሙን አቂዳ ማበላሸት እና ሙስሊሙን እስር በእርስ ማበጣበጥ ነው በተጨማሪም ከእስላም ጠላቶች እየተከፈላቸው የሚሰሩ ቅጥረኞች ናቸው ሼሁ አለፍ በማለትም እንዲህ ይላሉ አብደላ ሀረሪ በየቦታው ፅብ እንዲያስነሱ ተማሪዎቹን መክሯል ለምሳሌ ሳይንሳዊ መርሆችን ሳይቀር በመጋጨት አሜሪካ ውስጥ /ግልፅ ያልሆነ/ ትክክል አይደለም የሚል ውዝግብ የፈጠሩ ሲሆን ጃፓን ውስጥም ተመሳሳይ ተግባር ፈፅመዋል ሌሎችንም በርካታ ነጥቦች ካነሱ በኋላ ዶክተሩ ከቡድኑ እያስጠነቀቁ ያሉ ሌሎች ታዋቂ እስላማዊ ተቋማትን በመጥቀስ ፈትዋቸውን ያጠናቅቃሉ 3ኛ ሀይ አትኪባር አለኡለማ በርካታ የሙስሊም ሊቃውንትን ያካተተ የፈትዋ ስጪ ድርጅት ሲሆን በሰለፍያው የዳዋ መስመር ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ተቋም ነው ሀባሽ የተባለውን ቡድን አስመልክቶ ታላላቅ አለማዎችን በማሳተፍ እና እንዲፈርሙ በማድረግ ስለቡድኑ የተሳሳቱ እምነቶች እና ፈትዋዎች በርካታ ነጥቦችን ከዘረዘረ በኋላ የሚከተለውን ፈትዋ ሰጥቷል ሀ የሀባሽ /ግልፅ ያልሆነ/ የጠመመ ጀምአ ነው ለ ቡድኑን ፈትዋ መከተል በፍፁም አይበቃል ሐ በማንኛውም ወቅት ንግግራቸው ላይ መተማመን አይገባም 4ኛ የአለም ኡለማዎች ማህበር ፕሬዘዳንት የሆኑት እና ሚዛናዊ አቋማቸው የሚታወቁት ኢማም

6034

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፕሮፌር የሱፍ አልቀርባዊ ስለሀባሽ ቡድን ባስጠነቀቁበት የፈትዋ ስብስብ መፅሐፉቸው ፈታአዋ አሉመዋ ሲራ ፕራዝ 3 ገፅ 685 የሚከተለውን /ግልፅ ያልሆነ/ ሊባኖስ ውስጥ ስለተቋቋመው ቡድን ከሰማው ዓመታት ተቆጥረዋል አፈንጋጭ አስተሳሰቦችን በማስተማር ሊባኖስ ውስጥ ውዝግብ ፈጥረዋል የተጣመሙ አቅጣጫዎችን እና አደገኛ አመለካከቶችን አሰራጭተዋል ይህ ደግሞ በአቂዳም በፍቅህም ሆነ በስነ ምግባር ዘርፍ ነው ዛሬ ሰዎች በገንዘብነት የሚጠቀሙበትም የወርቅ ብር ከዘካ ግዴታ ውጪ አድርገዋል ከወርቅ እና ብር ውጪ ያለ ሕጋዊ /ግልፅ ያልሆነ/ መገበያያ ነው በማለትም የወረቀት ገንዘብ ወለድም ፈቅደዋል አለፍ ብለው ዶክተሩ እንዲህ ይላሉ ያለምንም ድንበርም የወንድ እና ሴት ቅልቅልን ፈቅደዋል ከእዚህ በላይ የፈጠሩት አደጋ ደግሞ በኃሳብ የተለያቸውን ሙስሊም በሙሉ /ግልፅ ያልሆነ/ የዘመናችንም ሆነ ቀደምት ኡለማዎችን አክፍረዋል ሼህ /ግልፅ ያልሆነ/ እስላም /ግልፅ ያልሆነ/ በእነሱ አስተሳሰብ የተገነቡትን ሁሉ አክፍረዋል በአረብያ የተነሳውን /ግልፅ ያልሆነ/ ተሀድሶ ፋኖ ሼህ መሐመድ /ግልፅ ያልሆነ/ አክፍረዋል የዘመናችን አለማዎችም /ግልፅ ያልሆነ/ የመሳሰሉትን በርካታ አለሞች አክፍረዋል አለፍ ብለው ዶክተሩ እንዲህ ይላሉ እነዚህ ድንበር ኃላፊ እና የጠመሙ ሰዎች በአቂዳ /ግልፅ ያልሆነ/ በፍቅህ ኢማሙ /ግልፅ ያልሆነ/ በስነ ምግባርም /ግልፅ ያልሆነ/ የተባለውን የሱፍያ /ግልፅ ያልሆነ/ እንደሚከተሉ ይናገራሉ በተግባር ሲታይ ግን ከ3ቱም ፍፁም የራቁ ናቸው በአስተሳሰብም በስነ ምግባርም አዲስ ዓይነት /ግልፅ ያልሆነ/ ትልቁ አጀንዳቸው አንድነትን መበተን መልካም ሰሪዎችን መወስወስ በሙስሊሞች ሰልፍ መሀል የፈተና እሳት መለኮስ እና ለዲኑ የቆመን ሁሉ ማደናቀፍ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ እጅግ ታዋቂ የሆኑት እና የሀባሽ የውግዘት በትር ያረፈባቸው ሼህ መሐመድ ሰይድ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለሀባሽ ጥያቄ ቀርበላቸው የሰጡት መልስ ይሄንን ይመስላል ጥያቄ ቤሩት ውስጥ አብደላ ሀረሪ የሚባሉ መሪ ያሏቸው ሀባሾች ወሀብያን ተከትሎ መስገድ አይበቃም ኢማም /ግልፅ ያልሆነ/ የሚል ንግግር ተናግረዋል እርሶ ምን ይላሉ ሼሁ እንዲህ ብለው መለሱ ወያብያን ተከትሎ መስገድ ሀራም አይደለም የተከታዩም ሰላት ትክክል ነው /ግልፅ ያልሆነ/ መሞቱን ያላረጋገጥነውን ሰው ካፊር ማለት ክልክል ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ሲሞቱ ለመክፈራቸው ምስክር የሆነ ሰው ደግሞ የለም በእዚህ ላይ ሰዎቹ ወይም ሀባሾች አብዛኛውን ሙስሊም አክፍረዋል /ግልፅ ያልሆነ/ እና እኔንም ጭምር አክፍረውኛል በእነሱ አመለካከት ... ትክክለኞቹ

3089 6035

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሙስሊሞች እነሱ ብቻ ናቸው ንፁህና ሁድን አውስትራሊያ ውስጥ ቱሌም ኤፍ ኤም የተባለ ሬዲዮ ጣቢያ አቋቁሞ ፍቃዱን ለማሳደስ በ 2006 ባመለከተበት ወቅት 36 ሙስሊም ተቋማትን የወከሉ እና በቁጥር 100 የሚደርሱ የአውስትራሊያ ታዋቂ አሎሞች ፍቃዳቸው እንዳይታደስ ያመለከቱ መሆኑን ሙስሊሙ ቪሌጅ ዶት ኮም የተባለው ድህረ ገፅ እንደምታዩት ዘግቧል አውስትራሊያ እስላማዊ ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት አሚር አሊ እና የሲዲኒ ላኬም /ግልፅ ያልሆነ/ ኢማም ሼህ ታጁዲን አልሂላሊ አቤቱታውን ካቀረቡት ውስጥ ዋነኞቹ ሲሆኑ የሀባሾች ባህሪ እና ተግባር በሰዎች መካከል ጥላቻ እና ክፍፍልን መፍጠር ነው ይህ ደግሞ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ጎጂ ከመሆኑ ሌላ አውስትራሊያ ሕብረ ብሔራዊ ማህበረሰብ አጠቃላይ ፖሊሲ ጋር ይጋጫል ሲሉ ገልፀዋል ያቀረቡት አቤቱታም ሀባሽ ተቀባይነት የሌላቸውን እምነቶች በሰዎች ላይ ይጭናል በማለት ቡድኑን ያወግዛል /ግልፅ ያልሆነ/ ስለእነዚህ ሰዎች ምን እንደሚሉ ተመለከቱን እውን እነዚህ አለሞች ሁሉ /ግልፅ ያልሆነ/ የተሳሳተ አቋም ይዘዋል በፍፁም እነዚህ ለናሙና ያህል ተጠቀሱ እንጂ በርካታ የአለማችን አለሞች አውግዘዋቸዋል የሕንድ እና የፓኪስታን ታላላቅ የዳዋ /ግልፅ ያልሆነ/ ከቡድኑ አጥፊ አስተሳሰብ እንዲጠነቀቁ ሰዎቻቸውን አስተምረዋል በሀገራችን ኢትዮጵያ የሚገኙ /ግልፅ ያልሆነ/ ተቃውሞአቸዋል አዎ ሀባሽ ሙስሊሙን ለመከፋፈል በአይሁዶች የተላከ ቅጥረኛ ቡድን መሆኑን የአለም ኡለሞች ተስማምተዋል እርሶስ አይስማሙምም ከመንትያ ሕንፃዎች ጥቃት በኋላ አሜሪካ እና ሀጋሮቿ ፊታቸውን በሙሉ ወደ እስልምና አዙረዋል ይህም የሆነበት ዋነኛው ምክንያት ከቀዝቃዛው ጦርነት መጠናቀቅ እና የራሽያን መበታተን ተከትሎ ለምዕራቡ አለም በተለይም ለአሜሪካ ትልቅ እራስ ምታት መሆን መቻሉ ነው አሜሪካ እና የምዕራቡ አለም ይሄንን የእስላም ስጋት ከእነ አካቴው ለማጥፋት አሸባሪነት እና አክራሪነት ስም በኢራቅ እና አትጋኒስታን ላይ ወታደራዊ ወረራ አድርገዋል ጦራቸውን ሊልኩ ባልቻሉባቸው ሀገራት ደግሞ ከፍተኛ የባህል እና የአስተሳሰብ ወረራ ሲያካሂዱ ቆይተዋል ጠላቶቻቸውን ለማጥቃት ምንም ነገር ከማድረግ የማይመለሱት የምዕራቡ አለም ሀገራት በእነዚህ ወታደራዊ እና የባህል ወረራዎቻቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ለህልፈተ ሕይወት እና ለአእምሮ ልሽቀት ዳርገዋል ይህንን ሁሉ ፈፅመው ግን የእስልምና ኃይማኖት ሊበገርላቸው አልቻለም እነሱም በድል አድራጊነት ስሜት ወደ ሀገራቸው አልተመለሱም የእስላምን ሕልውና ከስሩ መንግሎ የሚጥል መላ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲፈልጉ ቆይተዋል በመጨረሻም መላውን አንድ አለማቀፍ ድርጅታቸው አግኝቶላቸዋል ድርጅቱም /ግልፅ ያልሆነ/ ኮርፔሬሽን ይባላል በሌላ ስሙ ሴንተር ኦፍ ሚድል ኢስት ፐብሊክ ፖሊሲ ወይም ናሽናል ሰኩሪቲ ሪሰርች ዲቭዥን ይባላል ድርጅቱም አሜሪካ እና አጋሮቿ አለማቀፍ ደረጃ ሊከተሏቸው የሚገቡ ፖሊሲዎችን የሚያረቅ እና ለስራ የሚያዘጋጁ /ግልፅ ያልሆነ/ አሜሪካ የሰላ ድርጅት ወይም ሲአይኤ አሜሪካ አየር ኃይል እና ሌሎች ወታደራዊ እና ሲቪል ተቋማት ጋር በመጣመር ሰፋፊ የፖሊሲ እቅዶችን ይነድፋል የአዋጪነት እና የቅድመ ውሣኔ ረቂቆችንም ያዘጋጃል በመካከለኛ ምስራቅም ለአሜሪካ የጦርነት እና የፖሊሲ ውሣኔዎች ምንጭንም ይኸው ተቋም ነው ከ 1600 በላይ ቋሚ ሠራተኞችም አሉት ለአሜሪካ እና ለምዕራቡ ሀገራት እስልምናን ለማሽመድመድ መላ አገኘሁ ያለውም ራንድ ነው ራንድ ያገኘው መላ እስላምን በሰርጎ ገቦች ማሽመድመድ ነው ይህንንም በሙስሊሙ ወርድል አፍተርናይን ኢለቨር ሲቪል ዲሞክራቲክ ኢዝላም እና /ግልፅ ያልሆነ/ ኔት ወርክስ በተባሉ የጥናት ስራዎች አካቶ ለአለም አስተዋውቋል ራንድ ከጥናቱም አሜሪካ እና አጋሮቿ ደህንነታቸውን አለማቀፋዊ ጥቅሞቻቸው እና ተሰሚነታቸውን ለማስጠበቅ ለዘብተኛ ሙስሊሞችን ማስልጠን እና ሁሉንም ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት እንደሚጠበቅባቸው /ግልፅ ያልሆነ/ ለዘብተኛ ተብለው ከተጠቀሱ ሙስሊም ቡድኖች መካከል በመጀመሪያ ተርታ የተቀመጠው /ግልፅ ያልሆነ/ ወይም የሀባሽ ቡድን ነው ይህ ቡድን በብዙ መልኩ የምዕራባውያንን ፍፁም የበላይነት የማስጠበቅ ፍላጎት እንዳለው እና /ግልፅ ያልሆነ/ ሙስሊም እንደሆነ ራንድ ይመሰክራል ምዕራባውያን ያለው ልዩ ተቆርቋሪነት እና የአለም ሙስሊሞችን ሁሉ በጠላትነት መፈረጁም ስለ አጋርነቱ ከሚያስመሰክሩት ድንቅ አቋሞቹ መካከል በዋነኛነት እንደሚጠቀስ ራንድ እና /ግልፅ ያልሆነ/ የመሳሰሉ ግለሰቦች /ግልፅ ያልሆነ/ የጥናት ተቋሙ ራንድ እነዚህን ሁኔታዎች ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከጥናቱ ማጠናቀቂያ ላይ ተከታዮቹን ማህበራዊ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ የውሣኔ ምክሮች ለአሜሪካ ለግሷል ሀ ለዘብተኛ ሙስሊሞችን ማለትም የሀባሽ አስተሳሰብን ለሚያራምዱ /ግልፅ ያልሆነ/ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ ለ መስኪዶች አካባቢ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለዘብተኛዎች ማለትም በሀባሾች ቁጥጥር ስር እንዲገቡ እገዛ ማድረግ ሐ በለዘብተኛች ወይም በሀባሾች ለሚሰሩ ባህላዊ እና ትምህርታዊ ቅስቀሳዎች ድጋፍ መስጠት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር

http://ethcriminalawnetwork.com/

መሆኑን እና መ በሁሉም /ግልፅ ያልሆነ/ የሚገኙ ለዘብተኛ የሀባሽ ቡድኖች አንድ እንዲሆኑ እና እንዲረዳዱ አለምአቀፍ ኔትወርክ መዘርጋት ድጋፎች እና እገዛዎች ማድረግ ያለባት አሜሪካ ብትሆንም እገዛውን ማድረግ ያለባት በተዘዋዋሪ እንጂ በቀጥታ መሆን እንደሌለበት ራንድ ያስጠነቅቃል በእዚህ ምክንያት አድርጎ የሚያነሳውም ለዘብተኞቹ ቡድኖች ከአሜሪካ ድጋፍ ማግኘታቸው ከታወቀ በሙስሊሞች ዘንድ ውግዘት ሊገጥማቸው እንደሚችል በመገመት ነው በምስራቅ አፍሪካ የአሜሪካ ልዩ አጋር እየተባለች የምትጠራው ሀገራችን ኢትዮጵያ የእዚህ አለምአቀፍ ፀረ እስላም ዘመቻ አካል ከሆነች ሰንብቷል የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ነፃ መሪ ድርጅት እንዳይኖራቸው ሙስሊም ተማሪዎች ኃይማኖታቸውን ጠብቀው ትምህርታቸውን እንዳይማሩ እንቅፋት በመፍጠር ሽብር ሲነዛ የቆየው የኢህዴግ መንግስት አሜሪካ የሰጠችውን የቤት ስራ ለማስፈፀም ዕቅድ ይዞ መንቀሳቀስ ከጀመረ 10 ዓመት ሊሞላው ጥቂት ዓመታት ብቻ ቀርተውታል የአቶ መለስ መንግስት ቤት ስራውን በአግባቡ እና በታዛዥነት ስሜት እየሰራ ለመሆኑም አሜሪካውያን እራሳቸው ምስክር እየሆኑ ነው ኢትዮጵያ የአሜሪካ ጉዳይ አስፈፃሚ የነበሩት ቪኪያዲስተን በአሜሪካ ኮንግረስ ቀርበው የአቶ መለስ መንግስት ምስራቅ አፍሪካ ያለውን የእስልምና እንቅስቃሴ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚደረገው ጥረት ትልቁን አስተዋፆ እየበረከቱ በመሆኑ አሜሪካ በብዙ መልኩ ልትደግፈው ይገባል በማለት አቶ መለስ ያላቸውን አጋርነት በጉልህ ያንፀባረቀ ንግግር አድርገዋል ሴትየዋ ይሄንን ንግግር ያደረጉት ግን አቶ መለስ መንግስት ተቃዋሚዎችን በማሰብ ጋዜጠኞችን /ግልፅ ያልሆነ/ ዲሞክራሲን በመደፍጠጥ እና የአንድ ግለሰብ የበላይነት የነገሰባትን ኢትዮጵያ እየፈጠረ ሳለ ነበር ኢህዴግ መራሹ የኢትዮጵያ መንግስት ሙስሊሞችን አንድነት ለማናጋት ባስቀመጣቸው የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ባለስልጣናት ጋሻጃግሪነት የቤት ስራውን እየሰራ የሚገኘው በብዙ አቅጣጫ ነው ዋነኛው ግን ለዘብተኛ ሙስሊም ተብዬውን የሀባሽ ቡድን በኢትዮጵያ ዋነኛው የሙስሊም አንጃ አድርጎ መትከል ነው ይህ እንቅስቃሴ የተጀመረው በ 1995 ሲሆን በወቅቱ የሀባሽ መስራች እና መሪ ሼህ አብደላ ሀረሪ ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ጥረት ተደርጎ በመሳካቱ በ 1996 ሰውዬው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል በወቅቱም ቦሌ አየር ማረፊያ ድረስ በመሄድ አቀባበል ያደረጉለት አቶ ጁነዲን ሳዶ እና የመከላከያ ኢታዥር ሹም [illegible] ሼህ አብደላ አዲስ አበባ በቆዩበት ወቅት የተለያዩ የሀገሪቱ ቦታዎችን በመንግስት ሄሊኮፕተር የጎበኙ

ሲሆን ፎርጅድ ፓስፖርት ተዘጋጅቶም በሀሰተኛ ስም የሀጂ ጉዞ እንዲሄዱ ተደርጓል ይህ የሆነው ከሊባኖስ የሳውዲ ኢምባሲ ለሰውዬው ቪዛ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ ነበር እራሱን ብቸኛ ሙስሊም እና አዋቂ የሚያደርገው ግለሰብ ሀሰተኛ ስም እና ፎርጅድ ፓስፖርት ሲጠቀም ማየቱም ምን ያህል አሳፋሪ ነው አብደላ ሀረሪ ከሀጂ ጉዞ መልስ በአዲስ አበባ የተወሰኑ ቀናት የቆየ ሲሆን በአሜሪካ እና የእንግሊዝ ኢምባሲ የባህል ክፍል ኃላፊዎች ሰውዬውን እጅ ለመንሳት ያረፉበት ቦታ ድረስ ሄደውም እንደነበር በሰፊው ይነገራል ሆኖም ከእዚያ ቀድሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ሌላ አንድ ግለሰብ የሀባሽን አስተሳሰብ ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት ስለሚቻልበት ሁኔታ ከእነ ራንድ ተሞክሮ በመነሳት አንድ ጥናት እንዲያዘጋጁ ተደርጓል ሳሚር አዲ የተባለ የሀባሽ ቡድን ከፍተኛ አመራር እና ከእዚህ ቀደም በሊባኖስ በወንጀል ድርጊት ተከሶ የነበረ ሰው በመጅሊስ በኩል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ትምህርት እንዲሰጥ የተደረገ ሲሆን ትምህርት ለመስጠት በተገኘባቸው አንዋር መስኪድን ጨምሮ የተለያዩ መስኪዶችም የኢትዮጵያ ሙስሊም በሙሉ ከፍረዋል ብሎ በማስብ ዳግም ሸሀዳ ሲያስይዝ ተስተውሏል መጅሊሱም በሀባሾቹ ድጋፍ እንዲሰጡት በይፋ ጠይቋል ይህ ጥረት በእዚያው ዓመት በ 1996 በሀባሾች የመጀመሪያው ማዕከል አዳስ አበባ ቶታል 3 ቁጥር ዙር ማዞሪያ አካባቢ እንዲከፈት መከንያት ሆኗል በእዚህ ማዕከል ምክትል ስራ አስኪያጅ የነበሩት አቶ መሐመድ ኢብራሒም /ግልፅ ያልሆነ/ በተመራው እና በ 2001 ወንበር ላይ በተቀመጠው አዲሱ መጅሊስ ውስጥ ምክትል ስራ አስኪያጅ ሆነው ኋላ ላይ ተመርጠዋል የማዕከሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ደግሞ አቶ አህመድ ባሻ ይባላሉ ተጀምሮ በማዕከሉ ይፋዊ ሀባሽ አስተሳሰብ ትምህርት ሊባኖስ በመጡ አስተማሪዎች መስጠት ተጀምሯል የሀባሽ ትምህርት መስጫ ማዕከሉን ፋይናንስ ሲደግፉ የነበሩት አስተሳሰቡን በዝምድና እንጋራዋለን የሚሉ አንዳንድ ባለሀብቶች ሲሆኑ ከእነዚህም ማዕከል የፔራም ካምፓኒ ባለቤት አቶ አብዱል ከሪም ይገኙበታል ማዕከሉ የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች በብሔር እና በዘር የነገጠለ በመልመል ወደ ዋና ማዕከሉ ሊባኖስ መላክ የጀመረው በ 1998 ነው በወቅቱም በመጀሪያ ዙር የእስኮላርሽፕ ትምህርት 37 ተማሪዎች ወደ ሊባኖስ ተልከዋል ሆኖም በማዕከሉ አጫጭር ስልጠናዎችን ወሰደው የወጡ ወጣቶች የዩኒቨርስቲዎችን ሙስሊም ጀማዎች ማመስ ጀምረዋል ነበር ሙስሊም ጀማ ተሪማሪዎች በመነጠል የተለየ የመስገጃ ቦታ ይሰጡን ከማለት አንስቶ የተለያዩ

አስነዋሪ ተግባራትን እስከመፈፀም ደርሰው ነበር አንዳንድ ዩኒቨርስቲዎችም ሙስሊም የጀማ አባላት እነዚሁ አባሾች ምክንያት ከዩኒቨርስቲ ለመባረር እና ለእስር ለመዳረግ በቅተዋል /ግልፅ ያልሆነ/ በየካቲት 10/2000 በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል ውስጥ በአዲስ አበባ እስራኤል ኢምባሲ ተባባሪነት አንድ መድረክ ተዘጋጀ የመድረኩ የጥናት ወረቀት የማቅረብ እቅድ ተይዞ አንድ እስራኤላዊ ግለሰብ ተጋብዟል የጥናት ወረቀቱ እስፖንሰር አድራጊ ደግሞ በኢትዮጵያ የእስራኤል ኢምባሲ ነው በቦታውም በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር እና ሌሎች የእስራኤል አጋሮች ተገኝተዋል ግለሰቡ ኢትዮጵያን በክርስቲያናዊ ገፅታ በመሳል ሙስሊሞችን በፀባጫሪነት የሚነቅፈው ፕሮፌሰር ሀጋይ ኤርሊች ነበር ሀጋይ በዕለቱ አልሀባሽ ኤንድ ወሀብያ ኢንተርፕሪቴሽንስ ኦፍ እዝላም የሚል ርዕስ የሰጠውን የጥናት ወረቀት ለታዳሚያን አቅርቧል ታጋይ ኤርሊች /ግልፅ ያልሆነ/ ተቋማት ሀባሽን ለዘብተኝነት በመግለፅ ለኢትዮጵያ ሀባሽ የሚባለው እስልምና ይሻላችዋል የሚል ሰይጣናዊ ምክሩን ለገሰ ሀጋይ ሀባሾች ከክርስቲያኖች ጋር ተቻችለው ስለመኖር ያስተምራሉ ሴቶች በነፃነት የፈለጉትን እንዲለብሱ ይፈቅዳሉ ሙዚቃ እና ዳንስም አይከለክሉም በማለት ሀቦሾች ለዘብተኛ ስለመሆናቸው ማስረጃዎችን በመጥቀስ ለማሳመን ጥረት አደረገ በቦታው የተገኙ እድምተኞች በፕሮፌሰሩ ፊጣን /ግልፅ ያልሆነ/ በመስጠት የፕሮፌሰሩን ኃሳብ አጣጥለውታል ይህም መድረኩን ሙሉ በሙሉ ያልተሳካ እንዲሆን አድርጎታል ሀጋይ መድረኩ ባይሳካለትም ሀባሽ ለኢትዮጵያ ይበጃታል የሚለውን ኃሳብ ተግባራዊ ለማስደረግ የመንግስት ባለስልጣናትን ሲጎተጉት ቆይቷል ኃሳቡ በባለስልጣናቱ ተቀባይነት እንዲያገኝም በወቅቱ ለሚዲዎች ገልፆ ነበር እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ኢህዲግ መንግስት ሼህ አብደላ ሀረሪን በኢትዮጵያ ለ 2ኛ ጊዜ ለማስመጣት ጥረት እያደረገ ነበር በአሁኑ የሰውዬው አመጣጥ /ግልፅ ያልሆነ/ የነበረው ግን በቋሚነት በኢትዮጵያ ለማኖር በማሰብ ነበር በአምባሳደር መዲህ የሚመራ እና ሰውዬውን የሚቀበል ብሔራዊ ግብረኃይል በማቋቋም እና እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንዳለ ድንገት አንድ አስደንጋጭ ዜና ተሰማ በ 2001 ረመዳን ወቅት ኢትዮጵያ እንዲደርሱ ታስበው የነበሩ ሼህ አብደላ ሀረሪ ሞቱ እና ሴራቸውን አላህ አከሸፈባቸው አላህም ተንኮላቸውን መለሰባቸው የሴራቸውን ድር እና ማግ ለአዲስ ፈትለው አዲስ ሴራ ለመጎንጎን ሲያደፍጡ ቆይተው 2003 የአዲሱ ሴራቸውን ዕቅድ ይፋ አደረጉ የኃይማኖት አክራሪነት እና የኃሳ ግጭቶችን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አለምአቀፋዊ ወንድምአማችነት መመስረት እስልምና ግዴታ ያደርጋል እና ሰዎች አስተሳሰባቸውን የሚገነቡባቸው ምንጮች የተለያየ ሊሆን ይችላል ኃይማኖታዊ ሊሆን ይችላል ኃይማኖታዊ ያልሆኑ ደግሞ እረዮተ አለሞች ሊሆኑ ይችላሉ አንድ ሰው ስምንቱን ስትወስድ ማርክሲዝምን ሊከተል ይችላል ኃይማኖት ዘር ምናምን ምናምን የምትለው አልሰማም እኔ የምሰማው የክላስ ጉዳይ ነው ሊል ይችላል ያንን የክላስ ጉዳይ እረዮተ እረዮተ አለሙን በዛ መልክ ሊያስኬድ ይችላል እስልምናን ስትወስድ ግን ሙስሊም ነኝ ካለ አንድ ግለሰብ ኢሚዲየትሊ ምን ሊሆን ይችላል ምናልባት የማያውቅ ካልሆነ በስተቀር ምን አይነት አስተሳሰብ ውስጥ ይገባል ሁሉም ነገ የኔ ወንድም ነው ብሎ ያስባል ስለዚህ /ግልጽ ያልሆነ/ እኔ በአምላክ ዘንድ የሚኖረኝ ቦታ እኔ ከሷ የተሻለ የምሆነው እሳሆን እስከሆንኩ ነው አላህ የሚፈልገውን ካደረግኩኝ ድረስ ብቻ ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ የመልክተኛውን ትእዛዝ ይቀበላል ማለት ነው የመልክተልናው ትእዛዝ ደግሞ ሰላህ ወይሰለም መበደል የማይፈቅድነው ማለት ነው ከሁሉም ጋር በሰላም እንድትኖር ያዝሃል ስለዚህ ሙስሊም መሆን ማለት ከእንስሳጋር
- ከየትኛውም ፍጡር ጋራ በሰላም የመኖርን ባህሪ የሚያዳብር ማለት ነው
- ከምትኗኗራቸው ሰወች ጋር ሰላምን እንዳይሰጡህ የሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ እየሬጠሩ ከሆኑ ግን እምትመርጠው ማንን ይሆናል ማለት ነው ኢትዮጵያ ውስጥ በዜግነት የምትወዳጀውን ወንድምህን ቢባል ሳይሆን ምናልባት ቻይና ውስጥ ያለ አንድ ሙስሊም ለአንተ ከፍተኛውን ሚና ይወስዳል ማለት ነው እና ደብል የሆኑ ነገሮች አሉ ኢትዮጵያዊ ሆነው ሙስሊሞች ከሆኑ የተሻለ ቦታ ይኖራቸዋል ኢትዮጵያ ሆነው ሙስሊሞች ያልሆኑ ግለሰቦች ቻይና ውስጥ ካለ ጣኦት አምላኪ ሰው የተሻለ ቦታ አላቸው ማለት ነው ስለዚህ በጥሩ ነገሮች ላይ መኗኗር እስከታዘዘ ድረስ ያለ ሙስሊም ሊኗኗር ይችላል ሰወች ግን ሃይማኖታትውን ፈልገው ኃይማኖታቸውን ለማሳደግ ፈልገው የሌሎችን ኃይማኖት ለመጨቆን በሚነሱበት ወቅት ላይ ግን የግሩፕ አይደንቲቲ ... ሁኔታዎች የተለየ ኬዝ መያዝ ይጀምራሉ ማለት ነው ስለዚህ ከዘሩ ይልቅ እምነት ይስቀድማሉ ማለት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

360 2006

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ነው ይሄ አስተሳሰብ በዋናነት በጣም /ግልጽ ያልሆነ/ ሰወች የኃይማኖት ... እየነፈግካቸው ስትመጣ ለረጅም ምእቲአመታቶች የተገነባ ስርዓት ... ይሄኛው ስርዓት ፌደራል ስርዓት ከመምጣቱ በፊት ማለት ነው ሙስሊሞች እንደ 2ኛ ዜጋ ይታዩ ነበረ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ይታዩ የነበረው በእምነታቸው ምክንያት ከሆነ እርግጠኛ በ2ኛ ዜግነት እንዲታዩ ያረጋቸው ሃይማኖታቸው ከሆነ አሁንም ደግሞ ኃይማኖት ... ጣልቃ እየገባ ኃይማኖታቸውን በስርዓት እንዳይከተሉ የምታደርግ ከሆነ የድሮውን ስርዓት ማምጣት እንደሆነ ስለሚታሰብ የፌደራል ስርዓቱ ሕልውና ጥያቄ ውስጥ ይገባል

- ኃይማኖታዊ ነፃነት ብቻ ሳይሆን የኃይማኖታዊ ነፃነት እንደተጠበቀ በሆኑ ኃይማኖትህ ላይ የሚደርስ ማናቸውም አይነት ጫናዎችንም መከላከል እንዲያስችሉ መሆን መቻል አለባቸው ማለት ነው የተለያዩ ጭቆናዎች እና መገለሎች እንዲቀሩ ማስቻል አለባቸው ማለት ነው ከዛ ባሻገር ደግሞ ምንን ማምጣት መቻል አለብን ሕገመንግስታዊ ስርዓቱ የሚለው ግለሰቦችን ማለት ማድረግ ያለባቸው ፌደራል ስርዓቱን የሚጠብሱ ያሁኑም አይነቱም ... ማስቻል አለባቸው ኃይማኖታቸው መሃል የኢታሪሊጂየስ ኢኩዋሊቲ እንዲኖረው ያስፈልጋል ማለት ነው የሴኩራል እስቴት መሰረታዊ የሆነ ስራዎች መሆን አለባቸው ማለተ ነው በዋናነት ይሄ ነው እነዚህን ነገሮች ደግሞ ለማራመድ እና የፌደራል ስርዓቱን ለማጠናከር ማለት ነው ምን ያስፈልጋል እስቴቱ ሴፐሬትድ መሆን አለበት ... ከሆነ እሪሊጅን እና ከሪሊጅን የኃይማኖታዊ ከሆኑ ኢንስቲቲውሽኖች ሙሉ በሙሉ ... አለበት ነፃ መሆን መቻል አለበት ማለት ነው አንድ በሕገ መንግስት 2ኛ ሕገመንግስቱን በሚያስተገብሩ ግለሰቦች ሁሉ ይሄ መገኘት መቻል አለበት የመንግስት ተወካይ የሆነ በፌደራል ደረጃ ፖለቲካዊ አስተሳሰቡን ለማራመድ ሲል እንኳን አንድ ግለሰብ ስለሚያምንበት ውስጥ ጣልቃ ከገባ ፌደራል ስርዓቱን የሚጠብቅ ግለሰብ ብሎ ለማለት ያስቸግራል ማለት ነው እና ያንን የሚያስቡ ደግሞ ሰወች ከተፈጠሩ ያንን ግለሰብ ከስልጣን ማውረድ አስፈላጊ ነው ብለው የሚያስቡ ሰወች ከተፈጠሩ የስልጣን ጥያቄውንም ... ውስጥ ይከቱታል ማለት ነው ፌደራሊዝም ያለዲሞክራሲ ሊኖር ይሄ ግልጽ ነው በዋናነት የሚታሰብ ነገር አይደለም በተለይ ደግሞ ማለት ነው ሆዳን የሚባል ፌደራሊዝም ከሆነ ይሄ ነገር የሚታሰብ አይደለም ያለዲሞክራሲ.

- ይታሰባል ይኖራል ብሎ የሚያስበው ነው?
- አርጉዩ ለማድረግ አይቻልም ማለት እንደዛ ብለን ለማለት መጀመሪያ ... አሸነፍክ እንደማለት ነው ሰወች አደለም ያንን አስተሳሰብ ...

http://ethcriminalawnetwork.com/

ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ከሌለ እንዴት የተለየዩ ሰወችን አንድ ቤተ ውስጥ ማስተዳደር ትችላለህ አንዱ ለመሳሌ ዲሞክራሲን በአጭሩ ስንገልፀው ማለት ነው ዲሞክ... መብት ነው ብለህ ካሰብክ ሕዝብ የሚመሰርተው ስርዓት ነው ብለህ ካሰብክ ... ሊንከን ያለውን ማየት ትችላለህ ዲሞክራሲ ኢዝ ሩል ኦፍ ዘ ፒፐል ነው ያ ሩል ... የሚመጣው ፍሮም ዘ ፒዩፐል ቱ ዘ ፒፐል ማለት ነው እና ባይ ዘ ፒፐል ማለት ... ሕዝቡ ከሕዝቡ ነው የሚመጣው ለራሱ ነው ሕግ እንደገና የሚተገበረውም ... በሕዝቡ ነው እንዴት አድርገህ እራሳቸውን የማያስተዳድሩ ሰወችን ሕዝቡን እራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ እያደረግክ እንዴት አንድ ላይ እንዲሆኑ ማረግ ትችላለህ

- አልተቻለም ወይ አሁን ለምሳሌ ለመንግስት ያላችሁ ስልጣን ባይታወቅ ለምሳሌ በፌደራል ስርዓት ላይ የሸዋ ገገር አለ የጐንደር ገገር አለ የበጌ ምድር ገገር አለ እነዛ /ግልጽ ያልሆነ/ ሰብስበው ለማእከላዊ መንግስቱ ይሰጡ ነበረ እነዛ አካባቢ ያሉት ሰወች የአንድ አንትናን ናቸው ተሰብስበው ኖረዋል በአንድ ኮሚቴ ውስጥ በኤርያ ማለት ነው የጅማው እንደዚሁ ኖረዋል ያ አልኖረም ወይ
- ያ ማለት አሁን ያለውን ሁኔታ ይገልፃል ብለህ ለማነሳት አስቸጋሪ ነው እንደገና ... ስርዓት የሰለሞናዊ ስርዓቱን ስትመለከት ማለት ነው አረጅም መቶ አመታት ነው የፌዴራል አረጅም መቶ አመታት ስርዓት ውስጥ አንድን እስትራክቸር ለመስራት አረጅም ... እንደሚወስድ ማለት ነው የኢትዮጵያም ኬዝ በዛ አይነት ሁኔታ የተገነባው እና ሆነ ተብሎ ከማስተዳደር ስልጣን የተገለሉ ሰወች እንዴት አድርገው እራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር እና ከሌላ የሚመጣባቸውን ጭቆና መከላከል ይችላሉ ብለህ ታስባለህ በጦርነት ወይ ይሸነፋሉ በጦርነት ሲሸነፉ ግዴታ ምንድን ነው የሚሆኑት ገባሪ ነው የሚሆኑት ላሸነፋቸው አካል ማለት ነው እንጂ ተስማምተው ኀብረት እየሰበሰቡ ከራሳቸው ለሌላ የሚሰጡ አሉ ብለህ ለማሰብ ይከብዳል
- አሁን በዚህ ስርዓት ውስጥ ፌደራሊዝም መክኗል ይላል ፌደራሊዝም የአሁኑ ስርዓት መክኗል ይላል ያ ምንድን ነው በብሔር የተመሰረተ ፌደራሊዝም በመሆኑ ኢትዮጵያን አንድ አርጐ ለመያዝ አልቻልም ስለዚህ በክልልመሆን አለበት ያላሉ እንዴት ነው ያዛ
- ፌደራሊዝም ስርዓት አድቫንቴጅም ዲስ አድቫንቴጅም አለው አሁን የጠቀስከልኝ ሁለት አይነት ነገሮችን ነው ጆግራፊክ ቤዝድ ፌደራሊዝም እና በዘር ላይ የተመሰረተ መነሻውን የኢትዮጵያን ኬዝ ስትመለከት መነሻውን ነው ማየት ያለብህ ኢትዮጵያ ውስጥ ጭቆና ይደርስ የነበረው ምንን መሰረት አድርጐ ነው ነው ማየት ያለብህ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኃይማኖት እና ብሄር ላይ ነው ኃይማኖት እና ብሔር ላይ [illegible] ስልጣን ለመስጠት እንዴት አድርገህ ማደራጀት እንዳለብህ ስታስብ [illegible] ምንድን ነው በቋንቋ ይበደል የነበረን ሰው ቋንቋውን መብት ማስጠበቅ እና [illegible] እንዲያስተዳድር ማድረግ በኃይማኖት ይጨቆን የነበረን ሰው ከዘር ጋር [illegible] ማለት [illegible] እንደዛ ይጨቆን የነበረን ሰው መብቱን ትሰጠውና /ግልጽ ያልሆነ ማስረጽ [illegible] ማለት ነው የራሱ እንትን አለው ውጋት አለው ሰወች ዘራቸው ላይ [illegible] ቁጥር ሃገር የሚባልን ነገር ሊረሱት ይችላሉ ነሰሰርሊ ግን አስፈላጊው ነገር [illegible] አስተሳሰቤን ሰወች እራሳቸውን ማስተዳደር እስከፈለጉ እና እስከቻሉ ድረስ [illegible] መተዳደር ያለባቸው ለምን ሁሉም ሰው ነፃነቱን አግኝቶ አንድ [illegible] ነፃነቱን አግኝቶ ቢኖር ምንድን ነው ችግሩ የነበሩ እንትኖችን ተመልከት [illegible] ፌደራሊዝም ማየት ትችላለህ በጣም ግዙፍ በጣም አሁንም እራሱ በጣም [illegible] የምትባለው ሃገር እራሻ የራሻ ፌደሬሽን ያኔ ሰውቤት ሕብረት በምትባልበት ወቅት [illegible] ማለት ነው የነበረውን በጣም ብዙ ግዛት ነው የምታስተዳድረው ግን በኃይማኖት [illegible] ይደርስባቸዋል በዘራቸው ጭቆና ይደርስባቸዋል ልክ የኮልድ ዋር ሲጠናቀቅ ቀዝቃዛው ጦርነት ሲጠናቀቅ እራሳቸውን ነፃየማውጣት ስራ ውስጥ ነው የገቡት ማለት ነው [illegible] ፌደራሊዝም ስርዓት የአንድን ሕዝብ ነፃነት ለማስጠበቅ እንትን አይደለም
- ወሳኝ አይደለም ማለት ነው
- አዎ እና ሕዝቡ ነው መሰረት
- እንደዚሁ ማለት ትችላለህ አሁን ሕዝቡ ነው ነፃነቱን ማግኘት ያለበት ማለት ነው እና [illegible] ነው እራሻ ልትፈረካከስ የቻለችበት ዋንኛው ምክንያት በወቅቱ በፌደራል ስርዓት [illegible] የኃይማኖት እና የዘር መብት የተጠበቀ አልነበረም ማለት ነው ከዛ በኋላ ደግሞ ማለት ነው የኮሚኒዝም ስርዓት በሶቤት ሕብረት ውስጥ ከፈረሰ በኋላ እንደገና [illegible] የኮሚኒዝምን አስተሳሰብ ቃራምድ የነበረች ዩጉዝላቢያንም መመልከት ትችላለህ ሕዝቦች የነበራቸውን ነፃነት በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላቸው የተነሳ ነው ሊፈረካከሱ የቻሉት እነዚህ ሁለት አገራቶች የሚል ሁኔታ እንደዚሁ ማየት ትችላለህ ማለት ነው
- ከብሔር እና ከጉራጌ ሕዝብ የመገንጠሉ ሁኔታ ከፌደራሊዝሙ አኳያ እንዴት ታየዋለህ ለምሳሌ አንድ ሕዝብ ተደርገው ነበረ የሚታሰቡት የፌደራል ሲስተሙ [illegible] ብሔረሰብ ጉራጌ አይደለም የሚል ተደረገ የራሱ ከተማ [illegible] የራሱ ከተማ [illegible] እንዴት ነው

3163 2009

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በቋንቋ አንድ አይነት አይደለንም ካለ
- አሁን በቋንቋ ነው እነሱ የተገነጠሉት ማለት ነው
- ቋንቋቸው ይለያል የስልጤ ሕዝብን ስትመለከት ደግሞ በኃይማኖቱ ሙስ በሙስ እስልምና ነው የሚከተለው ስለዚህ እራሱን የማስተዳደር መብት የተሻለ እድገት ያመጣል ብሎ ካሰበ የመገንጠሉን ጥያቄ ያነሳል ብዙ የመገንጠል ጥያቄ ያላቸው
- የብሔር መነሻዎችን አይተን ነበረ የፌደራሊዝም ለመመስረት መነሻዎች አይተን ነበር ዘዐ በፌደራሊዝም መመስረት ላይ የሃይማኖት ሚና ምንድን ነው
- ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ነው ብለህ ለመናገር በእርግጥ የሚመች እንትን አይደለም ያለ አንድ እንትን ማየት ትችላለህ ለምሳሌ ሳንሳልህ እና የስዊዘርላንድን ቢዝ እንወስድ ሲውዘርላንድ ውስጥ ይሄ ሲቪል ኢንዲቪጁዋል እና ኮሌክቲቭ ራይት ከምንድን ነው ይሄንን እምነት የምናነሳው አንድ እምነትን በብዛት እንደውም ሙቶ ፐርሰንት የሚከተል ቦታዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ማግኘት ትችላለህ እንደ ሶማሌ እንደ አፋር ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ አይነት ኃይማኖልት ያላቸውን ሌሎች ክልሎች ማየት አትችልም ኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትያኖች ቁጥራቸው ብዙ ነው ሙስሊሞች ግን አማራ ክልል ቁጥራቸው ሲበዛ ይገኛል ግን ሙስሊሞች በጣም ከፍተኛውን ቁጥር ይሸፍናሉ ሌሎቹንም ግዛቶች ባታዎች እንደዚህ ስትመለከት ማለት ነው ከኢንዲቪጁዋል ሊበርቲ የሚባለውን ነገር ስትመለከት ሕገመንግስቱ ማለት የፌደራል ስርዓቱን ለመገንባት በሚነሳበት ጊዜ የግለሰቦችና የቡድን መብትን በቃል ወይም በሌላ መንገድ እንትን ያደርጋል ይበልጥ ለሕዝቦች መብት ከፍተኛ ግምት ቢሰጥም ማለት ነው አንቀጽ 39 ስትመለከት የኢትዮጵያ ሕገመንግስት ውስጥ ማለት ነው እንደገና በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ እንትንን ማየት ትችላለህ የአፍሪካ እስላማዊ አብቶች ድንጋጌ እዛም ውስጥ ስትመለከት አንድ አይነት ነገር ማየት ትችላለህ ሕዝቦች እራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ይሰጣል ሁለቱንም ድንጋጌ ማለት ነው ይሄኛውን ሕገመንግስት ያኛው ድንጋጌ የኢትዮጵያውን ሕገመንግስት ግን ልዩ የሚያደርገው እስከ መ ገንጠል ነው የሚፈቀደው ማለት ነው በእርግጥ ይቻላል አይቻልም እሱ ሌላ ጥያቄ እንዳለ ቢሆንም ማለት ነው ልክ እንደ ኢትዮጵያ ስዊዘርላንድም በምሳሌነት ሲነሳ ስዊዘርላንድ መልቲ ካልቸራል እስቴት ናት መልቲ ካልቸራል እስቴት ማለት ሲባል በኃይማኖት እና በዘራቸው የሚለያዩ ሕዝቦች ናቸው በዋናነት በእንትኖች ጀርመኖች አለ ጀርመን በምታዋስነው ቦታ ላይ ጀርመኖች ነው የሚኖሩት ስዊዘርላንድ ውስጥ ጀርመን ዝርያዎች ማለት ነው እንደገና ጣልያኖችንም እንደዛው ማግኘት ይቻላል ማለት

3/64 7010

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በምታዋስንበት ቦታ ላይ ማለት ነው እንደገና እንትኖችንም ማየት [illegible] ማለት ነው ሃስቱም ቋንቋዎች የተለያዩ ናቸው [illegible] ኃይማኖታቸው እራሱ የሚለያዩበትን ሁኔታ ማየት ትችላለህ ማለት ነው ፈረንሳዮች ካቶሊኮች ናቸው ካቶሊክን ነው የሚከተሉት በብዛት እንደገና ደግሞ ጣሊያኖችን [illegible] እንደዛው ካቶሊክ እሮማን ካቶሊክ ናቸው ጀርመኖችን ስታይ ጀርመን በደቡብ ልና በሰሜን በኩል ጀርመን እራሷ ትለያያለች ፌደራላዊ ስርዓት ሆና የጀመርመን ፌደራላዊ ስርዓት ኃይማኖታዊ ነው ብለህ ለማንሳት ባትችልም በዋናነት ግን ሰሜናዊው እና ደቡባዊው ጀርመን በካቶሊኮች እና በፕሮቴስታንቶች የተሸፈነ ነው ማለት ነው በትደም [illegible] አደለም ያስቀመጥኩት ማለት ነው እና እንደ ስዊዘርላንድ ኢትዮጵያም በጣም ከፍተኛ የሆነ ፖተንሺያል አላት የምን ፖተንሺያል ኮንፍሊክት ሊፈጠርባት ስለሚችል ማለት ነው ምክንያቱም የኃይማኖት እና የዘር ጥያቄ ሙሉ በሙሉ መንግስት እጅን ነፃ እያደረገውም ሕዝባች እራሳቸውን በራሳቸው መንገድ ማስተዳደር እስካልቻሉ ድረስ በእምነታቸው በአስተሳሰባቸው እስካልቻሉ ድረስ ከፍተኛ የሆነ /ግልጽ ያልሆነ ግጭት [illegible] የሚችልበት ሁኔታ አለ ማለት ነው ለምን ኃይማኖት የአንድ ሕዝብ መገለጫ ስለሆነ የኃይማኖቱ መገለጫ የሌላ ኃይማኖት መገለጫ አካላቶች መንግስት እንዲህ በሚወግንበት ጊዜ እየተሸፈበት እየተፈዘበት እያለ የሚያስብ ሕዝብ መፈጠሩ አይቀርም 2ኛ ዜጋ እንደሆነ ማሰብ የሚጀምር ሕዝብ መፈጠሩ አይቀርም ስለዚህ ይሄ ሆነ ማለት ደግሞ ሰላም ይደፈርሳል ማለት ነው የፌደራል ስርዓቱ ደግሞ እንዲጠፋ ሊያደርጉ ከሚችሉ ነገሮች አንፀር በዋናነት የሚጠቀሰው ምንድን ነው የተለያዩ ግዛቶችን አንድ አይነት ባልሆነ መንገድ ቱዊት የማድረስ ሁኔታ ማለት ነው ይሄ የረጅም ጊዜ ታሪካቸውን ስትመለከት በዚህ አይነት መንገድ ልታረጋግጥ ትችላለህ ማለት ነው እና ሊያፈርሰው ይችላል የሚል ሃሳብ አለ

- እንደው በዚህ በፌደራሊዝም ሲስተም ውስጥ ፌደራላዊ መንግስቱ ምን ማድረግ አለበት ሁሉም በፌደራል የየራሳቸው ክልላዊ ስልጣን አላቸው እንዴት ነው አሁን ትሪት ማድረግ ያለበት
- ይኸው እነዚህ ነፃነቶች ምኖች ምናኛ ስማረጋገጥ መንግስት የፌደራል ኮንስቲትዩሽን ይኖረዋል የኢትዮጵያ መንግስት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርዓት [illegible] ኮንስቲትዩሽን ክልሎች የራሳቸው አላቸው ይሄ ምንን መስርቷል ፖለቲካዊ ኢንስቲትዩሽኖች እና ፕሮሲጀሮችን መስርቷል ያንን ማጠናር ነው የሚያስፈልገው [illegible] በጣም አያዘናክር

3/68 [illegible]

http://ethcriminalawnetwork.com/

በሄድክ ቁጥር ክልሎች እራሳቸው የሚያስተዳድሩበትን በዘር ደረጃ ገጽታዎች ብዙ
መልኩ ጣልቃ የማትገባባቸው ከሆነ እራሳቸውን በጣም የሚጠናከር እድሉን ከፌደራሉ
በነፃነት እንዲኖሩ ታደርጋቸዋለህ ያ የተሻለ ነገር ሊፈጥር ይችላል ለኢትዮጵያ
የሕገመንግስት ስርዓት ማለት ነው ሌላው የዲሞክራሲ ስርዓትን በጣም ማስፋት
ዲሞክራሲ ስርዓት በጣም እየሰፋ በሄደ ቁጥር ሕዝቡ እራሱን የሚያስተዳድር
ለራሱ እያደረገ በሄደ ቁጥር ይሄ ሶቨርኒቲ ሉአላዊነት በሕዝብ ላይ እንዲመሰረት እያደረግክ
በሄድክቁጥር የተሻለ ነገር ትፈጥራለህ ማለት ነው ያ ደግሞ ዲፔንዳንሲ ስላለ አንዱ
ያለውን ሌላው ስለሌለው ያንን በመጋራት ስርዓት ውስጥ የተሻለ እንዲጠናከር ካደረግ
ክልል ከክልል ጋር የተጠናከረ ኢንተር ገቨርንመንታል እረሌሽን እንዲመሰርት ካደረግከው
የተሻለ እድገት ላይ ይደርሳሉ የሚል ሃሳብ ስለሚፈጠር እንኳን በኢትዮጵያ ቤዝ እያደረግ
በአለምአቀፍ ደረጃ እራሳችንን እንችላለን ብለው ከማንም እርዳታ ሳይፈልጉ ንብረታቸውን
ለማንም ሳይሸጡ የሚኖሩ አገራቶች የሉም ያ ትስስሩ ኢንተር ዲፔንደንስ ኢትዮጵያ
ውስጥ እንዲመጣ ማድረግ ካስቻልክ የተሻለ ነገር ይፈጥራል ከዛ ባሻገር ደግሞ ሁሉም ሰው
ሕዝቡ ሁሉም ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ፌደራል ስርዓትን የመሰረተ ሁሉም ሕዝብ የራሱ
እምነት የራሱ ታሪክ የራሱ ቋንቋ እና የራሱ ባህል አለው ያንን ባህል እንዲያከብር
ማድረግ ማስቻል ያንን እያደረግክ በሄድክ ቁጥር የመተማመን ስራ እንዲኖር ማድረግ
በኃይማኖቶች መካከል ተሪሊጂያስ ዲያሎጎች ፎር ፒስ ማለት ነው በጣም ለሰላም
እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል ማለት ነው ያ የበለጠ ኢትዮጵያ የፌደራሊዝም ስርዓት
በኢትዮጵያ ውስጥ /ግልጽ ያልሆነ/ እንዲጠናከር ያደርጋል ማለት ነው

- እንደው እንደ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሙስሊም በፌደራል ሲስተም ተጠቅሟል ወይስ አልተቀመም ብለን መመዘን እንችላለን?
- በብዛት ዶሚኔት ያረገባቸው አካባቢዎች እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ማድረግ ተችሏል የተሻለ ነገር ፈጥሮላቸዋል የሚል ሃሳብ አለኝ ከዛ ባሻገር ግን ጉዳቱ የፈጠረባቸው ቦታዎች ይኖራሉ ሙስሊሞች ቁጥራቸው አናሳ የሚሆንባቸው አካባቢዎች ላይ በማስብ ደረጃ እንደ ቡድን መብት እየታየ ብቻ ሙስሊሞች በመንግስት መስሪያቤት ውስጥ በ ትምህርት ቤት ውስጥ በየተለያየ ቦታ ላይ የሚደርስባቸው ጭቆናን አስቀርቷል ወይ ብለን መጠየቅ ግን ያስፈልጋል ፌደራሊዝም ስርዓት ስለተፈጠ ብቻ ... የፌደራሉን መብት በራሳቸው ያስተዳድራሉ የሚል ሕግ ስለተፃፈ ብቻ ሕብረተሰቡ መብቱን አግኝቷል ወይ ብለን መጠየቅ አለብን ያ ነገር ስላለ ግዴታ ነፃነት ተሰጥቶታል ...

3166

7012

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሁኔታ አይደለም ከዛ ባሻገር ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የፌደራሊዝም [illegible]

የተነሳ -ያጣቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ አንድነቱን አጥቷል እንድነቱን የሚያጣበት [illegible]

ምንድን ነው ሰው ከኃይማኖቱ ይልቅ ዘሩ ላይ እንዲያተኩር በጣም ከፍተኛ ሁኔታም [illegible]

ከፍቷል ያ ማድረጉ ደግሞ ሙስሊሙ ለሙስሊሙ ወገን አደጋ እንደሆነ እንዲያስብ

እየተደረገ ያለበት ሁኔታ አለ ማለት ነው ሴራዎች ይሴራሉ ስለዚህ ሙስሊሙ አንድነቱን

ለማጠናከር እያንዳንዱ ግለሰብ እራሱ ላይ ኃላፊነት መጣል አለበት የጋራ የሆነ መግባቢያ

ቋንቋውን ማዳበሩ እስልምና የሚነቅፈው ነገር አይደለም መሰረቱ እራሱ ሰው በቋንቋ

እንዲያወራ ማድረግን መሰረቱ እራሱ እስልምና ነው አላህ በተለያየ መንገድ ነው የፈጠረ

ሰውን ዘሩን ቋንቋውን ምኑም የለየው ማለት ነው ከዛ አንፃር እንደዛ ማረግ ትችላለህ ግን

አንድነቱን ለማጠናከር ምን ማድረግ ይችላል ነው አትሊስት አብዛኛው ሕብረሰብ ቁርአን

ይቀራል ስለዚህ መግባቢያ ይሄው ነው ሱማልኛ የሚያወራው ሱማልኛውን እያወራ አፋርኛ

የሚያወራው አፋርኛውን አማርኛ የሚያወራ አማርኛውን ጉራግኛ የሚያወራ ጉራግኛውን

ኦሮምኛ ሁሉንም ቋንቋዎችን ጥቀስ ኢትዮጵያ ውስጥ በራሳቸው ቋንቋ እየተናገሩ ሙስሊም

ወንድሞቹ ጋር ሊያስተሳስር የሚችል ግን ነገር ማድረግ ይችላሉ አረብኛ ቋንቋ መግባቢያ

አረብኛ የጋራ ቋንቋቸው እንዲሆን መስራት አለባቸው አረብኛ ቋንቋን ለመማር

መብታቸው ነው ሙስሊም እስከሆኑ ድረስ ግን እስልምና የጋራ የሆነ አስተሳሰብ አንድ

አንድ አይነት አመለካከትን ማስፈን ያስፈልጋል የሚል ሃሳብ አለኝ

- አንዳንድ ሰዎች ከሃገር እና ከኃይማኖት የሚል ደረቅ የሆነ እንትን ያነሳሉ አንተ የቱን ታየዋለህ እስቲ ይሄንን አንተ ?
- ሁለቱንም ማስኬድ የሚቻልበት ሁኔታ አለ ይሄ እንትን በእርግጥ በጣም አከራካሪ የሆኑ ነገሮች አሉት በሙስሊም ምሁራን ብቻ ሳይሆን አለም አቀፍ በሆነ ማለት ሙስሊም ባልሆኑ እስኮላሮች መሃል የናሽናሊዝም አጥኚዎችን የብሄርተኝነት ትምህርት የሚያጠኑ ሰወችን ስትመለከታቸው የራሳቸው የሆነ አመለካከት አላቸው የአገር ፍቅር የሚባል ነገር እንዳለ ሆኖ እምናምታታቸው ነገሮች አሉ ይሄ የፓትሪዮቲዝም የሚባል ነገር የአገር ፍቅር ምናምን የሚባል ነገር ናሽናሊዝም የሚባለው ደግሞ ብሔርተኝነት የሚባለው ጉዳይ ማለት ነው ለሁለት ከፍሎ ማየት ያስፈልጋል ይሄ ናሽናሊዝም የሚባለው ነገር ምንድን ነው ያለ ብሔርተኝነት የሚባለው ጉዳይ ዘርህን ብቻ መመልከት ነው በአንተ ዘር ውስጥ ያሉ አካላቶች በሙሉ ጠላትህ እንደሆኑ አድርገህ ማሰብም [illegible] ነው የሚያደርገው መጨረሻ ላይ የሚያመጣው አስተሳሰብ [illegible] ነው ለምን አንተም ተከራ[illegible]

3/67 ፵ 2013

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የምትሰጠው ለዘርህ ነው እኔ የዚህ ብሔር ቡድን አባል ነኝ ብለህ ነው ... የሚያደርገው ፓትሪዮቲዝም የሚባለው ነገር ግን የሃገር ፍቅር ምናምን የሚባለው ... ሰዎች አታች የሚያደርጉት ከዘር ጋር ሳይሆን ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር ነው ከሚኖሩበት ቦታ ጋር ነው ሙስሊሞች ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራሉ ስለዚህ ኢትዮጵያን ሲወዷት ይታያል ሙስሊሞች ግን እስልምናው እንዳለ ሆኖ ስለኢትዮጵያም ሳይጨነቁ ይችላሉ ስለዘራቸው ብቻ የሚያስቡ ግለሰቦች አሉ አግኝተዋል ሃሳቡን እና ስለዚህ በአገር ፍቅር ይሄ የአገር ፍቅር የሚባል ነገር አገርን መውደድ የሚባል ነገር ይሄ አርበኝነት ብለው የሚያስቡት ፓትሪዮቲዝም ማለት ነው እሱ እና የብሔርተኝነት ጉዳይ ደግሞ የዘለለ አይነት ... ማለት ነው ለምሳሌ የናዚ ጀርመንን አስተሳሰብ መውሰድ ትችላለህ የናዚ ፓርቲ የጀርመን ብቻ ናቸው ምርጥ ዘሮች ብሎ ባሰበ ቁጥር አይሁዶች እዛ ጀርመን ውስጥ የነበሩ ... ዘር ይበክላሉ ዘር የሚያጠፉ ናቸው ብሎ ሲያስብ ጨፍጭፏቸዋል ይሄ በጣም ከድምበር የዘለለ ጉዳይ ነው ማለት ነው እና እስልምናን የራሱ መልስ ብቻ ነው ስለዚህ እንትና ሰላህ ሰለምን ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ ከመካ ሲወጡ ተመልክተዋታል መካን እና መካ ዞር ብለው ተመልክተው እንደው አንቺ ከተማ ውስጥ አንቺ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ባያስወጡኝ ኖሮ ከአንቺ የበለጠ ምን ምርጥ አገር ነበር አንቺጋ ነበር የምኖረው ብለው ነው የተናገሩት እና ለአገራቸው የነበራቸው ለመኖሪያ ቤታቸው የነበራቸው ፍቅር በጣም ከፍተኛ ነበር እንደዛ ነበር ያደረጉት ማለት ነው

- አንፃራዊ ሁለቱም
- እስልምና ውስጥ ሁለቱንም ታገኛለህ የመጨረሻ የመሰናበቻ ንግግር ላይ እራሱ ሰላወሰለም ሲናገሩ ያኔ ሲናገሩ የነበረውን ኬዝ ስተመለከት ጥቁሩ ከአረብ አረቡ ደግሞ አረብ ካልሆነው አይለይም በለው የተናገሩበት ሁኔታ አለ በአንድ ወቅት ላይ ስትመለከት ቢላል ... እሱም እዛች የጥቁር ሴት ልጅ ብሎ ሲናገር ምንንም አይቶ አይደለም የራሱ ከለሩን ጥቁር በመሆኑ ያን አይቶ ሲናገረው ወደ እራሱል ነው ይዙት የሄደው ቢላል ያንን ጉዳይ ... የጀህንና ዘመን ቅሪት ልቡ ውስጥ አለች አልጠፋችም ማለት ነው ብለው ነው የተናገሩት በኋላ ኢማን ይበልጣል እስልምና ይበልጣል ብሎ ስላሰበ ያ ሰሃባ ምንድን ነው ያደረገው የቢላልን ፊት ጥቁረቱን አይቶ ነው የተናገረው ፊቱን አይቶ ነው የተናገረው እሱ ፊቱን ነው መሬት ላይ ያስተኛው አፈር ላይ አድርጎ ይሄንን ፊት እርገጠው ብሎ ነው ቢላልን የጠየቀው ቢላል ያንን አላደረገም በእርግጥ እና ሰዎች አይደሉም [illegible] ነገሮች ኤትኒሲቲ ይሄ እሪሊጅን ምናምን የሚባሉ ነገሮች እና ሰዎች [illegible]

3168

7014

http://ethcriminalawnetwork.com/

ወይ በሌላ መንገድ ሙስሊሙ ግን የበለዘ ማትከር [illegible]

ነው

- አበቃን አዘጋጆቹ ያቀረብኩላቸው የሱፍ ጌታቸው ነኝ ወሰላማሊኩም ወራማቱላሂ ወበረካቱ
- ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል

ትእዛዝ

- በዛሬው እለት ከቀረቡት ሁለት ሲዲዎች ውስጥ ተመርጠው ከተሰሙት ትራኮች በድምፅ መቅረጽ የተቀዳው ንግግር ወደ ጽሁፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተብሏል የችሎቱ ፕሮግራም ለመቀጠል በአዳሪ ለ21/12/2005 ዓ.ም ስምንት ሰዓት ላይ ቀጠሮ ተይዟል

3/69

2015

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የመ.ወ.ቁ 124754

ቀን 22/12/05 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብስራት ተዕልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ፡-የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ቴዎድሮስ ጌታቸው እና ዘረሰናይ ምስግና ቀርበናል

ተከሣሾች፡-አቡበከር አህመድ የቀረ ሁሉም ቀርበዋል

ጠበቆች ከ 1ኛ እስከ 27ኛ ላሉ ተከሣሾች ባህሩ መካንጋ፣ ምላልኝ መለሰ ሀሰን ሁሴን እና መሐመድ አብደላ ቀርበናል

- ትላንት ከቆመበት ይቀጥል ሙብራት ተቋርጦ መሀል የቆመ አለ ትላንት ከቆመበት ይቀጥል
- /ግልፅ ያልሆነ/ አዲስ የመጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ አባላትን ለማስመረጥ ቅድመ ዝግጅት አድርጎ ስራውን ጀመረ ከ 500 ያላነሱ አባላት ያሉት ጠቅላላ ጉባኤ የመጀመሪያ ጉባኤውን በአዲስ አበባ ከተማ ማካሄድ ቻለ በእዚህ በአዲሱ ጠቅላይ ጉባኤ አመራር ምርጫ ላይ ሼህ አህመድ ሰይድ ፕሬዘዳንት ተደርገው ሲመረጡ ሀጂ መሐመድ አወል ረጃ ደግሞ 2ኛ ምክትል ሊቀመንበር እና የኢኮኖሚ ዘርፍ ኃላፊ ሆነው ተሾመዋል ከእነዚህ በተጨማሪም ለመጅሊስ የተለያዩ የዘርፍ ኃላፊነት ቦታዎች የተለያዩ ሰዎች ተመርጠው ተቋሙን ተቀላቅለዋል በብዙ ወገኖች እንደሚታመነው አዲሶቹን አመራሮች በማስመረጥ ረገድ የመንግስት ሚና ቀላል እንዳልነበረ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ቢሮ የተሰማው ዜና ግን አስደንጋጭ ሆነ መጅሊሱ ከእኔ ውጪ ሆነ ሌሎች እስላማዊ ማህበራት እና ኤንጂዎች እኔ የም[illegible] የሚሰሩ በመሆኑ መኖራቸው ትርጉም የለውም በሚል እሳቤ እስላማዊ ማህበራት ሁሉ መፍረስ አለባቸው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚል ውሣኔ ያሳለፈ መጅሊሱ በእዚህ ውሣኔው በርካታ አመርቂ ተግባራት ቢያከናውኑ የነበሩ እስላማዊ ድርጅቶችን /ግልፅ ያልሆነ/ በኢትዮጵያ አሎማዎች ማህበር እና /ግልፅ ያልሆነ/ የመሳሰሉ ድርጅቶች በጋራ በመሆን መጅሊሱ ማህበራቱን ለማፍረስ ካሰበው ድርጊቱ እንዲታቀብ ጥረት እና ቅስቀሳ ማድረግ ጀመሩ እነዚህ ድርጅቶች የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ጉዳዩን ለሕዝብ ውይይት አቀረቡት በመቀጠልም ከ 300 ሺህ በላይ የሚሆን የአዲስ አበባ ሙስሊምን በማስተባበር በሕዳር 1987 የሙጅሊሱን አመራር የሚቃወም ሰልፍ አካሂደዋል እነዚህ ሰልፈኞች በወቅቱ የሽግግር መንግስት ፕሬዘዳንት አቶ መለስ ዜናዊ ጋር የተገናኙ ሲሆን ፕሬዘዳንቱ በምላሻቸውም ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የፈለገውን የመጅሊስ አመራር የመሾምም ሆነ የመሻር መብት እንዳለው በመግለፅ ሰልፈኛውን ሕዝበ ሙስሊም ወደ ቤቱ አሰናብተዋል ሰልፈኞቹን ያደራጁት ማህበራትም በጋራ በመሆን ፕሬዘዳንቱ ባገኙት መልስ ተነሳስተው የመጅሊሱን አመራር ከስልጣን ለማውረድ እና በአዲስ ለመተካት እንቅስቃሴ ጀመሩ ማህበራቱ ቅንጅት በመፍጠር ወደ ሸሪያ ፍ/ቤት በመሄድ ክስ በመጅሊሱ አመራር ላይ መስርተው የመጅሊስ አመራሩ በሸሪያ ፍ/ቤት ውሣኔ ከስልጣኑ እንዲለቅ ተወሰነ ሆኖም ስልጣን ላይ ያለው የመጅሊስ አመራር የሸሪያ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አልቀበልም በማለት ወደ ዋናው ፍ/ቤት ሄደ ስልጣን ላይ ያለውን በአዲስ ለመተካት የሚንቀሳቀሰው የማህበራት ቅንጅትም የተለያዩ የመንግስት ቢሮዎች በመሄድ የመጅሊሱን አመራር ከስልጣን ለማውረድ በሚደረገው ጥረት መንግስት አጋዥ እና ተባባሪ እንዲሆን ቢጠይቅም የተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናት ግን የሚፈልጉትን አላማ ከዳር ለማድረስ ከስልጣን አልወርድም ያለውንም ሆነ የመጅሊሱን አመራር ከስልጣን ለማውረድ የሚንቀሳቀሰው ቡድን አይዞህ አይዞህ እያሉ በ/ግልፅ ያልሆነ/ ግርግር ያደፋፍሩ ነበር ሁኔታዎች ከቀን ወደ ቀን ከመሻሻል ይልቅ እየከፉ እና የ 2 ቡድን አባላትም እርስ በእርስ መቃቃር እየተባባሰ መጣ የመንግስት አካላትም የ 2ቱ ቡድኖች ግጭት ወደ መጨረሻው እንዲደርስ በርቱ በርቱ ማለታቸውን ቀጠሉ ባለስልጣናቱ 2ቱንም ወገን ሲያደፋፍሩበት የነበረው ዓላማ ፍፃሜ የካቲት 14/1987 በተከሰተው ግርግር በግልፅ መታየት ቻለ የካቲት 14 አንዋር መስኪድ ውስጥ የረመዳን ወር ሕዝቡ ሰላት ሰግዶ ከተጠናቀቀ በኋላ መንግስት 2ቱን ቡድኖች ለማጋጨት ባደረገው ድራማ ከፍተኛ ሁከት እና ግርግር ተፈጠረ የመንግስት ታጣቂዎችም በአፋጣኝ በአካባቢው በመድረስ ሕዝቡ ያለ የጥይት ቃታ ሳቡ ሰላማዊ እና የረመዳን ፆም ያደከመው ሕዝበ ሙስሊምም እራሱን ለማዳን ከአካባቢው መሸሸ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ጀመረ የወታደሮቹ ጥይት ግን ወደ ሕዝቡ ተወረወር በለነበር ሕዝቡን ማርገፍ ጀመረች ጨብጦ በረከተ የመንግስት ወታደሮች የሀጂን መካን ተማፅኖ እንዳልሰሙ ሆነው ከእነ ጫማቸው የመስኪዱን ምንጣም በመርገጥ ወደ ውስጥ ዘለቁ /ግልፅ ያልሆነ/ በየቦታው ረገፈ የመስገጃ ምንጣፎች በደንብ ጨቀዩ ቅዱሱ መስኪድ ጨኸት በረታበት አስከሬን ተጎተተበት /ግልፅ ያልሆነ/ በርካቶችም ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ ደረሰባቸው መንግስትም የፈጠረውን የግርግር ድራማ ተከትሎ በድል የሚሰሩ ግለሰቦችን ሁሉ በእዚያው ዕለት ምሽት ጀምሮ በገፍ ወደ ወህኒ አጋዘ /ግልፅ ያልሆነ/ መድረሳ የሚያስፋፉ ግለሰቦች ሙስሊሙን ስለሙብቱ የሚያስተምሩ እና የሕዝቡን ንቃተ ሕሊና ለማዳበር የሚጥሩ ሁሉ በግርግሩ ሰበብ ለመንግስት ኢላማ ሆኑ ድርጅቶች እና ተቋማትም ተዘጉ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ብዙ ዓመታትን ወደ ኋላ እንዲጓዝ ምክንያት ሆነ መንግስት በወቅቱ ያሰራቸውን ሰላማዊ ሰዎች ልክ እንደአሁኑ በሽብር ተግባር ተሰማርታችዋል ብሎ ቢወነጅላቸውም ከዓመታት እንግልት በኋላ ግን ምንም ወንጀል ሳይጠይቋቸው ከ 25 በላይ ሰዎች በነፃ ተለቀዋል ከእዚህ በኋላ ነበር መጅሊስ በመንግስት እጅእንዲገባ ተደርጎ አቅሙ የተልፈሰፈሰ እና ለሕዝብ የማይሰራ ሸክም የሆነው የመጅሊሱ አመራር አባላትም ምርጫ የማይታሰብ ሆነ መንግስት ከእዚያው ወቅት ጀምሮ ለመጅሊሱ ቁልፍ የአመራር ቦታዎች በደህንነት መስሪያ ቤቱ በኩል የሚመለመሉ ሰዎችን በጓሮ በር መሾም ጀመረ መጅሊሱም ያለ ስሙ ከእኔ በላይ ለአሳር እያለ በግልፅ /ግልፅ ያልሆነ/

- በእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት መስራች አባቶች ይሄንን ተቋም ሲያቋቁሙ ዋና ናቸው ያሏቸውን ዓላማዎች በፁሑፍ መተዳደሪያ ደንቡ ላይ ያሰፈሩ ሲሆን እኚሁ አላማዎቻቸው ዛሬም ዘመናትን ተሻግረው በ 1996 በተሻሻለው የመጅሊሱ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ሌሎች አዳዲስ ዓላማዎች ተጨማምረውባቸው ሰፍረዋል ዛሬ በጓሮ በር ገብተው በተቆጣጠሩት ጥቅም አሳዳጅ በአዳን ግፍ የወረቀት ነብር የሆነው ይኸው መተዳደሪያ ደንብ የተቋሙን አላማዎች እንደሚከተለው ይዘረዝራቸዋል 1 በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮችን በበላይነት መምራት 2 የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በተጎናፀፉ ሰብአዊ እና ዲሞክራሳዊ መብቶች በመጠቀም ተደራጅተው እምነታቸውን የሚያፀኑበትን እና የሚያስፋፉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት 3 የሙስሊሙን አንድነት እና ሕብረት ማጠናከር 4 ከሌሎች ኃይማኖት ተከታዮች ጋር በእኩልነት በመከባበር እና በሰላም አብሮ የመኖር መንፈስ የሚያዳብርበትን [illegible] ድርሻ ማበርከት 5 ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የራሱን የእምነት ተቋማት የሚያደራጅበት እና የሚያስፋፋበትን በበጎ አድራጎት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ስራዎት በተጨማሪ ሸሪያው በሚፈቅደው መሠረት በልማት ስራ ላይ የሚሳተፍበትን ሁኔታ መፍጠር 6 ከሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር እርዳታ በማሰባሰብ ለሙስሊሙ ጥቅም እንዲውል ማድረግ 7 በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም እርከን ተጠሪነታቸው በየደረጃው ለሚገኙ እስልምና ጉዳይ ምስክር ቤቶች የሆኑ የሸሪያ ፍ/ቤቶች እንዲቋቋሙ ተገቢውን ጥረት ማድረግ 8 በእስላማዊ ስራ ላይ የተሰማሩትን አካላት ለማደራጀት እንዲሁም ችሎታቸውን ለማሻሻል እና አቅማቸውን ለመገንባት ተገቢውን ጥረት ማድረግ 9 የሀጂ እና ኡምራ ስራዎች ኃይማኖታዊ ግዴታ በመሆናቸው መጅሊሱም ተጓዥ ምዕመናን ያለምንም ጣልቃ ገብነት ከቀበሌ እስከ ሀገራዊ አቀፍ የኃይማኖታዊ የማጣሪያ ፎርም በማዘጋጀት በብቸኝነት ማደራጀት እና መብት ማስፈፀም እና መቆጣጠር 10 ለሙስሊሞች መብት እና ጥቅሞች መከበር መታገል 11 እስላማዊ ዳዋን ወይም ትምህርትን ማስፋፋት መቆጣጠር 12 የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች እና ተቋሙን በተመለከተ ከአለማቀፍ ተቋሞች ወይም ድርጅቶች /ግልፅ ያልሆነ/ ማህበራት ከሕዝባዊ እና ከግል ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች ጋር ግንኙነት ማድረግ 13 እስላማዊ የእርዳታ ድርጅቶችን ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ በሚጠቅም መንገድ ማስተባበር መቆጣጠር 14 በሙስሊሙ መካከል የሚፈጠሩ የተሳሳቱ አመለካከቶች ስር ሳይሰዱ እንዲታረሙ ማድረግ 15 አለማውን ተግባራዊ ለማድረግ ፌዴራል መንግስት እና ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ጋር ግንኙነት ማድረግ 16 ለፌዴራል ጠቅላይ ምክር ቤቱ አጋዥ አካል የሆኑ እንደ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ከኦለማ ምክር ቤት ሙስሊም ሙሁራን ወጣቶች ሴቶች እና ሌሎች መንፈሳዊ ማህበራትን ማደራጀት መቆጣጠር ማገዝ 17 የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ልማት ኤጀንሲ የሀገሪቱ ሙስሊም ሕብረተሰብ ያለበትን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ማደራጀት ማገዝ መቆጣጠር 18 ሌሎች ከአላማዎቹ ጋር አግባብነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን ከላይ የተጠቀሱትን መልካም አላማዎች ሰንቆ በአስቸጋሪ ስራ የተነሳ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ግን ከእነዚህ ዓላማዎች ውስጥ ጥቂቱን እንኳን ለማሳካት አልቻለም ምንም እንኳን በእዚህ ክስረቱ በርካታ ችግሮች እንደመንስኤነት መጠቀስ ቢችሉም ዋነኛው የተቋሙ ችግር ግን ገና ሲቋቋም ጀምሮ መዋቅራዊ ሕልውናው ደካማ መሆን ነበር በአፄ ኃይለስላሴ የበላይ ጠባቂነት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ሕልውናውን ያገኘው በአዋጅ ወይም በቻርተር ሆኖ ሳለ መጅሊሱ ግን ይሄንን ማዕረግ በጭራሽ አላገኘም ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ ነጋሪት ጋዜጦች በታተሙላት ሕጋዊ መብቶቿ እጅግ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ጠንካራ በራ መብራት የታለችው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በአዋጅ በተሰጣት መብት መሠረት ለሕልውናዋ ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ አልተቀመጠም ኃይማኖትን አስመልክቶ ሙሉ ስልጣን የተጎናፀፈች ሲሆን የቤተክርስቲያኗን ሕግጋቶች እና አስተዳደራዊ አካሄዶች ሁሉ የመወሰን በስሯ ማህበራትን እና ኮሚሽኖችን የማቋቋም እና የመቆጣጠር ሀብት እና ንብረት ያለምንም ተቆጣጣሪ አካል የማፍራት እና የመሰብሰብ መብቶች ተጠቃሚ ሆና ቆይታለች ምንም እንኳን ቤተክርስቲያኒቱ መዋቅሯን ከማንኛውም ዓይነት የመንግስት ጣልቃ ገብነት እና ቁጥጥር የመጠበቅ በአዋጅ የተሰጣት መብት ያላት ቢሆንም የኢህዲግ መንግስት ግን የሚፈልገውን ሰው በጳጳስነት እስከመሾም በመድረሱ በርካታ አማኞች ከፍተኛ ቅሬታ ተሰምቷቸዋል በ 1987 በፀደቀው ሕገ መንግስት የኃይማኖቶች ሁሉ እኩልነት የታወጀ ቢሆንም ከእነዚህ መብቶች ውስጥ አንዱን እንኳን ለማግኘት ያልታደለው መጅሊስ ግን ከተራ ኤንጂኦ የዘለለ እውቅና በመንግስት አልተሰጠውም ይህ እስክሪኑ ላይ የምትመለከቱት በጥር 1997 ከፍትህ ሚኒስቴር ለመጅሊሱ የተሰጠው የፍቃድ ወረቀት ሲሆን ይኸው የተራ ኤንጂኦ ፍቃድ የሚያገለግለው እስከ 2000 ዓመተ ልደት መሆኑን እዚያው ላይ ተጠቅሷል በተጠቀሰው የማብቂያ ጊዜ መጅሊሱ የበጀት ዓመት ክንውኑን እና የኦዲት ምርመራ ውጤቱን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የተባሉ መረጃዎችን ሁሉ አስመርምሮ አዲስ የፍቃድ ምስክር ወረቀት ማውጣት ያስፈልገዋል ፍትህ ሚኒስቴር አስፈላጊ መስሎ ከታየውም ፍቃዱን ነጥቆ ድርጅቱን ሊዘጋው ይችላል የኃይማኖት እኩልነትን አስከብሬአለሁ እያለ የሚፎክረው የኢህዲግ መንግስት ግን ይሄንን ልዩነት እስካሁን ለመፍታት ፍቃደኝነቱን አላሳየም ይልቁንም ተቋሙ ለከፍተኛ /ግልፅ ያልሆነ/ አጋልጦታል እንደአቻው የኦርቶዶክስ ተቋም ተቋሚዊ ጥንካሬ እንዳኖረው በማድረግም ለገዛ ደህንነቶቹ እና አለቆቻቸው አገዛዝ አጋልጦታል እስካሁን ድረስ በርካታ የሕዝበ ሙስሊሙ አባላት በእንዲህ ዓይነቱ ተቋም እንዴት መብታችን እናስከብራለን ሲሉም ይጠይቃሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ዛሬ በበርካታ እና ዘረፈ ብዙ ችግሮች ተተብትቦ ያለ ተቋም ነው ምንም እንኳን ዋነኛው የችግሮቹ ምንጭ ሕጋዊ አቅም የለሽ መሆኑ ቢሆንም አሁን ላለበት የውድቀት ደረጃ ያበቁት ሌሎች ምክንያቶችም አሉ አንድ በአንድ በአጭሩ እንመለከታቸዋለን /ግልፅ ያልሆነ/ ስርዓቶች ቱሩፋት አንዱ እና ዋነኛው መሪዎችን የመምረጥ መብት ሲሆን የኃይማኖት ተቋሚትም ቢሆኑ ከእዚህ ሕግ ውጪ እንዳልሆኑ ይታወቃል ከዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል እና መስዋትነት ፍሬ የሆነው የኢፌድሪ ሕገ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አብዱሰላም የተባሉትን ሰው አዳራሽ ውስጥ እንዳይገቡ ያገደ ሲሆን ሰውዬው ግን ሳይገቡም እንኳን ተመርጠው ወደ ወረዳ ምርጫ ተዛወሩ ወረዳ ላይም ግን 2ኛ ድርሽ እንዳይሉ በደህንነቶች ማስፈራሪያ የተባረሩ ሲሆኑ እስካሁን የአዲስ አበባ መጅሊስ ፀሐፊ የሆነው እና ከእዚያ ቀደም ከቀበሌ አስተዳደር በሙስና የተባረረው ካድሬ አቶ ሁሴን ኑረዲን /ግልፅ ያልሆነ/ በጉልበት ወስዶ እስካሁንም /ግልፅ ያልሆነ/ አዛ ማድረጉን ቀጥሏል በወቅቱ ሀጂ አብዱልሰላም እና ሌሎች ሕዝብ /ግልፅ ያልሆነ/ ሳለ በደህንነቶች የተባረሩ 43 ተመራጮች አፈጉባኤ ዳዊት ዮሐንስ ዘንድ ሄደው አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይጣራል በሚል ጉዳዩ ተረሳስቶ እንዲቀር ተደርጓል በጅማ ከተማ በተደረገው ምርጫ የሆነውም ቢሆን ከእዚህ የተለየ አልነበረም ምርጫው በድንገት እና በሚስጥር እንዲከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የጅማ ሕዝብ ግን ምርጫውን ላለማስነካት ባደረገው ከፍተኛ ጥረት ቅን አሳቢዎች እንዲመረጡ ተደርጎ ነበር ለሕዝበ ሙስሊሙ በቅንነት የሚሰሩ ሰዎች ግን መጀመሪያኑ የማይፈለጉ ነበር እና ሰበብ ተፈልጎላቸው እንዲባረሩ ተደረገ መንግስት ተመራጮቹን ወዲያኑ በጅማ ማዘጋጃ ቤት በመሰብሰብ ከእኛ ጋር ተባብራችሁ ያልናችሁን እየፈፀማችሁ ለመስራት ፍቃደኛ ናችሁ ወይ የሚል ቀጭን ጥያቄ አቀረበላቸው ተመራጮቹ ግን እኛ የምንሰራው ለሕዝቡ ነው ፖለቲካ ውስጥ መግባት አንፈልግም ሲሉ ቁራጥ አቋሚቸውን በማሳወቃቸው 2ኛ ድርሽ እንዳይሉ ተነግሯቸው ተባረሩ በቦታቸውም /ግልፅ ያልሆነ/ የሚባል ሰው ተተክቶበት አሁንም ድረስ የጅማ መጅሊስ ፕሬዘዳንት ሆኖ ሕዝቡን እየበደለ ይገኛል በ 1992 በተደረገው ምርጫ በደቡብ ክልል የሚመረጡትን ሰዎች ቢሆኑ ቀደም ብሎ በደቡብ መንግስት ፕሬዘዳንት አባተ ኪሾ የተመረጡ ሲሆኑ የአባተ ኪሾ የደህንነት እና ፀጥታ አማካሪ ማንንም ሰው ብትመርጡ ከእነዚህ ሰዎች ስም ውጪ ተመርጠዋል ብለን ለመንግስት አናስተላልፍም ሲል የምርጫው አስተባባሪዎች በግልፅ ያለማፈር መርዶውን አርድቷል በሕዝብ ተመርጠው የነበሩ የኦሮሚያ መጅሊስ ተመራጮችም ቢሆኑ ለ 2 ዓመታት የተተው ቢሆንም በደህንነቶች አቀነባሪነት እና የጅማ ዞን መጅሊስ በነበረው አቶ ሰይድ አህመድ አስፈፃሚነት በኦሮሚያ ክልል የፀጥታ ኃላፊ ሱሌማን /ግልፅ ያልሆነ/ ትዕዛዝ ከስራቸው እንዲባረሩ ተደርጓል በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች የመጀመሪያም የመጨረሻም በነበረው በእዚህ የይስሙላ ምርጫ በተፈፀሙት ኢፍታዊነቶች ምክንያት ቅር የተሰኙ ሰዎች በርካታ አቤቱታዎችን አቅርቦ ነበር የአዲስ አበባ ወረዳ 4 ቀበሌ 35 ሙስሊም ነዋሪዎች መጋቢት 27/1992 /ግልፅ ያልሆነ/ የፃፉት በእዚህ ደብዳቤ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መንግስት አንቀፅ 27/3 የኃይማኖት ተከታዮች ኃይማኖታቸውን ለማስፋፋት እና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የኃይማኖት ትምህርት እና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ ሲል ይሄንን በኃይማኖት የመደራጀት መብት እውቅና የሰጠ ሲሆን የእስልምና ጉዳዮች አመራር አባላት በምርጫ ብቻ መምጣት እንዳለባቸው የሚደነግገው የመጅሊሱ መተዳደሪያ ደንብ ደግሞ እንደምትመለከቱት በአንቀፅ 22/1 በየትኛውም እርከን የሚገኝ የእስልምና ጉዳይ ምክር ቤት የጠቅላላ ጉባኤው አባላት እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን 5 ዓመት ብቻ ነው ሲል ደንቡን ያስቀምጣል በፍትህ ሚኒስቴር ፊት ላፀደቁት መተዳደሪያ ደንብ ተገዢ ሆነው የማያውቁት የመጅሊሱ ካድሬ አመራሮች ግን ያለምንም ምርጫ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚሾሙ ሲሆን በሚሰሩትም ወንጀል አንዳችም ጠያቂ እንደሌለባቸው ይልቁንም የሚሾፈሩት በመንግስት ደህንነት አባላት መሆኑን ለዓመታት ስንታዘብ ቆይተናል ከ 1987 ጀምሮ በትግራይ ክልል መጅሊስ እና ትግራይ ሸሪያ ፍ/ቤት ፕሬዘዳንት የነበሩት ታጋይ ሼህ ከድር ላደረጉት የትጥቅ ትግል የተሰጣቸው ሽልማት እና የቤተሰብ ርስት እስከሚመስል ድረስ ያለምንም ምርጫ የመጅሊሱን ስልጣን ለ 17 ዓመታት ተቆጣጥረውታል ያለሕዝብ ድምፅ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ቆይተዋል መንግስት በ 1987ቱ የአንዋር መስኪድ ግጭት አሳቦ በርካታ ለዲን የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን በማሰር እና ድርጅቶችን በገፍ በመዝጋቱ የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት መንግስት የሚፈልጋቸውን ሰዎች መጅሊሱ ላይ መሾሙ መቼም ያልረሳነው ትዝታችን ነው በ 1988 ደብረዘይት ከተማ ላይ በተደረገው ስብሰባ በአዲስ አበባ መስተዳድር ከንቲባ የነበሩት አቶ አሊ አብዶ መድረክ ላይ በግልፅ በመጅሊስ መሪነት የሚመራቸው ጎበዝ ሰው አምጥቼላችዋለሁ በማለት አቶ አብዱራዛቅን በመጅሊሱ ላይ በሕዝብ ፊት ሾመዋል መንግስት ቀደም ብሎ በወሰደው አስከፊ እርምጃ አከርካሪውን የተመታው ሕዝበ ሙስሊም በወቅቱ የሚሰራውን ሁሉ ታዝቦ ዝም ማለት መርጦ ነበር በኋላ ግን በ 1992 ምርጫ መደረግ አለበት ተብሎ በመታሰቡ ሕዝባዊ ምርጫ ለማድረግ ዝግጅቱ ተጀመረ ምንም እንኳን ምርጫ የሚደረገው በቀበሌ ነው ተብሎ በመወሰኑ ብዙዎች ድምፅ እንዳይጭበረበር ስጋት ቢይዛቸውም ምንም ማድረግ የሚቻል ነገር አልነበረም ሕዝበ ሙስሊሙ ይታዘበኛል የሚል ይሉኝታ ያልያዘው መንግስት ግን በደህንነቶቹ አማካይነት በምርጫው እንዲሳተፉ የማይፈልጋቸውን ሰዎች ለማግለል ከፍተኛ ጥረት አድርጓል የማይፈለጉ ሰዎች ገና አዳራሽ በር ላይ በግልፅ እንዳይገቡ ሲደረግ ብዙዎች ታዝበዋል በአዲስ አበባ በወረዳ 24 መንግስት ሕዝቡ እንይመርጣቸው የሰጋቸውን ሀጂ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የቀበሌያትንን ምርጫ አንድ ሰው እንደፈለገ አድርጎ ሰው በሌለበት እራሱን አስመርጧል በመሆኑም ምርጫው ሕዝብ ባለበት ተደግሞ ትክክለኛ ወኪሎቻችን እንምረጥ የሚል አቤቱታቸውን ከአቤቱ ፊርማዎቻቸው ጋር አስገብተዋል ከፊታችሁ የምታዩት የሻሸመኔ ወረዳ እስልምና ጉዳዮች ሊቀመንበር በሆኑት ሼህ መሐመድ በዳሶ ተፈርሞ የወጣው ደብዳቤ ደግሞ ሕዝብ የመረጣቸው ተወካዮች ኦሮሚያ መጅሊስ ውስጥ ባሉ ግለሰቦች ከስራ መታገዳቸውን በመቃወም በመተዳደሪያ ደንባችን መሠረት /ግልፅ ያልሆነ/ እስልምና ጉዳይ አመራር ኮሚቴን የመሻር እና የመሾም ስልጣን የዞኑ ጠቅላላ ጉባኤ እንጂ የክልል ጠቅላላ ጉባኤ አይደለም ሲል አቋሙን በግልባጭ ለመንግስታዊ መዋቅር አካላት አሳውቋል አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች /ግልፅ ያልሆነ/ የያዘው የኦሮሚያ ክልል በየቀበሌው ካድሬ ለማስመረቅ ትዝብት ላይ የሚጥል ይሉኝታቢስነት ካሳዩ የመንግስት ደህንነቶች ጋር ታግሎ ሕዝቡ የመረጣቸው ተወካዮች ከ 2 ዓመታት በኋላ ሰይድ አህመድ በተባለ ግለሰብ አቀናባሪነት እንዲወገዱ ሲደረግ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ምክትል ፕሬዘዳንት ሼህ አህመድ መሐመድ ኪቦ ተፈርሞ በወጣው በእዚህ ደብዳቤ ተቃውሞውን አሳውቆ ነበር በጋራ ተነጋግረን እናስተካክላለን በማለት ከመግባባት ደረጃ የደረስንበትን የጅማ ዞን እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ነባር የስራ አስፈፃሚ አባላት ሳይገመገሙ እና ጥፋታቸው ሳይታወቅ ሙሉተጉባኤ ባልተሟላበት ስብሰባ አዲስ ምርጫ እያካሄዳችሁ መሆኑን በቁጥር ዲኤች አይ አ/218/12/94 በ 9/6/94 ለዞኖች ስትፅፉ በግልባጭ አሳውቃችሁናል አሁንም ቢሆን ተካሄደ የተባለው ምርጫ በእኛ መመዘኛ ፍታዊነት የጎደለው እና ደንብን የጣሰ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ይህ በእዚህ እንዳለ አካሄዳችሁን እኛ በማናውቀው ሁኔታ በተለያዩ አካባቢዎች እየተንቀሳቀሳችሁ ለሕዝብ አሳቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸውን የመጅሊስ አባላት በማስወገድ በሌሎች ለመተካት ጥረት እያደረጋችሁ መሆኑን ተረድተናል ይላል በወቅቱ ይወጡ የነበሩ የእስላማዊ ጋዜጦች ሕዝቡን የምርጫ ሮሮ የቻሉት ያህል ለማሰማት ጥረዋል ሚያዝያ 6/1992 የወጣው ሰልፍ ያ ጋዜጣ የተመራጭ ያስመራጭ ታይቶ አይታወቅም ዘንድሮ እየታየ ነው በሚል አስመራጭ ተብሎ የተቀመጡ ሰዎች እራሳቸው አጭበርብረው ተመርጠው ቁጭ ማለታቸውን ለታሪክ ምስክርነት አቅፎት ነበር ሳይመርጧቸው መጅሊሱ ወንበር ላይ ቁጭ ያሉትን ግለሰቦች በመቃወም ያልመረጥነው መጅሊስ በግድ ሊያገለግለን አይገባም መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ይስጥ ሲሉ የቻግኒ ሙስሊሞች ያቀረቡትን ቅሬታም እንዲሁ በሰኔ 23/1992 እትሙ ማውጣቱ ይታወሳል

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከላይ ባሉት ምሳሌዎች ባየነው መሠረት ኢህዲግ እና ለኃይማኖት ነፃነት ግድ የሌላቸው ካድሬዎቹ የሕዝበ ሙስሊሙን ድምፅ በግላጭ ቀምተው ወስዱት በተመረጡት ሰዎች ምትክም ኪሳቸውን ለማድለብ ያለሙ ለእስልምና ግድ የሌላቸው እና ከካድሬነት ውጪ አንዳች የእስልምና ፍላጎት የሌላቸውን ሰዎች በቦታው ላይ አስቀመጡ ከእዚህ የይስሙላ ምርጫ በኋላም የሚቀጥለው ምርጫ ጊዜ በ 1997 ሲደርስ ደህንነቶች አስቀድመው ስራቸውን ሰሩ የመንግስት አሻንጉሊት የሆነው ጠቅላይ ጉባኤውም ተሰብስቦ ከፊታችሁ በቃለጉባኤው ላይ የምታዩትንም ውሣኔ አሳልፎ ተለያየ አሁን ያለው የጠቅላይ ምክር ቤቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ገና 6 ወሩ በመሆኑ በእዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ስር ነቀል የሆነ ለውጥ ስላመጣ ችግር ፈጣሪዎች በምርጫ አጋጣሚ ሰርገው ገብተው ሰላምን ጥያቄ ላይ እንዳይጥሉት በ 1997 የመንግስት ምርጫን ሂደትን ሰላም ከማስጠበቅ አኳያ እገዛ ለማድረግ ሲባል ለምርጫ ሲባል የሚወጣው ወጪ ለተጎዶ የክልል እስልምና ጉዳይ ጽ/ቤት ድጎማ ማድረግ ስለሚቻል የምክር ቤት መተዳደሪያ ደንብ ምርጫን ለ 1 ጊዜ ማራዘም ስለሚፈቅድ በመጨረሻም የአመራር ችግር ባለባቸው የክልል የዞን የወረዳ እና ከእዚያም በታች ባሉ የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት የፌዴራሉ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ወርዶ ግምገማ በማካሄድ ማረም ማስተማር ማገድ መተካት እና ለሚመለከተው አካል ወቅቱን ጠብቆ ሪፖርት ማድረግ እንዲችል በማድረግ ዙሪያ ቤቱ በሰፊው ተወያይቶበት በአንድ ድምፅ ወስኗል ይላል በእዚህ መልኩ ያ ታሪካዊ የ 1992 ምርጫ በመጅሊሱ ታሪክ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ምርጫ ሆኖ ቀረ ሕገ መንግስቱ በግልፅ ተጣሰ ሕዝበ ሙስሊሙ ግን ብሶቱን ሁሉ ውጦ በትዕግስት አሳለፈ ዛሬም የሕዝበ ሙስሊሙ ድርጅት ካድሬዎቹን ሊቆጣጠር የሚፈልገው መንግስት አሁንም ቢሆን የመጅሊሱን መተዳደሪያ ደንብ ካማስቀየር አልተቆጠበም በእዚሁ ዓመት ጥር 2004 በመጅሊስ አሻንጉሊቶቻቸው ቀያይረው እና ለዋውጠው ያፀደቁት መተዳደሪያ ደንብ ይሄንን እውነታ ግልፅ አድርጎ ያሳያል በአንቀፅ 42 ንዑስ ቁጥር 1 በየትኛውም እርከን የሚገኝ የእስልምና ምክር ቤት የጠቅላላ ጉባኤው አባላት እና የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን 10 ዓመት ነው ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በሁኔታዎች አስገዳጅነት በጠቅላላ ጉባኤው ከተወሰነ የምርጫውን ጊዜ ማራዘም ይቻላል በማለት ያለምንም ምርጫ ከ 10 ዓመት ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ካድሬዎቹ በስልጣን ላይ መቆየት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል በተቋቋመበት ሕዝበ ሙስሊሙን የማገልገል ዓላማ አመራሮቹ ሁሉገብ ብቃት ይኖራቸው ዘንድ ግድ ይላል ይህ ይሆን ዘንድ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ያልፈቀዱት የኢህዴግ ደህንነቶች ግን ወደ ተቋሙ በጓሮ የሚያስገቧቸው ሰዎች በሙሉ እጅግ ብቃት አልባ እና መሐይማን ብቻ ናቸው ተቋሙ በመተዳደሪያ ደንቡ ለአመራር የሚመጡ ሰዎች ብቃት ላይ በግልፅ የሚያስቀምጠው ነገር አለመኖሩን ለእዚሁ ችግር የራሱን ሚና ተጫውቷል የኢትዮጵያን ግማሽ ሕዝብ እወክላለሁ የሚለው ተቋም መሪዎች የትምህርት ደረጃቸው እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ ይታወቃል በአብዛኛዎቹ ከ 8ኛ ክፍል ያላለፉ በዛ ከተባለ ከ 12ኛ ክፍል በላይ የት/ቤትን ደጃፍ ያልረገጡ ናቸው እስቲ ይሄንን ደብዳቤ ይመልከቱ ከፌዴራሉ መጅሊስ ወደ አዲስ አበባው መጅሊስ የተላከ ደብዳቤ ሲሆን የአዲስ አበባው መጅሊስ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይቅረብ ሲል ለምሪት ያሰፈረውን የእጅ ፁሑፍ ይመልከቱ እውን ይህ በከፍተኛ ትግል የተፃፈ ፁሑፍ የፀሐፊውን መሐይምነት አይገልፅም አማርኛ እንኳን ለመፃፍ እንዲህ የሚቸግረው ሰው ለምን ሲባል ይሁን በኃላፊነት ቦታ የሚቀመጠው የመጅሊሱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች እና ሌሎች የአመራር አባላት በሙሉ በፊደል ድርቅ ከፉኛ የተመቱ ናቸው ለዓመታት የስራ ኃላፊነቱን እያቀያየረ መጅሊሱን ሲሾፍር የቆየው እስከሪኑ ላይ የምታዩት አቶ ጀማል መሐመድ ተቋሙን በፖስተኝነት ሲቀላቀል ያስገባው የትምህርት መረጃ የሚኒስትሪ ካርዱን ብቻ መሆኑን ይነገርለታል ይህ መሐይምነቱ እንዳይነቃበት ከፍተኛ ጥረት የሚያደርገው አቶ ጀማል ግን መጅሊሱ ገዝቶ በሚያስተዳድራቸው የጥቅም አሳዳጅ ጋዜጦች ዶ/ር የሚል ማዕረግ ከስሙ በፊት በማስቀመጥ የተማረ ሰው ለመምሰል ይሞክራል ገና የ 2ኛ ት/ቤት ደጃፍ ያልረገጠ ሆኖ ሳለ ከሚስተርዳም ዩኒቨርስቲ በግጭት አፈታት ተመርቂአለሁ እያለ ሰዎችን ለማታለል ይሞክራል ጋዜጠኞች በሚገኙባቸው ስብሰባዎች ላይም ጋዜጠኛ ነኝ እያለ እስከመገናት ደርሷል ይህ በአመራሮቹ ጎን ተብሎ እንዲሰናከል የተደረገ ተቋም ይሄንን መሰል መሀይማንን ይዞ ከቶ የት ይደርስ ይሆን /ግልፅ ያልሆነ/ አባላት ከእዚሁ እውቀት አልባነት ጋር ተያይዞ የአስተዳደር እውቀት ደሀ መሆናቸውም የአደባባይ ሚስጥር ነው የስራ ደብዳቤዎችን እንኳን አስተካክሎ መፃፍ አይሆንላቸውም ሕጋዊ ደረሰኝ አያያዝ እና አሰራር ለእነሱ በአድ በመሆኑም የድርጅቱን ሒሳብ ሠራተኞች ያልተወራረደ ገንዘብ ወጪ እንዲደረግላቸው ያስቸግራሉ ከፊርማ ውጪ ገንዘብ ያስወጣሉ ያስገባሉ ከስርዓት ውጪ ለመስራት ፍቃደኛ ያልሆኑ የሒሳብ ሠራተኞችን ያለአግባብ ያባርራሉ ለድርጅቱ ዋነኛ የገንዘብ ምንጭ የሆነውን ቅዱሱን የሀጂ ጉዞ በብቸኝነት የተቆጣጠረው ይኸው መጅሊስ ዓመት እስከ ዓመት ሲፈፅመው የቆየውን ሂደት እንኳን ማስተካከል እና ማስተዳደር አልቻለም የፊደል ሽፍታ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሆኑት አመራሮቹ ለሀጂ ከፍተና ገንዘብ የሚያስከፍሉ ቢሆንም ተገቢውን አገልግሎት ሲሰጡ እስካሁን በታሪካቸው አልታየም ኢትዮጵያዊያን /ግልፅ ያልሆነ/ ምን ጊዜም በሀጂ ሰፍራ ጥሩ ማረፊያዎችን የማያገኙ ትራንስፖርት እንኳን ሳይዘጋጅላቸው በበረሀው ሀሩር በእግራቸው የሚኳትኑ በአየር ማረፊያዎች ውስጥ ቀናትን ያለማደሪያ የሚያሳልፉ እና በማንነታቸው እንዲሸማቀቁ የተደረጉ ናቸው ለዕድሜያቸው ግድ የሌላቸው ሼህ ተብዬ ካድሬዎች ግን /ግልፅ ያልሆነ/ ለማስተናበር አበል በገፍ እየተከፈላቸው ሳለ አጃቢዎችን /ግልፅ ያልሆነ/ ፊንታ በምርጥ በምርጥ ሆቴሎቻቸው ክፍል ውስጥ በኢቲቪ ድራማ ይከታተላሉ በዲን እውቀትም ቢሆን የመጅሊሱ አመራር አባላት እዚህ ግባ የሚባል መሰረታዊ እውቀት እንኳን የላቸውም ብዙዎቹ ቁርአን እንኳን ማንበብ የማይችሉ ሲሆኑ ትንሽ ቀርተዋል የሚባሉት ከ 1 ሁለት ከታቦች ያለፈ ቂርአት በፍፁም የላቸውም ሱቡሀን አላህ የአላህን ቁርአን መረዳት ቀርቶ በተገቢው እንኳን ማንበብ የማይችል ሰላቱን በስነ ስርዓት እንዴት መፈፀም እንዳለበት የማያውቅ ከነብዩ የሀዲስ ማዕድ ጥቂት እንኳን ያልተቋደሰ እንዴት ሚሊዮኖቹን ይመራል የኦለማ ሀብታም በሆነችው ሀገራችን ኪታብ ያልቀራ ሰው የመጅሊሱ መሪ ሲሆን እጅግ አያሳዝንም ይህም ሁሉ በሰቡር ያልፍ ይሆናል የመጅሊሱ አመራሮች በስነ ምግባር እና ስብዕና ያሉበትን አዘቅት ማየት ግን በእርግጥም ልብ ይሰብራል በኋሮ በር ተሹለክልከው በሕዝበ ሙስሊሙ ተቋም የሚርመሰመሱት ሰዎች በስነ ምግባር እጅግ የወደቁ ናቸው ቡዙዎቹ እንኳን ለሕዝበ ሙስሊሙ አርአያ ሊሆኑ ይቅር እና እራሳቸውን ከሱስ ተጠማጅነት ነፃ ማድረግ ያልቻሉ ናቸው የጅማ ከተማ የመጅሊስ ተመራጮችን በ 1994 አስባሮ በቦታቸው እስከዛሬ ድረስ ቁጭ ያለው /ግልፅ ያልሆነ/ ስብሰባዎች ላይ አስካሪ መጠጥ የሚቋደስ ጀግና ሕዝበ ሙስሊሙን ወክሎ በኃይማኖት መሪነት በተገኘባቸው ስብሰባዎች ላይ የመንግስት አካላት ጋር አልኮል ሲቋደስ ወይም ሲጎነጭ ማየት ከቶ እንዴት ልብ ይሰብር በጎንደር ከተማ መጅሊስ ለኦለማዎች ምክር ቤት ኃላፊ ሆነው የተሾሙት አቶ ሙስጠፋ አሚኑ በመንደር ኪዮስካቸው ውስጥ ቁጭ ብለው ሲጋራ ሲሸጡ የሚውሉ ሰው ናቸው ሕዝበ ሙስሊሙን ፍሬ አልባ አድርጎ ያስቀረው ኢህዲግ ግን በኦለማዎች ምክር ቤት ዋነኛ ፈላጭ ቆራጭ አድርጓቸዋል መስኪዶችን የጦር አውድማ በማድረጉ ሂደትም ዋነኛ ተዋናይ ናቸው ለ 6 ዓመታት የፌዴራል መጅሊሱን በምክትል ፕሬዘዳንትነት የመራው እና በ 2001 በሙስና የተባረረውን አቶ ኤሊያስ ሬድማንን ይመልከቱ ለመጅሊስ መሪነት በተሾመበት ወቅት ጎጃም በረንዳ ፋሲል ፋርማሲ አጠገብ የሚገኝ አንድ ሆቴል ከረንቡላ ቤት

3180 7026

http://ethcriminalawnetwork.com/

ውስጥ ሲቀምር የሚውል ሰው ዝሬ የሙስሊሞችን መብቶች ቢረግጡ ምንም የማይመስላቸው የመንግስት ደህንነቶች እና ባልስልጣናት ግን ከከረንቡላ ቤት አውጥተው የ 40 ሚሊዮን ሙስሊሞች መሪ አደረጉት ከሌሎች አቻ የእምነት መሪዎች እና ትላልቅ ፓፓሳት ጋር በሚሰበሰብባቸው ስብሰባዎች እና ጉባኤዎች ላይ የክቡር አባታችን ሼህ ኤልያስ ሬድማን እየተባለ በአንቱታ የሚጠራው ይህ ሰው በስብሰባዎቹ እረፍት ሰዓት ወደ ጓሮ እየወጣ ሲጋራ በማጨስ የብዙ ሙስሊሞችን ቀልብ ሲሰብር ኖሯል የሌሎች ኃይማኖት መሪዎችን እና ፓፓሳት ተከብረው ኃይማኖታቸውን ሲያስከብሩ ቀለው ያቀለሉኝ እኒህ ባዕዳን ስርጎ ገቦች አላህን አይፈሩም የፌዴራል መጅሊሱም የጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ መጅሊሱን ሲመራ የቆየውን አቶ ጀማልን ይመልከቱ በየመንደር ሺሻ ቤቶች በተደጋጋሚ የሚታየው ይኸው ግለሰብ ከአሁን ቀደም መጅሊሱን የረገጠው በፖስተኛነት ለመስራት ነበር በእዚሁ ስራ ላይ እያለ ግን በገንዘብ ማጭበርበር ተከሶ እንዲባረር ተደርጎ ነበር እስከሪኑ ላይ እንደምትመለከቱት ከታህሳስ 30/1994 በመጅሊሱ ምክትል ፕሬዘዳንት ሼህ አህመድ መሐመድ ኪቦ ፊርማ እና ማህተም የወጣው ይኸው ደብዳቤ አቶ ጀማል መሐመድ አቶ ከሊፋ ሙስጠፋ ከተባሉ ግለሰብ ላይ 14ሺህ 802 ብር በማጭበርበሩ ለወረዳ 16 ፖሊስ እርምጃ እንዲወስድበት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ይሄኛው በ 24/06/2001 የተፃፈ ደብዳቤ ደግሞ ከ 7 ዓመታት በኋላ አቶ ጀማል በጽ/ቤት ኃላፊነት እንዲሰራ የተሾመበት ማስረጃ ነው ሱብሀን አላህ አቶ ከሊፋ ሙስጠፋ ከዓመታት በፊት ገንዘብ ያጭበረበራቸው ግለሰብ ዛሬ እሳቸው እና የ 40 ሚሊዮን ሙስሊሞች መሪ ተደርጎ በመንግስት መሾሙን ቢሰሙ ምን ይሰማቸው ይሆን የአዲስ አበባ መጅሊስ ዋና ፀሐፊው አቶ ሁሴን ኑረዲን ተመሳሳይ የተጨማለቀ ታሪክ ያለው ቢሆንም ከመጅሊስ መሪነት ግን አንዳችም ያገደው ነገር የለም ይህ ሰው በወረዳ 24 ቀበሌ አስተዳደር ውስጥ ሳለ የፈፀመው ሙስና ከኢህዴግ መዋቅር በግምገማ የተተፋ እና የተባረረ ሰው ነው ምንም እንኳን ኢህዴግ ለመዋቅሩ ተፀይፎ ቢያባርረውም ሕዝበ ሙስሊሙ መዋቅር ውስጥ ግን አስገብቶታል በ 1992 የወረዳውን ተመራጮች ካስባረረ በኋላ ቀስ በቀስ መጅሊሱ ቅጥር ድረስ ተንፏቆ የደረሰው ይህ ሙሰኛ ግለሰብ ዛሬ ሺዎችን ያስለቅሳል የመስኪድ ኮሚቴዎችን ይሽራል ይሾማል መስኪዶችን ያዘጋል ያስቀማል ሀጂ ሳኒን የመሳሰሉ አባቶች የመሰረቱት ባለመልካም ራዕይ ድርጅት ወንበር ዛሬ በቁማርተኞች እና በጋጠወጦች ተሞልቷል የቀድሞው የፌዴራል መጅሊስ ዋና ፀሐፊ አልመሐመድ ሲራጅ ከመሰል ቁማርተኞች አንዱ ነው በአንድ ታዋቂ ሆቴል ውስጥ በሚገኝ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ቁማር ቤት በተደጋጋሚ ማንነቱ እንዳይታወቅ ባርኔጣ ለብሶ ሲገባ በአይን ምስክሮች ታይቷል የተለያየ ጊዜ የመጅሊሱን መንበር የተቆናጠጡ ሰዎች በአብዛኛው እንዲሁ ነበሩ ጎረቤቴ ያለው መስኪድ የሱቢህ አዛን አላስተኛ ብሎኛል በሚል የተከራዩትን ቤት እስከመቀየር የደረሱ መሪዎችን ያስተናገደው ይኸው ድርጅት በአጋጣሚ ቅንብር የገቡ ጥቂት የተማሩ እና ብቃት ያላቸው ሰዎች ሲመጡ ግን በተፅኖ ለማባረር የደረሰበት አልነበረም 40 ሚሊዮን ሙስሊሞችን ለመምራት መንግስት በጓሮ እያስገባ ያስቀመጠልን ሰዎች እኒህ እንጂ ሌላ አይደሉም /ግልፅ ያልሆነ/ ወቅቱ 1999 ነበር ለዓመታት በጥቃቅን የኃሳብ ልዩነቶች እስላማዊ ወንድማማችነት መደፍረሱን ያስተዋሉ አለማዎቻችንን ተሰባስበው በልዩነቶታቸው ዙሪያ መወያየት ጀመሩ የሚያለያዩን አጀንዳዎች ጥቂት አንድ የሚያደርጉን ግን ሺዎች ናቸው ተራርቀን የጎሪጥ መተያየቱ ይብቃ ተዋደን ሕዝበ ሙስሊሙን እናዋደው የሚል ቁርጠኝነታቸውን በርካቶችን አስደሰተ እነ ቀዳሚ ሙፍቲት ሀጂ ኡመር እድሪስን እነ ዶ/ር ጀይላን እና ሌሎችንም በርካታ የተለያዩ መዛብ አለማዎችን ያካተተው ይኸው ጉባኤ ለ 9 ወራት ያህል በጥሩ ሁኔታ ዘለቀ አለማዎቹም የወንድማማችነት እና የአንድነት ስሜት ገነቡ /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ ልንሆን ነው በሚል ተስፋ ተሞልተው መጨረሻውን ይጠባበቁ ጀመር በ 9ኛው ወር ግን ያልተጠበቀው ተከሰተ ቀደም ሲል የሙሊሙን አንድነት የሚጠየፉት የኢህዲግ ደህንነቶች 20 ዓመት እንኳን ቢወያዩ በፍፁም ሊስማሙ አይችሉም እንደውም በደንብ ተጨቃጭቀው ፀብ ይፈጥራሉ በሚል ተስፋ ችላ ብለዋቸው የነበሩ አለማዎች መስማማት ላይ መሆናቸው ስላስደነገጣቸው በየተራ ለየብቻ በማስፈራራት በአስቸኳይ የአንድነት እንቅስቃሴአቸውን እንዲያቆሙ አዘዙ መጀመሪያ የአዲስ አበባ መጅሊስ ዋና ፀሐፊ የሆነውን ሀጂ መሐመድ አወል ነጋን አስፈራሩ ከእዚያም የመጅሊሱ ምክር ቤት አባል የሆነውን አቶ አህመድ ኢማምን አስፈራሩ በመቀጠልም የኑር መስኪድ ምክትል ኢማም ሼህ ሰይድ ከጉባኤው እንዲወጡ ቀጭን ትዕዛዝ ተሰጣቸው የአንዋሩ ሀጂ ጣሀም እንዲሁ ውጣ ተባለ በመንግስት ደህንነቶች ማስፈራሪያ ፊት አንዳች አቅም የሌላቸው የጉባኤው አባላት አለሞች ቀልባቸው እንደተሰበረ ጉባኤውን ተራ በተራ እየለቀቁ ይወጡ ጀመር የሙፍቲህ ሀጂ ኡመር ግን ደህንነቶች እንዲያቆሙ ሲያዟቸው እኛም ለሀገራችን ደህንነቶች ነን ለምን አንድ አትሆኑም ትሉናላችሁ በማለት ቁጣቸውን ገልፀዋል የወቅቱ የመጅሊስ ምክትል ፕሬዘዳንት የነበረው አቶ ኤልያስ ሬድማንንም ጉባኤውን ለማስቆም እላይ እታች በመውረድ ከኦለማዎች ጋር ተጣላ መጨረሻም እሱ እንዲወርድ ሲደረግም አሁን በስልጣን ላይ ያለው

http://ethcriminalawnetwork.com/

የአቶ አህመዲን አብዱለሂ ካቢኔ ጉባኤው የእኔ ስራ ነው በሚል ሙሉ በሙሉ ከበተነው በኋላ ሀጂ ኡመርም ቀድሞ ከያዙት ቦታ ተነስተው ምንም ዓይነት ተፅኖ መፍጠር ወደ ማይችሉበት /ግልፅ ያልሆነ/ ዘርፍ ኃላፊነት ተዘዋወሩ የመዘዋወራቸው ሰበብም አንድነት አንድነት ትላለህ የሚል ነበር በአቶ አህመዲን ካቢኔም ዛሬ የአንድነት ፀር የሆነውን የሀባሽ ጠመቃ ዘመቻውን ጀምሯል ይህ ሙስሊሙን የመከፋፈል እና አንድ እንዳይሆን የማድረግ ሴራ ለዓመታት በጓሮ በር ስልጣን ላይ በሚቀመጡት የመጅሊስ መሪዎች ሲተገበር የቆየ ነው ድርጅቱ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ አባት እንደመሆኑ የመዛብ ልዩነቶችን አቻችሎ እና አስማምቶ ማስተዳደር ሲገባው አንዱን ከሌላው ጋር ለማጋጨት የተለያዩ ስያሜዎችን በመስጠት ልዩነቱን ያጋግላል ይሄንን የመዛብ ዘረኝነት የሚያራምደውም መተዳደሪያ ደንቡን ከማሻሻል ጀምሮ ነው በ 1996 የተሻሻለው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 5 በየትኛውም እርከን የሚገኙ የእስልምና ጉዳይ ምክር ቤቶች እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ከፅንፈኝነት ከወሀብያ ከተክፊር እንደአጠቃላይ ከችግር ፈጣሪዎች ነፃ የሆነ መሆን አለበት ሲል በንዑስ አንቀፅ 6 ደግሞ በየትኛውም እርከን የሚገኝ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ምክር ቤት መመረጥ የሚችለው የሀገር አቀፉ አለማ የሰጠውን ፈጥዋ የተቀበለ መሆን አለበት በማለት የመዛብ ልዩነቶችን አቻችሎ እንደማይሄድ ይገልፃል ከሌሎች ኃይማኖት ተከታዮች ጋር ተቻችሎ የመኖርን መርህ ለማስፈን በሚል በጀት መድቦ የሚንቀሳቀሰው መጅሊስ ግን እንደአባት ድርጅት ፅንፈኝነት ቢኖር እንኳ ስህተቶችን ለማረም በጋራ የወንድምነት ስሜት ሁሉን አቀራርቦ መስራት ሲገባው ሙስሊሞች ላይ የተለያዩ ስሞችን እየለጠፈ የመዛብ ዘረኝነትን ያስፋፋል ሌሎችን ለማቀራረብ እለፋለሁ እያለ ሙስሊሞችን ግን ያርቃል በ 1992 የእስልምና ምክር ቤቶች ምርጫ ወቅት መጅሊሱ ልዩነት ፈጣሪ እና ከፋፋይ ብሎ የሰየማቸውን ሙስሊሞች እንዳይገቡ ማጭበርበሩን እና ምርጫውም ሆን ተብሎ ዲሞክራሳዊ እንዳይሆን እንደተደረገ በድፍረት የሚናገረው በሙስሊሙ መካከል እየተካሄደ ያለውን ክፍልል ለመግታት የቀረበ ፁሑፍ የሚለው ይህ ሰነድም የመጅሊሱን ሕገ ወጥ አካሄድ በግልፅ የሚያሳይ ነው ምርጫው በዲሞክራሳዊ መንገድ መካሄድ አለበት ከተባለ ትክክለኞቹ ሆኑ ከፋፋዮች የድምፅ ምርጫ ካገኙ ይመረጣሉ ማለት ነው በ2ኛው ዙር የመጅሊስ ምርጫ አከፋፋዮች ተመርጠው ወደ መጅሊስ እንዳይገቡ ለማድረግ በሰውር እና በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ኢ ዲሞክራሳዊ በሆነ ዘዴ ተከላከለናል ሲልም ይገልፃል ሱቡሀን አላህ ልዩነት የሚስተካከሉ ሰዎችን መርጦ

http://ethcriminalawnetwork.com/

በማግለል እና በማራቅ ነው'ን በ 2003 የጅማ መጅሊስ ባዘጋጀው የ2 ቀን የሰላም እና የመቻቻል ጉባኤ ላይም የጅማ ሙስሊሞችን ወሀብያ እና ሱፍያ በሚል አጓድሉ መስኪድ ለመቀማት በመንግስት ኃላፊዎች ፊት መድረክ ላይ የመጅሊስ አመራር አባላት ያደረጉት ንግግር በወቅቱ ብዙዎችን አሳዝኖ ነበር ይህ ሁሉ አንድነትን የመጥላት አባዜ የሙስሊሙን አንድ መሆን ከማይፈልጉ አካላት የተጣለብን እገዳ መሆኑ ግልፅ ነው ከበርካታ ዓመታት በፊት ለኢሀዴግ ቅርብ የነበሩት ሼህአብዱራህማራ ሙዳ የተባሉት የመጅሊስ ፕሬዘዳንት ሙስሊም አለማዎችን ወደ አንድነት ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረት እንዲያቆሙ ቀጭን ትዕዛዝ ከመንግስት የተሰጣቸው ሲሆን አንድነት አንድነት ማለትህን አቁም በሚል ልክ እንደችግር ተቆጥሮ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል በ 1990ዎቹ የመጅሊሱ ፕሬዘዳንት የነበሩት ሀጂ ኑሩ ሙሳም ቢሆን አለማዎችን ወደ አንድነት ለማምጣት ብዙ ተስፋ ሰጪ ጥረቶችን ካደረጉ በኋላ ወዲያውኑ ከስልጣን ወርደው በሌሎች እንዲተኩ የተደረገው ሙስሊሙ ሕብተሰብ ተከፋፍሎ እንዲቆይ የመንግስት ፍላጎት በመሆኑ ነበር ሱብሀን አላህ ይህ ወንድማማችነትን በመንግስት የተከለከለ ሙስሊም ሕብረተሰብ ችግሩ የሚያበቃው መቼ ይሆን መጋቢት ወር 1998 አዋሳ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሙስሊም ተማሪዎችን ከክርስቲያን ወንድሞቻቸው ጋር ለማጋጨት ድብቅ ዓላማ ያነገቡ እና የሕወሀት አባላት የሆኑ 4 ተማሪዎች ቁርአንን በተደጋጋሚ ለሽንት ቤት ሲጠቀም ተያዙ ስማቸውም ፀጋዘሀብ ሀጎስ ኃይለሚካኤል ሙሴ ሀጎስ ገ/ጨርቆስ እና ዘመን ፍስሀ ይባል ነበር ዓላማው ግልፅ ነበር ኢሀዴግ ሙስሊሞችን በተደጋጋሚ በማስቆጣት አላስፈላጊ የአፀፋ እርምጃ ሲወስዱ አክራሪነት ተፈጥሯል በሚል ሰበብ ለመምታት ማመቻቸት የጀመረው ገና ከዓመታት በፊት ነው እና ምንም እንኳን ድርጊታቸው ትንኮሳ ቢሆንም ከፋፍለህ ግዛን መርህ የሚያስፈፅሙ ጠንቀኞች እንጂ የኃይማኖት ሰዎች አለመሆናቸውን የተረዱት ሙስሊም ተማሪዎች ግን ከስሜታዊ እርምጃ በመቆጠብ ወንጀለኞቹን ለሕግ አቀረቡ ምንም እንኳን ሙስሊም ተማሪዎቹ ከሕጋዊ አካሄድ ክስ ቢመሰርቱም ሰዎቹ ግን የሕወሀት አባላት በመሆናቸው ባልታወቀ ሁኔታ በዋስ እንዲለቀቁ ተደርጎ በፍ/ቤቱ ዳሮ በኮብራ መኪና በደህንነት አባላት ተወስደው ተለቀቁ ይህ ፍርደ ገንቢልነት በፈጠረው ሀገራዊ ቁጣ ምክንያት ጉዳዩ የከነከናቸው የባህርዳር ሙስሊም ነዋሪዎች ሚያዝያ 1998 ሕገ መንግስቱ አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚፈቅድላቸው መሠረት በአዋሳ እና በከሚሴ ቁርአን ላይ የተፈፀመውን ፀያፍ ተግባር በሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሞአቸውን ለመግለፅ በእዚህ ደብዳቤ ፍቃድ ይጠይቃሉ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሙስሊሞች መብታቸውን ለማስከበር የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሁሉ ለማቅለም በስልጣን ላይ ቂብ ያለው የአማራ ብሔራዊ ክልል እስልምና ምክር ቤት ግን የምታዩት ደብዳቤ ሰላማም ሰልፍ የጠየቁት ሰዎች በኃይማኖታችን በኩል የማይታወቁ በመንግስት በኩል እውቅና ያልተሰጣቸው የኃይማኖቱ ተከታይ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ያልተሰጣቸው ናቸው በማለት የፃፈ ሲሆን ደብዳቤውን ሲደመድምም 9 ገፅ ሙሉ ስም ዝርዝራቸውን አቤቱታ ፊርማዎቻቸው ጋር ያያዙትን ሙስሊሞች በሙሉ ሙስሊሞች መሆናቸውን የማናውቃቸው እና ሙስሊሞችን የማይወክሉ መሆናቸውን እንገልፃለን ብሎ ለመንግስት አሳልፎ ሰጥቷቸዋል ሱብሀን አላህ ቁርአን የሸንት ቤት በስውር የደህንነት አባላት ጥቅም ላይ ሲውል መታገል የነበረበት መከራከር እና ሰዎችን ለፍርድ ማቅረብ የነበረበት መጅሊስ አልነበረም ይሄንን ሁሉ ማድረግ ቢቀር እንኳን ተቋውሞአቸውን የገለፁ ሙስሊሞችን እስልምና እውቅና መንፈግ እና ማከፈር ከመናፍቅ እንጂ መቼ ከሙስሊም ይጠበቃል ይሄንን መሰል ምሳሌዎች የመጅሊሱ ታሪክ በጣም በርካታ ናቸው ሴት እህቶቻችን በዩኒቨርስቲ ሊጃብ እንዲያወልቁ ሲገደዱ አንዳችም ጊዜ መጅሊሱ ተከራክሮላቸው አያውቅም ይልቁንም በ 2001 በአሁኑ ፕሬዘዳንት አቶ አህመዲን ፊርማ በወጣው በእዚህ ደብዳቤ ላይ እንደምታዩት ከተማሪዎች ጀርባ በተሰከሰኩ ፅንፈኛ እና ወሀብያ ኃይሎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድልን በሚል ፖሊስ ኮሚሽን በሴቶች መብት የሚደረገውን ሕጋዊ እንቅስቃሴ እንዲያስቆም በአበክሮ ይጠይቃል ሕዝበ ሙስሊሙንም ያስመታል ትምህርት ሚኒስቴር ሙስሊም ተማሪዎችን የጀማ ሰላት እና ሂጃብ የሚከለክል መመሪያ ባወጣ ወቅት ጥር 26/2000 ዓመተ ልደት የተፃፈው ይህ የምትመለከቱት ደብዳቤ ለደህንንት ሚግሬሽን እና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን የተፃፈ ሲሆን በመጅሊሱ ምክትል ፕሬዘዳንት አቶ ኤልያስ ሬድማን የተፈረመ ነው ደብዳቤውን እንደምታዩት የትምህርት ሚኒስቴር አምልኮ መመሪያ አሁን ባለበት መልኩ እንዳይፀድቅ እንቅፋት የሆኑትን አካላት ይመለከታል ሲል የሚጀምር ሲሆን መመሪያውን የተቃወሙ ሙስሊሞች እና ጋዜጦች እርምጃ እንዲወሰድባቸው አጥብቆ ይጠይቃል ፅንፈኛ ፀረ ሰላም እና አክራሪ ሲል ይፈርጃቸዋል ደብዳቤው የተዘጋበትን የመጨረሻ አረፍተ ነገር መመልከቱ ደግሞ የድርጅቱ መሪዎች የቆሙለትን ፀረ እስልምና አቋም እና የባዕድ አካላት አገልጋይነት ፍንትው አድርጎ ያሳያል እንዲህ ይላል የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት መመሪያው እንዲተገበር የሚያደርገውን ያላሰለሰ ጥረት ዳግም እያረጋገጠ ከላይ በተጠቀሱት አካላት ላይ አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩን አጊዜው ካረጋጋን በኋላ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሰው ሲዘጋ ሲፀድቅ ሙስሊም ነው የሚል ፅኑ እምነት እንዳለው በተሀትና ይገልፃል ሱብሀን አላህ የመጅሊሱ መሪዎች የሕዝበ ሙስሊሙን መብት ለመሸራረፍ እና ለማዘናጋት በኢህዴግ መንግስት የተሾሙ ለመሆናቸው ከእዚህ የበለጠ ማስረጃ ከየት ይገኝ ይሆን ከአሁን ቀደም ከኃይማኖት መቻቻልን በተመለተ መንግስት ባዘጋጀው ስብሰባ ት/ቤት ኢጃብ ስለመልበስ ሲነሳ መጅሊሱ አለማዎቼ ናቸው ያላቸውን ሰዎች አስተባብሮ ኢጃብ እና የጀማ ሰላት በት/ቤት እንዲከለከል ለመንግስት አረንጓዴ መብራት ያበራ ሲሆን አለማ ተብዬዎቹ የሰጡት ምክንያትም ሳይንስ እና ኃይማኖት የተለያዩ ስለሆኑ ኢጃባቸውን አውልቀው ይማሩ እና ቤት ሲሄዱ ይልበሱ የሚል ነበር በእዚህ አስገራሚ ስብሰባ ላይ የመጅሊሱ ዋና ጋሽ አጃግሬ አንዋር መስኪዱ አስጋጅ ጣሀ ተገኝቶ የነበረ ቢሆንም አንዳች ሳይተነፍስ ተመልሷል ይህ የባዕዳን ቅጥረኛ የሆነው መጅሊስ የሚጠበቅበትን ስራ አለመስራቱ ሳያንሰው ሌሎች አካላትን ጭምር እንዳይሰሩ በማገድ የሚደርስበት የለም መጅሊስ መስኪድ አይሰራም ሌሎች ሲሰሩ ግን ለማሳገድ ይሯሯጣል /ግልፅ ያልሆነ/ ለማሳገድ እና ለማስባረር ይጥራል ት/ቤት አይገነባም ሌሎች ሲገነቡ ግን ይዘጉልኝ ብሎ አቤት ይላል መጅሊስ የእስላማዊ መድረኮችን አያዘጋጅም ሌሎች ሲያዘጋጁ ግን ያግዳል /ግልፅ ያልሆነ/አይረዳም ሌሎች ሲረዱ ግን ይበሳጫል የሌሎች ኃይማኖት ተቋማት በሺዎች የሚቆጠሩ ድርጅቶታቸውን እና ማህበራቶቻቸውን ከለላ ሆነው ሲያስጠልሉ መጅሊሱ ግን ለሙስሊሙ ብርቅ የሆኑትን 5 እና 6 የማይሞሉ ብቸኛ ድርጅቶች ለማዘጋት ይጥራል በአጠቃላይ ሲታይ መጅሊሱ በአመራሮቹ የፃፋቸው በርካታ የእግድ ደብዳቤዎች ተቋሙ የሙስሊሙን እጅ ለመጠምዘዝ እና ለማዳከም አበክሮ የቆመ መሆኑን በግልፅ ያሳያሉ ከጊዜ እጥረት አንፃር እንደምሳሌ ጥቂቶቹን ብቻ እናያቸዋለን ይህ ሰኔ 3/1994 በመጅሊሱ ፕሬዘዳንት ሼህ አብዱራህማን ሁሴን ሙሳ ተፈርሞ የወጣ ደብዳቤ እንደምታዩት የተፃፈው ከፍትህ ሚኒስቴር ሲሆን መልዕክቱም እስላማዊ ዳዋ እና እውቀት ማህበር እና ዳሩር /ግልፅ ያልሆነ/ የተባሉ እና ሌሎች ድርጅቶች ለምን ፍቃድ ተሰጣቸው የሚል ቅሬታ መግለጫ ነው በእነዚህ እና በሌሎችም ድርጅቶች ላይም ሌሎች የእግድ መጠየቂያ ደብዳቤዎች ተፅፈዋል ሱብሀን አላህ የእስላማዊ ድርጅቶች መስፋፋት ማን ይሆን ቅር የሚሰኘው ይህ በሰኔ 6 በተመሳሳይ ሰው የተፃፈው ደግሞ ሕገ ወጥ ኃይማኖታዊ ቅስቀሳ በሚያካሂዱ አካላት ላይ እርምጃ ይወሰድልን ሲል ከፈቃድ ነጠቃ ባለፈ ድርጅቶቹ እንዲዘጉ መንግስትን ይጠይቃል በ 1994 ዓመተ ልደት ከነሐሴ 3 እስከ 19 በተደረገው የመጅሊሱ ሰሚናር የወጣው ይህ የአቋም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መግለጫ ደግሞ በርካታ የኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በፀረ ሰላምነት ይፈርጃል እስላማዊ ጋዜጦችን ሁሉ አንድ ሳይለይም ሕብረተሰቡን የሚጎዱ ኃይላት መሣሪያ ሆነው ተገኝተዋል በሚል መንግስት ጠንካራ ቁጥጥር እንዲያደርግባቸው ልመናውን ያቀርባል ቀድሞውኑም ወንበሩ ላይ ያስቀመጣቸውን ኃይል አጀንዳ አላህን ሳይፈራ ያስፈፅማል ይሄኛው ደብዳቤ ደግሞ በነሐሴ 24/1998 በኤልያስ ሬድማን የተዘጋጀ ሲሆን በኢትዮጵያ ቅዱስ ቁርአን ድርጅት እና ሌሎችም ድርጅቶች መድረሳ እያቋቋሙ ስለሆነ ይዘጉልኝ የሚል መልዕክት ያለው ነው ይሄኛውንም የአማራ ብሔራዊ ክልል እስልምና ጉዳዮች ደብዳቤ ይመልከቱ በርካታ እንቅስቃሴዎችን እና ድርጅቶችን ስም በሀሰት ካጠፉ በኋላ በያዘው አቋም በብቸኛው የሙስሊሞች መንፈሳዊ ድርጅት እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የማይተዳደሩ እና እውቅና ያልተሰጣቸው በሙስሊም ስም የተሰሩ ሕገ ወጥ ተቋማቶች እንዲዘጉልን እንጠይቃለን በማለት የሙስሊም ድርጅቶች ሁሉ እንዲዘጉለት ይጠይቃል ከእዚህ ሁሉ ማን ይሆን ተጠቃሚው አቶ ኤልያስ ሬድማንም በአንድ ወቅት እስላማዊ ግብረሰናይ ድርጅቶችን አስመልክቶ የሚከተለውን ተናግሮ ነበር

- የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላቶች ደብዳቤ በተለያየ ወቅት ፅፏል /ግልፅ ያልሆነ/ በእርዳታ ድርጅት ስም እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ እየገባ እናዳለ እና በተለይ አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በስፋት እየተሄደ አላስፈላጊ ነገሮችን እየፈጠሩ እንዳሉ ገልፀናል
- የባዕድ ቅጥረኛው መጅሊስ ሰዎች ሀይር ስራ ሲሰሩ ያመዋል ይቆጨዋል ያንገበግበዋል ይህን በነሐሴ 16/1992 ለፖሊስ ኮሚሽን የተፃፈ ደብዳቤ ይመልከቱ በገነት ሆቴል ሊደረግ የታሰበውን ሀገር አቀፍ የቁርአን ውድድር በመቅረፅ ምክር ቤታችን የማያውቀው መሆኑን እየገለፅን በእዚሁ አጋጣሚ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ እንጠይቃለን ሲል ይደመድማል ሱብሀን አላህ እነዚህ የአላህ ቁርአን ሲቀራ የሚያቅራቸው ሙስሊም መሪ ነን ባዮች ከምን ይሆን የተፈጠሩት እርሶ በእዚህ ሁሉ ግር ይሎት ይሆናል ለምን ብለው ነው እንዲህ የሚያደርጉት የሚል ጥያቄ ለራስዎት ያቀርቡ ይሆናል ይህ እስከሪኑ ላይ የሚያዩት ደብዳቤ መልሱን ይሰጦታል ይኸው ጉደኛ ደብዳቤ ሐምሌ 23 ቀን 1985 በአንድ አወዛጋቢ የመጅሊስ አመራር ስም እና ፊርማ በሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የተፃፈ ሲሆን እንዲህ ይላል የእስልምና ጉባኤን ሕልውና ለመምታት ስል ባደረኩት ጥረት ተሳክቶልኝ ስልጣን ከያዝኩኝ በኋላ የኢትዮጵያ እስልምና ጠቅላይ ጉባኤን አፍርሼአለሁ ካፈረስኩኝ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን አክራሪ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሙስሊም ድርጅቶች ከመታሁ እና ካጠፋሁኝ በኋላ በጣም የሰቸገረኝ ቢኖር የመስኪድ አስተዳደሮች እና በተለይ አንዋር መስኪድ አስተዳደር ብቻ ስለሆኑ ለወደፊቱ ሁኔታ ፖለቲካ ከፍተኛ ችግር የሚፈጠር ስለሆነ ይሄንን ግለሰብ የሆኑትን ማለትም የአንዋር መስኪድ አስተዳደር ከአንዳንድ አክራሪ ሙስሊም ድርጅቶች እና ከአረብ አክራሪ መንግስታቶች ጋር ግንኙነት እያደረገ እና እየተጠናከረ ስለመጣ ይሄንን ታጥቀንበት በአዲስ መልክ ለማዋቀር እና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሙስሊማዊ ድርጅቶች ለማጥፋት በመንግስት ብርቱ ድጋፍ እና እገዛ እንዲደረግልኝ /ግልፅ ያልሆነ/ ይህ የጥፋት አላማ እንዴት እንደሚፈፅሙት ግራ የሚገባዎት ከሆነ ደግሞ ሐምሌ 2/1994 በሰሜን ሸዋ መጅሊስ የተፃፈው ይኸው ደብዳቤ የበለጠ ግልፅ ያደርግሎታል የፌዴራል እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ወሀብያዎችን ለማጥፋት ከመንግስት ጋር ስምምነት እንዳደረገ በመግለፅ ሚስጥሩ ተጠብቆ እንዲቆይ አደራ በማለት የሚጀምረው ይኸው ደብዳቤ እነዚህን ማለትም ወሀብያዎችን ለማጥፋት ጊዜው አሁን ነው አነግ አሊቲሀድ አክራሪ አሸባሪ እና አልቃይዳ ናቸው በማለት መንግስትን በማሳመን ድራሻቸውን ለማጥፋት ሁላችንም ግዴታችን በጥንቃቄ መወጣት አለብን በማለት ሊሰራ የተዘጋጀውን ታላቅ ወንጀል አላህዋክበር በሚል መፈክር ይደመድመዋል ሱብሀን አላሁ በጥቃቅን ልዩነቶች ምክንያት ሙስሊሞችን በሀሰት በአሸባሪነት በወንጀል ማሳሰር ለአንድ አማኝ እንደምን ተገቢ ይሆንለታል በ 2003 ሐምሌ ወር መንግስት እና መጅሊስ ባዘጋጁት የሀባሽ ማጥመቂያ ስልጠና ላይ አሁን የመጅሊስ ፕሬዘዳንት አህመዲን አብዱላሂ የአክራሪዎች መፈልፈያ አወሊያን አፈራርሰነዋል በማለት ሙስሊሙ ተቋመት መዘጋት ምን ያህል ደስታ እንደሚሰጣቸው በተግባር አሳይተዋል

- በእኛ በኩል በጠቅላይ ምክር ቤታችን ትልቁን የአክራሪ መፈልፈያ መድረክ አፍርሰናል /ግልፅ ያልሆነ/ ማዕከላቸው ፈርሷል
- እነዚህ ሁሉ መረጃዎች የሚያሳዩት መጅሊሱ ሙስሊሙን ለመጥቀም ሳይሆን ለመጉዳት በሚፈልጉ የባዕድ ቅጥረኞች እጅ እየተሾፈረ መሆኑን ነው በግቢው ውስጥ ስራ ኃላፊነታቸው ከሹፌርነት እና ከመሰል ስራዎች ያለለፈ ነገር ግን በዋነኛ የግቢው ፈላጭ ቆራጭ ሆነው የሚሰሩ እና አመራሮቹን እንደልብ እያስፈራሩ ፀረ ሙስሊም አጀንዳዎችን የሚፈፅሙ ደህንነቶች በግቢ ውስጥ ሲርመሰመሱ ለዘመናት ስንታዘብ ቆይተናል የድርጅቱ እውነተኛ መሪዎችም እነዚሁ ደህንነቶች እንጂ ሌላ አይደሉም ለ 7 ዓመታት ያህል የመጅሊሱ ስራ አስተዳዳሪ የነበረው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ደህንነት ታምሩ ስሙ በጣም ግልፅ በመውጣቱ በግምገማ ወደ ሱማሌ ክልል ተዘዋውሮ ዛሬ ውጥረት ሲበዛ ተመልሶ መምጣቱም የአደባባይ ሚስጥር ሆኗል ረጅም ጊዜ በተቋም ውስጥ ከቆዩ ደህንነቶች አንዱ መሐመድ ወርቁ አህመድ የተባሉ ግለሰብ አንዱ ነው ይህ ግለሰብ ከአቶ ኤልያስ ካቢኔ በፊት የመጅሊሱ ፕሬዘዳንት በነበሩት ሼህ አብዱራህማን ሙዳ ጊዜ የነበረ ሲሆን ሼሁ ቢሮ ስጡት የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው ተቋሙ ውስጥ ቢሮ እንዲሰጠው አድርጓል በቢሮ ውስጥም የራሱ ማህተም የነበረው ሲሆን እሱ ካልፈረመበት በስተቀርም ሌሎች ድርጅቶች ከፍትህ ሚኒስቴር ፍቃድ ሊያገኙ አይችሉም ነበር ዋናው የአስተዳደር ክፍል የማያውቃቸውን በርካታ ደብዳቤዎችን የሚፅፈው ይኸው ግለሰብ ነበር በወቅቱ በፖስተኛነት ይሰራ የነበረው አቶ ጀማልም የቅርብ ረዳቱ በመሆን ገና በመለማመድ ላይ እንደነበረ ይታወቃል ሼህ አብዱራህማን ሙዳ ሀጂ በሄዱበት ወቅት ይህ ሰራተኛ በተደጋጋሚ ከስራ በመቅረቱ ማንነቱን እና ዓላማውን የማያውቁ የመጅሊሱ ኃላፊዎች ማስጠንቀቂያ ይሰጡታል ይባስ ብለውም የሰውዬው የስራ ድርሻ የተቋሙ መደበኛ መዋቅር ውስጥ የሌለ በመሆኑ በአድ አካልን ኃላፊነት በመስጠት በሚል ሼህ አብዱራህማን ሙዳን በሌሉበት ይገመግሟቸዋል በእዚህ ተግባራቸው የተበሳጨው መንግስትም ወዲያውኑ ሁሉንም በማባረር በአቶ ኤልያስ ሬድማን ካቢኔ እንዲተኩ አደረገ ፕሬዘዳንቱ የደህንነት አማካሪ ተብሎ በቋሚነት ለወደፊትም ጭምር የተሾመው ይህ ኮማንደር ሙራድ የተባለ ግለሰብም በወረዳ 8 እና 10 የፖሊስ ኃይል አመራር የነበረ ሲሆን ለእዚሁ ዓላማ የመጅሊሱን ግቢ ከተቆጣጠሩ ደህንነቶቹም አንዱ ሆኗል ከተቋሙም ከፍተኛ ገንዘብ ሲመዘብር ቆይቷል የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ባልሆነችው ባለቤቱ እህት ስም ቤት የሰራ ሲሆን ከሌሎች ደህንነቶች ጋር በመሆን በሼር ለሕንፃዎች የጥበቃ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት አቋቁሟል በእዚሁ ድርጅት አማካይነትም በተለያዩ ሕንፃዎች ላይ ያሉ ቢሮዎችን እንደልብ ለመበርበር መቻላቸው አደባባይ የወጣ ሚስጥር ነው እኚህ ደህንነቶች መብታቸውን ሊጠይቁ የመጡ ሙስሊሞችን በመጅሊሱ ቢሮዎች ውስጥ በማገት እና በማስፈራራት እንዲሁም በመደብደብ ጭምር ሲያደርሱ የቆዩትን በደል ታሪክ ታዝባዋለች በገፆቿም ከትባ አስቀምጣዋለች /ግልፅ ያልሆነ/ ሙስና የእድገት ፀር ነው ሰፊውን ሕዝብ የጥቂቶች ጥቅም የመበዝበዝ ከፉ ልማድ ነው በባዕዳን የተጠለፈው ሞሪ ድርጅታችን መጅሊስ ግን ለአንድ ኃይማኖት ተቋም እጅግ አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ በሙስና የተጨማለቀ ነው ከኢህዴግ መዋቅር በግምገማ እና በስኳር ቅሌት የተባረሩ ሰዎች በገፍ የሚገቡበት ድርጅት ሲሆን

389 9034

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መሪዎቹም በተደጋጋሚ እንዲወገዱ ሲፈለግ የሚመዘዝባቸው ይኸው የሙስና በትር ነው ከአሁን ቀደም 5 ሚሊዮን ብር የማያወጣ ሕንፃ በ 17 ሚሊዮን ብር ገዝቼዋለሁ በሚል ማጭበርበር እና በሌሎችም የሙስና ክሶች ከስልጣን የተወገደው የኤልያስ ሬድማን ካቢኔ በሌሎች ሀገር አጥፊ ካድሬዎች የተተካ ሲሆን ይጣራ እና ለፍርድ ይቀርባሉ የተባሉት አቶ ኤልያስ እና ጀሌዎቹ ስንጥር እንኳን ሳያገኛቸው የሰላም ሕይወት እየመሩ ይገኛሉ በአንዱ ሙሰኛ ምትክ ሌላኛው የተራበ ሙሰኛ በሚፈራረቅበት መጅሊሳችን ውስጥ የሚሰሩ መሪዎች ያለፉት ሙሰኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ የማያደርጉበት ምክንያት ግልፅ ነው ለግበኔ ከሚል ስሜት የመነጨ ነው ለእዚያም ሲባል ነው ያለፈው አመራሮችን ለፍርድ በማቅረብ ፋንታ ሸልመው የሚያወጧቸው ጠቅላላ ጉባኤው በ 1997 ባደረገው ስብሰባ የተያዘው ይኸው ቃለጉባኤ እንደሚገልፀው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎቹ ስራ ሲለቁ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ከተስማሙ በኋላ የሚከተሉት የክፍያ መጠኖች ውሣኔ አግኝተዋል ለፕሬዘዳንቱ 75 ሺህ ለምክትሉ 50 ሺህ ለዋና ፀሐፊው 50ሺህ ለሌሎች ስራ አስፈፃሚዎች ደግሞ 30 ሺህ እነ አሊላሂ /ግልፅ ያልሆነ/ ምንም እንኳ አዲሱ የአህመዲን አብዲላሂ ካቢኔ ወደ ስልጣን ሲመጣ በሙስና የተባረረውን የእነ አቶ ኤልያስ ካቤኔ ለሕግ እንደሚያቀርብ ቃል ገብቶ የነበረ ቢሆንም ስልጣኑን ካደላደለ በኋላ ግን ወዲያኑ ክሱን በመተው እና የሽልማት ዝግጅት በማዘጋጀት ለአቶ ኤልያስ እና ሌሎች ስራ አስፈፃሚዎች 30 /30 ሺህ ብር የሸለመ ሲሆን እርቁን ላመቻቹት አንድ ግለሰብም 200 ሺህ ብር ስጦታ ሰጥተዋል የብዙዎች ለፍርድ ይቅረቡልን ጥያቄም በእዚያው ውኃ በልቶታል አዲሱ የአህመዲን አብዱላሂ ካቤኔም ቢሆን ሙስና እስከአንገቱ ድረስ የተዘፈቀ ሆኖ ተገኝቷል ተቋሙን የሚሾፍሩት ደህንነቶች እና መሪ ተብዬዎቹ ግለሰቦች የተቋሙ ሙስና ዋነኛ ምንጭ ከሆነው ቅዱሱ የሀጂ ጉዞ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ብሮችን /ግልፅ ያልሆነ/ ሲመዘብሩ ቆይተዋል የአላህን ቤት ለመዘየር ሕዝበ ሙስሊሙ አቅም እስካለው እንደማይሰስት የሚያውቁት የመጅሊስ ሙሰኞች ከአገልግሎቱ ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃሉ መሐመድ ኑር ከተባለው በጅዳ ከሚገኝ ዋነኛ የሙስና አመቻች ሰው ጋር በመተባበርም ብዙ ሚሊዮን ብሮችን አቅልጠው ያስቀራሉ የቤት ኪራይ እና ሌሎችንም አገልግሎቶች በመጅሊስ አመራር አባላት በማመቻቸት ከፍተኛ የምዝበራ ገንዘብ የሚካፈለው አቶ መሐመድ ኑር 6 ሚኒባሶች ሀገር ውስጥ ያለው መሆኑ ይታወቃል እነዚህን በርካታ ሰነዶች ቢመለከቱም ምን ያህል ሚሊዮን ብር በ 2003 /ግልፅ ያልሆነ/ እንደተመዘበረ በቀላሉ ይረዳሉ በተለይ በቤት ኪራይ በሚል አዲሱ

3190 7035

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መጅሊሱ በአንድ /ግልፅ ያልሆነ/ የተቀበለው ገንዘብ 15 ሺህ 943 ሲሆን መጅሊሱ መካ ካለው አከራዮች ጋር የተፈራረመው ግን በ 12 ሺህ 150 ብር ብቻ ነው ለውጡ 3793 ብር ሲሆን በ 5 ሺህ /ግልፅ ያልሆነ/ ቁጥር ሲባዛ 18 ሚሊዮን 965 ሺህ ብር ወደ ግለሰቦች ኪስ ገብቷል ማለት ነው መጅሊሱ ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በነፃ ያገኛቸውን ጥቂቶችም ከተጓገች በማስከፈል በርካታ ሺህ ብሮችን ደብዛቸውን ያጠፋ ሲሆን 50 ሣንቲም የሰራትን አንዳት እስቲከር በብር 300 በመሸጠም አንድ ሚሊየን 496 ሺህ 250 ብር አጭበርብሯል ይሄንን ሁሉ ገንዘብ አጭበርብረው እንኳ ያልበቃቸው የመጅሊስ ሙሰኛ አመራሮች ግን /ግልፅ ያልሆነ/ የአላህ ክብር መፅዋት የሚያደርጉትን የ/ግልፅ ያልሆነ/ ክፍያ በሕገ ወጥ መልኩ ከአንድ የሳውዲ ድርጅት ጋር በመዋዋል በዘመናት ኢትዮጵያዊያን ሀጂአጂዎችን ሲመዘብር በቆየው በአቶ አማን ሁሴን ፊርማ ከእያንዳንዱ ሀጂ ሀጅ 350 ሪያል ተቀብሏል በጎችም በፍፁም እንዳልታረዱ ብዙዎች በቁጭት ይመሰክራሉ ይህ ምስኪን ሕዝብ በእዚህ በግልፅ እየተመዘበረ እንኳን ጥሩ አገልግሎት አግኝቶ አያውቅም ከ 2003 ሀጂ መልስ መጅሊሱ ያደረሰባቸው በደል ያንገበገባቸው/ግልፅ ያልሆነ/ በአዲስ አበባ መጅሊስ ጥቅር ግቢ አቤቱታቸውን ለማሰማት ተገኝተው የነበረ ሲሆን በእዚህ መልኩ ብሶታቸውን ገልፀዋል

- የመጣን ቀን ኮሚቴዎች እራሳቸው ቆመው ከእኛ ጋር ለሉ አንድ እቃ ሊገባ ከለከሉን እኔ /ግልፅ ያልሆነ/ 3 ሻንጣዬን ከ 15 ሺህ ብር በላይ ጥዬ ነው ለእቤቴ አልቅሼ ለልጆቼ ልብስ አላገኘሁም ይኸው እስካሁን ድረስ እንዲህ ተቀምጬአለሁ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ ሙስባህ ለሀዲያ የገዛሁት ሙስባህ ለልጆቼ ለወዳጆቼ በአቅሜ የያዝኩትን ከ 15 ሺህ ብር በላይ ሻንጣዬ ቀርቷል እኔ ምንም ለመናገር አልቻልኩም በየቀኑ /ግልፅ ያልሆነ/ እነሱ ግን ተውት እና ሂዱ /ግልፅ ያልሆነ/ ጭነን እንልክላችዋለን ሂዱ አየሩ ሊነሳ ነው ብለው ለሉ ከምሽቱ እስከ 2 ሰዓት ተኩል አፋችን ደርቆ መነጋገር አቅቶን እንደዚያ ሆነን አልቅሰን
- /ግልፅ ያልሆነ/ ከራሱ ጋር ተከትሎ ይሄዳል ኮሚቴው አናውቃቸውም አላየናቸውም ችግራችን ለመንገር ማንንም አላገኘንም ብንነግራቸው መልስ አልሰጡንም የሰጡኝ መልስ እራሳቸው ያውቁታል ከመካ ሚና ካወጡን በኋላ አንድ መኪና አላገኘንም /ግልፅ ያልሆነ/ ካርዱላ አረፋ ጀምረን ሙዘሊፋ በእግራችን ከሙዘሊፋ ሚና በእግራችን ከሚና መካ በእግራችን የሰው ሀገር እንዲህ ያለ የለም መዲና ደግሞ በግል ለመሄድ አትሂዱ ወረቀት አንሰጣችሁም ያቺ የምትመለስ ገንዘብ አለች መስለኝ እሷን ለማግኘት ያየነው ስቃይ ይሄ አይደለም

391 7036

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እያንዳንዱ መኪና የኢትዮጵያ መኪና የናይጄሪያ ቁጥር 14 ቁጥር 20 ቁጥር እየተለጠፈበት የሀጂ ኮሚቴ እዚያ ኮሚቴ አንድ ሳይኖር የእኛ ሕዝብ ከምሽቱ 4 ሰዓት እና 5 ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ።! ቁጥር 20 ቁጥር 14 ቁጥር ተለጥፎ ናይጄሪያ ብቻ ይጓዝበታል ይሄ ከአንዱ አረብ መጥቶ ለምኖን አሁን መኪና በአስቸኳይ 30 መኪና ይመጣል ብሎ ሞተን እዚያ በመከራ ምንድን ነው ስንለው የእናንተ ሀጂ ኮሚቴ ድክመት ነው ጥለው ሄደዋል ማን ነው እዚያ ቦታ የሚያስተናግደን
- እኛ ስንገባ አንድም ጊዜ ሽንት ቤታችን አይፀዳም ክፍላችን አይፀዳም ምንጣፍ እያራገፍን ነው የምንኖረው መጥረጊያ እንኳን አልተሰጠንም ክፍሎቻችን እንድንዘጋ አይፈቀድልንም በእዚች በሀጂ አካባቢ ብዙ ጥፋት እንደጠፋ ብዙ ንብረት እንደጠፋ ተነግሮታል ሕዝቡ ያውቃል
- ተጓዦች እንዲህ ሲንገላቱ በቀን 200 ዶላር ወይም 3600 ብር አበል የሚከፈላቸው የመጅሊስ አመራር አባላት ግን በሚዘርፉት ገንዘብ ሌላ ለ 2 ወራት ያህል በመቆየት የአበል ገንዘባቸውን ያጠራቅማሉ በስልጣን ላይ ያስቀመጧቸው መንግስት ግን ይሄንን ሁሉ እያየ እና እየሰማ ለፍርድ አቅርቧቸው አያውቅም ይልቁንም የተቋሙ ሙስና ቀጥተኛ ተጠቃሚዎቹ የመንግስት ደህንነቶች እራሳቸው ሆነው ነው የሚገኙት አንዳንድ ታዋቂ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄንን የ 40 ሚሊዮን ብር ሙስና በበቂ ማስረጃ አጠናክረው ለመክሰስ በዝግጅት ላይ እያሉ እንጋለጣለን ብለው ከሰጉ ደህንነቶች በደረሰባቸው ማስፈራሪያ ምክንያት ለማቋረጥ ተገደዋል እኚህ አላህን የማይፈሩ መሪ ተብዬዎች መንግስት አውቆ ቢያልፋቸው አላህ የማይመረምራቸው መሆኑን ያስባሉን
- የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 27/2 ተከሣሾች ከተከሣሾቹ የ27 ቃል መረዳት የሚቻለው ይሄንኑ ነው ሲዲው አንድ ሰዓት ከ 4 ደቂቃ የሚፈጅ ነው በክስ ማመልከቻ እና ቀደም ብሎ በተሰሙ ማስረጃዎች ተደጋግመው ሲገለፅ እንደነበረው የተከሣሾች የረጅም ጊዜ እቅድ ምናልባትም በእነሱ አገላለፅ ከ 30 እስከ 40 ዓመት ባሉ ጊዜ ውስጥ እስላማዊ መንግስት ማቋቋም ይቻላል የሚል የረጅም ጊዜ እቅድ አለ ከእዚህ እቅድ በፊት ግን ሊደረጉ ስለሚገባቸው እስቴጆች መታለፍ ስለሚገባቸው ደረጃዎች በአህመድ ሙስጠፋ እና በካሚል ሸምሱ ገለፃዎች ይደረጋሉ በተለይም አህመድ ሙስጠፋ የኢትዮጵያ ሙስሊም እየደረሰበት ያለውን አስከፊ ጭቆና ይገልፃል ቀደም ብሎ በተጠቀሱ ሲዲዎች ከእዚያ ጋር በሚቀራረብ መልኩ ይሄንን የተጨቆነ ሕብረተሰብ ለአዓላማው የእኛ ዓላማ እንዴት መጠቀም እንችላለን

3192 2037

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በሚልም ያብራራል በእዚያ ባለፈም መፅሐፎትን እየዳሰሰ ማለት ነው መፅሐፎች ላይ ትንቱና ነው የሚሰጠው ሌላው ለሼሪያ ሊሞት የተዘጋጀ ሕዝብ አለን እና ይሄንን ሕዝብ እንዴት ሞብላይዝ እናድርግ እንዴት ወደ መሬት እናውርደውም እያለ ይቀጥላል ሌላው የሰው አይምሮ ሶፍትዌሩን እንሜንበት የሚፈለገውን አስተሳሰብ እንጫንበት ከእዚያ በኋላ ከጀግንነቱ በፊት ይሄንን አስተሳሰብ ጭነን እንቀጥል ይላል እንቅፋቶቹን እናስወግድ እንቅፋቶቹ የሚላቸው መጅሊስ እና መንግስትን እንደሆነ በምሳሌም ያስረዳል ቻሌንጆቹን ወደ እስላማዊ እንቅስቃሴ እንቀይራቸውም እያለ ይቀጥላል ማለት ነው ከእዚያ ባለፈ መልካም ባህሪ ማለት በእስላም ትህትና አይደለም በተለያዩ አካላት የሚደረገውን መከፋፈል እና ነፃነታችን በማወጅ እንፍታው አስተሳሰቡ ላይ ፎከስ እናድርግ አሁንም ደግመን እንደምንገልፀው በእኛ ግምት ምናልባት እነሱ ተምረው የመጡት የሙስሊም ብራዘር ውድ አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል ከእዚያ ጋር የሚመሳሰሉ ነገሮች ነው ሲያብራሩ የነበሩ የተከሣሾች የ 27 ቃልም ያንን ከእዚያ ጋር የሚጣጣም ነው ተቃውሞ እንደሚገጥመን ቀድመን እናስባለን ሆኖም ይሄንን ተቃውሞ እንዴት ገርስሶ ማለፍ እንዳለባቸው መከራ እንዴት መታገስ እንዳለባቸው 2ኛ ዜጋ ሆነው እየቀጠለ እንደሆነ ሙስሊሙ እዚህ ሀገር ላይ የሙስሊሙን የበታች ነን የሀገር ፍቅር የለንም እንዲህ እንዲህ መሰል አነሳሽ የሆኑት ነገሮችን ያደርጋል ሌላው ካሚል ሸምሱ ነው ካሚል ሸምሱ በተመሳሳይ እሱ በሚተቸው መፅሐፍ ላይ ያሉትን ኮንሰብቶች ለማስረዳት ይሞክራል 8 ደረጃዎች እንዳሉትም ያስረዳል እንቅስቃሴው እነዚህ 8 ደረጃዎችም አንድ በአንድ ስለሴንትራል አይዶሎጂ ሊኖራቸው እንደሚገባ ሶሀቢት እና ቋሚ ሶሀቢት ማለት ቋሚ እና ተለዋዋጭ እንትኖች ቫሊውስ ሊኖሩት እንደሚገባ ከእነዚያ እነዚያ ቫሊዎች ተዳምረው እነዚህ መከራን መታገስ እንዲህ የመሳሰሉ ነገሮችን ካለፉ በኋላ ለውጡንም ሲጀምሩ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደሚገጥማቸው በአሁኑ ሰዓት ሙስሊሙ መሪ እንደሌለው ሙስሊሙ ተጨቁኖ እንዳለ ተለፍልቆ እንደሚኖር ስለዚህ እንዴት እንቀስቅሰው እንዴት እነዚህን ጭቆናዎች ለዓላማችን እንዲሰለፍ እናብቃው እያለ ያስረዳል ከእዚያም ባለፈ አቅም ካለን ወደ ጦርነት እንገባለን አቅም ከሌለ ወደ ጦርነት ወይም ወደ አቢዮት አቅም ከሌለ ደግሞ ከሌለ ደግሞ ከእዚያ መለስ ያሉ እንደፖሊቲካል ኢንተርፌረንስ ሲቪል ሲስአቢዲየንስ የመሳሰሉ ትግሎችን ማድረግ እንችላለን በመሆኑም ለለውጥ እንነሳ እያለ ይቀሰቅሳል ሚናችን መለየት አለብን የለውጥ አራማጆች የለውጡ ተግባሪዎች እና ለውጡን ተረክበው እስከእስላማዊ መንግስት ሊያደርሱ የሚችሉ

http://ethcriminalawnetwork.com/

የመጨረሻዎቹን ደረጃዎች ያብራራል በእዚያ ባለፈም የእዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ የመጨረሻ ግብ እስላማዊ መንግስት እንደሆነ ካሚል ሽምሱ እራሱ በቃሉ እያረጋጠ ይገልፃል ማለት ነው በመሆኑም ከሞላ ጎደል አሁን የሚቀርበው የቪዲዮ ማስረጃ ይሄንን ጭብጥ የሚያስረዳ ነው

- ይቀጥል ከመጀመሪያው ሲዲው ከማን እንደተገኘ እና መቼ እንደተገኘ
- ሲዲው ከማን እንደተገኘ አሁን ንግግር 2ቱ ተከሣሾች ካሚል ሽምሱ እና አህመድ ሙስጠፋ ስልጠና ወሰዱ ተብሎ የተገለፀው እና በ 90 ዎቹ ውስጥ ነው በ 98 ውስጥ ነው በ 1998 ውስጥ ነው ተከሣሾች የተከሰሱት ግን ከ 2001 ጀምሮ ነው ስለዚህ ይሄንን ንግግር 1ኛ የት ተናገሩ ለማን ነው ከተከሣሾች ጋር ያለው ግንኙነት የሚመለከተው 2ቱን ብቻ ነው ወይስ አጠቃላይ ተከሣሾችን የሚሆነው ግልፅ ስላልሆነ ነው ንግግር አደረጉ የሚለውን ተከሣሾች ባሉበት ነው ከእዚያ በፊት ነው ሌላ ቦታ ነው የሚለውም ነገር ግልፅ ስላልሆነ ይሄ በዐቃቤ ሕግ በኩል እንዲገለፅ ቢደረግ ለማለት ነው
- እሺ ዐቃቤ ሕግ
- 2 ጥያቄዎች ላይ ነው እንግዲህ የተያዘውን ማስረጃው የሚመለከተው 9ኛ እና 4ኛ ተከሣሾችን እንደሆነ እነሱ ንግግር እንደሚያደርጉበት ግልፅ ነው ከእዚያ ባለፈ ደግሞ ሲዲው ላይ የተፈረመው ፊርማ እንደሚያሳየው ከ 24ኛ ተከሣሽ ከሀሰን አቢ የተያዘ መሆኑን የሳያል ከእዘ የ ባለፈ ግን ለማን ነው ንግግር ያደረጉት ምናምን በሚል የተነሱት ከጠበቃው የተነሱት መቃወሚያዎች በተመለከተ ይሄንን እኛ ልናውቅ አንችልም ያው ለወጣቶች እንደሆነ ከንግግራቸው ያስታውቃል በምስል ነው ካሜራው ዞሮ ያሉትን ሰዎች ሁላ ካልቀረፀ እኛ ማወቅ በጣም ነው የምንቸገረው እና ግን ለወጣቶች እንዲህ አድርጉ እንዲህ ይሁን እያሉ በእዚያ መልኩ ትምህርቱን ኢንተረዲዩስ ሲያደርጉ እንደነበር ያሳያል
- ከላይ ያለውን አስተያየት ስጥቷል ከእዚህ የበለጠ ደግሞ ከማስረጃው የሚሰማ ስለሆነ ይቀጥል ተብሏል
- /ግልፅ ያልሆነ/ ያው የመጀመሪያው መፅሐፍ /ግልፅ ያልሆነ/ የኢስህባ በምሳሌ ሲገልፁት ሰው ከእንቅልፉ ልክ ሲገባ ያለው ባህሪ ነው ማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ የሚታየው በእስላማዊ እንቅስቃሴ ይሁን በሌላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ ከእንቅልፉ እንደተነሳ በደንብ አይታየውም ከተለያዩ ነገሮች ጋር ይጋጫል ግን በተጋጨ ቁጥር ይነቃል እና እንቅስቃሴዎቹ ተመሳሳይ ባህሪ ነው ያላቸው ገና ሲነሱ አንድ ነገር ይታየዋል ብዙ ነገር አይታየውም የመደናበር የመጋጨት

http://ethcriminalawnetwork.com/

ትክክል ያልሆነ አካሄድ ይፈጠሩ እና እነዚህ ግጭቶች እንዲነቃ እና ሁሉ ነገር በትክክል ማየት እንዲችል ያደርጉታል ይሄንን ከሳህባ ወደ /ግልፅ ያልሆነ/ ለመቀየር የሚያስችሉ ወይም ደግሞ መቀየር የሚፈልግ ማንኛውም ሕብረተሰብ ሊያውቃቸው የሚችሉ ነጥቦች ናቸው እዚህ ላይ የሰፈሩት ቅድም ለማንሳት እንደተሞከረው እዚህ መፅሐፍ ላይ ዋና ትኩረት የሚያደርገው ከሰው /ግልፅ ያልሆነ/ እንዲኖረን ለማድረግ ከእዚያ በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/ መንቀሳቀስ እንድንችል ነው የሰው አይምሮ ልክ እንደኮምፒዩተር ይመስላል አንድ ሶፍትዌር ከጫንክበት ከእዚያ አንፃር ነው ነገሮችን የሚተረጉመው ወይም ደግሞ ሊሰጥ የሚችለው ውጤት እና ኡማው ላይ ያልተጫነ ሶፍትዌር አለ ይሄ ሶፍትዌር ካልጫነው ወደ ኤርትራ መሄድ አንችልም እና ይሄንን /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ አይምሮ ኮንሸስ እና ሰብኮንሸሳችን ውስጥ ያሉ ነገሮችን ተንቢይ ማድረግ ለምንፈልገው ዓላማ ወይም ደግሞ በምንፈልገው መልኩ ሰዎችን መቅረፅ ውጤታቸውን ማግኘት እንድንችል መጫን ያለባቸው ነጥቦች አሉ መረዳት ያለብን አስተሳሰቦች አሉ ይላል ከምንም ነገር በፊት በፊትም አለማዎች የሚሉት ነገር አለ ብሎ ይገልፃል አራእዩ /ግልፅ ያልሆነ/ ከጀግንነት ከጀግኖች ጀግንነት በፊት ትክክለኛ የሆነ አመለካከትና አስተሳሰብ መኖር አለበት መፅሐፉ ሰዎችን በ 4 ከፍሎ ያያቸዋል 1ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ ዲን የሚወድ እስላማዊ እንቅስቃሴ የሚወድ እና በስሜት የተሞላ ሰው አለ ግን ይሄ ሰው ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ቁጭ ብሎ ነገሮችን በእውቀት በፈህ ዲፐሊ ነገሮችን ማየት እና ማስተንተን አይወድም በቃ እንቅስቃሴ ብዛት ያለው ሰው ያለበት ቦታ የመድረክ ውይይቶች ምናምን እንደዚህ ነገር ነው የሚያምሩት 2ኛው ሰው /ግልፅ ያልሆነ/ ትንሽ ለማንበብ ይሞክራል ከእዚያም ከእዚህም መፅሐፍ ይቀራምታል በባህሪው ይህ ሰው /ግልፅ ያልሆነ/ ብዙ ነገር ይተቻል ትንሽ አንብቧል እንቅስቃሴዎች ኃሳቦች ሲመጡ መተቸት ነው በተግባር ስታየው ግን ምንም አይሰራም እና በመተቸቱ ብቻ የሚጠግብ አለ ልክ የሰራው ያህል ሳትስፋይድ የሚሆን አለ ችግሮቹንም በመተቸት የፈታቸው የሚመስለው አለ እና ሕብረተሰቡን ካለበት ችግር ሊያወጣ የሚችሉ ኃሳቦች ሲመነጩ እሱ ከኃሳቦቹ በላይ ሆኖ ይተቻል እና በእዚህም የሆነ የሚሰማው ፕራውድ አለ በቃ እዚህ ጋር ይቆማል ይሄ ሰው 3ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ ነገሮችን ክሪቲካሊ ያያል ያያቸውን ነገሮች ከጥርጣሬ ተነስቶ ውሣኔ ላይ ከመድረስ ያንኑ በጥልቀት ለማንበብ ጉዳዩ እውነታው ላይ ለመድረስ ጥረት ያደርጋል ከእዚያ የአቅሙን ያህል ለመስራት ይሞክራል 4ኛው ሰው ከእዚህኛው ቀረብ ያለ ነው ከመጀመሪያው ከአንባቢ ደግሞ የተወሰነ ባህሪ 2ቱን ሼር

http://ethcriminalawnetwork.com/

ያደርጋል ያገባል ይመራመራል ግን አንተናቹ ኃሳቦቹ ካለው ተጨባጭ ጋር መሄዱ አድርጎ በቃ አይዲያ /ግልፅ ያልሆነ/ አይነት ነገር ይሆናሉ እና እንዲህ ዓይነት ሰዎች አሉ ባለንበት ተጨባጭ ከሳህባህ /ግልፅ ያልሆነ/ መቀየር 2 ነጥቦች ያስፈልጉናል ብሎ ያምናል 1ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ ነው 2ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ የእውቀት ክፍል አለ ከእዚያ በኋላ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ከ 2 አንዱ ከጎደለ የምንመኘው ላይ መድረስ አይቻልም አንዳንድ ጊዜ እውቀት ሳይኖር ስራዎች ይሰራሉ ይሄ በራሱ ተመልሶ እኛኑ ነው የሚጎዳን በሌላ ጊዜ ደግሞ እውቀቱ ይኖራል ስራ ላይ ይዳከማል እውቀትን እና ስራን አንድ ላይ ማቀናጀት ከቻልን ይሄ 2 መሠረታዊ የሆኑ ጃኒቦች ናቸው ብሎ 2ቱን በሚመለከት የማነሳቸው ነጥቦች አሉ በእዚህ ከታብ ላይ ለማንኛው እንቅስቃሴ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ነጥቦችን ያብራራል /ግልፅ ያልሆነ/ ለምሳሌ ፕሮጀክት ሲባል እንስማለን ደቨሎፐመንት ሲባል እንሰማለን /ግልፅ ያልሆነ/ እንሰማለን ሲቪላይዜሽን እንሰማለን ሜክአይዶሎጂ አይዶሎጂ ፓራዳይም እንደዚህ ሲባሉ እንሰማለን እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው እስላማዊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ሰው እነዚህን ነገሮች ማወቁ ኢንፖርታንስ አለው ብሎ ስለሚያምን እነዚህን ነገሮች ያስረዳል /ግልፅ ያልሆነ/ ሬሰሳንስ ሲባል ምን ማለት ነው ምን ዓይነት ባህሪ አለው ወደ ሬሰሳንስ ለመሄድ ምን ምን ያስፈልጋሉ ሀባራ ሲቪላይዜሽን ሲባል ምን ማለት ነው ሜክአይዶሎጂ አይዲዮሎጂ እና እነዚህ ፓራዳይ ኢንፓራይዳይ ሽፍት ሲባል እስትራቴጂ እነዚህን ቃላቶች በጥሩ ሁኔታ ያብራራቸዋል በመቀጠል /ግልፅ ያልሆነ/ የሊደር ባህሪያቶች የሚያስፈልጉት ነገሮች ምንድን ናቸው /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ ፕሮጀክት ስኬታማ እንዲሆን የሚያስፈልጉ የግድ መሆን ያለባቸው ምንድን ናቸው የሚለውን /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ ማንኛውም ሀገር ወይ /ግልፅ ያልሆነ/ ሲቪላይዜሽን ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት የሚያልፋቸው ነጥቦች አሉ እና እነሱን ያሳያል ለምሳሌ ሳህባህ የመጀመሪያው ነው እንደምታዩት ሀማሱ በጣም ከፍተኛ ነው ሩስዱ ዝቅተኛ ነው እውቀቱ ነገሮችን የማየት ኃይሉ በጣም አነስተኛ ነው ከእዚያ ወደ/ግልፅ ያልሆነ/ ሲመጣ ሙቀቱ እና ሩሽዱ ፓራራል ናቸው ዲያሬክትቲ ፕሮፖርሽናል ናቸው አንዳንዴ ምን ይፈጠራል ሰዎች ሳህዋ ላይ እየነበሩ በጣም ሀማስ ይኖራቸው እና ከእዚያ ወደ ምን ይመጣሉ ሩሽድ ማግኘት ሲጀምሩ ሀማሳቸው ዲክላይን ያደርጋል እና ሩሽዱ ያላቸው እቤታቸው ይቀመጣሉ እና አዲስ ሀማስ ይዘው የተነሱ ሰዎችን ይተቻሉ እነዚህ እንደው እኛ ተሳስተን ያለፍነውን ነገር ብለው እነሱን ይተቻሉ እና እንዴት ነው ከሳህዋ ሰዋህ ሀማሱ ሳይቀንስ /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ናህባ መምጣት የሚቻለው ከናህባ እንዴት ነው ወደ ሀባራ

3/96

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲቪላይዜሽን መግባት የሚቻለው የሚለውን አጡዋር አረከትን ህባራ በሰፊው ያብራራል /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ናቸው ከሳህዋ /ግልፅ ያልሆነ/ መሰራት ያለባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው እና እዚህ ላይ አንድ የሚለው ነገር አለ /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ሙስሊሙ ሕብረተሰብ /ግልፅ ያልሆነ/ በጣም አንገብጋቢ በሆነ ወቅት ላይ ነው ያለችው የቀባ ከሳህባህ ወደ የቀባ ለመሄድ በጣም አንገብጋቢ ወቅት ላይ ያለው ሙስሊሙ ኡማ ለምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ 30 ሚሊዮን በላይ ሙስሊም አለ ከእዚያ ውስጥ ምን ያህል ሚሊዮን /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚያ ውስጥ ምን ያህሉ ለዲን አስተዋፆ ለማበርከት የሚፈልግ አለ ይሄ ሁሉ ጣቃ ባክኗል እና ይሄ ሙባረክ የሆነው ብንጠቀምበት ብዙ ፍሬ ሊያፈራ የሚችለውን ጣቃ መጠቀም እንድንችል /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ተጠናና እና ወደ ተሰላ በሆነ መንገድ ለምን እንዲያገለግል አድርገን ለናህ ሲቪላይዜሽን /ግልፅ ያልሆነ/ በሚያገለግል መልኩ እንድንጠቀምበት ኡማው /ግልፅ ያልሆነ/ የሚያስፈልገው በጣም አንገብጋቢ ወቅት ላይ ነው ያለው ይላል ይሄንን በሚመለከት ማብራሪያዎችን ያደርጋል ሌላ በእዚህ መፅሐፍ ላይ የሚገለፁት /ግልፅ ያልሆነ/ በእዚህ በመርሀ ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ግባቸው ምን መሆን አለበት ለእያንዳንዱ መርሀ ላይ የራሱ የተለያዩ ግቦች አሉት እና ሕብረተሰብ ወደ ሳህባ ወደ ኢቀዳ ሲቀይረው ሀደፉችን ምንድን ነው መሆን ያለበት /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄንንም በማመለት /ግልፅ ያልሆነ/ ያብራራል ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ ማን ናቸው በእዚህ ከሳህባ ወደ ኢቀዳ በሚደረገው ለውጥ ማንን ነው ማካተት ያለበት የሚለውን ይመልሳል /ግልፅ ያልሆነ/ 3 መሠረታዊ አስፈላጊቶች አሉ /ግልፅ ያልሆነ/ የቀባ ላይ ምን ምንድን ናቸው ዋና ኢንፖርታት ነገር መደረግ ያለባቸው የሚለውን ያነሳል ከሳህባ ወደ ኢቀዳ ትራንስፈር ስናደርግ /ግልፅ ያልሆነ/ ስናደርግ ፖሊሲአችን ምንድን ነው መሆን ያለበት የሚለውን ያብራራል ከእዚህ በኋላ መፅሐፉ የአስተሳሰቦች ኡደትን ሊያስተካክሉ የሚችሉ እና ለለውጥ እንቅፋት የሆኑ ነጥቦችን ሊያርሙ የሚችሉ ትምህርቶችን በሰፊው ይሰጣል የሙስሊሙ ኡማ የአስተሳሰብ /ግልፅ ያልሆነ/ ወይም ፓተርአፍ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚሉትን ችግር አለ የአስተሳሰብ ኡደታችን ወይሞ ደግሞ የአስተሳሰብ ፍሰታችን ችግር አለው ይሄንን ፍሰት ሊያስተካክል የሚችል ነገር እና ለለውጥ እንቅፋት የሚሆኑ ደግሞ እምነቶች ይዘናል እስላማዊ ያልሆኑ ከምንጫችን ያልፈለቁ በተለያዩ ምክንያቶች እኛ ውስጥ ስርፀው የገቡ ለለውጥ እንቅፋት የሆኑ አስተሳሰቦች አሉ እነሱን ደግሞ የማያርሙበት እንቅን ያነሳል ከእዚያ ውስጥ የመጀመሪያው /ግልፅ ያልሆነ/ ብሎ ይጀምራል ይሄ ብዙ ጊዜ የምናውቀው ነገር ነው /ግልፅ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያልሆነ/ ቢባል ብዙ ጊዜ የሚመጣብን /ግልፅ ያልሆነ/ እነዚህ መቅራቶችን ኤልም የምንላቸው እነዚህን ነገሮች ናቸው ግን ከእዚህ ዘለንም አልፈንም መሄድ አለብን /ግልፅ ያልሆነ/ የምንሰራውን ስራ ከመስራታችን በፊት ማለት ነው እስላማዊ እንቅስቃሴ ከሆነ የምንፈልገው /ግልፅ ያልሆነ/ እስላማዊ እንቅስቃሴ አይደረግም ሰፊና የራሱ የሆነ ክብር አለው የራሱ የሆነ ጥቅም አለው ያንን ለማሳነስ አይደለም ግን ልንሰራ የምንፈልገው እና የምንማረው የተለያየ መሆን የለበትም ይሄንን በሚመለከት /ግልፅ ያልሆነ/ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ እና የእዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ አለመኖሩ የሚፈጥረውን ፕሮብሌም በሰፊው ያስረዳል /ግልፅ ያልሆነ/ እውን ለማድረግ የሚያስፈልጉ 2 ነጥቦች አሉ ይላል 1ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ ሀሪጃ ማለት ማንኛውም ነገር ለምሳሌ ውኃ ከቀዝቃዛ ወደ ሙቅ ለመቀየር ልትቀየር የመጨረሻው ፖይንቷ አለች ክሪቲካል ፖይንቱ ማለት ነው ይሄ አንድ ነገር ግሎ ግሎ ሊፈነዳ ዲፈረንሷ ትንሽ ነች ያንን ነገር የሚያደርስ ክፍል ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ /ክሪቲካል ፖይንት /ግልፅ ያልሆነ/ ምን ለማለት ነው ሬለሳንስን ለመፍጠር ከእውነትም ይሁን ከብዛት አንፃር የሚያስፈልገው የሰው ብዛት እና እውቀት አለ ያንን እስካላሟላን ድረስ ከሳህባህ /ግልፅ ያልሆነ/ መቀየር አይቻልም እና ከሳህባህ ወደ ኤቃዳ መየቀር የሚችል ኃይል ከብዛትም አንፃር ከብቃትም አንፃር ማድረስ ይፈልጋል ስለዚህ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ከሳህባ ወደ ኤቀዳ ለመቀየር ምን ያህል የሰው ኃይል ያስፈልገናል በምን በምን ሙያ ብቃት ያለው ያስፈልገናል ብለን ይሄንን ማሟላት መቻል አለብን ይሄ ሲሟላ /ግልፅ ያልሆነ/ ደርሷል ይባላል 2ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ 2ኛው ነገር ከብዛትም ከሙያም አንፃር ይሄንን /ግልፅ ያልሆነ/ ለማስገኘት እንቅፋት የሆኑ ነገሮች አሉ እነዚህን ነገሮች ማስወገድ የኢኮኖሚ ሊሆን ይችላል ኩትላህሊጃው ላይ ለመድረስ በጣም ብዙ ማስተማር ያለብን ሰው ይኖራል በጣም ብዙ ገንዘብ ማውጣት ይኖርብናል ኮሌጆችን ዩኒቨርስቲዎችን ት/ቤቶችን ማስፋፋት ይኖርብናል ገንዘብ ከሌለን ይሄ አውድ ነው እንቅፋት ነው እና እነዚህን የምናስወግድበት አሊያም ደግሞ ይሄንን ኩትላህሊጃ በምንፈልገው ብዛት ልንሰበስበው የተለያዩ እንቅፋቶች ሊኖሩብን ይችላሉ የመጅሊስ ሊሆን ይችላል የመንግስት ይሆናል የተለያየ ነገር ሊሆን ይችላል እነዚህን /ግልፅ ያልሆነ/ ማስወገድ እነዚህን 2ቱን ስናስገኝ/ግልፅ ያልሆነ/ ሳይንስን እውን ማድረግ እንችላለን ይላል ቀጥሎ /ግልፅ ያልሆነ/ እስላማዊ የተለያዩ ሙቭመንቶች የራሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/ አላቸው እና ወደ እስላማዊ ስንመጣ ምንድን ናቸው መደረግ ያለባቸው እነሱም በእዚህ መልኩ ያስቀምጣቸዋል መ[illegible] /ግልፅ ያልሆነ/ እዚህ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ላይ መዘመት ያለበት ትምህርቶች መበጠተ ያለባተው አቂዳ ሲባል ኢብን እና ያለን አስተሳሰብ ጨምሮ መስተካከል ያለባቸው ነጥቦች ይኖራሉ ይሄ የመጀመሪያው መሠረታዊ ነገር ነው ከእዚያ በኋላ ማህበረሰቡ ኤባዳ የሚመለከቱ በዋኢፍ ናቸው ይሄ መስተካከል አለበት ቀጥሎ ደግሞ ስነ ምግባሩ በሰፊው ስነ ምግባር ማለት ትሁት መሆን ፀባየኛ መሆን ማለት አይደለም /ግልፅ ያልሆነ/ ማለትም በእስላም ፀባየኛ ማለት አይደለም /ግልፅ ያልሆነ/ አሳምሮ ነገሮችን መስራት እና ሱሉኩ መስተካከል አለበት እነዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ እነዚህ ነገሮች ላይ ስራዎች መስራት ይኖርባቸዋል ከእዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ በእኛ ተጨባጭ እስከእዚህ ድረስ ባሉት ልንሰራቸው የምንችላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው ይሄ ስንል ምንድን ማለታችን ነው እንዴት ልናስገኘው እንችላለን የሚሉትን በሰፊው ያብራራል ቀጥሎ መፅሐፉ /ግልፅ ያልሆነ/ ብሎ /ግልፅ ያልሆነ/ ከሳባህ ወደ ኤቀባ እንድንወጣ ከሚያደርገን ነገር አንዱ ታህዲያት ነው ወይም ደግሞ ቻሌንጆች ናቸው በሌላ አስተሳሰብ ቻሌንጅ ከሌለ ይፈጠራል ችግር ከሌለ በእዚያ ሕብረተሰብ ላይ የሚያስደነግጠው ነገር ከሌለ መፈኪሮች የሚባሉት ወይም ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚባሉት ለሕብረተሰቡ የሌለ ችግር ያወሩለታል ለምን ሕብረተሰቡ ደንግጦ ጣቃውን ማውጣት ስላለበት እኛ ግን እንደጥሩ ነገር የሚጠቀሰው በጣም ብዙ የሆነ ውስጣችን ያለውን ጣቃ ሊየወጣ የሚችል ታህዲያት አሉበት ቻሌንጆች አሉበት እነዚህን /ግልፅ ያልሆነ/ ብሎ ያስቀምጣቸዋል እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው ነኛው ተኸሉፍ ሲል ምን ማለቱ ነው ምናምን ለብቻው አብራራዋለሁ ተኸሉፍ አለ ቀጥሉ ኢስቴማር አለ በአካልም ይሁን በአስተሳሰብ እቴማር አለ ከእዚያ ትፍቲት አለ ኮሌኔዛዬሽን ቅኝ ግዛት በቅኝ ግዛት ዋቅባችንን ወይ ደግሞ ሀገራችን ይይዙታል አለም ያለው ቅኝ ግዛት እንዲቀር ሲደረግ እንደእስትራቴጂ የታሰበው ምንድን ነው ለአፍሪካዊያን ወይም በቅኝ ግዛት ለተያዙ ሀገሮች ተብሎ አይደለም እነዚህን ሰዎች ሀገራቸው ሆነው ስንገዛቸው እንደሰብአዊነታቸው እኛን በጠላት ኃይል የማየት ሁኔታ አለ ወይም ደግሞ ልንዘልቀው ስለማንችል አይምሮአቸውን መግዛት ነው የተሻለ አማራጭ ብለው ነው በባህሪ በአስተሳሰብ መግዛቱ የተሻለ ነው ብለው የተቀየረው እና በአካል ያልተገዙ ሀገሮች ካሉ በአስተሳሰብ ተገዝተዋል /ግልፅ ያልሆነ/ አለ ቀጥሎ የሙስሊሙ ኡማ መሠረታዊ ፕሮብሌም ተፍቲት ነው አንድ የነበረ አማ በአንድ ኸሊፋ በ 1924 ድረስ ሲመራ የነበረ ኡማ ቆራርሰው ቆራርሰው አሁን በምናየው መልኩ አስቀምጠዋቸዋል ከእዚያም አልፈው ደግሞ በአስተሳሰብ እያንዳንዱ ሀገር እየገቡ ሰዎች 20 /30

http://ethcriminalawnetwork.com/

ጀማ እየሆኑ እርስ በእርስ እንትን ይላል ይከፋፈላሉ ይሄ ተፍቲት /ግልፅ ያልሆነ/ የሚሰራ ነገር ነው በሙስሊሞች ደጋፊነት እና ተግባራዊነት የሚሰራ በካፊሮች አስተሳሰብ ማለት ነው እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ተኸልፎአችንን ወደ /ግልፅ ያልሆነ/ መቀየር አለብን /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ታሪር ነፃነታችን ልናውጅ ይገባናል ተፍቲቱን ደግሞ ወደ ዋህዳ ልንቀይረው ይገባል ብሎ እነዚህን በሚመለት ያስተምራል ተኸሉፍ ማለት ምን ማለት ነው ኢስተማር ማለት ምን ማለት ነው ተፍቲቱ እንዴት ተፈጠረ ከእዚያ ወደ ዋህዳ እንዴት ልንመጣ እንችላለን ወደ ታህሩር ወደ ናህባ እንዴት ልንመጣ እንችላለን የሚሉትን ያስረዳል ቀጥሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ከምንድን ነው እሺ የምንጀምረው ተኸልፍ ነው እስተመር ያመጣው ወይስ እስተመሩ ነው ተኸልፍ ያመጣው እስተመሩ ነው ተፍቲት ያመጣው ወይስ ተፍቲቱ ነው እስተመር ያመጣው ከየትኛው ብንጀምር ነው መፍትሔ የሚሆነው የሚለው እነዚህን ነገሮችን ያብራራል ሌላ ያው መሀይር /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ ማህበረሰብን የምንመዝንበት ነጥቦችን ብሎ እነሱን ይገልፃል ፖለቲካ አለ ኢኮኖሚ አለ ሶሻል ጉዳዮች አለ /ግልፅ ያልሆነ/ አለ ሪሰርች የመስራት ብቃቱ ከእዚያ በኋላ ደግሞ የማምረት ብቃቱ ያመረተውን ነገር ደግሞ የመጠቀም ብቃቱ እነዚህን ያው መመዘኛዎች ናቸው እነዚህ እንዴት እንደሆኑ ያያል ሌላ ደግሞ 3 አለሞችን ያያል አለዋአል /ግልፅ ያልሆነ/ አውጥቷል አለም ለአፍካር አለም /ግልፅ ያልሆነ/ አለም ለአሺያ የምናያቸው አሁን ነገሮች አለም ለአሺያ ይባላሉ ይሄ ቤቱም ነገሮች በሙሉ አለም ለአሺያ ናቸው አለም ለአሺያ የምን ውጤቶች ናቸው የአለም ላፍካር ውጤት ናቸው እና እንትን ላይ ጆይሽ ኮንስፓረሲ ላይ ካነበባችሁት አለም ላይ መምራት ያለብን እኛ ነን ለመምራት የምንችለው ደግሞ አይዲያ ላይ ፎከስ ካደረግን ነው ያ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎች አይዲያ ላይ ትኩረት እንዳያደርጉ ማድረግ ስንችል ነው ይላሉ ሌሎች ሰዎች በአስተሳሰብ ላይ ትኩረት አድርገው ኃሳባቸው ውውይታቸው እዚያ ላይ እንዳይሆን መደረግ ያለበት በአልም ላሽባስ እና በአለም ላሺያ ቢዚ ማድረግ ነው ከእዚያ ውስጥ ኳሱ ሙዚቃው ፊልሙ ምናምን ሁላ ሰዎችን ከአለም ላከፋር ለመውጣት ተብሎ የተደረገ እና እና አሁን በእስላማዊ አስተሳሰብ ስትወስዱ አንዳንድ ስብስቦች ከአለም /ግልፅ ያልሆነ/ አይወርዱም አይዲያ ዲስከስ ማድረግ አይችሉም አለም ላሽካስ ላይ ነው እከሌ እንዲህ ነው እከሊት እንዲህ ነች እንጂ ይሄ የሕፃናት አለም ይሉታል 2ቱን አለሞች አዋቂዎች ቁም ነገሮች አለም ለአፍካር ላይ ነው ያሉት ይሄ አስተሳሰብ ጎጂ ነው ወይስ ጠቃሚ ነው አሁን ያለንበት ተጨባጭ ምንድን ነው አፍካር አስተሳሰብን የሚመለከት ነው የሚወያዩት እና እነዚህ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ንቱ አለሞችን የነሰቸዋል ከእስላም በፊት በነበረው ጃሂ ሊያ ላይ የነበረባቸው መሽኪላቸወ መሻኪል አለም ላፍካር ጃህሊያን ደግሞ ያነሳቸዋል እነዚህ ነገሮች እኛም ውስጥ አሉ እንዴት ሊታረሙ ይችላሉ ብሎ ያብራራል /ግልፅ ያልሆነ/ ፐሪንስፐል እና ወይም መንገድን እና ጎላችንን ፐሪንስፐልን መቀላቀል /ግልፅ ያልሆነ/ እያለ እንደዚህ የሚገልፃቸው ነገሮች አሉ አንዳንዶቹን እንትን ለማድረግ /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት /ግልፅ ያልሆነ/ ወይም ደግሞ ከእኛ በፊት የነበሩ መንግዶችን ዝም ብሎ ተከትሎ መሄድ የአላህ በቁርአን ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ብለው አሉ ብሎ እንደሚተቸው ማለት ነው እንደዚያ ዓይነት አካሄዶች መከልል አዳ መከልል አዳ ማለት እንዲህ ነው የሚሰራው በቃ ዳዋም ሲታሰብ እንዲህ ነው ዳዋ የሚደረገው ተብሎ የበፊት ከእነ ፐሮብሌሙ እና ከእነ እንትኑ ወደ እዚህ የማምጣት ችግሮች አሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ በማንኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ የሚታይ ነገር ነው ለውጥ ይዞ የሚነሳ ሰው ተቃውሞ ይገጥመዋል ይሄ በራሱ ደግሞ ሱና ነው ይሄንን በዝርዝር እናየዋለን /ግልፅ ያልሆነ/ ጥርጣሬን መሠረት ያደረገ ጉዞ ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ስብስቦች ሰዎች የሚፈልጉት ነገር በጣም ሩቅ ነው የኢትዮጵያ ሙስሊም ችግር የመፍታት ጡሙህ አላቸው ስብስቦች ይዘው የሚነሱት ነገር ግን በጣም ተራ የሆነ ጉዳይ መፍታት ላይ ይሆናል እንደዚህ ዓይነት እንትን ይላል /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ ሰው የተናገረው ነገር ላይ ሳይሆን ተናጋሪው ላይ ትኩረት ማድረግ እያለ የሚያነሳቸው አለ /ግልፅ ያልሆነ/ የምንመኘው እና የምንፈልገው ደግሞ የአስተሳሰብ አለም አለ ያንን ነኛ ሪመትሊ ወቅት ይላል ሪመትሊ ወቅት ጊዜአችንን በአግባብ ከመጠቀም ኮንስፐት አልፎ አሁን በፍጥነት አንድ ሙቭመንት ካልፈጠርን ሊያጠፉን ይችላል ብለህ ለጊዜው የምንሰጠው ቫሊውን /ግልፅ ያልሆነ/ እያንዳንዱ የማባከን ሂደት የኃላቀርነታችን ላይ ተጨማሪ አስተዋፆ ማበርከት ነው በተለይ ደግሞ የእኛ ተቃራኒ ኃይል ቀን እና ማታ የሚለፋ ከሆነ ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል ይሄ በመተል ወቅት ነው ከእዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ የተረዳንበት መንገድ እራሱ መስተካከል አለበት ብሎ ያምናል /ግልፅ ያልሆነ/ መልካም ስራ ላይ ያለን አስተሳሰብ ፍልስፍናው እራሱ ስህተት አለው ከእስላማዊ አመለካከት አንፃር ይላል /ግልፅ ያልሆነ/ በጋራ የመስራት ባህላችን መዳበር አለበት ይሄ መብቶችን ሕጎችን የማክበር አሰቡር ይላል ትዕግስት አሰቡር ምን ብሎ ይገልፀዋል /ግልፅ ያልሆነ/ ሰቡር ማለት ማለት በሙስሊሙ አለም ላይ ያለው አስተሳሰብ ችግር ሲደርስብህ መታገስ ትክክለኛው ሰቡር ማለት ግን ኢማው ካለበት ችግር ለማውጣት ቁጭ ብለህ ማንበብ ማጥናት መልፋት መድከም

3201

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እዚህ ላይ ነው ሰቡር ነው ሪል ሰቡር ማለት ስራዎችን ስትሰራ መታገስ ነው ሰቡር ማለት እንደ የሚደርስበትን መከራ መታገስ ብቻ አይደለም ግን ሙስሊሙ አለም ሰቡር የሚታወቀው ይሄ ነው ገዳይ የሆኑ አስተሳሰቦች ምን ዓይነት ጉዳቶች ያመጣሉ የሚለውን ያብራራል ቀጥሎ /ግልፅ ያልሆነ/ ታሪህ መማር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃል ሌላው /ግልፅ ያልሆነ/ ይህ ማለት ደግሞ መረጃዎችን በሚመለከት ሙስሊሙ ያለበትን ችግር ያነሳል እያንዳንዱ ጉዳይ ዳታን መሠረት ያደረገ እስታስቲክን መሠረት ያደረገ ነገር አይንቀሳቀስም ሙስሊሙ ኢቭን መረጃን መሠረት አድርጎ /ግልፅ ያልሆነ/ ኢቭን ትክክለኛ እና ጥልቅ የሆነ እንኳን /ግልፅ ያልሆነ/ ባይሆን ግርድፋን ቃል መረጃ የለውም ሙስሊሙ እና ይሄንን ምን ያህል /ግልፅ ያልሆነ/ ትምህርትም የራቀ እንደሆነ ያነሳል /ግልፅ ያልሆነ/ መጀመሪያ መዲና ሲገቡ ካዘዙት ነገር አንዱ መዲና ውስጥ ያሉ ሙስሊሞችን ቁጥር አሳውቁኝ ነው ያሉት በመቀጠል ደግሞ ከሙስሊሞቹ ውስጥ ማንበብ እና መፃፍ የሚችለውን ቁጥራችሁ አሳውቁኝ ያሉት እኛ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሙስሊም አናውቀውም ምን ያህል እንደተማረ አናውቀውም እና ይሄንን በሚመለከት የሚያነሳቸው ነገሮች አሉ ከእዚያ ምን አለ /ግልፅ ያልሆነ/ ያለውን ተጨባጭ ለመቀየር የሚያስፈልጉ ነጥቦችን በሚመለከት ምን ይላል /ግልፅ ያልሆነ/ ያሉ ጉዳዮቻችንን በትክክል ካወቅን በኋላ በጣም አንኳር የሆኑ ፖይንቶች ምንድን ናቸው ብሎ ማውጣት ከእዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ ጉዳዮን የሚከታተል ተግባራዊ ስራዎችን የሚሰራ እና መረጃዎችን በተከታታይ የሚያመጣ አካል መኖር ከእዚያ በኋላ ደግሞ ወደ ውጤት ሊቀየሩ የሚገባቸው ነገሮችን እነሱንም ያያል በእሱ አስተሳሰብ /ግልፅ ያልሆነ/ ቅድም ያየናቸው /ግልፅ ያልሆነ/ የሙስሊሙ አስተሳሰብ ፈውብ አለበት ይላል /ግልፅ ያልሆነ/ ፓተርን ኖርት ስርዓት ይዞ የሚሄድ አይደለም የሚፈልገውን ነገር የሚያጠፋ አስተሳሰብ ማለት ነው ፈውብ ያለበት አስተሳሰብ /ግልፅ ያልሆነ/ ያለ /ግልፅ ያልሆነ / የሕግ ጉዳይ /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ሙስሊሙ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ስናየው የበታችነት ስሜት ይሰማዋል የመገለል ስሜት ይሰማዋል የ 2ኛ ዜግነት ስሜት ይሰማዋል የሀገር ፍቅር የለውም ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/ እንትኖች ችግር አለበት ኢቭን በታሪኩ እንኳን አይኮራም ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስሊሞች የሰሩትን ታሪክ አይደለም ፌል የምናደርገው የእነሱ ታላቅነት ገዝፎ እኛ ምንም ሚና የሌለን ዓይነት ስሜት ይሰማናል እና የመጨረሻው /ግልፅ ያልሆነ/ ብሎ የሚያነሳቸው አሉ /ግልፅ ያልሆነ/ እነዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ይላል እነዚህን አሁን ያነሳናቸውን ነጥቦች በጣም /ግልፅ ያልሆነ/ መልኩ ወደ ተግባርም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለመለወጥ በሚያጓጓ እንዲሁም ሪሊ የእኛን ፐሬብሌም ተች በሚያደርግ መልኩ ያቀርበዋል መፅሐፉ አጠቃላይ ይሄንን ይመስላል ይሄንን ጉዳይ ቁጭ ብለን ብንወያይበት ብናብላላው የቻልነውን ያህል ደግሞ ወደ ሕብረተሰቡ አሰራጭተን ወደ ስራ ብንቀይረው ይጠቅማል ብለን ካመንን ወደ ውይይቱ እንገባለን ብዬ አስባለሁ ትንሽ ብሬክም ለማድረግ ቀጥታ ካሚል ከሚቀጥል በእዚሁ ርዕስ ላይ ትንሽ ተወያይተን ወደ 2ኛው ብንሄድ የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ /ግልፅ ያልሆነ/

- /ግልፅ ያልሆነ/ 2ኛው መፅሐፍ ከዋኒን እናህ በሚል ነው ይህ እያየን ያለነው ናህባ መሰረታዊ የሆኑ ሕግጋቶች አሉት እነዚህ ሕግጋቶች እስከ 8 የሚደርሱ ቃዋኒን አሉ የሺአላህ የተወሰነውን እንደው እያንዳንዱ ላይ ምን ምን እንደሚል ለማየት እንሞክራለን የእዚህ መሪ ቃል ምንድን ነው የእዚኛው ፓርት ላይ ለምሳሌ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚባል አስተሳሰብ መኖር አለበት ሴንትራል አይዶሎጂ አስተሳሰብ ይሄ ሴንትራል አስተሳሰብ መፅሐፉ እንደሚያስቀምጠው /ግልፅ ያልሆነ/ ጀነራል አስተሳሰብ የሆነ ሆኖ መባዲና እያንዳንዱ በዓለማችን ላይ ያሉ ወይም ያለፉ አስተሳሰቦች የየራሳቸው የሆነ ሴንትራል አስተሳሰብ አላቸው ወደ እኛ አሁን ስናመጣ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ እስላም ነው ለእኛ ማለት ነው በውስጡ ባለው ሙሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለ አፈረ ስለኢዛ ስለዲን /ግልፅ ያልሆነ/ እንዲህ ያሉ ነገሮች ለእኛ ሴንትራል ፖይንት ናቸው ሌሎቹ አስተሳሰቦች ጋር ግን ለምሳሌ ብንሄድ ከእስላም ውጪ ያሉ አስተሳሰቦች ጋር ሌበራሊዝም ጋር ስትሄድ ሶሻሊዝም ጋርም ስትሄድም እንዲሁ የየራሱ የሆነ ሴንትራል የሆነ አስተሳሰብ አለው ማለት ነው አልፈኪራል መርከዚያ የሚባል ማለት ነው እና እስላም የእነሱ ከእነሱ በሙሉ የተለየ መሆኑን በእዚህ ፓርት ስር በሰፊው ይዳስሳል ከእዚያ ደግሞ 2ኛው አስተሳሰብ አልፈኪራ አልመፈዚያ የሚባል አለ ወደ እዚህ ነገር ደግሞ ሰዎችን የሚገፋፋ እና በጣም ሰዎች ሊዳስሱት ተጨባጭ በሆነ መልኩ ይዟቸው ወደ እዚህ ሴንትራል አይዲያ የሚያመጣቸው አስተሳሰብ አለ ይሄንንም በሰፊው ይተነትናቸዋል ሌላ በእዚህ ስር የምንፈልገውን ህባ እስላምን ሴንትራል አድርጎ ምን ምን ዓይነት ስርዓቶች ሊኖሩት ይገባል ምን ምን ዓይነት ደግሞ ሸክል እስትራክቸር ሊኖረው ይገባል እንዴት አድርጎ ነው ሰውን የተለያዩ የማህበረሰቡ ክፍሎችን አስነስቶ ከኋላው ቀስቅሶ ይዟቸው የሚሄደው የሚለው ነገርን በእዚህ ስራ አሁንም እነዚህ 3 ነጥቦችን ያስቀምጣቸዋል ሌላው ፍክርን መርከዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ ብሎ የሚያስቀምጣቸው ነገሮች አሉ 1ኛ እያንዳንዱን የሰው ሕይወትን የሚዳስስ መሆን መቻል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አበዘት ይሄ ሴንተራል አይዶሎጂ የምንለው ነገር ማለት ነው አሁን ሶሻሊዝምን ብትወስድ የጀማ ጉዳይ እንጂ ኢንዲቪዡዋል ጉዳይ ብዙም ቦታ የለውም ሌብራሊዝም ስትወስድ የኢንዲቪዡዋል ጉዳይ እንጂ የጀማ ጉዳይ ቦታ የለውም እስላም ግን /ግልፅ ያልሆነ/ የሚያደርገው ስለዚህ እያንዳንዱን የግለሰብን የማህበረሰብን እያንዳንዱ ነገርን ተች የሚያደርግ መሆኑ በ2ኛ ደረጃ ደግሞ ከለውጦች ጋር አዳብት እያደረገ እራሱን የሚያስኬድ መሆን መቻሉ አውትዴትድ ሊሆን አይችልም ፍክረመርከዚያ አሁን እስላምን ሴንትራል አይዶሎጂ አድርገን ስንወስደው አውትዴትድ ሊሆን አይችልም ከየትኛውም ማህበረሰብ ጋር ከየትኛውም ጊዜ የሚሄድ መሆኑ ሌላው አንዳንድ ነገሮች ውብስብስ የሆኑ ነገሮች ደግሞ አሉበት በደንብ ጠለቅ ብለን ካላየነው ወይም እዚህ ወደ ናህባ ይሄዳል የሚል ሰው ጠለቅ ብሎ ካላየ በስተቀር ትንሽ ራመድ የሆኑ ፖይንቶች ይኖሩበታል ማለት ነው የኢስላምን ሴንትራል አይዶሎጂ ስንወስድ 2 መሠረታዊ ነገሮች ላይ ነው የቆመው 1ኛ እስትሮንግ የሆነ ኮንክሪት የሆነ አስተሳሰብ ላይ እሱ ያው አዲቃ የማይቀሩ የሆኑ እስላም ውስጥ ያሉ ፕሪንሲፕሎች አሉ /ግልፅ ያልሆነ/ የምንላቸው ነገሮች ማለት ነው ሌላው ጁዝ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ጁዝ መሪ ይላቸዋል ሊቀያየሩ የሚችሉ ፊከ ጉዳዮች ላይ አካሄድ ጉዳዮች ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ላይ ይቀያየራሉ ስለዚህ ወደ ናህባ የሚመጣ ሰው /ግልፅ ያልሆነ/ ለማደባለቅ እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች አሉ ይሄም አንዱ እዚህ ጋር አብሮ የሚስተካከል የሆነ ነገር ነው ማለት ነው ሌላው ይሄንን ካልን በኋላ ወዴት ነው የምንሄደው ወደ ለውጥ ነው የምንሄደው ወደ ለውጥ ስንሄድ ለውጣችን 3 ዓይነቶች ለውጦች ናቸው እዚህ ላይ የሚመጡት ማለት ነው ሰዎችን አሁን ይሄንን ፕሪንስፕል ይዘን ወደ ሰው ውስጥ ገብተን ለእስላም የሚሰሩ ሰዎችን ሀሽ አድርገናቸው ስንመጣ የምንቀይረው 3 ቦታዎች አሉ 1 /ግልፅ ያልሆነ/ እንቀይራለን 2ኛ አልመልመሻር እንቀይራለን ፊሊንግን ስሜትን ማለት ነው ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ የምንለው አለ እነዚህ 3ቱ ነገሮች ታርጌት እናደርጋለን የሚለወጡት የሚቀየሩት እነዚህ 3 ቦታዎች ናቸው ማለት ነው አፍካር ይቀየራል ከእዚያ በኋላ አልመመሻር ሰዎች /ግልፅ ያልሆነ/ በስነ ልቦናቸው የሚያዩዋቸው ነገሮች ከእዚያ የሚሰሯቸው ነገሮች እየተቀየረ የሚሄድበት ሁኔታ ነው የሚመጣው ማለት ነው ወደ እዚህ ለውጥ ጉዞ ስንመጣ መንገዶች ሙሉ በሙሉ አልጋ በአልጋ ወይም ምንጣፍ በአበባ የተነጠፈ ነገር አይደለም እዚህ ላይ 4 መሠረታዊ ነገሮችን የግድ እናልፋለን ለውጥን ይዘህ ስትመጣ አንተ አብረህ ከምትሰራቸው ሰዎች የምትሰራበት ማህበረሰብ ከአንተ በላይ ካሉ ከበታችህ ከጎህ ካሉ ሰዎች

http://ethcriminalawnetwork.com/

በመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ነው የሚገጥመህ ኢንካር ነው ሙሉ በሙሉ አንተን አለመቀበል አለ በ 2ኛ ደረጃ ግብግብ ነው የሚመጣው ሙካባ የምንለው ነገር ማለት ነው ሬዚስታንስ በኋላ ይቆዩ እንዴ ለካ እነዚህ ሰዎች /ግልፅ ያልሆነ/ የሚለው ነገር አለ እነዚህ ሰዎች ያሉት ለካ ልክ ነው ከእዚያ በኋላ ምን እንስራ እንዴት እናድርግ እኛም በቃ እኔም በእዚህ ውስጥ እንዲህ መሄድ አለብኝ ብሎ የሚለው ነገር አለ አንተ በመጀመሪያ እንካሩ ሲገጥምህ እዚያው ከቆምክ ተቃውሞ ሲገጥምህ ኃይለኛ ሙግዘት ሲገጥምህ እዚያው ከቆምክ ቆምክ ማለት ነው እዚያኛው መርሀላ ላይ ልትደርስ አትችልም ማለት ነው ስለዚህ እኛም በተጨባጭ ወደ እዚህ ስራ እንመጣለን ብለን ስናስብ የምንነግረው ሰው የሚሰማን ሰው በሙሉ ማሽአላህ ብሎ መጀመሪያ ይቀበለናል ብለን እንዳናስብ የተወሰኑ ፕሪንሲፕሎች እዚህ ስር ይኖራሉ 2ኛው ሕግ ደግሞ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ሰዎችን ሮህ ውስጥ ገብተህ ሰዎችን ከውስጣቸው የሆነ ነገርን አውጥተን ወደ አንተ እንዲመጡ ወደ እዚህ አስተሳሰብ እንዲመጡ የምታደርግበት ሂደት ነው ያለው ይሄንን ለማድረግ 3 መሠረታዊ ጥያቄዎች አሉ 1ኛ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ማንን ነው የምትለውጠው ወዴት ነው የምትለውጠው በምንድን ነው የምትለውጠው ለውጦችንስ በምንድን ነው የምትለካቸው ሌላ ወዴትስ ድረስ ነው መሄድ የምትፈልገው የአንተ ለውጥ ሂደት እስከምን ድረስ ነው እስከ ምን ድረስ መለወጥ የምትፈልገው እና ከእዚያ ደግሞ ለውጦችህን ትላንት ከነበርክበት እና አሁን ለወጥኩ ከምትለው ኃሳብ እንዴት አድርገን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አድርገህ ልትመዝነው የምትችለው የሚለው ነገር ነው ስለዚህ ሰዎችን /ግልፅ ያልሆነ/ መየቀር ብሎ ማለት ምንድን ነው ሰዎች ተስፋ ቆርጠዋል ስሜታቸው ወድቋል በቃ አሁን ወደ ኢትዮጵያ /ግልፅ ያልሆነ/ ስንወስድ በቃ ሙስሊሞቹ አንድ ሆነው ሊሰሩ አይችሉም መሪ የለንም በሌላ ስር ተውጠን ነው ያለነው ታሪካችን እንዲህ ነው ብለን ኔጌቲቭ ነገር ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ተሞልቶ ያለው ስለዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ውስጥ ስትሰራ ሰዎችን /ግልፅ ያልሆነ/ እንዲሆኑ /ግልፅ ያልሆነ/ ስራ አለ በጣም ብራይት የሆነ ፊውቸር እንዳለ የበላይ እንደሚሆኑ ከእዚያ በኋላ አዲስ ሕይወት ውስጥ እንዲገቡ በእዚህ ዓይነት መልኩ ታደርጋቸዋለህ ማለት ነው እና ይሄ ፕሪንስፕል አሳሳቢነቱ ምንድን ነው ሰዎች /ግልፅ ያልሆነ/ ፊርክ አለው ይላል ፊርክ /ግልፅ ያልሆነ/ የሆነ ቁጭ ብሎ ከመመኘት ወደ ተግባር ገብተህ ተጋፍጠህ ተግባራዊ የምታደርጋቸው ነገሮች አሉ ስለዚህ እዚህ ፕሪንስፕል ስር ሰውን ሮህ ውስጥ የምትሰራው ነገሮች ናቸው ያሉት ማለት ነው ሌላ ሰዎችን ለመቀስቀስ የመጀመሪያ ልትጠቀምባቸው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚገቡ መስፈርቶች አሉ አንደኛ የአንተን ፊክራ እንዲያምኑ ማድረግ መቻል አለብህ ኢማኑ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄንን ፕሮጀክትን አሁን ፊክራችን ምንድን ነው ብለናል እስላም ነው እስላም ሕይወታችንን በሙሉ ሊገዛ የሚገባው ይዳስሳል ይገዛናል ከሁሉም አስተሳሰብ ከሁሉም አካሄድ የተሻለ ነው ብሎ ሙሉ ኢማም ሸክ ሳይኖርባቸው እስላም ትክክል ነው እስላም ሁሉንም ነገር መቀየር ይችላል ጥያቄዎችን ሊመልስ ይችላል የግለሰብን የማህበረሰብን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እያንዳንዱ ነገርን ሊመልስ ይችላል ብሎ እንዲያምኑ ማድረግ መቻል ነው በ2ኛ ደረጃ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ እንዲሰማው እዚህ ስር የምትሰራው ነገር እዚያ በራስ መኩራት /ግልፅ ያልሆነ/ በዲን እስላም በያዘው ነገር አንገቱን ደፍቶ አፍሮ ተናንሶ መሄድ ሳይሆን እዚያ እንዲሰማው ማድረግ በ3ኛ ደረጃ አመል ነው ተስፋ እንዲኖረው አሁን ያለበትን /ግልፅ ያልሆነ/ አታሳየውም አሁን የበታች ነው ታፍኖ ተጨፍልቆ የተለያየ ነገር ስር ሊኖር ይችላል ግን ተስፋ ፊቱ ላይ እንዳለ ታሳየዋለህ ማለት ነው ከእዚያ መፅሐፉ የሚዳስሳቸው ነገሮች ምንድን ናቸው ምንድን ነው መገለጫዎቹ ሰውዬው በአንተ አስተሳሰብ አምኗል ብለህ የሚገለፅበት ይሄ ኢማን አለው ብለህ ሰውዬው ስሜቱ ተቀይሯል ሰውዬው ተስፈኛ ሆኗል ብለህ ደግሞ የምታይ እና ኢቫሉየት የምታደርጋቸው ነገሮች አሉ እነሱንም እዚህ ስር ይዳስሳቸዋል ማለት ነው

- /ግልፅ ያልሆነ/
- አንተ ትሰጣለህ ከእዚያ በኋላ ደግሞ ፕሮዳክቱን አይተህ የምትገመግምበት ነገር አለ እያንዳንዱ ነገር በዝርዝር እዚህ ስር ተቀምጧል ማለት ነው እንደምሳሌ አሁን ያነሳቸዋል ለምሳሌ /ግልፅ ያልሆነ/ መካ ላይ ሰሀቦችን እንዴት አድርጎ ነው እንደዚያ ውስጣቸው ያንን ትልቅ ኢነርጂ ጭኖ ያንን ዓይነት በቃ ለውጥ እንዲሰሩ ያደረጓቸው አንድ ሁለት ሶስት አራት ብሎ ያስቀምጣቸዋል ምዕራቡ አለም እንዴት አድርጎ በጣም ትላንትና በጣም ወድቆ ኋላ ቀር በማህይምነት በጨለማ እራሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/ የሚያስቡት ዘመን ነበር ከእዚያ ስር ሕዝቡን ምንድን ነው ፊቱ ላይ አሳይቶት ያንን ዓይነት በቃ /ግልፅ ያልሆነ/ ሊሰራ የቻለው ትልቅ ለውጥ ሊሰራ የቻለው እነዚህ ነገሮችን ያስቀምጣቸዋል 2 መሠረታዊ ነገሮች አሉን የምዕራቡ አለምን ስትወስድ ማለት ነው 1ኛ ታሪኩን የትላንት ታሪኩን አሳየ እንደገና ደግሞ የትላትናውን ያለፈውን ነገር መልሶ እንዲያነበው አደረገ ሌላኛው ደግሞ ከአንዱ ድል ወደ ሌላ ድል እየተሸጋገረ እንዲሄድ ነው ያደረገው ከአንዱ አቢዮት ወደ ሌላ አቢዮት ከአንዱ ለውጥ ወደ ሌላ ለውጥ እንዲሄድ አደረገ የእዚያኔ ሕዝቡ ሁሉ ተነሳ እኩል ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ነው ያደረገው እሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/

3206

7051

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ዘንድ የወረደላቸው ታሪክን ኢህባ ማድረግ አለ ከአደም ጀምሮ ኑር ኢብራሒም ሙሳ ኢሳ የነቢያቶችን ታሪክ እያንዳንዱ ነገር ዝርዝር ይዘረዘራል በቁርአን ላይ ያለው ነገር ከእዚያ በኋላ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ የአለል ከታብ የነበራቸውን ሌጋሲቲ ዲኔይ ማድረግ ነው እነሱን ዲኔይ ማድረግ ይሄም እራሱን የቻለ እዚህ ስር አለ ሌላ ደግሞ አሁን ያሉትን መራሂሎችን እንደገና እያዩ መሄድ ይሄም እኛ ወደ ለውጥ ስንሄድ ሕዝባችንን የቱ ጋር ኮርኩረነው ምኑን አሳይተነው ነው ልንቀሰቅሰው እና ወደ ፊት ይዘነው ልንሄድ የምንችለው ሌላ የተለያዩ ችግሮች እዚህ ስር ደግሞ እንዳሉ አሁንም መዘንጋት እንደሌለበት ያስቀምጣል /ግልፅ ያልሆነ/ አለ ከተቃራኒው ማለት ነው አንተ ላይ ይሄንን እንቅስቃሴ ይዘህ ስትነሳ የአንተ ተቃራኒዎች በጣም ይበዛሉ በተለያየ ዓይነት መልኩ ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ በስብስቡ መካከል የተለያዩ ነገሮች መርጨት እንዲህ ዓይነት ነገሮች አሉ እነዚህ ነገሮችን ደግሞ ልታልፍ የምትችለው 3 አቅል ነው እዚህ ላይ ያሉት ይላል 3 አቅል ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ሊደር ሽፑ አስተሳሰብ አለ ሙሁሩ ክፍል አለ ተራው ማህበረሰብ አለ አንዳንድ ጊዜ ሙህሩ ክፍል እና ተራ ማህበረሰብ አንድ የሚሆንበት ሁኔታ አለ ሙሁሩ ክፍል እራሱን ለይቶ እራሱን ሚና ለይቶ አውቆ የማይሄድ ከሆነ /ግልፅ ያልሆነ/ አብሮ ይሄዳል 2 ክፍል ነው የሚሆኑት ይሄንንም እንዴት አድርጎ /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ናቸው ተራው ሰው ሙህስፋቱ ምንድን ነው የሚለው ነገርን እዚህ ስር በሰፊው ያስቀምጣል ማለት ነው 3ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ነው ተዚ ረዳት ነው እራስን መቀየር ለውጥ ማለት ነው ይሄ ምንድን ነው ይህ ተሂር ሊመጣ የሚችለው ሰዎች በሚሰሯቸው በስነ ምግባራቸው ተለውጠው ካልታዩ በስተቀር አስተሳሰባቸው ብቻ መሻራቸው ብቻ መየቀሩ ለውጥ የለውም ይላል ይሄ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ሕግ ውስጥ ያለ ነገር ነው ለውጥ አለ ሁል ጊዜም ይህ ለውጥ ግን የሚመጣው ምንድን ነው በ 2 መሠረታዊ ቦታዎች ላይ ይመጣል /ግልፅ ያልሆነ/ አቅል ይቀየራል ከልብ ይቀየራል አቅል በምን ይቀየራል ከልብ በምን ይቀየራል 2ቱም የየራሳቸው የሆነ መዋድ አላቸው የሚቀይሯቸው አቅል በእውቀት ይቀየራል ምን ቅድም በመጀመሪያ ክፍል ላይ የተቀመጠው ነገር አለ ከልብ በምን ይቀየራል /ግልፅ ያልሆነ/ ይቀየራል ይሄም መራህላ እንዴት ተደርጎ ነው የሚታለፈው /ግልፅ ያልሆነ/ የለውጥ መሠረቶች አሉ ይሄም /ግልፅ ያልሆነ/ ለውጥ የምንፈልግ ከሆነ ቤዚክ የሆነ ፕሪንስፐሎች አሉ 3 ቤዚክ ፕሪንሲፐሎችን ይዳስሳል እዚህ ስር 1ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ እንዴት መማር እንዳለበት ማስተማር ማለት ነው እና ሰዎች ይማራሉ ይሄንን ማልፋ እንዴት ... እንዴት ... እንዳለባቸው

http://ethcriminalawnetwork.com/

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከየት እንደሚጀመሩ ምን እንደሚማሩ ለምን እንደሚማሩ እንዴት እንደሚማሩ አያውቋቸውም ስለዚህ እኛ /ግልፅ ያልሆነ/ አንዱ ቤዚክ የሆነ ነገር ነው ሌላው ወደ ለውጥ አሁንም ስንመጣ የተለያዩ በውስጣችን የወረስናቸው የተለያዩ ችግሮች አሉ እነዚህን ደግሞ ለማለፍ /ግልፅ ያልሆነ/ ከንቶ ምኞትን ሰብረን ማለፍ መቻል አለብን የውድቀት ባህሎቻችንን ነገሮችን ኔጌቲቭሊ ማየት አንችልም እንደርስበትም አናደርገው እኛ እንዲህ ነን ብለን የትላንትና ኔጌቲቭ ነገሮቻችንን ዝም ብለን ማየታችንን ቆርጠን ማለፍ መቻል አለብን ማለት ነው እነ እከሌ ትላንት እንዲህ ነበሩ /ግልፅ ያልሆነ/ እነ ሼህ እከሌ እዚያ ሀገር እከሌ የምትለው ነገር ሁሌ ካለ በፍፁም ይሄ ሊመጣ አይችልም ሌላው /ግልፅ ያልሆነ/ መምጣት መቻል አለበት ማለት ነው መፅሐፉ ላይ ይህ ነገር እንደሰው ምስል ነው ተቀምጦ ያለው ይሄንን 3 ቤዚክ ነገርን ሲያስቀመጠው 1 አቅል አለ አይምሮ አለ የሰው ምስል አለ ከእዚያ በኋላ ልቡ አለ እጁ እዚህ ጋር አለ እና ይሄንን ሲያመጣው ምን ማለት ነው ለውጥ ስታደርግ ፍክር ስትቀይር አቅሉን ነው የቀየርነው ልቡን ስትቀይር ፊሊንጉን ነው የቀየርከው መሻኢውን ማለት ነው ሱሉኩን ስትቀይር የሚሰራቸው ተግባራቱን ነው የቀየርከው ማለት ነው እነዚህ ነገሮችን እኛም ልንደርስባቸው እንዴት እንደምንችላቸው በእዚህ ላይ ያስቀምጣል 4ኛው ሕግ እና ምናልባት እኔ እንደውም ወሣኝ ከምላቸው ውስጥ አንዱ ምንድን ነው ወደ ለውጥ ጎዳና ስንገባ ሚናችንን መለየት መቻል አለብን ይላል 3 የለውጥ አካላት መኖር አለባቸው ለውጡን የሚጀምሩ /ግልፅ ያልሆነ/ ይላቸዋል የለውጥ አራማጆቹ ጀማሪዎቹ ከእዚያ በኋላ ለውጡን ተግባራዊ የሚያደርጉ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ተከዚር ይላቸዋል ለውጡን እራሱን የሚያመጡት እነዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ አስተሳሰብን መስርቶ ነው የሚሄዱት አስቀምጦ ማለት ነው ስለዚህ የሚቀጥሉት ደግሞ ያንን አስተሳሰብን ይዞ ወደ ተግባር ይቀይሩታል ለውጥ ያመጣሉ 3ኛው ክፍል ደግሞ የመጣውን ለውጥን ተጠቅሞ በሼሪያ ተልበና ነው ግንባታ ይሰራል ማለት ነው ይገነባል ማለት ነው ይሄንን በምሳሌ ሲያስቀምጠው /ግልፅ ያልሆነ3 3 ቦታ ይከፋፍላቸዋል የመጀመሪያ አካባቢ እነ አቡበከር እነ አሊ መጀመሪያ ላይ የሰለሙ ሰዎች /ግልፅ ያልሆነ/ ናቸው ከእዚያ በኋላ ወደ መዲና መጥቶ ወደ መዲና ከመምጣታቸው በፊት እንደዚሁ /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ መዲና የመጠው እንደዚህ አደረጉ ሰዎችን ትግል ያደረጉ /ግልፅ ያልሆነ/ ዘመቻ ላይ የገቡ ሰዎችን ሲያስቀምጣቸው /ግልፅ ያልሆነ/ ከቢር ናቸው ወይም ደግሞ እዚያው /ግልፅ ያልሆነ/ እራሱ ደግሞ የጀመሩት ጀማሪዎች አሉ ከእዚያ በኋላ ደግሞ ለውጡን ያመጡት ደግሞ እነ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

/ግልፅ ያልሆነ/ እነ ሀምዛ መስለም እራሱን የቻሉ ከእዚያ በኋላ ወደ ዲና ነው የተሄደው ሀገርን መገንባት እስላማዊ እስቴትን መመስረት እነዚህ 3ቱ ነገሮች መደባለቃቸው እና አንድ መሆናቸው የሚፈጥራቸው ችግሮችን እዚህ ስር ይዳስሳቸዋል ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን የቅድሞቹ /ግልፅ ያልሆነ / ጀማሪዎቹ ፕሪንሲፕሉን ሲያስቀምጡ ትልቁ ስራ ያለው ሼሪያ /ግልፅ ያልሆነ/ ላይ ነው ሸሪያ ተተቢር ደግሞ ሁሉንም ማህበረሰብ ክፍልም /ግልፅ ያልሆነ/ ማድረግ መቻል አለበት ይላል መሣሪያ መጠቀም አለበት የለውጡ ቡድን ማለት ነው ከዕድሜ ለምሳሌ ስንነሳ ከታች ከተማሪዎች መጠቀም መቻል አለበት /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ሶሻል እስትራክቸርም ስመጣ ሁሉንም ሶሳይቲውንም ክፍል እንዴት መጠቀም እንዳለበት ባለሙያዎች ጋር ስትመጣ የእውቀት ደረጃቸውንም እንዲሁ በእዚያ ልክም ሲያስቀምጥ እያንዳንዱ ክፍል ከፋፍለህ እንዴት አድርገህ ለለውጥ እንደምትጠቀማቸው እዚህ ስር በሰፊው ይተነትናል ሌላው 5ኛው ፕሪንስፕል ወይም ሕግ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ እንደ ሎን እዚህ ስር የሚጠቀመው እንደ መርህ መፈክር /ግልፅ ያልሆነ/ የማንኛውም ማህበረሰብ ጥንካሬ እና እንዲሁም /ግልፅ ያልሆነ/ ብስለት ደረጃ የሚለካው ምን ዓይነት ሰው ነው የሚያመርት ያለው ይህ ማህበረሰብ እንደውም የወንድነት ባህሪ በውስጣቸው ሙሉ በሙሉ ተሟልቶ ያለውን ነው የሚያመርተው ያለው የሚለውን ነገር እዚህ ስር ይዳስሳል ማለት ነው ይሄ ምን ማለት ነው በሌላ ቋንቋ ተርቢያ እንዴት ነው የሚደረገው እንዴት ሰዎች ይዘጋጃሉ የሚደረግ ተርቢያ ምንድን ነው ማን ነው እዚህ ተርቢያ ውስጥ መግባት ያለበት የሚለውን ያስቀምጥ እና እዚያ ስር አሁን ምን ይላል /ግልፅ ያልሆነ/ እዚህ ስር የምትሰራው ሰው ሕፃናትን ቅድም ያልነው /ግልፅ ያልሆነ/ ያሉ ሰዎችን ነው እኛ ማምጣት የምንፈልገው ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ መስራት የምንፈልገው ይላል /ግልፅ ያልሆነ/ ሌላው የሆነ ነገር ሰርቶ እንዲያመጣለት የሚፈልግ ዓይነት ትውልድ ሳይሆን እራሱ የሚሰራ እራሱ ቀድሞ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚያደርግ /ግልፅ ያልሆነ/ ስድብ ነው አክቲዋሊ እምነቱን አንድ የሚያደርግ እንጂ ወደ የራሱ ስብስብ ወደ የራሱ ድርጅት ወደ እየራሱ ቢሮ አንዳንድ ጊዜ አንድ አሊም የሚሉት አባባል አለ አንዳንድ ዳኢ ይላል ዳዋ ይጀምራል ዳዋ ማድረግ ይጀምር እና ዳዋው መጀመሪያ ዳዋው ወደ እስላም ነው ከእዚያ በኋላ ከጊዜ በኋላ ደግሞ ዳዋው ወደ ምን ሆነ ወደ ሸክስያ ይሆናል አሉ እራሱ ወደ እራሱ ነው ሰው መጥራት የሚጀምረው ሰዎች በእሱ አስተሳሰብ በእሱ አካሄድ በእሱ ስሜት በእሱ ፍላጎት ብቻ እንዲሄዱ አዲስ ነገር እንዲፈጠር አይፈልግም ወደ እራሱ ብቻ ማለት ነው እንደውም ሌላ እንደሱ የሆነ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ቦታ ሲመጣ በአዳዋ ማየት ሁሉን ነገር /ግልፅ ያልሆነ/ ማድረግ ወደ እዚህ ይመጣል እና እንደዚህ ዓይነት ጅል አንፈልግም ይላል /ግልፅ ያልሆነ/ የምንፈልገው ወጣት ትውልድ ነው የምንፈልገው የምንፈልገው ያረጀ ወጣት በአስተሳሰቡ በስሜቱ /ግልፅ ያልሆነ/ በቆራጥነቱ ያረጀ ሳይሆን ኢነርጂ ሁል ጊዜ እንደው የሞቀ የጋለ ስሜት ያለውን ወጣት መፍጠር ነው የምንፈልገው ከእዚያ እዚህ ጋር 4 መሠረታዊ ይሄንን ዓይነት አካሄድ ለማምጣት 4 መሠረታዊ ነገሮችን ይዳስሳል /ግልፅ ያልሆነ/ ሊያደርግ የሚችል ካኢድ መሪ 4 መዋሰፋቶች አሉት አንደኛ /ግልፅ ያልሆነ/ እራሱ ሰርቶ የሚያሳይ ምን ምንድን ነው የሚሰራው መፈክር እራሱ አስተሳሰቡ ከሌላ ዝም ብሎ የሚጠብቅ ሳይሆን ኃሳብን የሚያፈልቅ የሚያመነጭ /ግልፅ ያልሆነ/ የማይፈራ /ግልፅ ያልሆነ/ 3ቱ ሊኖረው ይችላል ሙንቲጅ አለ ፕሮዳክቲቭ የሆነ አለ /ግልፅ ያልሆነ/ ፈሪ ይሆናል ይሄ ግን /ግልፅ ያልሆነ/ መፈክር ነው ጅሪ ነው ሞንቲጅ ነው ይሄ ዓይነት ካሪብ ያስፈልገዋል ብሏል ለተርቢያ ደግሞ የሚያስፈልጉ ቁልስ አሉ መሣሪዎች አሉ 1ኛ እነዚህ መሣሪዎች አንድ ሼሬኢያ የሆኑ ነገሮች አሉ ከቁርአን ከህዲስ የሚወሰዱ የሆኑ ነገሮች አሉ 2ኛ ኢዳሪ የሆኑ ነገሮች አሉ ከማኔጅመንት የሚወሰዱ የሆኑ ነገሮች አሉ ከእዚያ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ከሶሻል ሳይንስ የሚወሰዱ የሆኑ ነገሮች አሉ እነዚህ 3ቱ ጥርቅሞች በእነዚህ 3ቱ ነገሮች /ግልፅ ያልሆነ/ እንዴት ይደረጋሉ የአንዱ ጉድለት /ግልፅ ያልሆነ/ ብቻ አድርገህ ከእዚያ በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/ እንዴት ማስተዳደር እንዴት መምራት እንዴት ሰውን መለወጥ የማያውቅ ከሆነ መአና የለውም /ግልፅ ያልሆነ/ የሰውን እንዲሁ አይቶ /ግልፅ ያልሆነ/ ማድረግ የሰውን ሳይኮሎጂ መረዳት የማይችል ከፈጠርክ አሁንም ችግር ነው ስለዚህ 3ቱ ነገሮች ይኖራሉ ይላል ሌላኛው 6ኛው /ግልፅ ያልሆነ/ እና ሴንሴቲቭ የሆኑ እዚህ ፓርት ስር ያሉ ሴንሴቲቭ የሆኑ አመላካች የሆኑ ነገሮች አለ ኢቫሉኤት የምታደርግባቸው ነገሮች ማለት ነው 7ኛ ወደ እዚህ ስራ በምትመጣበት ጊዜ /ግልፅ ያልሆነ/ ትገባለህ ይላል ፋክክር ውስጥ ተዳፋ ማለት መገፋፋት ውስጥ ትገባለህ /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አንተ ይሄንን ናባዊ ይዘህ ይሄንን አስተሳሰብ ይሄንን ነገር ይዘህ ወደ ኡማ በምትመጣበት ጊዜ ግብግብ ውስጥ ትገባለህ ይሄ ግን ስራ ምን ዓይነት ነገር ውስጥ ነው የምትገባው 1ኛ አንዳንድ ጊዜ ጉልበት ኖሮህ ምን ብሎ ቀጥታ ጦርነት ውስጥ ልትገባ ትችላለህ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄም አንድ እንዴት አድርገህ አንዳንድ ጊዜም ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ምን ያመጣል ወደ መቀላብ ይሄ ብዙ አፍሪካ ሀገሮች ውስጥ በየጊዜው የምናያቸው ነገሮች አንዳንድ ጊዜ ወዴት ነው የሚሄደው ሰውራ ወደ አቢዮት የየራሳቸው ባህሪ

http://ethcriminalawnetwork.com/

አላቸው /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ነው ባህሪው ይተነትናቸዋል /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ነው ባህሪው ሰውራ አቢዮን ምንድን ነው ባህሪው ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ ሌላው ደግሞ ፖለቲካል ፓርቲስፔሽን የምትለው ነገር አለ እሱ ነው ወይ የአንተ ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ ድርድር /ግልፅ ያልሆነ/ ያለበት ፖለቲክስ ውስጥ መግባት ሌላ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ ሲቪል የሆነ ሲቪልዲስኦቢዲያንስ እና እዚያ ውስጥ መግባት አለ አንዳንድ ጊዜም ደግሞ አልፎ ወደ አርሁብም ወደ አርሁብም የመግባት ሁኔታ አለ /ግልፅ ያልሆነ/ የሆነ መርሀ እላዩ ላይ ማለት ነው ስለዚህ ይሄንን ተስፊስ ታደርጋለህ ይላል ይሄንን ዝርዝሩን እዚህ ላይ ያስቀምጠዋል የመጨረሻው /ግልፅ ያልሆነ/ አፖርቺኒዮቶችን እንዴት አድርገህ ትጠቀማለህ አንዳንድ ጊዜ በጣም ብዙ ዘመን የምትለፋባቸው ነገሮች በአንድ ጀምበር የምታገኛቸው ነገሮች አሉ ግን ሬዲ ሆነህ ምን ምን ዓይነት ግራውንድ ኖሮህ አፖርቺኒዎቶችን ልትጠቀም ትችላለህ አሁን በኢትዮጵያ ኮንቴክስት ብትወስድ ዛሬውኑ የሆነ ዕድል ተገኝቶ ኑ እና ውሰዱ ብባል ማን አለ የሚለው ጥያቄ እዚህ ጋር ነው በዝርዝር የሚመለሰው ማለት ነው እና እስከእዚህ ድረስ ነው የሺህአላህ የመጨረሻው

/ግልፅ ያልሆነ/ እኛ አሁን በዳዋ አለም ላይ ትልቁ ችግራችን መኸፈዛዎችን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ የምትለው ስለእስላም የምናወራው ፕሪንስፕሎቹ /ግልፅ ያልሆነ/ መህፊዛ ግን ሪሊ ስቫል የሆኑ ተች ሶሳይቲውን ተች የሚያደርጉ ጉዳዮች ናቸው ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሙስሊም የዳቦ ጥያቄው /ግልፅ ያልሆነ/ የኢትዮጵያ ሙስሊም በሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ የተደረገበት ያለውን ነገር መፍትሔ መስጠት /ግልፅ ያልሆነ/ ማህበረ ቅዱሳን በምን እየተደረገበት ያለውን ነገር ሄደህ መልስ መስጠቱ መህፊዛ ነው እነዚህ ነገሮች ናቸው ሰዎች አንተ ጋር አብረው እንዲጓዙ የሚያደርገው አይዲያ ብቻ ብታወራላቸው አይዲያ የሚገባው ሰው ጥቂት ነው አይዲያን /ግልፅ ያልሆነ/ ይዘህበት አትሄድም እና በተለይ ትልቁ ፕሮብሌማችን የኢትዮጵያ ሙስሊም ሪል ፕሮብሌሙ ተች ማድረግ አለመቻላችን ይሄንን ያመጣውን ችግር እዚህ ላይ እንትን ይላል የእዚያን በሚመለከት /ግልፅ ያልሆነ/ ትዝ ስላለኝ ነው አንድ ሰውዬ እንዲህ ተጎንብሶ ጭርምት ብሎ ሲሄድ አይቶት ምን ችግር ገጥሞሀል ቤተሰብ ላይ የሞተ ሰው አለ አለው የለም ታመህል አልታመምኩም እና ምንድን ነው ጎንበስ ብለህ የምትሄደው /ግልፅ ያልሆነ/ ዲናችንን /ግልፅ ያልሆነ/ እና እዚያ እና ውስጡ የሚቃጠል ስሜት የሌለው ሰው ብፍፁም ስራ ኣያሰራህም እና ብዙ /ግልፅ ያልሆነ/ በጣም አስቸጋሪ በሆነበት ወቅት /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ግን በየመስኪዱ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሰው ምንድን ነው የሚለው ወይ ስለቂያማ ይነገረጣል ወይ ከአሁን በኋላ ቂያማ ደርሷል /ግልፅ ያልሆነ/ የሚመጣው ኡማ የተበላሸ ነው ምናምን እንዲሁ ተስፋ የሚያስቆርጥ ከቤት ሰውዬው እራሱ ዳዋ ለምን እንደሚያደርግ አይገባውም ከእዚያ በባሰ ፈሳ የሚጠብቅ ከሆነ ምን ሊያስተካክል ነው ዳዋ የሚያደርገው እነዚህ ሁኔታ ላይ ሆነን ግን በጣም የሚገራርሙ /ግልፅ ያልሆነ/ አሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ልናደርስለት የሚገባው አክፍሩ የተሻለ ጊዜ ይፈጠራል ብሎ የእዚያ እንዲሰማው መድረግ አለበት /ግልፅ ያልሆነ/ ብዙ ጊዜ የሚነሳ ነገር ስላለ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ የማንችለው ስራ እንዳይመጣ የሚል ስጋቶች ብዙ ጊዜ ይነሳሉ ይሄ የመጣው ለምንድን ነው እኛ የምንሰራ ስለሚመስለን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ እራሴ እሰራለሁ ካለ ችግር ነው /ግልፅ ያልሆነ/ መዲና ሄደው /ግልፅ ያልሆነ/ እስኪገናኙ ድረስ ዳይናሚክ ለውጦች አልተገኙም ለምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አልተገኘም ነበር ከ 10 በላይ ቀዲላዎችን /ግልፅ ያልሆነ/ ዞረው ሲለምኑ ነበር ምንድን ነበር የሚፈልጉት /ግልፅ ያልሆነ/ አይዲያው አለ ለአይዲያው ሊሞት የተዘጋጀ አለ ግን ይሄንን አስተሳሰብ ወደ ምድር ሊያመጡት የሚችሉት ሰዎች /ግልፅ ያልሆነ/ ስብሰብ ውስጥ አልነበሩም ስለዚህ እኛ አይዲያ አዘጋጅተን /ግልፅ ያለሆነ/ እናደርሰዋል እነሱ ናቸው የሚቀይሩት እነሱ ናቸው የሚሰሩት ስለዚህ ብዙ እንዳያስጨንቀን ማለቴ ነው አይዲያ ላ ከተስማማን አስተሳሰብ ላይ ይሄ አይምሮአችን ላይ የዛጉ ነገሮች ጠርገን ካወጣን ይሄ ትልቅ ስክሰስ ነው ይሄንን ለመጨመር ነው

- ለውጥ ስናመጣ አቅል ነው መጀመሪያ መለወጥ ያለበት ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/ ለኢስላም አሁን አእኛ እስላምን /ግልፅ ያልሆነ/ እስላም ነው ብለናል እስላማችን ላይ እራሱ በጣም ሸዋህ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ ይሄ እስላምን ሹምይላው እራሱ መረዳት ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ እስላምን ሁለንተናዊነት መረዳት ላይ ሌላ ችግር አለ እዚህ ከእዚህም እራሱ የጠራን ነገር አይደለንም ሌላኛው ደግሞ ይሄ ነገር እዚህ ጋር በትክክል ከገባ ወዴት ይመጣል ወይ /ግልፅ ያልሆነ/እዚህ ጋር /ግልፅ ያልሆነ/ ይመጣል እዚህ ጋር ብቻ የሚቀር ከሆነ ያው እስላምን ሌላ ሰው የሚረዳው እንደሚረዳው መረዳት ነው ነን ሙስሊም የሆነ ሰው እስላምን በሚረዳው መልኩ መረዳት ከእዚያ ደግሞ ሱሉህ አለ /ግልፅ ያልሆነ/ አንዳንድ ጊዜ ዳዋችን /ግልፅ ያልሆነ/ ይጀምር እና ቀልቡ ባዶ አቅሉ ባዶ ወደ እዚህ እንዲመጣ ይደረጋል አንዳንድ አስተሳሰቦችን እንዲሁ በምድር ላይ ያሉት እራሳቸው ስናያቸው ማለት ነው አንዳንዱ መሰቡ ጋር ብቻ ትኩረት ያደርጋል አቅሉ ባዶ ነው የሚሆነው አንዳንዱ አቅሉን ብቻ /ግልፅ ያልሆነ/ ይህ ባዶ ይሆናል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እነዚህ 3ቱ ከዋኒን ሕጎት አብሮ ተሳዡ እንዳላቸው ነው ይሄ ፒክቸር በእዚህ መልኩ የሚያሳየው ማለት ነው እና ውጤቶቹም እንዲህ በማቴማቲኪስ መልኩ ነው የሚቀመጠው /ግልፅ ያልሆነ/ ትጠቀማለት ፕላስ /ግልፅ ያልሆነ/ ኢዝ ኢኳል ቱ ምን ይሆናል /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄንን ይመስላል አንድ ሀገርን 6ቱን መፅሐፍ ብታነቡ አረብ ሀገርን ወይም ሙስሊም ድሮ ከእዚህ በረት እንደውም እስለምና ይመራ የነበሩቸው ሀገሮችን ኮንሲደር አለም ኢስለም ማንም ነው የሚጠቀመው ፕላስ ደግሞ ሙስሊሙ ብቻም አይደለም ይሄ እሳቸው ኮንሲደር የሚያደርጉት አንዳንድ ጊዜ አስተሳሰባቸው ላይ ከእሳቸው ሄደው ኮርስ የሚወስዱ ሰዎች እንደው ሲነግሩን ነን ሙስሊም የሆኑ የተለያዩ ሀረፋ ውስጥ ያሉ ሰዎችም ሄደው ይወስዳሉ አቼዋሊ እሳቸው በአቅለ ሙስሊም ነው የፃፉት ሜን ታርጌታቸው ሙስሊሞች ናቸው ሀደፋቸው ሙስሊም ነው ሆኖም ግን ሌላውም ሰው ሊጠቀምበት ይችላል /ግልፅ ያልሆነ/

- የመጀመሪያው መፅሐፍ
- ሰዓቱ ወደ 7 ሰዓት ሊሆን ነው ስለዚህ የጠዋቱን በእዚሁ አጠናቀናል ከሰዓት 8 ተኩል ላይ እንገናኝ፡፡

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የኮ/መ/ቁ 124754

ቀን ታህሳስ 3 ቀን 2006 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብስራት ተኽልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ የፌ/ዓ/ህግ 1 ብርሃኑ ወንድምአገኝ ቀረቡ

2 ቴዎድሮስ ጌታቸው ቀረቡ

3 ዘረዘናይ ምስግና ቀረቡ

ተከሳሾች 1. አቡበከር አህመድ ሁሉም ቀርበዋል

2. አህመድ ጀበል

3. ያሲን ኑር

4 ካሚል ሽምሱ

5 በድሩ ሁሴን

6. ሼህ መከተ ሙሄ

7. ሳቢር ይርጉ

8. መሀመደ አባተ

9 አህመድ ሙስጠፋ

10. ሙራድ ሽኩር

11 አቡበከር አለሙ

12 ኑር ቱርኪ

ጠበቆች አዲስ መሃመድ በሃሩመካንጋ

አብደላ አህመድ ጀማል ቀርበዋል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

13 ሺ.ህ ባህሩ ዑመር

14 ሀሰን አሊ

15 ሙኒር ሁሴን

16 ሺ.ህ ሰሂድ አሊ

17 ሺ.ህ ሱልጣን አጅ አማን

18. የሱፍ ጌታቸው

19 ሺ.ህ ጀማል የሲን

20 ሙባረክ አደም

21 ሺ.ህ ጣሂር አብድልቃድር

22 ካሊድ ኢብራሂም

23 አብድራዛቅ አክመል

24 ሀሰን አሊ

25. አሊ መኪ

26. ሺ.ህ አጂ ኢብራሂም

27. ሺ.ህ አብድርአማን ሁስማን

28. ሀቢብ መሃመድ

29 ዶ/ር ከማል ሀጅ ገለቱ

30. አልቢር ዲቨሎኘመንት እና ኦኘሬሽን አሶሴሽን

31. ነማእ የበጎ አድራጎት ማህበር

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው መርምሮ ብይን ለመስጠት ነበር መርምረን የሚከተለውን ብይን ሰጥተናል፡፡

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ብ ይ ን

መዝገቡ ተከፍቶ ለቀረብ የቻለው የዐ/ህግ በቁጥር ፍ/ማ/ፋ.09/121/05 በቀን 15//02/2005 ዓ/ም በተፃፈ የወንጀል የክስ ማመልከቻ በማቅረብ ነው ክክሱም ከ1ኛ -29ኛ ድረስ ያሉት ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በማን እና የአድማ ስምምነት በማድረግ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወ/ህ/ቁ 32/1/ሀ/ለ/ ፣38/1/ እና የፀረሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/1/2/6 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በህገ መንግስት የተቀመጠውን የእምነት ነፃነት በመቃረን ከራሳቸው አክራሪ አስተሳሰብ አስተምህሮት ውጭ በኢትዮጰየ ው ነፃነት በመቃረን ከራሳቸው አክራሪ አስተሳሰብ አስተምህሮት ውጭ በኢትዮጰያ ውስጥ ሌላ እምነት እና አስተሳሰብ እና አስተምሮት እንዳይኖር በሚል ሃይማኖታዊ አላማ እና በሀገሪቱ ሀይማኖታዊ መንግስት መቋቋም የሚል ፖለቲካዊ ግብ በማስቀመጥ የሽብር ወንጀል ፈፅመዋል በማለት በጊዜ በቦታ እና የተከሳሾችን የወንጀል ተሳትፎ እና የወንጀል አይነት በመዘርዘር ተከስዋል የሚል 1ኛ ክስ ነው 2ኛ ክስ በብይን ቀደም ሲል ውድቅ ሆኗል፡፡

23ኛ ተከሳሽም ክስ ተነጥሎ እንዲታይ ተብሎ ተነጥሎ እየታየ ነው 30ኛ እና 31ኛ ተከሳሾች ደግም የወ/ህግ አንቀጽ 34/1/ እና የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዐ/ም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 5/1/ መ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በ17 እና በ10ኛ ተከሳሾች ምክትል ስራ አስኪያጅነት በ30ኛ ተከሳሽ ድርጅት እና በ21ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅነት በ31ኛ ተከሳሽ ድርጅት የሆኑት በ1ኛ ክስ ላይ በተጠቀመጠው የሽብር ቡድን በ**መደገፍ** 30ኛ ተከሳሽ የስበሰባ ቦታ በማዘጋጀት እና መስተንግዶ አገልግሎት መስጠት እንዲሁም የመቀስቀሻ የሆነ ተሽከርካሪ መኪና በመስጠት 31ኛ ተከሳሽ ድርጅት የሰበሰበ እና መስተንግዶ አገልግሎት በመስጠት እያንዳንዳቸው በፈፀሙት የሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት ወንጀል ተከሰዋል በሚል በ3ኛ እና በ4ኛ ክስ ላይ በቅድም ተከተል የወንጀል ስፍራ እና ጊዜ ተጠቅሶ ክስ በመቅረቡ ነው፡፡ ሙሉ ዝርዝሩን ከዋናው ክስ ላይ በመመልከት ይቻላል፡፡

ተከሳሾችም ክሱ ደርሷቸውና በንባብ ከአዳመጡ በኃላ በጠበቆታቸው እየታገዙ በክሱ ላይ የመ/ደረጃ መቃወሚያ አቅረበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ 2ኛ ክስ ውድቅ ሆኖ በ1ኛ 3ኛ እና 4ኛ ክሶች ቀጥለው ተከሳሾችም እምነት ክህደት ሲጠየቁ ሁሉም ክደው ተከራክረዋል፡፡ ዓ/ህግም ተከሳሾች የካዱ ቢሆንም እንደክሱ ያስረድልናል ያላቸውን የሰው የሰነድ የድምፅ ምስል እና

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢግዚቢት ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል። የቀረበው ክስ እና ማስረጃ በመመርመር በእያንዳንድ ተከሳሽ ላይ የአለውን እንደሚከተለው መርምረናል።

በመጀመሪያ ደረጃ የ1ኛ ተከሳሽ አቡበከር አህመድ የቀረበውን ማስረጃ ስንመለከት በመጀመሪያ ደረጃ ተከሳሽ በደሴ ከተማ በቅድሚያ በወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሰረት የሰጠውን ቃል ስንመለከት ተከሳሽ በደሴ ከተማ በቅድሚያ በወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሰረት የሰጠውን ቃል ስንመለከት ከመደበኛ ት/ቤት ውጭ የወሃቢያ አስተሳሰብ የአለው የኃይማኖት ትምህርት እንደተማረ ይህ አስተሳሰብ አንድ ሀገር በቁራን ብቻ መገዛት አለበት በማለት የእስላማዊ የበላይነትም የሚሰበክ ሲሆን ይህን ተቀባዮችም በእውቀት በክህሎት እና በፖለቲካ ንቃት ህሊና ማሳደግ ላይ የቅድሚያ ተግባሩ ነው እኔም ይህንን ተግባር በደሴ በተለያዩ መስጊደኛ እና በደሴ ዩንቨርስቲ በኋላም በአ.አ ከተማ በተለያዩ መስኪዶች አስተምሬአለሁ ከዚያም በ2001 ዓ/ም መጨረሻ በሽር እና አብድልሀፊዝ ከተባሉ ሰዎች ጋር አ/አ ተገናኝተን ምስሊሙን የሚወክል ሚዛን የተባለ ፓርቲ እናቋቁም ብለው ነግረውኝ ነበር ከዝያም በሌላ ቀን ከ11 ሰዎች ጋር ተገናኝተን ለጊዜው የህዝቡን ንቃት ህሊና የሚያነቃ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ሆነን እነሰራለን ተባብለን ፓርቲ መመስረት ቀረ ከዚያም ቆይቶ በ2003 ዓ/ም ጥቅምት ወር ካሚል ሸምሱ እና አህመድ ኑር ከኳታር ተምረው መጥተው የመጡትን መፅሀፍ ለ8 ቀን ስልጠና ወስጃለሁ ስልጠናውም የውሃ ብያ አስተሳሰብ ሆኖ ነቅታችሁ ጠብቁ ጊዜው አሁን ነው የሚል እና ሌሎችም ርዕሶች ነበሩ ከዚህ ስልጠና በኋላ በራሪ ወረቀቶችን መበተን ጀምረን ይህንንም ያለስጋት ለመጠቀም የአጭር የመካከለኛ እና የረጅት እቅድ አወጥተናል ይኸውም ከአጭር ጊዜ እቅድ መጅሊሱን ማውረድ ከመካከለኛ ጊዜ አንፃር በመንግስት ስልጣን 50% መያዝ ከረጅም ጊዜ እቅድ ደግሞ በቀረን የሚተዳደር ወይም እስላማዊ መንግስት ማቋቁም እና ቁሳዊ ህገ መንግስት ማፅደቅ የሚል አለማ ያለው ሆኖ 17 ከሚቴዎች በአዋሊያ በ2004 ዓ/ም ተቋቋም 1/መጅልስም ምርጫ ይካሄድ 2ኛ መጅልስ የህበሻ አስተሳሰብ አይጫንብን 3ኛ አወሊያ በገለልተኛ ቦርድ ይተዳደር የሚሉ ጥያቄዎችን ይዘን በመንግስት አቅርበን ምላሽ ባለማግኘቱ ቅስቀሳውን ቀጥለናል። ስንቀጥልም በውጭ ያለ አንዳንድ ድርጅቶች በመጥቀስ እንረዳችኋለን አይዟችሁ ሲሉን እኛም እስከህወት መስዋትነት እንከፍላለን ህዝቡንም አትፍሩ ከጎናችን ተሰለፉ በማለት ቀሰሰናል የሰደቃ እና የአንድነት ኘሮግራም አዘጋጅተናል ለዚህ ድጋፍም ሼህ ሱልጣን ሀጂ የተባለም ብር 200.000 ሰጥተውናል በዚህ ቅስቀሳም በአዲስ አበባ አንዳንድ በ[illegible] እና ንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል። ለድምፃችን ይሰማ በራሪ ወረቀቶች [illegible] እና CDዲዎች አሳትመን ተንቀሳቅሰናል ከዚህም ጥፋተኛ ነኝ ይቅርታ ይደረግልኝ በማለት በፈቃደኝነት የተሰማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

በተጨማሪ በቀጥታ እና በታዛቢ ምስክሮች በድምሩ ወደ 21 ምስክሮች ቀርበው ሲያስረዱ ከነዚህም አብዛኞቹ ተከሳሽ በመጥቀስ በአወሊያ እና በታላቁ አንዋር መስኪዶች እንዲሁም በሀምዛ መስኪዶች በክሱ ላይ በክቡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለተሰበሰበው ህዝብ ከላይ የተከሳሽ በሰጠው ቃል ላይ የተጠቀሱትን 3 ጥያቄዎች እያነሳ እነሱ አልመለሱም እስከ ህይወት መስዋትነትን እንታገላለን መንግስት የገደላቸው አስክሬን ይሰጠን መስኪድን ተቆጣጥረናል መንግስት እና መጅልስ አዲስ ኃይማኖት አምጡተውብናል ለኃይማኖር መሞት ፀጋ ነው ጅሃድ ማወጅ አለብን ህገ መንግስታዊ ለወጥ ያስፈልገናል መንግስት ከአሜሪካን እና ከእስራኤል ገንዘብ በመቀበል ኃይማኖታችን ሊያጠፋብን ነው ይህንንም እስከመጨረሻው እንታገላለን እና ብንሞትም አይዟችሁ የጀመርነውን የሚያስቀጥል ወጣት አለ በማለት ይቀሰቅስ እንደነበር መስክረዋል ሙሉ እና እና ዝርዝሩ ቃላቸውን ከመዝገቡ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡ ሌሎች የሰው ምስክሮች ቤቱ ሲፈተሽ እና እሜሉ ሲፈተሽ የነበሩ ናቸው በነዚህ ታዛቢዎች ፊት የተገኘ የሰነድ እና የ CDዲ ካሴት ቅስቀሳዎች ታይተዋል ድምፃችን ይሰማ እስራቱ ተጠናክሮ ቀጥሉ እስላማዊ ባንዳዎች አለህ አሳልፎ ይሰጣቸዋል ለዲናችን ደም ከፍለው በማዕናት ከፊት ቆመዋል. መንግስት በኃይማኖት ጣልቃ ገብቷል የግንቦት 20 ድራማ የሚሉ የሰነድ ማስረጃዎች የቀረቡ ሲሆን በሲዲ በአብዛኛው በመንግስት ላይ ጫና መፍጠር አለብህ ጥያቄአችን አልተመለሰም እስከ አልተመለሰ ድረስ እስከመጨረሻው እንቀጥላለን የሚሉ እና የ17 ኮሚቴ የተሰሩ ሪፖርቶች በማቅረብ የሚታዩ ናቸው እነዚህን ማስረጃዎች ድምፅን ስንመለከት ተከሳሽ የነበረውን የወንጀል ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ነው

2ኛ ተከሳሽ /አህመዲን ጀበል ከላይ በ1ኛ ተከሳሽ እንደተጠቀሰ ሁሉ 3 ጥያቄዎች የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ እንዲሆን ከውጭ አገርም ግንኙነት እንደነበረው ጥያቄአችን አልተመለሰም ወንጀልስ ለማውረድ ትኩረት በአወሊያ መስኪድ በ2004 ዓ/ም የሰደቃ እና የአንድነት ፕሮግራም አዘጋጅተን ቀስቀሰናል፡፡ በየመስኪዱም ቀስቀሰናል የመጀመሪያው አመራር ቢታሰር ሌላ ማዘጋጀት አለበን ብለን ተወያየተን ነበር ብዙም ሳይሰራ ቀረ ፈቃድ ሳይኖረን ህገ -ወጥ ስብሰባ አድርገን ህዝቡን ማነሳሳት እና ቀስቀሳ አድርገናል ጥያቄአችን ካልተመለሰ በማለት በመንግስት ለማስገደድ ቀስቀሰናል በዚህ ጥፋተኛ ነኝ እኔ የማላውቀው እና የማላምንበት ግን እስላማዊ መንግስት መመስረት በሚለው ነው በማለት ቃሉን ሰጥቷል በፈቃደኝነት እንደነበረም ተገልፃል ዝርዝሩ ከመዝገቡ ላይ ይገኛል

http://ethcriminalawnetwork.com/

በዚህ ተከሳሽ ላይም በጠቅላላ ወደ 14 የሚሆኑ የሰው ማስረጃዎች ቀርበው አስረድተዋል ጠቅለል በአለመልኩ ተከሳሽ በክሱ ላይ በተጠቀሰ ቀን እና ጊዜ በአወሊያ መስጊድ በአምዛ መስጊድ እና በታላቁ አንዋር መስጊድ በቤኒን መስኪድ በመገናኘት መንግስት ሀበሻ አምጥቶብናል ጥያቄዎችን አልተመለሱም በሚል መንገስትም በኃይማኖት ጣልቃ ገብቷለ በማለት የሰደቃ ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው እንደነበር በነዚህም የሰደቃ እና የሰበሰባ ቦታወች በኃይማኖት መታሰርም መሞትም ፀጋ ነው ወደ 80% የሚሆነው ከዚህ አገር ውስጥ ሙስሊም ነው የራሳችንን መንግስት ማቋቁም አለበን ይህ መንግስት ሀበሻ ስለአመጣበን እያስተዳዳርንም ሺህ አብደላ አረሪን ይደግፋለ እኛ አንፈራም በአወሊያ ብቻ ሳይሆን በመላሀገሪቱ ቀስቀሳ እየተደረገ ነው ይህ ጅሃድ ነው ሞትም ቢሆን አንፈራመ አሁን ብዙ ጆረ ጠቢ ይኖራል እና ብንሞት እናንተ በማለት ይቀሰቀስ እና የነሳሳ እንነበር መሰከረዋለ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቤቱ እና በማዕከላዊ ምረመራ ክፍለ ተገኝተው ከተከሳሽ የተያዙ የሰነድ እና የሲደ ማስረጃዎች እንደተያዙ ገልፀዋል፡፡ ይህን መሰረት አድርገው የተያዙ ሰነዶች እና ሲዲዎች ቀርበው ታይተዋል

ከታዩትም የሰነድ ማስረጃወች ከኮምፒውተር የተገኘ የአህአዴግ መንግስት ለብዙ አመታት የቆየውን ጭቆና አሁን በባሰ ሁኔታ ቀጥሎበታል ሱዳንን እና ጎረቤት አገሮችን እያደከመ ነው የምስራቅ አፍሪካ ተወካይ ሆኗል የ7 ሰዎች ደም እናስብ ብዙ ሰው እየሰራ ነው በርቱ ትግላችሁ ቀጥሉ ጊዜው የእስላም ነው የሚሉ በኢትዮጲያ የአለ አመጽ የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የፈሰሰው ደም ይጣራል እኔም አልታሰርኩም በህበሻ ዙሪያ የተፃፈ በኢትዮጲያ ሙስሊሞች ላይ የአለ ግፍ የሚሉ ፁሑፎች በእኛ የተፃፈ ብዛት ያላቸው ማስታወሻዎች ምስሊም አገር እንደሌለው መገለለ መቻቻል ኑሮ እያውቅም የታሪክ ፀሐፊዎች ስራ እና ተንኮለ ለክርስቲያን ያደላ የታሪክ መዛባት የተዛባው ትረካ ይቁም ኢትዮጲያ ውስጥ እስለማዊ መንግስት እንዳልነበረ የሚካድ አይደለም የአላማው ችግሮች በኢትዮጰየ ምስሊሞች ላይ በመጅልስ እና በመንግስት ጣልቃ ገብተዋል ምስሊም በአገር አቀፈ ደረጃ ለተቃውም በአዲስ መልክ ተደራጅቷል የሚል የሰነድ ማስረጃም የቀረቡ ሲሆን የሲዲ ማስረጃዎች ላይም ከአፄ ዮሐንስ እስከ አሁን እስከአለው መንግስት ድረስ የአለ የሙስሊም ጭቆና ታሪካዊ ዳራ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለውን ግፍ እና በደል የሚያመለክቱ የሲዲ ቅስቀሳዎች ቀርበው ታይተዋል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች ስንመለከት ምንም እንኳን ተከሳሽ እስላማዊ መንግስት ለማቋቋም የሚለውን የማላውቀው ነው የሚል በከፊል የሚል ቢሆንም በሌሎች የሰው እና

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሰነድ ማስረጃ እንደሚያመለክተው የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመ እና ተካፋይ የነበረው መሆን የሚስገነዘበን ነው።

3ኛ ተከሳሽ /ያሲን ኑሩ / ለፖሊስ የሰጠው ቃል ስንመለከት በአወሊያ በተቋቋመው 17 ኮሚቴ ውስጥ አባል የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በዱባይ በኳታር በሳውዲ አረቢያ አይማኖታዊ ትምህርት ወስደ የተመለሰ መሆኑን ከዚያም በኩርቱ ህንፃ ተገናኝተን መክረናል በመቀጠልም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በትምህርት በንግድ በፖለቲካ እንዲሁም ልማታዊ መንግስትም ሀበሻን ስለአመጣብን አስቆጥቶናል ለዚህም በጋዜጣ በካሴት በመፅሔት ቅስቅስናል የሰደቃ ፕሮግራሞችን አዘጋጅተናል ሐምሌ 8/2004 ዐ/መ አንዋር መስጊድም ለተሰበሰበዋ ሰው 63 ሰው በSMS ጥሪ አስተላልፌአለሁ በአወልያ መስጊድ ህገ ወጥ ሰብሰባ መሰብሰቤ ጥፋተኛ ነኝ ምንም ያክል ባጠፋ መንግስት ይቅርታ ያድርግልኝ በማለት በፈቃደኝት የሰጠው ቃል መሆኑ ተገልጾ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል ከዚህ በመቀጠልም በክሱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ እና ቦታ የነበረውን ተሳትፎ የሚገልጽ ወደ 20 የቀጥታ እና ታዛቢ ምስክሮች ቀርበው ያስረዳ ሲሆን ወደ 15 የሚሆኑ ምስክሮች መንግስት ሀበሻ አምጥቶብናል መረገል አለብን በአፍሪካ ህብረት ቀንም ቢሆን መታገል አለብን ለመንግስት መታዘዝ የለብንም እስላማዊ መንግስት እናቋቁማለን በተለይም ይህን ያለው በአንዋር መስጊድ በማጉያ8/11/2004 ዓ/ም መሆኑን ከዚሁ ጋር ተያይዞ መንግስት እጅን ያንሳ የሚል የሰደቃ ፕሮግራም አዘጋጅቷል በቅስቀሳም ወንድሞቻችን ሞተዋል በ.ባል የሞተው ለሀይማኖቱ ብሎ ነው።

ለዱናችን መሞት አለብን መጀልስ አይወክለንም ጥያቄያችን መንግስት መመለስ አለበት የ7 ሰው አስክሬን ይመለስልን በማለት መንግስት ነዳጅ ያርከፈክፋል በተለይ በአወሊያ እና በአኑዋር መስጊድ ይቀስቅስ የነበረ የነበረ መሆኑን መስክረዋል ከዚህ ጋር በታዛቢነት የቀረቡትም ምስክሮች ከተከሳሽ ቤት እና በማዕከላዊ ምርመራ ክፍል የተገኙ ማስረጃዎች የተመለከቱ መሆኑም ገልፀዋል ፈቃደኝነትም የነበረ መሆኑን ገልፀዋል። ይህን መሰረት አድርገው የቀረቡ የቪዲዮ ማስረጃዎች ቀርበው ተይዘዋል የእስላም ታሪካዊ ጭቆና ታሪካዊ ዳራ -የሚል ሰፊ ዘገባ ያለው ኢህአዴግ ኃይማኖትን የሚያፍን መሆኑን ተበለይም በአእህመዲን ጀበል እና የከሚል ሽምሱ ትንታኔ እና ቅስቀሳ የያዘ እና የእስልምና ጭቆና የማያሳዩ የቅስቀሳ ካሴቶች ቀርበው ታይተዋል። እነዚህን ማስረጃዎችን ስንመለከትም የተከሳሹን የወንጀ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ መሆኑን ተገንዝበናል።

http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ተከሳሽ /ከሚል ሽምሱ / ላይ በቅድሚያ የተመለከትነው በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 27 መሰረት ለፖሊስ የሰጠውን ቃል ሲሆን ይዘቱም የ17 ኮሚቴዎች አባል መሆኑን ጠቅሶ በኳታር እና በሌሎች አገሮች ሄዶ ኃይማኖታዊ ትምህርት ወስዶ የተመለሰ መሆኑን ተቅሷል ኮሚቴውም ከላይ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በመያዝ መንግስት ጥያቄ አቅርበን አልተመለሰም በዚህ ምክንያት ቅስቀሳ እና ማነሳሳት ሰርተናል፡፡ ጠቅለል ብሎ ሲቀመጥም የአጭር የመካከለኛ እና የረጅም ግዜ እቅድ በመያዝ መጀመሪያ እስላማዊ ቤተሰብ መፍጠር ከዚያም እስላማዊ ማህበረሰብ መፍጠር ከዚያመ ኢትዮጵያ ውስጥ እስላማዊ መንግስት ማቋቋም የሚል አላማ ይዘው ይሰሩ እንደነበር በተለይም እንዲህ አይነት ስልጠናዎች በኩርቱ ሀንፃ ሰጥተናል በ30ኛ 31ኛ ተከሳሽ ድርጅቶችም ተሰብሰበናል በፊስ ቡክም በስብሰባው ጥሪ አስተላልፈአለሁ የወረቀት ቅስቀሳ በመስጊዶች እየተገኘም ቀስቅሰናለል በአጠቃላይ በ40 አመት ውስጥ መንግስት በመጣል እስላማዊ መንግስት ለማቋቋም የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ብሎ ራሱን በሚጠራው ቡድን በማቋቋም መንቀሳቀሳችን ጥፋተኛ ነኝ ለዚህም ይቅርታ እጠይቃለሁ ማለት ቃሉን የሰጠ ሲሆን በፈቃደኝት የሰጠው መሆኑ ተገልፃል ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀርበው ወደ 12 የሚሆኑ የሰው ምስክሮች ወዲያ የሚሆኑት በክሱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ በአወሊያ እና በታላቁ አንዋር መስጊድ በተሰበሰበው ሰው የ17 ኮሚቴ አባል እንደሆነ መንግስት በኃይማኖት ጣልቃ ገብቷል ሀበሻን አምጥቶብናል በኢትዮጵያ ያለው ስታቲክስ ትክክል አይደለም ከአለው ህዝብ ሙስሉም 65% ነው መንግስት ጠርቶ አያስፈራራንም በመንግስት አንገዛም የውጭ ተቀባይነት አለን ጀሃድ ነው መሞት አለብን የራሳችን መንግስት ወይም ኃይማኖታዊ መንግስት መመስረት እንችላለን ወንድሞቻችን ተጎድተዋል ጎጂው ይጠየቅልን ውሃ እና ኩክስ ይዘው ይመጡ የነበሩ ሰዎች ታስረዋል በማለት ይቀሰቅስ እንደነበር እንዴት እንዳወቁትም ሲጠየቅ በስብሰባው ስማቸን እየተጠራ በተራ ይቀሰቅስ ስለነበር ነው በማለት መስክረዋል ወደ 4 የሚሆኑ ደግሞ በቤቱ እና በእሜል የተገኘ ሰነዶች እና ሲዲዎች የተገኘ መሆኑን በታዛቢነት የተመለከቱ መሆኑን ጠቅሰዋል ይህን ተከትሎ የቀረቡት ሰነደች በላኘቶፕ የተገኙ በአወሊያ መስኪድ ወንድሞቻችን እየተጎዱ ነው እባካችሁ ይህን በዳይ መንግስት እንጣለው ለሁላችንም ነፃነት እንታገል የሚል ለሁሉም ወጣት አዛውንት የቀረበ ጥሪ የአወሊያ መስጊድ በር ተሰብሮ ሙስሊም ተደበደበ አስለቃሽ ጭስም ተወርውሯል ግልፅ መልክት በአሸባሪው መንግስት የሚሉ ይዘት ያላቸው ሌሎችም ሰነዶች ቀርበዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ሲዲዎች በስብሰባ መካከል በስላማዊ መንግድ እስከመጨረሻው እንታገላለን የሚል ቅስቀሳዎች በተለይም በአንድ ሲዲ ላይ በስክሪን በታየው ከ9ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከውጭ በመጣ መፃህፍ ላይ ስልጠና በሚሰጥበት ጊዜ መጀመሪያ ለሙስሊሙ በፊት የነበረውን በደል በመንገር ስሜቱን እንዲኮረክረው ማድረግ ክዚያ ለትግል ዝግጅ ማድረግ ሳይክለፏካል ዝግጅት ማድረስ ክዚህ ከደረሰ በኃላ ማንኛውንም መስዋትነት መክፈል እንዲችል ማድረግ በረጅም ጊዜ ደግሞ እስልማዊ መንግስት መመስረት eslamic stat/ መመስረት እንችላለን በማለት የአረቡን አለም እንትስቃሴ ምን እንደሚመስል በሚገልጽ ስልጠና ሲሰጥ በምስልና በድምፅ ቀርቧል፡፡ እነዚህም ማስረጃዎች ተደምረው ሲታዩ የወንጀል ተሳትፎ የአለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

5ኛ ተከሳሽ /በድሩ ሁሴን/ የሰጠው ቃል የኮሚቴው አባል መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ጉዳይ ከ1995 ዓ/ም ጀምሮ የእስላም ወንድምአማቶች ከሚያራምደው አስተምሮት ቡድን ነበር አለማውም ሙስሊም ግለሰበ ቤተስበ ማህበረበስ እና እስላማዊ መንግስት መመስረት ሲሆን በኃላ ወደ 13 ሰዎች ሆነው ተወያይተው ይህ በእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ በዚህ ጊዜ አይሰራም በማለት ሲጠና ቆይቶ በ1997 ዓ/ም ወደ 20 ሰዎች ሆነው ተሰባስበው ሚዛናዊነት እና የኢትዮ ታሪክ የሚል ተቋቁሞ አሁንም እስላማዊ ወንድሞአማቶች ፊርሶ የተገነባ እንዳልሆነም ተወያይተው ኢትዮጰያዊ መልክ መያዝ አለበት ተብሎ እንደገና ጥናት ተካሄደ አሁንም ሌላ ቡድን ተመስርቶ እንደነበር እና እስላማዊ አስተምሮት ላይ ያተኮረ መሆኑን ጠቅሶ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአወልያ ጉዳይ እና የሙስሊም ጉዳዮች 3 ጥያቄዎች ከላይ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ተጠቅሷ ማለት ነው በዚህ ጉዳይ 17 ኮሚቴ ተመረጦ አብሮ ተመርጦ ይንቀሳቀስ እንደበር ክዚያም ከጎንደር ይመላለስ ስነለበር ስለአልተመቸው መቀጠል እንዳልቻለ ግን ተሳትፎ እና ድጋፍ ያደርግ እንደነበር በሰደቃ ኘሮግራሞች የተሳተፈ መሆኑን እና ድጋፍ ይሰጥ እንደነበር ገልጾየመንግስትም መግለጫ ወደ ጎን በመተው ይህን ጥያቄችን ካልተመለሰ በሚለ በመንግስት ላይ ጫና መፍጠር በሚለው መሳተፉ ጥፋት ነው ይቅርታ ይደረግልኝ በማለት በፈቃደኝነትም እንደሆነ ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ሌላው ወደ 7 የሚሆኑ ምስክሮች ቀርበው ወደ 3 የሚሆኑት ምስክሮች በክሱ በተቀሰው ጊዜ በተለይም በአንዋር መስጊድ በሀምሌ ወር 2004 ወንድሞቻችን ታስረው እኛ መተኛት የለብንም እስከመጨረሻው እንታገላለን መሞት አለብን በብደሴ ላይ ሰው ሞቷል እኛም እንታሰራለን እናንተ ትተኛላችሁ ምስሊም በአልሆኑ ሰዎች እየተመሩ ነው በማለት ይቀስቅስ እና ያነሳሳ እንደነበር በተቀራረበ ቃል መሰክረዋል ሲለዩትም ያቻሉት ስም እየጠሩ ስልነበር ጠቁመዋለ ወደ 4 ምስክሮች ደግሞ ቤት ሲፈተሽ ሲፈተሽ የተያዘበ ሲሆን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ስለይዘቱም እናስታወስም ያሉ ቢሆንም የሰነድ ማስረጃዎች እንደተገኘ ገልፀው ከዚህ ጋር የቀረበውን ስንመለከት ዋና ዋናዎቹ ከቤቱ የተገኘ ድምፃችን ይሰማ የትግሉ ድልም የሁለሙ ሰው ነው ለኢትዮጵያ ሙስሊም የሚሆን የትግል ቅስቀሳ ገዞ ወደ አወሊያ ወደ አወሊያ ጥይት እየተተኮሰ ነው በደሉ ይብቃን ዲናችን እንታደግ ትግላችን መቼ ይቆማል ተወካዮቻችን ሽብረተኛ ማለት ሙስሊሙን መፈረጃ ነው መጅሊስ ይውረድ አቡበከረ እና አህመዲን ጀበለ በፖሊስ ታስረዋለ ኮሚቴዎች መንካት ህዝብ መንካት ነው ተራራ የሚያንቀጠቅጠው የነፃነት ትግል አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች አዜ/ዮሐንስ ሙስሊሙን ሲያስቃዩ አንገታቸውን ተቆርጠ አዜ ኃ/ስላሴ ሽንት ቤት መቀበሪያን ሸሮን ከአሉት በታች ከሞቱት በላይ ነው። የአህዴግ መንግስትም ጀምላ እይጨፌጨፈ ነው የአንዋር መስጊድ ተቃውሞ መሪዎች ይፈቱ ታጋይ ይሞታል ትግል አይሞትም የሚሉ ዕሑፎች ቀርበዋል። እነዚህም ማስረጃዎች እርስበርሳቸው የሚደጋገፋ በመሆናቸው የተከሳሹን የወንጀል ተሳትፎ የሚሳዩ ናቸው።

6ኛ ተከሳሽ /ሼህ መከተ ሙሄ / ከሰጠው የእምነት ቃል በወ/መ/ስ/ስ/ቁ 27/መሰረት ከ17 ኮሚቴዎች ጋር ስሜን አገኘሁት እኔም ፈረምኩ ከዚያም 3 ጥያቄዎችን ይዘን አብሬ ተንቀሳቅሻለሁ ይህም እስከ ጥር የካቲት 2004 ዓ/ም ነው ኩርቱ ህንፃም በአቡበከር ሰብሳቢነት ተሳትፌአለሁ ሌላ ጊዜም 16 ተወያይቻለሁ በሰደቃ ኘሮግራሞች በግንቦት ወር 2004 ዓ/ም በወል እና ማስረጃ ሂደን ጠበቃ ኮማፀቴዎች ብንታሰር ብለን በዚሁ በግንቦት ወር 2004 ዓ/ም በወል እና ማስረጃ ሂደን ጠበቃ ውክልና ከእኔ የተያዘውም የእጅ በግንቦት ወር 2004 0/ም በወል እና ማስረጃ ሂደን ጠበቃ ውክልና ከእኔ የተያዘውም የእጅ ዕሁፍ ሲሆን በተለየዩ ጊዜ የኮሚቴውን ውይይት የያዝኩበት ነው እኔ ኮሚቴ የሆንኩት እስላማዊ መንግስት ለመመስረት አስቤ አላውቅም ነገር ግን ከ17 ኮሚቴ ጋር መንቀሳቀሴ ጥያቄወችን መንግስት ተገድዶ እንዲመልስ ማድረጌ ጥፋት ነው በማለት በፈቃደኝት የሰጠ መሆኑንም በግለፅ ቃሉን ሰጥቷል ። ከዚህ ጋር ወደ 4 ምስክሮች ቀርበው 3ቱ ምስክሮች ተከሳሽ የ17 ኮሚቴ አባል እንደነበረ ወሃብየት ያስፋፋል አህበሻ የሚባል ኃይማኖት አምጥቶብናል መንግስት ይህን ካለስቆመ እስከመጨረሻው እንታገላለን የሚለ ሲሆን ቀሪው ምስክር ደግሞ ቤቱ ሲፈተሽ ታዛቢ የነበረ ሲሆን ይዘታቸውን ባላስታውሳቸውም በአረቢያ እና በአማርኛ የተፃፈ የሰነድ ማስረጃወች የተገኘ መሆኑን እና የተፈራረሙባቸው መሆኑን ገልፀል ከዚህ ጋር ተያያዞ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ በማስታወሻው [illegible] ኮሚቴው መቋቋም እና ኘሮግራሞች ዝርዝር የያዘ ተተኪ ኮሚቴ ማደራጀት [illegible] ስልፍ [illegible] ማቅረብ ከ46 መስግዶች ወደ 100 ማድረስ የሀበሻ ማብሪሪያ የሽግግ[illegible]ወቅት የአገር አቀፍ መጅሊስ ምርጫ

http://ethcriminalawnetwork.com/

እንዴት እናደራጅ ኃይማኖታዊ መንግስት ማቋቋመ ዙሪየ ላያ ፍላጎት አሏቸው በኃላቸው ነጥቦች ላይ ስለጥናት የሚል ሰነድ የሚያወራ ሲሆን በሌሎች ሰነዶች ደሞም የኦርቶዶክስ ቤተብርስቲያን አይገባም ማህበረቅዱሳን ግን አብረውት መንቀሳቀሱን ሊፈልጉት ይችላሉ ብዙ መስዋትነት ይፈልጋል ሽምግልና የሚባል አካሄድ በጣም ጥሩ አይደለም በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ስራዎችን በትክክል ማስቀመጥ በየክልል በየብሔሩ ማደራጀት ሰዎችን መምረጥ የሚገልጽ ዕሁፎች ከኢሜልም በእድሮች ኡላማዎች ድርጅቶች ከውጭ ያሉትንም ማደራጀት ትግሉ ከማነ ጋር ነው።

የሚሉ የእስራት እጣፋንታ ምን ይሆናለ መቃወሚያዎች እንዴት ይዘጋጅ ለሚዲያዎች እንዴት እናሰራጭ ጊዜአዊ እና ዘለቄታ ያለው ውይይት የሚል ኃይማኖታዊ ማህበር መመስረት የሙስሰው ተወካይ የሚሆን የሚለ በመጨረሻም የፖለቲካ ፖረቲ መፍጠር የሚለ ኃሳብ የአለበት ዕሑፍ የተገኘ መሆኑን ነው ሙሉን ከመዝገቡ ላይ መመልከት ነው እነዚህንም ስንመለከት ተከሳሽ በከፊል አምኖ በከፊል የእስላማዊ መንግስት መመስረት የሚለውን አላውቅም የአለ ቢሆንም በሌሎች ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃወች የወንጀል ድርጊቱ ላየ የተሳተፉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

7ኛ ተከሳሽ /ሰቢር ይርጉ /በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 27/1/ መሰረት የሰጠው ቃል ከ17 ኮሚታዎች ጋር አባለ እንደሆነ በወሊያ መስገድ የተለየዩ የቀስቀሳ መፎክር አሰምቻለሁ በ8/1/2004 በአንዋር መስጊድ የሰብሰባ ፕሮግራም መርቻለሁ በፖሊስ የተጎዱ ሰዎችን እየነሳ እንድናገር አድረገአለሁ በአጠቃላየ በህዝብ ላልመረጥ ለ12 ቀን አር አርብ መድረክ መርቻለሁ ስለዚህ የራሴን አስተሳሰብ የህዝብ በማስመሰል መግለጫ እና ቅስቀሳ ማድረጌ ጥፋተኛ ነኝ በማለት በፊቃድም የሰጠ መሆኑን ገልጾ የሰጠው ቃል ነው።

ከዚህ ጋር ተያያዞ የቀረቡ ምስክሮች 7 የሚሆኑ ቀርበው ወደ 5 የሚሆኑት መንግስት ለጥየቄአችን መልስ ካልሰጠን ከዚህ እንቀሳቀስም አቡበከር እንዳለው የሰደቃ ፕሮግራም ተዘግቷል በ80 መስኪዶች ጅሃር መውጣት አለብን መጅልስ አይወስለንም ወደ 60 ማሊዮን ብር ከውጭ እየመጣ መንግስት እና መጃልስ ሌላ ኃይማኖተ አምጥቷል ዱናችን በፍርፋሪ እየተለወጠ ነው በማለት የመሰከሩ ሲሆን ሌሎች የሰነድ እና ሲዲ ሲገኝ መሆኑን በታዛቢነት የተገኙ መሆኑን የገለፀ ናቸው ከዚህ ጋር ተያይዞ የያሲን ኑሩ የተያዘው ሲዲ ላይ በተደረገው ስቅበሳ እስከ መጨረሻው እንረገላለን በማለው ድምጽ ምስል ከታየው ላይ ኢብሮ ተሳታፊ የነበረ መሆኑን ያመለክታለ በአጠቃላይ የሰው እና የሰነድ ማስረጃውን ስንመለከት ተደግጋፊነት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የአለው መሆኑ በተለይም ከሰው ምስክሮች የተረጋገጠው በ80 መስጊዶች ጅሃድ መውጣት አለብን በማለት ሲቀሰቅስ የነበረ መሆኑን አረጋግጠዋል በመሆኑም ተከሳሽ በቀረበው የወንጀል ድርጊት ተካፋይ የነበረ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው

8ኛ ተከሳሽ /መሃመድ አባተ/በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሰረት የሰጠው ቃል የ17 ኮሚቴ ጋር አብሬ ተንቀሳቅሼያለሁ 3 ጥያቄዎችንም ለመንግስት በመንቀሳቀስ ተሳትፌአለሁ ተተኪ ኮሚቴ መርጠናል እኔ የምቃወመው መጅሊሱን ነው እንጂ መንግስትን አይዳለም አንዋር መስገድም በተሰባሰበው ህዝብ 17 ኮሚቴ በአለበት ከሳቢር ይርጉ ጋር መድረክ መርቻለሁ በማለት ቃሉን ሰጥቷል።

ከዚህ በመቀጠስ ወደ 6 ምስክሮች በተከሳሽ ላይ ቀርበዋል 3ቱ በክሱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ በአወሊያ እና በአንዋር መስጊድ መንግስት በኃይማኖት ጣልቃ ገብቷል ለዲናችን ስንል እንሰበሰብ ለሲናችን እስከመጨረሻው እንታገላለን ሰላማዊ ትግል አያዋጣንም ለጅሃድ እንነሳ መንግስት በወሰደው አሰቃቂ እርምጃ ወንድሞቻችን ሞተዋል። ፖሊስም በአወሊያ እና በአንዋር መስጊድ ሰዎችን ገድሏል በአፍሪካ ህብረትም በደሎቻችን እናቀርባለን በማለት ይቀሰቅስ እንደነበር ማን ነው ብለው ስሙን ጠይቀው የተረዳ መሆኑን አስረድተዋል ቀሪዎች ምስክሮች ደግሞ ከተከሳሽ ቤት እና ኮማ8ውተር የተያሉ የሰነድ እና የካሴት ማስረጃወች ሲገኙየታዘቡ መሆናቸውን ገልፀወለ ከዚህም ጋር ተያያዘው የቀረቡ የድምፁችን ይሰማ በውስጡ ሰፊ የትግል ቀስቀሳ በምርጫ አወቃቀር እና ምክር ቤት አመሰራረት በሚል በተከሳሽ እጅ የተገፉ ሰነዶች ከኢሜሉም የተገኘ ዘሬ ሰሚ ጆሮ ያጣው ጩኸህታችን ነገ የሚያናውጥ ኃይል ይሆናል በየመስጊዶች የሚካሄድ የሙብት ጥየቄዎች አስመልከቶ የተሰጠ መግለጫ በአወሊያ የተፈጠረው ሙቀት እንዲይቀዘቅዝ መስጊድ የማይመጡት በይፋ የትግሉ አጋር ማድረግ በእስልምና እና ለክርስትና እምነት ተከታዬች በሙሉ ለህዝባዊ አመፅ እንነሳ የሚል ደብዳቤ የሚል ሰፊ ቅስቀሳ የአለበት የኮምፒውተር ፀሐፊ እና ሌችም በምስሉም ላይ ግፍ ስራዎች እየተጠቀሱ የተደረጉ ቅስቀሳዎች ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል እነዚህን ስነመለከት ተከሳሽ ለፖሊስ የሰጠው ቃል በከፊል የተካደ ቢሆንም በሌሎች የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ተደጋጋፊ በሆነ መንገድ በወንጀል ድርጊቱ ተሳታፊ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው ከዚህም በተጨማሪ በምስል በታዩ ሲዲዎች ውስጥ ከኮሚቴው ጋር ቅስቀሳ የካሄድ የነበረ መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል ።

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

9ኛ ተከሳሽ /አህመድ ሙስጠፋ/ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሰረት የሰጠው ቃል በ1992 ዓ/መ ጀምሮ ከተለየዩ ሰዎች የሙስሉም ብራዘር ሀድ አስተሳሰብ ነበረኝ በዚህም መስማማት ባለመቻሉ እንደገና ሌላ እንቀጥላለን ብለን ተደራጅተን ይህን ለማስፈፀም 20 ሰዎች ተመርጠው 8 ስራ አስፈፀሙ መርጠን በሂደትም እስላማዊ ማህበረሰብ በኢትዮጵየ ውስጠ ለመመስረት ከዚዓመ ጎን ለጎን የኃይማኖት ልዩነተ እነዴት እንፍታ የሚለ ይዘን እየለን በ2001 ዓ/መ ጀመር ከሚል ሽምሱ ካታር ተምሮ መጥቶ መፅሃፎች ላይ ውይይተ አደርገን ከዚያም በተለያየ መስጊዶች ተወያይተው እንዴት መድረክ እንደምንመራ ስራ ተከፋፍለን ከዚያም በአወሊያ ኮሚቴ እንዲመረጥ በማድረግ በወሊያ የነበረውን ብጥብጥ እና ሁለት መርተናል በአጠቃላይ የምስሉም ብራዘር ሁዱ እስላማዊ መንግስት መመስረት የአለውን አመለካከት ብቀብለው በኢትዮጲያ ግን ተግባራዊ ለማድረግ አይቻልም የተለያዩ እምነቶች በአሉበት ሊሳካ እንደማይችል አምኛለሁ ግን ይህን አስተሳበስ ይኸ መንቀሳቀስ እና መደራጀቴ መንግስት አቁመ ሲሉንም ወደ ጎን በመተው ህዝቡን በስሜተ እንዲንቀሳቀስ በአወሊያ እና በአ.አ አካባቢዎች በንግሰት ጫና ለመምከር አመፅ እና ሁከት መምራታችን ጥፋት ነው በማለት ቃሉን ስጥቷል በፈቃደኝነተ የሰጠ መሆኑም ተገለፃል፡፡

ከዚያም በተጨማሪ በተከሳሹ ላይ 4 ምስክሮች ቀርበዋል በተለይም አንዱ ምስክር በሐምሌ 2004 ዓ/ም በአንዋር መሰጊድ በተሰበሰበው ህዝብ መንግስት እጅን የነሳ የወንድሞቻችን ደም ፈሶ አይቀርም እያሉ በሰፊው ይቀሰቅስ እንደነበረ የሚያስረዳ ሲሆን ቀሪዎች ቤቱ ሲበረበር እና ከኮምፒውተር ሲወጣ የኦደትን የሰነድ እና ሲዲ ካሴት በታዛቢነት የፈፀሙ መሆናቸውን የሚያስረዱ ናቸው ከዚህ በመቀጠልም ተከሳሽ ከ4ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን በድምፅ ምስል በስክርን በታየው ሲዲ ካሴት ላይ ሙስሊሙን ማንቃት በሚል መፅሃፍ በመያዝ ለሞት የተዘጋጀ ህዝብ አለ እንዴት እንጠቀምበት እንደት ወደ መሬት እናውርደው በዚህ ህዝብ ላይስ ሶፍትዌሩን እንዴት እንጫነበት አንድ ጊዜ ለሞት ከአዘጋጀነው ወይም ውሃ እስኪፈላ ድረስ እንዴት ማያያዝ /ማሞቅ/ /borling point /ላይ እናደርሰው ከዚህ ከደረሰ ወደኃላ አይመለስም የሰው ባህሪ አይነት በመከፋፋል ትንታኔ በመስጠት ይህን እይሰለጠኑ ማንቃት እና ወደ እስላማዊ መንገድ ማምጣት እና እስላማዊ መንግስት መመስረት እንዲያመች ለሞት የተዘጋጀውን ህዝብ ወደ ትግል የማመጣበትን መንገድ በሙተንተን ስልጠና የሰጠን መሆኑን ያሳያል፡፡

3226

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በሌላኛው ሲዲም በአዋሲያ ወሎ በሚለው ላይ ከሌሎች ጋር በመሆን በተሰበሰበው ህዝብ ፊት ቀስቀሳ እና ማነሳሳት ሲፈፅም የነበረ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከተያዘው የዕሑፍ ሰነድም በኮሚቴው ስበሰባ ላይ በተለያዩ ጊዜ ቃለ ጉባኤ እና ማስታወሻዎችን ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃወች በሚደግፍ መልኩ ተያይዟል በነዚህ ማስረጃወች መሰረት ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት የተሳተፉ መሆኑን የሚያስገንዘቡ ናቸው ፡፡

11ኛ ተከሳሽ /አቡበከር አለሙ /በፖሊስ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሰረት የሰጠው ቃል በኩርቱ ህንፃ ተሰብሰበን ክርስትያኖች የክርስቲያን ደሴት የሚሉትን ምላሽ ለመስጠት ተወያየን ለዚህም እስላማዊ ሚዲያ ለማቅቋመ ተወያየን በዚህ ላይ እንዳለን 10ኛ ተከሳሽ ጠርቶኝ ከተገናኘን በኃላ በሳመንት በሳምንት እንሰበሰባለን የሚል ሲሆን በ 2003 ዓ/ም ደግሞ ተለይቻለሁ ከዚያም እንደገና በአወሊያ በተደረገው ተቃውሞ ላይ በመንግስት የቆሰሉ ሁለት ሰዎችን ሁኔታ አስተላልፌአለሀ ለወጭ አገርም አስተላልፌአለሁ ከኮሚቴው ጋር አብሮ የተንቀሳቀሱ መሆኑን አምኖ ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው የሰው ማስረጃ አንዱ መንግስት ሀበሻ የሚባል ኃይማኖተ አምጥቶብናል በማለት በህዝብ ይቀሰቅሱ እንደነበር በሚያዚያ ወርም ዓ/መ በመጅልስ ተጠርቶ የተሰበሰበውን ህዝብ በመበተን ተንቀሳቅሷለ የሚል ሲሆን ሌሎች ሁለት ምስክሮች ደግሞ ከኮምፒውተር የወጡ የሰነድ ማስረጀ እና በቤቱ የተገኘ የሰነድ ማስረጃዎች ለመገኘታቸው ታዛቢ ሆነው የተመለከቱ ናቸው ይህን መሰረት አድርገው የቀረቡ የሰነድ ማስረጃወች ድምፃችን ይሰማ የሚል እና በእጅ የተፃፈ ማስታወሻ እስላማዊ መንገስት ለምን አስፈለገ ቢላደነን ለምን ያወግዛሉ ቢላደን የተነሳው በእስላም ጠላቶች ናቸው ቢላደንን ያወገዘ ለምን አሜሪካ እና እስራኤልን ለምን አላወገዘም እስልምናን አላማ ከአደረጉ እና ትግል ከአሉ ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር አስልምና ያለመለመ ፖለቲካ ጥያቄ ማንሳት ሙስሉምችን የሚያስተዳድራቸው ሸሪያ ነው በመንግስት ምርጫ አትሳተፉ ግብዕ ሻቢያን ይዞ ሲያተራምስ ይፈልጋል ነገር ግን የትግሬ እና የአማራ መንግስት እንቅፋት ሆኖባቸዋል እና ሌላም ሰፋ ያለ ይዘት ያለው የሰነድ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይህም አለም አቀፍ አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀውን ሀሳቡን በመቀጠል እና በማንገስ ቅስቀሳው እና ማነሳሳት በወንጀል ድርጊት ተካፋዩ የነረ መሆኑኑ ግንዛቤ ተወስደበታል፡፡

15ኛ ተከሳሽ /ሙኒር ሁሴን /የሰጠው ያእምነት ቃል/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 27 መሰረት ሲሆን ተከሳሽ ከ1995 ዓ/መ ጀምሮ ውሃቢያ ኃየማኖር ተከታይ ነኝ በአወሊያ ተቃውሞ

http://ethcriminalawnetwork.com/

በዚሁ ተቃውሞም 3 ጥያቄዎችን ተነስተው በኮሚቴው ምርጫውመ ተሳትፌአለሁ በወቅቱም በአወሊያ ለዚህ በሰጠው ህዝብ አመፅ ቀስቀሽ ግጥም አቅርቤአለሁ ሌሎችም ግጥሞችን ስያመጡ እኔ አይቻቸው ነው የሚያልፉት በሰደቃ እና አንድነተ ፕሮግራምም ተሳታፊ ነበርኩኝ የእንቅስቃሴው አላማ እስላማዊ አላማ መገንባት ዩንቨርስቲዎችን ማቋቋም የመጅልስን ስልጣን መቆጣጠር ስልጣኑን ከተረከብን በኃላ የረጅም ጊዜ እቅድ እስላማዊ መንግስት ማቋቋመ ይመስለናል የሚል ቃል አሰመዝግቧል ይህመ በፌቃደኝት የተሰጠ መሆኑንም የሚጠቁም ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል የቀረበው ታዛቢ ምስክር ሲሆን ቤቱ ሲፌተሽ የተያዘ የሰነድ ማስረጃወች የቪዲዮ እንዲሁም ወደ 90 ሺ ብር የተገኘ መሆኑን እና ብሩንም ከውጭ ባለቤቱ የላከችለት መሆኑን የነገራቸው መሆኑን የሰማ እና የታዘበ ምስክር ነው ይህን መሰረት አድርጎ የቀረበው ሰነድ እስላም ሰላም ነው እና ውሻ አይዳለንም አሳልፌው የሚሰጡ መናፍቃን ናቸው የሚሉ እና ሌሎችም ሲያነሳሳ እና ሲቀሰቅስ የሚችል ቃላቶች በመጠቀም ተሳታፊ መሆኑን የሚያመለከቱ ናቸው በመጨረሻም የቀረበው ከ3ኛ ተከሳሽ ላይ በተያዘው የድምፅ ምስል ሲዲ ካሴት ላይ ቀደም ሲል በእምነተ ቃሉ እንዳስቀመጠጠው ግጥም በማቅረብ እሱም በንዴት እና በለቀሶ አዎ አሸባሪነኝ የሚለ የአለበት ሌሉም አብዛኛውን ህዝብ እንባውን እያፌሰሰ እና እያለቀሰ የሚያነሳሳ ቅስቀሳ ቀርቦ ታይቷል፡፡ ከላይ ከእምነተ ቃሉ ጀምሮ እስላማዊ መንግስት ለማቋቋም እቅድ እንደበራቸው ይህንን ለማሳካት በተለያዩ ቅስቀሳወች እና ማነሳሻዎች ላይ እንድንሳተፍ የሚያስረድ በመሆኑ የወንጀለ ድርጊተ ላይ ተሳታፊ የነበረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

16ኛ ተከሳሽ /ሼህ ሰኢድ አሊ / በበኩሉ በወ/መ/ህ/ስ ቁ 27 መሰረት የሰጠው ቃል በፌቃደኝነት እንደሆነ ገልጾ እኔ ውሃብየ ሰነፊ ኃይማኖት ተከታይ ነኝ ሱዳን ነበርኩኝ ከዚህም ተመልሶ ቂራ መስጊድ እንደሚስተምር ሀበሻ ተማር ተብሎ ተጠይቂ አልፌልገም አልኩኝ የኮሚቴው ምርጫም አገር አቀፍ እንደሆነ ለማሳወቅ የሰደቃ እና የአንድነት ፕሮግራም የተዘጋጀ እና የተሳተፉ መሆኑን በዚህም በሚሴጅ ጥሪ ሲያስተላልፍ የነበረ መሆኑን በመቀጠልም ከ30 እና ከ40 አመታት በኃላ በኢትዮጵያ ውስጥ እስላማዊ በሸሪያ የሚተዳደር መንግስት ለማቋቋም አለማ የነበራቸው መሆኑን ይህንንም ለማስተማር የተሳተፉ መሆኑን የሚገልፅ ሰፊ ገለፃ ያለው ነው፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከዚህ በመቀጠል የቀረበው ምስክር በሐምሌ ወር 2004 ዓ/ም ተከሳሽ በአቡበከር አህመድ ጋር በመሆን በቤኒር መስጊድ በተሰበሰበው ህዝብ መድረክ ላይ ወጥተው ምርጫችን በመስጊዶች መጅልስ አይመራንም የለፋንበትን የደከምንበትን ማንም አይወስድም እስከ ህይወት መስዋትነት እንታገላለን እያሉ በተራ በተራ እየተጣሩ ይናገሩ ነበር እኔም አብሬ ነበርኩ በማለት አስረድቱል ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበው ከቤቱ እና ከላፕቶፕ ላይ የተገኘ የሰነድ ማስረጃዎችን ለመታዘብ የቀረቡ ሁለት ምስክሮች የተመለከቱ መሆኑን ገልፀዋል በዚህም መሰረት የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ኮሚቴዎች በአሸባሪነት ተፈርጀዋል ሁላችንም ወደ አወሊያ ኮሚቴዎች ቢታሰሩም ትግላችን ይቀጥላል እና እስላማዊ መንግስት ለማቋቋምም እንጂ ሽብር ለመፍጠር አይዳለም የሚል ከኢሜል የተገኘ ማስረጃ የስረዳል ፡፡ ለሳው ከዚህ ተከሳሽ የተያዘ 17 ሰዎች ታሰሩ ህዝቡ ነቅቶ መጠበቅ አለበት የአፍሪካ ህብረት መሪዎች ስብሰባ ጊዜ ዲናችን ተደፍሯል የሚል ከBBN ካሴት ተደምጧል አላህ አክበር የሚል እና ስደት ሞት ረሃብ ስለመጅልስ እና አህዲህ ሙስሉሙን አለመቀበል የሚል ቅስቀሳ ይዘት ያለው ሲዲ ቀርቡል ይህ ማስረጃ ጠቅለል ተብሎ ሲታይ የወንጀል ድርጊቱ ተሳታፊ የነበረ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

20ኛ ተከሳሽ /ሙባረክ አደም/ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሰረት የሰጠውን ቃል በፈቃደኝነት መሆኑን ገልጾ እኔ የተማሪወች እንቅስቃሴ አስተባብሬአለሁ በአወሊያ የተጠራ ስብሰባ ተሳታፊ ነበር በ8/11/2004 ዓ/መ ለሚደረገው የሰደቃ እና የአንድነተ ኘሮግራም ገንዘብ ያሰባስበ እንደነበር ኮሜቴው /ቡድኑ/እስላማዊ መንግስት ለማቅቋም ሲንቀሳቀስ አብሬ ተንቀሳቅሻለሁ በዚህም ጥፋተኛ ነኝ በማለት አስመዝግቧል፡፡

ከዚህ ጋር ተያያዞ 4 ምስክሮች በተከሳሽ ላይ የቀረቡ ሲሆን ያስረድትም በጥር ወር ዐ/ም በአወሊያ መሰጊድ ት/ቤት ተማሪዎችን በስብሰብ በማነሳሳት መጅልስ ይውረድ መንግስት ጣልቃ አይግባ በኃይማኖታችን ድርድር የለም የአረብኛ ኮሌጅን መንግስት ዘግቷል ተማሪዎች ቤታቸው እንዳይሄዱ ይከላከሉ ነበር በዚያው ወር እና ዐ/መ አንድ ከእስልምና ጉዳዮች እንደ ተወካይ መጥተው ጉዳዩ ምንድ ነው በማለት ስብሰባ ሲጀምር እና ጉዳዩን ሲናገሩ ሌላ ተከሳሽ ማይኩን ነጥቆ ወስደባቸው ነገ ወስድ በኃላ ተወካዩ ሲውጡ ሲሉ ሲደበድቧቸው ስለነበር ከግቢ ውጭ ፖሊስ ስለነበር ወዚያ ወጡ ሲወጡ የመጡበት መኪና ነበር ከበው ተከሳሽ ጭምሮ

http://ethcriminalawnetwork.com/

የመኪናውን 4 ጎማ አስተንፋሱት በተለይ ፖሊስ ይህ ጥሩ አይደለም ብለው ከአንድ ምስክር ጋር ሲነግሩት እሱም በኃየማኖት አስከፍሻማ አሄዳለሁ ያለ መሆኑን እሳት እና ሙስሊም ከነኩት አይፈራም ይል እንደነበር ሶስቱ ምስክሮች ያስረድ ሲሆን ሴላ ደግሞ በወሊያ በአሊያ ተከሰሽ በአወሊያ መድረክ ሲመራ እሱም ተከትሎ ያስፈጽመ ነበር በማለት አስረድተዋል ፡፡ ይህመ ማስረጃ ከእምነት ቃል ጋር ተገናዝበው ሲዩ በወንጀል ድርጊት ውስጥ ተሳታፊ የነበረ መሆኑን የማያስገነዝብ ነው፡፡

22ኛ ተከሳሽ /ከሊድ ኢብራሂም/ በፖሊስ የሰጠው ቃል 17 ኮሚቴዎች መመረጣቸውን እንደሚያውቀ ድምፃችን ይሰማ የሚል የበተነ መሆኑን ኮሚቴው በህገ ወጥ መንገድ መቋቋሙን አላውቅም የሰደቃ እና አንድነት ፕሮግራም ድንኳን እና እንጨት በማምጣት ተሳትፌአለሁ የሚል ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበው አንድ ታዛቢ ምስክር ሲሆን ከተከሳሽ ቤት የተገኘ ወደ 86 የቴፕ ካሴቶች የኢትዮጵያ ምስሊም ከየት ወዴት የሚል መፅሄት እና ጋዜጣ ወደ 5 የሚደርሱ በራሪ ወረቀቶች ቀርበዋል ከዚህመ በተጨማሪ በብሔራዊ መረጃ እና ድህንነት ቢሮ የድምፅና እና በአጭር መልከት የተወዋወጡኩት በቀን 15/11/2004 ዓ/መ የተቃውሞ እንቅስቃሴ መቀጠል እንዳለበት እና በኃየማኖታችን ጠላት የሆነ ሰዎችን ታርጌት አድርጎ መግደል እንቀስቃሴአቸውን ማስቆም ብሎ ለአንድ ስሙ ላልታወቀ ሰው መመሪያ የሰጠ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያያዟል እነዚህም ማስረጃወች ስንመለከት ተያየዥነት የላቸው እና የወንጀል ድርጊቱን የተሳተፉ መሆኑኑ የሚያመለክት መሆኑ ፍ/ቤት ተገንዝቧል፡፡

ወደ ሌሎች ተከሳሾች ከማየታችነ በፊት ከዚህ በላይ የቀረቡትን ከ1ኛ --9ኛ ተከሳሾችን እንዲሁም 11ኛ 15ኛ 16ኛ 20ኛ እና 22ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ የቀረበው ክስ እና ማስረጃ በአለቸው የወንጀል ተሳትፎ መጠን ስንመለከት ክሱ እንደሚያመለክተው እነዚህ ተከሳሾች በጋራ እና በተናጥለ በኮሚቴ ተተደራጅተው በማሴር በመዘጋጀት በአነሳሽት እና በቀስቀስት ምክንያት

http://ethcriminalawnetwork.com/

በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በታላቁ አኑዋር መስጊድ በመነሳት መርካቶ አካባቢ እና በዚያው ባዩሽ መስጊድ አካባቢ የመንግስት የከተማ አውቶብስ እና የግለሰብ መኪኖች እንዲሁም ሕንፃዎች ይህን ለማስከበር የወጡ ሕገ አስከባሪዎች የአካል ጉዳት እንደደረሰ የደረሰውም ጉዳት በክሱ ላይ በተጠቀሰው መልኩ እንደሆነ 22 በሰው ማስረጃ በህክምና ማስረጃ እንዲሁም የወደመ ንብረት በባለሙያ ግምት ተረጋግጧል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ሲደርስ ግን በመነሳቱ ምክንያት የተፈጠረ ብዛት ያለው ሕዝብ በመውጣት የፈፀመው በመሆኑ የዚህ ድርጊት ተካፋይ የሆነውን መለየት ያልቻሉ መሆኑን እና ምስክሮችም በአጠቃላይ በተፈጠረው ድርጊት እንጂ በተናጥል ማን እንደፈፀመ በመለየት እንደማይችሉ ነው፡፡ ሙሉ ዝርዝሩን ከመዝገቡ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

አሁን ከዚህ በላይ ሲነሳ የሚችለው ጉዳይ ተከሣሾች የነበራቸው የወንጀል ድርጊት በቀረበው ክስ መሠረት ያሚላል አያሚላም የሚለው ነው፡፡ ይህንንም ስንመለከት የፀረ ሽብር አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ጉዳቱን ራሳቸው በአካል የፈፀሙት ለመሆኑ መረጋገጥ የሚገባው ነው ተከሣሾች ላይ የቀረበው ማስረጃ ስንመከተው ከተከሣሾች ውስጥ በቀጥታ በንብረት በአካል ጉዳት ላይ የተሳተፈ መሆኑን አመላካችም የሚያመለክተው ቀደም ብለን በክስ ዝርዝር ላይ አልፎ አልፎ እንደተገለፀው ለደረሰው ጉዳት መንስኤ የሆነውን ጉዳይ እንዲፈፀም በጋራ እና በተናጥል በመሞከር በመዘጋጀት በማቀድ በማነሳሳቱ እና በመቀስቀስ እና ከረጅም ጊዜ የሚፈለገው የእስላማዊ መንግስት ምስረታ አላማ ለማሳካት መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የተከሣሾች ድርጊት ሊሸፈን የሚችለው በተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ ሳይሆን በፀረ ሽብር አዋጅ አንቀጽ 4 ሥር ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተከሣሾች የተከሰሱበትን የሕግ ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 113/2 መሠረት በመቀየር በወ/ሕ/ቁ 32/1/ሀ 38 እና የፀረሽር አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 4 መሠረት ለውጠን በዚሁ በተመስከረባቸው መጠን እያንዳንዳቸው መከላከል እንደሚገባቸው ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

10ኛ ተከሣሽ ሙራድ ሽኩር በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሠረት በፖሊስ የሰጠው ቃል በማህበረ ቅዱሳን የክርስትና ኃይማኖት ተከታዮች ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት እያሉ በመጽሄት እና በቲሸርት ስለሚያወጡ እኛም ለዚህ ምላሽ ለመስጠት መስራት ጀመርን ወደ 12 የሚሆኑ የተጠቀሱትን ተከሣሾች ስም ዝርዝር በመጥቀስ እና ሌሎችን በመጨመር ሲሰሩ እንደቆዩ በመቀጠልም በመስሊሙ ውስጥ ያለውን እንዴት እንፍታ በሚል ተወያየን በዚህ ዙሪያ ቁራን እና ኃይማኖታዊ ታሪኮች ሙስሊሚያ አካባቢ ተወያየን

ን

3231 1016

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሌላም መጽሃፍ ላይ ዙሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ በሚለው ላይም ተወየይተናል አህመድ ሙስጠፋ እና ከሚል ሸምሱ ኳታር ሄደው ተምረው መጥተው "ናሂዲ" የሚል መጸሃፍ መስሊሙን መነቃቃት የሚል ስልጠናም በ2002 ዓ.ም. እንደወሰዱ ከዚያም በመቀጠል ሙስሊሙን በንግድ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም ማሳተፍ አለብን በሚል ቀጥለጥ ቢያንስ ጠቅላይ ሚኒስተር ወይም ም/ጠቅላይ ሚኒስተር ሙስሊም መሆን አለበት በ20 እና በ30 ዓመታት በሁሉም መስክ ብቁ ማድረግ ወደ ፊት ሙስሊሙ ስልጣን ላይ ከወጣ ለቀጣይ ለምንፈልገው መንገድ ምቹ ይሆናል በማለት ጥረት አድርገናል በዚህም ነው ቀደም ሲል የተጠቀሰውን በመደገም ከሚል ሸምሱ እና አህመድ ሙስጠፋ በዶ/ር ደሶን የተባፊ ከቁጥር 1-6 ተከታታይ ምዕራፍ ያለውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዉ ጉዳይ ላይ ሙስሊሙ እንዲነቃ የሚለው የተማረ ነው ከዚያም በኋላ ነው 17 ኮሜቴ ተቋቁሞ ሃበሻ መጥቶ መጂልስ በዚህ ገፋ በማለት በመቃወም እንቅስቃሴ ተደምሮ ጥያቄዎችንም በመንግስት ለማቅረብ ሕዝቡንም በማሣወቅ ተንቀሳቅሷል ከዚያም ጥያቄዎች አልተመለሰም በሚል የሰደቃ ፕሮግራም አዘጋጅተን ቅስቀሣ አድርገናል እኔም ገንዘብ በማሰባሰብ ወረቀት በመበተ ተሳትፌአለሁ በኋላም እጅ በእጅ በመያያዝ ስልፍ አድርገናል በማለት በዚህም ጥፋት እንደሆነ በፈቃዱም እንደሰጠ የሚያመለከት ቃል ተያይዟል። በመቀጠልም በዚህ ተከሣሽ ላይ የቀረቡት 5 ምስክሮች ሲሆኑ አንድ ምስክር ተከሣሽ ጠርቶ ዘካ ክፍል አለኝ ለታሰሩ ሰዎች የሚሆን ነው ብሎ ብር 50 ሺህ ብር ሰጥተዋቸው ያለ ሲሆን ሌላኛው ምስክር የአልቢር ደቨሎኘመንት ሥራ አስኪያጅ ሚያዚያ 4/2004 ከቀኑ 10 ሰዓት ጠርቶኝ ተ/ኃይማኖት አካባቢ መኪና ይገፍ ሄድኩኝ ከዚያም ተከሣሽን አገኘሁት ወደ ካራቆሬ ውስደኝ አለኝ ይገፍው ሲሄድ በፖሊስ ተያዝን ከመኪናው ውስጥ ድምጻችን ይሰማ የሚል በራሪ ወረቀት ተያዘ የእኔ ነው በማለት ተከሣሽ ገለፀ መኪናው በተያዘ ጊዜ የተገኘውም ሌላ ምስክር በዚህ ቀን ከምሽቱ 1:30 ሲሆን ነፋስ ስልክ አካባቢ የሰሌዳ ቁጥሩ 3574 አ.አ ፒካፕ መኪና ስንፈትሽ ብዛት ያለው በ3 ቦታ በክብ በክብ ተጠቅልሎ በፌስታል አገኘን ሳየው ይሰማ የሚል ነው ሹፌሩን ስጠይቀው የተከሣሽ ነው አለ ተከሣሽም የኔ ነው ብሎ ያረጋገጠለት መሆኑን መኪናውም የአልበር ደቨሎኘመንት የሚል ድርጅት ነው ብሎ ሹፌሩ የነገረው መሆኑን እንደገለፀለት አስረድቷል ሌሎች ሁለት ምስክሮችም የተከሣሽ ቤት ሲፈተሽ የተገኘ የሰነድ ማስረጃዎችን በታዛቢነት የተመለከቱ ናቸው እነዚህን ማስረጃዎች ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው ከእምነት ቃል ጀምሮ በኮሜቴው ስልጠና ወስዶ ድምፃችን ይሰማ የሚል ወረቀት ይዞ የተገኘ መሆኑን እና

2

http://ethcriminalawnetwork.com/

በገንዘብ አሰባሰብ እና እስረኛ ማስፈታት በሚለው የተሳተፉ መሆኑን የሚያመለክት ነው ይህ ደግሞ በፀረ ሽብር አዋጅ አንቀጽ 3 ሥር የተጠቀሱትን የሚያሟላ አይደለም በመሆኑም ሊያሟላ የሚችለው በቀረበው ክስ ላይ የቀረበውን ለመፈፀም ስልጠና መውሰድ እና በማናቸውም መሳተፍ በሚለው በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 7/1/ ሥር የሚወድቅ ነው በመሆኑም በዚሁ በተመሰከረበት መጠን መከላከል እንዳለበት ፍ/ቤቱ አምኖበታል።

12ኛ ተከሣሽ /ኑሪ ቱርኪን/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት በፈቃደኝነት ነው ብሎ ቃሉን ሲሰጥ እኔ ወይም ስልፊ ነኝ ይህን በማጠናከር ለኮርቱ ሕንፃ ተወያይተናል ክርስቲያኖች አንድ ጥምቀት አንድ ክርስትና ሲሉ ለዚህ ምላሽ ለመስጠት ተወያይተናል ጅሃድ እንዴት ይካሄዳል እስላም ፍርሃቱን ትቶ ለጅሃድ እንዴት መዘጋጀት አለበት የሚል ተወያይተናል የሚል ሲሆን

ሌላ የቀረበ ማስረጃ አንድ ታዛቢ ሲሆን የተከሣሽ ቤት ሲፈተሽ ከ60 በላይ ሲዲ ካሴቶች ከ20 በላይ የቴፕ ካሴቶች በእጅ የተፃፈ ደብዳቤዎች ሰልፍ የሚል ጋዜጣ አንድ ሞባይል የተገኙ መሆኑን ሲገልጽ በእጅ የተፃፈውን ይዘቱን አላስታወሰውም በማለት አስረድቷል። ይህ ተከትሎ የቀረበው ማስረጃ ድምፃችን ይሰማ የሚል እና በእጅ የተፃፈ ሃበሻ እድሜው አጭር ነው የበሬ እና የሽንኩርት መግኘ የሚል ነው ከዚህ ውስጥ በእጅ ከተፃፉት እና ከድምጾች ይሰማ ውጭ ያሉት በማስረጃነት ጠቅሶ አልቀረበም ቀርበውም አልታዩም።

ከነዚህ ማስረጃዎች የምንረዳው ተከሣሽ ከቀረበበት ክስ ውስጥ በቤኒን መስገድ የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ.ም. ያደገው ቅስቀሣ ላይ የቀረበ ማስረጃ የለም ወይም አልስረዳም ቀደም ብሎ ግን በ2001 ዓ.ም. ጀምሮ በእምነት ቃሉ የሰጣቸውን ጉዳዮች እየተሰበሰበ ይወያይ እንደነበረ እና ድምጾችን ይሰማ የሚሉ ወረቀቶች የተያዙበት መሆኑን እንዲሁም ለሰደቃ የሚሆኑ የበሬ እና የሽንኩርት መግኘ የሚሉ የእጅ ጽሑፎች የተገኙበት መሆኑ ሲታይ የከሣሽን ተሳትፎ የሚያሳዩ ናቸው ተሳትፈውን ግን ስንመለከተው ቀደም ሲል የነበረ ውይይተ በኮሚቴው ውስጥ የተሳተፈ መሆኑ በቅስቀሳም የሰደቃ እና አንድነትም ድጋፍ መስጠቱ ከኮሚቴው ማገዝ ጋር የተያየዘ በመሆኑ በእምነት ቃሉ እንደጠቀሰው ጅሃድ እንዴት ይካሄዳል የሚል ስልጠና ወስዶ መሆኑ ሲታይ ተከሣሽ ድርጊት በተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ ሳይሆን በፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 7/2/ መሠረት ሊካተት የሚችል በመሆኑ በዚሁ ይከላከል ብለናል።

ገ

3237 1078

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

13ኛ ተከሣሽ ሺ.ህ ባሕሩ ኡመር በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/ መሠረት የሰጠው ቃል 3 ጥያቄዎችን በመንግስት ለማቅረብ ተንቀሣቅሻለሁ በኮርቱ ሕንፃም በዚህ ጉዳይ ተወያይተናል ጥያቄው ምላሽ እስኪያገኝ በጥናት ጠበቃ እስላማዊ መንግስት በመቋቋም አልተንቀሳቀስኩም የሚል ሲሆን ከኮሜቴውም አቋርጭ ነበር ግን መምህር ስለሆነ እንደገና ማገዝ ጀመርኩ የሚል ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ምስክር መስጊድ የተሰበሰበውን ሰው ማን እንደጠራ ሲጠይቅ ተከሣሽ እንደጠራ ነግረውናል የሚል ሲሆን ከዚሁም በመቀጠል ከያሲን ኑሩ በተገኘ ሲዲ ላይ የኢ/ምስሊሞች የሙብት ጥያቄ እና ሠላማዊ ትግል ቁጥር 2 በሚል ካሴት ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሲነጋገ ሲል ይጨልማል ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ኃይለ ስላሴ ድርስ ብሎም እስካሁን ድረስ የሙስሊሙ ጭቆና ያለውን ቀደም በአሉ መንግስታት ወይ ክርስቲያን ሁን ወይም አገር ለቀህ ውጣ የሚል እና አሁንም ፈተናው በዝቷል በ6 ማምንት ትግል ላይሳካ ይችላል ከባድ ፈተና ይገጥመናል ትግሉ አረጅም ነው ጽናት ያስፈልጋል የሚል ማነሳሳት እና መቀስቀስ ላይ የተሳተፈ መሆኑን ቀርቦ በችሎት ከታየው መገንዘብ የሚችል ነው፡፡ ተከሣሽ ምንም እንኳን የእምነት ቃሉን ሲሰጥ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት አላማ የለኝም በማለት የገለፁ ቢሆንም ኮሚቴውን ማገዙን መረዳት ይቻላል ከዚህም በላይ በተሰበሰበ ሕዝብ መኃል ከላይ የተጠቀሰውን ቅስቀሣ እና ማነሳሳት ኮሚቴውን በማያግዝ መልኩ የረዳ መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው ይህ የወንጀል ተሳትፎም አሁን በቀረበበት ክስ የሚያርፍ ሳይሆን በማናቸውም መልኩ መሳተፍ በሚለው በፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 7/1/ ሥር የሚካተት ስለሚሆን በዚሁ እንዲከላከል ፍ/ቤቱ አምኖበታል፡፡

18ኛ ተከሣሽ የሱፍ ጌታቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27 መሠረት የሰጠው ቃል ፊ.ቃደኛ መሆኑን ጠቅሶ በጋዜጣ ላይ ቅስቀሳ ይጽፍ እንደነበር በ2004 ዓ.ም. በአወሊያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በማድረግ በቅስቀሳው ወቅትም መግልጫዎችን እና ጥያቄዎችን በዜና ያስተላልፍ እንደነበር ገልጿል፡፡

ከዚህ በመቀጠል 6 ምስክሮች ቀርበው በተከሣሽ ላይ ሲያስረዱ ስብሰባ ላይ መበጥበጥ እንዲሁም የቅስቀሳ የሚሆን ወረቀት ይበትን እንደነበር ሁለቱ ምስክሮች ያስረዱ ሲሆን ቀሪዎች ከላፕቶፕ እና ሃርድ ዲስክ እና የሰነድ ማስረጃ ... የነበሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የቀረቡት የሰነድ ማስረጃ በእጅ የተፃፉ ጠበንጃ አንሱ የሥርዓት ለውጥ ያስፈልጋል ትግሉ ይቀጥል የሚሉ ... ድምፃችን ይሰማ ላይ ደግሞ በኢትዮጵያ አንድነት ዘላቂነት አይኖርም ... ለይለን ሠላም ሲበዛ እራሱ

ገ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያማል እስላማዊ መንግስት መመስረት ሲሉኝ የኃይማኖት ነፃነት የለም የኃይማኖት መሪዎች ለመንግስት ሰለባዎች ሆኑ እኔ ወሃብያ ነኝ BBN ድረገጾች ላይ የተሰሩ ሥራዎች የወያኔ እና የአላሙዲ ፌሲቲቫሎች አወሊያ የተቃውሞ አደባባይ የሚሉ እና ሌሎችም ቀርበው ታይተዋል፡፡ በመጨረሻም ከ16ኛ ተከሣሽ የተያዘ ሲዲ ላይ ካሴት ላይ የኘሮግራሙ መሪ ሆኖ ሕዝቡ ነቅቶ መጠበቅ 17 ሰዎች በ3 ተከፋፍለው ታስረዋል የሚል ቅስቀሳዎች የሚያመለክት ማስረጃ ያመለክታል ይህም የወንጀል ተሳትፎውን የሚያሳይ ነው ሆኖም ግን የወንጀሉ ተሳትፎ ግን የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሱትን የሚያሟላ ሳይሆን በዋና ወንጀል ፈፃሚዎችን በማናቸውም መንገድ በመደገፍ የተንቀሳቀሰ መሆኑን የሚያሣይ በመሆኑ በዚሁ አዋጅ ቁጥር 7/1/ ሥር መከላከል የአለበት መሆኑን ፍ/ቤቱ ግንዛቤ ወስዷል፡፡

14ኛ ተከሣሽ ሃሰን አሊ በወ/መ/ሕ/ቁ 27 መሠረት የሰጠው ቃል ፈቃደኛ መሆኑን ገልፆ በሌሎች ሲጠየቅ የነበሩ 3 ጥያቄዎችን ጠቅሶ ወደ ሚመለከተው ሲያደርስ እንደቆየ የተመረጡ ኮሚቴዎች መፃሃፍ ከ15ኛ ተከሣሽ ብር 15 ሺህ ብር ተቀብሎ ራሱም 19 ሺ. ብር ጨምሮ የአሳትም መሆኑን ጠቅሶ ከሚል ሽምስ እና አህመድ ሙስጠፋ በሰጡት ትምህርት ተከታትየአለሁ በኮሚቴውም ተሳትፎ አድርጌአለሁ በማለት የእምነት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበው አንድ ታዛቢ ምስክር ሲሆን ተከሣሽ ቤት ሲበረብር ተከሣሽ በሌለበት ነው ወደ 200 ሲዲዎች መጽሃፍ ቅዱስ ሬዲዮ መቅረጫ ብዙ መጽሃፎቶች እና ቁራኖች የተገኘ መሆኑን ታዝቤአለሁ በማለት አስረድቷል ከዚሁ ጋር ተያይዞ በማስረጃነት ተያይዞ የቀረበው በ08/10/2004 ዓ.ም. 23 ሣምንት 2 ገጽ ማስረጃ ቀርቦ ተመልከተነዋል በሲዲ ተይዟል የተባለው ከቀረበት ውስጥ አልተገኘም ከቀረበት ወጭም 0/ሕግ በቂ ነው ያለ በመሆኑ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ ማስረጃ እንደምንመለከተው ተከሣሽ የሰጠውም የእምነት ቃል 3 ጥያቄዎች ለመንግስት ለማቅረብ ነው በሚል መብቱን ጠብቆ የሰጠው ቃል ነው፡፡ በሌላ ማስረጃ ካለተደገፈ በበቂ ሁኔታ የሚያስረዳ አይደለም የቀረቡም በታዛቢው የተግገሩት ሁሉም የቀረቡ አይደለም የቀረቡትም ሰነዶች ቢሆኑም ተከሣሹ የፈፀመውን የወንጀል ድርጊት በበቃ ሁኔታ የሚያረጋግጡ አይደለም ታተመ የተባለውም መጽሃፍ በማስረጃነት አልተቀበለውም፡፡

በመሆኑም ተከሣሽ ከቀረበበት ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት በይነናል፡፡

ፇ

3?3 1060

http://ethcriminalawnetwork.com/

17ኛ ተከሣሽ/ሼ.ህ ሱልጣን ሃጂ አማን/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/ መሠረት የሰጠው ቃል በምሳሌም አመራሮች ላይ ቅሬታ ነበረን ይህንንም በጽዋ እና እውቀት ማህበር ተወያይተናል ይህንንም የተወያየነው ለአበይ ስብሃት ነው ጥያቄው የተለመደ መጅሊስ ይመርጥ የሃበሻ አስተምሮት አይምጣብን አወሊያ በገለልተኛ በቦርድ ይታደደር የሚሉ ናቸው ሐምሌ 8/2004 ዓ.ም. ሰደቃ ኘሮግራም ነበር ከዚያም በ6/11/2004 ዓ.ም. የተደበደቡ ሰዎች አሉ እየተባለ ይቀሰቀስ ነበር እኔ አላውቅም የኮሚቴውን ድብቅ ሴራ አላውቅም ሕጋዊ መስሎኝ ብር 200 ሺ.ህ ብር ሰጥቻለሁ በማለት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ከዚ.ህ በመቀጠል 5 ምስክሮች ቀርበው የመጀመሪያው ተከሣሽ በአንድ መስጊድ ውስጥ በ2003 ዓ.ም. በክርስቲያን አገር መኖር አይገባም ሴቶች ገልጠው መሄድ በሚፈቅድ ሕገ መንግት ከኃይማኖት ውጭ ነው በይል ነበር ሌላው ምስክር ተከሣሽ ከሳውዲ አረቢያ እታች ቢሮ ደሞዝ ለመቀበል ይመጣ ነበር አስተማሪ ይመስለኛል በማለት ያስረዳል ሌሎች 3 ምስክሮች ከተከሣሽ የተያዙ የሰነድ ማስረጃዎችን አይተናል በማለት ድምፃችን ይሰማ የሚሉ በራሪ ወረቀቶች ቶሽባ ላኘቶፕ አንድ ሲ.ዲ ካሴት ሞባይል ቀፎዎች ወደ 25 ገጽ የሚሆኑ እትም ቡረሽሮች የሚባለውን ጥያቄ መልዕክተ ለመንግስት የጠየቁበት ደብዳቤ ወደ 12 ገጽ ወለቂጤ ከተማ ላይ የሚል ስም ዝርዝር የያዘ ወረቀት ሁለት ክብ ማህተም አንድ ፎቶ ካሜራ 2 ፍላሾች እና ወደ 63 ሲ.ዲ.ዎች የተያዙ መሆኑን ታዝበናል ብለዋል፡፡ ሌላው በብርበራ ተይዘው የቀረበው 3 እትም ሰነዶች ተመልክተነዋል የተያዘው ሲ.ዲም ምን እነደሆነ አይገልፁም ሌሎች በማስረጃነት አልቀረቡም በአጠቃላይ እነዚ.ህን ማስረጃዎች ስንመለከተው ተከሣሽ ገንዘቡንም ሲሰጥ ኮሚቴው ጥያቂ ለመንግስት እንደሚያቀርብ በማማን እንጂ እኔ የኮሚቴውን ድብቅ ሴራ አላውቀም የሚል መብቱን ጠብቆ የሰጠው ቃል ከመሆኑም በላይ ቀደም ብሎ ሴቶች ገልጠው መሄድ አይገባም የሚለውም ከእምነት ጋር ተያይዞ የመጣ ከመሆኑ ይህ ቅስቀሳም ኮሜቴ ከመሆኑ በፊት መሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችም በሌላ ሰው የተዘጋጁ መሆኑን የሚያስረዳ በመሆናቸው እነዚ.ህ ማስረጃዎች ጠቅለል ብለው ሲታዩ ተከሣሽ የቀረበበትን ክስ በበቂ ሁኔታ የሚያረጋግጡ አይደለም በመሆኑም ተከሣሽ ከቀረበበት ክስ መከላከል ሣያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበት በማለት ፍ/ቤቱ ስምምነት ወስዷል፡፡

19ኛ ተከሣሽ /ሼ.ህ ጀማል ያሲን/ ለፖሊስ በሰጠው ቃል ላይ ከ17 ኮሜቴዎች ላይ ተገኙቹ 3 ጥያቄዎችን ለመንግስት ለመቅረብ ተንቀሳቅሻለሁ ጥያቄዎችንም ለዶ/ር ሽፈራው አቅርበናል ከዚ.ህ ወጭ እንቅስቃሴውን ሲቁሙ ሲባል አለማቆሜ ጥፋት ነው

ኘ

3236 1081

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚል ነው ሌላ በተከሣሽ ላይ 3 ምስክሮች ቀርበው በአወሊያ ተማሪዎች ወደ ውጭ እንዳይወጡ ይከላከል ነበር በማለት አንዱ ምስክር ሲያስረዳ ሌላኛው ምስክር ደግሞ አንተ የድርጅቱ ሰራተኛ ነህ ለምን አትተውም ሌላው አልተውም አለኝ ይህንንም እስከ ግንቦት ድረስ የቀጠለ ይመስለኛል ያለ ሲሆን ሌላኛው ምስክር ደግሞ ከተከሣሽ ቤት ሲፈተሽ አንድ ላፕቶፕ፣ አንድ ፈቃድ ያለው ሽጉጥ እና ጥይት ቪዲዩ ካሴት አጀንዳዎች መጽሃፎች ክርስትና እና እስልምና በኢትዮጵያ የሚል ድምጾችን ይሰማ የሚል አንድ ወረቀት የተገኘበት መሆኑን በታዛቢነት ተመልክቷል ይህ መሠረት ተደርጐ የእጅ ጽሁፍ ሲሆን ሃበሻን ለማስለጠን ዝግጅት ተደርጐል ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶች መስጠት አለበት እና ስሜታዊ መሆን ያለብን ስርዓት ይዘን መሄድ አለብን የሚሉ እና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው ቀርበው የታዩትም ጋዜጦች በእሱ ይገኝ እንጂ ያዘጋጃቸው ሌላ ሰው ነው ሌሎች ቀርበው አልተያያዙም ካሴቱም ቀርቦ ከተየው ውስጥ አልተገኘም ስለዚህ ከላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች ስንመለከት ተከሣሽም የሰጠው የእምነት ቃል መብቱና ጠብቆ የሰጠው በመሆኑ ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችም የጠቀሰበትን ክስ በበቂ ሁኔታ የሚያስረዱ አይደለም በመሆኑም ተከሣሽ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 241 መሠረት በነፃ መሰናበት እንዳለት ታምኖበታል፡፡

21ኛ ተከሣሽ ሼህ ጣሂር አብዱልቃድር በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 27/2/ መሠረት የሰጡት ቃል እኔ መንግስትን ለመጣል አልተንቀሳቀስኩም እኔ በኮሚቴው ውስጥ የተንቀሳቀስኩት መጂሊሱን በመቃወም ጥያቄዎችን በመንግስት ለማቅረብ ነው ይህን በተመለከተም ከኮሚቴዎች ጋር እኔ በምመራው ድርጅት ተሰብስበን የአፍሪካ ሕብረት ጊዜም ተው ሲባል እንዲህ አይነት እንቅስቃሴ ጊዜም ጥያቄአችን ተሰሚነት እንዲያገኝ እንጂ በመንግስት ላይ ተቃውሞ የለኝም የሚል ነው ሌላው ተከሣሹን ላይ የቀረቡ ሁለት ምስክሮች 1ኛው ሲያስረዳ ተከሣሽ በሚመሩት የሠላም እና እውቀት ማህበር ላይ ነው ብሎ በዚህ ድርጅት ውስጥ ሰብሰባ የተካሄደ መሆኑን በዚህ ቦታ ካሚል ሽምሲ እና ሌሎች ስማቸውን የማላውቃቸው ብሎ 4ኛ፣ 17ኛ እና 25ኛ ተከሣሽ ጠቁም በማሳየት እነዚህ በተደጋጋሚ ይመጡ ነበር ሲሰበሰቡ ግን አላየሁም ሜዳው ልይም ቁመው ጥያቄአችን ለመንግስት እናቅርብ ሲሉ ሰምቻለሁ እንጂ መደበኛ ስብሰባ አይቼም አላውቅም እኔም የድርጅቱ ሂሳብ ሹም ነኝ ድርጅትም ገንዘብ ምንም ከውጭ እና ከግለሰቦች እንዲሁም ከአገር ውስጥ ድርጅቶች ያገኛል በቁራን እና ለፈጠራ ስራዎች ይውላል ከሃጂ ኢብራሂም ብር 500 ሺህ ብር ተቀብለናል ከየት እንዳመጡት አላውቅም የተቀበልኩት እኔም ለማፍጠሪያ ስጥ ተብዬ

1082

ለማፍጠሪያ ልኬቀስሁ መቼም ለሌላ ሲውል አይችልም ሌላ ተደርጎው መሣመድ ሁሌንም 292 ሺ.ህ ብር ሰጥቸው ሲባል ሰምቻልሁ አንድ ስሙን የማላውቀው ሰው 242 ሺ.ህ ብር ሰጥቶል የድርጅቱ አለማም ኃይማኖታዊ ስራዎችን ነው የምሰራው በማለት ያስረዳ ሲሆን አንድ ምስክር ቤታቸው ሲፈተሽ ቤታቸው ውስጥ 1. አንድ ሽጉጥ ከነጥይቱ 2. በአረበኛ የተፃፈ መጽሃፍ 3. ሁለት ላፕቶፕ 4. አንድ በአማርኛ የተፃፈ መጽሃፍ ወደ 60 የሚሆኑ ሲዲዎች ተገኝተዋል የሚል ሲሆን እነዚህም ማስረጃዎች አልቀረቡም ዐ/ሕግም በማስረጃ ዝርዝርም በሰነድነት አልጠቀሳቸውም ሌላ ማስረጃ አልቀረበም በተከሣሹ ላይ የቀረበው ማስረጃ ተከሣሽ በድርጅታቸው ስም ገንዘብ የሰበሰቡ ነበር የተሰበሰበውም ገንዘብ ለማፈጠሪያ እና ለኃይማኖታዊ ሥራ የሚሰራ ነው እኔም ገንዘብ ተቀብዩ ለማፍጠሪያ የከፈልኩ መሆኑን የድርጅቱም ሂሣብ ሹሙ መሆኑ ሲታይ ስብሰባውንም ሁል ጊዜ እንዳሌለ አንድ ቀንም ሜዳ ላይ ተሰብስበው ጥያቄአችን ለመንግስት እናቅርብ ሲሉ ሰማው እንጂ ሌላ የሚያቀው ነገር የለም የሚለው ሲታይ በዚያ ቦታ ላይ በእርግጠኝነት የወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል ወይ የሚለው አጠራጣሪ ነው ገንዘብም ድርጅት ስለሆነ ገንዘብ ሊሰበሰብ ይችላል ይህ ከሆነ ደግሞ ለሽብር ተግባር ውሏል ለማለት የሚያስረዳው አይደለም ይህን ከአለን ብቸኛ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርበው የተከሣሽ በፖሊስ የሰጡት ቃል ነው ይህም ቃል ተከሣሽ መብታቸውን ጠብቀው እኔ መንግስትን ለመጣል ሽብር ለመፍጠር አልተንቀሳቀስኩም መጅልሱን በመቃወም ጥያቄዎችን ለመንግስት ለማቅረብ ነው ከኮሚቴው ጋር የተንቀሳቀስኩት በሚል ነው ይህ ደግሞ የእምነት ቃል ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም እንዲህ ባየን ጊዜም በሌላ ማስረጃ እስከአልተረጋገጠ ድረስ ተከሣሽ መብቱን ጠብቆ የሽብር አላማ የለኝም ያለውን ሃሣብ እንዳለ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ በቀረበው ትንታኔ መሠረት ተከሣሽ ላይ የቀረበውን ክስ በበቂ ሁኔታ ሊያስረዳ የሚችል ማስረጃ ቀርቧል የሚያስብል ባለመሆኑ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ መሰናበት እንደሚገባው ፍ/ቤቱ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

24ኛ ተከሣሽ /ሣሰን አሊ / የሰጠው ቃል የተሰናበቱ የአወሊያ አስጋጆች ይመለሱ ተብሎ መመለሳቸውን አውቃለሁ በመቀጠልም 3ኛ ጥያቄዎች ለመንግስት እናቅርብ ተብሎ ድጋፍ መስጫ ላይ ፈርሜአለሁ አንድ አንድ ነገሮችን ከሕዝብ ወደ ኮሚቴው አስተላልፎ ነበር በአወሊያ የተሰበሰበውን የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም አውቅም ከላይ በቀረበው መንገድ ኮሚቴውን መተባበሬ ጥፋተኛ ነኝ የሚል ነው፡፡ ሌላው የቀረበው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አንድ ምስክር ተከሣሽ ቤቱ ሲፈተሽ ቁጥሩን የማላውቀው ካሴት 2 ሞባይል የተለያዩ በአማራኛ እና በአረበኛ የተፃፉ አጀንዳዎች እና መጽሃፎች የተለያዩ መጽሄቶች እና ፔሮል ያገኘ መሆኑን ታዝበናል በማለት አስረድቷል። ሌላው በዐ/ሕግ ክስ የማስረጃ ዝርዝር አንድ ሲ.ዲ. አለ ቢባልም ፍ/ቤት ቀርበው ከታዩት ሲ.ዲ.ዎች አልተገኘም ሌሎችም በዝርዝርም ተያይዘው አልቀረቡም ይህ ማስረጃ ሲመዘን ተከሣሽ የእምነት ቃልህም ሲሰጥ መብቱን ጠብቆ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ በቂ ነው የሚባል አይደለም የሰደቃ እና አንድነትም አላውቅም የሚል ነው። ሌላ ማስረጃም ታዛቢ ምስክር ካልሆነ በስተቀር ሌላ ማስረጃ አልቀረበም ይህንን አጠቃለን ስንመለከተው ተከሣሽ ተጠቅሶ የቀረበበትን ክስ በበቂ ሁኔታ ሊያስረዳ የሚችል ባለመሆኑ ተከሣሽ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበት በማለት ፍ/ቤቱ ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

25ኛ ተከሣሽ /አሰ. መኪ/ ለፖሊስ የሰጠው ቃል በተወካይ ኮሚቴዎች ስም ዝርዝር ላይ አስፈርሜአለሁ ኮሚቴው መመረጡን ያወቅኩት እስር ቤት ሆኘ ነው በአንዋር መስጊድ በራሪ ወረቀቶችን ለጥሪ በትኛለሁ ከሰደቃው ፕሮግራም ላይም የተገኘሁት መጅልስ በመቃወም ነው በማለት ቃሉን ሰጥቷል ከዚህ በመቀጠል አንድ ምስክር ቀርቦ ከተከሣሽ ቤት የተገኘው 6 መጽሃፍ ከማስታውሰውም ምርጥ የእስልምና ታሪክ የአበሻ እና የአላህ ባሕሪያት የኢትዮጵያ ሙስሊም የት ነው ድምፃችን ይሰማ የሚል በራሪ ወረቀቶች ንቁ አላህ ከእኛ ጋር ነው የሚል እና ወደ 18 ጋዜጦች ማግኘታቸውን ታዛቢ ሆኖ ተመልክቷል ሌላው ድምፃችን ይሰማ መጅልስ ሊሰጠን ተነስቷል የሚል በኮምፒተር የተዘጋጀ የተገኘ ስለመጂልስ እና ስለሃበሻ የሚያወራ ጽሑፍ ሲሆን በሌላ ሰው የድምፃችን ይሰማ የሚል ነው በአጠቃላይ ስንመለከተው ተከሣሽ የሰጠው ቃልም መብቱን ጠብቆ የሰጠው ነው ለዚህም የሚያሳየው ኮሚቴው የተመረጠው ከእስር ቤት ከገባሁ በኋላ ነው የሚል ሲሆን ሌሎች ማስረጃዎችም በበቂ ሁኔታ የቀረበበትን ክስ የሚያረጋግጡ አይደሉም። ስለዚህ ተከሣሽ ከቀረበበት ክስ መከላከል ላይ ሰያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበት በማለት ፍ/ቤቱ አምኖበታል።

26ኛ ተከሣሽ /ሃጂ አብራሂም ቱሂፋ/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/ መሠረት ለፖሊስ የሰጡት ቃል መጂሊስ አበሻን አያምጣብን ብየአለሁ ለታሰሩ ሰዎች 88ሺ.ህ ብር ለ22 ቤተሰብ እያንዳንዱ ብር 4000 ሰጥቻለሁ በድርጅቱ የሚሰራው መስጊድ እና ት/ቤት ነው የአወሊያን ችግር ለመፍታትም በሽምግልና ተወያይተን ነበር ብር 5000,000 /አምስት ሚሊዮን ብር/ ተልኮልኝ ለሺ.ህ ጣሂር ሰጥቻለሁ ቢላል የወንጀል ድርጊት ያልሰሩ

ጉ

http://ethcriminalawnetwork.com/

መሆኑን አመልክተው እኔ ለታሰሩ ሰዎች ብር መስጠቱ ጥፋት ነው የሚል ቃል ሰጥተዋል።

ከዚህ ጋር ቀጥሎ የቀረቡት ሁለት ምስክሮች ሲሆኑ 53ኛ ምስክር በሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም. ረመዳን ቀኑን አላስታውሰውም አንዱ ምስክር ብር 2292 ብር ከተከሣሽ ተቀብዩ ለፋይናንስ እና አስተዳደር ገቢ አድርጌአለሁ የት እንደመጣ አላውቅም ሳውዲ አረቢያ መጣ ሲባል ሰምቻለሁ እኔ የድርጅቱ ሰራተኛ ነኝ የሚለውም ለማፍጠሪያ ለመስጊድ የሚሰጥ እና ለድሃ ቤተሰብ ይሰጣል የተከሣሽ ድርጅትም በእምነት ዙሪያ የሚሰራ ነው ያለ ሲሆን ሌላኛው /54ኛ ምስክር ተከሣሽ ለ31ኛ ተከሣሽ ድርጅት ብር 500.000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ ለፆም መፍቻ የሚከፋፈል ብለው ለማፍጠሪያ እና ቁራን ለሚቀሩ ሰዎች ይከፈል ብለው መስጠታቸውን አውቃሁ ብሩ የት እንደመጣ አላውቅም በማለት አስረድቷል።

ሌላው የዐ/ሕግ ምስክር ባለመገኘቱ በፖሊስ የሰጠው ቃል ቀርቦ ፍ/ቤቱ ተመልክቶታል ይዞታው ምስክሩ ተከሣሽን እንደሚያውቋቸው ገልፆ 31ኛ ተከሣሽን ድርጅቶችን ጨምሮ 5 ድርጅቶች /ኃይማኖታዊ ድርጅቶች እንደሆኑ ጠቅሶ የሚከፋፈል የሚል እንዲሁም ለታሰሩ ቤተሰቦችም የሚሰጥ ከመሃመድ ሁሴን የተላከ የሚል ብር 2 ሚሊዮን ብር በላይ ተልኮለታል የሚል የኢሜል መልዕክት ከኢሜሉ ፕሪንት አድርጌ ሰጥሃለው በማግስቱ ታርጋዋን የማላውቃት መኪና ብሩ መጥቶ ወደ ቢሮ ገብቶ ከዚያ በኋላ የብር መጠን አላውቀውም መሐመድ ሁሴን እና በፔስታል አድርስ አብዱርቃድ ለተባለ ሰው ሰጡት እኔም የሳቸው ሹፌር ስራ ስለለቀቁ በመኪና አድርሼ ተመለስኩ የተሰጠው የዳዋ እና እውቀት ማህበር ነው አሁንም በሐምሌ ወር 2004 ቀኑን አላስታውሰውም በኤሜል ተልኮልኛል ብለው ብር መጥቶልኛል ብለውኛል ከዚያም ለአልብረ በተሰኘው እስላማዊ ድርጅት መሃመድ እንድሪስ ለተባለው ሰው ብር 50 ሺ ለባሕርዳር ምስሊሞችም 100 ሺህ ብር ይሰጣቸው ብለው ነበር መጨረሻ ላይ ባሕርዳር የአሉ ሰዎች ስንጠይቅ 15,000 ብር ተሰጥቶናል ብለው ነገሩን በሌላ ጊዜ የተላከ ብር 500,000 ቀርቷል እና ደህንነት ያውቅብናል ብለው ብሩ በሌላ ሰው አማካኝነት ወደ ባንክ እንደገባ ይገልፃል ከዚህ ውጭ ሌላ ማስረጃ አልቀረበም።

ይህ ማስረጃ ሲመዘንም ብሩ የመጣበት ምንጭ አይታወቅም ከመጣ በኋላም የሚከፋፈለው ለማፍጠሪያ እና ለታሰሩ ቤተሰቦች በቀጥታ የሚሰጥ መሆኑን በተለይ የመጀመሪያው ቀርቦ የመሰከረው ብሩን ለሚፍጠሪያ የሚሆን ነው ብሎ ያከፋፈለ መሆኑን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚያስገነዝብ ሲሆን ምስክሩም ባለመቅረቡ የሰጠው ቃልም ቀርቦ ሲታይ ለተበዳይ የኃይማኖት ድርጅቶች እና ለእስረኞች የሚሰጥ ነው ከሚል በስተቀር ለሌላ የወንጀል ድርጊት የዋለ ነው አይልም ሳውዲ አለ የተባለውም ሰው በዚህ መዝገብ ተከሣሽ የሽብር ወንጀል ለመፈፀሙ አልተረጋገጠም በኃይማኖት ድርጅት እና ለእስረኛ ድርጅት ገንዘብ መስጠት ወንጀል አይሆንም ተከሣሽም ቢሆን ለእስረኞች ብር መስጠቴ ነው እንጂ ሌላ ጥፋት የለብኝም የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ነው በመሆኑም የእምነት ቃሉም በተሟላ ሁኔታ የታመነ አይደለም በሌሎች ማስረጃዎችውም ተከሣሽ በሽብር ተግባር የረዱ እና ገንዘብ የሰጡ መሆኑን የሚያጠራጥር እና የሚያረጋግጥ ስለሆነ ተከሣሽ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት በነፃ መሰናበት ይገባዋል በሚል ፍ/ቤቱ አምኖበታል፡፡

27ኛ ተከሣሽ /ሼህ አብዱርአማን ኡስማን/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27 መሠረት በፖሊስ የሰጡት መልስ ሃበሻ የሺህ አብዲል ሃገሬ ነው እንጂ እኔ አልቀበለውም ብየአለሁ ከሙስሊም አመጽ ላይ ተገኝቼም አላውቅም አብዲልቃድር ቀሪውን ስለሚያከፋፍል ስጠኝ ብቻ ጠይቆኝ ሰጥቻዋለሁ የአቶ ጂነዲሳዶ መስጊድ እንደሰራ ከሳውዲ አረቢያ አስፈቅጂ በስሜ ከሆነው ድርጅት ለ28 ተከሣሽ 1.5 ሚሊዮን አውጥቼ ሰጥቻለሁ ለማፍጠሪያ የሚሆን ቴምር እና ብር 50 ሺህ ብር እና 500 ቀሪውን ይህንንም ለ28 ተከሣሽ ሰጥቻለሁ መስጊድም ወደ 170 ማስጊዶች አሰርቻለሁ በማለት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 7 ምስክሮች ቀርበው እንደኛው በኦሮሚያ ውስጥ ምን ያክል እንደሆነ አላውቅም መስጊድ አሰርተዋል ከ28 ተከሣሽ ባለቤት ቦታም ላይ አሰርተዋል፡፡ ሌላኛው ምስክር በሳዲ አረቢያ ኢምባሲ ማለቶ የተባለ የኃይማኖት ማስፋፊያ ድርጅት 27 እና 29ኛ ተከሣሾች ደሞዝ ይወስዳሉ ይቀጣሩ አይቀጠሩ አላውቅም ሲል ሌላኛው ወይም 3ኛ ምስክርም ደሞዘ የሚከፈላቸው የኃይማኖት አስተማሪ ስለሆኑ ይመስለኛል ያሉ ሲሆን በመጨረሻም ሌላኛው ምስክር ደግሞ ከተከሣሽ ቤት 1. ሁለት ላፕቶፕ 2. ያልመርጥናቸው መጅሊስ አይመራንም የሚል ቲሸርት 3. የቪዲዮ ካሜራ 4. የቴፕ ካሴት 5. የሙስሊም ተማሪዎች ሚና የሚል ትንሽ መጽሃፍ መገኘታቸውን አውቃለሁ ብሎ ሌሎች 3 ምስክሮች የሚቀጥረው ወሃብያ ነው አጭር ልብስ የለበሰ አትቅጠሩ አንድ ሰው የእስልምና መንግስት ቢመጣ ብሎ ዱዓም ሲያደርግ ነበር በማለት መስክረዋል ፡፡

የቀረበው ማስረጃ ይኸው ሲሆን የቀረበው ማስረጃ መስጊድ አሰሩ ከሚባል በስተቀር ተከሣሽ መስጊድ ሽብር ድረጊት አስፋፍቷል የሚል አይደለም፡፡ መስጊድ ያለመጅልስ

3341 7086

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አውቅና ተሰርቷል ቢባልም እንኳን በዚያው በውስጥ አስተዳደር የሚወሰዱት እርምጃ ካልሆነ በስተቀር የሽብር የወንጀል ድርጊት ተሰርቷል የሚያሰኝ አይደለም ደሞዝ መከፈሉም ከወንጀል ምንጭ ካልመጣ በስተቀር መቀጠር አለመቀጠራቸው የሚያመጣው ለውጥ አያመጣም ተከሣሹም ቢሆን የሰጠው ቃል በኮሚቴው እና በሙስሊም አመጽ ተገኝቼ አላውቅም በማለት ክዷል በታዛቢ ምስክሩ ከተከሣሽ ቤት ተገኘ የተባሉ መጽሃፎች እና እቃዎች ዐ/ሕግ በማስረጃ ዝርዝር ላይ ጠቅሶ አላቀረበም በሌ መንገድም ቀርበው ይዘታቸው አልታየም በመሆኑም ተከሣሽ የሠራ የሚባለው የሽብር ድርጅት ተብሎም ባለመፈረጁ ይህን መረዳት ወንጀል የሚያደርገው አይደለም ምንአልባትም አንድ ሰው አክራሪነት ቅስቀሣ አካሄዶበታል ቢባልም እንኳን ተከሣሽ ሰርቷል የሚያሰኘው አይደለም በመሆኑም ተከሣሽ በቀረበበት ክስ መሠረት በበቂ ሁኔታ ማስረጃ ቀርቦበታል የሚያሰኘው ማለት አይቻልም ስለሆነም ተከሣሽ ከቀረበበት ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት በነፃ መሰናበት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

28ኛ ተከሣሽ /ሃቢባ መሃመድ/ ላይ የቀረበው ማስረጃ 2 የሰው ምስክሮች እና የኢግዚቢት ማስረጃ ሲሆን የቀረቡት ምስክሮች ከሣውዲ አረቢያ ተፈቅዶ ይመስለናል በኦሮምያ ውስጥ በሚሰራው መስጊድ ማቴሪያል አደርስ ነበር መስጊድም አለቀ ሐምሌ 9 ቀን 2004 ዓ.ም. የመስጊድ ምረቃን ነበር እሱን አስመርቀን ቀደም ተብሎ ቃል የተገባ ገንዘብ ነበር ከዚያው 5000 ቀሪን እና ብር 50 ሺህ ብር ተሰጠና ለምረቃው ከአዲስ አበባ የአመጣነው እቃ ነበር ይህ እቃም ጭልፋ ብረትድስት እና የምግብ ሳህኖች ለመመለስ ስንመጣ ተያዝን በማለት አንድ ምስክር ያስረዳ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በክስ በተጠቀሰው ቀን ላንድ ክሮዘር መኪና ውስጥ ሲፈተሽ ብረድስት፣ ጎድጓዳ ሳህን፣ ጭልፋ ድጅታል ካሜራና 25000 ብር ከሳውዲአረብያ ኢምባሲ ሲወጣ የተያዘ መሆኑን አውቃለሁ የሚል ሲሆን ሌላው የተያዙት ጭልፋ ብረትድስት እና የምግብ ሳህኖች በፖሊስ የተያዘ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የቀረበው ማስረጃ ይኸው ሲሆን ይህ ማስረጃ ሲመዘን ተከሣሽ ከ27ኛ ተከሣሽ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ አክራሪነትን የሚያስፋፋ መስጊድ አሰራች የሚል እና የሰደቃ እና የአንድነት ፕሮግራም በመደገፍ ተንቀሳቀሳለች ቢሆንም የተሰራው መስጊድ በአክራሪነት የአሸባሪ ቡድን ውስጥ ካልተፈረጀ በስተቀር ይህን መስራት ወንጀል ነው ተብሎ ሊወሰድ የማይችል ከመሆኑም በላይ የሰደቃ እና አንድነት ፕሮግራም ለመረዳት ቀርቦ የተላው ማቴሪያል መስጊድ ሲመረቅ ከከተማ ወሰድነው ለመመለስ ስንመጣ ተያዝን አለ እንጂ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለሰደቃ እና አንድነት ፕሮግራም ለሚወሰድ እንዳልሆነ ምስክሩ አረጋግጧል በመኪናው ውስጥም እቃዎቹ ሲያዙ ነበርኩ ያለውም ምስክር እቃው ከሳውዲ አረቢያ ኢምባሲ ሲወጣ ተያዘ ያለው በትክክል የት እንዳመጣ የማያውቅ አይሆንም ምክንያቱም ምስክሩ ታዛቢ ምስክር ከግምት የዘለለ ሲሆን አይችልም ከዚያው ቢጠጣም እንኳን የሽብር ድርጊቱን ለመስራት ነው ተብሎ ካልተረጋገጠ በራሴ ወንጀል ሲሆን አይችልም የተቀበለችውም ብር ለተመረቀው መስጊዱ ቀሪ ሥራዎች ማስፈፀሚያ እንደሆነ የተሰጠችውም ከመስጊድ ምርቃን ቀን መሆኑን ምስክሩ መረጋገጡ መስጊድንም የመንግስት አመራሮች በእለት መመረቁን አረጋግጧል በመሆኑም ተከሣሽ ተጠቅሶ የቀረበበትን ክስ ሊያስረዳ የሚችል በቂ ማስረጃ ባለመኖሩ ተከሣሽ መከላከል ሳያስፈልጋት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ መሰናበት እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

29ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ከማል ሃጅ ገለቱ ላይ የቀረበው ማስረጃ አንድ ታዛቢ ማስረጃ ከተከሣሽ መኖሪያ ቤት የቴፕ ካሴቶች እና ሲዲዎች ኮሚፒተር 2 ሲም ካርድ እና አንድ ባነር በአረበኛ የተፃፈ የተገኘ መሆኑን አስረድታለች ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበው ማስረጃ አንድ ከአህአዴግ እና የአበሻ ሴራ የሚል ሲዲ ቀርቦ ታይቷል የሐሰት ፕሮፖጋንዲ የእምነት ጥያቄን ሕገ ወጥ አያደርገውም የሚል ነው ከዚህ ውጪ ሌላ ማስረጃ አልቀረበም ይህን ስንመለከተው ሲዲው ከቤት መገኘቱ ብቻ መሆኑ ይህ ሲዲም ከውጭ አገር የተዘጋጀ መሆኑ እንዲህ አይነት ሲዲም ለማየት ሲባል ተይዞ በአጋጣሚ የሚያዝ መሆኑ ተከሣሽም በዚህ ሲዲ ሌላ ቅስቀሳ ለማካሄድ በሌላ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችም ተከሣሽን የቀረበበትን ክስ በበቂ ሁኔታ የሚያስረዳ አይደለም በአጠቃላይ ሲታይ ተከሣሽ የቀረበበትን ክስ በበቂ ሁኔታ የማያስረዳ በመሆኑ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ መሰናበት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

30ኛ ተከሣሽ ድርጅትን /አልቢር ዲቨሎኘመንት እና አፍሬሽን አሶሴሽን/ በተመለከተ በ17ኛ ተከሣሽ የሚመራ ሲሆን ይህ ተከሣሹም ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ተከሣሽ በቀረበበት ክስ መሠረት በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ በነፃ እንዲሰናበት የተባለ በመሆኑ የድርጅቱ የማስረጃ መሠረትም ከዚሁ ሰው ጋር ተያይዞ የቀረበ በመሆኑ ከዚህ የተለየ የቀረበውም ድርጅቱ ሕጋዊ ፈቃድ ያለው የሚል እና ስራውም አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን መገንባት የሚል የሰነድ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ይህም ቢሆን ተከሣሽ ድርጅት በወንጀል ድርጊቱ ተሳታፊ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ አይደለም ከዚህ ላይ ልናነሳ የምንችለው ነገር ቢኖር የድርጅቱ መኪና የተገኘው በ10ኛ

ፒ

3413 1088

http://ethcriminalawnetwork.com/

ተከሣሽ የሸኘት የቅስቀሳ ወረቀቶችን ለመበተን ሲባል በ10ኛ ተከሣሽ አመካኝነት መያዙን የማስረጃ የቀረበ ነው ይህ ማለት ግን መኪናው ከድርጅቱ ውጭ የወንጀል ድርጊት ተፈፀመበት ከሚባል በስተቀር ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል የሚያሰኘው አይሆንም በመሆኑም መኪናው 10ኛ ተከሣሽ ለፈፀመው ድርጊት እንደ ኤግዚቢት ማስረጃ የሚወሰድ ይሆናል ማለት ነው በመሆኑም ይኸው ተከሣሽ ድርጅት መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ መሰናበት እንደሚገባው ታምኖበታል።

31ኛ ተከሣሽ ድርጅት /ነመአ የበጐ አድራጐት ማህበር ይህም ተከሣሽ ይህን ድርጅት የሚመራው 21ኛ ተከሣሽ ሲሆን ካለው ለመጥቀስ እንደተሞረው ይኸው 21ኛ ተከሣሽ በቀረበበት ማስረጃ በበቂ ሁኔታ የሚያረጋግጥ በመሆኑ በነፃ ተሰናብተል በዚህ ድርጅት ላይም በተከሣሽ አማካኝነት ሆኖ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የቀረበ ማስረጃ ነው ይህ ማስረጃም ተከሣሽ ድርጅቱን በተለየ መንገድ የወንጀል ተካፋይ መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም ከዚህም ሌላ በድርጅቱ ላይ የቀረበው ማስረጃ ሕጋዊ ሰውነት ያለው እና መተዳደሪያ ደምብ ነው ይህም ድርጅቱ የወንጀል ድርጊት የፈፀመ መሆኑን አያረጋግጥም በመሆኑም ተከሣሽ ድርጅት ከቀረበበት ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት በነፃ መሰናበት እንዳለበት ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል።

ሲጠቃለልም 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ፣ 9ኛ፣ 11ኛ፣ 15ኛ፣ 16ኛ፣ 20 እና 22ኛ ተከሣሾች በቀረበባቸው የማስረጃ መጠን እና የወንጀል ድርጊት መሠረት በማድረግ ሁሉም በወ/ሕ/ቁ 32/1/ሀ/ንና በፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 ሥር እንዲከላከሉ በማለት ብይን የሰጠን ሲሆን

10ኛ፣ 12ኛ፣ 13ኛ፣ እና 18ኛ ተከሣሾች ደግሞ በወንጀል ተሳትፏቸው እና በተመሰከረባቸው መጠን እያንዳንዳቸው ፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7/1/ መሠረት እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥተናል።

በመጨረሻም 14ኛ፣ 17ኛ፣ 19ኛ፣ 21ኛ፣ 24ኛ፣ 25ኛ፣ 26ኛ፣ 27ኛ፣ 28ኛ፣ 29ኛ፣ 30ኛ እና 31ኛ ተከሣሾች በቀረበባቸው ክስ በበቂ ማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ እያንዳንዳቸው መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ ስንል በሙሉ ድምጽ ብይን ሰጥተናል።
ገ

http://ethcriminalawnetwork.com/

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

- ተከላከሉ የተባሉ ተከሣሾች የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር ሲያቀርቡ መጥሪያ ይፃፍላቸው
- በነፃ የተሰናበቱ ተከሣሾች መፈቻ ይፃፍ፡፡
- እንዲከላከሉ በተባሉት ተከሣሾች ላይ የመ/ማስረጃ በመስማት ቀጠሮ ለጥር 22-27 ቀን 2006 ዓ.ም. ተቀጠረ፡፡

ተጨማሪ ትዕዛዝ

- የተከሣሽ ጠበቆች ችሎት ክፍት ይሁንልን ብለው አመልክተዋል ቀደም ሲል ችሎቱ ዝግ የሆነው ለምስክሮች ደህንነት ስለሆነ አሁን የዐ/ሕግም ምስክሮች ስለሚሰማ በፊት ያለው ይህንኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ችሎቱ በክፍት እንዲሆን ብለናል፡፡

የዳኞች ፊርማ፡- ብሥራት ተኸልቁ

ባሕሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

አ/ገ ፯

5/04/2006 ዓ.ም.

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር ....
Re.NO
ቀን ....
Date

ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

ልደታ ምድብ 4ኛ ወንጀል ችሎት

አዲስ አበባ

ከሣሽ....የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ

ተከሣሾች...እነ አቡበከር አህመድ መካከል ስለለው የሽብር ወንጀል ክስ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ታህሣሥ 3 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/141/ መሰረት በነፃ እንዲሰናበቱ እንዲሁም ክሳቸውን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/113/1/ መሰረት በመለወጥ እንዲከላከሉ በማለት የሰጠውን ብይን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/187/1/ መሰረት ይግባኝ ግልባጭ እንዲሰጠን በትህትና እናመለክታለን።

ብርሃኑ ወ/አገኝ
ፌ/ዐቃቤ ሕግ

ሚ/ደ.

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC
OF ETHIOPIA
FEDERAL HIGH COURT

የመዝ/ቁ፡ 124754

ቀን 14-05-06

ለ [illegible]

አዲስ አበባ

በከሣሽ ዐቃቤ ሕግ እና በተከሣሽ [illegible] መካከል ስላለው ሽብር ወንጀል ክስ ጉዳይ፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የውሣኔ መስጠት ንዑስ የስራ ሂደት ልደታ ምድብ [illegible] ወንጀል ችሎት ቀርቦ ከታየና ከተመረመረ በኋላ ፍ/ቤቱ 3-4 ቀን 06 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተከሣሽ ይግባኝ በጠየቀው መሰረት፣ የውሣኔ ግልባጭ [illegible] ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር እየላክን፣ ለይግባኝ ባይ እንዲደርሰው ሆኖ፣ ይግባኝ ጊዜው ከማለፉ በፊት ቅሬታውን አዘጋጅቶ በማ/ቤቱ በኩል ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ መስጠት ንዑስ የስራ ሂደት እንዲላክ እናሳስባለን፡፡

የፈፃሚ ስም፡- ዓለማየሁ ለገሠ አበበ

ፊርማ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ም/ሬጅስትራር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ስልክ Tel. 0112751911
ፋክስ Fax 0112755399
ፖ.ሣ.ቁ. 3483 P. O. Box

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር 5/ቢን/ፊ/ሰ/ዐ/ዐ7/2418/06
Re.NO
ቀን 13-05-2006
Date

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

አዲስ አበባ

ፌ/ከ/መ/ቀ.124754

የግባኝ ባይ...... የፌደራል ማዕከል ዐቃቤ ህግ

መልስ ሰጪ.....ሀሰን ዓቢ ሰኢድ

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/189/1/ መሰረት የቀረበ የይግባኝ ቅሬታ

ይግባኙ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ታህሣሥ 3 ቀን 2006 ዓ.ም በመ/ቁ/ 124754 በሰጠው ብይን ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የይግባኝ ቅሬታ አቀራረቡ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/187/1/ እና /2/ ስር ያለውን የሕግ ድንጋጌ እና ጊዜ የጠበቀነው፣-

የቅሬታችን ዋና ፍሬ ጉዳይ በአሁን መልስ ሰጪ ላይ እነ አቡበከር መሀመድ 32 ሰዎች በተከሰሱበት የሽብር ወንጀል ክስ ተከሣሽ /መልስ ሰጪ/ 24ኛ ተከሣሽ በመሆን በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ 32/1/ሀ/፣ /ለ/ እና /38/ እንዲሁም በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/1/2/፣ /4/፣ /6/ እና አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ክስ ቀርቦበት በነፃ እንዲሰናበት በሰጠው ብይን ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የይግባኙ ዝርዝር

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመልስ ሰጪ እና በግብረአሮቹ ላይ የመሰረተንው ክስ፣

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ለ/፣ 38/1/ እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/1/፣ /2/፣ /4/፣ /6/ እና አንቀጽ 4 ስር

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia

" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

344 7096

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር...
Re.NO
ቀን...
Date

የተመለከተውን በመተላለፍ ሲሆን ዝርዝሩ፣ ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን እና የወንጀል አድማ ስምምነት በማድረግ፣ በመላ ሀሰባቸውና አድራጎታቸው የወንጀል ድርጊቱን እና ወንጀሉ የሚሰጠውን ውጤት ሙሉ በሙሉ በመቀበል እና የራሣቸው በማድረግ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት ከተረጋገጠው የእምነት ነፃነት በመቃረን ከራሣቸው አክራሪ አስተሳሰብ አስተምህሮት ውጪ መኖር የለበትም በሚል ሃይማኖታዊ ዓላማ እና በሀገሪቱ ሃይማኖታዊ መንግስት ማቋቋም /መመስረት/ የሚል የፖለቲካዊ ግብ በማስቀመጥ ቀኑና ወሩ በውል ተለይቶ ካልታወቀበት ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የሃይማኖት አስተማሪዎች ቡድን በማለት በሕቡዕ ባቋቋሙት ቡድን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጀም ጊዜ እቅድ በማውጣት እና እስትራተጂዎችን በመንደፍ በተለይም የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማቋቋም እና በነዚህ ድርጅቶች አማካኝነት የሽብር ዓላማቸውን ለማስፈፀም አክራሪነትን በማስፋፋት ከፍተኛ መጠን ያለውን ገንዘብ ከተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ምንጮች በማሰባሰብና በማሰራጨት፣ ከመጀሊስ እውቅና ውጪ አክራሪነትን ለማስፋፋት የሚረዱ ተቋማትን በማቋቋም፣ አክራሪነት የሚሰብኩ መገናኛ ብዙሃንን በመመስረትና በመጠቀም በሃይማኖታዊ ፅንፈኝነትና በአክራሪነት ዙሪያ በውጭ ሀገር ስልጠና በመውሰድና የተጻፉ መፅሐፍቶችን ከተለያዩ ሀገራት በማስመጣትና መፅሐፍቶች ላይ ሃይማኖታዊ መንግስት ለመመስረት ስለሚቻልበት ሁኔታ ውይይት በማድረግ፣ የዝግጅት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ፣ ከቆዩ በኋላ በታህሣሥ ወር 2004 ዓ.ም በኮልፌ ቀ/ክ/ከተማ ክልል ውስጥ በሚገኘው አወልያ ኮሌጅ የኮሌጁ ተማሪዎች ካነሱት አስተዳዳራዊ ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተነሳውን አለመግባባት የሽብር ዓላማቸውን ለማስፈፀም እንደመልካም አጋጣሚ በመቁጠር፣ የተማሪዎቹን ጥያቄ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ መፍትሄ የሚያፈላልግ ኮሚቴ በሚል የሽብር ቡድኑን ዓላማ የሚያስፈጽም ኮሚቴ እርስ በራስ በመመራራጥ የሽብር ቡድን አቋቁመው ወደ አወሊያ በመሄድ፣ በሕዝብ የተመረጡ ለማስመሰል አስቀደመው ባቀዱት መሰረት የተማሪውን ጥያቄ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር..
Re.NO
ቀን..
Date

ሃይማኖታዊ አስተማሪዎችን ሊመሩት ይገባል በማለትመድረኩን በመቆጣጠር በካሄዱት ምርጫ የመስሊሙ ሕብረተሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ በማለት ሰይመው፣ በሕዝቡ የተወከሉ ለማስመሰልና ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ፊርማ በማሰባሰብ፣ የተማሪዎቹን ጥያቄ ለሽብር ዓላማቸው በሚመች መንገድ በመቀልበስ ሂደቱን በመቆጣጠርና በመምራት፣ የሽብር ዓላማቸውን ለማስፈፀም ከጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በየሣምንቱ አርብ ለፀሎት በአወሊያ መስጊድ ለሚሰባሰበው ሕዝብ የሽብር ዓላማቸውን ለማራማድ በአዲስ አበባና በክልሎች ባዘጋጁት የሰደቃ እና የአንድነት ዝግጅቶች በማለት ለሚጠሩት ሕዝብ፣ በማህበራዊ ድህረገፆች፣ ለዚህ ተግባር በተቋቋሙት የተለያዩ ሃይማኖታዊ መገናኛ ብዙሃኖች በመጽሐፍት በራሪ ጹሁፎችና ዘጋቢ ፊልሞች አማካይነት የሙስሊሙ ማህበረሰብ የእምነት ነፃነቱ ያልተከበረ ሃይማኖታዊ ነፃነቱን የተነፈገ እንደሆነ፤ መንግስት እንደቀድሞ ሥርዓቶች እስልምናን በተቀነባበረ መንገድ እየጨቆነ እንደሆነ፣ ሃይማኖቱን በግድ እንዲቀይር እያደረገውና ሆነ ተብሎ በከፍተኛ ትምህርት እንዳይማር እየተደረገ እንደሆነ በማስመሰል፣ ሕዝብ ሙስሊሙ ጀሀድ በመውጣት ሃይማኖትህን ነፃ ልታወጣ ይገባል!! ገፒው መንግስት አያስተዳደረንም! ከአክራሪ አስተምሮት ውጪ የሚያስተምሩ ኢማሞችን መግደል ጀሀድ ነው! ሌላው አስተምሮት ከኢትዮጵያ ተጠራርጕ እስካ ልወጣ ድረስ ትግላችን እስከ ሕይወት መሰዋእትነት ለመክፈል መዘጋጀት አለብን፣ በማለት ሕዝቡን ለሽብር ዓላማቸው በመቀስቀስና በማነሳሳት ሲሆን በተለያየ ጊዜ የዓመፅ ጥሪ በማስተላለፍ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ በኮልፌ ቀ/ክ/ከተማ በአንበሳ አውቶቢስ ላይ ጉዳት ደርሷል። ሕግን ለማስከበር በተሰማሩ የፖሊስ አባላት ላይ በአካላቸው ላይ ጉዳት አድርሰዋል፣ በባንክ ቤት በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል። የአሁን መልስ ሰጪ የክስ ማመልከቻ ደርሶት እምነት ክህደት ተጠይቆ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለቱ ዓቃቤ ሕግ ከግብረአበሮቹ ጋር ከ101 በላይ የሰው ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል፤ ቀጥታ ማስረጃ፤ አካባቢና የተከሣሾች መኖሪያ ቤት ሲፈተሽ በብርበራ ወቅት የነበሩ ታዛቢ ምስክሮች እንዲሁም በእራሳቸው ፍቃዳኝነት ከኢሚይል ሲያወጣ በነበሩ ተከሣሾች ላይ ታዛቢ የነበሩ ምስክሮች

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.....................................
Re.NO
ቀን.....................................
Date

ፍ/ቤት ቀርበው የምስክርነት ቃል ከሰጡት በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/27/2/ መሰረት የሰጠው ተከሣሽ የእምነት ቃል፣ የተለያዩ የቅስቀሳና የአመፅ ጥሪ ሲያስተላልፉ የነበሩ የሰነድ ማስረጃ ደምፅ ከምስል VCD በሃይማኖት ሽፋን ቅስቀሳ ሲደርጉ የነበሩ እና በአካላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው የፖሊስ አባላት የሕክምና ማስረጃ በንብረት ሰለደረሰው ጉዳት የሚገልጽ ማስረጃ ከክስ ማመልከቻችን ጋር በመያይዝ አቅርበናል፡-

24ኛ ተከሣሽ ሀሰን አቢ ላይ በስር ፍ/ቤት የቀረበው ክስ የኮሚቴውን የሽብር ዓላማ እና አጀንዳ በመቀበል ይህንኑ አጀንዳ ለማስፈፀም በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ልዩ ቦታው አወሊያ መስጊድ በተሰበሰበው ሕዝብን ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው ግጥሞችን ወደ መድረክ እንዲቀርቡ በማድረግ እንዲሁም መስጊዱን በመቆጣጠር እና ሰዎችን በመፈተሽ የተሳተፈ በመሆኑ እንዲሁም ከ28/08/2004 ዓ.ም እስከ 20/10/2004 ዓ.ም ድረስ ላልታወቁ ግብረአበሮቹ አወሊያ በሚቀጥለው ሳምንት የጁምአ ትግላችን ይቃጥላል እኛ የመቱ ሙስሊሞች በደህና እንጠራ ነበር በአሁኑ ሰዓት ግን እስልምናችን እየተረገጠ ይገኛል፣ ሙስሊሞች ለመሆኑ በሕይወት እያለን ሃይማኖታችን የማንም አይሁድ እና የማንም ለሆዳቸው ባደሩ መናፍቅ ካድሬዎች ማጫወቻ መሆን የለበትም፣ ወይም እንዴት ይሆናል የመቱ ሙስሊሞች ፀጥ ብለው አክራሪ ያልሆኑ ስልጠና መከታተላቸው ትክክል አይደለም ወኔ ይጉድላቸውል በአንዋር መስጊድ ለሚደረገው ተቀውሞ አፋቸውን የሚለጥፉበት ፕላስተር፣ ማዘጋጀቱንና የሚበተን ወረቀት እንደያዘጋጀ መመሪያ በመስጠት፣ በተለይም ሚያዚያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ለ4ኛ ተከሣሽ ለሆነው ካሚል ሽምሱ ስልክ በመደወል ለሕገ-ወጥ ሰልፍ እንደዘጋጁ የድምፅና ፁሁፍ መልዕክት በማስተላለፍ ክስ ቀርቦበታል ማስረጃ በሚመለከት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ሕ/ቁ/27/2/ መሰረት በሰጠው የእምነት ቃል ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አረጋግጧል ከተከሣሽ መኖሪያ ቤቱ በብርበራ ሲደረግ የነበሩ ታዛቢዎች የቅስቀሳ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel. 51 50 99 P.0. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

3244

7093

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር..
Re.NO
ቀን..
Date

CD መገኘቱን መስክረዋል ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይን መልስ ሰጪ መብቱን ጠብቆ ነው፣ የሰጠው ማስረጃ አልቀረበም በማለት መከላከል አያስፈልገውም በማለት በነፃ እንዲሰናበት ብይን ሰጥቷል።

በይግባኝ እንደተረምልን የምንጠይቀው ዳኝነት

መልስ ሰጪ በስር ፍ/ቤት ክስ ከቀረበባቸው የሽብር ቡድን አባላት በአዋለያ ትምህርት ቤት እና በአንዋር መስጊድ ሲያደርጉት በነበረው የአመጽ ጥሪ እና ቅስቀሳ ዋና አስተባባሪ በመሆን የተሣተፈ ነው። አመፅ በየጊዜው መቀጠል ያለበት ስለመሆኑ የሚበተን ወረቀት እንዲዘጋጅ መመሪያ በመስጠት በአመጽ ለሚሣተፉት አፋቸውን የሚለጥፉበት ፕላስተር በማዘጋጀት ሕጉ-ወጥ የአመፅ ሰልፍ እንደዘጋጀ ለ4ኛ ተከሣሽ ካሚል ሽምሱ የደምፅና የፁሁፍ መልዕክት አስተላልፎአል መልስ ሰጪ ድርጊቱን አምኗል። ፍ/ቤት በመልስ ሰጪ ላይ ያቀረብነውን የቴክኒክ ማስረጃ ሣይመረምር የግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት መብቱን ጠብቆ ቃሉን ሰጥቷል በማለት በነፃ እንዲሰናበት የሰጠው ብይን አግባብ አይደለም ምክንያቱም የስር ተከሣሽ የአሁን መልስ ሰጪ የፈፀመው ድርጊት ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን የፈፀመው የወንጀል አድማ ስምምነት (Conspiracy) ሲሆን ማስረጃው ሊሚዘንልን የሚገባው የሽብር ቡድኑ ይዞት ከተነሳው ዓላማና ግብ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ተሽሮ መልስ ሰጪ እንዲከላከል ብይን እንዲደስጥልን በትሕትና እናመለክታለን።

ብርሃኑ ወ/አገኝ
ፌ/ዐቃቤ ሕግ

ማ/ደ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

http://ethcriminalawnetwork.com/

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የወ/መ/ቁ.________________

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሣኔ መስጠት ንዑስ የሥራ ሂደት

የአንድ መዝገብ መከታተያ ቅፅ /ከጊዜ አንፃር/

ከሣሽ [illegible]

ተከሣሽ [illegible]

ተ.ቁ	ቀን	ፋይል አካል	የተሰጠ አገልግሎት	አገልግሎቱን ለመስጠት በአፈፃፀም መመሪያው የተቀመጠ	ጉዳዩ የመጣበት ሰዓት	ጉዳዩ የተፈፀመበት ሰዓት	ቀን	
1	16/05/06	ሬጅስትራር ረዳት ሬጅስትራር	የይግባኝ አቤቱታውን ፎርማሊቲ ማረጋገጥ	3 ደቂቃ	9:00	3 ደቂቃ	16/05/06	
			ፋይል መክፈት	10 ደቂቃ	11:30	10 ደቂቃ		
2		ዳኛ						

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሣኔ መስጠት የሥራ ሒደት

ቁጥር 97/82
ቀን 13/6/2006

ለ ፌዴራል ማረሚያ ቤት
አ/አበባ

14/6/06

በይግባኝ ባይ የፌ/ዐ/ሕግ እና
በመልስ ሰጪ ሀብታሙ ዓለሙ ዘውዴ መካከል ስላለው
የ ሽብርተኝነት ወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ ይግባኝ ባይ
የሚያቀርቡትን ቅሬታ ለመስማት ለ 2/7 ቀን 2006
ቀጠሮ ስለተያዘ ዐ/ሕጉ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ መስጠት የሥራ ሂደት 4ኛ
ወ/ችሎት ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እንዲቀርቡ ችሎቱ አዟል።

ባላቸው እንሺሶ ኤምቤጫ
ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዳኛ

☎ 011 1 55 34 00

3250

7019

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ቀን 15-08-06

እኔ ሀሰን ሽቦ ________________ የተባልኩኝ በተከሰስኩበት ወንጀል ክስ ጉዳይ

ፌ/ከ/ፍ/ቤት ፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ጠቅላይ ፍ/ቤት ወ/ችሎት 17-08-06 ዓ/ም ስለሆነ

ቀጠሮ ከቀኑ በ 2:30 ሰዓት ለመቅረብ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ በወ/መ/ቁ 97182

በቀን 6-08-06 በተባፊ ደብዳቤ የተሰጠውን ትዕዛዝ የተነገረኝ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

በ5 ገፅ የተፃፈ ቻርጅ
ጋር ፈርሜ ወስጃለሁ

የተከሳሽ ሙሉ ስም ሀሰን ሽቦ ሰዒድ

የተከሳሽ ፊርማ [signature]

15/08/06

5 ሰዓት (ከአምስት ሰዓት)

3251 [signature]

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በኢት/ፌደ/ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ

የታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት

Eth. Federal Police Crime Investigation Sector

Tactic Investigation Directorate

ቁጥር 97182/06

Ref.No

ቀን 16/08/06

Date

ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

<u>አ/አበባ</u>

ሀሰን አቢ በተከሰሰበት ወንጀል ክስ ጉዳይ ተከሳሹን ለ17/8/06ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ እንድናቀርብ በቁጥር 97182 በቀን 6/08/2006ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ታዘናል፡፡

ስለዚህ በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ለመፈፀም ተከሳሽ በሰጠው አድራሻ ተንቀሳቅሰን የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ነግረን ስለመንገራችን ያስፈረምንበትን መተማመኛ 1 ገፅ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግጅን መሐመድ አሚን

የፍርድ ቤት ትእዛዝ አፈፃፀምና ሪከርድ ማህደር አገልግሎት ማስተባበርያ ሃላፊ

ቴሌ ፋክስ Fax 0111 579450
☏ 251 011 111 579450 881 free call
✉ 80358 E-mail Crimeinvest29@yahoo.com
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa Ethiopia

" ዓላማችን ከወንጀል ስጋት ነጻ የሆነች ኢትዮጵያን መገንባት ነው "

3251

4004

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/